ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ አንድምታና ፋይዳ በጎንደር

በ

ጋሻው አሻግሬ

ሰኔ 21 /2013 ዓ.ም

ዐዲስ አበባ

# ምስጋና

በመጀመሪያ አልፋና ኦሜጋ እግዚአብሔር ይህችን ትንሽ ሥራየን ስለ ባረክልኝ ለሕያው ስምህ ክብርና ምስጋና ይግባህ።

የቤተ ክርስቲያኗ ትውፊት "አሐደ ቀለም ዘነገረከ ይኩን ከመ አቡከ ወ ክልዔተ ቀለማት ዘነገረከ ይኩን ከመ ፈጣሪከ" ይላል። እናንተ ግን ከአንድም ኹለት፣ ሠለስት፣ ሠላሳ፣ ስሳ፣ ምእት ቀለማትን እና እርማትን ችራችኹኛል። በመኾኑም ደከመኝ እና ሰለቸኝ ሳትሉ ጥናቱን ወግ ለማስያዝ ከጅማሬ እስከ ፍጻሜ ድረስ ያለ መሰልቸት ላተጋችሁኝ ለዶክተር ዓለሙ ካሣዬ እና ለዶክተር ዘላለም መሠረት ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

በመረጃ ሰጪነት ሚናችሁ ከፊት እና ጉልህ ለኾነው ለሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ ለመልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ፣ ለአቶ ልዕልና ኀይለ መስቀል እና ለመ/ር ዳዊት ሥራው ምስጋናየ ይድረሳችሁ እላለሁ። በመቀጠል ለኹሉም መረጃ ተባባሪዎቼ እና ለጎንደር ማኅበረሰብ በሙሉ ከፍ ያለ አክብሮት እና ምስጋና አለኝ።

እንደ ጎንደር ሥርዐትና ወግ እግር አጥባችሁ፣ ቀጤማ ጎዝጉዛችሁ፣ ጠጅ አዘንብላችሁ፣ መጥን ሠርታችሁ እና ላመነት አንጥፋችሁ ተቀብላችኹኛል። በሙያችኹ ደግሞ በመቅረጽ ድምጽ በፎቶ ካሜራ እና በመረጃ መሰብሰብ እገዛችኹ ላቅ ያለ ነው። ስለኾነም ለዶክተር ታደሰ ዳርገው፣ ለተመስገን ታደሰ፣ ለሙሉቀን ዘመነ እና ለመላኩ አለምነው ምስጋናዬ ከልብ ነው።

በመቀጠል ለጎንደር ከተማ ባህልና ቱሪዝም፣ ወሳኝ ኩነት እና ከንቲባ ጽሕፈት ቤቶች አስፈላጊ የመረጃ ጽሑፎችን በማቅረብ፣ የትብብር ደብዳቤዎችን በመጻፍ እና የመረጃ መሰብሰቢያ ፈቃዶችን በመስጠት ላደረጋችሁልኝ ትብብር ኹሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ። ይህ ጥናት ከግብ ይደርስ ዘንድ ለተባበሩኝ፣ ላተጉኝ እና ለደገፉኝ ቤተሰቦቼ ለፋንታነሽ ለገሰ፣ ለሐብለ ጋሻው፣ ለማርያማዊት ጋሻው፣ ለአቶ አሻግሬ ገላየ፣ ለለገሰ ዓለሙ፣ ለቂስ ወርቁ አሻግሬ እና ለሚኪያስ ላውጋው ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

በማሳረጊያ የሀገራችን የዕውቀት መቅረዝ በኩር ከኾነው ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለሚቀዳው ፎክሎር ትምህርት ክፍል ከመጀመሪያው ዓመት ጅምሮ በትጋት እና በብርታት በመከታተል ከዚህ ስለ አደረሰኝ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ።

# ማውጫ

ምስጋና ........ i

ማውጫ ........ ii

አጠቃሎ ........ vi

ሙዳዬ ቃላት ........ vii

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ ........ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........ 1

1.2. የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት ........ 6

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ ........ 7

1.4. የጥናቱ ዓላማዎች ........ 8

1.4.1. የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ ........ 8

1.4.2. የጥናቱ ንኡሳን ዓላማዎች ........ 8

1.5. የምርምሩ ጥያቄዎች ........ 9

1.6. የጥናቱ ወሰን ........ 9

1.7. በመረጃ አሰባሰብ እና ትንታኔ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሒዎች. 11

1.7.1. ያጋጠሙ ችግሮች ........ 11

1.7.2. የተወሰዱ መፍትሒዎች ........ 12

1.8. የጥናቱ አደረጃጀት ........ 13

ምዕራፍ ኹለት፡- ክለሳ ድርሳናት ........ 14

2.1. ጽንሰ ሐሳባዊ ማሕቀፍ ........ 14

2.1.1. የክብረ በዓል ምንነት ........ 14

2.1.1.1. የክብረ በዓል ፋይዳዎች ........ 16

2.1.1.2. የክብረ በዓል ባሕርያት ........ 19

2.1.1.3. የክብረ በዓል ዘውጎች ........ 24

2.1.2. ሃይማኖት ........ 29

2.1.3. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ክብረ በዓላት ........ 33

2.1.4. የጥምቀት ክብረ በዓል ........ 34

2.2. ንድፈ ሐሳባዊ ማሕቀፍ ........ 36

2.2.1. የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ ........ 36

2.2.2. ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ........ 40
2.2.3. የሚት ንደፈ ሐሳብ ........ 42
2.2.4. የሥነ ፍካሬ (Hermenetics) ንድፈ ሐሳብ ........ 44
2.3. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ........ 46
**ምዕራፍ ሦስት፡- የጥናቱ ሥነ ዘዴ፣ አካባቢያዊ ዳራና የመስክ ተሞክሮዎች** ........ 61
3.1. የጥናቱ ሥነ ዘዴ ........ 61
3.1.1. የጥናቱ ዘዴ ........ 61
3.1.2. የመረጃ ምንጮች ........ 62
3.1.3. የጥናት ንድፍ (Research Design) ........ 63
3.1.4. የጥናት ንሞና ዘዴዎች ........ 64
3.1.5. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 67
3.1.5.1. ምልከታ ........ 67
3.1.5.2. ቃለ መጠይቅ ........ 69
3.1.5.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት ........ 73
3.1.6. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 75
3.1.7. የመረጃ መተንተኛ ስልት ........ 76
3.1.8. የጥናቱ ሥነ ምግባር ........ 79
3.2. የመስክ ተሞክሮ ........ 80
3.3. የጎንደር ከተማ አካባቢያዊ ዳራ ........ 85
3.3.1. የጎንደር ከተማ መሠረተ ልማት ........ 86
3.3.2. የጎንደር ከተማ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ87
3.3.3. የከተማዋ የልህቀት ማእከልነት ........ 88
3.3.4. የከተማዋ ታሪካዊ ቅርሶች ........ 90
3.3.4.1. የዐፄ ፋሲል ግቢ ........ 90
3.3.4.2. ራስ ግንብ ........ 91
3.3.4.3. የጥምቀተ ባሕር ግንብ ........ 92
3.3.4.4. የጎንደር ከተማ ሕዝብ እና ሃይማኖት ........ 94
ምዕራፍ አራት፡- የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ዐውድ ........ 95
4.1. ቅድመ ጥምቀት ........ 95

4.2. የከተራ እና ጥምቀተ ባሕር ዐውድ ........................................................................ 100
4.3. የዕለተ ጥምቀት ዐውድ እና ክዋኔ......................................................................102

**ምዕራፍ ዐምስት የጎንደር ጥምቀት ሥርዓተ ክዋኔ እና አንድምታው** ........................................ 110

5.1. በጎንደር ጥምቀት የሊቃውንቱ ክዋኔ እና አንድምታው .............................................. 110
5.2. የካህናት ክዋኔ እና አንድምታ በጎንደር ጥምቀት ................................................... 114
5.3. የሰንበት ተማሪዎች ክዋኔ በጎንደር ጥምቀት ....................................................... 116
5.4. የልጆች ተሳትፎ በጎንደር ጥምቀት ............................................................... 119
5.5. የልጃ ገረዶች ክዋኔና አንድምታው በጥምቀት ......................................................... 121
5.6. የእናቶች ክዋኔ እና አንድምታው በጥምቀት ......................................................... 130
5.7. የወጣት ወንዶች ክዋኔ እና አንድምታ በጎንደር ጥምቀት .......................................... 134
5.7.1. የወጣቶች "አይብላሆ መኔ" ክዋኔ ሥርዓት ...................................................... 139
5.7.2. በወጣቶች የሚቀነቀኑ የሆታ ቃል ግጥሞች ክዋኔና አንድምታ .................................. 142

**ምዕራፍ ስድስት፡- የጥምቀት ክብረ በዓል ማኅበራዊ አንድምታ እና መስተጋብር** ...........151

6.1. በጥምቀት ክብረ በዓል ዐውድ የሚገለጹ ክዋኔዎች አንድምታ እና ማኅበራዊ መስተጋብር ........................................................................................ 151
6.1.1. የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮችን ማቀራረብ ................................................... 151
6.1.2. ሀገረሰባዊ ዕውቀትን እና ሀገራዊ ማንነትን ማስቀጠል .......................................... 154
6.1.3. ከቤተሰቦቻቸው የተለዩ ማኅበረሰቦችን ማገናኘት ................................................ 157
6.1.4. የባህላዊ አልባሳት ቀለማት እና ምልክቶች ማኅበራዊ መስተጋብር.................................. 160
6.2. ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚነገሩ ታሪኮች እና አንድምታቸው ........................................ 163
6.2.1 ስለ ጎንደር ጥምቀት እና ነገሥታቱ ግንኙነት የሚነገሩ ታሪኮች (narratives) እና ማኅበራዊነት ........................................................................................ 164
6.2.2. ስለ ጥምቀት ክብረ በዓል የሚነገሩ ሃይማኖታዊ ታሪኮች እና ማኅበራዊ አንድምታቸው .................................................................................... 169
6.2.3. ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚነገሩ የሚት ትረካዎች አንድምታ እና ማኅበራዊ ፋይዳዎቻቸው.......................................................................................... 171

**ምዕራፍ ሰባት፡- የጎንደር ጥምቀት ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ እና አንድምታ** .........................177

7.1. በጥምቀት ክብረ በዓል የባህል አልባሳት ንግድ እና ምጣኔ ሀብት......................................... 177
7.2. በጥምቀት ክብረ በዓል የባህል መጠጥ ቤቶች ንግድ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ እና አንድምታቸው..................................................................................184

7.3. በጥምቀት ክብረ በዓል የምግብ እና አልጋ ቤቶች ንግድ ምጣኔ ሀብት ..................186
7.4. በጥምቀት ክብረ በዓል የሴቶች የውበት ሳሎን ንግድ ..........................................189
7.5. በጥምቀት ክብረ በዓል የእደ ጥበባት ባህላዊ ቁሶች ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ እና አንድምታቸው ..........................................................................................................191
7.6. በጥምቀት ክብረ በዓል የንዋየ ቅድሳት ንግድ ምጣኔ ሃብታዊ ፋይዳ ...................201
7.7. በጥምቀት ክብረ በዓል የባህላዊ ግብዣ እና ቅርጻቅርጾች ምጣኔ ሀብት.................202
7.8. የጎንደር አዝማሪዎች ውዳሴ እና ገቢ በጥምቀት ክብረ በዓል ...............................203
**ምዕራፍ ስምንት የጥምቀት ክብረ በዓል ሰባዊ ንጽሕና እና አንድምታው በጎንደር............210**
8.1. የጥምቀት ክብረ በዓል እና ግብረ ገብነት.........................................................210
8.2. የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል እና ፍቅር ..........................................................217
8.3. የጥምቀት ክብረ በዓል እና ሀዘን .....................................................................222
8.4. በጎንደር ጥምቀት ክበረ በዓል ላይ የሚገኙ ቁሳዊ ባህል ሰባዊ ፋይዳ እና አንድምታቸው ..........................................................................................................226
8.5. በጥምቀት ክብረ በዓል የሚቀነቀኑ ቃል ግጥሞች ሰባዊ አንድምታቸው ................231
**ምዕራፍ ዘጠኝ፡- የጥምቀት ክብረ በዓል ለቱሪስት፣ ለቅርስ እና አካባቢያዊ ጥበቃ** .............241
9.1.የጥምቀት ክብረ በዓል የቱሪስት መስኅብ እና ፋይዳዎቹ.........................................241
9.1.1.በጥምቀት ክብረ በዓል የቱሪስት ፍሰቱ ኺደት እና ሀገር የማስተዋወቅ ............241
9.1.2.በጥምቀት ክብረ በዓል የቱሪስት ፍሰት እና የምጣኔ ሃብት ፋይዳ....................247
9.2. የጎንደር ጥምቀት እና የቅርስ ጥበቃ ..............................................................251
9.3. የባህላዊ አልባሳት፣ እደ ጥበባት ጥበቃ እና ፈጠራ ..............................................255
9.4. የጎንደር ጥምቀት ለአካባቢ ጥበቃ ያለው ፋይዳ....................................................259
**ምዕራፍ ዐሥር፡- ማጠቃለያ**.................................................................................262
**የይኹንታ ሐሳብ**...............................................................................................267
**ዋቢ ጽሑፎች** (Reference).....................................................................................269
**የመረጃ ሰጭዎች ስም ዝርዝር**..................................................................................282
**አባሪዎች** ...........................................................................................................285

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት “የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ፣ አንድምታ እና ፋይዳዎቹ በጎንደር” በሚል ርእሰ ጉዳይ ተጠንቶ የቀረበ ነው፡፡ የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት የጥናቱ ዐዲስነት እና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ከሃይማቱ በሻገር ያለውን ማኅበራዊ ጉዳይ ለመመር በማሰብ ነው፡፡ የጥናቱ ዓላማ የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ፣ አንድምታ እና ፋይዳዎቹን መመርመር እና ማጥናት ነው፡፡ ለጥናቱ መመልከቻ የክዋኔ፣ የሚት፣ የሥነ ፍካሬ እና የተግባራዊ ንድፈ ሐሳቦች በጥምረት ተወስደዋል፡፡ ጥናቱ ዐይነታዊ ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ ለጥናቱ መረጃ በዋናነት ታላሚ ንሞናን ተጠቅሜአለሁ፡፡ በታካይነት ደግሞ የብድግ ብድግ ንሞናን እና የድርሻ ንሞናን ተግባራዊ አድርጌአለሁ፡፡ ጥናቱ በቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ላይ ተመሥርቶ የተጠና ነው፡፡ ከቀዳማይ መረጃ ሰጪዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከካልዓይ ምንጮች ደግሞ ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶች እና ከመመረቂያ ጽሑፎች ለጥናቱ ሥነ ጽሑፋዊ ቅኝት በግብዓትነት ተወስደዋል፡፡ ከመስክ የተገኙት መረጃዎች በመቅረፀ ድምፅ፣ በፎቶ ካሜራ እና በማስታወሻ ደብተር ተሰብስበዋል፡፡ ከመረጃ መሰብሰብቢ ዘዴዎቹ መካካል ምልከታ ቃለ መጠይቅ እና ተተኳሪ ቡድን ውይይቶችን ለጥናቱ ተግባራዊ አድርጌያለኹ፡፡ 66 ግለሰቦች ባልተገደበ፣ በከፊል በተገደበ እና በተገደበ የቃለ መጠይቅ ዐይነቶች መረጃ ሰጥተዋል፡፡ ባለ 7 አባላት ያሉት ኹለት የወንዶች እና ኹለት የሴቶች በድምሩ 28 መረጃ ሰጪዎች የተሳተፉበት ተተኳሪ የቡድን ውይይት ተካሂዷል፡፡ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት 54 ወንዶች እና 40 ሴቶች በድምሩ 94 መረጃ ሰጪዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡ ጥናቱን ለመተንተን የክዋኔ፣ የፍካሬ፣ የዐይነታዊ፣ የአሐድ እና የዐውዳዊ የትንተና ስልቶች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ የጥናቱ ትንታኔ በዋናናት ከተጠኚዎቹ ፍልስፍና ዐይን አትኩሮት ያደረገ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጥናቱ ሳይንሳዊ መንገድን ይከተል ዘንድ በታካይነት ከአጥኚው መነጽር እና ዕውቀትም ጭምር ትንታኔ ተሰጥቷል፡፡ በጥናቱ ትንታኔ ውስጥ የወጣት ወንዶች ክዋኔ አባዊ ሥርዓቱን የሚወክል ሲኾን የልጃ ገረዶች ክዋኔ ደግሞ እማዊ ሥርዓቱን የሚወክል መኾኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ ክብረ በዓሉ በማኅበራዊ፣ በምጣኔ ሀብታዊ፣ በሰባዊ፣ በቱሪስት እና የአካባቢ ጥበቃ ላይ ተመሥርቶ ተተንትኗል፡፡ የጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔዎች ከማሕሌቱ እና ቁመቱ ውጪ ከሃይማኖታዊ ይዘታቸው ይልቅ ማኅበራዊ ይዘታቸው ሚዛን ይደፋል፡፡ በዚህ መልኩ የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ ኹሉንም የማኅበረሰብ ክፍል አካታች የሆነ ፋይዳ አለው፡፡ በመኾኑም የክብረ በዓሉ ክዋኔዎች ለማኅበራዊ፣ ለምጣኔ ሀብታዊ፣ ለሰባዊ፣ ለቱሪዝም እና ለአካባቢ ጥበቃ ወሳኝ ፋይዳዎች ያሉት መኾኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ እነዚህ ፋይዳዎች ታልበው በማይነጥፉ፣ ተቀድተው በማይደርቁ ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ የጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ የማኅበረሰቡ ሥሪት፣ ተስፍ፣ ምኞት፣ ዕውቀት እና ፍልስፍና የሚታይበት ነው፡፡ በዚህ መልኩ የጥምቀት ክብረ በዓል ለማኅበረሰቡ ፍልስፍና እና ዕውቀት አንድም ማሳያ መነጽር፣ አንድም ማጓጓዣ መርከብ በመኾን ያገለግላል፡፡*

# ሙዳዬ ቃላት[1]

1. ሆተኛ፣ በሆታ ላይ የሚሳተፉ ቁርጥ፣ ቁርጥ ሠርተው የተደራጁ በቡድኖች መጠሪያ
2. ልዕልና ፡- ከፍታ፣ ስኬት
3. ሌማት፣ የእንጀራ ማቅረቢያ አለላና ግራምጣ ስፌት
4. ላመነት፣ ምንጣፍ
5. መጠመን፣ "ጠ" ይጠበቃል መሬት ለእኩል ፣ ለአምሾ እና ለሢሶ ተጠምኖ የሚያረስ
6. መጣመን፣ መጥፋት፣ መራቆት
7. መፈንጠዝ፣ መዝለል፣ መሮጥ ለጥጃ
8. ሙሴ፣ የጽዋ ማኅበር መሪ ኹኖ የተመረጠ ሰው
9. ሙሪት፣ ለያዥ ለገራዥ የአቃተች፣ ነውር እና ጸያፍ ያለየች
10. ማስጠመን፣ የመሬት ባለቤት ለተጠማኝ በአበል የሚያሳርስ
11. ሞረሽ፣ በምሽት ሰው የሚጠራበት ስም ነው፡፡
12. ሰክሰክ፣ ሽማ ሠሪዎች ከአካባቢያቸው ውጭ ወቅታዊ የሽማ ሥራ ክንውን
13. ቀንጃ፣ ነጠላ፣ ክፋይ፣ ግንጥል ቀንጃ በሬ ይባላል
14. ቀጸላ፣ የሊቃውንቱ የሻሽ አጠማጠም
15. ሽልም ግና፣ ነጭና ጥቁር የእንቁር መልጊያ በትር
16. ቅማንት፣ ከአያት በፊት የሚጠቀስ የዘር ኀረግ፣ አያት ቅማንት
17. ቆለምሸሽ፣ የእንጀራ መብያ ስፌት
18. ቱልቱላ፣ ጥሩምባ
19. ትሕትና፡- ደግነት፣ ውድቀት፣ ውርደት
20. ኀጸጽ፣ ችግር፣ ጎደሎ
21. ነጎደ፣ ተጓዘ
22. ነጎድጓድ፣ የመብረቅ ድምጽ
23. አልቦ፣ ከእግር ቁርጭምጭሚት የሚገባ ባህላዊ መጊያጊያጫ
24. አሽከር፣ ልጅ
25. እንቁር፣ ጥንግ፣ ሩር
26. ኩታራ፣ ልጅ

[1] ፍች የተሰጠባቸው ቃሎች እንደዚህ ጥናት ዐውድ እንጅ በሌላ ዐውድ ደግሞ ከቃላት ባሕርይ አንጻር ሌላ ፍች ሊኖረው ይችላሉ፡፡

27.ኪንኪ፣ ከርዳዳ ጸጉር

28.ካራ፣ ቢላዋ

29.ኮበሌ፣ ወጣት፣ አፍለኛ ለወንድ

30.ኮተኛ፣ ሆ ባይ ወጣት

31.ወማ፣ ስድ፣ገደል፣ መቀንበቢያ የሌለው

32.ዋሴራ፣ ድብልቅ፣ ሰርገኛ

33.ደንገጡር፣ "ሲጠሩት አቤት፣ ሲልኩት ወዴት" የሚል የባለምዋይ አገልጋይ

34.ድንጅት፣ የማይፍረከረክ እና ቋሚ የኾነ ማኅበረሰባዊ መተዳደሪያ ደንብ

35.ጀብጀብ፣ ድምጽ፣ ኮቴ ያለው ርምጃ

36.ጀርሲ፣ የሴቶች ሽብሽቦ በአብዛኛው አረንጓዴ ቀለም ያለው ነው፡፡

37.ጋጃ፣ የሳር ዓይነት ፍሬው በነፋስ የሚሄድ

38.ግጻዌ፣ የአጽዋማት፣ የበዓላት፣ የምስባክ፣ የወንጌል እና የፍሬ ቅዳሴ ማውጫ መጽሐፍ፡፡

39.ጥቁር ደም፣ በእጁ ነፍስ የጠፋበት፣ ነፍስ የጠፋባት

40.ጥንግ ድርብ፣ ካህናት በክብረ በዓል ጊዜ የሚለብሱት የሸማ ዓይነት

# ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

የሰው ልጆች በሕይወት ዘመናቸው ውስጥ እንደሚኖሩበት ማኅበራዊ ሥሪት፣ እንደሚፈቅድላቸው ባህላዊ መዋቅር እና እንደሚከተሉት ሃይማኖታዊ ቀኖና መሠረት የተለያዩ ክብረ በዓሎችን ያደርጋሉ፡፡ ሰዎች ክብረ በዓላትን የማድረግ እና የማክበር ዋናው ግባቸው ሥጋዊ ይኹን መንፈሳዊ በረከትን ለማግኘት ካላቸው መሻት የሚመነጭ ነው፡፡ በዚኽ ምክንያት በዓለም ዙሪያ ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ እና ባህላዊ የኾኑ ክብረ በዓላት ይደረጋሉ፡፡ ሀገራችንም ሃይማኖታዊ እና መንግሥታዊ የኾኑ ብሔራዊ ክብረ በዓላት አሏት፡፡ ከመንግሥታዊ ክብረ በዓላት መካካል እንደየ ሥርዓተ ምንግሥቱ ልደት እና ሞት አብረው የሚፈኩ እና የሚረግፉ እንደ መስከረም ኹለት ያሉ በዓላት አሉ፡፡ እንደ አድዋ እና ጀግኖች አርበኞች ያሉት ደግሞ ዘመናትን ተሻግረው የሚከበሩ የሀገራችን ብሔራዊ በዓላት ናቸው፡፡ ከሃይማኖታዊ ብሔራዊ በዓላት መካከል ደግሞ በእስልምና ሃይማኖት የኢድልአድሃ፣ የመውሊድ እና የአረፋ ክብረ በዓላት በየ ዓመቱ እየተመላለሱ የሚከበሩ ናቸው፡፡ የገና፣ የጥምቀት፣ የመስቀል እና የትንሣኤ ክብረ በዓላት ደግሞ በክርስትና ሃይማኖት ዘንድ ዓመት እየጠበቁ ሲከበሩ ይኖራሉ፡፡ ይህ ጥናት ከክርስትና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት መካከል በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የተመሠረተ ሲኾን "የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ፣ አንድምታ እና ፋይዳዎቹ በጎንደር" በሚል ርእሰ ጉዳይ የተጠና ነው፡፡

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

ሰዎች እና ክብረ በዓል ግንኙነታቸው ሩቅ፣ ተራክቧቸው ደግሞ ጥብቅ ነው፡፡ በረጅም ዘመን የሰዎች እና የክብረ በዓል ግንኙነቶች ምክንያት ቀን ቆርጦ ቦታ መርጦ በውል ማስቀመጥ ያስቸግራል፡፡ ይኹን እንጂ በቡድን ኹነው አስቸጋሪ የኾኑ የአደን እና የፍራፍሬ ለቀማ ከእጅ ወደ አፍ የኾኑ የኑሮ ውጣ ውረዶችን ለማሸነፍ ሲታትሩ በነበሩበት ወቅት ክብረ በዓልን ማክበር እንደጀመሩ ይገመታል (Bell 2009, 1)[2]፡፡ ክብረ በዓል በዚህ መልኩ ከሰዎች በቡድን እና በጋርዮሽ መኖር ጋራ ተጀምሮ እና ዕያደገ መጥቶ የሥልጣኔ መገለጫ፣ የሃይማኖት ማስኬጃ ለመኾን በቅቷል፡፡ እንደነ ባቢሎንያን፣ አቴንስአውያን፣ ሮማውያን፣ ግብጻውያን እና

[2]የእንግሊዘኛውን ጥቅስ ለማመሳከር ይቻል ዘንድ እንደዚህ በግርጌ አስፍሬዋለኹ፡፡ ይህን ያደረግኩበት ምክንያት ውብትንም ድረታንም ሊያስከትል ይችላል ከሚል እሳቤ በመነሣት ነው፡፡ "Human beings have been involved in ritual activities of some sort since the earliest hunting bands and tribal communities. Bell (2009, 1) *"የሰው ልጆች ከቀደሙት የአደን እና የጎሳ ቡድኖች ጀምሮ የክብረ በዓል እንቅስቃሴዎችን ያደርጉ ነበር"* (ትርጉም የእኔ) በማለት ይገልጻሉ፡፡

ሜሶፖታሚያን የመሳሰሉት ጥንታዊያን የሥልጣኔ ባለቤቶች ለነግሥታቱ እና ለልዑላኑ በቤተ መንግሥታቸው የደመቀ ክብረ በዓል በማድረግ የግብዣ እና የሲመት ሥርዐት ያደርጉ ነበር (S. R. F Price, 1984, ), Bell 1997, 3)፡፡

ክብረ በዓል ለሰው ልጆች ኹለንተናዊ ጉዳያቸው ማስፈጸሚያ እና የሃይማኖታቸው መቀመሪያ በመኾን ዘመናትን የተሻገረ ግልጋሎት አግኝተውበታል፡፡ ይህን በተመለከተ በሚት እና በክብረ በዓል ትምህርት ቤቶች ውስጥ ምርምር የሚያደርጉ የማኅበረሰብ እና የሥነ ሰብእ አጥኚዎች ክብረ በዓል እና ሚት የሃይማኖት መሠረቶች ናቸው በሚል የክብረ በዓልን ቀዳሚነት የሃይማኖትን ተከታይነት ለማረጋገጥ ሞክረዋል (Cather Bell 1997, 3)፡፡ በዚህ መልኩ የቅደም ተከተል ክርክር ከመነሣቱ ባለፈ በክብረ በዓል እና በሃይማኖት መካከል ያለው ዝምድ እና ቅርርቦሽ ላይ ተመራማሪዎች ብዙ ልዩነት ያለባቸው አይመስልም (Cather Bell 2009, 3)::

ክብረ በዓል ረጅም ዕድሜ ያስቆጠረ፣ ዘመናትን የተሻገረ ይኹን እንጂ በውል መጠናት የጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አካባቢ ነው፡፡ በዚኹ ክፍለ ዘመን በCambridge ትምህርት ቤት ውስጥ ስለ ክብረ በዓል ጥናቶች እና ሙግቶች ይካኼዱ ነበር፡፡ በትምህርት ቤቱ የሚካኼዱት የክብረ በዓል ጥናቶች የክብረ በዓል ክዋኔዎች እና እንቅስቃሴዎች ለፎክሎርና ለሥነ ጽሑፍ መገኛዎች እና መሠረቶች እንደኾኑ የሚጠቁሙ ነበሩ፡፡ ይህ በfunctionalist approach ላይ የተመሠረተው የማኅበረሰብ እና የሥነ ሰብእ ተመራማሪዎች ክብረ በዓልን ከማኅበረሰባዊ ሥሪት፣ ከሃይማኖታዊ መስተጋብር ጋራ ይመለከቱት ነበር (Zyphur 2009):: በሌላ አንጻር ደግሞ የPsychoanalytic Approachን ተከትለው ጥናት የሚያደርጉት እንደነ Robertson Smith's ያሉ አጥኚዎች ደግሞ ክብረ በዓል ንቁ ያልኾነውን የሰው ልጅ አእምሮ በመግራት ማኅበረሰባዊ ባሕርይን ወግ የሚያስይዝ ነው በማለት ከሥነ ልቡና ዐይን ይመለከቱታል (Bell 12, 2009)፡፡

የfunctionalist approachን ተከትለው ክበረ በዓል ላይ ያጠኑ ተመራማሪዎች ማኅበረሰቦች ዕሴታቸውን እንዲጠብቁ እና ማኅበረሰባዊ መዋቅራቸውን ጠንካራ እንዲኾን ክብረ በዓል ያደርጋሉ የሚል ጠንካራ አቋም እያስቀመጡ መጥተዋል (Radcliffe-Brown, Malinowuski እና Robertson Smith, Segument Freud, Durkheim in Bell 2009, 16- 25) ፡፡

የዚኽ ጥናት ዋንኛ መንሻ መነገድም የእነዚኽ ተመራማሪዎች ፈለግ ነው፡፡ ክብረ በዓል አንድ ማኅበረሰብ በጋራ በሚኖርበት አካባቢ ከግላዊ የዕለት ከዕለት ሕይወቱ ባሻገር በማኅበር ይኖር ዘንድ አንድነቱን አብሮነቱን፣ ትውፊቱን እና ዕሴቱን እያስቀጠለ የሚኖርበት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ክብረ በዓል ለክብረ በዓሉ ባለቤቶች ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ሰባዊ እና ኹለንተናዊ ፋይዳዎቹ ብዙ ናቸው፡፡ ክብረ በዓል ማኅበረሰባዊ መዋቅርን በማስተካከል እና ዝምድናን በመፍጠር ማኅበረሰቡ የተረጋጋ ሕይወት እንዲኖረው ያስችላል፡፡ ክብረ በዓል በአክባሪዎቹ ውስጥ የማኅበረሰባዊ ሥሪታቸውን የሚማሩበት፣ የሚያስቀጥሉበት፣ የሚያስተላልፉበት እና ተግባቦት የሚፈጥሩበት በመኾኑ ከነፍስና ከሥጋቸው ጋራ የተቆራኘ ነው (Turner Victore (1991, 6, Rappaport 1999, 46, Mariza G.S Peirano 200,11 እና Ogunleye 2014, 209)፡፡

በዘርፉ ደጋግመው ጥናት ካደረጉ ምሁራን መካከል Cather Bell (2009, 3) ክብረ በዓል ከሃይማኖት ጋራ ያለውን ዝምድና አጥብቀው ተመልክተውታል፡፡ እንደ እሳቸው ሐሳብ ክብረ በዓል ሲሳብ ኹል ጊዜ የሃይማኖት እና የባህል ሐረጎች አብረው ይመዘዛሉ ባይ ናቸው፡፡ ስለኾነም በአንድ ክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች፣ ባህላዊ መስተጋብሮች እና ሚታዊ ትረካዎች ተባብረው የሚከወኑበት ነው ይላሉ፡፡ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎች የነፍስ እና የሥጋ፣ የውዳሴ እና የግሳጼ ጭብጦች ተዛንቀው ስለሚከወኑበት ከፍ ያሉ ፎክሎራዊ ትውፊቶችን እና ዕሴቶችን የተሸከሙ ናቸው፡፡ እነዚህ ዕሴቶችና ትውፊቶች[3] ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው በመኾኑ ማኅበረሰባዊ ዋጋቸው ከፍ ያለ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ባላቸው ብርቅ እና ድንቅ ትውን ጥበባት ምክንያት ለቱሪስት መስሕብ፣ ለማኅበረሰባዊ መስተጋብር፣ ለምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት እና ለሰባዊ ልዕልና የማይነጥፉም፣ የማይጎድፉም ናቸው፡፡ ዐኹን ዐኹን ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትን ወደ ገበያ በማስገባት እና በማስተዋወቅ እየተጠቀሙ ያሉ ሀገሮች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካካል እንደ ግብጽ፣ እንደ ግሪክ እና እንደ ሮማን የመሳሰሉ ሀገሮች ፎክሎራዊ የኾኑ ትውፊታዊ ቅርሶችን እና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎችን ለቱሪስት መስሕብነት በማዋል ከዘርፉ በርካታ ጥቅሞችን በማግኘት ላይ ናቸው (S. R. F Price, 1984, 1)፡፡

---

[3]ቃሉ ከግእዝ የተወሰደ ሲኾን አወፈየ ሰጠ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ትውፊት ደግሞ ስጦታ ማለት ነው፡፡ ይህም ከአባት ወደ ልጅ፣ ከማኅበረሰብ ወደ ማኅበረሰብ እና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚደረገውን የባህል ቅብብሎሽ ማለቱ ነው፡፡ በእንግሊዘኛው ደግሞ (Tradition) የሚለውን ይወክላል፡፡

እነዚህ የቱሪስት መስሕብ በመኾን የሚያገለግሉ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎች ከሃይማኖታዊ ይዘታቸው በተጨማሪ ዓለማቀፋዊ ዕውቅና፣ የረዘመ ዕድሜ እና የጸና ክዋኔ ባለቤቶች ናቸው፡፡ በዚህ መለኪያ የሚያልፈው የክርስትና ሃይማኖት የበርካታ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት መሠረት ነው፡፡ ከክርስትና[4] ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት መካከል የጥምቀት ክብረ በዓል ተጠቃሽ ነው፡፡ የጥምቀት ክብረ በዓል መነሻው የኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ እጅ መጠመቅ ነው፡፡ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጥቶ በፍጥረቱ በዮሐንስ እጅ ሲጠመቅ ብዙ ስውር ምስጢራት ተገልጸዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል የስላሤ መገለጥ፣ የአዳም አዳ ደብዳቤ መሻር እና የውሐዎች መቀደስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው (ማቴ 3፣11፣ ቆላይሲስ 2፣14 እና ጥዑመ ልሳን ካሳ 1959፣ 22)፡፡ እነዚህ ምስጢራት ክርስቶስ ዝቅ ብሎ በዮሐንስ እጅ መጠመቁ የተደበቀው ስውር ምስጢር መገለጡ እና የውሐዎቹ መቀደስ ሃይማኖታዊ ይዘት ብቻ የተሸከሙ ሳይኾን ማኅበረሰባዊ፣ ሰባዊ እና ሥነ ምግባራዊ ይዘትም ያላቸው ናቸው (ዘማርያም ኤፍሬም እና በእደ ማርያም ዳንኤል 1998፣ 5-8)፡፡

በመኾም የጥምቀት ክብረ በዓል የመዳን፣ የአብሮነት፣ የመመለስ፣ የመቀደስ፣ መባረክ የፍቅር፣ የመንጻት ጽንሰ ሐሳቦችን (concepts) የተሸከመ ነው፡፡ ለጥምቀት ክብረ በዓል መነሻም መዳረሻም የሆኑት ውሃ የንጽሕና፣ ታቦት የድኅነት፣ ማኅበረሰብ የአብሮነት፣ ርኁቅ የመመለስ፣ ኅጹጽ መቀደስ ትእምርቶች ናቸው፡፡

በክርስቶስ መነሻነት የጥምቀት ክብረ በዓል በክርስትና አማኞች ዘንድ በዓለማቀፍ ደረጃ ይከበራል፡፡ በተለይ በሩሲያ፣ በግሪክ፣ በአሌክሳንደሪያ እና አርመንያ በመሳሰሉት ሀገራት እንደየ ሀገራቱ የእምነት ሥርዐት፣ ባህል እና የአየር ጸባይ ኹኔታ የጥምቀት ክብረ በዓል በየዓመቱ በግግር በረዶ ውስጥ ጥምቀተ ባሕር በመፍጠር እየተጠመቁ ያከብሩታል፡፡ በሀገራችን ኢትዮጵያ ደግሞ የጥምቀት ክብረ በዓል በጃንደረባው ኢትዮጵያዊ የተጀመረ እንደኾነ ቢነገርም በዋናነት ግን በድምቀት መከበር የጀመረው በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በዐፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ከቅዱስ ያሬድ መሕሌታዊ መምጣት ጋራ ተያይዞ እንደኾነ ይገለጻል (ዘማርያም ኤፍሬም እና በእደ ማርያም ዳንኤል፣ 1998፣ 5-8)፡፡

[4] ክርስትና ያልኩት የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ውስጥ ይከበር እንጅ በክርስቶስ ጥምቀት ላይ ኹሉም የክርስትና ሃይማኖቶች አስተምህሮ የተቀበሉት በመኾኑ ነው፡፡

የጥምቀት ክብረ በዓል በሀገራችን በድምቀት በየ ዓመቱ ጥር 11 ቀን እየተከበረ ይኖራል፡፡ የበዓሉ ዓከባበር ሥርዐት በኹሉም አካባቢዎች እና የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በሃይማኖታዊ ቀኖናው የአከባበር ተመሳስሎ ይታይበታል፡፡ ሃይማኖታዊ ቀኖናው እና መንፈሳዊ አስተምህሮው ተመሳሳይ ይኹን እንጂ ባህላዊ ይዘቱ እና ድምቀቱ ከቦታ ቦታ እና ከጊዜ ጊዜ የሚለያዩበት ኹኔታዎች አሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ በሀገራችን ክብረ በዓላትን እና ንግሥን ለተወሰኑ ቦታዎች እና ጊዜያቶች ከፍ አድርጎ መስጠት የቆየ ሥሪት ይኹን ልማድ መኖሩ ነው (ዘማርያም ኤፍሬም እና በእደ ማርያም ዳንኤል፣ 1998፣ 5-8)፡፡

የዚኽ ጥናት ማጠንጠኛ የኾነው የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል በጎንደር በየ ዓመቱ እየደመቀ እና እያሸበረቀ[5] ይከበራል፡፡ የጎንደር ጥምቀት አጀማማር ከኢትዮጵያ የጥምቀት ክብረ በዓል አከባበር ጋራ የሚዘከር ነው፡፡ ይኹን እንጂ ኺደቱ እና ዕድገቱ ከጎንደር የመናገሻ ከተማ የመኾን፣ ከነገሥታቱ እና ከሊቃውንቱ ጋራ ተሰናስሎ የሚታይ ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ እና ልዕልና ኀይለ መስቀል 20011 ቃ.መ)፡፡ የጎንደር ጥምቀት በዋናነት በ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተለይ በአጼ ፋሲል ዘመነ መንግሥት የቤተ ክህነት እና የመንግሥት ክብረ በዓላት ለመኾን በቅቷል፡፡ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል የመዋኛ ባሕሩ መገንባት እና የጥምቀቱ ሥርዐት መበጀት አንዱ ምክንያት ዮርዳኖስን በጎንደር ለመወከል ካለ መንፈሳዊ ፍላጎት እንደ ነበር ይገመታል (ልዕልና ኀይለ መስቀል 20011 ቃ.መ)፡፡

ይህን ሃይማኖታዊ ፍላጎት ለማሳካት የጎንደር ጥምቀት ከዮርዳኖስ ጋራ የሚፈካከርባቸው መንፈሳዊ እና መልክዓ ምድራዊ ውክልናዎች አሉት፡፡ የዮር እና የዳኖስ ወንዞችን ለመወከል ሲባል የጎንደር ጥምቀት በቀሐ እና በአንገረብ ወንዝ መካካል ይገኛል፡፡ ክርስቶስ የተጠመቀበትን ዮርዳኖስን የሚወክል ድግሞ በፋሲል የተገነባው ጥምቀተ ባሕር ይገኛል፡፡ በዮርዳኖስ ወንዝ ላይ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ የነበሩትን በርካታ ተጠማቂዎችን የሚወክሉ በጎንደር ባሕረ ጥምቀት ውስጥ በርካታ ወጣቶች ገብተው እየዋኙ ይጠመቃሉ፡፡ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ የማይተዋወቁ እና ከተለያዩ ቦታዎች የመጡ በዮሐንስ እጅ ይጠመቁ ነበር፡፡ በጎንደር ጥምቀት ከዚህ በፊት በውል የማይተዋወቁ ወጣቶች በአንድ ላይ ጥምቀተ ባሕሩ ብቻ አገናኝቷቸው ይጠመቃሉ፡፡

---

[5] ያልኩበት ምክንያት በፎቶ ለማሳየት ከዚህ ገጽ ላይ ቦታው ባለመኾኑ እንጂ በ2013 ዓ.ም የጎንደርን ጥምቀት ስታደም በየ ዕድሜ ደረጃቸው፣ በአካባቢዎቻቸው፣ በትዳር አጋሮቻቸው፣ በጽዋ ማኅበራቸው እና በመሰል ፎክሎራዊ ቡድኖች ተመሥርተው የሚለበሱትን የጥምቀት አልባሳት ፎክሎራዊ ውበት ለመግለጽ ነው፡፡

የጎንደር ጥምቀተ ባሕር የሚዋኙት በዕድሜ ወጣት መኾናቸውም ክርስቶስ በ30 ዓመቱ የመጠመቁ ምሳሌ ነው፡፡ በባሕረ ጥምቀቱ ሥርዐት ወጣቶች ከመዋኘታቸው በተጨማሪ በዙሪያው ከሚገኙ ትልልቅ እና ረጃጅም ዛፎች ላይ በመውጣት ወደ ታች በመወርውር ወደ ጥልቁ ይገባሉ፡፡ ይህም የሕይወትን ውጣ ውረድ ዑደት የሚተረጉም ነው፡፡ በባሕረ ጥምቀቱ ዋና ውስጥ የሚታይ ጠብ፣ ግፊ እና ተንኮል የለም፡፡ የጎንደርን የባሕረ ጥምቀት ሥርዐት ለመመልከት የሚታደመው የሰው ቁጥር እጅግ ብዙ ነው፡፡ የሚታደመው የሰው ቁጥር ከመብዛቱ የተነሣ የሚሠራው ርብራብ የሚደረመስበት ኹኔታ ዐልፎ ዐልፎ ያጋጥማል፡፡ ለዚህም በ2012 ዓም የተከሰተው የርብራብ መደርመስ ተጠቃሽ ነው፡፡ በ2013 ግን ይህን አደጋ ለማስቀረት ሲባል ርብራቡ በብረት የተሠራ በመኾኑ ችግሩ አላጋጠመም፡፡ በባሕረ ጥምቀቱ እና በጎንደር ጥምቀት ነጋዴዎቹ፣ ዘማሪዎቹ ሊቃውንቱ ወጣቱ፣ ሕፃናቱ፣ አዛውንቱ እና የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚታደሙበት ነው፡፡ በዚህ ውስጥ በርካታ የኾኑ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ እና ሰባዊ ጉዳዮች ይስተናገዱበታል፡፡

አጥኚው በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ቤተኛ በመኾን ደጋግሞ የመመልከት እና የመሳተፍ ዕድል ገጥሞታል፡፡ ይህ ደጋግሞ የመመልከት እና የመሳተፍ ዕድል የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ እና ማኅበራዊ ፋይዳዎቹ ምን እንደሚመስሉ ለማጥናት በአጥኚው ላይ ጉጉት አሳድሮበታል፡፡ በዚህ መልኩ ጥናቱ “የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ እና ፋይዳዎቹ በጎንደር” በሚል ርእሰ ጉዳይ ተጠንቶ ቀርቧል፡፡ ዓላማውም በጎንደር የሚከበረውን የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ እና ፋይዳዎቹን መመርመር፣ ማጥናት እና ማሳየት ነው፡፡

### 1.2. የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት

የጥምቀትን ክብረ በዓል በUNESCO ለማስመዝገብ እንቅስቃሴ በተጀመረበት በ2008 ዓ.ም ከክልልና ከፌደራል ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለ ሙያዎች ወደ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ መጥተው ነበር፡፡ በዚሁ ወቅት ስለ ጎንደር ጥምቀት በጥምቀቱ ላይ ተገኝተው የክብረ በዓሉን ክዋኔ ቀረጻ እንዲያካኺዱ እና መረጃ እንዲያቀርቡ ከተመረጡት የዩኒቨርሲቲው አባላት አንዱ እኔ ነበርኩ፡፡ በዚህ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ላይ ባደረግኹት ምልከታ የክብረ በዓሉ ድምቀት እና የክዋኔው ሥርዓት ያሳደረብኝ ተመስጦ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ባደረግኹት

ምልከታ ምክንያት በጎንደር ጥምቀት ላይ ጥናት ለማካኼድ ቀጣይ አራት መነሻ ኹኔታዎች ገጥመውኛል፡፡

አንደኛው አነሣሽ ምክንያት በጥምቀት ክብረ በዓል ወቅት የሚዘመሩት ዝማሬዎች፣ የሚቆሙት ቁመቶች፣ የሚቀነቀኑትን ቃል ግጥሞች፣ የሚጨፈሩት ጭፈራዎች፣ የሚለበሱት አልባሳት እና የሚያዙትን ንዋየ ቅድሳት ከሃይማኖታዊ ይዘታቸው በተጨማሪ ያላቸውን ማኅበራዊ ገጽታ ለመመርመርና ለማጥናት በማሰብ ነው፡፡

ቀጣዩ እና ኹለተኛው አነሣሽ ምክንያት ደግሞ የጥምቀት ክብረ በዓል መነሻ ሃይማኖታዊ ነው፡፡ ብዙው ማኅበረሰብም በዚኹ መነጽር ይመለከተዋል፡፡ በመኾኑም ከሃይማኖታዊ አስተምህሮው ባሻገር በቱሪዝም፣ በምጣኔ ሀብት፣ በማኅበራዊ መዋቅር፣ በሥነ ምግባር አስተምህሮ እና በባህላዊ አስተዳደር የሚያበረክተው አስተዋጽኦ እንዳለ በጥናት ለማረጋገጥ ስለፈለግኹ ነው፡፡

ሦስተኛው አነሣሽ ምክንያቴ ደግሞ ኢትዮጵያ ቀደምት ሥልጣኔ ያላትና የተለያዩ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ባለቤት ናት፡፡ ይኹን እንጂ እነዚህን ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት እና ቅርሶች ለሰላም፣ ለቱሪዝም እና ለአካባቢ ጥበቃ ትግበራ ብዙ እየተጠቀመች አይገኝም፡፡ በመኾኑም በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ጥናት በማካኼድ መጠነኛ የኾነ መፍትሔ ለመጠቆም ስለፈለግኹ ነው፡፡

አራተኛው እና የመጨረሻው አነሣሽ ምክንያት ደግሞ የርእሰ ጉዳይ ዐዲስነት ነው፡፡ በዚህ ርእሰ ጉዳይ ላይ ልሠራ ስነሣ በልኬም ቢኾን የተሠሩትን ሥራዎች ዳሠሣ አድርጌአለሁ፡፡ ባደረግኩት ዳሠሣ ስለ ቤተ ክርሰቲያኗ የገዳማት ታሪኮች ላይ እና በማሕሌት ዙሪያ የተሠሩ ውስን ጥናቶችን ከማግኘት ባለፈ "የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ አንድምታና ፋይዳዎቹ" በሚል የተሠራ ሥራ ባለመኖሩ በዐዲስ ርእሰ ጉዳይ ላይ ጥናት ማካኼድ ስለፈለግኹ ነው፡፡

### 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በፎክሎር ትምህርት ክፍል ያለውን የጥናት ዘርፍ ከፍ ከማድረግ አኳያ ውስን ጠቀሜታ አለው፡፡

በዚህ ርእሰ ጉዳይ እና ጥናቱ በተካኼደበት አካባቢ ቀጣይ ጥናት ማድረግ ለሚፈልግ ተመራማሪ ንድፈ ሐሳባዊ፣ ፅንሰ ሐሳባዊ እና አካባቢያዊ መረጃዎችን በመስጠት ያገለግላል፡፡

ስለ ጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ፣ ስለ ጎንደር ማኅበረሰባዊ መዋቅር፣ ዕሴት፣ ፍልስፍና እና ሥነ ልቡና ያለውን መስተጋብር መረዳት ለሚፈልጉ አካላት ፍንጭ ይሰጣል፡፡

ለተጠኚዎቹ ማኅበረሰቦች ከጥምቀት ክብረ በዓል ጋራ በተያያዘ ስለ ሃይማኖታቸው፣ ባህላቸው፣ ማኅበራዊ መዋቅራቸው፣ ሰባዊ ዕሳቤያቸው እና ዕሴታቸው በጥናት የተደገፈ መተዋወቅ ይፈጥርላቸዋል፡፡

ጥናቱ የጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔን መሰነድና መቅረስ ዓላማው ባይኾንም እግረ መንገዱን የጥምቀት ክብረ በዓልን ክዋኔ በሰነድ መልክ ሰብስቦና ቀርሶ በማቆየት የራሱ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ጥናት በዐቢይ እና ንኡስ ዓላማዎች የተዋቀረ ነው፡፡

### 1.4.1. የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ

የጎንደርን ጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔው፣ አንድምታ፣ሚታዊ ታሪክ፣ ቃል ግጥም፣ ቁሳዊ ባህል እና ፋይዳዎቹን መመርመር፣ መተንተን እና ማጥናት ነው፡፡

### 1.4.2. የጥናቱ ንኡሳን ዓላማዎች

- የጥምቀትን ክብረ በዓል ዐውድ ማጥናት እና መተንተን፣
- በክብረ በዓሉ ዐውድ ላይ የከዋኞቹን ክዋኔዎች መመርመር እና መተንተን፣
- የጥምቀት ክብረ በዓል ያለውን ማኅበራዊ አንድምታ እና መስተጋብር ማጥናት፣
- የጥምቀት ክብረ በዓል ያለውን ምጣኔ ሀብታዊ አንድምታ እና ፋይዳ መተንተን፣
- የጥምቀት ክብረ በዓል ያለውን ሰባዊ ጠቀሜታ እና ንጽኅና ማጥናት እና
- የጥምቀት ክብረ በዓል ለቱሪዝም እና ለአካባቢ ጥበቃ ያለውን ፋይዳ መተንተን ናቸው፡፡

### 1.5. የምርምሩ ጥያቄዎች

- የጥምቀትን ክብረ በዓል ዐውድ ምን ይመስላል?
- የክብረ በዓሉ ከዋኞች እና ክዋኔዎቻቸው ምን ይመስላል?
- የጥምቀት ክብረ በዓል ምን ማኅበረሰባዊ መስተጋብር እና አንድምታ አለው?
- የጥምቀት ክብረ በዓል ምጣኔ ሀብታዊ አንድምታ እና ፋይዳ ምን ይመስላል?
- የጥምቀት ክብረ በዓል ምን ሰባዊ ጠቀሜታ እና ንጽኅና አለው? እና
- የጥምቀት ክብረ በዓል ለቱሪዝም እና ለአካባቢ ጥበቃ ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

  የሚሉት ናቸው፡፡

### 1.6. የጥናቱ ወሰን

ይህ ምርምር በጥናት ዘውግ፣ በጥናት አድማስ፣ በንድፈ ሐሳብ፣ በሥነ ዘዴ፣ በጊዜ እና በቦታ የተወሰነ ነው፡፡

**የጥናት ዘውግ፡-** ከጥናት ዘውግ አኳያ የጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የተወሰነ ነው፡፡ የጥምቀት ክብረ በዓል የአደባባይ፣ የፍስክና የሐሤት በዓል ነው፡፡ ክብረ በዓሉ ከሕፃናት እስከ ዐዋቂ፣ ከልሂቅ እስከ ደቂቅ ያሉትን በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎች እና መገልገያ ባህላዊ ቁሶች በአንድ ላይ የሚያገናኝ ነው፡፡ በመኾኑም የጥምቀትን ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ፣ አንድምታ እና ፋይዳ በማሳየት ላይ የተወሰነ ነው፡፡

**የጥናቱ ጥልቀት ስፋትና አድማስ፡-** በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል በክብረ በዓሉ ዐውድ ላይ እና ስለ ጥምቀት ክብረ በዓል በሚነገሩ ምልኪዓዊ ታሪኮች እና ቃል ግጥሞች ላይ ተመሥርቶ የተጠና ነው፡፡ ከጎንደር ውጭ ስለሚከወኑ የጥምቀት ክብረ በዓላት እና ስለ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓላት ብዛትና ምንነት፣ አወንታዊና አሉታዊ ጎኖች እና መሰል ከበዓላት ጋራ የሚነሡ ዕሳቤዎችን ጥናቱ አይዳሥሥም፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ-ክርስቲያን በዓላት በርካታ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ይዘቶችን ያቀፉ ናቸው፡፡ በሰፊ ይዘትና ቅርጽ የተሸመኑትን የቤተ ክርስቲያኗን ክብረ በዓላት እና በዓላት ከዚህ ጥናት ጋራ አዳብሎና አዛንቆ ለማየት መሞከር ጥናቱን ገደብ የለሽ እና ዋላይ ያደርገዋል፡፡ በመኾኑም ይህ ጥናት የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓልን ሥርዐተ ክዋኔ አንድምታ እና ፋይዳዎቹን ለማሳየት ክብረ በዓሉ በሚከበርበት ዐውድ እና ስለ ጎንደር

ጥምቀት የሚነገሩት ሥነ ቃሎች፣ ምልኪዓዊ ታሪኮች እና ባህላዊ ቁሶች ላይ ብቻ ተመሥርቶ የተጠና ነው፡፡

**የንደፈ ሐሳብ ወሰን፡-** ጥናቱ ከንደፈ ሐሳብ አኳያ በአራት ንድፈ ሐሳቦች የተጠና ነው፡፡ እነሱም የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ፣ የተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ፣ የምልኪ ንድፈ ሐሳብ እና የሥነ ፍካሬ ንደፈ ሐሳቦች ናቸው፡፡ የጥምቀትን ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ ለመመልከት በዋናነት የክዋኔ ንደፈ ሐሳብን ተጠቅሜአለሁ፡፡ የፋይዳዎቹን ዕሳቤ ለማየት ደግሞ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ተመርጧል፡፡ የሃይማታዊ፣ የአፈ ታሪካዊ እና የሥነ ቃል ዕሳቤዎች ለመመልከት የምልኪ ንድፈ ሐሳብን ተጠቅሜያለሁ፡፡ የሥነ ፍካሬ ንደፈ ሐሳብ ደግሞ በዚህ ትምህርት ክፍል ዐዲስ ንደፈ ሐሳብ ቢኾንም እንደ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ላሉ የፎክሎር ጥናቶች አስፈላጊ ኹኖ በመገኘቱ ለክብረ በዓሉ አንድምታ መመልከቻ ተመርጧል፡፡ ይህ ንደፈ ሐሳብ በክብረ በዓሉ ክዋኔ እና በክብረ በዓሉ የፋይዳዎች ላይ ጥልቅ ዕውቀት ያላቸውን ተጠኚዎች ለማግኘት ሲባል ለጥናቱ መመልከቻ ተመርጧል፡፡ በመኾኑም ይህ ጥናት በክዋኔ፣ በተግባራዊ፣ በምልኪ እና በሥነ ፍካሬ ንድፈ ሐሳቦች ላይ ተወስኖ ተጠንቷል፡፡

**የሥነ ዘዴ ወሰን፡-** ሌላው ተጠቃሽ የሥነ ዘዴ ወሰን ነው፡፡ ጥናቱ ዐይነታዊ ሥነ ዘዴን የተከተለ ነው፡፡ በዚህ ሥር ታላሚ ንሞና፣ የብድግብድ ንሞና እና የድርሻ ንሞና[6] በሚሉት ላይ ተወስኖ ተጠንቷል፡፡ እንዲኹም የዐይነታዊ፣ የአሐድ[7]ና ዐውድ፣ የክዋኔ እና የፍካሬ የመተንተኛ ስልቶች ላይ ተወስኖ ተተንትኗል፡፡

**የጥናት ቦታ ወሰን፡-** የጥምቀት ክብረ በዓል በሃይማኖታዊ ቀኖና እና ክዋኔ ላይ በየትኛውም ቦታ ተመሳስሎ የሚታይበት ነው፡፡ ክብረ በዓሉ ምንም ያክል የሃይማኖታዊ ቀኖና ያለው ይኹን እንጂ እንደየ አካባቢው ምልኪ፣ አፈታሪክ፣ ዕውቀት እና ባህል የጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ከቦታ ቦታ የሚለያይበት ባህላዊ ክዋኔ አለ፡፡ በዚህ መነሻ የዚህ ጥናት ቦታ በጎንደር የተወሰነ ነው፡፡ ጎንደር የተመረጠበት ምክንያት ከ#4ቱ[8] ታቦታት ጋራ ተያይዞ በዚህች ከተማ ክብረ በዓሉ በድምቀት በየዓመቱ የሚከበር መኾኑ ነው፡፡ በመኾኑም በየዓመቱ እየደመቀ የሚከበረው የጎንደር ጥምቀት አንድምታና ፋይዳ ለመመርመር ያለመ ነው፡፡

---

[6] Quota Sampling ለሚለው ቃል የአማርኛ ትርጉም ነው፡፡

[7] Text ለሚለው ቃል የአማርኛ ትርጉም ነው፡፡

[8] የኢትዮጵያ (የግዕዝ) ቁጥር ሲኾን 44 ማለት ነው፡፡

**የጥናት ጊዜ፡-** የጥናቱ የጊዜ ወሰን የጥምቀት በዓል የሚከበረው በየዓመቱ ጥር 11 ቀን ነው፡፡ በጥምቀቱ ዐውድ በ2011 ከጥር አንድ እስከ ሠላሳ በምልከታ እና ዐልፎ ዐልፎም በቃለ መጠይቅ በጎንደር ከተማ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት ከጥምቀት ዐውድ ውጭ በ2011 ከሐምሌ አንድ እስከ ነሐሴ ሠላሳ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት 16 ወንዶች እና 13 ሴቶች በድምሩ 29 መረጃ ሰጭዎችን ያሳተፈ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ከእነዚህ መካካል ኹለት የቡድን ውይይቶች አንድ የወንዶች እና አንድ ደግሞ የሴቶች ባለ ሰባት አባላት ያሉት በድምሩ 14 ተጠኚዎችን ያሳተፈ የቡድን ውይይት ተካኺዷል፡፡ እንደዚኹም በ2012 ዓ.ም ጥር 05/2012 ዓ.ም በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ዐውድ ላይ በምልከታ መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በዚኹ ዓመት ከጥር 12//2012 እስከ የካቲት 10/2012 ድረስ በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት 21 ወንዶች እና 9 ሴቶች በድምሩ 30 መረጃ ሰጭዎችን ያካተተ መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በ2013 ዓ.ም ጥር 11 ቀን በጥምቀት ክብረ በዓል ዐውድ በምልከታ በፎቶግራፍ እና በቪዲዮ ካሜራ መረጃ ሰብስቤአለሁ፡፡ እንደዚኹም በቃና ዘገሊላ ጥር 12/2013 ዓ.ም ኹለት ተተኳሪ ቡድን ውይይቶችን አከናውኛለሁ፡፡ እነዚህ የቡድን ውይይቶች ባለ ሰባት አባላት ያሏቸው ናቸው፡፡ ቡድኖቹም አንዱ በሴቶች የተከናወነ ሲኾን ሌላው ደግሞ በወንዶች የተካኼደ የቡድን ውይይት ነው፡፡ በ2013 ዓ.ም ከጥር 12/2013 እስከ ጥር 29/2013 ዓ.ም ድረስ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት 17 ወንዶች እና 18 ሴቶች በደምሩ 35 መረጃ ሰጪዎች የተሳተፉበት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ በሦስት ዓመታት ውስጥ 54 ወንዶች እና 40 ሴቶች በድምሩ 94 መረጃ ሰጪዎች በጥናቱ ተሳትፈዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል 66ቱ በቃለ መጠይቅ እና 28ቱ ደግሞ በቡድን ውይይት መረጃ የሰጡ ናቸው፡፡

## 1.7. በመረጃ አሰባሰብ እና ትንታኔ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

### 1.7.1. ያጋጠሙ ችግሮች

- አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች ለቃለ መጠይቅ፣ ለፎቶ ግራፍ እና ለመቅረጸ ድምፅ ፈቃደኛ ያለ መሆን ተግዳሮቶች ገጥመውኝ ነበር፡፡
- በባህልና ቱሪዝም ቢሮ ለአጥኚ ተብሎ የተዘጋጀ የመግቢያ ካርድ ባለመኖሩ ምክንያት በሚከለከሉ ቦታዎች ላይ እየተዘዋወሩ ምልከታ እና መቅረጸ ድምጽ ለማካኼድ ተቸግሬ ነበር፣

- በጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ላይ በአርምሞና በትእምርት የሚገለጹትን ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ማኅበራዊ ዕሳቤዎች ለመመልከት፣ ለመረዳት እና መረጃ ለመሰብሰብ ችግር ገጥሞኝ ነበር።
- ከፒያሳ በኋላ ታቦታቱ ሰላምታ ተሰጣጥተው ስለሚለያዩ በየ ቤተ ክርስቲያኖቹ ያሉትን የክዋኔ ሥርዐት ለማዳረስ እና ለመቅረጸ ድምጽ መቸገር፤ በተለይ የፊት አቦ፣ የእልፍኝ ጊዮርጊስ እና የመንበረ ልዑል ቅዱስ መድኃኔዓለም ታቦታት በተመሳሳይ ሰዓት ስለሚገቡ የሚከወኑትን ክዋኔዎች ለመመልከት፣ ለመቅረጽ እና ለመከታተል መቸገር ናቸው።

### 1.7.2.የተወሰዱ መፍትሔዎች

- ጊዜ ወስጄ የጥናቱን ዓላማ በማስረዳት እና በማሳወቅ መረጃ ሰጪዎቹ ለቃለ መጠይቅ፣ ለፎቶ ግራፍ፣ ለመቅረጸ ድምፅ እና ስማቸውን በጥናቱ ውስጥ ለመጠቀም ፈቃደኛ እንዲኾኑ በማድረግ የነበረውን ችግር ለመቅረፍ ችያለሁ።
- የካህናቱን አለባበስ በመልበስ በዋዜማው ያለውን መረጃ ሰብስቤአለሁ። ለጥምቀቱ ዕለት ደግሞ ለጋዜጠኞች የተዘጋጀውን መግቢያ ካርድ በመጠቀም እና ለመረጃ ሰጪዎች ዓላማዬን በማስረዳት ተገቢውን መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ።
- በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ከፍ ያለ የዕውቀት ደረጃ ያላቸውን የአራቱን ጉባኤ ቤት የአንድምታን፣ የተክሌ አቋቋምን፣ የጎንደሬ ቋቋምን፣ የቅዳሴን፣ የቅኔን፣ የድጓንና የዝማሬ መዋሥዕትን ምስክር ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን በታላሚ ንሞና ዘዴ በመጠቀም ተገቢ የኾነ መረጃ መሰብሰብ እና መተንተን ችያለሁ። በተጨማሪ ስለ ጎንደር ጥምቀት ላቅ ያለ ዕውቀት ያላቸውን ምእመናን በቃለ መጠይቅና በቡድን ውይይት በማሳተፍ ትርጓሜ የሚያስፈልገውን መረጃው ለመገንዘብ ችያለሁ። እንደዚሁም በአንደበት የማይገለጠውን የክብረ በዓል ዕሳቤ በሥነ ፍካሬ፣ በንዋየ ቅድሳቱና በቁሳዊ ባህሎቹ ውክልና በመታገዝ ለመረዳትና ለመተንተን ችያለሁ።
- በዘርፉ ያሉ ኹለት አጋዥ ባለሞያዎችን በመጠቀም በሦስቱም ወሳኝ ቦታዎች መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ። እንደዚኹም በ2011 መንበረ መንግሥት መድኃኔዓለም፣ በ2012 ፊት አቦ እና በ2013 ደግሞ እልፍኝ ጊዮርጊስ በመገኘት መረጃ በተገቢው መንገድ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

## 1.8. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት "የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ፣ አንድምታ እና ፋይዳዎቹ በጎንደር" በሚል ርእሰ ጉዳይ የተጠና ነው፡፡ ውስጡም በዐሥር ምዕራፎች የተዋቀረ ነው። ምዕራፍ አንድ የመግቢያ ክፍል ሲኾን በውስጡ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሣሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓላማ፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ወሰን፣ በጥናቱ ያጋጥሙ ችግሮች እና መፍትሒዎቻቸው የሚሉትን ንኡሳን አርእስት የያዘ ነው፡፡

ምዕራፍ ኹለት ክለሳ ድርሳናት የሚለውን ክፍል አቅፏል። በዚህ ሥር ጽንሰ ሐሳባዊ ማሕቀፍ፣ ንድፈ ሐሳባዊ ማሕቀፍ እና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት የሚሉት ነጥቦች ተዳሰውበታል። ዕራፍ ሦስት የጥናቱ ሥነ ዘዴ፣ የጎንደር አከባቢያዊ ዳራና መስካዊ ተሞክሮዎች የሚሉትን ነጥቦች የያዘ ክፍል ነው።

ምዕራፍ አራት የጥምቀት ዐውድ የተተነተነበት ክፍል ሲኾን በሥሩም ቅድመ ጥምቀት፣ ከተራ እና ዕለተ ጥምቀት የሚሉትን ንኡሳን አርስት ይዟል። ምዕራፍ ዐምስት ደግሞ የጥምቀት ሥርዐተ ክዋኔ የሚለውን የትንታኔ ክፍል የያዘ ነው። ምእራፍ ስድስት የጎንደር ጥምቀትና ማኅበራዊ ፋይዳ የሚለው ክፍል የተተነተነበት ነው። ምዕራፍ ሰባት ደግሞ የጎንደር ጥምቀትና ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ ተተንትኖ ቀርቦበታል። ምዕራፍ ስምንት የጎንደር ጥምቀት ሰባዊ ፋይዳ የሚለው ክፍል ትንታኔ የተሰጠበት ምዕራፍ ነው። ምዕራፍ ዘጠኝ ደግሞ የጥምቀት ክብረ በዓል ለቱሪዝም እና ለአካባቢ ጥበቃ ያለው ፋይዳ ተተንትኖበታል። ምዕራፍ ዐሥር የመጨረሻው ክፍል ሲኾን ማጠቃለያውን የያዘ ነው። በሥሩም ማጠቃለያ፣ የይኹንታ ሐሳብ፣ ዋቢዎችን እና ዐባሪዎችን አካቷል።

# ምዕራፍ ኹለት፡- ክለሳ ድርሳናት

በዚህ ምዕራፍ ሥር ጽንሰ ሐሳባዊ ማሕቀፍ፣ ንድፈ ሐሳባዊ ማሕቀፍ እና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት የሚሉት ነጥቦች ተዳሰውበታል፡፡

## 2.1. ጽንሰ ሐሳባዊ ማሕቀፍ

### 2.1.1. የክብረ በዓል ምንነት

የሥነ ማኅበረሰብእ እና የሥነ ሰብእ አጥኚዎች functionalist" approachን መሠረት በማደረግ ከፍተኛ የኾነ ማኅበረሰባዊ ጉዳዮች የሚስተናገዱበት እና በማኅበራዊ ጠቀሜታ ውስጥ የሚለካ ነው በማለት ክብረ በዓልን ከማኅበረሰብ ዕሳቤ ጋራ አያይዘው ይበይኑታል፡፡ የPsychoanalytic Approacheን ተከትለው በዘርፉ ጥልቅ ጥናት ያደረጉ እንደነ Robertson Smith ያሉ የሥነ ልቡና ተመራማሪዎች ደግሞ "ክብረ በዓል ማለት ንቁ ያልሆነውን የአእምሮ ክፍል የሚገራ እና ማኅበረሰባዊ ባሕርይን የሚቀርጽ ነው" በማለት በሥነ ልቡና መስፈሪያ ይለኩታል Cather Bell (2009, 12-29), Islam እና Zyphur (2009, 6)::

ክብረ በዓል በአንድ በኩል ያልሠለጠኑ ቡድኖች ተግባር፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሥልጣኔ ምንጭ ተደርጎ በኹለት ፈርጆች የሚደረጉ ብያኔዎች ነበሩ፡፡ ከእነዚህ ብያኔዎች መካካል እነ Durkheim ክብረ በዓልን ከኋላ ቀርነት (primitive) ጋራ አያይዘው ለመመልከት ሞክረዋል፡፡ ይኹን እንጂ የነDurkheimን የኋላ ቀርነት ምልከታ ከተሜዎች እና ሥልጡን ነን የሚሉ ማኅበረሰቦች ክብረ በዓልን በብዙ ሰበብ እየደጋገሙ እንደሚያከብሩት በማስረጃነት በመጥቀስ የሰላ ትችት ገጥሞታል (Rappaport Ray 1999, 18 እና Zyphur 2009,7)::

በብዙ ተመራማሪዎች ዘንድ የተለያዩ ዐተያዮች እና ምልከታዎች መኖር የክብረ በዓልን ውስብስነት አመላካች ነው፡፡ ክብረ በዓል በውስጡ የተዛነቁ ባህሎች፣ ማኅበረ ግንኙነቶች፣ ቡድናዊ ተግባቦቶች እና ውጥንቅቅ ቁም ነገሮች የሚበለቱበት በመኾኑ ውስብስብ ባሕርይ ይታይበታል፡፡ ይህን ሐሳብ በተመለከተ Cather Bell (2009, 12) እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> *ክብረ በዓል ውስብስብ የኾነ የማኅበረ ባህል መግባቢያ ነው፡፡ ይህ የሚኾነው ክብረ በዓል በውስጡ በተለያዩ፣ ትውፊቶች፣ ልማዶች፣ የራስ ግንዛቤዎች ወይም*

*አረዳዶች የተገነባ ተግባቦት መኾኑ ነው፡፡ የክብረ በዓል ተግባቦት መፍጠሪያው መንገድ ተመራጭና ተደማጭ መኾኑ በሰዎች መካከል ሥርዓታዊ ተግባቦት እንዲኖርና እንዲቀጥል ያስተምራል፤ ያሠርጻል[9] (ትርጉም የግል)፡፡*

ክብረ በዓል በውስጡ የሥነ ልቡና፣ የማኅበረሰባዊ ጉዳዮች፣ ባህላዊ ዕሳቤዎች እና ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች ተዛንቀው የሚከወኑበት ዘውግ ነው፡፡ ክብረ በዓልን ከማኅበረሰባዊ ግንኙነቱ እና ሥሪቱ ባሻ በየ ቡድኑ የሚለበሱት አልባሳት፣ የሚቀርቡት ባህላዊ ምግቦች፣ የሚጠጡት ባህላዊ መጠጦች፣ በቃላት እና በድርጊት የሚፈጸሙት ክዋኔዎች ኹሉ ተዳምረው የተለያዩ ዕይታዎች እንዲኖረው አስችሎታል (Rappaport in Bell 2009, 31)፡፡

Jim Watts (2013,1) ስለ ክብረ በዓል ሲያትቱ "ክብረ በዓል ሲነሣና ብያኔ ሲሰጥ ቀድሞ ጥያቄ የሚፈጥረው እንዴት ይከወናል? እና ክዋኔው እንዴት ይተረጐማል? የሚሉት ነጥቦች ናቸው" ይላሉ፡፡ የJim Watts ብያኔ ማጠንጠኛ ሐሳብ በክብረ በዓል ላይ የሚከወኑት ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ጉዳዮች መዛነቅ እና ትእምርታዊ መኾን የክዋኔውን ትርጉም ለመረዳት፣ መረጃ ለመሰብሰብ እና ትንታኔ ለመስጠት ውስብስብ ያደርገዋል የሚሉ ናቸው፡፡ ክብረ በዓል ማለት ምን ማለት ነው? ለሚለው ጥያቄ Sims እና Stephen (2005, 95) ሲያትቱ “ክብረ በዓል በአንድ ፎክሎራዊ ቡድን ውስጥ በተደጋጋሚ ጊዜና ቦታ የሚከወን ፎክሎራዊ ዘውግ ነው ካሉ በኋላ ይህ ክዋኔ የማኅበረሰቡን አልባሳት፣ ምግቦች፣ ልማዶች፣ እምነቶች፣ ሥነ ቃሎች እና ሙዚቃዎች የመሳሰሉትን ኹሉ ያጠቃልላል” ይላሉ፡፡ በዚህ መልኩ የተቃኘው የSnims እና Stephen ብያኔ ከፎክሎር መስክ የሚቀዳ ነው፡፡

የክብረ በዓል ስፋት እና ውስብስብነት የሚለካው በውስጡ ትውን ጥበባት፣ሀገረሰባዊ ልማድ፣ ቁሳዊ ባህል እና ሥነ ቃል በአንድ ተባብረው የሚቀርቡበት ዐውድ መኾኑ ነው፡፡ እነዚህ የክብረ በዓል ስፋት፣ ጥልቀት እና ውስብስብነት ለክብረ በዓሉ ባለቤቶች አንዳች ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሰባዊ እና ሥነ ልቦናዊ ፋይዳዎች የሚያስገኙ ናቸው፡፡

---

[9] *Ritual as a complex socio-cultural medium variously constructed of tradition, exigency and self expression it is understood to play a wide variety of roles and to communicate … For the most part, ritual is the medium chosen to invoke those ordered relationships that are thought to obtain between human beings*

#### 2.1.1.1. የክብረ በዓል ፋይዳዎች

ክብረ በዓል ከሃይማኖት፣ ከልማድና ከማኅበራዊ መዋቅር ጋራ ያለው መስተጋብር ጠንካራ በመኾኑ የክብረ በዓሉ ባለቤቶች ባህላቸውን፣ ሃይማኖታቸውን እና ዕሴታቸውን በድንጋጌና በሥርዐት ያስቀጥሉበታል (Green 1997, 734)።

የምልኪ፣ የክብረ በዓል፣ የባህልና የሃይማኖት ግንኙነት ከመላቁና ከመጥበቁ የተነሣ አንዳቸው ለሌላቸው የመኖር እና የተስተላልፎ መሠረቶች ናቸው። በዚህ የተስተላልፎ ኺደት ውስጥ ክብረ በዓል እየተደጋገመ በመከወን ቀጣይነት ይኖረዋል። ክዋኔውም ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ቅደም ተከተላዊ እና ሥርዐታዊ ነው (Cather Bell 2009: 3 እና Green (1997, 134)። ክብረ በዓል ለመከበር ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊ እና ባህላዊ መንሥኤዎችን እና ምክንያቶችን ይፈልጋል። ክብረ በዓል በመከበሪያ ሰበቦች ምክንያት እየተመላለሰ እና እየተደጋገመ ይከበራል። በዚህ እየተደጋገመ እና እየተመላለሰ በመከበር ኺደት ውስጥ የሰዎች ማኅበራዊ ልማድ፣ ግብረ ገብነት እና ተግባቦት ቀጣይ እንዲኾን በማስቻል ሚናው የጎላ ነው (Kyalo 2013, 35፤ Watts 2013,1-25)።

የክብረ በዓል ፋይዳ ሲነሣ ከግላዊነት ይልቅ ማኅበራዊነትን፣ ከተናጠል ይልቅ አንድነት ባለው ማኅበረሰባዊ ዕሴት፣ ሕግ፣ ሥርዐት፣ ደንብ፣ ሃይማኖት፣ ተግባቦት እና አምላካዊ አዘክሮት ላይ ይጸናል (Kyalo, 2013, 35)።

**የክብረ በዓል ማኅበራዊ ፋይዳ፡-** የክብረ በዓል ተግባር ከሚመዘንባቸው እና ከሚለካባቸው ጠንካራ ነጥቦች መካከል አንዱ ማኅበረሰባዊ ፋይዳው ነው። ክብረ በዓል በማኅበረሰባዊ ተግባቦት፣ በዝምድና መፍጠር እና በዕርቀ ሰላም ማውረድ የሚለኩ በርካታ ማኅበራዊ ተግባራት አሉት። እንደዚኹም የማኅበረሰቡን ጸጥታ በመጠበቅ እና የአካባቢን ሰላም በማስፈን በኩል ክብረ በዓል ኹነኛ ፋይዳ አለው (Robertson Smith in Bell 2009, 27)።

ለዚህ ማንጸሪያ እንደ ጥምቀት ባሉ ክብረ በዓላት ላይ የሚከወኑት ክዋኔዎች ተጠቃሾች ናቸው። በጥምቀት ክብረ በዓል የፈረስ ጉግስ፣ የገና ጨዋታ፣ የትግል ግጥሚያ፣ የወጣቶች ንጥቂያ እና መሰል የጥንካሬ መለኪያ፣ ጉልበትን፣ ዐቅምንና ኃይልን የሚፈትኑ ውድድሮች ይከወኑበታል። እነዚህ ተግባራት ወጣቱን በአካል ብቃት እንዲጠነክር በማድረግ አካባቢን ከጥቃት እና ከሥጋት ለመጠበቅ ማኅበራዊ ደኅንነት (social armiy) ለመፍጠር ትልቅ ሚና

አላቸው፡፡ እንደዚሁም ክብረ በዓል በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ እርቀ ሰላም በማውረድ እና ግጭትን በማለዘብ በኩል ኹነኛ ፋይዳ አለው (Watson 43, 2016, Shultz, Noe, McGraw እና Dunbar, 2004)፡፡

**ክብረ በዓል ለሥነ ምኅዳር ጥበቃ ያለው ፋይዳ፡-** ክብረ በዓል ከማኀበራዊ ተግባቦት በተጨማሪ የአካባቢን ሥነ ምሕዳር ለመጠበቅ የራሱ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ይህን በተመለከተ Kay Milton (2005, 22) ክብረ በዓል ሥነ ምኅዳርን ለመጠበቅ ትልቅ ፋይዳ ያለው መኾኑን ጠቅሰው፣ የአካባቢን ሥነ ምኅዳር ለመጠበቅ የባህሉን ባለቤቶች ዕሴቶች እና ሀገረሰባዊ እምነቶች መንከባከብ እና ማክበር እንደሚገባ አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ በክብረ በዓሉ ባለቤቶች ዘንድ የክብረ በዓሉ ቦታና ጊዜ ከተራው ጊዜና ቦታ በተለየ መልኩ የተቀደሱና የተባረኩ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ በዚህ የቅድስና ቅቡልነት ምክንያት በማክበሪያው ቦታ የሚገኙ ዕፀዋት፣ አዕዋፋት፣ አራዊት እና እንስሳት እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡ በዚህ መልኩ ክብረ በዓል ሥነ ምኅዳርን በማስጠበቅ ማኅበረሰቡ ከአካባቢ እና ከተፈጥሮ ጋራ ተስማምቶ እንዲኖር ያስችለላል፡፡

ይህን በተመለከተ Bell (2009, 29) በበኩላቸው ክብረ በዓል ለአካባቢ እና ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ እንደነ ጉይኒያ ባሉ አገራት በከፍተኛ ኹኔታ ጥቅም ላይ እየዋለ እንደኾነ ያዘክራሉ፡፡ በተጨማሪም Geertz's in Kevin Schilbrack (2004, 131) የክብረ በዓል ዐጸድ፣ አልባሳት፣ ምርቃት እና እምነት ኹሉ ተዳምረው ለሥነ ምኅዳር መጠበቅ ትልቅ ፋይዳ ያላቸው መኾኑን አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡

እነ Candace S. Alcorta (2006,4) በበኩላቸው ደግሞ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎች ሰዎች እንዲግባቡ፣ ማኅበር እንዲፈጥሩ እና አካባቢያቸውን እንዲጠብቁ በማድረግ አስተዋጺቸው ከፍተኛ እንደኾነ ያስረዳሉ፡፡ የእምነት እና ቀኖና ሥርዐቶች በክብረ በዓሉ ውስጥ ጸንተው መኖራቸው ለሥነ ምኅዳር መጠበቅ እንደ ዋና ምክንያቶች ሊወሰዱ ይችላሉ፡፡ እንደ ጥምቀት ያሉ ክብረ በዓላት መንፈሳዊ ይዘት ስላላቸው በላቀ መልኩ ሥነ ምኅዳርን የማስጠበቅ ዐቅማቸው ከፍ ይላል፡፡ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት አካባቢያዊ ሥነ ምኅዳር ተጠብቆ ይቆይ ዘንድ አስተምህሮና ቀኖና፣ ውግዘት እና አፈ ታሪክ[10] ዋና ዋናዎቹ የማስፈጸሚ መሣሪያዎች

[10] "የቤተ ክርስቲያንን አጸድ ትጉሃን መላእክት፣ ዘንዶ እና ነብር ይጠብቁታል፡፡ ከዚያች አጸድ በድፍረት አንዲት የጥርስ ማሚጫ የቆረጠ ግለሰብ ከሦስቱ በአንዱ መቅሰፍት ይመታል፡፡ ገዳማት ከኾነ ነብሩ

ናቸው፡፡ በዚህም እንደ ጥምቀት ያሉ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎች አራዊትን ከአደን፣ ዛፍን ከምሣር በመከላከል የአካባቢውን ሥነ ምኅዳር ያስጠብቃሉ፡፡

**ክብረ በዓል ለቱሪዝም መስሕብነት ያለው ፋይዳ፡-** ክብረ በዓል ለቱሪዝም መስሕብነት ያገለግላል ሲባል ክብረ በዓል ባሉት ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዋዠራ[11] ምክንያት የማኅበረሰቡን ማንነት፣ ዕሴት፣ አኗኗር እና ፍልስፍና ማሳየት መቻሉ ነው፡፡ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች፣ ሀገረሰባዊ ቅርሶች እና ታሪኮች የሚታዩበት ነው፡፡ እንደ ጥምቀት ያሉ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ባላቸው የአከዋወን ባህላዊ ሥርዓት ምክንያት ከባለቤቶቹ ዐልፎ የእንግዳን ቀልብ የመሳብ ኀይል አላቸው፡፡ በዚህ ምከንያት የውጭ ታዳምሚች፣ እንገዶችና ቱሪስቶች ሀገር አቋርጠው፣ ባሕር ተሻግረው በመምጣት በዓሉን ይታደማሉ፡፡ በዚህ መልኩ ክብረ በዓል በቱሪዝም መስሕብነት፣ በምጣኔ ሀብት ዕድገት፣ በማኅበረሰባዊ ግንኙነት እና ሀገርን በማስተዋወቅ በኩል ከፍተኛ ሚና አለው (Bell 2009, 151)።

**ክብረ በዓል ለተግባቦት መፍጠሪያ ያለው ፋይዳ፡-** ከክብረ በዓል ክዋኔ ጠቀሜታዎች መካካል አንዱ በአክባሪዎቹ ዘንድ ተግባቦት መፍጠር ማስቻሉ ነው፡፡ ክብረ በዓል እጅግ ውስብስብ የኾኑ የባህልና የሃይማኖት ክዋኔዎችን በመግለጥ ዘርፈ ብዙ ተግባቦቶችን ይፈጥራል፡፡ ክብረ በዓል በሰዎችና ሰዎች፣ በማኅረሰብና ማኅበረሰብ፣ በሰው እና ተፍጥሮ መካከል መልካም የኾነ ተግባቦትን ይፈጥራል፡፡ እንደዚኹም የተደበቁ እና የታፈኑ ማኅበረሰባዊ ምስጢራት፣ ባህላዊ እና ትእምርታዊ ፍልስፍናዎች እንዲገለጡ እና ሥግው እንዲኾኑ ያደርጋል (Rappaport 1999, 50)፡፡

---

ይሰብረዋል፤ ዘንዶው ይውጠዋል፤ መላእክት ይቀላዋል፡፡ ሊጋብ ታደሰ የሚባሉ ሰው ነበሩ ባርቃይባ ጊዮርጊስ ታቦት ማደሪያ ገብተው ሲያሳሳቸው ስለት እሰጣለሁ ብለው ጊዮርጊስ በስለት ስለሚምር አንድ ሞፈር ቆርጠው መኼድ፣ ከዚያማ ከቤት ሳይደርሱ ሆዳቸው ተነፍቶ ቃተው፣ ቃስተው ሞፈሩ ተወስዶ ከታቦት ማደሪያው ለመፈራረጃ ተጥሎ እሳቸውም ባሳር ተረፉ፤ ይጠምዱት በሬ፣ ያዙት ገበሬ አተው በድሕነት ሲሰቃዩ ኑረው አረፉ ይባላል፡፡" (አቶ ሰጡ ዳርጌ 20012 ቃ.መ) የሚል ታሪክ ነግረውኛል፡፡

[11] ቃሉ በጎንደር አካባቢ ተዘውትሮ የሚነገር ሲኾን ትርጉሙም ዝንቅ፣ ድብልቅ፣ ቅይጥ እና ሽርም ማለት ነው፡፡ ስንዴና ገብስ፣ አተር እና ባቄላ በአንድ ላይ ተዛንቀው ሲዘሩ አዝመራው ስንዴ፣ ገብስ፣ አተር እና ባቄላ የሚለውን መጠሪያ ለቆ ዋሴራ ይባላል፡፡

### 2.1.1.2. የክብረ በዓል ባሕርያት

**የክብረ በዓል ባሕርያት፡-** ከክብረ በዓል በርካታ የብያኔ ማሕቀፎች መካከል የዘርፉ አጥኚዎች ባህርያቱ ላይ ተመሥርተው ከፍ ያሉ ብያኔዎችን የሰጡ ይመስላል፡፡[12] በብዙ አጥኚዎች ዘንድ የክብረ በዓል ሥርዐታዊነት፣ ትውፊታዊነት፣ ጸናንነት፣ በህግና ደንብ መመራት፣ ክዋኔ እና ትእምርት በሚሉት ላይ ትኩረት ሰጥተው ሲመለከቷቸው ይስተዋላል፡፡

**የክብረ በዓል ሥርዐታዊነት: -** ከክብረ በዓል ባሕርያት መካከል አንዱ ሥርዐታዊነት ነው፡፡ የክብረ በዓል ሥርዐታዊ መኾን የክብረ በዓሉን የክዋኔ ልዩነት እና አከባበር ኹኔታ ለመገምገም፣ ለማወቅና ለመረዳት ወሳኝነት እንዳለው Bell (2009: 139) እና Rappaport (1999: 46) ያስረዳሉ፡፡ የክብረ በዓል ሥርዐታዊነት የክብረ በዓሉን ክዋኔ መነሻና መድረሻ፣ በቅደም ተከተል ዕሴቱን ጠብቆ እንዲከወን ያደርጋል፡፡ በዘፈቀደ ይኹን በልምድ ማነስ የክብረ በዓል ክዋኔ ከተለመደው ሥርዐት ተዛንፎ ሲገኝ የተፈጸመውን ግድፈት ለመረዳትና ለመተቸት ያስችላል፡፡ በዚህም ክብረ በዓሉ ከሚያዘው ከሚያስተላልፈው እና ቀደምት ከተለመደው በምን ያክል ብዛት እና ቅናሽ ተከወነ? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ያስችላል፡፡

**የክብረ በዓል ትውፊታዊነት፡-** ክብረ በዓል ከሚታወቅባቸው ባሕርያቱ መካከል አንዱ ትውፊታዊ መኾኑ ነው፡፡ አንድ ክብረ በዓል በየወቅቱ ግለሰቦች ስለ ፈለጉ ብቻ የሚከወን ሳይኾን ረጅም ዘመናትን ተሻግሮ እያለፈ የመጣና የሚቀጥል ትውፊት ነው፡፡ Bell (2009, 145) "ሃይማታዊና ባህላዊ ክብረ በዓላት የቀደሙና በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ ዘመናትን የተሻገሩና የሚሻገሩም ናቸው" በማለት ስለ ክብረ በዓል ትውፊታዊነት አፅንኦት ይሰጣሉ፡፡

---

[12]በዋናነት የክብረ በዓል ባህርያት የሆኑትን ድግግሞሽ (redundancy (repetition)፣ ተለዋዋጭነት (varying degree) ፣ የማይለወጡ stereotypy (rigidity)፣ ስምምነት (condensation (fusion)፣ የመሳሰሉትን የክብረ በዓላት ባህርያት ማወቅና መረዳት ተገቢ እንደኾነ Mariza G.S Peirano (200: 11) ያስገነዝባሉ፡፡ እንደ Pascal Boyerና Pierre Lienard (2006) ገለጻ ደግሞ "in a varity of circumstances, humans produce rituals, intuitively recognizable by their stereotypy, rigidity, repetition, and apparent." በማለት የMariza G.S Peiranoን ሃሳብ ያጠናክራሉ፡፡ እንደዚሁም Rappaport (1999: 23-54) የተባሉ የዘርፉ አጥኚ የክብረ በዓል ባሕርያትን እንደ ተግባቦት መፍጠሪያ (Ritual as communication)፣ ጸናንነት (invariance)፣ ሥርዐታዊነት (formality)፣ ቀድሞ የታወቀ (encoding)፣ ክዋኔ (performance)፣ ተጨባጭ (physical efficacy)፣ እንደ ተግባቦት መፍጠሪያ (Ritual as communication)፣ የመንጸት መልእክት (canonical message)ና ትእምርት (symbols) በማለት በዘጠኝ ከፍለው ይመለከቷቸዋል፡፡ እንደዚሁም Bell (2009, 139-159) ደግሞ የክብረ በዓል ባኅርያትን ሥርዓታዊነት (Formalism)፣ ትውፊታዊነት (Traditionalism)፣ ጸናንነት(Invariance)፣ በሕግና ደንብ መመራት(Rule Governance)፣ ክዋኔ (Performance)፣ ትእምርት (Symbolic) በማለትበስድስት ከፍለው ይመለከቷቸዋል፡፡

አክለውም Candace S. Alcorta (2006, 5) እና Cather Bell (2009, 6) በጥንት ዘመናት ለቅዱሳን ነገሥታት ይደረግ የነበረውን ክብረ በዓል ጠቅሰው ለፎክሎር እና ለሥነ ጽሑፍ እንደ ምንጭ ኹኖ አገልግሏል በማለት ስለ ክብረ በዓል ትውፊታዊነት ማረጋገጫ ይሰጣሉ። የክብረ በዓል ቀደምትነት የዐለፈውን፣ የአኹኑንና የሚመጣውን ትውልድ በባህል፣ በታሪክና በፍልስፍና የሚያስተሳስሩ ከመኾናቸው በተጨማሪ መልስ ሰጪዎችም ናቸው። በተለይ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል እንደ ኬት መጣነት፣ ልደት፣ ሞት፣ ምኞት፣ ተስፋና ፍርሃት የመሳሰሉትን ሥነ ልቡናዊ ዕሳቤዎች በማንሳት መልስ ለመስጠት ጥረት ያደርጋል። ክብረ በዓል ባለው የረጅም ዘመን ዑደት እና ክዋኔ ውስጥ የጥንቱን ከአኹኑ እና የአኹኑን ደግሞ ከመጪው ጋራ የሚያያስተሳስሩ ሠናይና እኩይ ተብለው የተለዩ ታሪኮች ይተረኩበታል። በዚህ ምክንያት ክብረ በዓል የቀደመውን፣ የዛሬውን እና የነገውን ትውልድ የማቀራረብ፣ የማስተዋወቅ እና የማስተሳሰር ዐቅም አለው (Bell 2009: 143)::

ስለ ክብረ በዓል ቀደምትነት ሲነሣ የሚነገሩት ታሪኮች እንደ ወይን ጠጅ ዕድሜ ባስቆጠሩ ልክ ወደ አፈ ታሪክና ምልኪ ስለሚለወጡ ማኅበረሰቡ ለምን? እንዴት? በማን? መቼ? እና የት? የሚል ሙግት ከማንሣት ይልቅ አሜን ብሎ ይቀበላቸዋል። በዚህ ቅብብሎሽ ውስጥ የክብረ በዓሉ የቦታና የጊዜ ቅዱስነት ይኹን ተቀባይነት ይጨምራል።

**ጸናን:-** ከክብረ በዓል ባሕርያት መካከል አንዱ ሲኾን በተመራማሪዎቹ ዘንድ ኹለት ዐይነት አተያዮች ይስተዋሉበታል። ከእነዚህ መካከል የRappaport (1999, 37) አተያይ "የተለያዩ ተመራማሪዎች ክብረ በዓልን አይለወጥም በሚለው ባሕርይ መበየን አለበት የሚል ማጠንጠኛ ያነሣሉ። በዚያኛው ጎራ ደግሞ ክብረ በዓል አይለወጥም የሚለው ጉዳይ እንደ ዋና ባሕርይ ተደርጎ መወሰድ የለበትም የሚል መሞገቻ ያቀርባሉ" ካሉ በኋላ "ክብረ በዓል ይብዛም ይነስም የማይለወጥ ባህርይ አለው" በማለት የራሳቸውን የሙግቶች ማለዘቢያ ሐሳብ ይሠነዝራሉ::

በሌላ መልኩ የBell (2009, 150) ማጠንጠኛ ሐሳብ ደግሞ "ክብረ በዓል የክዋኔው ይዘት፣ ጭብጥ፣ የአካል እንቅስቃሴ በጥንቃቄና በዕውቀት ላይ ተመሥርቶ የሚከወን እንጂ ከዋኙ እንደፈለገ እየሞላና እየቀነሰ የሚከውነው አይደለም። በመኾኑም ክብረ በዓል ጸናን ነው የሚለው ጉዳይ እንደ ዋና ባሕርይ ተደርጎ መወሰድ አለበት" የሚል መከራኪሪያ ሐሳብ አላቸው።

ከዚህ ላይ ገዥ ሐሳብ የሚኾነው ክብረ በዓል ፍጹም ተለዋዋጭ አይደለም የሚል ድምዳሜ ከመያዝ ይልቅ የክብረ በዓል የተለዋዋጭነቱ መጠኑ አንስተኛ እና ምክንያታዊ ነው ብሎ መገንዘብ ተገቢ ይመስላል፡፡ የክብረ በዓል ቋሚነት የሚለካው ዋና የሚባሉትና ለክብረ በዓሉ መፈጠር ምክንያት የኾኑት ምሰሶ ቁም ነገሮች ቀጣይ እና ዘመን ተሻጋሪ ናቸው፡፡ በመኾኑም የክብረ በዓል ጸናንነት ከቦታ፣ ከዘመን፣ ከጊዜ እና ከኹነት ጋራ ይራመዳል በሚሉት መስፈርቶች መለካት አለበት፡፡ ለዚህ ማሳያ ይኾን ዘንድ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓልን ብንወስድ እንኳ፣ ሃይማታዊ ክብረ በዓል በአብዛኛው የክዋኔው ሥርዓት ዘመን ተሻጋሪ፣ ቋሚና ቀጣይ ሲኾን ወቅትና ትውልድንም የተቀበለ ነው፡፡ ከአንደበት የሚወጡት አሐዶች፣ በወካይና በትእምርት የሚገለጹት ዕሴቶች በጥንቃቄ በየዘመናቱ መከወናቸው የክብረ በዓል ሥርዓት ቋሚ እንዲኾን አስችሎታል፡፡ በዚህም የክብረ በዓል ሥርዐቶች ከዓመት ዓመት ከዘመን ዘመን በጥንቃቄ ስለሚስተላለፉ የቀድሞ ዕሴታቸውን ይጠብቃሉ፡፡በዚህ መልኩ የሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ዋና ዋና የመባያ ጉዳዮች፣ ትእምርቶች እና አስተምህሮዎች ጊዜና ቦታን ተሻጋሪዎች ናቸው (Bell, 2009, 150፤ Rappaport (1999, 37)፡፡

ይኹን እንጂ እንደ አሐዶች፣ አልባሳት እና ምግብ ያሉ የክብረ በዓል ክዋኔዎች ከትውልድ እና ዘመን ጋራ ወቅትን የዋጁ ተራማጆች እንጅ ቁሞ ቀሮች አይደሉም፡፡ በዚህ መልኩ ክብረ በዓል በጽናት እና በለውጥ መሠረት ላይ የቆመ ዐምድ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ለዚህ ጉዳይ የጥምቀት ክብረ በዓል መልካም ማረጋገጫ ነው፡፡ ከክርስቶስ መጠመቅ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ የውሐው መቀደስ፣ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ መባረክ እና መጠመቅ የማይለወጡ እና የጸኑ አምዶች ናቸው፡፡ እንደ አጨፋፈር፣ አለባበስ፣ አመጋገብ እና አጊያጊያጥ ያሉት ዘውጎች ደግሞ የዘመኑ ማኅበረሰብ ዕውቀት እና ፍልስፍና መገለጫዎች በመኾን ከጊዜ እና ከቦታ ጋራ ተራማጆች ናቸው፡፡

**በሕግና ደንብ መመራት: -** ክብረ በዓል በሕግና በሥርዐት መመራቱ ሌላው ተጠቃሽ ባሕርይው ነው፡፡ ክብረ በዓል የተፈጠረበት ሕግ እና ደንብ በሚያዘው ልክ በእንቅስቃሴም ኾነ በአንደበታዊ ንግግሮች፣ ጭፈራዎች እና ክዋኔዎች ላይ ገደብ ይጥላል፡፡ ለምሳሌ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል በባህሉ ውስጥ ሐራም ተብለው የተወገዙ ድርጊቶችን ይከላከላል፡፡ ክብረ በዓል በሕግና በሥርዓት በመመራቱ ምክንያት የክብረ በዓሉ ከዋኝ፣ የክብረ በዓሉ ተሳታፊዎች ይኹኑ ታዳሚዎች ለክብረ በዓሉ ሥርዓት እና ደንብ እንዲገዙ ያደርጋል፡፡

Bell, (2009, 152) ስለ ክብረ በዓል ሕግና ሥርዐት ሲያብራሩ "አንድ የቦክስ፣ ግጥሚያ የጨዋታው ሕግ በሚያዘው መልኩ መተግበር አለበት" ይላሉ፡፡ የጨዋታውን ሥርዐት እስከተጠበቀ ድረስ በቡጢው ለሚደርሰው የአካል ጉዳት ይኹን ሞት እንደ መሥዋዕት ይቆጠራል እንጂ በቡጢ መቺው ላይ ቅጣት አይጥልም፡፡ የክብረ በዓል ሕጎችም እንደ ቡጢው ጨዋታ ሃይማኖታዊና ባህላዊ የኾኑ ጠንካራ ሕጎች አሏቸው" በማለት የክብረ በዓልን በሕግ መመራት ያረጋግጣሉ፡፡

የክብረ በዓል ክዋኔ የሚመራበት ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ሕጎች መኖራቸው በሥርዐት እንዲከወን ከማድረጋቸው ባሻገር የክብረ በዓሉ መገለጫዎችም ናቸው፡፡ ለምሳሌ በጥምቀት እና ገና ክብረ በዓሎች ክዋኔ ውስጥ እንደ ፈረስ ጉግስ እና ግና[13]ን የመሳሰሉት አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ዝግጁነትን የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በጉግስ ጊዜ በዘንግ ተወግቶ ከፈረስ መውደቅን እና የአካል መጉደልን ሊያስከትል ይችላል፡፡ እንደዚኹም የጅራፍ ግርፊያና የእንቁር ልጊያ ጨዋታዎች የዐይን መጥፋትና የጥርስ መውለቅ ያስከትላሉ፡፡ እነዚህን ጨዋታዎች በሥርዐት ለማስኬድ በክብረ በዓሉ ውስጥ ጠንካራ የኾኑ ሕጎች ይቀመጣሉ፡፡ በሃይማኖታዊ ክብረ በዓሉ ውስጥ የደንብንና የሥርዐትን ጥፋቶች ለመቆጣጠር እና ባህላዊ ዕሴቶቻቸውን ለመጠበቅ እንደ ውግዘት፣ ማግለል፣ ቅጣት ይኹን ርግማን በሕግ አፍራሹ ላይ ስለሚጣሉ የሕግን ጥሰቶች ይቀንሳሉ (Bell 2009, 153)፡፡

**ክዋኔ: -** ከክብረ በዓል ባሕርያት መካከል አንዱና ዋነኛው ክዋኔ ነው፡፡ ያለ ክዋኔ ክብረ በዓል ሊቀጥልም ኾነ ሊኖር አይችልም (Rappaport 1999, 37 እና Bell 2009, 161)፡፡

ክዋኔ በክብረ በዓል ውስጥ እንደ ሕግና መመሪያ በመኾን ያገለግላል፡፡ በክዋኔ ውስጥ የክብረ በዓሉ ትእምርት እና የማኅበረሰቡ ተግባቦት ዋነኛ መልእክት ይገለጣል፡፡ የአንድ ክብረ በዓል ክዋኔ እንደ ክብረ በዓሉ ዐይነትና ኹኔታ ለዐዋቂዎች፣ ለሕፃናት፣ ለሴቶችና ለወንዶች ባህሉ እንደሚፈቅደው ልክ ክፍትና ዝግ፣ ፍቁድና ክልክል ሊኾን ይችላል፡፡ ክዋኔ በአንድ ክብረ በዓል ውስጥ የክብረ በዓሉን ህልውና መጠበቅ ብቻ ሳይኾን ክብረ በዓሉ ለምን? ለማን? በማን? እንዴትና መቼ እንደሚከውን ከማሳወቁ ባሻገር የክብረ በዓሉን ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ዕሴቶች ለመረዳት ያስችላል፡፡ የክብረ በዓል ክዋኔ በአብዛኛው የሚታይ፣

[13] በባህሉ ውስጥ እንቁር ልጊያ ወይም ግና ጨዋታ እንጅ ገና ጨዋታ አይባልም ለዚህ ነው "ግና" ብየ የወሰድኩት፡፡

የሚዳሠሥ፣ የሚሸተትና የሚቀመስ በመኾኑ ለስሜታችን ቅርብ፣ ለአእምሮአችን ቅቡል በመኾን የክብረ በዓሉን መልእክት እንድንረዳ ያስችላል (Bell 2009, 161)::

**ዐውድ፡-** ዓለማዊም ይኹኑ መንፈሳዊ ክብረ በዓሎች ክዋኔያቸው እና ተስተላልፏቸው በዐውድ አማካኝነት ነው፡፡ ዐውድ የክብረ በዓሉ ተሳታፊ ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ቤተኛዎች እና ወሰንተኞች የሚሳተፉበትን ጊዜና ቦታ፣ እንቅስቃሴን እና አጋጣሚን ኹሉ ያጠቃልላል፡፡ ክብረ በዓል ከጊዜ አኳያ በወርና በዓመት፣ በሰርክ እና በጽባሕ ተደጋግመው በሚመጡና በሚታወቁ ቀናት ይወከላል፡፡ ዐልፎ ዐልፎ ማኅበረሰቡ አደጋና ሥጋት ሲገጥመው በአጋጣሚና በድንገት፣ ባልተጠበቀ እና ባልታሰበ ጊዜ ክብረ በዓል ሊያደርግ ይችላል፡፡ ክብረ በዓል ከቦታ አንጻር ደግሞ በወንዝ ዳር፣ በተራራ ጫፍ፣ በቤተ ክርስቲያን ዐጸድ፣ በታቦት ማደሪያ ስፍራ፣ በዛፍ ሥርና በመሳሰሉት ግርማ መፍርህ ባላቸው ስፍራዎች ይከበራል፡፡ ሁልጊዜም ቢኾን የክብረ በዓል ጊዜና ቦታ ከዘወትሩ ጊዜና ቦታ በተለየ መልኩ የክብርና ሞገስ፣ የቅድስናና ልዕልና ባለቤት ነው (Sims እና Stephen 2005,105)::

የክብረ በዓል ዐውድ ከቦታና ከጊዜ ባለፈ አጠቃላይ የክዋኔውን ድባብ የሚጨምር በመኾኑ እንደ ሥነ ቃሎች፣ ልማዶች እና ትውን ጥበባት የመሳሰሉትን ኹሉ ያጠቃልላል፡፡ በዚህም የክብረ በዓል ዐውድ የማኅበረሰቡን ዕሴት፣ ባህል፣ ሃይማኖት፣ አስተሳሰብ እና ፍላጎት የመግለጽ ዐቅም አለው (Bell, 2009, 191-194)::

**ክብረ በዓል እንደ ተግባቦት መፍጠሪያ: -** ከክብረ በዓል ባሕርያት መካከል አንዱ በቡድኖች መካከል ተግባቦትን መፍጠር ነው፡፡ የሰው ልጆች በዙሪያቸው ካሉ ከሚያውቋቸው እና ከሚረዷቸው ነገሮች ይልቅ እንግዳና ባይታወር የሚኾኑባቸው ጉዳዮች ይበዛሉ፡፡ ሰዎች ስለ ዛሬው እንጂ ስለ ነገው ሊያውቁና ሊረዱ አይችሉም፡፡ ስለ ጊዜና ቦታ፣ ስለ ዛሬ እና ነገ ያላቸው ዕውቀት ውስን በመኾኑ ሰዎች ኹል ጊዜ ከጊዜ እና ከቦታ፣ ከዛሬ እና ከነገ በታች ናቸው፡፡ ይህን የሰዎች የዕውቀት ውስንነት በመሙላትና ተግባቦትን በመፍጠር ክብረ በዓል ትልቅ ሚና አለው፡፡ በዚህ ምክንያት ሰዎች በክብረ በዓል አማካኝነት ስለ አካባቢያቸው፣ ስለ ማንነታቸው፣ ስለ ማኅበራቸው፣ ስለ ተፈጥሮና በዙሪያቸው ስላሉ ክሥተቶች እውናዊና ምናባዊ ተግባቦትን ያገኛሉ፡፡ ስለ ክብረ በዓል ተግባቦት መፍጠሪያ Rappaport (1999, 50) የተባለ ምሁር ተከታዩን ሐሳብ ሰንዝረዋል፡፡

*ክብረ በዓል የተግባቦት መፍጠሪያ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ አንዳንዶቹ በጊዜና በቦታ የተለዩና የታወቁ ሲኾን አንዳንዶቹ ደግሞ ከዕለት ተዕለት ሕይወት ጋራ የሚከበሩ ናቸው። አንዳንዶቹ የክበረ በዓል ዓይነቶች ደግሞ ቅርጽና ትእምርት ያላቸው ሲኾን እንደ ዕጣ ፈንታ ያሉ ክብረ በዓላት የመልካም ዕድል የልምላሜና የደስታ ስሜት ስለሚኖራቸው የእነዚህን ዓላማና መዋቅር መውሰድ ክብረ በዓሉን ግልጽ ያደረገዋል[14] (ትርጉም የግል)* በማለት ስለ ክብረ በዓል ተግባቦት ያስረዳሉ።

**ትእምርት: -** እንደ Bell (2009, 42) ገለጻ "ትእምርታዊነት የክብረ በዓል አንዱ ባሕርይ ሲኾን በሰዎች አእምሮ ውስጥ ሠርጾ በመግባት ተግባቦት መፍጠሪያ መንገድ በመኾን ያገለግላል" ይላሉ። የክብረ በዓል ትእምርት በአንደበት የሚነገሩትን፣ በድርጊት የሚከወኑትን እና በቁስ የሚወከሉትን ይመለከታል። በክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ የክብረ በዓሉ ዐውድ፣ የክብረ በዓሉ አልባሳት፣ የክብረ በዓሉ አመጋገብ እና የክብረ በዓሉ አጊያጊያጥ የየራሳቸው ፎክሎራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ሥነ ልቦናዊ ውክልና አላቸው። ይህም የክብረ በዓል ክዋኔ መለኪያ አንዱ ትእምርታዊነት ያለው መኾኑን ያሳያል። ትእምርት በክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ የውክልናዎቹን አንድምታ፣ የረቀቁ እና የራቁ ዕሳቤዎችን ሥግው በማድረግ ለክብረ በዓሉ ባለቤቶች ተግባቦትን ይፈጥራል።

### 2.1.1.3. የክብረ በዓል ዘውጎች

ክብረ በዓል የተለያዩ የመከወኛ ዘውጎችን ያቀፈ ነው። እነዚህ የክብረ በዓል ዘውጎች ባላቸው የማኅበረሰብ ፋይዳ፣ የሃይማኖት አስተምህሮ፣ የዕውቀት ፍልስፍና፣ የባህል፣ የልማድ፣ የአሐዶች፣ የዐውድ፣ የጊዜ እና የቦታ ቅድስና ተመሳስሎ የሚታባቸው በመኾኑ ድንበር ለማበጀት እና አንዳቸውን ከሌላቸው ለመለየት የሚያስቸግርበት ኹኔታ አለ። ይሁን እንጂ ባላቸው የክዋኔ ሰበብ እና መጠነኛ ልዩነቶች ምክንያት እንደሚከተለው ይዳሠሣሉ።

**የሕይወት ዑደት ክብረ በዓል (Riteof passage)[15]:-** ይህ የክብረ በዓል ዐይነት ሰዎች የሚያልፉባቸውን የሕይወት ዑደቶች ተከትሎ የሚከበር ነው። የሕይወት ዑደት ክብረ በዓል

[14] *"ritual to be a mode of communication some of its strangest features the separation in time and space of some rituals from daily life, the grotesque quality of some ritual postures and gestures, the weirdness of some ritual utterances, the exuberant elaboration of some objects and structures used in rituals become clear"* (Rappaport 1999, 50).

[15] Rite of passage *ለሚለው ቃል የሕይወት ዑደት ከማለት ይልቅ የሕይወት መሥመር (ዕጣ) የሚለው ትርጉም የሚሻል ይመስለኛል። ምክንያቱም ዑደት እንደገና መመለስን፣ መገኘትን፣ ይጠቁማል። ጉዳዩ ደግሞ*

በዋናነት በልደት፣ በጋብቻና በሞት የሚከወኑትን ክብረ በዓሎች ይመለከታል። በወሊድ ጊዜ፣ በአዋላጆች እና በጎረቤቶች የሚደረገውን ምርቃት፣ የገንፎ ዝግጅት፣ በሽልም ያውጣሽ፣ እልልታ እና በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ አማኞች ዘንድ የእምየ ማርያም ተራዳኢነት የሚዘከርበት በዓል ነው። ኹለተኛው የጋብቻ ክብረ በዓል ነው። ይህ በዓል ሴት ለዐቅመ ሔዋን ወንድ ደግሞ ለዐቅመ አዳም ሲደርስ በጋብቻ የሚተሳሰሩበትን ሥርዐት የሚመለከት ነው። ሌላው ተጠቃሽ የሞት ሥርዐት ነው። ሰው በዚህ ዓለም ከቆየ በኋላ በሞት ወደ ሌላኛው ዓለም ከማኅበረ ሕያዋን ወደ ማኅበረ ሙታን የሚቀላቀልበት መንገድ ነው። የሕይወት ዑደት ክብረ በዓል ከሌሎቹ ክብረ በዓሎች የሚለይበት ዋናው ምክንያት አንድ ሰው ከአንድ የሕይወት ምዕራፍ ወደ ሌላ የሕይወት ምዕራፍ ላይመለስ የሚያደርጋቸውን ሽግግሮች ይኹን ጉዞዎች የሚመለከት መኾኑ ነው።

ልደትን ብንወስድ አንድ ሕፃን ካለመኖር ወደ መኖር ካለ መቆጠር ወደ መቈጠር እና ወደ ማኅበረሰቡ አባልነት የሚቀላቀልበት ምዕራፍ ነው። ይህ ጉዞ ይመጡበት እንጂ ይመለሱበት መንገድ የለውም። ጋብቻ ሙሽራውን ወደ አባትነት ሙሽሪትን ደግሞ ወደ እናትነት የሚሸጋገሩበት ምዕራፍ እንጂ እንደገና ወደ ልጅነት እና አፈር ፈጪነት ለመመለስ የሚያስችል ዕድል የለውም። የሞትን ሽግግር ብንመለከት ሰው ከሞተ በኋላ በምናውቀው ሥጋ ለብሶ ግዘፍ ነሥቶ ልናየው አንችልም። በመኾኑም የሕይወት ዑደት በዓል ላይመለሱበት የሚሻገሩት የሰው ልጆችን ዕጣ ፈንታ የሚመለከት ነው። ይህን ሐሳብ አስመልክቶ *Bell (2009, 94)* እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> *የሕይወት ዑደት ክብረ በዓል ቢጋራ እና በተውኔት መልክ የሚከበር ነው። እንደ ልደት፣ የወንዶችን እና የልጃ ገረዶችን የዕድሜ መጨመር ተከትሎ የሚመጣን ጋብቻ እና ሞት የሚመለከቱ ጉዳዮችን የያዘ ነው። አንዳንዴም "የሕይወት ውድቀት" ወይም "የሕይወት ዑደት" ተብሎ ይጠራል። የሕይወት ዑደት በባህል የተገራ ሲኾን ግለሰቦች ከአንድ ማኅበረሳበዊ የሕይት ደረጃ ወደ ሌላው የሕይወት ደረጃ ሽግግር የሚያደርጉበት በዓል ነው" (ትርጉም የግል) በማለት አጽንኦት ይሰጣሉ።*[16]

---

ላይመለሱበት የሚሻገሩት ዕጣ ፈንታ ስለኾነ የሕይወት መሥመር (ዕጣ) የሚለው ይሻል ይኾን ባይ ነኝ። ለዚህ ጥናት ግን የተለመደውን የሕይወት ዑደት የሚለውን ወስጀዋለሁ።

[16] *Rites of passage are ceremonies that accompany and dramatize such major events as birth, coming of age initiations for boys and girls, marriage, and death. Sometimes called "life crisis" or "life-cycle" rites, they culturally mark a person's transition from one stage of social life to another".*

**ዓመታዊ፣ የዘመን መለወጫ እና የመታሰቢያ ክብረ በዓል፦** ይህ ክብረ በዓል ማኅበራዊ እና ዐውዳዊ ሲኾን የብሥራት ባሕርይ አለው፤ ዓመታዊ ክብረ በዓል በታወቀ ቦታ እና ጊዜ እየተመላለሰ ስለሚከበር እንደ ዐዲስ ሕይወትን በማስጀመር ለማኅበረሰቡ ትልቅ የኾነ ሥጋዊና መንፈሳዊ ርካታ ያስገኛል፤ ዓመታዊ ክብረ በዓል በሃይማኖታዊና ሥጋዊ ይዘቱ ምክንያት ለአክባሪዎቹ አንዳች በረከትን እና ተስፋን ያስገኛል ተብሎ ይታመናል (Bell 2009, 102-105):: ስለኾነም ዓመታዊ ክብረ በዓል ማኅበራዊ አንድነትን እና ሰዋዊ ዝምድናን በሰዎች ዘንድ ያሥርጻል። የበጋ፣ የበልግ፣ የክረምትንና የጸደይን ወራት በማስታወስ ሰዎች በዐዲስ መልክ ለሥራ እንዲነቃቁ ያደርጋል፤ በተጨማሪም ስለ ክብረ በዓሉ ጊዜና ቦታ ቅዱስነት በማስረዳት ሰዎች አካባቢያቸውን እንዲጠብቁና ለተፈጥሮ ያላቸው ግምት ከፍ እንዲል ያስችላል (Bell 2009, 105)::[17]

ዓመታዊ ክብረ በዓል ቁሳዊ ዕሳቤ ይኑረው እንጂ እንደመነሻ የሚያደርገው በአብዛኛው ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ላይ ነው። በክርስትና ሃይማኖት ዘንድ በዋናነት ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ሲል መወለዱን፣ የከፈለውን መከራና ራሱ መሥዋዕት ኾኖ የቀረበበትን፣ ሞትን ድል ነሥቶ የተነሣበትን፣ በክብር ወደ ሰማይ የዐረገበትን እና ምስጢረ መለኮቱን የገለጠበትን ዕለት በማስታወስ በየዓመቱ የሚከበሩትን ክብረ በዓሎች የሚመለከት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሰው ልጆች ከግእዞት ነጻ ይወጡ ዘንድ በዱር በገደል ዳዋ ለሚጥሱ፣ ድንጋይ ለሚንተራሱ ቅዱሳን እና በሰይፍ ለሚቀሉ፣ በመጋዝ ለሚሰነጠቁ ሰማዕታት የሚደረግ ክብረ በዓል ነው። ይህ ክብረ በዓል ሰማዕታቱ እና ቅዱሳኑ የተወለዱባቸውን እና ያረፉባቸውን ቀናት ምክንያት በማድረግ በየዓመቱ ይዘከራል። ዓመታዊ ክብረ በዓሎች በሰው ልጆች ዘንድ መግባባትን፣ ከአካባቢና ከተፈጥሮ ጋራ መስማማትን በመፍጠር እንደ ዐዲስ እየተከበሩ እና እየተዘከሩ ይቀጥላሉ። ይህን ሐሳብ አስመልክቶ Bell (2009: 105) ተከታዩን ማብራሪያ ሰጥተዋል።

> *ዓመታዊ እና የዘመን መለወጫ በዓል የማኅበረሰባዊ ትርጉም ብያኔ ያለው የጊዜን ዑደት የሚመለከት ነው። ዑደቱም የቀን፣ የወር እና የዓመት መታደስን የሚፈጥር ነው። ኹሉም*

---

[17] *ይህን ሃሳብ በተመለከተ Bell (2009, 105) እንደሚከተለው ያስረዳሉ። "calendrical rites give socially meaningful definitions to the passage of time, creating an ever-renewing cycle of days, months, and years. Both types of rites make time appear to be an ordered series of reternal rebeginnings and repetitions. Calendrical rites occur periodically and predictably, accompanying seasonal changes in light, weather, agricultural work, and other social activities"*

*ዑደቶች የዘመን መጥባትን የሚመለከቱ ሲኾን ሥርዐታዊ በኾነ መልኩ እንደገና መመመለስን፣ መጀመርን እና መደገምን ያበሥራሉ። የዘመን አቆጣጠር ዑደት ክብረ በዓሎች በተቆረጠ እና በታወቀ ጊዜ የመከበር ጥብቅ የኾነ የጊዜ ሥርዐት አላቸው። የዓመታዊ (ዘመን መለወጫ) ክብረ በዓሎች የብርሃን፣ የአየር ንብረት፣ የግብርና ሥራን እና ሌሎችም የማኅበረሰባዊ ተግባራት በዐዲስ መልክ የሚጀመሩበት ነው" በማለት ያትታሉ (ትርጉም የእኔ)።*[18]

**የስእለት ሰሚነት ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል: -** ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል የእምነቱ ተከታዮች ምእመናን በአንድ ላይ በመኾን በአፍኣ ወይም በውስጥ የሚያከብሩት የክብረ በዓል ዐይነት ነው። ይህ ክብረ በዓል በአብዛኛው ሃይማኖታዊ ይዘት ያለው ነው። የስእለት ክብረ በዓል ምድራዊ በረከትን፣ ረጅም ዕድሜን፣ ጤናና ሀብትን፣ ዐሽቶ መቃምን እና ወልዶ መሳምን ያድል ዘንድ እየተደጋገመ በየዓመቱ ይከበራል። ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ከመንፈሳዊ በረከት አኳያ ሲታይ መንግሥተ ሰማያትን ለመውረስ፣ ከደይንና ከኵነኔ፣ ከግዞት እና ከውግዘት ለመዳን የሚከበር የበዓል ዐይነት ነው። አማንያን እንደየ እምነታቸው ጽናት እና እንደየ ልቡናቸው ትጋት መጠን ቁሳዊና መንፈሳዊ በረከትን ለማግኘት ሲሉ ያከብሩታል። የስእለት ሰሚነት ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎች ፍጹም የኾነ ርኅራኄን፣ መተሳሰብን፣ መስመማትን እና በማኅብረሰቡ ዘንድ ጥሩ ግንኙነት መፍጠርን ያስችላሉ (Bell 2009, 112)። የስእለት ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ሃይማታዊ ይዘቱ ከፍ ማለቱ እና በብሔራዊ ደረጃ አለመከበሩ እንጂ ከዓመታዊ፣ ብሔራዊና የመታሰቢያ ክብረ በዓል ጋራ የጠበቀ ቁርኝት አለው።

**የድግስ እና የአጽዋማት ክብረ በዓል: -** ይህ የክብረ በዓል ዐይነት በርካታ ሕዝቦችና ማኅበረሰቦች የሚሳተፉበት ነው። ክብረ በዓሉ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ይዘት ያለው ሲኾን በጾም እና በድግስ ይከበራል። በመኾኑም ክብረ በዓሉ በአንድ በኩል ጾም፣ በሌላኛው በኩል ድግስ የሚሉትን ኹለት ዘርፎች የያዘ ነው። በጾም ወራት እንደ ሃይማኖቱ ቀኖና የሃይማኖት አባቶች፣ ወንዶች፣ ሴቶች፣ ሕፃናትና አዛውንቶች በአንድ ላይ በእምነት ተቋማት ይኹን በዓሉ በሚከወንበት ቅዱስ ቦታ በመገኘት ያከብሩታል። በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዘንድ ስቅለት፣ ሰሙነ ሕማማት እና ጾመ ፍልሰታ ከአጽዋማት በዓላት መካከል የሚመደቡ ናቸው። በእስልምና ሃይማኖት ዘንድም የረመዳን ጾም የሚጠቀስ ነው። በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ የጾም

[18]ይህን አስመልክቶ *Bell (2009: 105) "The traditional Christian calendar is particularly elaborate in its annual chronicle of the birth, suffering, death, and resurrection of Jesus Christ. Additional saints' days and other holy days have traditionally created an ongoing round of rites in which the rhythms of the year are formed by religious devotions and responsibilities"*

ወቅት ጭብጥ ሽምብራ፣ ዕፍኝ ውሐ እየቀመሱ በሱባዔ እና በአርምሞ የሚከበር ነው፡፡ በዚህ ገጽታው በዓሉ ረኀብና ጽም፣ ርዛትና ግርፋት፣ መለየት እና ጽናት የሚታይበት በመኾኑ ከሥጋዊ ይልቅ የነፍስ ፍላጎት ግዘፍ ይነሣል፡፡

በሌላ መልኩ በዓሉ ድግስ በመደገስ በመብላት፣ በመጠጣት፣ በመጨፈርና በመደሰት በፈንጠዝያ የሚከበር የበዓል ዐይነት ነው፡፡ በዚህም የበዓሉ ድባብ በደመቀ መልኩ ድግስና ዳንስ፣ መብልና መጠጥን፣ ሐሤትና ደስታ፣ ፈንጠዝያ እና እልልታ ይታይበታል፡፡ በዚህ ጊዜ በዓሉ ለሥጋዊ ደስታ እና ፈቃድ ተገዥ ይኾናል፡፡ ይህ የድግስ በዓል በብዙ ሀገራት ዘንድ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ከእነዚህ ሀገራት መካከል በዐዲሲቷ ጉይኒያ የዐሣማ ድግስ የሚጠቀስ ሲኾን በአውሮፓ እና በአሜሪካም በሰፊው የተለመደ ክብረ በዓል ዐይነት ነው (Bell 2009, 120)፡፡ በመኾኑም  የድግስና የአጽዋማት ክብረ በዓሎች አንድም ደስታ፣ አንድም ሱባዔ የተላበሱ ባለ ኹለት ገጽታዎች ናቸው፡፡

**የፖለቲካ በዓል፡ -** ይህ የበዓል ዐይነት ከፖለቲካ  ልሂቃን እና መሪዎች ጋራ ተያይዞ የሚከበር ነው፡፡ የፖለቲካ በዓል በክብረ በዓሉ ወቅት ሥለ ነገሥታቱ፣ ልዑላኑ እና መንግሥታቱ የሚደረጉ ተአምራዊ፣ አፈ-ታሪካዊና ምልኪያዊ ትረካዎች ይበዙበታል፡፡ እነዚህ ትረካዎች ባለሥልጣኑ በሕዝቦች ዘንድ መፈራትንና አብዝቶ መከበርን ስለሚፈጥር ሥልጣነ ሲመቱ እንዲረዝም እና ሕዝቡ አሜን ብሎ እንዲገዛ የማድረግ ዐቅም አላቸው፡፡ ከእነዚህ አፈ ታሪካዊና ምልኪያዊ ዕሳቤዎች መካከል በሀገራችን የነበረው የንጉሡ ሲመትና ቅብዐ መንግሥት ከአምላክ የተሰጠ እንደኾነ የሚያዘክሩ ነበሩ፡፡ ከእነዚህ መካካል "ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ" የሚለው ምልኪ ተጠቃሽ ነው፡፡ በአጠቃላይ የፖለቲካ ክብረ በዓል ዓላማው፣ መነሻና መድረሻው የነገሥታቱን ሥልጣነ ሲመት ለመጠበቅ እና ዘመናትን ለማሻገር የሚከበር የበዓል ዐይነት ነው (Bell 2009, 129)፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የጥምቀት ክብረ በዓል የክርስቶስን ጥምቀት ለመዘከር በየ ዓመቱ የሚከበር በመኾኑ ከዓመታዊ እና መታሰቢያ ክብረ በዓል ጋራ ተመሳስሎ ይታይበታል፡፡ ለጥምቀት ክብረ በዓል ስእለት በመሳል እና ስእለቱ በደረሰላቸው ልክ ወጣቶች፣ አዛውንቶች፣ እናቶች እና እኅቶች "ለጥምቀት ያልኾነ ቀሚስ፣ ለጥምቀት ያልሆነ አንገት" እያሉ እያሸበሸቡ እና እያደገደጉ ያከብሩታል፡፡ በዚህ መልኩ ሲታይ የጥምቀት ክብረ በዓል ከስእለት ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ጋራም ጥብቅ ቁርኝት አለው፡፡ ሌላው የጥምቀት ክብረ በዓል ረቡዕ

እና ዓርብ ላይ ቢውል እንኳን ገሃድ በሚባለው የጾም ሥርዐት ተተክቶ ዕለቱ ፍስክ ኾኖ ይውላል። በዚህ መልኩ ከድግስ ክብረ በዓል ጋራም የሚመሳሰልበት ኹኔታ አለ። በመኾኑም ጥናቱ ከዓመታዊ እና የመታሰቢያ ክብረ በዓላት፣ ከስእለት ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት እና ከድግስ ክብረ በዓላት ጋራ ጥብቅ ቁርኝት አለው።

### 2.1.2. ሃይማኖት

ስለ ሃይማኖት ሲነሳ በዘርፉ ሰፋ ያለ ጥናት ያደረጉት ተመራማሪዎች ሃይማኖትን ከመጡበት ድሲፕሊን አኳያ ሲመለከቱት ይስተዋላል። jaco (2010, 2)። Durkheim የተባሉ ተመራማሪ ክብረ በዓልን በዐዩበት የsociological approach መነጽር ሃይማኖትንም ይመለከቱታል። Durkheim ከሚታወቁበት የሥነ ማኅበረሰብ ዕይታቸው በመነሣት ሃይማኖት በአማኞች ዘንድ ጥብቅ የኾነ ማኅበረሰባዊ መዋቅር እና ትስስር መፍጠሪያም፣ መቀደሻም ነው ይሉታል። አክለውም Durkheim ከማኅበረሰባዊ ምልከታቸው በመታገግ እግዚአብሔር ማኅበረሰብ ነው (God[19] is society) በማለት ይህንኑ ማሕበረሰባዊ ዕይታቸውን ያጠናክራሉ (Bell 24-25, 2009)። ሌላው የDurkheimን ሃሳብ ደግፈው ከቆሙ የዘርፉ ተመራማሪዎች መካከል Radcliffe Brown የሚጠቀሱ ተመራማሪ ናቸው። እኒህ ምሁር "ሃይማኖት ማኅበራዊ ማሽን ነው። ማሽኑም የሰው ልጆች በአንድነት ተስማምተው ይኖሩ ዘንድ የማኅበረሰብ ግንኙነትን አደላዳይ ነው" በማለት የDurkheimን ሃሳብ ይደግፋሉ (Bell 27, 2009)።

ይኹን እንጂ የእነ Durkheimን ምልከታ ተችተው የተነሡ ተማራማሪዎችም አልጠፉም። ከእነዚህ መካከል Malinowski ማኅበረሰባዊ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥነውን የነDurkheimን እና የነRadcliffe- Brownንን የሃይማኖት ጽንሰ ሐሳብ ተችተው የተነሡ ተመራማሪ ናቸው። Malinowski ሃይማኖት ላይ ያላቸው ዕይታ ከሥነ ልቡና ዕሳቤ የሚቀዳ ነው። በዚህም ዕይታቸው ሃይማኖትን ከማኅበረሰባዊ ትስስሩ ይልቅ ሥነ ልቡናዊ፣ አእምሯዊ እና ግላዊ ጽናቱ ይጠነክራል ይላሉ። ለዚህ ማረጋገጫ ይኾን ዘንድ የሞትን እጣ ፈንታን እና አስፈሪነት ከግለሰባዊነት[20] ጋራ አያይዘው ባስረጂነት ይጠቅሳሉ። Malinowski ሃይማኖትን ሲያደማድሙ የሃይማኖት ማኅበረሰባዊ አስተሳሰስብ ኺደት እና በሰዎች ግንኙነት ዘንድም

[19] እንደየ ሃይማኖቱ ብዙ መጠሪያዎች ያሉት በመሆኑ ይህን ማለቱ ነው።

[20] "ሃይማኖት የግል ነው ሀገር የጋራ ነው የሚለው የሀገራችን ብሂል ከMalinowski ዕይታ ጋራ ይፈካከራል።

ቢኾን ልዝብ ነው በማለት የነDurkheimን የማይፈታ ማኅበረሰባዊ ቋጠሮ ውል ነው የሚለውን ዕሳቤ ይሞግታሉ፡፡

ስለ ሃይማኖት የሚነሣው ሌላው ጽንሰ ሐሳብ የዕውቀት ምንነቱ ላይ የሚመሠረት ነው፡፡ እነ Durkheim ሃይማኖት ጥበብም፣ ሳይንስም (art and science) ነው የሚል አቋም አላቸው፡፡ ይህ ጽንሰ ሐሳብ እስከ ብዙ ጊዜ ሃይማኖት ዕውቀትን ወይም ሳይንስን ገፊ ተደርጎ ይወሰድ ነበር ከሚለው እና ሃይማኖት በጥበብ እና በሳይንስ መለኪያ ሳይሆን በራሱ የሚለካ ነው የሚለውን ዕሳቤ የሞገተ ነው፡፡ ይህን የቆየ ዕሳቤ በመተቸት የነDurkheim ጥናት ሃይማኖት አንድም ሳይንስ አንድም ጥበብ ነው የሚል ማረጋገጫ አለው፡፡ Durkheim ሃይማኖትን የሚታወቅ እና የማይታወቅ[21] እንቅስቃሴ ውጤት ነው በሚሉ ኹለት ገጽታዎች ይከፍሉታል፡፡ የሰው ልጆችን የዕለት ከዕለት ኑሮ ከሚታወቀው ሃይማኖታዊ ዕውቀት ሥር ይፈርጁታል፡፡ ተፈጥሮአዊ አደጋዎችን እና የሞት እጣ ፈንታዎችን ደግሞ ሰዎች ለማወቅ ከማይችሏቸው ተርታ ይጠቅሷቸዋል፡፡ ከዚህ በመነሣት Durkheim ስለ ሃይማኖት የሚታወቅ እና የማይታወቅ፣ የቅድስና እና የሥጋ፣ የማኅበራዊ እና የግለሰባዊ የሚል ፈርጀ ብዙ የኾነ ጽንሰ ሐሳብ አላቸው (Rappaport 1999 16- 20)፡፡

Green, (1997, 710) በበኩላቸው ሃይማኖት የሰው ልጆች በሕይወት ዘመናቸው የሚያምኑት፣ የሚተገብሩትና የሚቀበሉት ነው በማለት ከDurkheim የዕለት ከዕለት ሕይወት ጋራ አያይዘው ይመለከቱታል፡፡ ይህ የሚያሳየው ሃይማኖትን የተለያዩ አጥኚዎች እንደየመጡበት ዲስፕሊን እና አረዳድ የሚመለከቱት መኾኑን የሚያጸና ነው፡፡[22]

አክለውም Turner (1991, 4) የሃይማኖት መገለጫዎች እምነትና ክዋኔ መኾናቸውን ከገለጹ በኋላ ሃይማኖት ሰዎችን ያቀራርባል፣ ማኅበራዊ መዋቅርን ያጠናክራል በሚል ከማኅበረሰባዊ ዐይን አኳያ ይፈርጁታል፡፡ ከሥነ ልቡናዊ ጠቀሜታው ስንነሣ ሃይማኖት ስለ ሰው ልጆች በእጅ ከሚዳሠሠው በዐይን ከሚታየው ባለፈ ስለ ኬት መጣነት፣ ስለ ተፈጥሮና ማኅበረሰብ ቁርኝት ለበርካታ ጥያቄዎች ሃይማኖታዊ ምላሽ ይሰጣል የሚለውን ቁልፍ የሥነ ልቡና

---

[21] divided into the known and the unknown (Rappaport 1999 16- 20))

[22]እንደVan den Heever, (2001: 4) አገላለጽ ከሆነ ሃይማኖት ማኅበራዊ ስራት ነው፡፡ (Turaki, 1999: 70) ሃይማኖት ትርጉም ያለው እውነትን መፈለጊያ መሳሪያ ነው እንደዚሁም እንደ (Van den Heever (2001: 4) ሃይማኖት የሰዎች የእውነት ውክልና ነው፡፡ Geertz, in Turaki, (1999: 89) ደግሞ ሃይማኖት የባህል ቅምር ነው፡፡ እንደዚሁም jaco, (*2010, 2)* የሌሎችን ስራ በመገምገም "ሃይማኖትን ተመራማሪዎቹ እንደየ ራሳቸው አረዳድና የዕውቀት ዘርፍ የሚበይኑበት ሁኔታ ይስታዋላል"የሚል ሐሳብ ይሰነዝራሉ፡፡ Durkheim in Bell (2009, 28) `ሃይማኖት ጠቅላላ ማኅበራዊ ክስተት ነው” የሚል አቋም አላቸው፡፡

መልስ ያስገኛል። ይህን ሐሳብ በተመለከተ በዘርፉ ጥልቅ ጥናት ያደረጉት እና ሃይማኖትን ከሥነ ልቡና ዐቅጣጫ የሚመለከቱት Robertson Smith ሃይማኖት ስለ ተፈጥሮ ትርጉም ፍች የሚሰጥ ሲኾን ፍቅርን፣ ደግነትን፣ ለሰው ልጅ ራስን አሳልፎ መስጠትን፣ አርዓያ መኾንን በማስረጽ የተረጋጋ ዓለም ለመፍጠር አስቻይ ነው Robertson Smith in Bell (2009, 21) በማለት ያስረዳሉ።

በተጨማሪም Candace S. Alcorta, (2006, 8) "ሃይማኖት የልዕለ ተፈጥሮ መገናኛ ወኪል በመኾን፣ የሰዎችን ኬት መጣነትና የሰዎችን የቀን ተቀን እንቆቅልሾች በመፍታት ለሰዎች አእምሮ ዕረፍት የሚሰጥ ነው" በማለት የሃይማኖትን እንቆቅልሽ ፈቺነት ያስረዳሉ። Cather Bell, (2009, 24) በበኩላቸው "ሃይማኖት ማኅበራዊ ጉዳይን መሠረት ያደረገ ሲኾን ይህ ማኅበራዊ ጉዳይም ማኅበረሰባዊ እውነታ (social fuct) ነው" በማለት የAlcortaን ሐሳብ ያጠናክራሉ።

ከላይ በምሁራኑ ዘንድ ተደጋግመው የተነሡ የሃይማኖት ጽንሰ ሐሳቦች ሲጨመቁ ማኅበረሳባዊ እና ሥነ ልቡናዊ በሚሉ ኹለት ጎራዎች ነጥረው የሚወጡ ናቸው። እነዚህ ዕሳቤዎች ሃይማኖት በምእመኑ ዘንድ ያለውን ማኅበራዊ እና ሥነ ልቡናዊ ጠቀሜታ አስረጅዎች ናቸው። ሌላው የብያኔዎቹ ማእከላዊ ጭብጥ ሃይማኖት እንደ ነገረ ተፈጥሮ ያሉ ሩቅ እና ረቂቅ ጥያቄዎችን በመመለስ የሰዎችን ውስብስብ ጥያቄዎች በመፍታት ኹነኛ መሣሪያ መኾኑን የሚያጸኑ ናቸው።

ሰው በተሰጠው የጠያቂነት ተፈጥሯዊ ባሕርይ ምክንያት ብዙ ያልፈታቸውና ያልደረሰባቸው እንቆቅልሾች አሉት። ከእንቆቅልሾቹ መካከል ሰው ስለ አካባቢው፣ ስለ ዓለማት፣ ስለ ዓለም ፈጣሪ፣ ስለ ሰው ምንነት፣ ስለ ቀላያት፣ ስለ እንስሳት፣ ስለ ሕይወት፣ ስለ ሞት በአጠቃላይ በዙሪያው ስለሚመለከታቸው እና ከምልከታ ውጭ ስለኾኑ ረቂቂና ሩቅ ዕሳቤዎች ጥያቄ ያነሣል። እነዚህ ዘወትራዊና ዘላላማዊ ጥያቄዎቹን የሚመልስለት አካል ያስፈልገዋል። ከእነዚህ አስፈላጊ ምላሽ ማግኛ መሣሪያዎች መካከል ሃይማኖት ትልቅ ድርሻ አለው። አማኝ ለኾነው ምእመን መንፈሳዊ ይኹን ሥጋዊ ዕረፍትን በመስጠትና ከአምሮው በላይ የኾኑትን ተመላላሽ ጥያቄዎች መልስ በማስገኘት በኩል እንደ ሃይማኖት የሚኾንለት ያለ አይመስልም (Peek እና Yankah 2004, 781)።

ሃይማኖት በከብረ በዓል መልክ እየተመሳለሰ እና እየተከወነ ማኅበራዊ ግብረገብነትን እና የሰዎች መተሳሰብን ያሠርጻል፡፡ ሃይማኖታዊ ከብረ በዓል መንፈሳዊና ዓለማዊ ዕሳቤው ከፍ ያለ በመኾኑ የሰዎችን ተፈጥሯዊ ባሕርይ በመግራት እና ቅርጽ በማስያዝ ኹነኛ ጠቀሜታ አለው (Rappaport, 1999, 1 እና Candace S. Alcorta, 2006, 12)፡፡

ሃይማኖት ቀኖናው እና አስተምህሮው ዓለማቀፋዊ ይኹን እንጂ ለማኅበረሰባዊና ባህላዊ መስተጋብር መልስ ለመስጠት ከባህልና ማኅበረሰብ ጋራ ቅርብ እና ሥሙር ነው፡፡ እንደ ጥምቀት ያለ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ከበቀለበት ማኅበረሰብ ባህል፣ ወግና ሥርዐት ጋራ በውል የተሸመነ በመኾኑ ማኅበረሰባዊ እና ባህላዊ መሠረት ያላቸውን ጥያቄዎች የሚመልሱ ናቸው፡፡ የማኅበረሰቡ ባህል ቅቡል አድርጎ የሚያምናቸው ሠናይ ምግባራት እንዲተከሉ እና እኩይ ብሎ የፈረጃቸው ደግሞ እንዲነቀሉ በማድረግ የሃይማኖት ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ከግብረ ገብነትና ከመንፈሳዊ ጥቅም ባለፈ ሃይማኖት ምጣኔ ሀብቱን ለማሳደግ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ ይህን በተመለከተ Aldashev and Platteau (2014, 587) ተከታዩን ሐሳብ ሰንዝረዋል፡፡ *"ሃይማኖት በሰባዊ፣ ማኅበረሰብ ውስጥ ከኢኮኖሚ ልማት አንጻር የራሱ ሚና አለው፡፡ በዚህ ጉዳይ ዳሠሣ (ጥናት) በምናደርግበት ጊዜ የሃይማኖት፣ የእምነት አስተዋፅኦ ከግምት ውስጥ ማስገባት፣ ሃይማኖታቸውንና እምነታቸውን መፈተሽ፣ የግለሰቦችን የኢኮኖሚ ልምድ ለመገንዘብ መሞከር ያስፈልጋል"*[23] *በማለት ያስረዳሉ (ትርጉም የእኔ)፡፡*

የሃይማኖት ዕሳቤ ማኅበረሰቡን በአንድ ክብረ በዓል በማገናኘት በክብረ በዓል አስተምህሮና በቀኖናው አማካይነት በማኅበረሰቡ ልብ ውስጥ ተግባቦትን ያሠርጻል፡፡ በዚህ መልኩ ክብረ በዓልና ሃይማኖት አንዳቸው በሌላቸው ላይ እየተከሰቱ፣ እየተገለጡ እና እተዳበሉ የሚቀጥሉ ናቸው (Rappaport 1999, 25-26)::

ጠቅለል ባለ መልኩ ሃይማኖት Durkheim ከአእምሮ በላይ (unknowen) ብለው ከሚያነሷቸው ያልታወቁ ሩቅ እና ረቂቅ ጥቄዎች አኳያ ሲታይ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ለኾኑ ጸናን እና ላልተፈቱ እንቆቅልሾች መልስ ይሰጣል፡፡ ሰዎች ከአምላካቸው፣ ብሎም ከመንግሥተ ሰማያት ወራሽነት ጋራ በተያያዘ ሐሳባዊና ረቂቅ መልስ ያስገኛል፡፡ በውስጡ

---

[23]*"the role of religion in human societies from a development economics perspective. We start by reviewing the contributions that consider religious beliefs as exogenously given and try to understand their effects on individual economic behavior" (*Aldashev and Platteau 2014, 587).

የእምነት ጉዳይ ስላለበት ሃይማኖት በማኅበረሰቡ መካከል እውነትን፣ መታመንን፣ ተግቶ መሥራትን፣ ሐቀኝነትን፣ በአጠቃላይ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ መንፈሳዊና ሰባዊ ዕሳቤዎችን ያስቀጥላል (Aldashev and Platteau 2014, 610)። ይህ ጥናትም ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ከሚቀዳው የጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የተመሠረተ ነው።

### 2.1.3. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና ክብረ በዓላት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን በውስጧ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ሰባዊ ጉዳዮችን ዐቅፋለች። ቤተ ክርስቲያኗ ከሃይማኖታዊ አስተምህሮዎቿ በተጨማሪ የሀገር በቀል ዕውቀቶች፣ ትውፊትና ቅርሶች ባለቤት ናት። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ዕውቀት ሲመረመር ከማኅበራዊ ዕሴቶች እና ከፎክሎራዊ ዕውቀቶች ጋራ የተሸመነ ነው (Tony Karbo (2013, 45 ፤ Peek እና Yankah 2004, 240)።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት የማኅበረሰቡ ዕሳቤዎች፣ ባህሉና ልማዱ፣ ትውፊቱና ቅርሱ እንደ ድር እና ማግ አብረው የተሸመኑበት ነው። በመኾኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖትና የኢትዮጵያ ባህል አንዳቸው በሌላቸው ላይ የሚገለጹ እና የሚከሰቱ ናቸው (Jacob Bulti Smørdal, 2012, 5)። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ባላት ረጅም ታሪክ ውስጥ ትምህርትን ስታስፋፋ፣ ቅርስና ታሪክን ስትጠብቅ ቆይታለች። ይህ የትምህርት፣ የታሪክና ቅርስ ባለቤትነቷ በዓለም ውስጥ፣ በተለይም በአፍሪካ የተለየ ቦታ እንዲኖራት አስችሏታል (የኢ.ኦ.ቤ.ታ[24] 2000፣60)።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የምዕራባውያን ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ ከመምጣቱ በፊት የራሷን ፊደል ቀርጻ፣ ጉባኤያት መሥርታ ታስተምር ነበር። እስከ አኹንም ድረስ ከቄጥር ትምህርት ቤቶች ዐልፎ እስከ ማስመስከሪያ ጉባዔ ቤቶች ባለቤት ናት። ከእነዚህ የምስክር ጉባዔ ቤቶች መካከል የቤተ ልሔም ድጓ፣ የዙራምባ ዝማሬ መዋስዕት፣ የደብረታቦር ኢየሱስ ተክሌ አቋቋም፣ የጎንደር በዓታ ለማርያም የጎንደሬ አቋቋም፣ የመንበረ መንግሥት መድኀኔዓለም አንድምታ ምስክር እና የደብርዓባይ የቅዳሴ ማስመስከሪያ ጉባዔ ቤቶች ተጠቃሾች ናቸው። ቤተ ክርስቲያኗ የራሷ የኾነ የምታስተምርበት ሥርዐትና የማስተማሪያ ሥነ ዘዴ አላት። ይህ የማስተማሪያ ዘዴ አንድ መሪጌታ ከቄጥር

[24] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

እስከ ዜማ ያሉትን ተማሪዎች በአንድ ወንበር ውስጥ የሚቆጣጠሩብት፣ የሚከታተሉበት፣ የሚያርሙበት እና የሚያሳልፉበት ዐቅም ያዳበረ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ቤተ ክርስቲያኗ በቀን እና በሌሊት፣ በማታ እና በጧት ከፋፍላ በማስተማር የጊዜ ብክነትን የምትቆጣጠርበት እና  የምታስተምርበት ልምድም እንደ ሞዴል የሚወሰድ ነው (የኢ.ኦ.ቤ.ታ 2000፤75)።

እስካኹንም ድረስ ቤተ ክርስቲያኗ በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ የኾነ የክብረ በዓል፣ የባህል፣ የትምህርት፣ የቅርስ እና የትውፊት ባለቤት ናት። የዚህ ጥናት ትኩረት የኾነው የጥምቀት ሥርዐተ ክዋኔ አንድምታ እና ፋይዳ በጎንደር የሚለው ርእሰ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ክብረ በዓሎች መካከል የሚቀዳ ነው። የጥናቱ ዓላማም የጥምቀት ክብረ በዓል ያለውን ማኅበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ሰባዊ ፋይዳ ማጥናት እና መመርመር ነው።

### 2.1.4.የጥምቀት ክብረ በዓል

በዓለ ጥምቀት ጥር 11 ቀን በየዓመቱ እየተመላለሰ የሚከበር የበዓል ዐይነት ነው። በዓሉ ሃይማኖታዊ ይኹን እንጂ ዕሳቤው ሰዋዊ ጉዳይ እና ለሰው ልጆች ብቻ የተሰጠ ጸጋ ነው። መነሻው ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጆች ድኅነት ሲል ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በማየ ዮርዳኖስ ተጠምቆ የሰዎችን የዕዳ ደብዳባቤ የቀደደበት የድኅነት ምሳሌ ነው (መዝ፣ 67፤22፤ ቆር 13፤10-2፤ ዮሐ 1፤5 እና ማቴ 3፤16)። ይህን በተመለከተ የኢትዮጵ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሚለው መጽሐፍ ስለ ጥምቀት አመጣጥ፣ ዓላማ እና ፋይዳ እንደሚከተለው ያብራራል።

> ***ጥምቀት፡-*** *ክርስቶስ በተወለደ በሠላሳ ዓመቱ የማዳን ሥራውን በጥምቀቱ ጀምሯል። ጌታ የተጠመቀው በፈለገ ዮርዳኖስ ነው። ያጠመቀው ዮሐንስ ወልደ ዘካርያስ ነው። በተጠመቀም ጊዜ አብ በደመና ኹኖ የምወደው ልጄ ይህ ነው ብሎ መስክሮለታል። መንፈስ ቅዱስም በጸዐዳ ርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀምጧል። ይህ በዓል በሚከበርበት ጊዜ በዋዜማው ታቦታቱን ከየቤተክርስቲያናቸው ወጥተው በወንዝ ዳር በድንኳን ያድራሉ። ሌሊት ስብሐተ እግዚአብሔር ሲደርስ ዐድሮ ሥርዓተ ቅዳሴው ይፈጸማል። ሲነጋ በጥምቀተ ባሕሩ ጸሎተ አኮቴት ተደርሶ አራቱም መንጌላት ከተነበቡ በኋላ ውሐው ተባርኮ ለተሰበሰበው ሕዝብ ይረጫል። በዓለ ጥምቀት የሚከበረው ጥር 11 ቀን ነው። ጥምቀት ረቡዕ ቢውል ገሃዱ ማክሰኞ ዐርብ ቢውል ገሃዱ ኀሙስ ለውጥ ኾኖ ይጾማል። በዓለ ጥምቀት የሚውልባቸው ረቡዕና ዐርብ አይጾሙም። በበዓለ ጥምቀት*

*የታቦቱ ወደ ወንዝ መውረድ ጌታ በእደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ የመኼዱ ምሳሌ ነው* (የኢ.ኦ.ቤ.ታ 2000፣41)፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የክርስቶስ በውሐ መጠመቅ በዋናነት ኹለት መሠረታዊ ነገሮችን አሳክቷል፡፡ አንደኛው በማየ ዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ የአዳምንና የሔዋንን ዕዳ ደብዳቤ "እንደ አምላክነቱ አቅልጦ፣ እንደሰውነቱ ረግጦ" ማጥፋቱ ነው፡፡ ኹለተኛው ደግሞ ውሐዎችን መቀደሱ ነው፡፡ ሃይማኖታዊ አስተምህሮው እንደሚያስረዳው ከክርስቶስ ጥምቀት በፊት ዓለም በኖኅ ዘመን በንፍር ውሐ ጠፍታ ነበር፡፡ እንደዚሁም በብሉያት ዘመን ሙሴን ባሕረ ኤርትራ እና ኢያሱን ደግሞ ባሕረ ዮርዳኖስ እንቅፋት ኾነውባቸው ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት እስከ ጥምቀተ ክርስቶስ ድረስ የውሐ ዕሳቤ የጥፋት እና የሥጋት ምንጭ ኾኖ ቀጥሎ ነበር፡፡ እነዚህ የሥጋት ውሐዎች ከክርስቶስ መጠመቅ በኋላ ደግሞ ለሥጋ እና ለነፍስ ድኅነት ኹነዋል (መድኀኒት በጥምቀት 1955፣ 26፤ ዘማርያም ኤፍሬም እና በእደማርያም ዳንኤል 1998፣5-8)፡፡

እነዚህ ኹለት መሠረታዊ ዕሳቤዎች ለሰው ልጆች የሚጠቅሙ ናቸው፡፡ የተቀደደው ደብዳቤ ለሰው ልጆች ነጻ መውጣት ምሳሌ ሲኾን የውሐው መቀደስ እና መባረክም ደግሞ ለሰው ልጆች ምግበ ነፍስ እና ምግበ ሥጋ እንዲሆን ያስቻለበት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ጥምቀት ለሰው ልጆች የተሰጠ የድኅነት እና የነጻነት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመኾኑም የጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ የክርስቶስን በጎ ተግባር በመድገም በማኅበረሰቡ ውስጥ በጎነትን ማሥረጽ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የጥምቀት ክብረ በዓል ትሕትና፣ ደግነት፣ መከባበር፣ መተሳሰብ፣ ሰላም የሚሉትን ሰዋዊ ዕሳቤዎች እና ክርስቶስ በጥምቀቱ ዕለት ያሳካቸውን በጎ ተግባራት የሚዘከሩበት ነው፡፡ በዚህ አስተምህሮ ውስጥ ሰዎች በጎ ተግባርን የሚያሳድጉበትና የሚያለመልሙበት ነው (መድኀኒት በጥምቀት 1955፣35፤ ዘማርያም ኤፍሬም እና በእደማርያም ዳንኤል 1998፣5-8)፡፡ ይህ ጥናትም የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ፣ አንድምታና ፋይዳዎቹን ለመመርመር እና ለማሳየት ያለመ ነው፡፡

## 2.2. ንድፈ ሐሳባዊ ማሕቀፍ

### 2.2.1. የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ

ፎክሎር የሚጠናባቸው በርካታ የንድፈ ሐሳብ ማሕቀፎች አሉ፡፡ ከእነዚህ የፎክሎር መመልከቻ ንድፈ ሐሳቦች መካከል የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ ተጠቃሽ ነው፡፡ ንድፈ ሐሳቡ ኹሉንም የፎክሎር መከሠቻዎች ለመመርመር በማስቻሉ ለዘርፉ እጅግ ተመራጭ እየኾነ መጥቷል፡፡ Bauman (1977, 190) እንደሚሉት የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ በፎክሎር ጥናት ውስጥ የክዋኔ ዐውድን፣ አጋጣሚን፣ አሐድን፣ ከዋኔን፣ ተሳታፊን እና የክዋኔውን ትውን ጥበባት በአንድ አስተባብሮ የሚያስገኝ በመኾኑ ለፎክሎር ጥናት መመለክቻ ከፍ ያለ ፋይዳ አለው የሚል አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡ Goldstein (1962, 95) በበኩላቸው ደግሞ ፎክሎር በክዋኔ፣ በዕውቀት፣ በጥበብ፣ በትርጉም እና በትውፊት የተሞላ የትምህርት መስክ ነው ካሉ በኋላ ፎክሎርን በክዋኔ ንደፈ ሐሳብ መመልከት አዋጭነት ይኖረዋል በማለት ስለ ንድፈ ሐሳቡ አስፈላጊነት ያስረዳሉ፡፡

እነ Mccarmik C.T እና White, K.K (20011, 96) በበኩላቸው ደግሞ ክዋኔ ለፎክ ቡድኑ አንዳች የጋራ ውጤትን በማስገኘት እና በቡድኑ ውስጥ ተግባቦትን በመፍጠር ከዋኝ፣ ተሳታፊ እና ዕውቀት በጋራ የሚገናኙበት ዐውድ ነው ይላሉ፤ እንደዚሁም በክዋኔ ግንኙነት ወቅት በዐውድ ዛፍ ጥላ ሥር፣ አሐድ፣ ከዋኝ እና ተሳታፊ የሚተዋወቁበት፣ አንድነት የሚፈጥሩበት እና የክዋኔው ባለቤት የኾኑት ማኅበረሰቦች ዕሴታቸውን የሚያስቀጥሉበት የግንኙነት ማሕቀፋቸው ነው በማለትም ያክላሉ፡፡

Yankah, Kwesi እና Peek, Philip (2004, 670) በበኩላቸው የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ በ1970ዎቹ አካባቢ ጀምሮ ለሥነ ሰብእ፣ ለፎክሎር፣ ለሶሲኦሎጅ እና ለመሳሰሉት የትምህርት መስኮች አዋጭ መመልከቻ መኾኑን ያረጋግጣሉ፡፡ እንደነ Sims and Stephen (2005, 133) እና Bauman (1977, 195) ዕይታ ደግሞ የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ የቅርብ ጊዜ የጥናት መስክ ቢኾንም ለፎክሎር ለሥነ ሰብእ፣ ለዘውግ እና ለባህል ጥናት ወሳኝና ዘመነኛ ንድፈ ሐሳብ ነው የሚል ምልከታ አላቸው፡፡ ይህ የሚያሳየው የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ ለሂዩማኒቲስ እና ለማኅበራዊ ሳይንስ ትምህርት መስኮች ማጥኛ አስፈላጊ መኾኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በአንድ የፎክሎር ዘውግ ውስጥ የሚታዩት የክዋኔ ዘውጎች፣ እንቅስቃሴዎች፣ ዳንሶች፣ ዘፈኖች፣ ቀረርቶዎች፣ ፍከራዎች እና ልማዶች ለየብቻ ተነጣጥለው የቆሙ ሳይሆን ርስ

በርሳቸው የሚሰናሰሉ፣ የሚተጋገዙ እና የሚተረጎሙ ናቸው (Richard Bauman 1975፣ 77):: የእነዚህ ፈርጀ ብዙ የፎክሎር ዘውጎች ህልውና እና ተስተላልፎ የሚጸናው በክዋኔ ደምሥር ነው፡፡ በመኾኑም የፎክሎር ዘውጎችን ለመረዳት እና ለመተርጎም የክዋኔ ንደፈ ሐሳብ አስፈላጊ ነው፡፡ የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ በአንድ ክብረ በዓሉ ውስጥ ያለውን ማኅበራዊ መስተጋብር፣ ማኅበራዊ መዋቅር፣ የክዋኔውን ጥበባት፣ ስሜት እና ትርጉም ለመረዳት ያስችላል፡፡ ይህን ሐሳብ በተመለከተ Peek እና Yankah (2004: 797) *"የክብረ በዓል ክዋኔ ማኅበረሰባዊ ጉዳዮችን ትርጉም የሚሰጥ ወይም የተለያየ ማኅበረሰባዊ ግንኙነቶች እና ግለሰባዊ ተግባራት የሚገለጹበት ነው፡፡ ከዐውድና ከቴክስት አኳያ የክብረ በዓል ክዋኔ የሚጠበቅ ስሜት ወይም ትውን ጥበባት በሰላ መልኩ የሚታዩበት አጋጣሚ ነው"*[25] በማለት ያትታሉ *(ትርጉም የእኔ)* ፡፡

እንደዚሁም Finnegan (1992, 93) ደግሞ ከነ Peek እና Yankah በሚስማማ መልኩ ክዋኔ የክብረ በዓል ዋና ማስኬጃ ሲኾን በክብረ በዓል ውስጥ የሚከወኑትን የሥነ ቃል ዘውጎች ለመረዳት ትልቅ ፋይዳ አለው ይላሉ፡፡ Bauman (1977, 14) በበኩላቸው አንድ የክብረ በዓል ክዋኔ በክዋኔው ወቅት ለማኅበረሰቡ ፈቃድን፣ ነጻነትን፣ መከወንን እና መሳተፍን የሚፈቅድ ነው፡፡ በነጻነት እና በመሳተፍ የሚደረግ ክዋኔ ደግሞ የማኅበረሰቡን ዕሴት፣ ፍልስፍናና የሕይወት ተሞክሮ ለመረዳት ያስችላል የሚል ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡ እንደነ Sims እና Stephen (2004, 141) ማረጋገጫ ደግሞ የክብረ በዓል ክዋኔ በአንድ በታወቀ ስፍራና ጊዜ የከዋኝ፣ የአሐድ፣ የዐውድና የተሳታፊን ተራክቦ በመፍጠር የፎክሎር ትውን ጥበባት እውን የሚሆንበት አጋጣሚ ነው በማለት የክዋኔ ንድፈ ሐሳብን መጠነ ርዕይ ይገልጻሉ፡፡ Bauman (2002, 72) በበኩላቸው የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ የክዋኔ አላባውያን የኾኑትን ከዋኝን፣ አሐድን፣ ዐውድን፣ ትእምርትን፣ ቁሳዊ ባህልን፣ በአንደበትና ከአንደበት ውጭ የሚገለጹትን ኹሉ የሚያጠቃልል ነው በማለት የንደፈ ሐሳቡን አስፈላጊነት ይገልጻሉ፡፡

የክብረ በዓል ክዋኔ አንድ ማኅበረሰብ ዕውቀቱ እና ዕሴቱን በአንድ ኹነኛ ዐውድ ውስጥ ለትዕይንት የሚያበቃበት አጋጣሚ ነው፡፡ በዚህ የክዋኔ ትዕይንት ውስጥ የማኅበረሰቡ ዕሴቶች፣ ፍልስፍናዎች፣ ሕጎች፣ ዕውቀቶች፣ ግብረ ገብነቶች እና ማኅበረሰባዊ ግንኙነቶች

[25] *`A ritual performance marks a meaningful social event or transition through various kinds of coordinated and individual actions. As occasions or events, ritual performances are often considered emotionally or esthetically heightened occasions as well` (* Peek እና Yankah 2004: 797).

እንዲታዩ እና እንዲቀጥሉ ያደርጋል፡፡ የክብረ በዓል ክዋኔ ሃይማኖትን፣ ፖለቲካን፣ ማኀበራዊ እና ባህላዊ ጉዳዮችን አደባባይ በማውጣት ግለሰቦችን ከማኅበረሰቡ፣ ዕውቀትን ከለማጁ ጋራ የማገናኘት ዐቅም አለው (Peek M.እናYankah 2004, 797-800)::

የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ ለክብረ በዓል ከንድፈ ሐሳብ ማሕቀፍነት በተጨማሪ የመተንተኛ ስልት በመሆን ላቅ ያለ ሚና አለው፡፡ ከእነዚህ ሚናዎቹ መካካል እንደ መረጃ መሰብሰቢያ እና በዋናናት ከመስክ የተሰበሰበውን መረጃ እንደ መተንተኛ ስልት በመኾንም ያገለግላል፡፡ የክዋኔ መተንተኛ ስልት በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የዘርፉን ተመራማሪዎች ቀልብ እየሳበና ተቀባይነት እያገኘ የመጣ ዘመነኛ ስልት ነው፡፡ የክዋኔ መተንተኛ ስልት በአንድ ክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ በክብረ በዓሉ የሚነገሩትን፣ የሚዜሙትን፣ የሚቀነቀኑትን፣ በአካል እንቅስቃሴ የሚተላለፉትን፣ በንዋየ ቅድሳት የሚወከሉትን፣ የማኅበረሰብ ዕሴቶች እና ባህላዊ ትውፊቶች ሥርዐት አሲይዞ ለመተንተን ያስችላል፡፡ የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ የክብረ በዓል ክዋኔን ውስብስብነት፣ የማኅበረሰብን የሕይወት ፍልስፍና እንደ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ሰዋዊ ዕሳቤዎችን ቅርጽና ትርጉም ሰጥቶ ለመተንተን ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ የክብረ በዓል ክዋኔ የጥበባዊ ዕሴት፣ የባህላዊ ትርጉም እና የማኅበረሰባዊ ማንነት ሽምን ነው፡፡ በመኾኑም በክዋኔ የመተንተኛ ስልት ሊታይ እና ሊዳኝ ይገባዋል፡፡ የዚህን ሐሳብ ማረጋገጫ በተመለከተ Peek እና Yankah (2004, 803) የሚከተለውን ማብራሪያ ይሰጣሉ፡፡

> *የክብረ በዓል ክዋኔ በክዋኔ ትንታኔ ውስጥ የሚዳኝ ነው፡፡ ስለ ክዋኔ ትንታኔ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ አተያዮች ነበሩ፡፡ እነዚህ የተለያዩ አተያዮች የባህል ዕሴት ግጭት፣ የማኅበረሰባዊ ግንኙነቶች ተቃርኖ አምጥተዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የተለያዩ የሃይል ተቃርኖዎች፣ በክብረ በዓል ሥርዓትና ትርጉም ላይ ለውጥ ያስከትላል፡፡ ለበለጠ ልማት የክዋኔ ትንታኔ ከ1982 ጀምሮ ትልቅ የኾነ ተቀባይነትና ትኩረትን የመሳብ ዐቅም አግኝቷል፡፡ ይህም ለኢኮኖሚ፣ ለምጣኔ ሀብት፣ ለታሪክ ኺደት የክብረ በዓል ክዋኔን ቅርጽ ለማስያዝ ያግዛል፡፡ እንደዚሁም በሥነ ውበት፣ በባህላዊ ዕሴት፣ በትርጉምና በማኅበረሰባዊ ሕይወት መካከል ቀጣይነት ያለውን ትኩረት ይሰጣል (ትርጉም የእኔ)::*[26]

[26] *Ritual performance should be prominent in performance analysis. At times these different perspectives diverge and can reveal tensions among the actors and interests involved, differences of power, contradictions within the cultural values and social relations that inform*

የክዋኔ ንድፈ ሐሳብ ለክብረ በዓል ትልቅ ሚና አለው ሲባል በክብረ በዓል ውስጥ የሚደረገው ክዋኔ የግለሰቦች ማንነት፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት በይፋ የሚታይበት መኾኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በክብረ በዓል አማካይነት የማኅበረሰቡ ፍልስፍና፣ ዕሴት እና ልማድ የመሳሰሉትን ማኅበረሰባዊ ውቅር ያሳውቃል። ክብረ በዓል ቀጣይ የሚኾነው በየወሩ፣ በየዓመቱና ክብረ በዓሉ በሚፈቅደው ልክ እየተመላለሰ በመከወኑ ነው።

የክብረ በዓል ክዋኔ በአብዛኛው ቡድናዊ በመኾኑ ማኅበረሰባዊ ፋይዳው ላቅ ያለ ነው። በክብረ በዓል ክዋኔ ማኅበረሰቡ በሚችለው መልኩ ወይም ክብረ በዓሉ በሚያዘው ልክ እየተሳተፈ ወይም ሳይሳተፍ በክዋኔው ውስጥ የራሱን አስተዋፅኦ ያደርጋል። ከዋኝ እና ተሳታፊው በእስክስታ፣ በቀረርቶ፣ በፉከራ፣ በዝማሬ፣ በሽብሻቦ እና በመሳሰሉት ተሳትፎ ውስጥ የደስታ ስሜት እንዲያገኝ እና ለአንዳፍታም ቢኾን ከችግሮቹ እንዲነጠቅ እና እንዲያመልጥ ያስችለዋል። የክብረ በዓል ክዋኔ የትዳር ጓደኛ፣ አበልጅ፣ የጡት አባት፣ የነፍስ አባት የመሳሰሉትን ዝምድናን በመፍጠር ቁሳዊ ወይም ሥጋዊ የኾነ ጥቅምን ለክብረ በዓሉ ባለቤቶች ያስገኛል። በሌላ መልኩ ደግሞ መመሰጥን፣ ከአምላክ ጋራ መገናኘትን፣ ይህን ዓለም መርሳትን፣ ይኾንልኛል ብሎ ማሰብን በማለምለም የተጠኚዎቹን ኀሊና ይገዛል። ክብረ በዓል በአንደበት፣ በምልክት፣ በትእምርትና በተምሳሌት አማካይነት ማኅበራዊ እና ሰባዊ ተግባቦቶችን ይፈጠራሉ። ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎችን ለመረዳት ከዘወትራዊው ውክልና በተጨማሪ ፍካሬያዊ ውክልናዎቹን፣ ትእምርቶቹን እና ተምሳሌቶቹን መረዳት ያስፈልጋል (Rappaport 1999, 50)።

ጠቅለል ባለ መልኩ የክብረ በዓሉ ክዋኔ በከዋኙ፣ በተሳታፊዎቹና በተመልካቾቹ ዘንድ ማኅበራዊ ግንኙነትን በመፍጠር እና ማኅበራዊ ዕሴቶች ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉ በማድረግ በኩል ላቅ ያለ ሚና አለው። በመኾኑም የክዋኔ ንደፈ ሐሳብ ለዚህ ጥናት መመልከቻ አስፈላጊ ኾኖ በመገኘቱ ተግባራዊ ተደርጓል።

---

*the ritual, and historical shifts in ritual procedures and interpretations. Further development of performance analysis in the 1990s has included greater attention to wider scale political, economic, and historical processes that help to shape ritual performance, as well as continued attention to the relations among esthetics, cultural values and meaning, and social life. (Peek እና Yankah 2004, 803).*

### 2.2.2. ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ

ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ የተቀነቀነው በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሐሳብ የአዝግሞተ ለውጥና የሥርጸት ንድፈ ሐሳቦችን ተቃውሞ የመጣ ነው፡፡ ንድፈ ሐሳቡ የማኅበረሰቡን መዋቅር፣ የክብረ በዓል ተግባራትን እና ባህላዊ ትእምርቶችን በዐውድ ለመመልከት አስቻይ ነው፡፡ Bell (2009, 42) ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ብቅ ያለውና እና ትግበራ ላይ የዋለው ከ1950ቹ ዘግየት ብሎ እና ከ1960ቹ ደግሞ ቀደም ብሎ እንደኾነ ያስረዳሉ፡፡ አክለውም ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ማኅበረሰባዊ መዋቅርን፣ የክብረ በዓል ክዋኔን እና የባህላዊ ትእምርትን ለማየት የሚያስችል ነው በማለት አስፈላጊነቱን ይገልጻሉ፡፡ Elliot Oring (1976, 78) በበኩላቸው ደግሞ "ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ባለፉት ጊዜያት ለሥነ ሰብእ፣ ለፎክሎር፣ ለሥነ ጽሑፍ እና ለሥነ ልሳን የትምህርት መስኮች የተሻለ መመልከቻ በመኾን አገልግሏል" በማለት የንድፈ ሐሳቡን ኹለ ገብነት ያስተነትናሉ፡፡

የተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ዋና አቀንቃኝ ከሚባሉት መካከል William Bascom, Bronsilaw Malinowski እና A.K Radcliffe Brown በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ William R Bascom ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብን መሠረት በማድረግ የፎክሎርን ተግባራት፡- የማምለጥ፣ የመትከል፣ የማስተማር እና የመቆጣጠር ተግባሮች እንዳሉት ይገልጻሉ William R Bascom (1965, 239), Sims እና Stephen, (2005, 175)፡፡ እንደዚሁም Radcliffe Brown ደግሞ የፎክሎርን ተግባር ከተፈጥሮ እና ከአልሰለጡት[27] ማኅበረሰቦች ጋራ አያይዘው ይመለከቱታል (Bell 2009, 29)::

ይህ የWilliam Bascom በአራት ክፍሎች ወስኖ መመልከት እና የA.K Radcliffe Brown ተፈጥሮአዊ እና የአልሰለጠኑ ማኅበረሰቦች ጉዳይ ነው የሚለው ማጠንጠኛ ሐሳብ ትችት ገጥሞታል፡፡ የትችቱ ማጠየቂያ ደግሞ የፎክሎርን ፋይዳ አስተሳሰብ ከፎክሎሩ ባለቤት (Emc perspective point of view) ይልቅ በምሁራኑ ዐይን (Etc perspective point of view) ለማየትና ለማጠቃለል መሞከር ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ ከሞጋቾቹ መካከል Sims እና Stephen, (2005, 176) የባህል ክዋኔዎች የተለያዩና ውስብስብ ከመኾናቸው የተነሣ አንዳች ፎክሎራዊ ፋይዳን ለመመርመርና ለማወቅ በመጀመሪያ ለምን እንደሚከወኑና ክዋኔውን መረዳት ተገቢ ነው ካሉ በኋላ አንድ የፎክሎር የዘውግ ክዋኔ ከተጠኚዎቹ ዐይን

[27] `Primitive community in the same way that every organ of a living body` (Bell (2009, 29).

በመመርመር እና በመተርጐም ፋይዳውን ማወቅ ተገቢነት አለው የሚል ማጠየቂያ ያነሣሉ፡፡ በተጨማሪ Dorson (1972, 167) ይህንኑ ሐሳብ በመደገፍ የፎክሎር ተግባር የሚለካው እንደየ ባህሉ እና ኹኔታው፣ እንደ ክዋኔው እና አጋጣሚ፣ እንደ ዐውዱ እና አሐዱ በባህሉ ውስጥ ተገብቶ መኾን አለበት ይላሉ፡፡

እነ Dan Ben Amos (1982,46) እና Shoe Maker (1990, 86) Sims እና Stephen (2005, 175) የተባሉ የዘርፉ አጥኚዎች ደግሞ ተግባራዊ ንደፈ ሐሳብ በማኅበራዊ፣ በሥነ ልቡናዊ እና በባህላዊ ፋይዳዎች በሚሉት ነጥቦች ላይ መመርኮዝ እንደሚገባ ይመክራሉ፡፡ ተመራማሪዎቹ አክለውም ፎክሎራዊ ተግባር የሚለካው በሚከወንበት ባህል ውስጥ በመግባት በዐውዱና በክዋኔው ሚዛን ልክ መኾን አለበት የሚል የነ Dorson (1972, 167) ዐይነት ጠንካራ አቋም አላቸው፡፡ ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ በአንድ የፎክሎር ቡድን ውስጥ መጠነ ሰፊ የኾነ ባህላዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቡናዊ ፋይዳን ለመረዳት ሚናው የጎላ ነው፡፡ ስለኾነም አንድ የፎክሎር አጥኚ የፎክሎር ቡድኑ የሚጋራቸው ክብረ በዓሎች፣ ሥነ ቃሎች ትውፊቶች፣ ልማዶችና እምነቶች ለምን? እንዴት? መቼና የት? እንደሚከወኑ፣ ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ በባህሉ ውስጥ ገብቶ መረዳት ግድ ይለዋል፡፡

ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ከዐአውድ እና ክዋኔ ጋራ የጠበቀና የጠነከረ ግንኙነት አለው፡፡ በዚህ ቁርኝት ውስጥ የፎክሎር ተግባር በክዋኔ ዐውድ ላይ በመመሥረት ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ኹለንተናዊ መስማማትን በማስገኘት በፎክሎሩ ባለቤቶቹ መካከል የተረጋጋ ማኅበረሰብ እንዲመሠረት ያደርጋል (Elliot Oring (1976, 72)::[28]

የፎክሎር ተግባር ጠቅለል ባለ ኹኔታ ሲታይ የማኅበረሰቡን መዋቅር በማስቀጠል፣ ሥርዐትና ሕግን በመደንገግ፣ በማጽናት እና በማስከበር የማኅበረሰቡን የሕይወት ጉዞ ያስቀጥላል፡፡ እንደዚኹም ማኅበረሰቡን በማረጋጋትና የተደላደለ ኑሮ እንዲቀጥል በማድረግ ትልቅ ሚና አለው፡፡ የፎክር ዘርፍ የኾነው ክብረ በዓል በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ በርካታ የአክባሪዎቹ ጉዳዮች አደባባይ የሚወጡበት ነው፡፡ ከእነዚህ ጉዳዮች መካከል ሃይማኖታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ማኅበራዊ እና ሰባዊ ጉዳዮች ዋና ዋናዎቹ ማጠንጠኛዎች

[28]*Folklore Function is a socio-cultural maintenance of stability pattern which contributes to the cultural system."* የሚል ማረጋገጫ ይሰጣሉ፡፡

ናቸው (Yankah, Kwesi and Peek, Philip M, 2004, 799)። በመኾኑም የክብረ በዓል ፋይዳ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህን የክብረ በዓል ተግባር ለመመልከት ሲባል ተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ ለዚህ ጥናት መመልከቻ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 2.2.3. የሚት ንደፈ ሐሳብ

ሚት ከግሪክ mythos ከሚለው ቃል የተገኘ ሲኾን ትርጉሙም ቃል፣ ንግግር፣ ተረት፣ ወይም ታሪክ ማለት ሲኾን በሰላ ቋንቋ፣ በራቀ ምናብ እና በበሳል ዕውቀት የሚተረክ ነው በማለት Morford, Mark P.O እና Lenardon, Robert J, (2003, 3) ያስረዳሉ፡፡ ሚት እንደ ክብረ በዓል በመሳሰሉ ፎክሎራዊ ዘውጎች በቃል፣ በትእምርት፣ በአካል እንቅስቃሴ እና በድራማ የሚገለጥ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት እንደነ Morford, Mark P.O እና Lenardon, Robert J, (2003,3) ያሉ የዘርፉ ተመራማሪዎች የሚት ብያኔ ሰፋ ባለ መልኩ ከአፈ ታሪክ፣ ከፎክሎር እና ከትውፊት ጋራ ተሰናስሎ መታየት እንዳለበት ይመክራሉ፡፡ Dorson (2006, 109) ይህንኑ ሐሳብ በመደገፍ ስለ ሚት ሲያትቱ "የፎክሎርና የሥነ ሰብእ አጥኚዎች ሚትን ከፎክሎር፣ ከሥነ ሰብእ፣ ከሃይማኖት፣ ከልዕለ ተፈጥሮና ከክብረ በዓል ጋራ ባለው የጠበቀ ግንኙነት ተመሥርተው ይመለከቱታል" የሚል ማስረጃ ይሰጣሉ፡፡

Campbell, (1960, 12) በበኩላቸ ከተካኑበት የሥነ ጽሑፍ ዕውቀት በመታገግ ሚትን "ከተለመደው ዘወትራዊና ዘመናዊ ዕሳቤ በራቀ መልኩ ጥልቅ ስሜትን በማጋራት ምናብን ይገዛል፤ ሥነ ጽሑፋዊ ዋጋውም ከፍ ያለ ሩቅና ረቂቅ ሐሳብን የተላበሰ ነው" በማለት ብያኔያቸውን ይሰጣሉ፡፡ Dundes (2009, 132) በበኩላቸው ደግሞ ሚት ለበርካታ ዓመታት የተዛባና የተዘበራረቀ ምስል (picture of chaos) ነበረው፡፡ ይኹን እንጂ ሚት የተዘበራረቀውን እና የተወሳሰበውን ዓለም ውል ያለው ማሰሪያ ለማበጀት ይጥራል የሚል በአንድ በኩል የዋለለ በሌላ በኩል የተማገረ የሚመስል ማንጸሪያ ያስቀምጣሉ፡፡ ይህ የDundes (2009, 1032) ዕይታ በአንድ በኩል ሚት ራሱ ውስብስብነት ባሕርይ ያለው መኾኑን አስረጅ ሲኾን በሌላ ገጽታው ደግሞ ውስበስብ ለኾነው ዓለም ያለውን መላ ሰጪነት አረጋጋጭ ነው፡፡

ሚት ስለ ኬት መጣነት ስለ ልዕለ ተፈጥሮ እና ስለ ተፈጥሮ የማተት ትልቅ ዐቅም እና ባህርይ አለው፡፡ ይህ ባህርይው ዓለማቀፋዊነት ተመሳስሎ እንዲኖረው አስችሎታል፡፡ የበርካታ አገሮች ሚት በሚያነሡት የልዕለ ተፈጥሮ ጉዳይና ለማኅበረሰቡ በሚያስተላልፉት

ጭብጥ መለኪያ የሚስማሙና የሚደጋገፉ ናቸው። ለምሳሌ የግሪክ፣ የሮም፣ የግብጽ፣ የሱሜሪያ፣ የባቢሎኒያና የሔብሪው ሚቶች በትይዩ የሚራመዱ እና የሚዛመዱ ትርጓሜዎች አሏቸው (Morford, Mark P.O እና Lenardon, Robert J 2003, 51)::

እንደነ Dundes (2009) እና Lenardon, Robert J, (2003, 52) አተያይ ደግሞ ሚት ለበቀለበት ማኅበረሰብ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ፍልስፍና እና ዕሴት ተገዥ ከመኾኑ በተጨማሪ የጠበቀ ቁርኝትም አለው ይላሉ። ይህ ማጠንጠኛ ሐሳብ ሚት የአካባቢውን ባህል መሠረት በማድረግ ስለ ነገረ ተፈጥሮ የሚያትትና መልስ ለመስጠት ጥረት የሚያደርግ መኾኑን ያስገነዝባል። ሚት አንድ ማኅበረሰብ ስለ አምላኩ፣ ስለ ጥንተ አመጣጡ፣ ስለ አካባበቢው፣ ስለ ቀደመው ዓለምና ከሞት በኋላ ስለሚኖረው የሕይወት እጣ ፈንታ እንደየ ሚቶቹ በተጠየቅ እና በአመክንዮ ባይኾንም በተአምኖ እና በሐልዮ መልስ የሚሰጥ መኾኑን ያጸናል።

Huskinson, (2008, 8) እና Merkur (2005, 15) "ሚት ከማኅበረሰባዊ ፋይዳው አንጻር የረቀቀውን በማጉላት፣ የራቀውን በማቅረብ እና የተሰወረውን በመግለጥ የተረጋጋ ማኅበረሰብ እንዲፈጠር ያደርጋል" ይላሉ። እንደዚሁም Dundes (92009, 1032) እና Huskinson, (2008, 8) ሚት በክብረ በዓል፣ በሃይማኖትና በባህል ውስጥ መነሻም መድረሻም በመኾን የተወሳሰበውን ዓለም (Distort world) ለመግራት ጥረት ያደርጋል ካሉ በኋላ በዚህም የሰው ልጆች ከአምላካቸው ጋራ ስለሚኖራቸው ግንኙነት እና ስለ ነገረ ተፈጥሮ ፍንጭ ይሰጣል ይላሉ።

የተመራማሪዎቹ ዕይታዎች ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታዩ ሚት በአንድ በኩል ዓለማቀፋዊነት ይዘት ያለው ሲኾን በሌላኛው በኩል ደግሞ ለባህል እና ዕሴት ተገዥ መኾኑን የሚያስረዱ ናቸው። ስለኾነም ሚት አንድም ዓለማቀፋዊ አንድም ለባህል እና ዕሴት ተገዥ ነው ማለት ይቻላል። በተለይ በሃይማትኖታዊ ክብረ በዓል እና በሚት መካከል ካላቸው የቅርብ ተራክቦ አኳያ ድንበር ማበጀት እና ነጣጥሎ መመልከት አይቻልም (Dorson 2006, 109):: እንደ ፎክሎር፣ ሃይማኖት፣ ሥነ ጽሑፍ፣ ሥነ ሰብእ እና መሰል የትምህርት መስኮች ሚት ንድፈ ሐሳብን ለሥራዎቻቸው መመልከቻ ያውሉታል። የዚህ ጥናት ዋና ጉዳይ የኾነው የጥምቀት ከብረ በዓልም ከሚት ጋራ የጠበቀ ቁርኝት አለው። በመኾኑም ለጥምቀት ክብረ በዓል መመልከቻ ተግባራዊ ተደርጓል።

### 2.2.4. የሥነ ፍካሬ (Hermenetics) ንድፈ ሐሳብ

ሥነ ፍካሬ የሚለው ቃል Hermes ከሚለው የግሪክ ቃል የተወሰደ ነው፡፡ ትርጉሙም "የትልቅ ትልቅ" ማለት ነው Stavish (205, 2)፡፡ እንደ Stavish (205, 2) ዕይታ የሥነ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ የጥንታዊ አውሮፓ እና የመካከለኛው ኤዥያን ሃይማኖታዊ ምስጢራት፣ ጥንታዊ ዕውቀት የሚመራመሩ ጠቢባን ግለ ሰቦችን ይመለከታል ካሉ በኋላ እነዚህ ግለሰቦች ከፊት ኹነው ሕዝቡን በዕውቀት ጎዳና የሚመሩ ፈላስፎች እና ሊቃውንት ናቸው ይላሉ፡፡

የሥነ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ በእውኑ ዓለም የሚኖር እና በታሪክ የሚታወቅን ጠቢብ ይመለከታል፡፡ ይህ ጠቢብ ስለ እሱ የሚነገሩ አፈ ታሪካዊና ምልኪያዊ ታሪኮች ባለቤት ነው፡፡ ስለ ግለሰቡ የዕውቀት ጣሪያ የሚመሰክሩለት በእጁ የተከተቡ መዛግብት እና በአንደበቱ የተነገሩ ቃላት ናቸው፡፡ በጥንታዊት ግብጽና በጥንታዊት ግሪክ ከፍተኛ ክብር ያላቸው ስለ ቀደምት ባህል ጸሐፍት እና ተርጓሚ የኾኑ ታላላቅ ሰዎቸ ነበሩ፡፡ ስለ እነዚህ ታላላቅ ሰዎች (Colton Swabb 2018, 2) ሲያስረዱ "የእነዚህ ሰዎች ሰብእና ከአፍአዊነት ይልቅ አርምሞት፣ ከሥጋዊነት ይልቅ መንፈሳዊነት ስለሚሰማቸው በሥራዎቻቸው ላይ ስማቸውን አይገልጹም ነበር፡፡ ከእነዚህ መካከል የግብጽ ካህናት፣ የግሪክ ፈላስፎች እና ጸሐፍት ተጠቃሾች ናቸው" የሚል መረጋገጫ ይሰጣሉ:፡ Stavish (2005, 2) በበኩላቸው ደግሞ "በአይሁዶች እና ክርስቲያኖች እምነት ውስጥ ሙሴ፣ አብርሃም እና ቅዱስ ዮሐንስ ባላቸው የላቀ ዕውቀት እና ጸጋ ምክንያት ከታላላቅ መንፈሳውያን ተርታ ይመደባሉ" በማለት ሐሳባቸውን ይገልጻሉ፡፡ እንደዚኹም Colton Swabb (2018, 4) የStavishን ሐሳብ በሚደግፍ መልኩ ሥነ ፍካሬ ከዘመኑ ራቅ እና ላቅ ያለ የአስተሳሰብ ልዕልና ያላቸውን ተፅኖ ፈጣሪ ልሂቃንን ይመለከታል ይላሉ፡፡ ለዚህም እንደነ (*Leonardo Da Vinci* እና *Self-Portrait)* ያሉ ግለሰቦች በማንጸሪያነት ይጠቅሳሉ፡፡ አክለውም "ሥነ ፍካሬ የሐሳብ እና የሕገጋት ትምህርት ቤት ነው[29] በማለት የንድፈ ሐሳቡን የዕውቀት መፍለቂያነት ያስረዳሉ፡፡

በሌላ መልኩ ሔርሜስ የሚለው ቃል ከምድራዉያን ጠቢባን ላቅ እና ራቅ ባለ መልኩ የጥንታውያኑን የግሪክን እና የግብጽን አማልክት ይወክላል፡፡ በግሪክ ውስጥ ሔርሜስ በምልኪ ደረጃ የሚነገር እና በውኑ ዓለም በታሪክ የማይታወቅ የጥበብ አምላክ ነው፡፡ የግሪኩ አምላክ ሔርሜስ እና የግብጹ ቶት ተመሳሳይ ሥልጣን እና አማልክታዊ ጠባይ አላቸው፡፡

---

[29] *"Hermeticism is a school of ideas and systems" (Colton Swabb 2018, 4).*

ከታላላቅ አማልክቶቻቸው መካከል ጥንታዊ ግሪኮች ሔርሜስ የተባለውን የጥበብ አምላክ ብለው ይቀበሉታል፡፡ ጥንታዊ ግብጾች ደግሞ ቶትን የጥበብ መገኛ ብለው ያምናሉ (Cole, 210, 4)፡፡ በዚህ መልኩ ሔርሜስ እና ቶት አንድም ሥግው፣ አንድም አማልከት ጠባይ ያላቸው ተደርገው ይወሰዱ ነበር፡፡ ይኹን እንጂ ሰብእም ይኹን አማልክት የሔርምስ እና ቶት ማጠንጠኛ ጉዳይ ከነባሩ ሰው ላቅ ያለ የጥበብ እና ዕውቀት መገኛ መኾናቸው ነው፡፡ በዚህ መልኩ የሥነ ፍካሬ ንደፈ ሐሳብ የአንድን ማኅበረሰብ የሕይወት ምስጢራት ከዘመን፣ ከጊዜ፣ ከሃይማኖት እና ከባህል ዕሳቤ ጋራ አጣጥሞ ለመረዳት ያስችላል (Cole, 210, 4)፡፡

የሥነ ፍካሬ ንደፈ ሐሳብ ከክርስቶስ ልደት በፊት ጀምሮ በግሪክ፣ በሮም፣ በግብጽ እና መሰል ሃይማኖታዊና መንግሥታዊ ሥልጣኔ በነበራቸው ሀገራት ተግበራዊ ይደረግ ነበር፡፡ ከክርስትና በፊት የነበሩት ሃይማኖታዊ ዶግማዎች፣ ቀኖናዎች እና ዕሳቤዎችም ይፈከሩበት ነበር፡፡ በዚህ መልኩ ለትውፊት፣ ለትእምርት፣ ለፈሊጣዊ ትርጉም፣ ለሀገር በቀል ዕውቀቶች መመልከቻ በመኾን አገልግሏል Mark (2010, 3)፡፡

እንደዚሁም Colton Swabb (2, 2018) ሲያስረዱ የሥነ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ ስለ ተፈጥሮ፣ ስለ አምላክ፣ ስለ ሕይወት፣ ስለ ሞት፣ ስለ ፈጣሪ ስለ ፍጥረታት አጠቃላይ አንድ ማኅበረሰብ በዙሪው ስለሚኖሩ እና ከሱ ርቀው ለሚኖሩ ጥያቄዎች ትርጓሜ ለማግኘት ያስችላል ይላሉ፡፡ Stavish (205, 7) በበኩላቸው ደግሞ ይህንኑ ሐሳብ በመደገፍ የሥነ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ ዋነኛ ጉዳይ ሐሳብን መተንተን፣ መተርጎም፣ ድብቅና ረቂቅ ዕውቀትን በግለሰቦች አእምሮ ውስጥ ማሥረጽ ነው፡፡ በዚህም ጥንታዊውና ዘመናዊው ዕሳቤ በፍልስፍና፣ በትርጓሜ እና በፍካሬ የሚሰናሰልበት ማሕቀፍ ነው የሚል አጽንዖት አላቸው፡፡

ይህ ንደፈ ሐሳብ በጥምቀት ክብረ በዓል ውስጥ ስለ ጥምቀት የሚነገሩትን ምልኪያዊ ታሪኮች፣ የሊቃውንቱን ክዋኔ እና ሀገረሰባዊ ልማዶች ለመረዳት ያስችላል፡፡ በተጨማሪም በክብረ በዓሉ ዐውድ የሚከወኑትን ሥነ ቃሎች፣ የሚቀነቀኑትን ትውን ጥበባት፣ የክብረ በዓሉን ንዋየ ቅድሳት፣ ባህላዊ አልባሳት፣ የመዋቢያ ጌጣጌጦች አጠቃላይ የጥምቀትን ክብረ በዓል ክዋኔ ትርጉም እና ፍካሬ ለማወቅ እና ለመተንተን የሚያስችል ንደፈ ሐሳብ ነው፡፡ በመኾኑም የሥነ ፍካሬ ንድፈ ሐሳብ ለዚህ ጥናት መመልከቻ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

### 2.3. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጥምቀት ክብረ በዓል ከፋይዳዎቹ ጋራ አያይዞ የተጠና ጥናት ባደረግኩት የቤተ መጻሕፍት ዳሠሣ አላገኘሁም፡፡ ይኹን እንጂ በክብረ በዓል ላይ የተሠሩ ሥራዎች ከዚህ ጥናት ጋራ የአንድ ወገን ዝምድና ያላቸው በመኾኑ ዳሠሣ ተደርጎባቸዋል፡፡

የሦስተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፎች እና የኤም.ኤ መመረቂያ ጽሑፍ ጥናቶች በፊደል ተራ ቅደም ተከተል መሠረት መጀመሪያ የሦስተኛ ድግሪ እና በማስቀጠል የኤምኤ. ድግሪ መመረቂያ ጽሑፎች በደረጃ ተቃኝተዋል፡፡ እንደዚሁም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ተመሥርተው ስለ ቤተ ክርስቲያኗ አስተምህሮ፣ ስለ ጥምቀት፣ ስለ ሕጋጋተ ቤተ ክርስቲያንና መሰል ጉዳዮች የሚያጠነጥኑ ድርሳናት ላይ ደሠሣ ተደርጎባቸዋል፡፡

ሙሉጌታ ነጋሣ "Documentation and analysis of Ritual performance of Sera Gada among the Karrayu Oromo" በሚል ርእስ በሥነ ልሳን ትምህርት ክፍል የPhD መመረቂያ ጽሑፍ (Dissertation) በ2014 ዓ.ም አዘጋጅተዋል፡፡ የጥናቱ ዓላማ በዋናነት የከረዩ ኦሮሞ የSera Gada ክብረ በዓልን መተንተን እና ዶክመንቴሽን ማድረግ ነው፡፡

ሙሉጌታ ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አኳያ Ethnographic approachን በዋናነት ተጥቅመዋል፡፡ የመረጡበትን ምክንያት ሲያስረዱ ደግሞ Ethnographic approach የማኅበረሰቡን ባህል፣ ዕሴት ፍልስፍናና መዋቅር ለመረዳት፣ ለማወቅና ለመተንተን አስቻይ በመኾኑ ነው የሚል ማረጋገጫ ይሰጣሉ፡፡ እንደዚሁም Ethnographic approach ከማኅበረሰቡ ውስጥ ኾኖ (emic perspective point of view) ክብረ በዓሉን ለማየት እንዳስቻላቸው በጥናታቸው አውስተዋል፡፡ የሙሉጌታ ጥናት ዐይነታዊ ሲኾን የተሳትፎ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይቶችን በመጠቀም በተፈጥሮ ዐውድ መረጃ ለመሰብሰብ ችለዋል፡፡ ሙሉጌታ ስለ Documentation እና Ritual ጽንሰ ሐሳቦች እንደነ Salmone, Zartman እና Schibrack ያሉ የመስኩ ተመራማሪዎችን ሥራዎች በማጣቀሻነት በማንሣት ሰፋ እና ዘርዘር ያለ ቅኝት አድርገዋል፡፡ ሙሉጌታ በዚህ ጥናታቸው ስለ ከረዩ ኦሮሞ ማኅበረ ባህል ስልት እና የSera Gada ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ላይ ጥልቅ ትንታኔ አካኺደዋል፡፡

ሙሉጌታ በSera Gada ውስጥ የሚገኙት ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ወታደራዊ እና ሃይማኖታዊ አደረጃጀቶች ለማኅበረሰባዊ ፋይዳ ወሳኝ ሚና ያላቸው መኾኑን በጥናታቸው ግኝት አረጋግጠዋል፡፡ በጥናታቸው መጨረሻ ክፍል ለSera Gada ባህላዊ ሥርዐት በአገር ደረጃ፣ በመንግሥት፣ በአካባቢዎች በባለሥልጣናት እና በባለድርሻ አካላት ተገቢው ድጋፍ እየተደረገ አለመኾኑን አመላክተዋል፡፡ የሙሉጌታ ጥናት የክብረ በዓል ክዋኔ ላይ መመሥረቱ እና ተፈጥሯዊ መቼትን ተከትሎ መጠናቱ ከእኔ ጥናት ጋራ በመጠኑ ያመሳስለዋል፡፡ በርእሰ ጉዳይ በጥናት ቦታና በጥናት የትኩረት አቅጣጫ ደግሞ ከኔ ጥናት ጋራ የተለየ ያደርገዋል፡፡

ኹለተኛው ዳሠሣ የተካኼደበት ጥናት የዘላለም አበበ ጥናት ነው፡፡ ዘላለም "የቃሉ ሃይማኖታዊ ከበራዎችና ፋይዳዎቻቸው በጉጂ ኦሮሞ" በሚል ርእስ በ2008 ዓ.ም በፎክሎር የሦስተኛ ዲግሪ መመረቂያ ጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ ዘላለም ለጥናታቸው አነሣሽ ምክንያት ብለው የጠቀሱት አንደኛው የቃሉ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎችና ፋይዳዎቻቸው በጉጂ ኦሮሞ ከዚህ በፊት በውል ያልተጠኑ መኾናቸው እና ለዘርፉ ትኩረት ለመስጠት ከመፈለግ እንደኾነ ገልጸዋል፡፡ እነደዚኹም በኹለተኛ ደረጃ ያነሡት አነሣሽ ምክንያት ደግሞ የቃሉን ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል እና ፋይዳዎቻቸውን በጉጂ ኦሮሞ በማጥናት የማኅበረሰቡን ዕሴት ለማውጣት አና ለማሳየት ከመፈለግ ነው ይላሉ፡፡ የዘላለም ጥናት ዋና ዓላማ በጉጂ ኦሮሞ የቃሉ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎችን በመተንተን ያላቸውን ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ሥነ ልቡናዊ ፋይዳዎችን ለማሳየት ያለመ ነው፡፡

ዘላለም ለጥናታቸው ኢትኖግራፊያዊ[30] የአጠናን ስልትን መርጠው ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ ለዚህ አንደምክንያት የሚያነሡት የማኅበረሰቡን መስተጋብር፣ የማኅበረሰቡን ወግ፣ ባህል፣ ልማድ፣ አስተሳሰቦቻቸውንና ስሜታቸውን ለማወቅ ስለሚያስችለኝ ነው የሚል ማጠየቂያ አንሥተዋል፡፡ ዘላለም መረጃን ለመሰብሰብ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት የተባሉትን ዘዴዎች በጥምረት ተጠቅመዋል፡፡ ዘላለም ምልከታ የተባለውን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለሦስት ጊዜ የተጠቀሙ ሲኾን በመጀመሪያው ዙር ከአማካሪያቸው ከአቶ ሞከና እና ከቃሉ ጋራ በመኾን ከ29/11/2006 እስከ 12/12/ 2006 ዓ.ም ድረስ ለኹለት ሳምንታት ያክል በቦታው በመገኘት የምልከታ ትግበራ አካኺደዋል፡፡ በምልከታ ያገኟቸውን

[30] ይህን ቃል የሙሉጌታ ጥናት ላይ በእንግሊዘኛ እና ከዘላለም ጥናት ላይ ደግሞ በአማርኛ የገለጽኩት ጥናቶቹ ከተጠኑባቸው ቋንቋ በመነሳት ነው፡፡

መረጃዎች በካሜራና በመቅረፀ ድምፅ ሰብስበዋል፡፡ ከዚህ በመቀጠል ለኹለተኛ ጊዜ የዩኒቨርሲቲውን የትብብር ደብዳቤ በመያዝ ለ20 ቀናት የሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎችን ሥርዓቶች በምልከታ መረጃ ለመሰብሰብ ችለዋል፡፡ በመጨረሻም በ2008 ዓ.ም ደግሞ የተካኼደውን የገዳ ሥርዐት ርክክብ በቦታው በመገኘት የምልከታ ተግባር አካኺደዋል፡፡

ኹለተኛው የዘላለም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ ታላሚ የናሙና ዘዴን በመጠቀም ከተተኳሪ መረጃ ሰጪዎችና ከሽማግሌዎች በቃለ መጠይቅ መረጃ ሰብስበዋል፡፡ የቃሉ አጎት የኾኑትን አቶ ሙካና ነገኦን በቃሉ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎች ስለሚከወኑና ስለሚጨፈሩ ቋጠላ፣ ማልጊቾ፣ ሳማጤ፣ ቃሉ ቢፊ በመሳሰሉት የጸሎትና የምርቃት ሥርዐቶች ላይ ቃለ ጠይቅ በማድረግ መረጃ ለመሰብሰብ ችለዋል፡፡ እንደዚኹም ዘላለም ተተኳሪ የቡድን ውይይት በታላሚ ናሙና እና በጥቁም ናሙና ዘዴ በመጠቀም ሴቶችን፣ የሀገር ሽማግሌዎችን፣ አባ ገዳዎችን እና የቃሉ አማካሪዎችን የያዘ አምስት አባላት እና ሰባት አባላት ያሉት በድምሩ ኹለት የቡድን ውይይት አደራጂተው በቪድዮ እና በመቅረጸ ድምጽ መረጃ ሰብስበዋል፡፡ ዘላላም በጥናታቸው 60 መረጃ ሰጪዎችን አሳትፈዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል 52 ወንዶች ሲኾኑ ቀሪዎቹ 8 ደግሞ ሴቶች ናቸው፡፡ ዘላለም ለመረጃ መሰብሰቢያ በዋናነት ተፈጥሮአዊ መቼትን ተጠቅመዋል፡፡ በታካይነት ደግሞ እንደ ሁሉቃ ያሉ ክብረ በዓሎችን በሰው ሰራሽ መቼት መረጃ ለመሰብሰብ ችለዋል፡፡

ዘላለም ቃሉ፣ የቃሉ ኦሮሞ፣ የቃሉ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓሎች፣ የቃሉ ክብረ በዓሎች ለውጥና ቀጣይነት በሚሉት አርእስት ተመሥርተው ትንታኔ አካኺደዋል፡፡ የዘላለም ጥናት ግኝት እንደሚያስረዳው የቃሉ ክብረ በዓል ዲሞክራሲያዊ ሥርዐትን በማሳደግ የትውፊቱ ባለቤት የኾኑት ማኅበረሰቦች አንድነታቸውን ጠብቀው እንዲቆዩ ያስቻለ ነው የሚል መደምደሚያ አለው፡፡

የዘላለም ጥናት ምልከታን፣ ቃለ መጠይቅን፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይትን እና የተፈጥሮ መቼትን በመጠቀም በመረጃ አሰባሰብ ዘዴ ከኔ ጥናት ጋራ የሚያመሳስለው ነው፡፡ በተጨማሪም በክብረ በዓል ላይ ተመሥርተው ጥናት ማካኼዳቸው እና የክብረ በዓሉን ፋይዳ ማሳየታቸው ከኔ ጥናት ጋራ በመጠኑ ያመሳስለዋል፡፡ በሌላ መልኩ በጥናት ርእሰ ጉዳይ፣ በጥናት ቦታ፣ በጥናት ጊዜ እና በትንታኔ ስልት ደግሞ ከኔ ጥናት ጋራ የተለየ ያደርገዋል፡፡

ቀጣይ የሚዳሰሰው ምርምር የመሶበወርቅ ቅጣው ጥናት ነው፡፡ መሶበወርቅ “የገና ክብረ በዓል በላሊበላ” በሚል ርእስ በ1997 ዓ.ም በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በፎክሎር የኤም.ኤ ድግሪ ለማግኘት መመረቂያ ጥናት አዘጋጅተዋል፡፡ የመሶበወርቅ ጥናት ዋና ዓላማ በላሊበላ የሚከበረውን የገና ክብረ በዓል በፎቶ ግራፍ፣ በመቅረጽ ድምጽ እና በጽሑፍ በመቅረስ ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፍ ማድረግ የሚል ነው፡፡ በዝርዝር ዓላማቸው ደግሞ የክብረ በዓሉን ታሪካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ገጽታ ማጥናት እንደኾነ አመላክተዋል፡፡

መሶበወርቅ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ለጥናታቸው ተጠቅመዋል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ደግሞ ምልከታን ቃለ መጠይቅ እና መጠይቅ (questionnaire) የተባሉትን የመረጃ መሰብሰቢ ዘዴዎች ተጠቅመዋል፡፡ መሶበወርቅ በ1996 እና በ1997 ዓመታት በኹለት ዙር ወደ መስክ በመውጣት መረጃ ሰበብስበዋል፡፡ በመጀመሪያው ዙር በታኅሣሥ ወር 1996 ዓ.ም ወደ መስክ ወጥተዋል፡፡ በመጀመሪያው የመስክ ስራ 113 ሰዎችን ስለ ክብረ በዓሉ ቃለ መጠይቅ አድርገዋል፡፡ መሶበወርቅ በ1997 ዓ.ም በታኅሣሥ ወር ደግሞ ኹለተኛውን የመስክ ተግባር አከናውነዋል፡፡ በኹለተኛው ዙር ለ110 ተጠኚዎች ቃለ መጠይቅ ያካኼዱ ሲኾን በድምሩ 223 ተጠኚዎችን በቃለ መጠይቅ አሳትፈዋል፡፡

መሶበወርቅ በጥናታቸው የገና በዓልን ታሪካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ላይ በመመሥረት ትንታኔ አካኺደዋል፡፡ በጥናታቸው ግኝትም የገና በዓል አወንታዊ የኾነ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ያለው መኾኑን አሳይተዋል፡፡ የመሶበወርቅ ጥናት ትንታኔ በክብረ በዓሉ ክዋኔ ላይ በተቀነቀኑት ቃል ግጥሞቻ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ የቃል ግጥሞቹ ዘውግ ደግሞ የላሊበላ ሳሚ ቃል ግጥሞች ሲኾኑ የልመና፣ የምህላ፣ እና በአብዛኛው በእናቶች የሚከወኑትን የሚመለከት ነው፡፡ ከዚህ ባለፈ የገና ክብረ በዓል በሌሎች ማኅበረሰብ ክፍሎች የሚደረጉትን ክዋኔዎች እና ተሳትፎዎች እንደዚኹም የገና ክብረ በዓል ማክበሪያ ቁሳዊ ባህሎች፣ አልባሳት፣ መጊያጊያጫ፣ ንዋዬ ቅድሳት፣ ልማድ እና ትውን ጥባበት የሚሉትን የክብረ በዓል ዘውጎች ላይ ትኩረት ሰጥተው ትንታኔ አላካኼዱም፡፡ የመሶበወርቅ ጥናት በሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ላይ መሠራቱ እና ማኅበራዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ላይ መመሥረቱ ከዚህ ጥናት ጋራ መጠነኛ ተመሳሰሎ እንዲኖረው

አድርጎታል፡፡ እንደዚኹም በአጠናን ዘዴ፣ ቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን መጠቀማቸው ከኔ ጥናት ጋራ እንዲመሳሰል ያደርገዋል፡፡

በጥናት ልዩነት ሲነሣ ደግሞ የኔ ጥናት የጥምቀትን ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ እና ፋይዳ ለማሣየት የዐለመ እንጂ መቅረስ ዋና ዓላማ አድርጎ ባለመነሣቱ በጥናት ዓላማ ከመሶበወርቅ ጥናት ጋራ ይለያል፡፡ እንደዚሁም የመሶበወርቅ ጥናት መጠይቅን (questionnare) መጠቀሙ ከፎክሎር መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ አኳያ ተገቢነት ያለው ባለመኾኑ በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ከኔ ጥናት ጋራ ይለያል፡፡ የመሶበወርቅ ትንታኔ ክብረ በዓሉ ቃል ግጥም ላይ ሚዛን የደፋ ሲኾን ስለ ለውጥና ቀጣይነትም ጭምር የሚዳሠሥ ነው፡፡ የኔ ጥናት ደግሞ በክብረ በዓሉ ዐውድ እና ከክብረ በዓሉ ውጭ የሚተረኩት ሚቶች ላይ ተመሥርቶ ክዋኔውን እና ፋይዳውን እንደዚኹም አንድምታውን የሚያሣይ ነው፡፡ በመኾኑም የእኔ ጥናት በቦታ፣ በርእሰ ጉዳይ፣ በጊዜ፣ በዓላማ፣ በመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ በትንታኔ እና በጥናት ግኝት ከመሶበ ወርቅ ጥናት ጋራ የተለየ ያደርገዋል፡፡

ሌላው ሰሎሞን ደርቤ በ2000 ዓ.ም "የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል አከባበር" በሚል ርእስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በፎክሎር የኤም.ኤ ድግሪ ለማግኘት መመረቂያ ጽሑፍ አዘጋጅተዋል፡፡ ይህ ጥናት ትኩረት አድርጎ የተነሣው በዝቋላ አቦ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን ክብረ በዓል ነው፡፡ ጥናቱ በዋናነት በጥቅምት እና በመጋቢት አቦ ክብረ በዓላት ላይ ተመሥርቶ የተጠና ነው፡፡ ሰሎሞን ከሃይማኖታዊ ክብረ በዓሉ ባለፈ በሀገረሰባዊ ልማዶች ላይም ጥናት አካኺደዋል፡፡ የአቡዬ ወንበር እና የሰይጣን መቃብር የጥናቱ ዋና ማጠንጠኛ ጉዳዮች በመኾን ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ ሰሎሞን በጥናታቸው የክብረ በዓላትን ምንነት፣ ጠቀሜታና ፋይዳዎች ለማሣየት ሞክረዋል፡፡ ጥናቱ በክብረ በዓላት ላይ መመርኮዙ ከኔ ጥናት ጋራ በመጠኑ ያመሳስለዋል፡፡ የሰሎሞን ጥናት በርእሰ ጉዳይ፣ በጥናት ዘውግ፣ በጥናት ግኝት እና መቼት ደግሞ ከኔ ጥናት ጋራ የተለየ ነው፡፡

ቀጥሎ የሚታየው የተስፋዬ ሞላ ጥናት ነው፡፡ ተስፋዬ "የክብረ በዓላት ሥርዐተ ማሕሌት ተግባር" በሚል ርእስ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል በፎክሎር የኤም.ኤ ድግሪ ለማግኘት በ2003 ዓ.ም የመመረቂያ ጽሑፍ አዘጋጅተዋል፡፡ የተስፋዬ ጥናት ዓላማ የክብረ በዓላትን ሥርዐተ ማሕሌት ክዋኔ ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳየት ሲኾን ጥናቱ

በመኼካሄድበት አካባቢ ያለውን ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስተጋብሮቹን አብረው ዳሠሣ አድርገዋል፡፡ የተስፋዬ ጥናት በኮረም አካባቢ ተመሥርቶ የተጠና ነው፡፡ አጥኚው በቅዱስ ጊዮርጊስ እና በቅድስት ማርያም ክብረ በዓላት ላይ በመወሰን በዋዜማና በክብረ በዓሉ ዕለት በቦታው በመገኘት መረጃ ሰብስበዋል፡፡ በመረጃ አሰባሰብ ወቅት ምልከታና ቃለ መጠይቅ ዘዴዎችን ተግባራዊ አድርገዋል፡፡ ተስፋዬ በምልከታ ኮረም በመኼድ በተፈጥሮ መቼት ከሚያዝያ 08/08/2003 እስከ ግንቦት 08/09/2003 ድረስ በፎቶ ካሜራና በቢድዮ ካሜራ መረጃ ሰብስበዋል፡፡ ተስፋዬ ለጥናታቸው የመረጡት የናሙና ዘዴ ዓላማ ተኮር ነው፡፡ በዓላማ ተኮር ንሞና በዘርፉ የጠለቀ ዕውቀት ያላቸውን እና ማኅበራዊ ደረጃቸው ከፍ ያሉትን 15 የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ አባቶች በመምረጥ በቃለ መጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ ችለዋል፡፡ የተስፋዬ ጥናት ግኝት ከቤተ ክርሰቲያኗ ሥርዓተ ማሕሌትና የማሕሌት መገልገያ ንዋየ ቅድሳትን ምንነት እና የተሸከሙትን ውክልና አመላክተዋል፡፡

የተስፋዬን ጥናት በክብረ በዓል ላይ መመሥረቱ ከኔ ጥናት ጋራ የሚያመሳስለው መጠነኛ ነጥብ ነው፡፡ እንደዚኹም በመረጃ አሰባሰብ ኺደት በዘርፉ የጠለቀ ዕውቀት ያላቸውን መረጃ ሰጪዎች መጠቀማቸው ከዚህ ጥናት ጋራ በመረጃ አሰባሰብ ዘዴ መጠነኛ ተመሳስሎ ይታይበታል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ጥናቱ በማሕሌት ላይ ብቻ ማተኮሩ፣ የክብረ በዓሉን አጠቃላይ ክዋኔ አለመመልከቱ ደግሞ ከኔ ጥናት ጋራ የተለየ ያደርገዋል፡፡ በመኾኑም የተስፋዬ ጥናት በጥናት ዘውግና በጥናት ዐውድ ከኔ ጥናት ጋራ የተለየ ያደርገዋል፡፡

**ዋለልኝ እምሩ** "The daynamic of religios rituals and secular cerimonies in public place of Addis Ababa (Spatial tempolar and symbolic Aspects)" **በሚል ርእስ በ**social anthropology **ትምህርት ክፍል በ**2003 **ዓ.ም የኤም.ኤ. መመረቂያ ጽሑፍ** አቅርበዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ የጥምቀት እና መስቀልን ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት በክብረ በዓሉ ወቅት ያለውን ትእምርት በመመርመር ያላቸውን ፋይዳ ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ዋለልኝ በክብረ በዓሉ ቦታ በመገኘት በዐውድ ተመሥርተው መረጃ ሰብስበዋል፡፡ በእነዚህ መስቀል እና ጥምቀት ኹለት ክብረ በዓሎች የተገኘውን መረጃ በዐይነታዊ ዘዴ ትንታኔ ሰጥተዋል፡፡ በትንታኔቸውም የክብረ በዓሎቹን ማኅበራዊ እና ባህላዊ ጠቀሜታዎች

አመላክተዋል፡፡ የጥናታው ግኝትም የጥምቀት እና የመስቀል ክብረ በዓሎች ማኅበራዊ አና ባህላዊ ጠቀሜታዎች ያሏቸው መኾኑን ያረጋገጠ ነው፡፡

የዋለልኝ ጥናት የጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ተመሥርቶ መጠናቱ በአንድ ጎን በርእሰ ጉዳይ መጠነኛ ተመሳስሎ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ እንደዚኹም የተፈጥሮ መቼትን ተጠቅመው መረጃ መሰብሰባቸው ከኔ ጥናት ጋራ መጠነኛ ተመሳስሎ እንዲኖረው አስችሎታል፡፡ የዋለልኝ ጥናት መስቀል ላይ መመሥረቱ እና መጠናቱ ደግሞ በርእሰ ጉዳይ ከኔ ጥናት ጋራ የተለየ ያደርገዋል፡፡ እንደዚኹም የዋለልኝ ጥናት በጥናት ዘውግ፣ በጥናት ቦታ፣ በጥናት ስልት እና በጥናት ጊዜ ከኔ ጥናት ጋራ የተለየ ነው፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተቃኙት እና በክብረ በዓላት ላይ የተደረጉ ጥናቶች አንድን ክብረ በዓል ክዋኔ በመምረጥ በዚያው በክብረ በዓሉ ክዋኔ ላይ መረጣ በማድረግ መጠነኛ ጉዳዮች ላይ ትንታኔ ማድረግ ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈ ክብረ በዓሎቹን ከክዋኔ ሥርዓት፣ ከከዋኞቹ ማንነት፣ ከማኅበራዊ፣ ከቱሪዝም፣ ከምጣኔ ሀብት፣ ከሰባዊ እና ከአካባቢ ጥበቃ ጋራ አሰናስለው አልተመለከቷቸውም፡፡ የጥናቶቻቸው መነሻ የኾኑትን የክብረ በዓሎቹ ክዋኔ አንድምታዎች ላይ ትኩረት የሰጡባቸው አይመስልም፡፡ እንደዚኹም የተዳሠሡት ጥናቶች ለተጠኑበት ጊዜ ቦታ እና ማኅበረሰብ የዋጁ ናቸው፡፡ ጥናቶቹ ከጊዜ አንጻር ለተጠኑበት የዘመን ዕሳቤ ባለቤቶች በመኾናቸው በመጠኑም ቢኾን ከኔ ጥናት ወደ ኋላ  የቀደሙ ናቸው፡፡ የተቃኙት ጥናቶች  ከቦታ አንጻርም ቢኾን የተጠኑበትን ቦታ መልክዓ ምድር፣ ከአየር ንብረት፣ ከእጽዋት፣ ከአእዋፋት፣ ከወንዞች፣ ከተራሮች፣ ከባሕሮች እና መሰል ከቦታዎች ጋራ ተራክቦ ያለቸው ናቸው፡፡ ስለኾነም ጥናቶቹ ከቦታ አንጻር ከኔ ጥናት ጋራ የተለዩ ናቸው፡፡ ጥናቶቹ ከማኅበረሰብ አኳያ ደግሞ የተጠኑበትን ማኅበረሰብ ዕሳቤ፣ ፍላጎት፣ ፍልስፍና፣ ዕድገት፣ ውድቀት፣ ምኞት፣ ተስፋ  የሚገልጹ ናቸው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተዳሠሡት ጥናቶች በጊዜ፣ በቦታ እና በማኅበረሰብ ከኔ ጥናት ጋራ የተለዩ ናቸው፡፡  ከጥናት የትኩረት አቅጣጫ በተጨማሪ በእነዚህ ሦስት የጊዜ፣ የቦታ እና የማኅበረሰብ መለኪያዎች ሲመዘኑ ከእኔ ጥናት ጋራ በብዙ መልኩ የተለዩ ናቸው፡፡ በመኾኑም የኔ ጥናት ከተቃኙት ጥናቶች ጋራ በብዙ መልኩ ልዩ ያደርገዋል፡፡

ቀጣዩ እና ኹለተኛው በዚህ ጥናት ቅኝት የተደረገባቸው ሥራዎች ስለ ጥምቀት ክብረ በዓላት ምንነት፣ አመጣጥ እና አጠቃላይ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

ላይ ተመሥርተው የተጻፉ መጻሕፍት እና መጽሔቶች ናቸው። እነሱም በደራሲው ወይም ደራሲው ካልታወቀ ደግሞ በጽሑፉ ርእስ በፊደል ተራ ቅደም ተከተል መሠረት እንደሚከተለው ተቃኝተዋል።

የመጀመሪያው ዳሰሳ የተደረገበት ሥራ የሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ "ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት" የሚለው መጽሐፍ ነው። ይህ መጽሐፍ ዐዲስ አበባ፡ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት በ1962 ዓ.ም የታተመ ነው። ደራሲው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ጥምቀት፣ ስለ ገና፣ ስለ ስቅለት፣ ስለ ትንሣኤ እና ስለ መሰል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አስተምህሮዎች ጥልቅና ዝርዝር የኾነ ትንታኔ የሰጡበት መጽሐፍ ነው። ሊቀ ሥልጣናት ሀብተማርያም ወርቅነህ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ድጓ፣ ስለ አቋቋም፣ ስለ ቅኔ፣ ስለ ዝማሬ መዋሥዕት፣ ስለ ቅዳሴ፣ ስለ ቅዱስ ያሬድ ድርሳናት እና መሰል የቤተ ክርስቲያኗ ምስጢራት ላይ ሰፋ ያለ ትንታኔ ሰጥተዋል።

ሌላው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን "መድኀኒት በጥምቀት" በሚል ርእስ በ1959 ዓም የታተመው መጽሐፍ ተጠቃሽ ነው። ይህ መጽሐፍ 45 ገጾች አሉት። መጽሐፉ ስለ ጥምቀት አዳኝነት፣ ስለ ክርስቶስ ልጅነት እና ስለ ጥምቀት እኩልነት የተብራርቶ የቀረበበት ነው። መጽሐፉ ጥምቀት ሀብታምና ድሀን፣ አለቃ እና ምንዝርን የማይለይ መኾኑን ለማስረዳት ክርስቶስ በፍጡሩ በእደ ዮሐንስ መጠመቁን በምሳሌነት ያነሣል። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሰዎች የጥምቀትን ምንነት እና አመጣጥ ተገንዝበው ደግነትን፣ መታዘዝን፣ ከክፉ ሥራ መጠበቅን እና ከኀጢአት መራቅን እንዲለማመዱ በስፋት ይመክራል። መጽሐፉ ስለ መታዘዝ እና መልካምነት ሲያብራራ (ሉቃስ 5፣5-11) ያለውን የወንጌል ቃል በመውሰድ ጴጥሮስ ሌቱን ሙሉ ሲደክም አድሮ አንድም ዓሳ ሳያገኝ መቅረቱን ይገልጻል። ይህ ከንቱ ድካም ክርስቶስ መጥቶ መረብክን በቀኝ በኩል ጣል ሲለው "እንዳዘዝከኝ አደርጋለሁ" በማለት መረቡን በቀኝ በኩል ቢጥልው ለመጎተት እስኪያቅተው ብዙ ዓሳዎች መያዛቸውን በማስረጃነት ያነሣል። በዚህ መልኩ ሰዎች በመታዘዝ፣ በመተሳሰብ እና በመከባባር መሥራት እንዲገባ አጽንኦት ይሰጣል። ይህ መጽሐፍ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የክርስቶስን ጥምቀት መነሻ በማድረግ ሰዎች በመልካም ሥነ ምግባር እንዲታነጹ የሚመክር ነው።

ቀጣዩ ሥራ አበባው ይርጋ "የጥምቀት በዓል ምንነቱ፣ ማኅበረ ባህላዊ ዐውዶቹ እና ፋይዳዎቹ በሚል የተጠና ነው። የጥናቱ ዓላማ የጥምቀትን በዓል ማኅበረ ባባላዊ ዐውዶቹ እና ፋይዳዎቹን መመርመር የሚል ነው። የአበባው ጥናት የሚከተለው ዓይነታዊ ገላጭ የምርምር ዘዴን ሲኖን ከፊል ዝግጁ ቃለ መጠይቅንም ለጥናቱ ተጠቅሟል። ይህ ጥናት የጥምቀት በዓል ምንድን ነው? የጥምቀት በዓል ለምን? መቼ? እና በማን ይከበራል? የጥምቀት በዓል ያለው ማኅበረ ባህላዊ ፋይዳ ምንድን ነው? የሚሉትን የምርምር ጥያቄዎች አካቷል። እነዚህን ጥያቄዎች መሠረት በማድረግ የጥናቱ ርእሶቹም በጥያቄ መልክ የተቀመጡ ናቸው።

የአበባው ጥናት የጥምቀት በዓል በኢትዮጵያ ከሌላው ዓለም በተለየ መልኩ እንደሚከበር በጥናቱ አሳይቷል። እንደዚሁም የአበባበው ጥናት የጥምቀትን እና ሀገረሰባዊ ልመድ አብረው እና ሰምረው እንደሚጓዙ ታቦታቱ በመጠጡበት ቦታ እንደሚመለሱ በማታቀሻነት አስቀምጧል።የአበባው ጥናት የጥምቀት በዓል ዐሁን ባለው ሁኔታ የቀደሞቹ ሥርዓቶች ተቀንሰውበት አዲሶች ደግሞ ታክለውበት ይከበራል የሚል ድምዳሜ ያስቀምጣል። ከዚህ ጋራ በተያያዘ የጥምቀት በዓል ተለያዩ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበረ ፋይዳዎች ያሉት መሆኑን ጥናቱ አመላክቷል።

የአበባው ጥናት የጥምቀት በዓል ምንነቱ፣ ማኅበረ ባህላዊ ዐውዶቹ እና ፋይዳዎቹ በሚል ርእስ የተጠና ነው። ይኹን እንጅ ጥናቱ የቦታ እና የጥናት አድማስ ወሰን የለውም። የአበባው ጥናት በቦታ እና በጥናት ዘውግ አለመወሰኑ ከባህል ጥናት አንጻር ጥያቄ የሚያስነሣ ይመስላል። ይኹን እንጅ ጥናቱ በጃንሜዳ ጥምቀት በዓል ላይ ተመሥርቶ እንደተጠና ይጠቁማል። በመኾኑም የአበባው ጥናት በርእሰ ጉዳይ፣ በከፊል በመረጃ አሰባሰብ ከኔ ጥናት ጋራ ይመሳሰለል። ከዚህ ባለፈ ግን የአበባው ጥናት የጥምቀትን በዓል ክዋኔ እና አንድምታ፣ የተሳትፎ ምልከታ፣ የጥናት ግኝት፣ የጥናት ቦታ የጥናት ርእሰ ጉዳይ ስያሜ እና ትንተና ዘዴ ከኔ ጥናት ጋራ የተለየ ያደርገዋል።

ቀጣዩ ሥራ ክንፈ ገብርኤል አልታየ በ1962 ዓም "ጥምቀት" በሚል ርእስ ያሳተሙት መጽሔት ነው። ክንፈ ገብርኤል አልታዬ በዚህ ሥራቸው ስለ ገሃድ፣ ስለ ሰንበተ ክርስቶስ እና ስለ ጥምቀተ ክርስቶስ ነጥቦችን አንሥተው ትንታኔ ሰጥተውበታል። በዋናነት ስለ ጥምቀተ ክርስቶስ የሰጡት ትንታኔ ጥምቀት ለሰው ልጆች ድኅነት፣ ነጻነት፣ ከፍዳ

መላቀቂያ፣ ሰውና አምላክ መታረቂያ እንደኾነ አብራርተዋል፡፡ አምላክ 99ኙን ነገደ መላእክት ትቶ አንዱን የጠፋውን የሰው ልጅ ሊፈልግ የመጣበት መንገድ ጥምቀት እንደኾነ በሥራቸው አሳይተዋል፡፡ በዚህ መጽሐፍ በጥምቀቱ ዕለት "መጸ ቃል እምደመና ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድዩ ዘአፈቅሮ" ከሰማይ እንዲህ የሚል ቃል መጣ የምወደው ልጀ ይህ ነው፡፡" የሚል የአብ ቃል እና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በርእግብ አምሳል ወርዶ በክርስቶስ ላይ እንደተቀመጠ በመጽሐፉ ተገልጿል፡፡ እነዚህ በጥምቀት ዕለት የተፈጠሩት ክርስቶስ በአካል መንፈስ ቅዱስ በርዕግብ አምሳል እና አብ ደግሞ በቃል በመገናኘታቸው የሰው ልጅ እና አምላክ የታረቁበት ዕለት እንደኾነ መጽሐፉ ያብራራል፡፡ ሌላው በዚህ መጽሐፍ የተጠቀሰው ስለ ነገሥታቱ የጥምቀት አከባበር ነው፡፡ የዐለፉት ነገሥታት እና መንግሥታት በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ይሳተፉ እንደነበር በፎቶግራፍ በማስደገፍ ጭምር አብራርተዋል፡፡ በተለይ በ1961 ዓም ጥር 11 ቀን በተከበረው የጥምቀት በዓል ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ እና የሮማው ሊቀ ጳጳስ እንደተገኙ ይገልጻል፡፡ የሮማው ሊቀ ጳጳስ ባጁስቲንን እና ሌሎችም ሊቃነ ጳጳሳት የጥምቀትን ክብረ በዓል ሲያከብሩ የሚገልጽ ፎቶ ግራፍ ጭምር መጽሔቱ ያሳያል፡፡

ቀጣዩ ዳሠሣ የተደረገበት ሥራ ደግሞ በ2007 ዓም ለሦስተኛ ጊዜ የታተመው "ወንጌል ለልማት" የተሰኘው መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ ሥራ ወንጌል ከሃይማኖታዊ አስተምህሮው በተጨማሪ ለልማት ያለውን ፋይዳ የሚያሳይ ነው፡፡ መጽሐፉ የተመሠረተው ከመስከረም ፩ እስከ ጳጉሜን ፭ ድረስ ያሉትን የመስከረም፣ የጥቅምት፣ የኅዳር፣ የታኅሣሥ፣ የጥር፣ የየካቲት፣ የመጋቢት፣ የሚያዝያ፣ የግንቦት፣ የሠኔ፣ የሐምሌ፣ የነሐሴ እና የጳጉሜን ወራት በኾኑት ምንባባት ላይ ትኩረት ያደረገ ነው፡፡ ይህም ግጻዌ[31] ላይ በመመሥረት በሚነበቡት ወንጌላት ላይ ትንታኔ በመስጠት የልማት ፋይዳዎቻቸውን ማሳየት ላይ የዓለመ ነው፡፡ ስለ ጥምቀት ክብረ በዓል ዓከባበር ጥር ዐሥራ አንድ ቀን መከበሩን ግጻዌው እንደሚያዝ እና ያለው ማኅበራዊ ፋይዳ ላይ ትንታኔ ሰጥቷል፡፡

መጽሐፉ በተለይ ማኅበራዊ ልማት ፋይዳ እና ሰባዊ ልማት ፋይዳ ላይ ትኩረት የሰጠ እና የተዋቀረ ነው፡፡ መጽሐፉ እንዲዘጋጅ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ቤተ ክርስቲያኗ ባለባት የምእመን ኀላፊነት ምክንያት የኤች አይቨ ኤድስን ሥርጭት ለመቀነስ በማሰብ ነው፡፡ በዚህ መነሻ ምክንያት በመጽሐፉ ውስጥ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ጤና ነክ ችግሮችን መፍታት

[31] የአጽዋማት፣ የበዓላት እና በቅዳሴ ጊዜ የምስባክ፣ የግብረ ሐዋርያት፣ የወንጌል እና የፍሬ ቅዳሴ ማውጫ መጽሐፍ ነው፡፡

ላይ በጥልቀት ትንታኔ ተሰጥቷል። በመጽሐፉ ውስጥ ስለ ሥራ፣ ስለ ደግነት፣ ስለ ፍቅር፣ ስለ ጋብቻ፣ ስለ አካባቢ፣ ስለ ንስሐ፣ ስለ ጽድቅ፣ ስለ ኀጢአት፣ ስለ ሃይማኖት፣ ስለ ሰው፣ ስለ ዓለም፣ ስለ ግብረ ገብነት፣ ስለ ይቅር ባይነት እና መሰል ሰባዊ ጉዳዮች ላይ ወንጌልን መሠረት በማድረግ በትንታኔ ተብራርቶ ቀርቧል። ጠቅለል ባለ መልኩ በመጽሐፉ ውስጥ በጥልቀትና በስፋት የተዳሠሡ ጉዳዮች እና ጭብጦች ሲመረመሩ ማኅበረሰቡን በማስተማር ላይ ያተኮሩ እና የተቃኙ ናቸው።

ቀጣዩ ተዳሣሽ ሥራ ዘማርያም ኤፍሬም እና በእደ ማርያም ዳንኤል "የጥምቀት በዓል አከባባር በኢትዮጵያ" በሚል በሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መጽሔት 14ኛ ዓመት፣ ቁ.1፣ ገጽ 5-8 በ1998 ዓ.ም ያሳተሙት መጽሔት ነው። ይህ ሥራ ስለ ኢትዮጵያዉያን የጥምቀት በዓል አከባባር ሰፋ እና ጠለቅ ባለ መልኩ ትንታኔ የተሰጠበት ነው። በትንታኔው ውስጥ ስለ ጥምቀት አመጣጥ እና ስለ ጥምቀት አከባባር ጅማሮ ያትታል። ይህ ሥራ በዋናነት በዐዲስ አበባ ያለውን ጥምቀት አከባባር ሰፋ አድርጎ የዳሠሠ ነው። እንዲኹም እነ የካ ቅዱስ ሚካኤልን፣ ቅዱስ ራጉኤልን እና መሰል ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናትን የዳሠሠ ነው። የዐዲስ አበባን የጥምቀት አከባባር በመጥቀስ ሥርዐቱን እና ወጉን ሳይለቅ እየተከበረ መኾኑን አሳይቷል። በዚህ መልኩ ከእንጦጦ እስከ ጃንሜዳ የነበረውን እና ያለውን የዐዲስ አበባ የጥምቀት አከባባር ሥርዐት የዳሠሠ መጽሔት ነው። ከዚህ በተጨማሪ የጥምቀት በዓል በጎንደር፣ በሸንኮራ እና በመሐል ሜዳ በድምቀት እንደሚከበር መጽሔቱ ያትታል።

የነ ዘማርያም እና በእደ ማርያም ሥራ በዋናናት የኢትዮጵያ የጥምቀት አከባባር በየ ዓመቱ እየተመላላሰ መከበሩ ጥምቀትን እየደጋገሙ ያደርጋሉ የሚለውን ቀኖናዊ ትችት ያነሣል። ለትችቱም ቤተ ክርስቲያኗ በየ ዓመቱ ዐዲስ ጥምቀት እያካኼደች ሳይኾን የክርስቶስን ጥምቀት ሥርዐት ማስታወስ ነው የሚል ሃይማኖታዊ መልስ ይሰጣል። ጽሑፉ በሀገራችን የተለያዩ ቦታዎች የጥምቀት በዓል ከከተራ እስከ ቃና ዘገሊላ ድረስ በድምቀት የሚከበር መኾኑን ይገልጻል። የከተራ ታቦታቱ ከየ መንበረ ክብራቸው ወደ ጥምቀተ አብሕርት መምጣታቸው ኢየሱስ ክርስቶስ በእደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ የመምጣቱ ተምሳሌት መኾኑም በጽሑፉ ተብራርቷል።

ጥምቀት በዋናነት በኢትዮጵያ በድምቀት መከበር የጀመረው በ6ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በዐፄ ገብረ መስቀል ሲኾን ማሕሌታዊውን ቅዱስ ያሬድን ተከትሎ ሊሆን እንደሚችል መጽሔቱ ይጠቁማል፡፡ ጥምቀት ከሃይማኖታዊ ሥሪቱ ባሻገር ለሀገራችን ማኅበረሰቦች የርስ በርስ ግንኙነት፣ ወጣቶች አረጋውያን፣ እናቶች አደባባይ ወጥተው ስሜታቸውን ደስታቸውን እና ስለታቸውን የሚያደርሱበት በዓል እንደኾነ በጥልቀት ያስረዳል፡፡ ለዚህም የሊቃውንቱ "ወተሰዓተ ነገደ"፣ የጎበዙ "ሆታ"፣ የእናቶች "እልልታ" እና የሰንበት መዘምራን "ዝማሬ" የሚሉትን የክብረ በዓሉን ማክበሪያዎች በምሳሌነት፣ በዋቢነት እና በማስረጃነት አቅርቧል፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ይህ ሥራ ስለ ሀገራችን ጥምቀት አከባባር ሰፋ እና ዘርዘር ያለ ትንታኔ የተሰጠበት ነው፡፡

ቀጣዩ "የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2002 ዓ.ም" የሚለው ሥራ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ብዙ የቤተ ክርስቲያኗን ታሪኮች እና ቀኖናዎች እና ስለ ጥምቀት ክብረ በዓል የሚያትት ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ስለ ክርስቶስ ልደት፣ ስለ ጥምቀት፣ ስለ ስቅለት፣ ስለ ትንሣኤ እና መሰል ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ሕግጋት ዘርዘር ያለ መረጃ ይሰጣል፡፡ ጥምቀት ለሰው ልጆች ድኅነት የመጣ ሲኾን ክርስቶስ የማዳን ሥራውን የጀመረበት እንደኾነም መጽሐፉ ያብራራል፡፡ ታቦታቱ ከየ አብያተ ክርስቲያኑ ወደ ወንዝ መውረዳቸው ደግሞ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ በዮሐንስ ለመጠመቅ የመጣውን ለማዘከር እንደኾነ በሰፊው ተገልጿል፡፡

ሌላው ተጠቃሽ ሥራ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን "ጥምቀተ ክርስቶስ" በሚል በ1959 ያሳተመችው መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ስለ ክርስቶስ ልደት እና ስለ ጥምቀት በሰፊው የተዳሠሠበት ሥራ ነው፡፡ ጥምቀተ ክርስቶስ የሚል ርእስ ይዞ የተነሣው መጽሐፉ በዋናነት ስል ክርስቶስ ጥምቀት አዳኝነት ያትታል፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የጥምቀት ዐይነቶችን ጥምቀተ አይሁድ፣ ጥምቀተ ዮሐንስ እና ጥምቀተ ክርስቶስ ብሎ በሦስት ከፋፍሎ ይመለከታቸዋል፡፡ ልዩነታቸውንም ጥምቀተ ዐይሁድ በልዩ ኀጢአት የረከሰውን ሰውነት የሚያነጻ እንጂ ለንስሐ የሚያበቃ አለመኾኑን ያትታል፡፡ እንደዚኹም ስለ ዮሐንስ ጥምቀት ሲያትት ደግሞ የንስሐ ጥምቀት እንጂ ልጅነትን የሚያስገኝ አልነበረም ይላል፡፡ ዮሐንስ በጥምቀቱ ጊዜ "ጎድጓዳው ከፍ ይበል፣ ተራራውና ኮረብታውም ዝቅ ይበል፤ ጠማማውም ይቅና፣ አቀበቱም ሜዳ ይኹን፣ እኔ በውሐ አጠምቃችኊለሁ፤

ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን እሽ ብትሉ በመንፈስ ቅዱስ እምቢብትሉ ደግሞ በእሳት ያጠምቃችኋል፤" እያለ የንስሐ ጥምቀት ያጠምቅ እንደነበር መጽሐፉ ያትታል። የክርስቶስ ጥምቀት ደግሞ ከኹለቱ ከአይሁድ እና ከዮሐንስ የጥምቀት ዐይነቶች በተለየ እና በላቀ መልኩ ኀጢአትን የሚሽር፣ ንስሐን የሚያሰጥ ብቻ ሳይኾን ልጅነትንም ጭምር የሚያስገኝ ጥምቀት እንደኾነ በመጽሐፉ ተብራርቶ ቀርቧል። ጠቅለል ባለ መልኩ ይህ መጽሐፍ የክርስቶስ ጥምቀት የሰው ልጆችን ነጻ ያወጣ፣ ዕዳ ደብዳቤ የሻረ፣ ግዞትና ባርነትን ያስወገደ ነው በማለት ያትታል።

በቀጣይ የተዳሠሠው ጽሑፍ "የጥምቀት በዓል አከባበር በኢትዮጵያ" የሚለው መጽሔት ነው። በዚህ መጽሔት ውስጥ ስለ ጥምቀት ዋዜማ ከተራ ሥርዐት፣ ስለ ዕለተ ጥምቀት፣ በዓሉ ስለሚከበርበት ምክንያት፣ ስለ ጥምቀት በዓል እና ስለ በዓሉ አጀማመር በሚሉት ነጥቦች ላይ በመጽሔቱ ትንታኔ ተሰጥቷል። መጽሔቱ የኢትዮጵያ ጥምቀት በዓል ከከተራ ጀምሮ በደመቀ ኹኔታ ወንዶች፣ ሴቶች፣ ሕፃናት አዛውንት ባህሉ እንደሚፈቅድላቸው እና እንደሚችሉት መጠን የደመቀ ሱታፌ እንደሚያደርጉ ያትታል። በጥምቀት ዕለት የገና ጨዋታ እና የተለያዩ ክዋኔዎች እንደሚደረጉም ያወሳል። የጥምቀት ክብረ በዓል ከክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ውጭ የኾኑትን የማኅበረሰብ ክፍሎች ጭምር እንደሚያከብሩት በመጽሔቱ ተገልጿል። የጥምቀት ክብረ በዓል መነሻው የክርስቶስ መጠመቅ ቢኾንም በተለያዩ የዓለም ሀገራት ለማስታወሻ ያክል ይከበራል እንጂ እንደ ኢትዮጵያ በደመቀ መልኩ የሚከበርበት ሀገር እንደሌለ መጽሔቱ ያትታል። በዚህ ምክንያት የኢትዮጵያ ጥምቀት ለቱሪስት መስሕብነት፣ ለታሪክ ነጋሪነት የሚያገለግል እንደኾነ የተብራራ ሲኾን አከባባሩም በሕዝቡ እና በነገሥታት ጭምር እንደ ነበር ያትታል።

በቀጣይ ዳሠሣ የተደረገበት ርእሰ ደብር ጥዑመ ልሳን ካሣ "ያሬድና ዜማው" በሚል ያሳተሙት መጽሐፍ ነው። ርእሰ ደብር ጥዑመ ልሳን ካሣ "ያሬድና ዜማው" የሚል መጽሐፍ በ1962 ዓ.ም አሳትመዋል። ይህ መጽሐፍ በዋናናት የቅዱስ ያሬድ ሥራዎች እና የቅዱስ ያሬድ የሕይወት ታሪክ ላይ ትኩረት ተደርጎ የተዘጋጀ ነው። የቅዱስ ያሬድ ታሪክ፣ ዕውቀት እና ቅዱስ ያሬድ ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ያበረከታቸው ዕውቀቶች ላይ በዋናነት የተመሠረተ ነው። ቅዱስ ያሬድ በወር በዓል እና እንደ ጥምቀት በአሉ ዓመት በዓል ላይ የሚቆሙት ቁመቶችና ዜማዎች በመጽሐፉ ተገልጸዋል። በመጽሐፉ ውስጥ

የቅዱስ ያሬድ ሥራዎች የኾኑት ድጓ፣ ቅኔ፣ ትርጓሜ፣ ጾመ ድጓ እና ዝማሬ መዋሥዕት ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

ሌላው እና በቀጣይ የተቃኘው ሥራ "ጽድቅን እንፈጽም" በሚል ርአሰ ጉዳይ በ1957 ዓ.ም የታተመው መጽሐፍ ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ጽድቅን እንፈጽም የሚል ርእሰ ጉዳይ ይዞ የተነሣ ነው፡፡ ለጽድቅ መፈጸም ደግሞ ጥምቀተ ክርስቶስ ዋናው እንደኾነ ያስረዳል፡፡ ጥምቀት "እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሐ ፈሳሽ" ሳይኾን በትንቢት ሲነገር የኖረ እና ለጠፋው አዳም ድኅነት ሲል የመጣ ነው በማለት መጽሐፉ ያትታል፡፡ ይህን ለማረጋገጥ (መዝ፣ 114)ን በመጥቀስ "ባሕርኒ ርዕት ወጎየት ወዮርዳኖስኒ ገብዐ ድኅሬሑ አድባር አንፈርዐጹ ከመሐራጊት" (የዮርዳኖስ ወንዝም ወደኋላ ተመለሰ፡፡ ተራሮች እንደ ጥጃ ዘለሉ፤ ደስም አላቸው፡፡") በማለት ስለ ጥምቀት ይነገር የነበረውን ትንቢት ያትታል፡፡ በተጨማሪም ጥምቀት ከውሐ ጋራ ተያይዞ ለኀጢአት ፈውስ መኾኑን ይገልጻል፡፡ ይህ መጽሐፍ ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮሐንስ መኼዱን በዮሐንስ እጅ መጠመቁን እና ትሕትናውን ያወሳል፡፡

መጽሐፉ ሰዎች በጥምቀት አማካይነት ደስታን፣ ሰላምን፣ ትዕግሥትን፣ ቸርነትን፣ በጎነትን፣ እምነትን፣ የዋህነትን፣ ራስ መግዛትን የሚማሩበት እና የሚጎናጸፉበት ነው የሚል ይዘት አለው፡፡ የመጽሐፉ ዋና ጭብጥ ጥምቀት ለሰው ልጆች ስለሰጠው ነጻነት እና በጎነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመጽሐፉ ከጥምቀት በፊት የሰው ልጅ በዲያብሎስ ግዞት ሥር እንደ ነበር በማንጸሪያነት ተጠቅሷል፡፡ የነበረውን የሰው ልጅ ግዞት እና ዕዳ ደብዳቤ ክርስቶስ "እንደ ሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ" ነጻ እንዳወጣው በመጽሐፉ ተብራርቷል፡፡ በመኾኑም መጽሐፉ ጥምቀት የሰው ልጆችን ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከግዞት ወደ ነጻነት፣ ከባርነት ወደ ልጅነት የመለሰ ነው የሚል መደምደሚያ ይሰጣል፡፡

ቀጣዩ ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥናት ካደረጉ ተመራማሪዎች መካከል Aymro Wendimagegn እና Joachim Motuvu "The Ethiopian orthodocs church" በሚል ርዕስ በ1970 ዓ.ም ያሳተሙት መጽሐፍ ተጠቃሽ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ትውፊት፣ ሥርዓት፣ ስለ ቀኖና ቤተ ክርስቲያን እና ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ክብረ በዓላት ተዳሠውበታል፡፡ እንዲኹም ቤተ ክርስቲያኗ ለማኅበራዊ፣ ለምጣኔ ሀብታዊ፣ ለግብረ ገብነት፣ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሕይወት ያላት ጠቀሜታ በሰፊው የተብራራበት መጽሐፍ ነው፡፡ እንደዚኹም Karbo, Tony ስለ ኢትዮጵ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት "Religion and social cohesion in Ethiopia." በሚል በ2013 እና

Samorda, Jacob Bulti. ደግሞ ስለ ሃይማኖት እና ልማት በኢትዮጵያ "Religion and Development in Ethiopia" በ2012 በሚሉ ርእስ ጉዳዮች ላይ ተመሥርተው ጥናትና ምርምር አካኺደዋል። እነዚህ ኹለት አጥኚዎች ስለ ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት፣ ስለ ሃይማት እና ልማት ዘርዘር እና ሰፋ ያለ ዳሠሣ አድርገዋል። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ለምጣኔ ሀብታዊ፣ ለማኀበራዊ፣ ለባህላዊ ልማትና ለአካባቢ ጥበቃ ከፍ ያለ ፋይዳ እንደሚያስገኝ በጥናታቸው ግኝት አሳይተዋል።

ከላይ የተቃኙት ጽሑፎች ጭብጥ በአብዛኛው ስለ ጥምቀት አመጣጥ እና በጥምቀት ስለተገኘው ልጅነት የሚገልጹ ናቸው። በዚህ ልጅነትም የሰው ልጅ ነጻ የወጣበት እንደኾነ አጽንኦት ሰጥተው ያስረዳሉ። የጥምቀት ክብረ በዓልም ከክርስቶስ መጠመቅ እና ዕዳ ደብዳቤ መሻር ጋራ ተያይዞ የመጣ እንደኾነ ይገልጻሉ። ከዚህ በተጨማሪ የተዳሠሡት መጽሐፍት፣ መጽሔቶች እና ምርምሮች ስለ ቅዱስ ያሬድ ሥራዎች፣ ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ምስጢራት፣ ቀኖና፣ ስለ ክብረ በዓላት፣ ስለ አጽዋማት፣ ስለ ስግደት፣ ስለ ንስሐ፣ ስለ ጥምቀት፣ ስለ ምስጢረ ትንሣኤ፣ ስለ ምስጢረ ሥጋዊ፣ ስለ ምስጢረ ጥምቀት፣ ስለ ምስጢረ ቁርባን፣ ስለ ቤተ ክርስቲያኗ ቀኖና እና መሰል አስተምህሮዎቿ ላይ ትንታኔ የሰጡ ናቸው።

# ምዕራፍ ሦስት፡- የጥናቱ ሥነ ዘዴ፣ አካባቢያዊ ዳራና የመስክ ተሞክሮዎች

በዚሁ ምዕራፍ ሥር የጥናቱ ሥነ ዘዴ፣ አካባቢያዊ ዳራና የመስክ ተሞክሮዎች የሚሉት የጥናቱ አካላት ተዳሠው የቀረቡበት ክፍል ነው።

## 3.1. የጥናቱ ሥነ ዘዴ

በዚህ ክፍል የጥናቱ ዘዴ፣ የጥናቱ ናሙና፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ፣ የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች፣ የመረጃ መተንተኛ ዘዴዎችና የጥናቱ ሥነ ምግባር የሚሉት ነጥቦች ተካተው ቀርበውበታል።

### 3.1.1. የጥናቱ ዘዴ

ይህ ጥናት በዋናነት ዐይነታዊ ዘዴን ተከትሎ የተጠና ሶኾን በታካይነት ደግሞ የመጠናዊ ዘዴን ተጠቅሟል።

ዐይነታዊ ዘዴ በአንድ ዐይነታዊ ጥናት ውስጥ ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይትን የሚጠቀም ነው። ይህን አስመልክቶ Ritchie እና Lewis (2010, 72) *"በዋናነት ዐይነታዊ ዘዴ ምልከታን፣ ጥልቅ ግለሰባዊ ቃለ መጠይቅን፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይትን፣ የሕይወት ታሪክ ዘዴዎች የኾኑትን፣ እንደ ሕይወት ታሪኮች፣ እንደ ትረካዎች፣ የጽሑፍ እና የአሐዶች ትንታኔዎችን ኹሉ የሚያጠቃልል ነው" በማለት አጽንዖት ይሰጣሉ (ትርጉም የእኔ)።*[32]

ዐይነታዊ ዘዴ በዋናነት በማኅበራዊ ሳይንስ እና ሥነ ሰብኣት (በሂዩማኒቲስ) ጥናቶች ውስጥ በስፋት ተግባራዊ ይደረጋል። በእነዚህ ጥናቶች ውስጥ የሚነሡት ሰዋዊና ማኅበረ ባህላዊ ጉዳዮች በመጠን እና በዐይነት ብዙም፣ ጥልቅም ናቸው። እነዚህን ውስብስብና ጥልቅ ጉዳዮች ፈር አሲዞ ለመኼድና መረጃን በአግባቡ ለመሰብሰብ ዐይነታዊ ጥናት ወሳኝነት አለው (Ritchie, እና Lewis 2010, 27)።

[32]"*Main qualitative methods include: observation, in-depth individual interviews, focus groups, biographical methods such as life histories and narratives, and analysis of documents and texts (*Ritchie እና Lewis 2010, 72)*"*.

Berg (2001, 3) በበኩላቸው "ዓይነታዊ ጥናት ትርጉምን፣ ጽንሰ ሐሳብን፣ ብያኔን፣ ባሕርያትን፣ ተለዋጮችን (ፈሊጦችን) እና ትእምርቶችን ለመረዳት የሚያስችል ነው" የሚል ማረጋገጫ ይሰጣሉ፡፡

አክለውም Daymon እና Holloway, (2005, 3) የBerg (2001, 3)ን ሐሳብ በመደገፍ "ዐይነታዊ ዘዴ የምርምርን ትእምርት፣ ፅንሰ ሐሳብ፣ ዐይነትና ባሕርይ ለመለየትና ትንተና ለማካሄድ አስፈላጊ ነው" በማለት ጥልቅ ማብራሪ ይሰጣሉ፡፡ እንደዚሁም Creswell, (2007, 24) የBergን (2001, 3) እና የDaymon እና Holloway, (2005, 3)ን ሃሳቦች በመደገፍ ዐይነታዊ ዘዴ በክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ በርካታ የኾኑ ትውፊታዊ ጥበባት፣ ባህላዊ አልባሳት፣ የመዋቢያ ጌጣጌጦች፣ ንዋየ ቅድሳት፣ ትረካዎች፣ ዜማዎች እና መሰል ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶችን ለመመልከት አስቻይ ነው ይላሉ።

የተመራማሪዎቹን ዕይታ ወደ አንድ ማሕቀፍ አምጥተን ስንመለከተው ዐይነታዊ ዘዴ በአንድ ክብረ በዓል ውስጥ የክብረ በዓሉ ዘውጎች ምን ምን ናቸው? የማኅበረሰቡ ፍልስፍና ምን ይመስላል? የተጠኚዎቹ ሀገር በቀል ዕውቀቶች፣ ዕሴቶች፣ የባህላዊ ቁሶች እና ትእምርቶች እንዴት ይተረጐማሉ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚያስችል እንደኾነ አረጋጋጭ ነው። በዚህ መልኩ ዐይነታዊ ዘዴ በክብረ በዓሉ ውስጥ የተገኙትን መረጃዎች ትርጓሜ፣ ትእምርት፣ ቁሳዊ ባህል፣ ዕሴት እና ተምሳሌት በውል ለመገንዘብ፣ ለመረዳት እና ለመተንተን ሲባል ተመራጭ ሁኗል፡፡

መጠናዊ ዘዴ ደግሞ እንደ ፎክሎር እና ማኅበረሰባዊ ባሉ ጥናቶች ብዙ ተመራጭ ባይሆንም ተጠኝዎችን ለማሳተፍ እና ለማካተት ሲባል ዐልፎ አልፎ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ እኔም በመጠኑ የብድግ ብድግ ንሞናን በመውሰድ ለጥናቱ ተግባራዊ አድርጌዋለሁ፡፡

### 3.1.2. የመረጃ ምንጮች

በዚህ ጥናት መረጃ አሰባሰብ ኺደት ውስጥ ቀዳማይና ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሜአለሁ፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ከጥናቱ ባለቤቶች በክብረ በዓል ዐውድ የሚሰበሰበውን መረጃ የሚመለከት ነው፡፡ ስለኾነም በዋናነት ቀዳማይ የመረጃ ምንጭን ለመረጃ መሰብሰቢያነት በጥናቱ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ ስለ ጎንደር ጥምቀት ታላሚ እና እድል ሰጭ ንሞና ዘዴን በመጠቀም በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይት 54 ወንዶችን 40 ሴቶችን

በድምሩ 94 መረጃ ሰጪዎችን አሳትፌአለሁ፡፡ እነዚህ መረጃ ሰጪዎች የክብረ በዓሉ ባለቤቶች እና ተጠኚዎች በመኾናቸው ከቀዳማይ የመረጃ ምንጭ የሚመደቡ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ይህ ጥናት ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን ጭምር በግብዓትነት ተጠቅሟል፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ካላዓይ የመረጃ ምንጮች የሚባሉት ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔት፣ ከመመረቂያ ጽሑፎች ከቤተ መዛግብትና ቤተ መዘክር የተገኙትን ሥራዎች የሚመለከት ነው፡፡ እነዚህ ሥራዎች ለጥናቱ ሥነ ዘዴ፣ ለንድፈ ሐሳብ ማሕቀፍ፣ ለሥነ ጽሑፋዊ ቅኝት እና ለጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ እንደ ግብዓት ኹነው በማገልገላቸው በካልዓይ የመረጃ ምንጪነት ተወስደዋል፡፡

### 3.1.3. የጥናት ንድፍ (Research Design)

የጥናት ንድፍ ከጥናት ርእሰ ጉዳይ የሚጀምር ነው፡፡ የጥናት ንድፍ ርእሰ ጉዳዩ በጥናቱ ላይ ያሠራል ወይስ ተግዳሮቶች አሉት የሚለውን በመፈተሽ ወደ ምርምር ሥራ ለመግባት የሚደረግ ኺደት ሲኾን የጥናቱን ይዘትና ቅርጽም ይመለከታል፡፡ እንደዚሁም ከጥናቱ ዓላማ፣ ጥያቄ፣ አነሣሽ ምክንያትና መሰል የጥናቱ ግቦች አንጻር ጥናቱ ምን ይመስላል የሚለውን በንድፍ ደረጃ የሚያሳይ ነው፡፡ የጥናት ንድፍ በአንድ ፎክሎር ጥናት ውስጥ የጥናቱን ርእሰ ጉዳይ ከመረጠ በኋላ የጥናት ቦታውን ለመለየት፣ ተጠኚዎችን ለመረዳት፣ ንደፈ ሐሳባዊ ማሕቀፍ ለመምረጥ፣ አካባቢዊ ዳራን ለመወሰን፣ የጥናቱን ጊዜ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴን ለመምረጥ፣ የጥናት ዘውግን ለመለየት፣ የጥናቱን ትንታኔ ለመወሰን እና የጥናቱን ግኝት ለመተለምና ውጤታማ ለመኾን ያስችላል፡፡

*ይህን በተመለከተ David de Vaus (2001, 1) “ጥናት ንድፍ የሚያስፈልገን ከጥናቱ ማጠኝጠኛ ሐሳብ እና ከጥናቱ ጥያቄዎች ጀምሮ እስከ ጥናቱ መረጃዎች እስከ ጥናቱ ትንታኔ እና ማጠቃለያ ድረስ በማመላከት አጠቃላይ የጥናቱን ኺደት የሚያሳይ መሆኑ ነው” በማለት ያብራራሉ (ትርጉም የእኔ)፡፡*[33]

የዚህ ጥናት ንድፍም ዐይነታዊ ጥናትን የተከተለ ነው፡፡ ከንደፈ ሐሳብ ማሕቀፍ ደግሞ የክዋኔ ንደፈ ሐሳብን፣ የሥነ ፍካሬ ንደፈ ሐሳብ፣ የሥነ ምልኪ ንደፈ ሐሳብን እና

---

[33] David de Vaus (2001, 1) *"Research design, We need to know where design fits into the hole research process from framing a question to finaly annalaysing and reporting data" በማለት ያስረዳሉ፡፡*

የተግባራዊ ንደፈ ሐሳብን መመልከቻዎች ተግባራዊ አድርጓል። እንደዚኹም ጥናቱ የክዋኔን፣ የአሐድንና የዐውድ፣ የፍካሬ እና የዐይነታዊ መተንተኛ ስልቶችን ተከትሎ ተጠንቷል።

### 3.1.4. የጥናት ንሞና ዘዴዎች

የንሞና ዘዴዎች እንደ Berg. L. (2001, 32) ማጠየቂያ ከኾነ ታላሚ ንሞና እና ዕድል ሰጭ ንሞና ተብለው በኹለት ይከፈላሉ። ታላሚ ንሞና የሚባሉት፣ ጉዳይ ተኮር ንሞና[34] ስምምነት ፣ ተዋጽኦ እና ጉልሕ የተባሉ አራት ክፍሎች አሉት። ዕድል ሰጭ ንሞና ደግሞ ቀላል የብድግ ብድግ ንሞና እና አመቻች ብድግ ብድግ ንሞና ተብሎ በኹለት ይከፈላል Berg. L. (2001, 32-33)[35]::

ዐይነታዊ ጥናት ሰፊ የኾነ የመስክ ሥራን የሚያጠይቅ በመኾኑ ምክንያት ናሙና መርጦ ወደ መስክ መግባት አስፈላጊ ነው። ከጥናቱ ስፋት አኳያ መረጃን ከመስክ ለመሰብሰብ አንድ የናሙና ዘዴ ብቻ መውሰድና መጠቀም መረጃውን ምሉዕ ለማድረግ ያስቸግራል። በመኾኑም እንደ ጥናቱ ስፋት፣ ዐይነትና ዓላማ ስኬታማ የሚያደርጉ የጥናት ናሙናዎችን መምረጥ እና መጠቀም አስፈላጊ ነው። ለዚህ ጥናት በአግባቡ ከመስክ መረጃ ለመሰብሰብ ይቻል ዘንድ በዋናነት ታላሚ ንሞና ተመርጧል። በታካይነት ደግሞ የድርሻ ንሞና እና የብድግ ብድግ ንሞና ለጥናቱ ተግባራዊ ኾነዋል።

Daymon እና Holloway (2005, 159) "በዐይነታዊ ጥናት ውስጥ ታላሚ ንሞናን መጠቀም ተገቢውን መረጃ ለማግኘት አስቻይና ወሳኝ ዘዴ ነው" ይላሉ። ታላሚ ንሞና መረጃ ሰጪዎቹን እና የክዋኔውን ዐውድ ከጥናቱ ጋራ ታላሚ በማድረግ ስኬታማ መረጃን ያስገኛል። በዚህም የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ፣ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፣

---

[34]Purposive Sampling ለሚለው ቃል አንዳንዶቹ ታላሚ ንሞና ይሉታል። (Non probably sampling) ታላሚ ንሞና የሚለውን ትርጉም ከያዘ Purposive Sampling ለሚለው ደግሞ ጉዳይ ተኮር ንሞና የሚለውን ትርጉም የተሻለ ይመስለኛል። እኔም ትርጉም ወስጄ ተጠቅሜዋለሁ።

[35]የንሞና ዘዴዎች እንደ Berg. L. (2001, 32) ማጠየቂያ ከሆነ ታላሚ ንሞና (Non probably sampling) እና ዕድል ሰጭ ንሞና (probably sampling) ተብለው በኹለት ይከፈላሉ። ታላሚ ንሞና የሚባሉት፣ ጉዳይ ተኮር ንሞና (Purposive Sampling)[35] ስምምነት (Convenience Samples) ፣ ተዋጽኦ (Quota Sampling) እና ጉልህ (Snowball Sampling) የተባሉ አራት ክፍሎች አሉት። ዕድል ሰጭ ንሞና ደግሞ ቀላል የብድግ ብድግ ንሞና (Simple Random sampling) እና አመቻች ብድግ ብድግ ንሞና (Stratified Random sampling) ተብሎ በኹለት ይከፈላል።

የመረጃ ዐውድንና መረጃ ሰጪዎችን ለመምረጥና በአግባቡ መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል (Creswell (2007: 125)::[36]

የCreswell (2007: 125) መረጃ እንደ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ያሉ ጥናቶች ውስብስብና ጥልቅ፣ ብዙ እና ረጅም ከመሆናቸው የተነሣ በታላሚ ንሞና መረጃ ለመሰብሰብ መጣር ያለውን አስፈላጊነት የሚጠቁም ነው፡፡ በአንድ ክብረ በዓል ውስጥ የከዋኞች ብዛትና ማንነት፣ በክብረ በዓሉ የሚከወነውን የዘውግ መብዛት ተከትሎ የመስክ ሥራውን ውስብስብ ያደርገዋል፡፡ በመኾኑም ጉዳይ ተኮር የንሞና ዘዴ በመጠቀም በክብረ በዓሉ ውስጥ የሚበዙትንና ውስብስብ የኾኑትን የክብረ በዓል ክዋኔዎች እና የተሳታፊዎች ወግ አስይዞ ጥልቅ መረጃ ለመሰብሰብ ያስችላል፡፡ ይህ ዘዴ የክብረ በዓሉን ዐውድ፣ አሐድ፣ ቁሳዊ ባህል፣ ልማድና ትውን ጥበባት እንደየ ፈርጃቸው በጥናቱ ልክ በመወሰን ተአማኒና ትክክለኛ መረጃን ለማግኘት የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ Berg L (200, 32)[37] እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡

> *ጉዳይ ተኮር ንሞና ይህ ንሞና አንዳንድ ጊዜ ብይን ሰጪ ንሞናም ይባላል፡፡ የጉዳይ ተኮር ንሞና እያደገ የመጣውና አጥኚዎች የሚመርጡበት ምክንያት በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያን ማኅበረሰብ ወክለው የተለየ ዕውቀት፣ ተሰጥዖ እና ዐቅም ያላቸውን ተጠኚዎች በመምረጥ መረጃ እንዲሰጡ የሚያስችል በመኾኑ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ጉዳይ ተኮር ንሞና ከመስክ ሥ/ራ በኋላ የቡድኖችን፣ የግለሰቦችን ወይም የሰዎችን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ሲባል ተግበራዊ ይደረጋል (ትርጉም የእኔ)፡፡*

---

[36] *"The concept of purposeful sampling is used in qualitative research. This means that the inquirer selects individuals and sites for study because they can purposefully inform an understanding of the research problem and central phenomenon in the study." Creswell (2007: 125 በማለት ያስረዳሉ፡፡*

[37] *Purposive Sampling. This category of sampling is sometimes called judgmental sampling. When developing a purposive sample, researchers use their special knowledge or expertise about some group to select subjects who represent this population. In some instances, purposive samples are selected after field investigations on some group, in order to ensure that certain types of individuals or persons displaying certain attributes are included in the study. (Berg L 200, 32).*

Kothari (2004, 32) በበኩላቸው ደግሞ ጉዳይ ተኮር ንሞና መረጃን በዐውድ ለመሰብሰብ ከማስቻሉ በተጨማሪ ተተኳሪ የቡድን ውይይት ለማደራጀትም ትልቅ ሚና አለው ይላሉ። ታላሚ ንሞና ብዛት እና ዐይነት ያላቸውን ተጠኚዎች እና የክዋኔ ተሳታፊዎች ለቃለ መጠይቅና የቡድን ውይይት ለማደራጃት እና ለማሳተፍ ያስችላል። አንድ ተመራማሪ ኹሉንም የዐውድና የክዋኔ ድባብ ተከታትሎና ሰብስቦ ስለማይዘልቀው የታላሚ ንሞናን ተግባራዊ በማድረግ አስፈላጊውን መረጃ መሰብሰብ እንደሚገባው Punch (2004, 105) ይመክራሉ። እኔም ታላሚ ንሞናን ተግበራዊ በማድረጌ ምክንያት ከጥናቴ ዓላማ ጋራ ቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን ተጠኚዎች ለማግኘት ከመቻሌ በተጨማሪ ጉልበትና ጊዜን በመቆጠብ ጥናቴን በአግባቡ እንዳከናውን ረድቶኛል። ታላሚ ንሞናን በመጠቀም ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ጉዳዮችን ለመረዳትና በትክክል ለማግኘት ከመቻሌ በተጨማሪ መሪ ጌቶችን፣ ካህናቱን፣ ዲያቆናቱን፣ የምስክር ትምህርት ቤት ሊቃውንቱንና ደቀ መዛሙርቱን ለመለየትና መረጃ በአግባቡ ለመሰብሰብ አስችሎኛል። በዚህ መልኩ በጥምቀት ዐውድ እና ከአውዱ ውጭ 15 ሴቶችን እና 29 ወንዶችን በድምሩ 44 ተጠኚዎችን በታላሚ ንሞና ዘዴ በመጠቀም መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

ሌላው እና በኹለተኛ ደረጃ የምጠቀመው የንሞና ዘዴ ድርሻ[38] ንሞና ነው። ይህ ዘዴ የጉዳይ ተኮር ንሞናን ያክል ተግባራዊ ባይደረግም በታካይነት ለጥናቱ ተግባራዊ ተደርጓል። እንደ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች በሚሳተፉበት ክዋኔ ውስጥ ተተኳሪ ቡድን ውይይት ማደራጀት ተገቢ ነው። ተተኳሪ የቡድን ውይይት ስኬታማ የሚሆነው በዕድሜ፣ በዕውቀት፣ በጾታ፣ በማኅበራዊ ደረጃ እና በመሳሰሉት ማኅበራዊ እርከኖች ማሳተፍ ሲቻል ነው። የኮታ ንሞና በዚህ መልኩ ተተኳሪ የቡድን ውይይት ለማደራጀትና ለማሳተፍ ሚናው የጎላ ነው (Bruce L. Berg 2001, 32)።

በመኾኑም ድርሻ የንሞና ዘዴን የተጠኝዎቹን ዘውግ መሠረት በማድረግ ተተኳሪ የቡድን ውይይት ለማካኼድ ያስችለኚ ዘንድ ለጥናቱ በታካይነት ተግበራዊ አድርጌዋለሁ። ይህን ዘዴ በመጠቀም 4 የተለያዩ ቡድኖች ኹሉም 7፣ 7 አባላት ያሉት 14 ወንዶች እና 14 ሴቶች በድምሩ 28 ተጠኚዎች የተሳተፉበት 4 የቡድን ውይይቶችን እንዳከናውን አስችሎኛል። የቡድን ውይይቶቹ ቁጥር 7 የኾነበት ምክንያት የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ በሽምግልና፣

[38] *Quota* ለሚለው ቃል የአማርኛ ትርጉም ነው።

በማዕድ፣ በሥርዐተ ፍትሐት እና በተለያዩ ጊዜያት ነገሮችን ከ7 ጋራ አያይዞ ስለሚመለከት በዚህ የቡድን ውይይትም የተጠኚዎቹን ቁጥር ሰባት፣ ሰባት በማድረግ አደራጅቻቸዋለሁ።

ሌላውና ሦስተኛው የዚህ ጥናት የንሞና ዘዴ የብድግ ብድግ ንሞና ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ በዋናነት በርካታ ተጠኚዎችን በዕድል ሰጪ መልኩ ለማሳተፍ የሚያስችል ነው። ይህ ንሞና የተጠኚዎቹን ብዛት ታሳቢ ስለሚያደርግ አጥኚው የጊዜ፣ የጉልበት እና የዘውግ ልየታ ላይ ፈተና ሊኾንበት ይችላል። ይኹን እንጂ የብድግ ብድግ ንሞና በታላሚ ንሞና ከተደገፈ የተጠኚዎችን እኩልነት እና ተሳትፎ ዕድል ስለሚሰጥ እንደ መልካም የመረጃ ናሙና ይወሰዳል። ተጠኚዎችን በማሳተፍ መረጃ ለመሰብሰብ ማስቻሉ የብድግ ብድግ ንሞና ጠንካራ ጎኑ ነው (Berg (2001, 31፣ Kothari (2004: 32)።

በመኾኑም ይህን ዘዴ የመረጥኩበት ምክንያት በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የሚሳተፉትን ልጃገረዶች፣ አዛውንቶች፣ እናቶች እና ወጣቶች በድንገት በመጠየቅ መረጃ ለመሰብሰብ ስላስቻለኝ ነው። በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በክብረ በዓሉ ዐውድ በመገኘት ስለ ዘፈኑ፣ ስለ እስክስታው፣ ስለ ጭፈራው፣ ስለ ሆታው ከተሳታፊዎቹ መካከል መረጃ ሰብስቤያለሁ። ከእነዚህ መረጃ ሰጪዎች መካከል 11 ሴቶች እና 11 ወንዶችን በድምሩ 22 ተጠኚዎች ተሳትፈዋል።

### 3.1.5. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

መረጃን በተገቢው መንገድ ለመሰብሰብ አንድ አጥኚ ከጥናቱ ርእሰ ጉዳይ እና ዓላማ ጋራ የሚዛመድ እና ሊያስኬደው የሚችል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን መምረጥ እና መጠቀም ይገባዋል Dawson (2007, 200)። እኔም መረጃ በአግባቡ ለመሰብሰብ እንዲያስችለኝ ምልከታ፣ ቃለ መጥይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት የተባሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች በቅደም ተከተል ተጠቅሜያለሁ።

#### 3.1.5.1. ምልከታ

በፎክሎር ጥናት ውስጥ መረጃን በተፈጥሮ ዐውድ መሰብሰብ ፋይዳው ላቅ ያለ እንደኾነ Goldstein, (1964: 76) እና Gray, (2004: 105) ይመክራሉ፡፡ ምልከታ በተፈጥሮ፣ በቅንብር ወይም በሰው ሰራሽ ዐውድ መረጃ ለመሰብሰብ ዕድል የሚሰጥ ነው። አስገዳጅ ነገር

ካልገጠመ በቀር አንድን ፎክሎራዊ ክዋኔ በተፈጥሮ ዐውድና አጋጣሚ መረጃን መሰብሰብ ተመራጭ ነው፡፡ ምልከታ ለፎክሎር፣ ለሥነ ሰብእ፣ ሥነ ዘውግ[39] እና አጠቃላይ ለማኅበራዊና ሥነ ሰብእ ጥናቶች መረጃ በአግባቡ ለመሰብሰብ ያስችላል፡፡ ይህን ጉዳይ አስመልክቶ Daymon እና Holloway (2005, 202)[40] *"ምልከታ ለኹሉም የጥናት ዘዴዎች መሠረት ነው፡፡ ኹል ጊዜ በማንኛውም አጋጣሚ ኹሉ መረጃ ለመሰብሰብ ምልከታ ብታካኺድ ስለ ጥናቱ ዐውድ እንድትረዳ የበለጠ ማረጋገጫ ሊሰጥህ ይችላል (ትርጉም የእኔ) በማለት የምልከታን ጠቀሜታ ይጠቁማሉ፡፡*

ይህንኑ ሐሳብ በመደገፍ Blaxter (2006, 189) እና Ellen, R.F. (1995, 25) ምልከታ በአንድ ክዋኔ ዐውድ ላይ አጥኚው በአካል በመገኘት በአንድ የፎክሎር ክዋኔ ላይ እየተሳተፈ ይኹን ሳይሳተፍ መረጃን የሚሰበስብበት ብልኀት ነው የሚል ማጠናከሪያ ሐሳብ ይሠነዝራሉ፡፡ አክለውም Ellen, R.F, (1995, 25) ሲያትቱ "ምልከታ መረጃን ክዋኔው በበቀለበት ዐውድ በአካል በመገኘት የሚደረግ የመረጃ መስብሰቢያ ዘዴ ነው" ካሉ በኋላ "በክብረ በዓሉ ዐውድ የክዋኔውን ጣዕም በመቅመስ፣ የክዋኔውን ልስላሴና ሸካራ በመዳሠሥና የክዋኔውን መዐዛ በማሽተት፣ በክዋኔው ውስጥ ያለውን አጠቃላይ ዝግጅትና እንቅስቃሴ በአካል በመገኘት መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ ነው" በማለት አጽንዖት ይሰጣሉ፡፡

የምልከታ ዐይነቶች በመሳተፍ እና ባለ መሳተፍ የሚደረግ ምልከታ በመባል በኹለት ዘርፎች ይከፈላሉ፡፡ በመሳተፍ የሚደረግ የምልከታ ዐይነት አጥኚው የባህሉ ባለቤት ከኾነ እና ክዋኔው እንዲሳተፍ የሚፈቅድለት ዕድል ሲያገኝ በክዋኔው ውስጥ ራሱን አስገብቶ እየቀመሰ፣ እያሸተተ እና እየዳሠሠ፣ ራሱን እንደ አንድ የክዋኔው አካል በማድረግ የሚከወን የምልከታ ዓይነት ነው (Dawsen 2005, 105)፡፡

እየተሳተፉ የሚደረግ ምልከታ የባህሉ ወይም አጠቃላይ የክዋኔው ዐዋቂና ተወላጅ መሆንን የሚጠይቅ ሲኾን ይህ የምልከታ ዐይነት መረጃ መሰብሰብን ቀላል ከማድረጉ ባሻገር

---

[39] Ethnography ለሚለው የተጠቀምኩት አቻ ቃል ነው፡፡

[40] *"observation is the fundamental base of all research methods. No matter which method you use, in any situation you will always be looking about you in order to gather more evidence to help you understand the research context." (*Daymon እና Holloway 2005, 202).

መረጃውን ለመረዳትና ለመተንተን ያግዛል። ለዚህ ጥናት እየተሳተፉ የሚደረግ ምልከታ ተግባራዊ ተደርጓል። የክብረ በዓሉ ክዋኔ ዐውድ ክፍት መኾናቸው፣ በባህሉ ውስጥ ተወልጀ ያደግኩ መኾኑ እና በክብረ በዓሉ ለመሳተፍ የሚገድበኝ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ቀኖናዎች ባለመኖራቸው በመሳተፍ የሚደረግ ምልከታን ተግባራዊ አደርጌያለሁ።

ሌላውና ኹለተኛው የምልከታ ዐይነት ያለ መሳተፍ የሚደረግ ምልከታ ነው። ያለመሳተፍ የሚደረገው የምልከታ ዐይነት አጥኚው በባህሉ ተወልዶ ያላደገ ወይም ስለ ባህሉ በቂ ዕውቀት ሳይኖረው ሲቀር ወይም ክዋኔው በጾታ በዕድሜ፣ በዕውቀት፣ በእምነት፣ በባህል፣ በሃይማኖት ወዘተ ምክንያት አጥኚው እንዲሳተፍ የሚከለክል ከኾነ በአስተውሎት እና በአርምሞት ከዳር ኹኖ እየተከታተለ የሚደረግ የምልከታ ዐይነት ነው (Fetterman 1998, 34 እና Creswell 2007, 135)። በዚህም ያለ መሳተፍ የሚደረግ ምልከታ አጥኚው ከውጭ ኾኖ መመልከትን፣ ማስተዋልን የሚጠይቅ በመኾኑ በብዙ የመረጃ ግብአቶች ላይ ባይታወርነት ሊገጥመው ይችላል። በዚህ ምክንያት ውስን ጉዳዮችን ብቻ ሊሰበስብና ሊረዳ ይችላል (Creswell, 2007, 135 እና Morgan, 1996: 9) ፡፡

እኔ በባህሉ ውስጥ ተወልጄ ያደግኩኝ ከመኾኑ ባሻገር የጥምቀትን ክብረ በዓል ለመሳተፍ የሚገድበኝ ባህላዊም ኾነ ትውፊታዊ ክልከላዎች ባለመኖራቸው ምክንያት እየተሳተፉ የሚደረግ ምልከታን ተግባራዊ አድርጌያለሁ፡፡ በመኾኑም በ2011፣ በ2012 እና በ2013 ዓ.ም በቦታው በመገኘት በበዓሉ ዋዜማ የከተራ ጀምሮ የጥምቀቱን ክብረ በዓል ክዋኔ በመመልከት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ምልከታው የጥምቀቱን ክዋኔ በዐይን በማሳየት፣ በእጅ በማስዳሠሥ እና በጆሮ በማስደመጥ መረጃ በአግባቡ እንድሰበስብ አስችሎኛል፡፡ በምልከታ ላይ ያስተዋልኳቸው የጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔዎች ተግባር ከትርጉም ጋራ ተያይዞ ወደ ቃለ መጠይቅ እንድሸጋገር አድርጎኛል፡፡

#### 3.1.5.2. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ ከመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካካል አንዱ ነው። ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በምልከታ ጊዜ የሚኖረውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል እና የሚከተል ነው። ቃለ መጠይቅ ተጠኚዎቹን ወይም በአንድ የፎክሎር ክዋኔ ማኅበራዊ ዐውድ ውስጥ ከመረጃ

ሰጪዎች ጋራ በአካል በመገናኘት መረጃን ለመሰብሰብ የሚያስችል ዘዴ ነው Daymon, and Holloway (2005, 167)፡፡

ቃለ መጠይቅ ተጠኚዎቹን በአካል ማግኘት ማስቻሉ ለሥነ ሰብእ፣ ለፎክሎር፣ ለባህል እና መሰል ጥናቶች ሚናው የጎላ ነው፡፡ በቃለ መጠይቅ ወቅት በሚነሣው ጉዳይ ላይ መልስ ማገኘት እና ውይይት ማድረግ የሚቻልበት እድል ሰፊ ነው (Blaxter 2006, 185)፡፡ በቃለ መጠይቅ ጊዜ አጥኚው እና ተጠኚዎቹ ፊት ለፊት በመገናኘታቸው ምክንያት በተጠኚዎቹ እና በተመራማሪው መካከል ዝምድናን ይፈጥራል፡፡ ይህ መልካም ግንኙነት አጥኚው የሚፈልገውን መረጃ በተሻለ እና በተጠናከረ መልኩ እንዲያገኝ ያስችለዋል (Gomm 2008, 222 እና Goldstien 1964, 103)፡፡

የቃለ መጠይቅ ዐይነቶች በፎክሎር፣ በሥነ ሰብእ፣ በሥነ ዘውግ፣ እንዲኹም በማኅበራዊ ሳይንስ ውስጥ በርካታ ቢሆኑም በዋናነት የተለመዱት እና አንድ አጥኚ በመስክ ላይ ተግባራዊ የሚያደርጋቸው ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም ገደብ የለሽ ቃለ መጠይቅ፣ በከፊል የተገደበ ቃለ መጠይቅና የተገደበ ቃለ መጠይቅ ናቸው (Dawson 2005, 28)፡፡

**ያልተገደበ ቃለ መጠይቅ**፡- ተጠያቂዎችን ያለ ገደብ በማሳተፍ የሚደረግ የቃለ መጠይቅ ዐይነት ነው፡፡ ይህ መጠይቅ ሰፊ የኾነ ጉዳይን በማንሣት እና ለጉዳዩ ተጠኚዎችን በማሳተፍ ያለ አጥኚው ጣልቃ ገብነት መረጃ አቀባዮች ጉዳዩን ማብራራት የሚችሉበትን ዕድል ያመቻቻል፡፡ ተጠኚዎች የፈለጉትን ጉዳይ ለመናገር ነጻነትን የሚሰጥ በመኾኑ በአጥኚውና ተጠኚዎች መካከል ጥሩ ዝምድናን ይፈጥራል፡፡ በተፈጠረው መግባባት ምክንያት አጥኚውን የተብራራ መረጃ ለማግኘት ያስችለዋል (Dawson 2005, 28)፡፡

ያልተገደበ ቃለ መጠይቅ ማኅበረሰቦቹ ያለ ከልካይ በራሳቸው ፍላጎት ስለሚተነፍሱ የመራጃውን ትርጉም፣ ምንነትና ባሕርይ ከመረዳት በተጨማሪ የተገኘውን መረጃ ለመተንተን ያግዛል፡፡ በዚህ ምክንያት ያልተገደበ ቃለ መጠይቅ ለፎክሎር፣ ለማኅበራዊ ሳይንስ፣ ለሥነ ሰብእና ባህል ጥናቶች ተግባራዊ የሚደረግበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡

*ይህን በተመለከተ Ritchie, እና Lewis (2010, 138) ቀጣዩን መረጃ ሰጥተዋል፡፡ "ጥልቅ ወይም ያልተገደበ ቃለ መጠይቅ ዋና ከሚባሉ የዐይነታዊ ጥናት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ እንደ Malinowski ያሉ ቀደምት የሥነ ዘውግ ተመራማሪዎች ጎላ አድርገው የሚጠቅሱት "ያልተገደበ ቃለ መጠይቅ የሰዎችን ምልከታ የማስረዳት፣ የግለ ሕይወት ታሪክ ለማወቅና ለመረዳት*

*የሚያስችል በመኾኑ በማኅበራዊ ሳይንስ ጥናት ውስጥ ትልቅ ጠቀሜታ አለው" ይላሉ (ትርጉም የእኔ)፡፡*[41]

ይህ የቃለ መጠይቅ ዐይነት ለመረጃ ሰጪዎች በሚሰጠው ከፍተኛ እድል ምክንያት የተጥኚዎችን የሕይወት ውጣ ውረድ፣ ፍልስፍና፣ ዕውቀት ለመረዳት የሚያስችል ጠንካራ ዘዴ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በሌላ መልኩ በሚሰጠው ነጻነት ምክንያት ከተፈለገው ርእሰ ጉዳይ በመውጣት መረጃ ሰጭዎቹ በርካታ ታሪካዊና ግለ ታሪካዊ ጉዳዮችን፣ ብሶቶች እና ፍላጎቶችን ሊተርኩ ይችላሉ፡፡ በዚህም አጥኚውን ለጊዜ ብክነት እና ለወጭ ከመዳረጉ በተጨማሪ ከርእሰ ጉዳዩ ውጭ የሆነ መረጃ በመኖሩ ምክንያት አጥኚው ምርቱን ከግርዱ ለመለየት ተጨማሪ ሥራ ሊሆንበት ይችላል፡፡፡፡

ይህን የቃለ መጠይቅ ዓይነት ለኔ ጥናት በተመጠነ ኹኔታ ተግባራዊ አድርጌዋለሁ፡፡ ተግባራዊ ያደረግኩበት ምክንያት በሥነ ፍካሬ የተመረጡትን እንደነ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ እና አባ በሪሁን አካላት የተባሉትን 9 መረጃ ሰጪዎችን ያልተገደበ ቃለ መጠይቅ ተጠቅሜ መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ ይህ የኾነበት ምክንያት ካላቸው ከፍ ያለ ማኅበረሰባዊ ደረጃ እና የዕውቀት ልዕልና በመነሣት ያልተገደበ የቃለ መጠይቅ ስልትን በመጠቀም የጥምቀቱን አንድምታ እና ትርጓሜ ለመረዳት በማሰብ ነው፡፡ ሌላው አራቱን የቡድን ውይይቶች 14 ወንዶችን እና 14 ሴቶችን በድምሩ 28 ተጠኝዎችን ባልተገደበ ቃለ መጠይቅ ዘዴ መረጃ ሰብስቤአለሁ፡፡ በዚህ መልኩ ባልተገደበ ቃለ መጠይቅ 37 መረጃ ሰጪዎችን አሳትፌአለሁ፡፡

**በከፊል የተገደበ ቃለ መጠይቅ**፡- ኹለተኛው የቃለ መጠይቅ ዐይነት በከፊል የተገደበ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ በከፊል የተገደበ ቃለ መጠይቅ አጥኚው ያለውን ጊዜ በአግባቡ እንዲጠቀም እና ተጠኚዎቹ ወደ ተፈለገው ርእሰ ጉዳይ እንዲገቡ በማድረግ የተሻለ መረጃን ሊያስገኝ የሚችል የቃለ መጠይቅ ዐይነት ነው (Dawson 2005, 28)፡፡

---

[41]ይህን በተመለከተ Ritchie, እና Lewis (2010, 138) `*In-depth or unstructured interviews are one of the main methods of data collection used in qualitative research. Classic ethnographers such as Malinowski stressed the importance of talking to people to grasp their point of view), and personal accounts are seen as having central importance in social research"* መረጃ ሰጥተዋል፡፡

ይህ ዘዴ በአብዛኛው በፎክሎር ጥናት መረጃ አሰባሰብ ወቅት ተግበራዊ መደረግ ያለበት እና በብዛት የተለመደ ነው። ዘዴው ተመራጩ የሚኾንበት ምክንያት ያልተገደበውን ቃለ መጠይቅ እንዲወሰን በማድረግ በጣም የተወሰነውን ቃለ መጠይቅ ደግሞ ሰፋ እንዲል በማድረግ በተገደበ እና ባልተገደበ ቃለ መጠይቅ ዐይነቶች መካከል ያላውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል ዘዴ መኾኑ ነው። በመሆኑም ሴት 17 ወንድ 23 በድምሩ 40 ተጠኚዎችን በዚህ ዘዴ ተጠቅሜ መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ።

**የተገደበ ቃለ መጠይቅ**፡- ሦስተኛው የቃለ መጠይቅ ዐይነት የተገደበ ቃለ መጠይቅ ነው። ይህ የመጠይቅ ዐይነት የተገደበ ከመኾኑ አንጻር የተወሰኑ ጥያቄዎችን ብቻ በመጠየቅ መልስ የሚያስገኝ ነው። ይህ ዘዴ የመረጃ ሰጪዎችን የመናገር እና የመሳተፍ ዕድል ስለሚገድብ ጥያቄ ይነሣበታል። የተገደበ ቃለ መጠይቅ ጊዜን በመቆጠብ እና ወጭን በመቀነስ ረገድ የተሻለ የቃለ መጠይቅ ዐይነት ነው (Dawson 2005, 30)፡፡ በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መስፈርት በበዓሉ ዋዜማ፣ ከበዓሉ መልስ ባሉ ጊዜያት ለ9 ልጃ ገረዶችና ለ8 ወንድ ወጣቶች በድምሩ ለ17 ተጠኚዎቸ ተግባራዊ አድርጌዋለሁ።

በዚህ ጥናት ውስጥ ያልተገደበ ቃለ መጠይቅ፣ በከፊል የተገደበ ቃለ መጠይቅ እና የተገደበ ቃለ መጠይቅ የተባሉትን ሦስት የቃለ መጠይቅ ዐይነቶች ተግባራዊ ተደርገዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት የጥናቱ ትኩረት የኾነው የጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የሚነሡ በርካታ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ሃይማኖታዊና ሰዋዊ ጉዳዮች አሉ። ሦስቱን የቃለ መጠይቅ ዐይነቶች በመጠቀም እነዚህን በርካታ ጉዳዮች የአንደኛውን የቃለ መጠይቅ ክፍተት በሌላኛው በመሙላት ጠንካራ መረጃ ለመሰብሰብ ስለአስቻለኝ ነው።

ጠቅለል ባለ መልኩ ወንድ 54 እና ሴት 40 በድምሩ 94 መረጃ ሰጪዎች በጥናቱ ተካተዋል። የቃለ መጠይቅ አካኼዱ ከእነዚህ ከሦስቱ የቃለ መጠይቅ አካኼዶች በተጨማሪ በጥምቀቱ ዐውድ እና አጋጣሚ ቃለ መጠይቆችን ተጠቅሜያለሁ። አንድ አጥኚ ለጥናቱ ግብዓት የሚኾነውን መረጃ ትክክለኛነት ማረጋገጥ እና መጠቀም ግድ ይለዋል። እኔም ይህን የመረጃ ትክክለኛነት እና ታማኝነት ለማረጋገጥ ኹለት መንገዶችን ተከትያለሁ። አንደኛው መንገድ ያገኘሁትን መረጃ በሌሎች ተጠኚዎች እና መረጃ ሰጭዎች ቃለ መጠይቁን በማቅረብ ከመጀመሪያው መረጃ ጋራ ያለውን ተመሳስሎ ማረጋገጥ ነው። በዚህ መልኩ አንድን ቃለ መጠይቅ ለሦስት እና ለአራት መረጃ ሰጭዎች በማቅረብ መረጃዎችን ማሚገት ነው። በዚህ ሙግት ውስጥ አስፈላጊ ኾኖ ከተገኘ ደግሞ በቡድን ውይይት ውስጥ ቃለ

መጠይቁን በማንሣት እንዲታሽ እና እንዲበስል በማድረግ የመረጃ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ጥረት አድርጌያለሁ።

ኹለተኛው የመረጃ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ የተጠቀምኩት ዘዴ ለአንድ መረጃ አቀባይ ያንኑ ቃለ መጠይቅ በተለያዩ ጊዜያት እና ቦታ በማንሣት ድጋሚ መልስ እንዲሰጠኝ የማድረግ ዘዴ ነው። በዚህም ለኹለት እና ለሦስት ጊዜ ቃለ መጠይቅ በማቅረብ በየ ወቅቱ የሚሰጠኝን የመረጃ ተመሳስሎ እና ተቀራርቦ ማጤን ነው። በዚህ መልኩ እነ ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሐዲስ፣ መ/ር ዳዊት ሥራው፣ አባ እንባቆም፣ ደስታው ፈንታው፣ ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ ቄስ ደስታው ዓለሙ፣ ምንትዋብ ደጌ፣ ስንታየሁ ሹሜ እና መሰል መረጃ ሰጪዎችን ከ2011 ዓ፣ም እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ የመረጃ ትክክለኛነትን ለማረጋገጥ ጥረት አድርጌያለሁ። ይህን ዘዴ መጠቀሜ ለጥናቴ ትክክለኛ መረጃ ከማግኘቴ በተጨማሪ በየ ዓመቱ ያሉትን ግብዓቶችም እንድጠቀም አስችሎኛል። በዚህ መልኩ አንድን ቃለ መጠይቅ ለብዙ መረጃ ሰጪዎች እና አንድን መረጃ በተለያዩ ጊዜያት ለአንድ መረጃ ሰጪ በሚሉት ኹለት የመረጃ ማረጋገጫ ዘዴዎችን ለጥናቴ ተጠቅሜያለሁ።

#### 3.1.5.3. ተተኳሪ የቡድን ውይይት

ተተኳሪ የቡድን ውይይት መረጃን በዐውድ ተነሥቶ ለመሰብሰብ እጅግ ወሳኝ ዘዴ ነው። ይህ ዘዴ ከምልከታ እና ከቃለ መጠይቅ ቀጥሎ የሚመጣ ሲኾን እንደ ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ ሰፊ ጊዜና ቦታን አይሸፍንም። ከጥናቱ ርእሰ ጉዳይ እና ከጥናቱ ዓላማ ጋራ ተያይዞ ውስን እና ዓላማ ተኮር ጥያቄዎችን ብቻ ያስተናግዳል (Daymon, and Holloway 2005, 186)::

ተተኳሪ የቡድን ውይይት ዓላማው እና ተግባራዊ የሚያደርገው በአንድ ጉዳይ ላይ የጉዳዩ ባለቤት የሆነው ማኅበረሰብ ምን ያስባል? ጉዳዩን እንዴት ይረዳዋል? እንዴት ይገልጸዋል? እና መሰል ጥያቄዎችን በመመለስ አጥኚው ጥልቅ አረዳድ እንዲኖረው የሚያስችል ዘዴ ነው። ይህን በተመለከተ William, (200, 22) *"ጥልቅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ጥናቱን ለመወሰን የተለዩ የመመዘኛ ጥያቄዎችን የሚመለከት ነው። ተተኳሪ የቡድን ውይይት በአንድ በተወሰነ ጉዳይ*

*የሰዎችን ጥልቅ አረዳድ እና ጥናቱን ተከትሎ ለሚመጡ ጉዳዮችን እንድንረዳ የሚስችል ነው” [42] በማለት ያብራራሉ (ትርጉም የእኔ)።*

ይህ ዘዴ አጥኚው በምልከታና በቃለ መጠይቅ መረጃዎችን ከሰበሰበ በኋላ የሚከተል ሲኾን በዋናነት እንደ ክብረ በዓልና መሰል ሰፊ ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን በአግባቡ ለመሰብሰብ ያስችላል፡፡ በዚህም በአንድ ክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ ከክዋኔው በኋላ ትእምርታዊና አንድምታ ያላቸውን በቁጥር አንስተኛ የኾኑ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ተተኳሪ የቡድን ውይይት በተመረጡ ሰዎችና የተለየ ትንታኔ በሚሹ የተመረጡ ጥያቄዎች ላይ ጥልቅ መረጃን ለመሰብሰብ የሚያስችል ነው በማለት Ritchie እና Lewis (2010፡171) ያስረዳሉ። በመኾኑም በቡድን ውይይት ወቅት ጥያቄዎች ከጥናቱ ርእሰ ጉዳይና ከጥናቱ ዓላማ ጋራ በውል የሚቆራኙና የሚዛመዱ መኾን ይገባቸዋል (Morgan, 1995, 3)፡፡

የቡድን ውይይት በናሙና አመራረጥ ረገድ ታላሚ ናሙናዎች ላይ በበመመሥረት አጥኚው በርእሰ ጉዳዩ ላይ የተሻለ መረጃ እንዲያገኝ ያስችለዋል፡፡ በዚህ ምክንያት ዕድል ሰጪ ናሙናን አይጠቀምም፡፡ በተተኳሪ የቡድን ውይይት መዋቅር የቡድኑ አባላት ብዛት፣ የቁጥር መጠን፣ የሚወስደው ሰዓት እና የጥያቄዎች ብዛት የሚሉት ነጥቦች እንደ የተመራማሪዎቹ ዐተያይ የተለያዩ ናቸው፡፡ የተመራማሪዎቹ ዐተያይ የተለያየ ይኹን እንጂ ተተኳሪ የቡድን ውይይት የራሱ የኾነ የናሙና አወሳሰድ፣ የተሳታፊ አወቃቀር እና የጥያቄ አቀራረብ ስልት አለው። አጥኚው ይህን ዘዴ ተግባራዊ ሲያደርግ የጥናቱ ርእሰ ጉዳይ፣ የጥናቱ ዓላማና የጥናቱ ዐውድ እንዲኹም የጥናቱ ስፋትና ጥልቀት በሚፈቅደው ልክ ክፍት ቃለ መጠይቅን መጠቀም አለበት፡፡ በተተኳሪ ቡድን ውይይት ወቅት የሚነሱት ጥያቄዎች ለውይይት የሚጋብዙና አሳታፊ መኾን ይገባቸዋል፡፡ ጥያቄዎቹም ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር መግባት በሚያስችል መልኩ መቅረብ አለባቸው የቡድኑ ተሳታፊ አባለት በዕድሜ፣ በጾታ፣ በሥራ፣ በማኅበራዊ ደረጃ ወዘተ ተመሳሳይና

[42] "Systematic research collecting in depth data as specific evaluation questions to determine program, Fgd provide in sight in to how people think and provide deeper understanding of the phenomena being studied" William, (200, 22).

ተቀራራቢነት ያላቸው ቢኾኑ ይመከራል፡፡ በዚህም ጥልቅ የኾነ የርእስ በርእስ ተግባቦት ውስጥ የተሻለ መረጃ ለማግኘት ያስችላል (kruger, 2002: 20 እና Morgan 1996, 5)።

ተተኳሪ የቡድን ውይይት በርካታ ጠንካራ ጎኖች ቢኖሩትም በዘዴው ላይ የሚነሡ ተግዳሮቶች አሉ፡፡ ከእነዚህ ተግዳሮቶች መካካል የተፈጥሮ መቼት ያለመገኘት፣ ገደብ የለሽ መጠይቅ መጠቀም፣ የቡድን ውይይቱን አባላት ለመቆጣጠር መቸገር፣ ያልተጠበቀ ነቀፋ እና ክርክር መከሰት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ እንደዚሁም በውይይቱ ወቅት በግለሰብ እና በዐውድ ተፅኖ ሥር የመውደቅ ኹኔታ ሊያጋጥም ይችላል፡፡ በመኾኑም አንድ አጥኚ ይህን ዘዴ ተግባራዊ ሲያደረግ እነዚህን ተግዳሮቶች ቀድሞ መረዳትና በአግባቡ መጠቀም ግድ ይለዋል፡፡

በዚህ ጥናት ያልተገደበ የቃለ መጠይቅ በመጠቀም አራት የቡድን ውይይቶች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ተተኳሪ የቡድን ውይቱን ለማስኼድ የጾታ ተመሳስሎን፣ ተቀራራቢ ዕድሜ እና የዕውቀት ደረጃ በሚሉት መስፈርቶች የተቃኘ ነው፡፡ ይህን ተግባራዊ ያደረግኩበት ምክንያት የክብረ በዓሉን ክዋኔ ተከትሎ የሴቶችን፣ የወጣቶችን የሊቃውንቱን እና መሰል የጥምቀቱን ሥርዓተ ክዋኔ ለመመርመር በማሰብ ነው፡፡ በዚህ መልኩ 7፣ 7 አባላት ያሉት ኹለት የወንዶች እና ኹለት የሴቶች በድምሩ 28 መረጃ ሰጪዎችን ያሳተፈ አራት ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ለጥናቱ ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

### 3.1.6. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

በማኅበራዊ ሳይንስ በሥነ ሰብእ፣ በፎክሎር እና በሥነ ዘውግ ጥናቶች መረጃ ከመስክ በሚሰበሰብበት ወቅት መስከኛው ለመረጃው እንደ አስፈላጊነቱ መቅረጸ ድምፅ፣ ቪዲኦ ካሜራ፣ ፎቶ ካሜራ እና ማስታወሻ ደብተርን በስብጥር መጠቀም አስፈላጊ ነው (Blaxtere (2006, 182፤ Punch, 2004, 1670 እና Fitterman 1998, 115 )። እኔም እንደ መረጃ ሰጪዎቹ ፈቃደኝነት እና እንደ መረጃው አስፈላጊነት ለዚህ ጥናት ማስታወሻ ደብተርና ፎቶ ካሜራ፣ ቪዲኦ ካሜራ እና ኦዲኦ ካሜራ የመሳሰሉትን የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ተግባራዊ አድርጌያለሁ።

### 3.1.7. የመረጃ መተንተኛ ስልት

ጥናቱ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል በመኾኑ ምክንያት አራት የመተንተኛ ስልቶች ተግባራዊ ተደርገዋል። ይህ የኾነበት ምክንያት ጥናቱ የሚጠይቃቸውን ስልቶች ታሳቢ በማድረግ የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ያለመ ነው። በመኾኑም ይህ ጥናት የክዋኔ ትንታኔ፣ ዐይነታዊ ትንታኔ፣ የአሐድ እና ዐውዳዊ ትንታኔ እና የፍካሬ ትንታኔ የመረጃ መተንተኛ ስልቶችን ተከትሎ ተተንትኗል። የጥናቱ ትንታኔ በዋናናት ከተጠኚዎቹ ፍልስፍና ዐይን አትኩሮት ያደረገ ነው። ይሁን እንጂ ጥናቱ ሳይንሳዊ መንገድን ይከተል ዘንድ በታካይነት ከአጥኚው መነጽር እና ዕውቀትም ትንታኔ ተሰጥቷል።

**የክዋኔ መተንተኛ ስልት**፡- የፎክሎር ክብረ በዓል ከሚተነተንባቸው ወሳኝ የመተንተኛ ስልቶች መካካል ክዋኔ የመተንተኛ ስልት እጅግ ወሳኝ ነው። የክዋኔ መተንተኛ ስልት ብቅ ያለውና በዋናነት ዕውቅና አግኝቶ ወደ ተግባር የገባው በ1970ዎቹ አካባቢ ነው። ይህ ስልት አንድን ፎክሎራዊ ይኹን ባህላዊ ክዋኔ በዐውድና በተፈጥሮ መቼት ተመሥርቶ ለመተንተን ያስችላል።

> *ይህን ሐሳብ Peek. እና Yankah (2004: 797) እንደሚከተለው ያስረዳሉ። ክዋኔና የክዋኔ ትንታኔ በዋናነት ለመስክ ጥናት እንደ ፎክሎር፣ ሥነ ሰብእ፣ የሃይማኖት ጥናት፣ ጥበባትና ታሪክ መስኮች ውስጥ ሚናው የጎላ ነው። ይህ ስልት የክብረ በዓልና የድግስ መረጃዎችን ትንታኔ ለመስጠት ጥቅሙ ከፍተኛ ነው። የክዋኔ ትንታኔ በ1962[43] ዓ.ም ጀምሮ ከፍ ያለ ዕውቅና እያገኘ የመጣ ሲኾን በተለይ በፎክሎርና ሥነ ሰብእ ጥናቶች ውስጥ ክዋኔን መሠረት በማድረግ መረጃዎችን ከዐውድና ከአሐድ ጋራ አስተባብሮ ለመተንተን ፋይዳው ላቅ ያለ የመተንተኛ ስልት ነው (ትርጉም የእኔ)።[44]*

---

[43] ዓ.ም የሚለው ወደ እኛ (እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጣር) ሲተረጎም ነው።

[44] ይህን ሐሳብ Peek. እና Yankah እንደሚከተለው ያስረዳሉ። *Performance and performance analysis also have more specialized, technical senses in fields such as folklore, anthropology, religious studies, and art history, where they refer to a mode of analyzing rituals and ceremonies. Performance analysis emerged as a recognized approach in the 1970s, initially rooted in attempts in folklore and anthropology to incorporate greater concern with context and move away from approaches that relied chiefly on text analysis, KRATZ, in Peek. and Yankah, (2004: 797).*

የክዋኔ መተንተኛ ስልት ከዋኝን፣ ክዋኔን፣ ዐውድን፣ አሐድን፣ ውበትን በተወሰነ ጊዜና ቦታ ለትይንት የሚያበቃ ነው፡፡ በመሆኑም በተለይ ለፎክሎር፣ ለሥነ ሰብእ፣ ለሶስኦሎጅ፣ ለሥነ ዘውግ ጥናቶች ከንድፈ ሐሳብ ማሕቀፍ ባለፈ ለጥናት መተንተኛ ስልትም እጅግ ተመራጭ ነው (Peek. and Yankah 2004, 802)።

ክብረ በዓል እየተደጋገመ በመከወን ከትውልድ ትውልድ በክዋኔ አማካይነት እየተላለፈና እየተዘከረ ይኖራል፡፡ ክዋኔ የአንድን ክብረ በዓል ትክክለኛ ምንነትና ኹነኛ ግኝት ላይ ለመድረስ በክዋኔው አማካኝነት ትንታኔ ሊደረግ ይገባል፡፡ የክዋኔ ትንታኔ የክብረ በዓሉን የፈጠራ እንቅስቃሴ የተጠኝዎቹን ዕውቀት፣ ምኞት፣ ምናብ፣ አስተሳሰብ፣ አጠቃላይ የማኅበረሰቡን ዕሴት፣ ፍልስፋና እና ተግባር ጭምር ያሳውቃል፡፡ የክብረ በዓሉ ባለቤቶች፣ በክብረ በዓሉ የሚሳተፋት፣ የሚተገብሩትና መሥዋዕት የሚያቀርቡት ለምን ጉዳይ እንደኾነ ማኅበራዊ አንድምታውን ለመረዳት ያስችላል (Peek እና Yankah, 2004: 802)::

አንድን ክብረ በዓል ለመበየን የጥንቱንና የአኹንን፣ የአለፈውንና መጻዒውን ለማወቅ ለመረዳት፣ ብሎም የጎደለና የሞላውን አጠቃላይ የክብረ በዓሉን ኹነት ለመረዳት የሚያስችል ወሳኝ ስልት ነው፡፡ በዚህም የክብረ በዓሉን ክዋኔ ሀገረሰባዊ ዳንስ፣ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ አስደናቂ እንቅስቃሴዎችን ኹሉ ለመተንተን የሚያስችል ወሳኝ ስልት በመኾኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የክዋኔ መተንተኛ ስልት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡

**የቴክስትና የዐውድ ትንታኔ**: - ይህ የመተንተኛ ስልት በኹለተኛ ደረጃ ለጥናቱ መተንተኛነት ተግበራዊ ተደርጓል፡፡ ቴክስትና ዐውድ በአንድ ክብረ በዓል ክዋኔ ላይ የሚገኙ ሲኾን ግንኙነታቸውም የጠበቀ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ Amos, (1992: 210) *"የቴክስት ትርጉም የዐውድ ትርጉም ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በዐዉዳዊ ትንታኔ ውስጥ በቴክስትና ዐውድ መካካል ድንበር ማብጀት አይቻልም"* [45] በማለት የዐውድን እና የቴክስትን ዝምድና ያስረዳሉ *(ትርጉም የእኔ)* ፡፡

የአሐድ እና የዐውድ ትንታኔ በክብረ በዓሉ የሚገኙትን ንዋየ ቅድሳት፣ ባህላዊ አልባሳት፣ ቃል ግጥሞች፣ ትእምርቶች እና ታሪኮች በክብረ በዓሉ ዐውድ በመነሣት ዐውድና ቴክስትን እስተባብሮ ለመተንተን ያስችላል፡፡ በዚህ ምክንያት የጥምቀት ክብረ በዓል ያለውን አንድምታ

[45] *Amos, (1992: 210) "The meaning of atext is its meaning in context. In terms of contextual analysis there is no dichotomy between text and context"*

እና ፋይዳ በዐውድ አማካኝነት ለመረዳት፣ ለመመርመርና ለመተንተን ስላስቻለኝ ለጥናቱ መተንተኛ ተግባራዊ አድርጌዋለሁ፡፡

**ዐይነታዊ መተንተኛ ስልት**፡- ዐይነታዊ የመረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ ስልት የአንድን ማኅበረሰብ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ ስሜት፣ ፍላጎትና ምኞት ለማሳየት ተመራጭ ነው[46]፡፡ በዐይነታዊ ዘዴ የተገኘን መረጃ በዐይነታዊ ዘዴ በሚተነተንበት ወቅት ትንተናው በአንድ ጊዜ የሚቋጭ ሳይሆን እንደገና የተሻለ መረጃ በተገኘ ቁጥር ትንታኔ እንዲካሄድ እድል የሚሰጥ ነው፡፡ ዐይነታዊ የመተንተኛ ስልት ጊዜን ዐቅምና ጉልበትን የሚፈትንበት ኹኔታ ቢኖርም ባህላዊ ጉዳዮችን እና የፎክሎር ሥራዎችን ለመተንተን ተመራጭ ዘዴ ነው Kothari (2004: 22)፡፡ ጠቅልል ባለ መልኩ ዐይነታዊ የመተንተኛ ስልት በትንታኔ ወቅት መረጃውን ከመስክ እንደመጣ በመጀመሪያው ወደ ትንተና ከመግባት ይልቅ በተደጋጋሚ መረጃዎችን የማጤን፣ ከመቅረጸ ድምፅ ወደ ጽሑፍ የመቀየር እና መረጃውን መላልሶና ከልሶ ለማየት ዕድል ይሰጣል Daymon (2005, 98)።

እኔም ዐይነታዊ መተንተኛ ስልትን ለጥናቱ ትንታኔ ተግባራዊ አድርጌያለሁ፡፡ ተግባራዊ ያደረግኩበት ምክንያት ከመስክ በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተገኘውን መረጃ በጥልቅ እና ሰፋ ባለ መልኩ ለመተንተን ስለአስቻለኝ ነው፡፡

**ፍካሬ የመተንተኛ ስልት**፡- ሌላው ለዚህ ጥናት ተግባራዊ የኾነው የፍካሬ መተንተኛ ስልት ነው፡፡ ስለ ፍካሬ ምንነት በርካታ ብያኔዎች ተሰጥተዋል፡፡[47] ፍካሬ የሚለው ቃል አንድን ጉዳይ በተለያየ መልኩ የጉዳዩን ቁመት፣ ወርድ እና ጠርዝ የሚተረጉም ነው፡፡ ክብረ በዓል ለፍካሬ ተገዥ መኾኑን Bell (1992, 186) "ክብረ በዓልን መረዳት ወይም ማወቅ

[46] በዚህ ጉዳይ ላይ Kothari (2004, 22) ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሰጥተውበታል፡፡

[47] *ፍካሬ ምንድን ነው? ደስታ ተክለወልድ (1962፡975) አዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት በሚል መጽሐፋቸው ውስጥ ፍካሬን "(ተረጎመ) ሙያውን፣ ዝብዱን ገለጠ፣ አስረዳ" በማለት ያብራራሉ፡፡ እንደዚኹም ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (1948፡700) ፍካሬን "ፈከረ፣ ተረጎመ፣ ፈታ፣ አፍታታ፣ ዘረዘረ ለማስረዳት፣ የሕልም የመጽሐፍ የቋንቋ" በማለት ይተረጉሙታል፡፡ መዝሙረ ዳዊት መጀመሪያው (መዝ፡1) ላይ "ፍካሬ ዘፀአድቃን ወዘኀጥአን መዝሙር ዘ ዳዊት ሃሌ ሉያ" በማለት የፃድቃንና የኃጥአን ትርጓሜ የሚል አንድምታ ይሰጣል፡፡ ዮናስ አድማሱ አስረኛዋንኳ ሀዲስ አለማየሁና ማኅበራዊ ሂስ ስልታቸው በሚለው Journal ላይ ስለ ፍካሬ ሲያብራሩ፤ "ልብ ወለድን ማንበብ ማለት በፊት ለፊት ከተነገረው ጀርባ ያለውን ትርጉምና አንድምታ (meaning and significance) ፈልፍሎ ማውጣት ማለት ነው፡፡ ይህንን ተግባር ፍካሬ (interpretation) እለዋለሁ" ይላሉ፡፡*

የሚቻለው በፍካሬ ነው፡፡ ክብረ በዓል በከፍተኛ ደረጃ የተለያየ ትእምርቶችና ማኅበራዊ ዕሴቶች ማሕቀፍ ነው፡፡ እነዚህን ዕሴቶች ደግሞ ለመረዳት የሚቻለው በትርጓሜ አማካኝነት ነው" በማለት ያጠይቃሉ፡፡

በመኾኑም የክብረ በዓሉን አንድምታ ለመረዳት በክብረ በዓሉ ክዋኔ ውስጥ የሚገኙትን ቁሳዊ ባህል፣ሥነ ቃል፣ ልማድ፣ ትውን ጥበባት፣ እምነት የመሳሰሉት ከማኅበረሰቡ ባህል ውክልና አንጻር መተርጎም እና መፈከር አለባቸው፡፡ የፍካሬ መተንተኛ ስልት በክብረ በዓሉ ውስጥ የሚሳተፉትን የማኅበረሰብ ክፍሎች ለመረዳት እና ለመገንዘብ ከፍ ያለ ዐቅም አለው፡፡ ፍካሬ የተሳታፊዎቹን፣ የከዋኞቹን፣ በአጠቃላይ የክብረ በዓሉን ተጠኚዎች በአንደበት ከሚናገሩት፣ በድምጽ ከሚገለጹት በላይ በቁስ፣ በምግብ፣ በአልባሳት፣ በንዋየ ቅድሳት የሚወክሏቸው እና የሚገልጿቸውን ትእምርት ለመረዳት ያስችላል፡፡ ፍካሬ በጥናት ትንታኔ ኺደት ውስጥ የማኅበረሰቡን የጾታ፣ የዕድሜ፣ የዕውቀት፣ የሃይማኖትና መሰል ጉዳዮችን ለመተንተን እና የጥናት ጥያቄዎችን ለመመለስ ያስችላል (Creswell 2010, 24)::

ከዚህ በመነሣት ክብረ በዓልን በፍካሬ ዐይን መመልከትና መተንተን ተገቢነት ይኖረዋል፡፡ እኔም የፍካሬ ስልት ለዚህ ጥናት የመረጥኩበት ምክንያት በክብረ በዓሉ ክዋኔ ላይ የሚገኙትን ቁሳዊ ባህል፣ ማኅበረሰባዊ ፍልስፍና፣ ተስፋ፣ ምኞት፣ ሕላዌ እና ሞት የሚሉትን በመተርጐም የለበሱትን ውክልና ለመተንተን ስላስቻለኝ ነው፡፡

### 3.1.8. የጥናቱ ሥነ ምግባር

ሥነ ምግባር ለአንድ አጥኚ ችላ የማይባል ወሳኝ ጉዳይና ግዴታ ነው፡፡ በተለይ የማኅበራዊ ሳይንስ፣ የሥነ ሰብእና የሥነ ዘውግ ተመራማሪዎች በመስክ ወቅትም ኾነ ከመስክ በኋላ የሚተገብሯቸው የሥነ ምግባር ግዴታዎች አሏቸው፡፡ ከግዴታዎቹ መካከል አንድ አጥኚ ለሚያሠራው ተቋም ዩኒቨርሲቲ፣ ኮሌጅ፣ ፋካልቲና ትምህርት ክፍል ታማኝ መኾን ይገባዋል፡፡ እንደዚሁም ለተጥኚዎቹ ማኅበረሰቦች ታማኝና እነሱን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሥራ ሊሠራ ይገባዋል (Berg L, Bruce,2001, 39)።

እንደ ዘርፉ ባለሙያዎች ፍረጃ እና አተያይ በርካታ የጥናት ሥነ ምግባር መርሖዎች አሉ፡፡ እነዚህ የሥነ ምግባር መርሖዎች በዐይነትም ኾነ በመጠን በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህ የሥነ ምግባር መርሖዎች መካከል እንደ Daymon እና Holloway, (2005, 78-82) አገላለጽ

በዐምስት አበይት ክፍሎች ይመለከቷቸዋል፡፡ እነሱም፡- የተጠኚዎችን ምርጫ መቀበል፣ ተጠኚዎቹን እና ግለሰቦችን ከሚጎዳ ማንኛውም ነገር መቆጠብ፣ የተጠኚዎችን የባለቤትነት መብት ማክበር፣ ታማኝ መኾን እና ከማጭበርበር መቆጠብ የሚሉት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል Atkinson እና Hammersley, (2007, 20) ደግሞ የጥናት ሥነ ምግባርን ሲገልጹ ከDaymon እና Holloway ጋራ ተቀራራቢ የሆኑ ነጥቦችን ሰንዝረዋል፡፡ እንዲኹም Berg L, Bruce, (2001, 39) ደግሞ አንድ አጥኚ ወደ መስክ ሲገባ  የማኅበረሰቡን ባህል አስተሳሰብና ዕሴት የሚያስጠብቁ የሥነ ምግባር መመሪያዎችን ዐውቆ እና ጠንቅቆ መግባት አለበት የሚል ማጠየቂያ ይሠነዝራሉ፡፡

ይህ ምርምርም ከላይ በዘርፉ ባለሙያዎች ተደጋግሞ እንደተገለጸው የጥናት ሥነ ምግባር መርሖች ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ በዚህም የጥናቱ ዐውድና ባህል በሚያዘውና በሚፈቅደው ልክ የተጠኚዎቹን ባህል፣ ሃይማኖት፣ ዕሴት፣ ፍልስፍና የመሳሰሉትን ማኅበረሰባዊ መዋቅር ባከበረና በጠበቀ መልኩ ጥናቱ ተካኺዷል፡፡ እንደዚኹም የጥናቱ ትንታኔ በተጠኚዎቹ መረጃ ላይ በመመሥረት በዋናነት (Emc perispective point of view) የተተነተነ ነው፡፡ ከጥናት ሥነ ምግባር መርሕ አንጻር በዚህ ጥናት የመረጃ ሰጪዎቹን ስም፣ ፎቶግራፍና መሰል ግብአቶችን በዐባሪነት ለመጠቀም የተጠኚዎቹ ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

### 3.2. የመስክ ተሞክሮ

በዚህ ጥናት ላይ የተጠቀሱት የመስክ ተሞክሮዎቼ በመስክ ጊዜ ያገጠሙኝን ተሞክሮዎች እና በወሰድኳቸው ወቅታዊ መፍትሒዎች ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ ይህም አንድ መስከኛ በመስክ ላይ እያለ ያልጠበቃቸው ገጠመኞች ሲከሰቱ እንዴት ማለፍ እንደሚችል ተሞክሮ ለማጋራት ከማሰብ ነው፡፡ ከዚህ ጋራ በተያያዘ ከብዙዎቹ ተሞክሮዎች መካከል ሦስቱን ብቻ በዚህ ጥናት ላይ አካትቻለሁ፡፡ ይህን ያደረግኩበት ምክንያት የተለያዩ የመስክ ተሞክሮዎቼ እና ገጠመኞቼ በጭብጥ ደረጃ በሦስቱ ሊገለጹ የሚችሉ ናቸው ብዬ ከማሰብ ነው፡፡

አንደኛው የመስክ ተሞክሮ በቀን 10/05/11 ዓ.ም የተፈጸመ ነው፡፡ ይህም የመስክ ሥራ ለመሥራት ወደ ጎንደር በኼድኩበት ወቀት የሚጠቀስ ነው፡፡ በዚኹ ዕለት በጎንደር ጥምቀተ ባሕር የከተራውን ሥርዐት ለመመልከት እና ለመረዳት ታደሜአለሁ፡፡ ታቦታቱ ወደ ጥምቀተ ባሕር ከወረዱ በኋላ በታቦት ማደሪያው የተለያዩ ምልከታዎችን ሳደርግ እና ስከታተል ሳይታወቀኝ ሰዓቱ እየመሸ ይኼዳል፡፡ ኹለት ፋሲል እና ደሴ የሚባሉ ዘመዶች

አሉኝ። እነሱ እየደጋገሙ ወደ ስልኬ ደውለው ነበር። ይኹን እንጂ ለምልከታዬ እንዳይረብሸኝ በማሰብ የስልኬን ድምጽ አጥፍቸው ስለ ነበር ያደረጉልኝን ተደጋጋሚ የስልክ ጥሪ አልሰማኹትም። ድንገት ሰዓቴን አውጥቸ ተመለከትኩ። ከምሽቱ 3:25 ይላል። ማደሪያዬ እና የዘመዶቼ ቤት አዘዞ መነኻሪያ አካባቢ ነው። ከጥምቀተ ባሕሩ ተነሥቶ አዘዞ ለመኼድ ከታቦት ማደሪያው እስከ ኮሌጅ እና ከኮሌጅ እስከ አዘዞ ቢያንስ ኹለት የባጃጅ መንገድ ያስኼዳል። ከመሸ በኋላ ደግሞ የጥምቀት ዋዜማ በመኾኑ ትራንስፖርት እንደ ልብ አይገኝም። በዚህ እና የማሕሌቱን ምልከታ ለመከታታል በማሰብ ከታቦት ማደሪያው ለማደር ወሰንኩኝ።

ይኹን እንጂ ቀኑ የገሀድ ጾም ስለነበር እና ሥራ ስለበዛብኝ ምሳ አልበላሁም። በዚህ ጊዜ ምግብ ፍለጋ ወደ ውጭ እንዳልወጣ ከወጡ በኋላ መመለስ አይቻልም። ወደ ካህናቱ ማረፊያ ድንኳን አመራሁ። ያመራሁትም በቅድሚያ እራቴን እበላለሁ፣ ቀጣይም ማሕሌቱን እከታተላለሁ ከሚል ዕሳቤ ነበር። ወደ ካህናቱ ማረፊያ ስገባ ውስጥ ያሉት ካህናት በአክብሮት ተነሥተው በዚህ ይምጡ ብለው ከአባቶች ካህናት በስተግራ ከዲያቆናት እና መዘምራን ደግሞ በስተቀኝ በኩል ካለው ምርፋቅ አስቀመጡኝ። በጣም እርቦኛል። ከአኹን አኹን ምግብ ይቀርባል እያልኩኝ ነው። ደግሞ አንድ ነገር እየታወሰኝ ነው። ገሀድ ስለዋሉ እና የጥምቀት ቅዳሴ ነግህ ስለኾነ እራት እሚበላ በጊዜ ነው። ድንኳኑ ደግሞ የተበላበት አይመስልም፤ እያልኩኝ ሳንሰላስል። ከአጠገቤ ያሉ ትልቅ ካህን “ቀደም ብለህ ቢሆን ከኛ ጋራ አብረህ ከሱታፌው እምትቀምሰውን” አሉኝ። በጎንደር ጥምቀት ዋዜማ አባ እንባቆም እንዳስረዱኝ ብዙም ድግስ የለም። *“እያመጡ የሚዘክሩ ብርቱ ሰዎች ነበሩ አልቀዋል። ሊቃውንቱ እና ካህናቱ ኹሉም ወደ ቤቱ ነው ኺዶ ቀምሶ የሚመጣ፣ እኛ ለመመለስ ይመሽብናል ብለን ነው። እንጂ እኽል ውሐ የሚያመጣ ብዙም የለም”* (አባ እንባቆም 10/05/11)[48]። በዚህ ጊዜ በውስጤ ማሰብ ጀመርኩኝ። ሐሳቤም እራት ልቅጣ ወይስ ምን ይሻለኛል? የሚል ነው። ይኹን እንጂ ምግብ እና ውሐ የማገኝበት አማራጭ ኹለት ዋጋ ሊያስከፍለኝ የሚችል እንደኾነ ተረዳሁ። አንድኛው ሰዓት ካለፈ በኋላ የሚደረገው ጉዞ ለዝርፊያ የሚያጋልጠኝ መኾኑ ነው። በእርግጥ በጎንደር ጥምቀት ሰሞን “የቀማ፣ ይመልሳል፣ የበደለ ይክሳል” የሚባልበት ክብረ

[48] በነጋው የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ሃላፊውን አቶ ቻሌን በፋሲል ሎጅ አግኝቻቸው ነበር። እኔም እንዴት ለካህናቱ የዋዜማ እህል ውሐ አይሄድም? የሚል ጥያቄ ጠይቂያቸዋለሁ። አቶ ቻሌ ብዙም ዕውቅናው እንደሌላቸው ተናግረው ግን ቅዱስ ቦታ ስለሆነ እህል ውሐ እንዲገባ የማይፈቀድ ሊሆን ይችላል የሚል የይኾናል መልስ ሰጥተውኛል።

በዓል ነው። ይሁን እንጂ "ያለ ሰዓት እየኼዱ ጅብን በደለኛ ያደርጋሉ" የሚለው የሀገሬው ብሂልም የሚረሳ አይደለም። እኔም በሃገሬው ብሂል መጽናት እንዳለብኝ ተሰማኝ። ሌላው እና ዋናው ደግሞ ከወጣሁ በኋላ መመለስ ስለማልችል የማሕሌቱ ምልከታ የሚያመልጠኝ መኾኑ ነው። "ማንን ብዬ ጽጌን ጾምኲት" እንደተባለው። በእነዚህ ኹለት መሠረታዊ ምክንያቶች ረሀቡን ለመቋቋ እና ምልከታዬን ለማስቀጠል ወሰንኩኝ። በውሳኔዬ መሠረት ረሀብና ጽሙን ውርጭ እና ቁሩን ተቋቁሜ የማሕሌቱን ምልከታ በሚገባ ተከታትያለሁ።

ከዚህ ላይ መጠቆም የፈለግኩት መስከኛ የጊዜ፣ የቦታ እና የዐውድ ችግሮች ሊያጋጥሙት እንደሚችሉ ቀድሞ መዘጋጀት እንዳለበት ለመጠቆም ነው። በመኾኑም አንድ አጥኚ መስክ ሲወጣ ከተለመዱት መሣሪያዎች በተጨማሪ ስሊፒንግ ባግ፣ ደረቅ ኮቾሮ እና መሰል አስፈላጊ ነገሮችን መያዝ እንዳለበት ለማስረዳት ነው። ሌላው እና ሦስተኛው ጥቆማዬ አንድ መስከኛ በተለይ የፎክሎር አጥኚ ዐልጋ በዐልጋ የኾነ የመስክ ሥራ ስለማይኖር ለሚደርሱት ችግሮች እንደ እኔ ጾም ሊያደር፣ ብርድ ሊመታ እንደሚችል ተዘጋጅቶ መግባት እንዳለበት ተሞክሮዬን ለማጋራት ነው።

ኹለተኛው የመስክ ተሞክሮ በመግቢያ ፈቃድ ምክንያት በኩል የሚጠቀስ ገጠመኝ ነው። የመግቢያ ፈቃድ ለመውሰድ ከባህልና ቱሪዝም ሃላፊው አቶ ቻሌ ጋራ ተደዋውለን ነበር። በወቅቱ አቶ ቻሌ የጥምቀት እንግዶች ስለነበሩባቸው ቋራ ሆቴል፣ ጃካራንዳ ሆቴል እና ፋሲል ሎጅ በመመላለስ እንግዶችን እያስተናገዱ እንደሆነ ነግረውኛል። ለኔ በሚመች እና በሚቀርበኝ ቦታ ፋሲል ሎጅ ተቀጣጥረናል። በቀጠሮዬ መሠረት ወደ ፋሲል ሎጅ እየኼድኩኝ እያለ ከዙብል ወደ ጥምቀተ ባሕሩ እየጨፈሩ የሚመጡ የእልፍኝ ጊዮርጊስ አካባቢ ልጃ ገረዶችን አገኘሁ። አለባበሳቸውን እና ጭፈራቸውን መመልከት ለሥራዬ አስፈላጊ እንደኾነ ተረድቻለኹ። ለልጃ ገረዶቹም የሚያቀነቅኗቸውን ቃል ግጥሞች በመቅረጸ ደምጽ ለመያዝ እና ለጥናቴ ፎቶግራፍ ለማንሣት ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር። እነሱም ፈቃደኝነታቸውን ስለሰጡኝ ስራዬን ፈጠን ብየ ጀምሬያለሁ።

ይኹን እንጂ ኹለት መጣቶች ከኋል፣ ከኋላ በቅርብ ርቀት እየተከተሏቸው ነበር። እኔ ግን የሚጨፍሩትን ልጃ ገረዶች እንጂ የሚከተሉትን ወጣቶች ተሳትፏቸው ፍዝ ስለነበር እንደ ጥምቀት አክባሪ እንጂ ልጃገረዶቹን እንደሚያጅቡ አላወቅኩም ነበር። ሥራዬን እየሠራሁ እያለሁ ከኋላዬ ምንድን ነህ? የሚል ድምጽ ድንገት ሰማሁ። ዘወር ስል ኹለት ወጣቶች

ናቸው። እኔም ምንነቴን እና ዓላማዬን አስረዳኋቸው። ይኹን እንጂ ነገሬን ለመቀበል ፈቃደኛ አልነበሩም። በዚህ ምክንያት የታለ ፈቃድህ? የሚል ጥያቄ አቀረቡልኝ። ልጃ ገረዶቹን አስፈቅጀ እኮ ነው አልኳው። ልጃ ገረዶቹም ምስክርነታቸውን አልነፈጉኝም ነበር። ፈቅደንለታል፤ ፈቅደንለታል፤ አሉ። ይኹን እንጂ ወጣቶቹ ልጃገረዶቹን "ያልጠሩት ምስክር" በማለት ምስክርነታቸውን ውድቅ አደረጉት። አንደኛው "በል ያነሣኸውን ፎቶ ደልት" ብሎ አዘዘኝ። እሺ ብየ የልጃ ገረዶቹን ፎቶ ብቻ ሳጠፋ ስል "ኧረ አይቻልም፣ በሙሉ የስልክህን አጥፋ ይልቅ" የሚል ትዛዝ አስተላለፈ። እኔም አንድም ብዙ የደከምኩባቸው፣ አንድም በቀላሉ የማላገኛቸው መረጃዎች አሉኝ። እንዴት ነው የማደርገው? የሚል ጥያቄ ተመላለሰብኝ። ከዚያ እንደመበሳጨት አሉና ከዚህ ይልቅ ሎሚ ይዘህ ብትወረውር አይሻልህም ነበር? አሉኝ። በዚህ ጊዜ እኔ እኮ በዚህ የምታማ አይደለሁም። አኹን ከእናንተ በፊት ወረብ ስወርብ ወልቆብኝ[49] እንጂ ብየ ከነጠላው ሥር የያዝኩትን ሻሽ አውጥቸ ጠመጠምኩኝ፣ ከዚያ በፊት ከላሊበላ ነው የመጣን ብለው የእጅ ምስቀል እና "ጎንደርን በጥምቀት" የሚል የተቀረጸበት መስቀል እየሸጡ ካገኘኋቸው ግለሰቦች መስቀሎችን ገዝቸ ነበር። ከሻሹ ጥምጠማው በተጨማሪ መስቀሉን ወጣ ሳደርግ አባቴ ይቅር ይበሉን አሉኝ። "ምን እናግዝዎት አየ የጥምቀት ኩታራ ቂም አትያዙብን።" ብለው ወደ ሰላም ተመለሱ። እኔም ሰላም ወርዶ የምፈልገውን ፎቶ ካሜራ እና ማስተወሻ በመያዝ ምልከታዬ አካኺጃለሁ።

ከዚህ ላይ አጽንዖት መስጠት የፈለግኩት አንድ ነገር ነው። ይኸም አንድ አጥኚ ወደ አንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ሲገባ ያ ማኅበረሰብ ከሥጋ እና ከነፍሱ ጋራ አቆራኝቶ የሚወደው እና የሚጠላው ምንድን ነው? የሚለውን ቀድሞ አውቆ ወደ መስክ መግባት ይኖርበታል። ከማወቅ ባለፈ የቻለውን ያክል መኾን አለበት ባይም ነኝ። በዚያ ቀን እኔ ተጠኚዎችን ባስፈቅድም ወጣቶቹን አለመገመቴ ለችግር ተዳርጌ ነበር። ይኹን እንጂ መስቀል በኪሴ፣ ሻሽ በራሴ እና የባህል ልብስ መልበሴ ከችግሩ አስመልጦኛል። አኹንም ደግሜ እማስረዳው አንድ አጥኚ የጥናቱን አካባቢ እና ኹኔታ ተረድቶ እና መስሎ ወደ መስክ መግባት እንዳለበት አጽንኦት እሰጣለሁ። ይኸኛው የመስክ ተሞክሮዬም የሚያረጋግጠው ይኸንኑ እውነታ ነው።

---

[49] በጣም የወረብ ችሎታ ያለው ካህን አቤት ሻሹ በሮ እስኪሄድ አወለቀው ይባላል። እና ወረብ ላይ ሻሽ መውለቅ የተለመደ ነው።

ሦስተኛው የመስክ ተሞክሮዬ በ11/05/2013 ዓ.ም ከታማኝ በየነ ጋራ በተያያዘ በጎንደር ጥምቀተ ባሕር ውስጥ የተፈጸመ ገጠመኝ ነው፡፡ በጎንደር ጥምቀት ታቦት እስኪነሣ ድረስ ያለው ድባብ የተረጋጋ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ወጣቶቹ፣ አዛውንቶቹ እና ልጃ ገረደሮቹ በባሕረ ጥምቀቱ ዙሪያ የሚዋኙትን ወጣቶች ከመመልከት ባለፈ ብዙም አይዋከቡም፡፡ ይህ ጊዜ ለእኔ ምቹ መኾኑን አረጋግጬ በማኅበር የተደራጁ እና የጥምቀቱን ክብረ በዓል በምንጣፍ ማንጠፍ፣ በማስከበር እና ውሐ ለጠማው ውሐ በማጠጣት ላይ የተሰማሩ ወጣቶች ጋራ በዐውዱ ውስጥ ከግብረ ገብነት አኳያ ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ፈልጌያለሁ፡፡ የእነዚህ ወጣቶች የጽዋ ማኅበሩ ሙሴ[50] ስንታየሁ ሙጨ ይባላል፡፡ በ11/12/ 2011 ዓም በነሐሴ ወር አግኝቻቸው ነበር፡፡ በወቅቱ ስለ ጥምቀት ክብረ በዓል እና ስለ ወጣቶቹ ግብረ ገብነት ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸው ነበር፡፡ ዛሬ ደግሞ በዐውዱ ተገኝተው እንዲያስረዱኝ እና ያለፈውን መረጃ ተአማኒነት ለማረጋገጥ ስለፈለግኩኝ ለኹለተኛ ጊዜ አግኝቻቸዋለሁ፡፡ ከጽዋ ማኅበር ወጣቶች ጋራ በጨረፍታ ከተወያየን በኋላ የጥምቀቱ ሥርዓት ስላልተጀመረ ለቃለ መጠይቅ አስፍቅጃቸው ይኹንታቸውን ገልጸውልኛል፡፡ በዚህ ተስማምተን ከታቦት ማደሪያው ወደ አንዱ ዛፍ ሥር በማምራት ቁጭ ብለናል፡፡ ከስምንቱ በተጨማሪ ሌሎች አራት ጓደኞቻቸው ለጊዜው እንደተጠፋፉ እና እንደሚፈላለጉ አጫውተውኛል፡፡ ለቃለ መጠይቁ ሰባቱ እንደሚበቁኝ ፈቃደኝነታቸውን ጠይቄ እሽ ብለውኛል፡፡

ከላይ እንደገለጽኩት ቦታ መርጠን ለ40 ደቂቃ የሚኾን ውይይት ለማድረግ ተስማምተናል፡፡ ከመካከላቸው ደረጀ ስመኝ የተባለውን ወጣት ቃለ መጠይቅ ማድረግ ጀምሬያለሁ፡፡ የጠየቅኩትን ጥያቄ አብራርቶ ሳይጨርስ የተለዩት አራቱ ወጣቶች ድንገት ከተፍ አሉ፡፡ “እናንተን በመፈለግ እኮ ደከምን የት ጠፍታችኹ ነው” የሚል ጥያቄ ጠየቋቸው፡፡ እኔ ቃለ መጠይቅ እያደረግኩለት ያለው ደረጀ “እኛንማ እያያችኹን ነው ይልቅ እናንተ የት ነበራችሁ?” አላቸው፡፡ እኛማ ከታማኝ በየነ ጋራ ነዋ፡፡ ፎቶ ስንነሣ የሚል ቃል ሲናገሩ ከኔ ጋራ የነበሩት ሰባቱ እና አንዱ ስምንተኛው ወጣቶች ግር ብለው ተነሡ፡፡ “ታማኝ ወዴት ነው ያለ? ሂዱ፣ እንሂድ” የሚል ወከባ ኾነ፡፡ በዚህ ጊዜ በቅጽበት አማራጭ ማንሰላሰል ጀመርኩኝ፡፡ ታማኝ በየነ በዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ትልቅ ቦታ ያለው ሰው ነው፡፡ በአውሮፕላን ከዐዲስ አበባ ጎንደር አብረን ኺደን እናውቃለን፡፡ ጎንደር ቴዎድሮስ አየር ማረፊያ ስንወርድ ሰው አንዱ ባንዱ ላይ እየተደራረበ ከፊት ከኋላ ለያዥ ለገራዥ አስቸግሮ

[50] ጽዋ ማኅበሩን የሚመራ የማኅበሩ አስተዳዳሪ፣ መሪ ነው፡፡

የነበረውን የፎቶ መነሣት ትርምስ አስታውሳለኹ። በመኾኑም እነዚህን ወጣቶች በዚህ ዐውድ ላይ ቃለ መጠይቅ ላድርግ ብል ፈቃደኝነታቸውም ኾነ ትክክለኛ መረጃ መስጠታቸው የማይታሰብ ነው። በጣም እየቸኮሉ እና እየተጣደፉ ነበር። ከእነሱ ዐልፎ እኔን "አንተም አብረህ እንኺድ እንጂ አታውቀውም ታማኝን? ነው አትወደውም? የሚል የተጣደፈ ጥያቄ ደረጀ አቀረበልኝ። እኔም "ኧረ በጣም ነው የምወደው ከእናንተም በላይ እወደዋለሁ። በሉ ፍጠኑ እንኺድ የኛን ነገ የቃና ዘገሊላ እናደርገዋለን።" በማለት የሙሴውን ስልክ ይዤ መንገድ በመጀመር እኔ ወደ ሥራየ ኺጃለሁ። በዚህ መልኩ የቃና ዘገሊላ ለሙሴው ደውየ በተረጋጋ ኹኔታ ቃለ መጠይቁን አከናውኛለሁ።

ከዚህ ላይ ለማሣወቅ የፈለግኩት ኹለት ጉዳችን ነው። አንደኛው ጥቆማዬ አንድ መስክኛ ለተፈጠረ ዐውዳዊ ጉዳይ ከመደናገጥ ይልቅ ዐውዳዊ መልስ መስጠት መቻልን መካን አለበት የሚል ነው። ኹለተኛው ማኅበረሰቡ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በጀግንነት፣ በደግነት፣ በብጹነት፣ በሀብት ይኹን በአንድ ጉዳይ ተመሥርቶ የሚወደውን ወይም የተቀበለውን ግለሰብ ማክበር እና ቅድሚያ መስጠት ተገቢ ነው። ይህኛው ተሞክሮዬም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። እኔም ቅድሚያ ለታማኝ በየነ ከመስጠት በተጨማሪ "አትወደውም እንዴ እንደ እኛ" ብሎ ላቀረበልኝ ጥያቄ "እወደዋለሁ እንጂ ካንተ አብልጬ፣ ፍጠኑ አብረን እንኺድ" የሚለውን ቅጽበታዊ መልስ መስጠቴ በተጠኝዎቹ ልብ ውስጥ ሳልገባ እንዳልቀረሁ በቃና ዘገሊላው ቃለ መጠይቅ አረጋግጫለሁ።

### 3.3. የጎንደር ከተማ አካባቢያዊ ዳራ

የጎንደር ከተማ በዐማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሥር የምትገኝ ነባር እና ታሪካዊ ከተማ ናት። ከክልሉ ርእሰ ከተማ ባሕር ዳር 174 ኪሎ ሜትር ርቀት አላት። ጎንደር ከሀገሪቱ ርእሰ ከተማ ዐዲስ አበባ ደግሞ በስተ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በ740 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች። ጎንደር በኢትዮጵያ ቀደምት ሥልጣኔ ካላቸው ከተሞች በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀስ ውብ ከተማ ናት። ይህች ከተማ በዐፄ ፋሲለደስ ዘመነ መንግሥት በ1628 ዓ.ም የተቆረቆረች ሲኾን ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ለ200 ዓመታት ያክል መናገሻ[51] ከተማ በመኾን አገልግላለች (የቱ.ሀ.መ. መ.[52]፣ 2009፣3 እና 2010፣ 3)።

---

[51] የቱሪስት ሀብቶች መስብ መጽሔት 2009፣3 እና 2010፣ 3 የኢትዮጵያ ዋና ከተማ በማለት ያስቀምጣል።
[52] የቱሪስት ሀብቶች መስብ መጽሔት

ከተማዋ ዘርፈ ብዙ የኾኑ ታሪኮች፣ የሥነ ሕንጻዎች፣ የባህሎችና የሥነ ጥበባት ባለቤት ናት። የጎንደር ከተማ በነበራት የነገሥታት መናገሻነት እና የሊቃውንት መፍለቂያነት እድል ምክንያት ለተጠቀሱት ትሩፋት እንዲኹም ለንግድ እና ለሥልጣኔ ማእከልነት አብቅቷታል (የቱ.ሀ.መ. መ.፣ 2009፣3 እና 2010፣ 3)። በመኾኑም የጎንደር ከተማ ባላት የየምጣኔ ሀብት እድገት፣ ሥልጣኔ፣ ሃይማኖታዊና ባህላዊ ትሩፋቶች ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ የሕዝብ ቁጥሯ በመጨመር ላይ ነው። በጎንደር ከተማ ወሳኝ ኩነት የተገኘው የሰነድ ማስረጃ እንደሚያሳየው ወንድ 197,770 እና ሴት 213,790 በድምሩ 411, 560 ነዋሪዎችን በውስጧ አቅፋለች (የጎንደር ከተማ ወሳኝ ኩነት ሰነድ፣ 2011)።

ከተማዋ በክፍለ ከተማና በገጠር ቀበሌዎች የተዋቀረች ናት። ጎንደር ከተማ ከእነዚህ መካካል ፋሲል ክፍለ ከተማ፣ ጃንተከል ክፍለ ከተማ፣ አራዳ ክፍለ ከተማ፣ ዞብል ክፍለ ከተማ፣ ማራኪ ክፍለ ከተማና አዘዞ ጠዳ ክፍለ ከተማ በተባሉ ስደስት ክፍለ ከተሞች የተዋቀረች ናት። እንደዚሁም ልደታ፣ አንችው፣ ሳቢያ ሳይና፣ ድባ ደፈጫ፣ ብላጅግ ደብርቋ፣ ክልል ኢየሱስ፣ ሎዛ ማርያም፣ ላይ ጤና፣ አዘዞ ተ/ ሃይማኖት፣ ደረስጌ ማርያም እና አባ እንጦንስ የሚባሉ ዐሥራ አንድ የገጠር ቀበሌዎችንም በውስጧ ዐቅፋለች (የጎንደር ከተማ ወሳኝ ኩነት ሰነድ፣ 2011)።

### 3.3.1. የጎንደር ከተማ መሠረተ ልማት

የጎንደር ከተማ የሥልጣኔ፣ የዕውቀትና የንግድ ማእከል ከመኾኗ ጋራ ተያይዞ በከተማዋ የተለያዩ የመሠረተ ልማት ዝርጋታዎች ይታያሉ። ከእነዚህ መካካል የዐፄ ቴዎድሮስ አየር ማረፊያ፣ የጎንደር ዩኒቨርስቲ፣ ከዐዲስ አበባ ተነስቶ በስተ ሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ ኢትዮጵያን ከሱዳን ካርቱም የሚያገናኘው የአስፋልት መንገድ ለከተማዋ እድገት እንደ ፋና ወጊ የሚጠቀሱ ናቸው። ከተማዋ በስተ ሰሜን ምዕራብ ኢትዮጵያ በኩል ያለውን የንግድ ቀጣና በዋናነት በመቆጣጠር ትልቅ የግብይት ማእከል ኾና ታገለግላለች። በተለይ የአራዳ፣ የፒያሳና የአዘዞ የገበያ ቦታዎች እሑድን ሳይጨምር ስድስቱን ቀናት የተጧጧፈ የግብይት ሥርዓት ይካኼድባቸዋል። ከተማዋ የአርማጭሆ፣ የደባርቅ፣ የደምቢያ፣ የቋራ፣ የገንዳ ውሐ፣ የመተማ፣ የሽዲ፣ የበለሳ፣ የጎንደር ዙሪያ፣ የጭልጋ፣ የዳባት፣ የደልጊ፣ የአለፋ፣ የጣቁሳ፣ የአርባያ፣ የንሀላ፣ የእንፍራዝ፣ የአምባጊዮርጊስ፣ የበየዳ፣ የጯሂት፣ የጎርጎራ፣ የገደብዬ፣ የኮሰዬ፣ የእንፈራዝ፣ የአደርቃይ እና መሰል ወረዳዎች እና ከተሞች የኢኮኖሚ

ፍሰት ማዕከል ናት፡፡ በምዕራብ አቅጣጫ የሚገኙ ቦታዎች ከፍተኛ የሰሊጥና የጥጥ ምርት የሚገኝበት አካባቢ በመኾኑ ለከተማዋ የንግድ ልውውጥ ጉልሕ ድርሻ አላቸው፡፡ እንደ ደስ ያሉ የጥጥ መዳመጫ ፋብሪካዎች፣ በርካታ የሆኑ የሰሊጥ መጋዘኖች፣ ማከፋፈያዎችና ማጣሪያዎች በከተማዋ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እንደዚሁም በአዘዞ ጠዳ ክፍለ ከተማ የዲማዛ ወንዝን ተከትሎ የሚገኘው የኢንዱስትሪ መንደር በጅማሮ ደረጃ ያለ ቢሆንም ተጠናቆ ወደ ስራ ሲገባ ለከተማዋ እድገት ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል (የጎንደር ከተማ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ መረጃ 2011)፡፡

ጎንደር የውጭ ዲየስፖራዎች በርከት ብለው የሚገኙባት ከተማ በመኾኗ በአንድም ኾነ በሌላ መንገድ ከተማዋ ደመቅመቅ ብላ እንድትታይ አድርጓታል፡፡ ጎንደር ከተማ በርካታ እንግዶች፣ ጎብኚዎች እና ዲያስፖራዎች በየጊዜው የሚጎበኟት ከተማ ናት፡፡ እነዚህን እንግዶች ሊመጥኑ የሚችሉ ደረጃቸውን የጠበቁ ሆቴሎች አሏት፡፡ ከእነዚህ ሆቴሎች እና ሎጆች መካካል ጉሐ ሆቴል፣ ዴንማርክ ሆቴል፣ ፍሎሪዳ ሆቴል፣ ቋራ ሆቴል፣ ኤጅ ሆቴል፣ ታየ በላይ ሆቴል፣ ዳውን ታውን ሆቴል፣ ጃካራንዳ ሆቴል፣ ሽንኮራ ሆቴል፣ ላመርግየር ሆቴል እና ፋሲል ሎጅ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ የጎንደር ከተማ ካላት ምቹ የመሠረተ ልማት ዕድል አኳያ በበቂ ኹኔታ የልማት እንቅስቃሴ አለ ለማለት ያስቸግራል፡፡ ይሁን እንጂ በብዙ መልኩ ለነዋሪዎቿ የምትመችና በመሠረተ ልማትም ቢኾን በርካታ የተጠናቀቁና ጅምር ልማቶች የሚንቀሳቀሱባት ከተማ ናት (የጎንደር ከተማ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ መረጃ፣ 2011)፡፡

### 3.3.2. የጎንደር ከተማ መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ

የጎንደር ከተማ የተመሠረተችበት ቦታ ተራራማ፣ ሜዳማ እና ወጣ ገብነት ያለው ነው፡፡ ይህ አመሠራረት ነገሥታቱን ከጥቃት ለመከላከል ትልቅ አገልግሎት ይሰጡ እንደ ነበር ይነገራል፡፡ ከእነዚህ ተራራማ ቦታዎች መካከል የጉሐ ሆቴል የሚገኝበት ተራራ፣ የማራኪ የብላጅግ፣ የደፈጫ ኪዳነ ምሕረት እና የሎዛ ማርያም ተራራዎች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከተማዋ በተራሮች የተከበበች በመሆኗ ምክንያት ወይና ደጋ እና ለአዝርዕት ምቹ የኾነ የአየር ንብረት አላት (የጎንደር ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት መረጃ፣ 2011)፡፡

የጎንደር ከተማ ወደ ጣና ሐይቅ የሚፈሱ የዓባይ ገባር ወንዞች ባለቤት ናት፡፡ ከእነዚህ ወንዞች መካከል የዲማዛ ወንዝ፣ የሽንታ ወንዝ፣ የቀሐ ወንዝ፣ የአንገረብ ወንዝ እና

የመገጭ ወንዞች ይገኛሉ፡፡ ለከተማዋ የመጠጥ አገልግሎትና መናፈሻ እንዲውል ታስቦ እየተሠራ ያለው የመገጭ ግድብ ፕሮጀክት እንደ ትልቅ የልማት አቅጣጫ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የጎንደር ከተማ ገጽታ ከውጭ ሲታይ በእንቁላል ቅርጽ የተገነቡ ሕንጻዎች ይገኙባታል፡፡ ጥምቀተ ባሕሩን፣ አድባራቱን እና ፋሲል ዙሪያ ገባውን ጨምሮ ትልልቅ የዋርካ እና የችብሐ ዛፎች እጅብ ብለው ይታዩባታል፡፡ ከዛፎቿ መካከል የጃንተከል ዋርካ ለከተማዋ መገለጫና የቱሪስት መስሕብ በመኾን ያገለግላል (የጎንደር ከተማ ኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት፣ 2011)፡፡

### 3.3.3. የከተማዋ የልህቀት ማእከልነት

የጎንደር ከተማ ገናናነት፣ ስመጥር ወይም እንደ መለያ ከምትጠቀስባቸው ምክንያቶች መካከል የቀደምት መናገሻ ከመኾኗ በተጨማሪ የዕውቀት ማእከል መኾኗ ነው፡፡ ከተማዋ ከነጋሥታቱ ጋራ ተያይዞ የበርካታ ሊቃውንት መፍለቂያ በመሆን እስካለንበት ዘመን ድረስ ቀጥላለች፡፡ በጎንደር ከተማ በበርካታ ጉባኤ ቤቶች መምህራን ወንበር ተክለው፣ መጽሐፍ ገልጠው የሚያስተምሩባቸው አድባራት በርካታ ናቸው፡፡ ከእነዚህ አድባራት መካካል የጎንደር ልዩ መታወቂያ የኾኑት የጎንደር አቋቋም እና የጎንደር 4ቱ ጉባኤ ቤቶች ተጠቃሾች ናቸው (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ፣ 2011 ቃ. መ)፡፡

የታች ቤት አቋቋም በጎንደር በዓታ ለማርያም ውስጥ ምስክር ጉባኤ ቤት በመሆን ያገለግላል፡፡ ጉባኤ ቤቱ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍል በአቋቋም ዕውቀታቸው ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ሊቃውንት ለማስመስከርና የምስክር ማዕረግ ለማግኘት የሚማሩበት ነው፡፡ በተለይ ተማሪዎቹ ከወሎ፣ ከጎንደር፣ ከትግራይ፣ ከሸዋ፣ ከጎጃምና መሰል የሀገሪቱ ክፍል ወደዚህ የምስክር ጉባኤ ቤት ይመጣሉ፡፡ ከነገሥታቱ ጀምሮ የጎንደሬ አቋቋም እስካሁን ድረስ የጎንደር ተምሳሌትና መገለጫ እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ ማኅበረ ቅዱሳን ጉባኤ ቤቱን በማሠራት እና ለተማሪዎች ሠርከ ኅብስት በመቻል ትልቅ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ 2011 ቃ. መ)፡፡

ሌላው በጎንደር ምስክር ከሚሰጥባቸው ጉባኤ ቤቶች መካከል አንዱና ታዋቂው የአንድምታው የምስክር ጉባኤ ቤት ነው፡፡ ጉባኤው በዐፄ ፋሲል ከታነጹት አብያተ ክርስቲያናት መካከል ተጠቃሽ በኾነው በመንበረ መንግሥት መድኀኔዓለም ይገኛል፡፡ ጉባኤ ቤቱ የብሉያትና የሐዲሳት ትርጓሜ ምስክር የሚሰጥበት ሲኾን በ4 ዐይናው ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ

ይመራል። በብሉያትና ሐዲሳት ትርጓሜ ከፍተኛ ደረጃ የደረሱ ሊቃውንት ለማስመስከር ሲሉ ወደዚህ ጉባኤ ቤት ይታደማሉ። ጉባኤ ቤቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ከዘመን ወደ ዘመን እየተሸጋገረና እየጨመረ መምጣቱ በሚዘጋጁት መጻሕፍት መረዳት ይቻላል።



*(በጉባኤ ቤቱ እየተዘጋጁ ያሉ መጻሕፍትና አራት ዐይናው ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ)*

በጎንደር የትርጓሜ ቤቱና የጎንደሬ አቋቋም ምስክርነት ከነገሥታቱ ጀምሮ እየተሸጋገረና እየጨመረ የመጣ የጎንደር መገለጫ ነው። ጠቅለል ባለ ምልኩ በምስክርነት የሚሰጡት የታችቤት አቋቋም በበዓታ ለማርያም፣ በቀሐ ኢየሱስ የላይ ቤት አቋቋም እና በመንበረ መንግሥት መድኀኔዓለም የትርጓሜ ማስመስከሪያው ተጠቃሾች ናቸው። ከዋና ጉባዔ ቤቶቹ

በተጨማሪ ጎንደር የድጓ፣ የቅኔ፣ የዝማሬ መዋሥዕት፣ የዜማና የቁጠር ጉባኤ ቤቶች ባለቤት ናት (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ 2011 ቃ. መ)።

### 3.3.4. የከተማዋ ታሪካዊ ቅርሶች

የጎንደር ከተማ ከነበራት የሥነ ሕንጻ ትሩፋት፣ የባህልና፣ የታሪክ አሻራ አኳያ የበርካታ ቅርሶች ባለቤት ናት። እነዚህ ቅርሶቿ ታሪካዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ አንድምታ ያላቸው ናቸው።

#### 3.3.4.1. የዐፄ ፋሲል ግቢ

ይህ ግንብ በጎንደር ከተማ ውስጥ የሚገኝ የከተማዋ አውራ ምልክት ነው። ግንቡ ከጎንደር ከተማ ዐልፎ ለሀገራችን በቅርስነቱ እና በቱሪስት መስሕብነቱ ትልቅ ድርሻ አለው። የዐፄ ፋሲል ግንብ 70,000 ካሬ ሜትር እና 900 ሜትር እርዝመት አለው። የዐፄ ፋሲል ግቢ ዐሥራ ኹለት በሮች፣ ሦስት አብያተ ክርስቲያናት፣ ስድስት አብያተ መንግሥታት እና ሌሎች ቀደምት ሕንጻዎችን አካቶ የያዘ ነው (የቱ.ሀ.መ. መ. ቅጽ 6 ቁ. 9፣ 2010፣3)።



*(የዐፄ ፋሲል ግንብ 2011 በአጥኚው የተነሣ ፎቶ ግራፍ)*

በግቢው ውስጥ ከሚገኙት አብያተ ነገሥታት ግንቦች መካካል አንዱና ዋናው የዐፄ ፋሲል ቤተ መንግሥት ነው። በመቀጠል የዐፄ ዮሐንስ ቤተ መንግሥት፣ የዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ ቤተ መንግሥት፣ የዐፄ ዳዊት ቤተ መንግሥት፣ የዐፄ በካፋ ቤተ መንግሥት፣ የእቴጌ ምንትዋብ ቤተ መንግሥት እና የኢያሱ (ቋረኛው) ቤተ መንግሥት ሕንጻዎች ተጠቃሾች ናቸው። ፊት አቦ፣ ፊት ሚካኤል፣ አደባባይ ኢየሱስ፣ ግምጃቤት ማርያም፣ እልፍኝ ጊዮርጊስ፣ መንበረ መንግሥት መድኀኔዓለም እና ደብረ ምሕረት አቡን ቤት ቅዱስ ገብርኤል ዐፄ ፋሲል በዋናነት ያሠሯቸው አብያተ ክርስቲያናት ናቸው። ንጉሡ በመጨረሻ ማንኪት ከሚባለው ቦታ ላይ የጥምቀተ ባሕር መከበሪያውን ቤተ መቅደስ አሠርተዋል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 2011 ቃ.መ)።



*(መንበረ መንግሥት መድኀኔዓለም የአንድምታው ጉባኤ ቤት የሚገኝበት 2011)*

### 3.3.4.2. ራስ ግንብ

ይህ ግንብ ከዐፄ ፋሲል ግንብ በስተሰሜን ምዕራብ አቅጣጫ በቅርብ ርቀት የሚገኝ ነው። ግንቡ በማን እና መቼ እንደተሠራ በትክክልና መረጃ እንደሌለ መዛግብቶች ያስረዳሉ። በግንቡ ላይ የሚገኘው ጽሑፍ ግን በእቴጌ ምንትዋብ እንደታነጸ የሚጠቁም ነው። ይህ ግንብ በጣሊያን ወረራ ጊዜ ለጀነራሎች መኖሪያነት፣ በዐፄ ኀይለ ሥላሴ ደግሞ ለሰሜኑ ጠቅላይ ግዛት በቤተ መንግሥትነት ሲያገለግል በደርግ መንግሥት ደግሞ በእስር ቤትነት

አገልግሏል፡፡ በጎንደር እና አካባቢው የሚገኙ ታሪካዊ እና ባህላዊ ቅርሶችን ወደ አንድ በማሰባሰብ ግንቡን ወደ ሙዚየም ለማምጣት በአሁኑ ሰዓት እየተሠራ ነው (መስሐብ ቅጽ 6 ቁ. 9፣ 2009፣ 6)፡፡



*(ራስ ግንብ በ2011 በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ)*

### 3.3.4.3. የጥምቀተ ባሕር ግንብ

ይህ የጥምቀተ ባሕር ግንብ በቆየው እና በሌላ አጠራር የዐፄ ፋሲለደስ መዋኛ እየተባለም ይጠራል፡፡ ግንቡ በጎንደር ከተማ ማዕከል ላይ በቅሐ እና በአንገረብ ወንዞች መካከል ማንኪት ከሚባለው ቦታ ይገኛል፡፡ የግንቡ አሰራር የእንቁላል ቅርጽ ያለው እና ዙሪያው በኖራ የተገረፈ ነው፡፡ የመዋኛ ግንቡ ዐፄ ፋሲለደስ ካሰሯቸው ስምንት አብያተ ክርስቲያናት መካካል በመጨረሻ ያስገነቡት ነው፡፡ ግንቡ ፎቅና ምድር ያለው ሲኾን በጥምቀት ክብረ በዓል ትልቅ የኾነ ግልጋሎት ይሰጣል፡፡ ግንቡ ከፋሲል ግንብ ቅጥር በእስተምዕራብ አቅጣጫ ኹለት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በቀሐ ወንዝ ዳርቻ ይገኛል፡፡ የግንቡ ስፋት 50 ሜትር በ30 ሜትር ስፋት ያለው ነው፡፡ በዙሪያውም 6 የዕንቁላል ግንቦች ይገኛሉ (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 2011 ቃለ መጠይቅ እና የቱ.ሀ.መ. መ.፣ 2010፣6)፡፡



*(የጥምቀተ ባሕር ግንብ 2011 በአጥኝው የተነሣ ፎቶ ግራፍ)*

የጎንደር ከተማ ከዐፄ ፋሲል በኋላ በነገሡ የተለያዩ ነገሥታት የተገነቡ የ#4ቱ አድባራት ባለቤት ናት፡፡ ከእነዚህ መካካል በጎንደር ከተማ ታሪካዊና ከ#4ቱ አድባራት የሚመደበው አንዱ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ነው፡፡ ደብረ ብርሃን ሥላሴ በ1674 ዓ.ም በአፀዌ ኢያሱ አድያም ሰገድ ዘመነ መንግሥት የተሠራ ታሪካዊ ደብር ነው፡፡ የቤተ ክርስቲያኑ ሕንጻ አሠራር፣ የቅዱሳን ሥዕላት አሣሣልና የቤተ ክርስቲያኑን ቅጽር ግቢ በአስተውሎት ሲመለከቱት መንፈስን እና ቀልብን የመሳብ ኀይሉ ከፍተኛ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ በ1880ቹ ዓ.ም በድርቡሾች ወረራ ጊዜ ለማቃጠል ያደረጉት ሙከራ በታቦቱ ታምረኛነት ሳይሳካ መቅረቱ ይነገራል (የቱ.ሀ.መ. መ.፣ 6 ቁ. 9 2009፣4፤ 20010፣6)፡፡


ሌላው ዐፄ ፋሲል ካሰሯቸው አብያተ ክርስቲያናት ውጭ ተጠቃሽ የኾነችውና በእቴጌ ምንትዋብ እንደታነጸች የምትታወቀው የደብረ ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ በቤተ ክርስቲያኗ ዙሪያ የእቴጌ ምንትዋብ አዳራሽና ፍርስራሽ ሕንጻዎች የገኛሉ፡፡ ቤተ ክርስቲያኗ በድርቡሾች ወረራ ጊዜ ቃጠሎ እንደደረሰባት እና በዐፄ ኀይለ ሥላሴ ዕድሳት እንደተደረገላት ይነገራል፡፡ በቁስቋም ቤተ ክርስቲያን ቅጽር ውስጥ የእቴጌ ምንትዋብ አዳራሽ፣ የጀምስ ብሩስ ቤተ መዛግብት፣ የእቴጌ ምንትዋብ እና የቋረኛው ኢያሱ ዐፅሞች ያረፉበት ቅዱስ ቦታ ነው (የቱ.ሀ.መ. መ.፣ 6 ቁ. 9 2009፣4፤ 20010፣6)፡፡

ሌላው ተጠቃሽ የአዘዞ ተክል ሃይማኖት ደብር ነው፡፡ አዘዞ ተክል ሃይማኖት ከ#4ቱ አድባራት አንዱ ሲኾን በመካከለኛው ዘመን በነበረው የቅባት፣ ጸጋና ተዋሕዶ እምነት

ተቃርኖ ምክንያት በርካታ መነኮሳት የተሰየፉበት ቦታ ነው ይባላል፡፡ የዐዜ ስሱንዮስ ዐፅምና ሌሎች ቅርሶችም በደብሩ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በጎንደር ከተማ ከሚገኙ ጥንታውያን እና #4ቱ አድባራት መካከል ደፈጫ ኪዳነ ምሕረት፣ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ግምጃ ቤት ማርያም፣ አባጃሌ ተክለ ሃይማኖትና ሌሎችም ተጠቃሾች ናቸው፡፡

### 3.3.4.4. የጎንደር ከተማ ሕዝብ እና ሃይማኖት

የጎንደር ከተማ ሕዝቦች በአብዛኛው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡ በመቀጠል በከተማዋ የሚኖሩት የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ብዙውን ቁጥር ይይዛሉ፡፡ በቁጥር አንስተኛ ቢኾኑም የፕሮቴስታንት እና የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮችም በከተማዋ ውስጥ ይኖራሉ፡፡ ከነገሥታቱ ጀምሮ በርካታ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት የሚስተናገዱባት ከተማ ናት፡፡ ይህ ትውፊት ከትውልድ ትውልድ እያደገ መጥቶ በአኹኑ ወቅት የጥምቀት እና የመስቀል ክብረ በዓላት በከተማዋ በድምቀት ይከበራሉ፡፡ በተለይ የጥምቀት ክብረ በዓል በጎንደር ካለው የክብረ በዓል ድምቀትና የማኅበረሰባዊ መገለጫ ምክንያት ትልቅ የኾነ የኢኮኖሚ፣ የቱሪስት፣ የማኅበራዊ ትስስርና የልማት ምንጭ እየኾነ መጥቷል፡፡ በዚህ ምክንያት የጎንደርን ጥምቀት በናሙናነት በመውሰድ በዩኒስኮ ለማስመዝገብ የፌደራል ቅርስና ጥናት ጥበቃ ባለሥልጣንና የዐማራ ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ርብርብ በማደረግ ላይ ነበሩ (የቱ.ሀ.መ. መ.፣ 6 ቁ. 9፣ 2010፣ 7)፡፡ ይህ ጥረት ተሳክቶ በ2012 ዓም በወርኀ ታኅሣሥ በዩኒስኮ ሊመዘገብ ችሏል፡፡ ይህ ጥናትም በጎንደር ከተማ በየ ዓመቱ በድምቀት የሚከበረው የጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የተመሠረተ ነው፡፡




*(የጎንደር ከተማን የሚያሳይ ካርታ ከጎንደር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የተገኘ 2011 ዓ.ም)*

## ምዕራፍ አራት፡- የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ዐውድ

በዚህ ምዕራፍ ሥር ቅድመ ጥምቀት፣ ከተራ እና ዕለተ ጥምቀት የሚሉት የጥምቀቱ ዐውድ ክዋኔዎች እና አንድምታዎች ተተንትነው የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡

### 4.1. ቅድመ ጥምቀት

የጎንደር ጥምቀት ዝግጅት ከወር በፊት ይጀምራል፡፡ ጥምቀት መምጣቱና መቃረቡ የሚታወቀው በብዙ ምልኩ ነው፡፡ ከእነዚህ መካከል አንዱ የልጆችና የልጃ ገረዶች እንቅስቃሴ ነው፡፡ ልጆች የጥምቀት ነፋስ መንፈስ ሲጀምር የተለያዩ እና ለክብረ በዓሉ የሚሆኑ ተግባራትን ይፈጽማሉ፡፡ ከእነዚህ የልጆች ተግባራት መካከል የገጠር ልጆች ሽልም ግና ከእምብስ ዛፍ፣ እንቁር ከክትክታ እና ቴልቱላ ደግሞ ከሸምበቆ ወይም ከቅል ቀርጸው ያዘጋጃሉ፡፡ እንቁሩ አንድም የአዳም እዳ ደብረዳቤ፣ አንድም የጎንደር ማኅበረሰብ ባላንጣ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሽልም ግናው ደግሞ አንድም የክርስቶስን ጥምቀት አንድም የጎንደርን ነገሥታት ይተረጉማል፡፡ በዚህም የአዳም እዳ ደብዳቤ በክርስቶስ ጥምቀት እና የጎንደር በአላንጣ ደግሞ በጎንደር ነገሥታት ይወገዳሉ (የአብሥራ ለገሰ፣19/04/11 እና አቶ ጠጋነው ደምሴ 25/05/2012 ቃ.መ)፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በጎንደር ዙሪያ የሚኖሩ የገጠር ልጆች እና እረኞች በውሏቸው የተለያዩ ዘፈኖችን እና ጭፈራዎችን ይለማመዳሉ፡፡ ልምምምድ የሚያደርጉት ከብቶችን በሚያገዱበት ውሐ በሚያጠጡበት እና ከውሏቸው ወደ ቤት ከብቶቻቸውን በሚያቀርቡበት ሰዓት ነው፡፡ የጥምቀትን መቃረብ ተከትሎ በሚያደርጉት የእስክስታ ልምምድ፣ የሽልምግና እና ቴልቱላ ዝግጅት ምክንያት ልጆች፣ እረኞች እና ልጃ ገረዶች የደስታ ስሜት በውስጣቸው ይታይባቸዋል፡፡ ልጆቹ እስክስታ የሚለማመዱት ከመሰል ጓደኞቻቸው ጋራ አንድ ለአንድ በመግጠም ነው፡፡ ከብት የሚያግዱት ለብቻ ከሆነና አጣማጅ ካጡ ደግሞ ከራሳቸው ጥላ ጋራ የእስክስታ ችሎታቸውን እየተገነዘቡ ይለማመዳሉ፡፡ በእነዚህ ቅድመ ድርጊቶች የጥምቀት ድባብ መዳረሱ በእረኞች እና ልጆች ዘንድ ይበሰራል (የአብሥራ ለገሰ፣ 19/04/11 እና አቶ ጠጋነው ደምሴ 25/05/2012 ቃ.መ)፡፡

የጎንደር ጥምቀት መቃረብ የሚታወቀበት ሌላው መንገድ የልጃ ገረዶቹ ዝግጅት ነው፡፡ ልጃ ገረዶቹ የጎንደር ጥምቀት ሲቃረብ በቁልፍ ያሸበረቀ ጀርሲ ይለብሳሉ፤ ሹርባ ይሠራሉ፤ ኩል

ይቀባሉ፤ ድሪ እርባን እና አልቦ የመሳሰሉትን መዋቢያዎች እየገዙ እና እያስገዙ ያጌጣሉ፡፡



*(በቁልፍ ያጌጠ ጀርሲ የለበሱ፣ ድሪ ያሰሩ እና ሹርባ የተሠሩ ልጃ ገረዶች በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ 2013)*

ልጃ ገረዶቹ ያላቸውን የውበት ማማር ይሁን ማጌጥ እነሱን በሚመስሉ አቻ ሴት ጓደኞቻቸው ያስተቻሉ፡፡ ከጓደኞቻቸው ጋራ እየተቀያየሩ የጥልፍ ቀሚሱን፣ መቀነቱን እና የመዋቢያዎቹን ማማር ይለካሉ፡፡ የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ከመቸውም በላይ በጎንደር ጥምቀት ልጃ ገረዶች አምረው እንዲውሉ ይፈቅዳል፡፡ ከዚህ ጋራ በተያያዘ (የአብሥራ ለገሰ፣ 19/04/11 *ቃ.መ*) “የአምና ጥምቀት እኔን ገደልክ፣ ዘንድሮ ደግሞ ማንን ትገድል ይኾን” ይባላል” የሚል መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ የዚህን ምሳሌያዊ ንግግር ዋና ጭብጥ እና ትርጉም እንዲያስረዱኝ ለየአብሥራ ለገሰ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ በጎንደር ጥምቀት ማንኛዋም ልጃ ገረድ አምራና ተውባ ስለምትወጣ ዐዓይን ዐዋጅነት፣ ከጉጉነት እና ከመጎምጀት ያለፈ ማበላለጥ አይቻልም፡፡ በዚህ ምክንያት ዞማዋን፣ ከኪንኪዋ እና ሰልካካዋን ከጎራዳዋ ለመለየት ይከብዳል የሚል መልስ ሰጥተውኛል፡፡ ይህ አንድምታ የሚያሳየው የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ለልጃ ገረዶች ከፍ ያለ መዋቢያና መድመቂያ ጊዜ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ልጃ ገረዶቹ በተመልካቾቻቸው ሲታዩ አንድ ዐይነት ወይም ወደ አንድ ዐይነት የተጠጋ ተክለ ቁመና አለባበስ እና አጊያጊያጥ አላቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ኹሉም ተመራጭ እንጂ ምራጩ የሚሆኑበት አጋጣሚ ያለ አይመስልም፡፡ በጎንደር ጥምቀት ይችኛዋ ከሌለኛዋ ትበልጣለች ወይም ታንሳለች ብሎ ከማወዳደር እና ከማነጻጸር ይልቅ በአንድ ላይ ከዓመት ያድርሳችሁ ብሎ ፈጣሪያቸውን ማድነቅ ይቀላል (መ/ር[53] ዳዊት ሥራው፣17/05/2012 ቃ.መ)፡፡

የጥምቀት ዐውድ ልጃ ገረዶች ፈክተውና አብበው የሚታዩበት ልዩ የኾነ ውበትን የሚጎናጸፉበት ድባብ ነው፡፡ ከዚህ በመነሣት የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ለሴት ልጆች የሚያስገኘው ፋይዳ ላቅ ያለ ነው፡፡ ከፋይዳዎቹ መካከል ነጻነት አንዱ ነው፡፡ የጎንደር ልጃገረዶች በአካባቢው ማኅበረሰብ ባህልና ሃይማኖት መሠረት እንቅስቃሴያቸው የተገደበ ነው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከአንድ ቦታ ተነሥተው ወደ ሌላ ቦታ ሲኼዱ እንኳን ወንድ ልጆችን ከኋላ አስከትለው ይኼዳሉ (የአብሥራ ለገሰ፣ 19/04/11 ቃ.መ እና ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡

ሴት ልጅ ብቻዋን ወንዝ አትሻገርም፤ ቀድማ አትናገርም፤ የሚለው የማኅበረሰቡ ነባር ልማድ በጥምቀት ክብረ በዓል ድል ይኾናል፡፡ በጥምቀት ልጃ ገረዶች የፈለጉትን ለብሰው ከፈለጉት ጋራ ተጫውተው፣ ዘፍነው፣ ጨፍረው እና ራሳቸውን አስደስተው የሚውሉበት ቀን ነው፡፡ በመሆኑም የጎንደር ጥምቀት ሲቃረብ ሴት ልጆች የመፍካት፣ የማማር እና የመዋብ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት እየተቃረበ እንደኾነ መረዳት ይቻላል (ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011 እና አቶ ጠጋነው ደምሴ 25/05/2012 ቃ.መ)፡፡

[53] መሪ ጌታ ማለት ሲኾን በቤተ ክርስቲያኗ ዘንድ ከፍ ያለ የዕውቀት ደረጃ ያላቸው ሊቃውንት መጠሪያ ማእረግ ነው፡፡ በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ የቅኔ፣ የአቋቋም፣ የቅዳሴ፣ የዝማሬ መዋሥእት፣ የድጓ እና የአንድምታ መሪጌታ እየተባለ ይጠራል (መ/ር ዳዊት ሥራው 17/05/2012 ቃ.መ)፡፡



*(የጎንደር ልጃ ገረዶች በጥምቀት ሰሞን አለባበስ እና አጊያጊያጥ 2013)*

ሌላው የጥምቀት ቅድመ መድረሻ ድባብ የሚታወቀው በነጋዴዎች እንቅስቃሴ ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀት ሽታ ነጋዴዎችን የሚያነቃቃ ነው፡፡ ነጋዴዎች ሱቆቻቸው አልበቃቸው ብሎ በረንዳ ላይ አልባሳት የሚሸጡበት፣ ልብስ ሰፊዎች በወረፋ የሚጨናነቁበት፣ ሸማኔዎችና ጥበብ ሠሪዎች ፋታ የሚያጡበት ጊዜ ነው፡፡ የአራዳ፣ የአዘዞ እና የፒያሳ የገበያ አደራሾች፣ የገበያ መካዝኖች፣ ቡቲክ ቤቶች፣ በሰው ይጨናነቃሉ፡፡ ሌላው የጎንደር ጥምቀት መቃረብ የሚታወቀው በከተማዋ ውስጥ የሚታየው ደማቅ ድባብ ነው፡፡ ጥምቀት ቀረብረብ ሲል በጎንደር ከተማዋ ውስጥ ከዘወትሩ የተለየ ድምቀት ይስተዋላል፡፡ ይህን በተመለከተ ልዕልና ኀይለ መስቀል ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ጥምቀት ከመምጣቱ ኹለት ሳምንት ቀደም ብሎ የጎንደር ሰማይ ይጠራል ነው የሚባለው፡፡ እንኳን ሰው ሰማይው ውሐ ሰማያዊ ይሆናል እውነት ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ቤቶች ኹሉ ይቀባሉ፡፡ አካባቢው ይዋባል፡፡ ምእመናኑ በተለይ የእምነቱ ተከታዮች አካባቢውን በአገራችን ባንዲራ ያሸቆጠቁጣሉ፡፡ ግም፣ ግም ሲል ስሜቱ ኹለት ሳምንት ቀደም ብሎ ይጀምራል፡፡ ከዚያ በኋላ ዋናው በዓል ሲከበር ያ ድምቀት ገዝፎ ሕፃናቱ፣ ዐዋቂው፣ በየፊናው ዕድሜውና ችሎታው በሚፈቅድለት መንገድ በዚያ ባማረ የባህል ልብስ ሲያከብረው ጎንደር በተለየ መንገድ በተለያዩ ጌጣጌጦችና በብዙ ቀለማት ትዋባለች፡፡ ከሰማይው ከአድማሱ ጀምሮ ማለት ነው፡፡ ስብጥሩ ይህ ነው የማትለው ድባብ ይፈጥራልና ዓመት ምን አለ እንደ ዕለት ፈጥኖ በደገምነው ኹሉ ያሰኛል፡፡ ስለዚህ የጎንደር ጥምቀት ይህን ያህል ጉልበት ያለው ነው (ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡*

ከላይ የተጠቀሰው መረጃ የጎንደርን ጥምቀት ድባብ የሚያሳይ ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀት ግም፣ ግም ማለት ሲጀምር የጎንደር ሰማይ ይጠራል የሚለው ብሂል በጥምቀት ሰሞን ጎንደር ምድር ላይ ምንም ዐይነት አቧራ፣ ጢስና መሰል አካባቢውን የሚበክል ነገር ባለመኖሩ የጎንደር ምድር እና ሰማይ ውበት ይማርካል፡፡ ሰውን ከፈጣሪ ያስታርቃል፡፡ ሰማዩ ይጠራል የሚለው ትርጓሜ የጎንደር ጥምቀት ምድርና ሰማይን፣ ሰውና እግዚአብሔርን፣ ማኅበረሰብ እና ማኅበረሰብን፣ ሰው እና ሰውን፣ ባልና ሚስትን፣ እኅት እና ወንድምን፣ አባት እና ልጅን፣ ሴት እና ወንድን ያስታርቃል የሚለውን የሚተረጉም ነው (ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡

በጥምቀት ሰሞን "እንኳን ምድሩ ሰማዩ ይጠራል" የሚለው ብሂል ሥጋዊና መንፈሳዊ ሐሤትን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ የምድሩ መጥራት አንድምታ ዕርቀ ሰላሙን፣ ደስታውን፣ ፌስታውን እና የጥምቀት ድባብ የሚፈጥረውን ማኅበረሰባዊ እና ሰባዊ ሐሤት ያሳያል፡፡ በጎንደር ጥምቀት ሰሞን አካባቢው እና አደባባይው ሁሉ በሀገር ባንዲራ የተዋበ እና የተሸቆጠቆጠ ነው፡፡ ይህም ጥምቀትን ከሃይማኖታዊው ዕሳቤው ዐልፎ ሀገራዊ እና ማኅበረሰባዊ መገለጫ መሆኑን አመላካች ነው፡፡






*(ኢትዮጵያን የሚዘክሩ ባንዲራዎች በጎንደር ጥምቀት 2013 ዓ.ም)*

በሌላው ጎኑ ደግሞ ሰማዩ ይጠራል የሚለው የሰውን እና የአምላክን እርቀ ሰላም፣ ጥምቀት ከሞት በኋላ ስለሚኖረው ሕይወትም ጭምር ዘላለማዊ ድኅነትን የሚዘክር ነው፡፡ በመኾኑም የጥምቀት ክብረ በዓል መቃረብ ሥጋና ነፍስን አስተባብሮ የሚኼድ መኖኑን ያስገነዝባል፡፡

ሌላው የቤቶቹ በቀለም መቀባት፣ የመንገዶቹ መታጠብ፣ የዕፀዋቱ መከርከም፣ እና አጠቃላይ የሚለበሰውና የሚጠመጠመው ኹሉ ጽዱ መኾን የጎንደር ጥምቀት መዳረሻ መገለጫዎች ናቸው (ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011 ቃ.መ)።

የሽረሪቱ ድር መወገድ እና የቤቱ በቀለም መዋብ የባጀው ቂም እና የከረመው ጥል በጥምቀት መወገዱን ይተረጉማል። የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ነውር እና ነገር፣ ቂም እና በቀል ብሎ የሚፈርጃቸውን በቆሻሻ ይመስላቸዋል። በውሐ መታጠብና መቀባትን ደግሞ የእርቅ እና የጽድቅ ተግባራት አድርጎ ይወስዳቸዋል። በመኾኑም የቤቶች ቀለም መቀባት፣ የመንገዶች መጠረግና መታጠብ ከነውር እና ነገር፣ ከቂም እና በቀል መመለስን የሚያዘክር ነው (የአብሥራ ለገሰ፣ 19/04/11 እና ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011 ቃ.መ)።

ጠቅለል ባለ መልኩ ቅድመ ጥምቀት በማኅበረሰቡ ውስጥ መልካም ነገር ወደፊት እንደሚመጣ ማብሰሪያ ነው። ነጎድጓድ የዝናብን መምጣት፣ ነፋስ የበልግን መባት፣ እንደሚጠቁም ሁሉ የቱልቱላው[54] መነፋት፣ የእንቁሩ መለጋት የጥምቀትን መቃረብ ማብሰሪያ ነው። ይህም ከዮሐንስ ጥምቀት ጋራ ይፈካከራል። ዮሐንስ "መንገዱን ጥረጉ፣ ጠማማው ይቅና እኔ በውሐ አጠምቃችኋለሁ ከኔ በኋላ የሚመጣው እሱ ብርቱ ነው በመንፈስቅዱስ እና በእሳት ያጠምቃችኋላ" ይላል። ይህ የዮሐንስ ድምጽ እና የእረኞች ጥሩምባ እና እንቁር ልጊያ ድምጾች እና ድርጊቶች የጥምቀትን መምጣት አብሳሪዎች ናቸው። የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ቀድሞ ዝግጅት የማድረግ የቆየ የይወት ልምድ አለው። ቀድሞ ዘግጅትን ለማንጸር "አጥር የለው በርበበሬ ትጥቅ ለው ገበሬ፣ ሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ፣ ለሞኝ ሰኔ በጋው ነው እና መሰል አስረጅዎችን በመጥቀስ ቀድሞ መዘጋጀትን ያጸናል። ቅድመ ጥምቀትም ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ የቅድመ ዝግጅት ዕሳቤ ነው (የአብሥራ ለገሰ፣ 19/04/11 እና ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011 ቃ.መ)።

### 4.2. የከተራ እና ጥምቀተ ባሕር ዐውድ

የከተራ ቀን ከየአድባራቱ ታቦታት ወደ ማንኪት ባሕረ ጥምቀት ይወርዳሉ። ታቦታቱ በሚወርዱበት ሰዓት ሊቃውንቱ፣ ካህናቱ፣ የሰንበት ዘማርያን፣ አረጋውያን፣ እናቶች እና በማኅበር የተደራጁ ወጣቶች እያጀቡ፣ እያነጠፉ እና ታቦታቱን እየከበከቡ ወደ ጥምቀተ ባሕሩ ይወርዳሉ። ከተለያዩ አካበቢዎች ከሀገር ውስጥና ውጭ የመጡ የአካባቢው ተወላጆች፣

[54] ጥሩምባ ለማለት የአካባቢው ሰው ቱልቱላ ነው የሚለው

እንግዶች እና ቱሪስቶች በባሕረ ጥምቀቱ ታቦታት መውረጃ ይታደማሉ፡፡ ወደ ጥምቀቱ ሲመጡ የተለያዩ ሥዕላት፣ ባነሮች፣ ጎንደርን እና ኢትጵያን የሚገልጹ አለባበሶች እና አጊያጊያጌያጦች ይታያሉ (የአብሥራ ለገሰ፣ 19/04/11 እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ 12/05/2013 ቃ.መ.)፡፡

ወደ ጥምቀተ ባሕሩ ወደ ታቦታቱ ማደሪያ የሚያስገባው ቦታ ስለሚሞላ አብዛኛው ሕዝብ እስከ አውቶፓርኩ[55] ድረስ ይታደማል፡፡ በዚህ ታቦታቱ ከወረዱ በኋላ በሊቃውንቱ የዋዜማ ቁመት፣ በዘማርያኑ ዝማሬ፣ እና በእናቶች እልልታ ለታቦታቱ ምስጋና ይቀርባል፡፡ የታቦታቱ ወንዝ መውረድ ከፊት የሚታየውን የመልካም ይሕወት መንገድ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህም ታቦታቱ ወደ ጥምቀተ ባሕር ከመውረዳቸው በፊት የነበረው ከራሚ ዘመን ብዙ ውጣ ውረዶች እንደ ነበሩ የሚያዘክር ነው፡፡

ከዚህ ላይ ተምሳሌቱን ለማምጣት መሠረቱን ማንሣት ያስፈልጋል፡፡ ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም ከመምጣቱና ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ ወርዶ ከመጠመቁ በፊት የሰው ልጆች በግዞተ ዲያብሎስ ሥር ነበሩ፡፡ ወደ ዮርዳኖስ ወርዶ በተጠመቀ ጊዜ የእዳ ደብዳቤያቸው ተደምስሶ አዳምና ሔዋን ነጻ ወጥተዋል፡፡ በዚህ መልኩ ወደ ባሕረ ጥምቀት የሚደረገው ጉዞ የነጻነት መውጫ ጎዳና በመሆኑ የነጻነት ብሥራት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የታቦት መውረጃ ቀንን በተመለከተ ለመ/ር ዳዊት ሥራው ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ *"የዚህ ሃይማኖታዊ መነሻ ምክንያት የጥምቀት ዋዜማ ታቦታቱ ሲወርዱ የደስታ ብስራት የሚነገረው ከዛሬ ነገ የተሻለ ዕድል እና ቀን እንዳለ በማሰብ ነው፡፡ ዛሬ ወደ ጥምቀተ ባሕር ክርስቶስ ሲወርድ ነገ ዐድሮና ነግቶ ጥምቀት ሲመጣ የተሻለ ቀን መምጣቱን ያበሥራል" (መ/ር ዳዊት ሥራው፣17/05 2011ቃ.መ)፡፡*

ይህ ዕሳቤ ሰዎች ከዛሬ ነገ የተሻለ ጊዜ ነው ብለው ማሰብን እና ከዛሬ ነገ ይሻላል የሚል ተስፋን በአእምሮቸው ውስጥ ያሠርጻል፡፡ ይህም በሥጋዊና መንፈሳዊ መልኩ የሚተረጉም ነው፡፡ የታቦታት ወደ ወንዝ መውረድ አንድም ሥጋዊ ጥንካሬን የሚያዘክር ነው፡፡ ምድራዊ ሕይወት የተባለቸው ደስታና መከራ የሚፈራረቁባት በመኾኑ ሥጋቶችና ፈተናዎች በሰዎች እና በማኅረሰብ ዘንድ እየተደጋገሙ ይከሰታሉ፡፡ ለምሳሌ ግለሰቦች በሕይወታቸው ስኬታማ ያለመሆን፣ የገንዘብ እጦት፣ የስደት፣ የጤና ማጣትና መሰል ጉዳዮች ሊያጋጥሟቸው

[55] አውቶ ፓርኩ ማለት በጎንደር ከተማ ከማንኪት ባሕረ ጥምቀቱ ሳይደርስ በኮሌጅ እና በሆስፒታል የሚሄዱት የአስፓልት መንገዶች መገናኛ ቦታ ነው፡፡ ስሙን ጣሊያኖች እንደሰየሙት ይነገራል፡፡

ይችላሉ። በቤተሰብ ደረጃም ቢሆን በሞት የመለየት፣ የግጭት፣ የትዳር መፍረስ እና መሰል ችግሮች ይከሰታሉ። በማኅበረሰብ ደረጃ ደግሞ የድርቅ፣ ጦርነት፣ የበሽታ፣ የችግር ተግዳሮቶች ሊገጥሙት ይችላሉ። የተጠቀሱትን ማኅበረሰባዊ ችግሮች ለመሻገር ደግሞ የሥነ ልቦና ልዕልና እና የማኅበረሰባዊ ጽናት ያስፈልጋል። በዚህ መልኩ የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ ከጥምቀተ ባሕር ላይ ቁሞ ችግሮችን ተጋፍጦ ድል አድራጊነትን የሚማርበት ነው (የአብሥራ ለገሰ፣ 19/04/11 እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ 12/05/2013 ቃ.መ)።

አንድም መንፈሳዊ ጥንካሬን እና ተስፋን የሚተረጉም ነው። ሰዎች የዚህ ዓለም ኑሮ ብቻ ሳሆን ከሞት በኋላ ያለው እጣ ፈንታም ያሳስባቸዋል። በመኾኑም የጎንደር ጥምቀት ዋዜማ እንደ ምድራዊ ዓለም ይወሰዳል። ጥምቀቱ ደግሞ እንደ ሰማያዊው ዓለም ይተረጎማል (የአብሥራ ለገሰ፣ 19/04/11 ቃ.መ)። ዋዜማው የዚህ ዓለምን ሕይወት የሚተረጉመው ታቦታቱ ከየ ዓሉበት አብያተ ክርስቲያን እና መንበረ ክብራቸው ተነሥተው ወደ ወንዝ የድንኳን ማደሪያ መውረዳቸው ነው። ይህም አንድም ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ለመጠመቅ ያደረገውን ጉዞ ይመለከታል። አንድም ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ሥጋ የለበሰበትን፣ የተንገላታበትን እና የተሰቀለበትን ይተረጉማል። ጥምቀት ደግሞ ታቦታቱ ከነበሩበት ወንዝ፣ ድንኳን ተነስተው ወደ መንበረ ክብራቸው ይመለሳሉ። ይህም ሰው ከነበረበት ግዞት ነጻ ወጥቶ ወደ ቀደመ ክብሩ መመለሱን ይተሩጉማል። በዚህ መልኩ የታቦታቱ መውረድ የክርስቶስን መወለድ እና የዚህ ዓለምን ኑሮ የሚተረጉም ሲኾን ጥምቀቱ ደግሞ ነጻ መውጣትን የሰውን አሸናፊነት ይተረጉማል (መ/ር ዳዊት ሥራው፣ 17/05/2011 እና ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011)።

የጥምቀት ዋዜማ በዚህ መልኩ የዚህን ዓለም እንግልት ወይም ሰዎች ጥረው ግረው፣ ደክመው እና ወጥተው ወርደው እሚኖሩበት የድካም ዓለም እንደሆነች በሰዎች አእምሮ ውስጥ ይተክላል። በዚህ መልኩ ሰዎች የሚደርስባቸውን እንግልት እንዲታገሱ እና እንዲቀበሉት ጽናትን ያላብሳል (መ/ር ዳዊት ሥራው፣ 17/05/2011 እና ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011)፡፡፡

### 4.3. የዕለተ ጥምቀት ዐውድ እና ክዋኔ

የጎንደር ጥምቀት እጅግ የደመቀ፣ የተዋበና የዐማረ ነው። ይህ የጎንደር ጥምቀት ከሰው ብዛት፣ ከአለባበሱ፣ ከሥርዐቱና አጠቃላይ ከክዋኔው ጋራ የተለየ ስሜት የሚፈጥር ነው።



*(ዕለተ ጥምቀትን በጎንደር በከፊል የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ 2011 ዓ.ም)*

የጎንደር ጥምቀት የስኬት የነጻነት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የጎንደር ጥምቀት ነጻነትን የሚሰጥ መኾኑ ከሐሳብና ከምናብ አልፎ የሚጨበጥና የሚዳሠሥ ነው፡፡ ለዚህም በጥምቀቱ የሚታደሙት ማኅበረሰቦች በነጻነት ነው፡፡ በዚህ ቀን አንዱ የበላይ አንዱ የበታች አይሆንም፡፡ የሰዎች የበላይና የበታች ዕርከን ተወግዶ አንድ የሚኾኑበት ዕለት ነው፡፡ ሰዎች በጾታ፣ በዕድሜ፣ በሀብት፣ ሳይለያዩ እንደየ ችሎታቸውና ተሰጧቸው ጥምቀትን ያከብሩታል፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት ሀብትን፣ ሥልጣንን፣ ዕድሜን፣ ጾታን በማቀራረብ ሰዎች እኩል እንዲሆኑ ያደርጋል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሀዲስ፣ 05/ 19/ 2012)፡፡

የጎንደር ጥምቀት የካህናቱን፣ የአዛውንቱን፣ የባሕረ ጥምቀቱን፣ የታቦታቱን ግርማ ሞገስ፣ የወጣቱን ሆታ፣ የልጃ ገረዶቹን አጊያጊያጥ፣ የሕጻናቱን ደስታ እና ፍንደቃ፣ የሰንበት መዘምራን ዝማሬ ኹሉ አስተባብሮ ሲያዩት የመንፈስና የሥጋ መንጻትን ያጎናጽፋል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ 05/ 19/ 2012፣ አቶ ጠጋነው ደምሴ 25/05/ 2012 ቃ.መ)፡፡

ጥምቀት ከምድራዊ ሕይወት ነጥቆ በምናብ ዓለም እየሩሳሌም ሰማያዊትን አስቃኝቶ፣ አስዳሥሦ እና አሳይቶ ይመልሳል፡፡ በዚህ መልኩ ትልቅ ማኅበራዊና ሰዋዊ መስተጋብርን

ይፈጥራል፡፡ ልዩ የሆነ የጥምቀትን ክብረ በዓል በረከት ለመቋደስ ሲል ከሕጻናት እስከ አዛውንት ያለው ማኅበረሰብ በኅብረት ይታደማሉ፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ የጎንደርን ጥምቀት ሳይሳለምና ሳይሳተፍ መዋል ክፉ ነገር ይገጥመኛል ብሎ የሚያምን በመሆኑ ጭንቅ ነገር ካልገጠመው በቀር ጥምቀትን ሳያከብር አይውልም (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ፣ 05/ 19/ 2012 እና አቶ ጠጋነው ደምሴ 25/05/2012 *ቃ.መ*)፡፡

ይህን በተመለከተ በዚህ አካባቢ ከኩተት እስከ ሽበት የኖሩትን አቶ ጌትነት አመራን የጎንደር ማኅበረሰብቦች የጎንደርን ጥምቀት ሳያከብሩ ቢውሉ ምን ይሰማቸዋል? የሚል ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ *"ሺዶ ጥምቀትን ሳይጫወት ሳይዘፍን ከዋለ ዓመት የሚደርስ አይመስለውም ውነቱን ለመናገር፡፡ ሺጀ ከዚያ ፈክሬ፣ ዘፍኜ ስለት ካለብኝ ሂጀ አድርሽ ታልሆነ ዓመት እምደርስ አይመስለኝም ከራሴ ጀምሮ፡፡ ተሳሌም ከኾነ ምንም ከኾነ ከጥምቀቱ ካልኼድኩ ዓመት እምደርስ አይመስለኝም፡፡ እና ስለዚህ ያን ማድረግ ግድ ነው"* (አቶ ጌትነት አመራ 13/05/2011 *ቃ.መ*)፡፡

ከዚህ መረጃ የምንረዳው ቁም ነገር የጎንደር ማኅበረስብ የጎንደርን ጥምቀት ሳያከብር ከዋለ አንዳች ነገር ይገጥመኛል ብሎ የሚያስብ መሆኑን ነው፡፡ በዚህም ስለት ካለበት፣ በፍከራ፣ በዘፈን፣ በዝማሬ፣ በሆታ እና በገና ጥምቀቱን ያከብራል፡፡ የጎንደር ወጣት በጥምቀቱ ተገኝቶ ዐቅሙ የሚፈቅደውን በጎ ተግባር ሠርቶ መመለስ *ሥጋዊና* መንፈሳዊ ደስታን ያስገኝልኛል ብሎ ያምናል፡፡ በዚህ ምክንያት በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ላይ አንዳንዶቹ ምንጣፍ በማንጠፍ በጎ ተግባር ይፈጽማሉ፡፡ እንዳንዶች ደግሞ ሕጻናት እንዳይረገጡ፣ አዛውንት እንዳይገፉ ደንብ የማስከበር *ሥራ* ሲያከናውኑ ይስተዋላል፡፡ የጥምቀቱ ዕለት *ሥ*ርዓት ባለው መልኩ ሰው እንደየተዋረዱ እና ማዕረጉ እንቅስቃሴ ያደርጋል፡፡ በጎንደር ጥምቀተ ባሕር የወረዱት ታቦታት በካህናቱና ሊቃውንቱ ታጅበው ሲነሡ የአሰላለፍ *ሥ*ርዓት አለው (የአብ*ሥ*ራ ለገሰ፣ 19/04/11 እና አቶ ጠጋነው ደምሴ 25/05/2012 *ቃ.መ*)፡፡

መጀመሪያ ታቦታቱ፣ ከታቦታቱ ቀጥሎ የሊቃውንቱ ማኅሌተ ያሬድ፣ ወረቡና ቁመቱ ይቀጥላል፡፡ ከካህናቱ በመቀጠል ደግሞ የሰንበት ትምህርት ቤት መዘምራን በየ አጥቢያ አድባራቱ እየዘመሩ ያከብራሉ፡፡ ከዚህ በመቀጠል አዛውንቱና አዝማሪዎች በገና መችዎች ይከተላሉ፡፡ እንዲሁም እናቶች፣ ላሊበላ ሳሚዎች እና "ግባግባ በወት[56] የአገራችን ታቦት"

[56]ወይዘሮ ዘርፌ (5/ 11/ 2012) የተባሉትን አቀንቃኝ ጠይቂያቸው "በወት" የሚለው ቃል ግባ በሕይወት፣ በሰላም ለማለት ነው የሚል ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

የሚሉት እናቶች ይከተላሉ። በመቀጠል ልጃ ገረዶች እንደየ መጡበት አካባቢ በዘፈን እና በእስክስታ ያከብሩታል። ከእነሱ በመቀጠል ወጣት ወንዶች በሆታ ወይም በዘፈን ጥምቀቱን ያደምቃሉ። ሆተኞቹ አንዳንድ ጊዜ የግፊያ እና የጉልበት ሃይል የተቀላቀለበት ባህርይ ያሳያሉ። በዚህ ጊዜ ልጃ ገረዶቹም ክብ ሰርተው የሚያቀነቅኑትም፣ መንገድ ገብተው የሚጓዙትም ሆነ ተመልካቾች ገለል በማለት የሆተኛውን አፎት ያሳልፋሉ።



*(የጥምቀት ሆተኛ በመምዘግዘግ ላይ ሲኾን ሌላው ገለል ሲል የሚሳይ ፎቶ)*

የጎንደር ጥምቀት ድባብ ሥርዓታዊ መኾኑ እና ታቦታቱን ከፊት በማስቀደም እንደዚህ በቅደም ተከተል መከበሩ የጎንደርን ማኅበረሰባዊ ሥሪት የሚተረጉም ነው። የጎንደር ማኅበረሰብ ለሥልጣን፣ ለዕውቀት፣ ለዕድሜና ለጾታ የሚሰጣቸው ትርጉሞች አሉት። እነዚህን ማኅበረሰባዊ ሥሪት ይዞ ጥምቀቱ መከበሩ የማኅበረሰቡን ሥርዓት ለማስጠበቅና ለማስቀጠል ይረዳል። እንዲሁም የጎንደር ማኅበረሰብ ለሥልጣነ ክህነት ትልቅ ቦታ ይሰጣል። ሥልጣነ ክህነት ያላቸውን ጳጳሳት፣ ኤጲስ ቆጶሳት፣ ቆሞስ፣ ካህናት፣ ዲያቆናት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ያሉ የመገናኛ ድልድዮች ናቸው ብሎ ያምናል። በዚህ

ምክንያት ታቦታቱንና ካህናቱን የማስቀደም ሥራ ይሠራሉ፡፡ በዚህ በታቦታቱና በምእመኑ መካከል ያለው ቦታ ሰፊ ነው፡፡ ሰፊ የሆነበት ምክንያት ለታቦታቱ ካለው ክብር የሚመነጭ ነው፡፡ ሌላው የጎንደር ማኅበረሰብ የሊቃውንት ሀገር ከመሆኑ ጋራ ተያይዞ ለዕውቀት ትልቅ የሆነ ቦታ አለው፡፡



*(የጎንደር ጥምቀት ማስረገጫ ቦታ ስፋት እና ሥርዓት በፒያሳ 2013)*

ከዚህ በመቀጠል የጎንደር ማኅበረሰብ ለዕድሜ ባለ ጸጎች የሚሰጠው ክብር ከፍ ያለ ነው፡፡ ማኅበረሰቡ የዕደሜ ባለጸግነት ከሰው ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተሠጠ ጸጋ እንደሆነ ያምናል፡፡ ለዚህም *"ሰው በቁመቱ ላይ ስንዝር የመጨመርም ሆነ የመቀነስ አቅም የለውም" በዚህ ምክንያት ሰው ለራሱ ባይታውር እንደሆነ ወስዶ የእደሜ ባለጸግነት መታደል አድርጎ ይወስደዋል" (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ 05/ 19/ 2012)፡፡*

ማኅበረሰቦቹ የዕድሜ ባለጸግነትን የሚረዱበት መንገድ ብዙ ነው፡፡ አንድም "በግማሽ ዘመኔ አትውሰደኝ" የሚለውን ብሂል እንደማጣቀሻ ይወስዱታል፡፡ ይህ በሂል በግማሽ ዕድሜ ማለት የወጣትነትን ዘመን የሚያጠይቅ ነው፡፡ አንድም አለመብቃትን የሚተረጉም ነው፡፡ ግማሽ ማለት ከጎደሎነት ጋራ ተያይዞ የሚተረጉም ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ሙሉ ሰው ለመሆን ጥሩ ሥራ መሥራትን ያጠይቃል፡፡ ጥሩ ሥራ ሠርቶ ለማለፍ ደግሞ ዕድሜ ወሳኝ ነው፡፡ ዕድሜ በቆየ ቁጥር ከማኅበረሰቡ ዕሴት፣ ልማድ፣ ዕውቀትና ጥበብን በመማር ለማኅበረሰቡ ጥሩ ሥራ ማበርከት እንደሚቻል የአካባቢው ማኅበረሰብ ያምናል፡፡ በዚህ መልኩ አዛውንቶች ከፍ

ባለ መልኩ በጥምቀት ክብረ በዓል ይከበራሉ፡፡ አዛውንቶች በዕድሜ ባለ ጸግነታቸው ብቻ ሳይሆን ስለ አዛውንቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ በሚነገረው ታሪክ ጭምር እንዲከበሩ ሁነዋል፡፡ ይህን በተመለከተ ለመ/ር ዳዊት ሥራው በጥምቀት ክብረ በዓል የሚታየውን የአዛውንቶች አከባባር ተመልክቼ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *መልአከ ሞት ወደ አደባባይ መጣ፣ ወደ መንገድ መጣ፣ ወደ ቤት መጣ፣ ወደ ቤተክርስቲያን መጣ የመጣበት ምክንያት አዛውንት ጊዜያቸው ስለ ደረሰ ለመውሰድ ነው፡፡ በዚህ አጋጣሚ አዛውንቶች ይቀመጡበታል፣ ይቆሙበታል ይተኙበታል ወደ ተባለው ከፍ ወዳለ ቦታ ይኼዳል፡፡ በዚህ ጊዜ በአዛውንቱ የማረፊያ ቦታ ድንገት ሌላ ወጣት ቢገኝ በመላከ ሞቱ ተቀሥፎ ዕድሜው ያጥራል (መ/ር ዳዊት ሥራው፣ 06/03/ 2012 ቃ.መ)፡፡*

ይህ ታሪክ ወጣቱ ወይም በዕድሜ ያነሰው የሚበልጠውን አረጋዊ ወይም ትንሽ ወንድም ለትልቅ ወንደም ትንሽ እኅት ለታላቅ እኅት መታዘዝን እና ማክበርን እንዲረጋገጥ የሚያስችል ነው፡፡ በዚህ መልኩ ቅሥፈትን በመፍራት ወጣቶች አዛውንቶችን ደግፈው አቅፈውና ቅድሚያ ለእነሱ ሰጥተው እንዲያከብሯቸው ያደርጋል፡፡ ይህ የአዛውንቶችን ማክበርም በጎንደር የጥምቀት ዐውድ በስፋት የሚታይ ተግባር ነው፡፡

ሌላው ደግሞ ለጾታ የሚሰጠው ክብር ነው፡፡ በጥምቀት ዐውድ ሴቶች በአለባበስና በአጊያጊያጥ የተለየ ቦታ አላቸው፡፡ በጎንደር ማኅበረሰብ ሥሪት ውስጥ ሴቶች በቀደሙት በነገሥታቱ ዘመን ጀምሮ በፖለቲካው ሳይቀር ክፍተኛ ተሳትፎ ነበራቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል እነ እቴጌ ምንትዋብ ይጠቀሳሉ፡፡ ሌላው ጎንደርን በሴት[57] ስለሚመስሏት ጎንደር ማለት የተሞሸረች ሴት ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡ በዚህም ለሴቶች ያለው ምልከታ እና ተቀባይነት ከፍ ያለ ነው (አቶ ጌትነት አመራ 13/05/2011፤ መ/ር ዳዊት ሥራው 17/05 2011 እና አቶ ጠጋነው ደምሴ 25/05/ 2012 ቃ.መ)፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የጎንደር ጥምቀት ክዋኔ የጎንደርን ማኅበረሰባዊ ሥሪት የሚወክልና የማኅበረሰቡን ባህል፣ ሃይማኖት እና ዕሴት የሚያዘክር ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀተ ባሕር፣ ዐፄ ፋሲል፣ ራስ ግንብ፣ አዘዞ ተክለ ሃይማኖት ያለው የዐፄ በካፋ ግንብ፣ የፋሲል ግንብ አጥር፣ የባሕረ ጥምቀቱ አጥር እና መሰል የጎንደር ጥንታዊ ቤተ መንግሥታት እና አብያተ ክርስቲያን በእንቁላል ግንብ የተሠሩ ናቸው፡፡ ጥምቀተ የባሕሩ ሆነ የባሕሩ ግንብ የእንቁላል ቅርጽ አላቸው፡፡ እንደዚኹም የጥምቀቱ ዑደት፣ የኹተኛው ዑደት፣ የሊቃውንቱ ማሕሌት በእንቁላል ቅርጽ የሚፈጸሙ ናቸው በመኾኑም የጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ እና የጎንደር

[57] በምዕራፍ ዐምስት ሥር በሴቶች ተሳትፎ ውስጥ አንድምታው በስፋት ትንታኔ ተሰጥቶበታል፡፡

ማኅበረሰብ የሕይወት ሥሪት ነገረ እንቁላል  በሚለው ማሕቀፍ የሚታዩ ናቸው፡፡ እንቁላል አንድም ውጫዊ አካሉ ባለ ቅርፊት እና ሞላላ ዑደታዊ ቅርጽ ያለው ነው፡፡ ውስጡ ደግሞ በውሐ እና በአስኳል የተሞላ ነው፡፡ ቅርፊቱ አንድም የአዳም እዳ ደብዳቤ፣ አንድም የማኅበረሰብ ችግር ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሞላላ ዑደታዊ መኾኑ ደግሞ አንድም የጊዜን፣ አንድም የቦታን፣ አንድም የጥምቀትን፣ አንድም የሕይወትን ዑደት የሚተረጉም ነው፡፡ ውሐው ደግሞ አንድም የጥምቀት፣ አንድም የሕይወት ምሳሌ ነው፡፡

አስኳሉ ደግሞ የማኅበረሰቡ የተስፋ ምሳሌ ነው፡፡ የእንቁላሉ ቅርፊቱ፣ ውሐው እና አስኳሉ ከ21 ቀናት እቅፍ በኂላ ሕይት ያስገኛል፡፡ ይህ 21 ቁጥር ምስጢረ ጥምቀትን ይወክላል፡፡ 2 ሲደመር 1 ሦስት ነው ይህም በጥምቀት አብ በደመና የምወደው ልጀ ይህ ነው እና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ በእርግብ አምሳል የወረደውን የሥላሴ አንድነት ይወክላል፡፡ አንድም 21 ድንግል ማርያም የምትውልበት ቀን ነው፡፡ ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ሥግው የኾነው ከድንግል ማርያም  በለበሰው ሥጋ መኾኑን ያዘክራል፡፡  አንድም 21 ሦስት ሰባት ሲደመሩ የሚገኝ ቁጥር ነው፡፡ ሰባት በማኅበረሰቡ ዘንድ አንድም የሥላሴ ቀን፣ አንድም የአራቱ ባሕርያተ ሥጋ እና የሦስቱ ባሕርያተ ነፍስ ድምር ውጤት፣ አንድም የሰባቱ ሰማያት፣አንድም የኢያሪኮ ግንብ መፍረሻ፣ አንድም የሥርዓተ ፍትሐት ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ 2 ፍጹም ሰው ፍጹ አምላክ የመኾኑ 1 ደግሞ አንድ አምላክ የመኾኑ ምሳሌ ነው፡፡

ውሐው እና አስኳሉ ወደ ሕይወት እንደተለወጡ ኹሉ ጥምቀት እና የተስፋው ቃል ሲፈፀም የሞተው አዳም ይድናል፡፡ በሦስት ሳምንት ቅእርፊቱ ሲወገድ ጫጩት፣ በክርስቶስ ጥምቀት እዳ ደብዳቤ ሲቀደድ ልጅነት ይገኛሉ፡፡ በመኾኑም ቅርፊት እና እዳ ደብዳቤ፣ ጫጩት እና ልጅነት ተፈካካሪዎች ናቸው፡፡ አንድም ከእንቁላል የሚገኘው ደሮ ከሌሎች እንስሳት በተሻለ መልኩ ለጊዜ እና ለቦታ ሥልጡን ነው፡፡ ዶሮ የመሰብሰቢያ ጊዘውን ማደርያ ቦታውን አይዘነጋም፡፡ ዶሮ ነግህ ላይ ሰዓቱን ጠብቆ የጨለማውን ማብቃት፣ የብርሃኑን መተካት ያበስራል፡፡ ጥምቀትም ከግዞት ወደ ነጻነት፣ ከባርነት ወደ ልጅነት የሚደረገውን ጉዞ ያረጋግጣል፡፡ የእንቁላል ወድቆ መሰበር ተሹሞ መሻርን፣ አግኝቶ ማጣትን፣ ለብሶ መራቁትን ሰባዊ እጣ ፈንታዎች ያዘክራል፡፡ በዚህም ነገሥታቱ እንቁላልነትን እያሰቡ እንዲሠሩ እንቁላል ግንቦች ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ የእንቁላል ቅርፊት የጎንደርን ማኅበረሰብ ስጋት፣ ድካም፣ ልፋት፣ እንከን የሚወክል ነው፡፡ ውሐው ደግሞ የጎንደርን ጥምቀት

የሚያዘክር ነው፡፡ አስኳሉ ደግሞ የጎንደርን ማኀበረሰብ ተስፋ፣ ፍላጎት፣ ምኞት፣ ስኬት አብሮነት ያሳል፡፡ ውሐው እና አስኳሉ ሕይወት ማስገኘታቸው የጎንደርን ማኀበረሰብ ትብብር፣ ግንኙት፣ አብሮነት፣ አማኒነት ያሳያል፡፡ በመኾኑም የጎንደር የሕይወት ፍልስፍና ከነገረ እንቁላል የሚቀዳ ለመኾኑ አንድም የእንቁላል ግንቦቹ አንድም የዶሮ ወጡ አስረጅዎች ናቸው፡፡ በመኾኑም የጎደር ጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ ቅርጽ እና ይዘት በነገረ እንቁላል የሚወከል ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 11/15/11 ቃ.መ)፡፡

## ምዕራፍ ዐምስት የጎንደር ጥምቀት ሥርዓት ክዋኔ እና አንድምታው

በዚህ ሥር የሊቃውንቱ፣ የቀሳውስቱ፣ የዲያቆናቱ፣ የሰንበት ተማሪዎቹ፣ የልጃ ገረዶቹ፣ የሴቶቹ እና የወጣቶቹን ክዋኔ የሚሉት ነጥቦች ተተንትነው ቀርበውበታል።

### 5.1. በጎንደር ጥምቀት የሊቃውንቱ ክዋኔ እና አንድምታው

በጎንደር ጥምቀት ከተሳታፊዎቹ የኅብረተሰብ ክፍሎች አንዱ የሊቃውንቱ ክዋኔ ነው። የሊቃውንቱ ክዋኔ በአብዛኛው የዕውቀት ደረጃን መሠረት ያደረገ መስተጋብር ነው። በተለይ ጎንደር የሊቃውንት ሀገር እንደመኾኗ መጠን ብዙ ጊዜ የዚህ ማኅበራዊ ዕርከን ጎልቶ የሚወጣበት አጋጣሚ ሰፊ ነው። በጥምቀቱ ዋዜማ ቁመት ጀምሮ የጥምቀቱን ክብረ በዓል በማስረገጥ፣ በቅኔ ምሪት፣ በአመላለስና በወረብ ያከብሩታል።

በዚህ የቁመት ሥርዓት ዘው ተብሎ አይገባም። በዋዜማው ባደረግኩት ምልከታ "አንተ ትሻል አንተ" በማለት እና በድምፀ ለኖሳስ ሲገላገሉና ሲመራረጡ አስተውያለሁ። ዕውቀትንና ዕድሜን መሠረት ያደረገ እና ቅድሚያ የመስጠት ተግባር እንዳለ በምልከታዬ ማረጋገጥ ችያለሁ። ከምልከታዬ ተመልሼ በጎንደር ጥምቀት የሊቃውንቱ የዕውቀት ደረጃ ምን እንደሚመስል የሰሚው ቅዱስ ሚካኤል የዝማሬ መዋሥእት መሪጌታ ለኾኑት ለመ/ር ሰሎሞን ረዳ ጥያቄ አቅርቤላቸዋለሁ። እሳቸውም ተከታዩን ሰፋ ያለ መረጃ ሰጥተውኛል።

> *ያበሻ ሻሽ ያልጠመጠመ አያስረግጥም፤ ክልክል ነው በጎንደር። አያስረግጥም የመቋሚያው አያያዝ አይነት አለው። የጸናጽል ዐይነት አለው። መቋሚያ አያያዝ ወደኋላ አያያዝ አለ። ዝም ብሎ አይያዝም። ጠቅላላው ነገር አገሩ ግን ያስደረገው ነገሥታቱ ከጥንት ጀምሮ ከቦታው አራት ትርጓሜ፣ የአቋቋም ምስክር አራት ስላለ ያ ዘንዳ ኹኖ መቸም የድምቀቱ ዓይነት በዚህ ሀገር አለ አይባልም። ብዙ ሀገር በመላው ኢትዮጵያ ዞሬበታለሁ። ግን እንደጎንደር ያለ ባህልና ተግባር የለም። አንድ ሊቅ ምን? አሉ ቀደም በደብረታቦርና በደብረ ብርሃን የሚል ቅኔ አምጡ አሉት አሉ። ኋላ አንድ ባለ ቅኔ ስሙ ጠፍቶኛል። ‹‹ዮም ዕለተ ብዙኅ ትፍሥሕት፣ እስመ በደብረታቦር ቆመ ፈጣሪ ወበደብረ ብርሃን ዳዊት።››[58] ተብሎ ይህ ኹሉ ታሪክ የኾነባት ሀገር ስለኾነ ግን ይህ ለወደፊት ብዙ ስለሚጠብቃት አሁንም ባህሉ ከዛ ደግሞ ዋናው ነገር ግን አቋቋሙ፣ ቅኔው፣ትርጓሜ፣ ትመሰገናለች። ኅብረተሰቡ በጎንደር ባህል ጎንደር ከተባለ በትግራይ፣ በዚህ በራያ አዘቦ ክብር ነው። ጎንደር ተምሮ ከመጣ በላይ ነው የሚቀመጥ። ከድሮ ጀምሮ አባቶቻችን የተከበረች ሀገር ስለሆነች ጥምቀትን በጣም ነው የሚያከብረው። ነገሥታቱ፣ እነ ፋሲል ግንብ እነ ደብረ ብርሃን እነ ቁስቋም በሙሉ እንደተከበረ ነው እሚኖር ማለቴ ነው (መ/ር ሰሎሞን ረዳ 16/05/2011 ቃ.መ)።*

---

[58] መ/ር ሰሎሞን ረዳ ባያውቁትም ዐፄ ኢያሱ አድያም ሰገድ በነገሡ ጊዜ ዐፄ ዳዊት ይባሉ ነበር እና በዚህ ዘመን መሪጌታ ክፍለ ዮሐንስ የተባሉ መሪጌታ የተቀኙት ነው (መ/ር ዳዊት ሥራው 17/05/2011 ቃ.መ)።

ቃለ መጠይቁ እንደሚያስረዳው የሊቃውንቱ ክዋኔ በዘፈቀደ የተመሠረተ ሳይሆን በዕውቀት ልዕልና ላይ የሚያተኩር ነው። ሊቃውንቱ እንደየ ዕውቀት ደረጃቸው እና መጠናቸው የሚገባቸውን ክብር በጥምቀቱ ሥርዓት ያገኛሉ። ማኅበራዊ ደረጃቸው እንደየ ዘርፉ ሊለያይ ይችላል። በዚህም የቅኔ ሊቃውንት፣ የአቋቋም ሊቃውንት፣ የድጓ ሊቃውንትና የትርጓሜ ሊቃውንት በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የየራሳቸው ድርሻ አላቸው። የአቋቋሙ ሊቅ በማኅሌት ሰዓት የቁመቱን ድርሻ በበላይነት ይመራል። ባለ ቅኔው ደግሞ በቅኔው ዙሪያ ባለቤትነትን ይወስዳል። የትርጓሜ ሊቃውንት ደግሞ በስብከት እና በወንጌል አንድምታ ያለውን የስብከት እና የትርጓሜ ተግባር ይወስዳል። ይህ ሥርዓት በጎንደር ጥምቀት የሊቃውንት ልዕልና ገዝፎና አብቦ የሚታይበት ነው። ጎንደር ሂዶ መማር ለሊቃውንቱ ክብር እና ተጠየቅ መሠረት እንደሆነ የመ/ር ሰሎሞን ረዳ መረጃ ያረጋግጣል።

ስለ ጎንደር ሊቃውንት እና የጎንደር ጥምቀት ግንኙነት እንዲያስረዱኝ ለመ/ር ዳዊት ሥራው ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ተከታዩን ማብራሪያ ሰጥተውኛል። *"ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም" ድንገት የሊቃውንቱን አጠማጠም፣ አለባበስ ጭራ አያያዝ መቋሚያና ሁሉን አድርገህ ብትገባ ከማኅሌት ላይ መዋረድን ያስከትላል። አጠማጠሙና ካባ አደራረጉ የሊቃውንቱን የዕውቀት ደረጃ የሚያሳዩ ናቸው። የሊቃውንቱ የቁመት በዐት በዕውቀት ደረጃቸው የሚወሰን ነው" (መ/ር ዳዊት ስራው፣ 06/03/ 2012 ቃ.መ)።*

"ከመጠምጠም ትምህርት ይቅደም" የሚለው ብሂል ከሻሽ ጥምጥሙ ባሻገር ከዕውቀት ጋራ የሚፈካከር አንድምታ አለው። ሻሽ መጠምጠም በጎንደር ሊቃውንት የተለየ ቅርጽ አለው። የሊቃውንቱ የሻሽ አጠማጠም ከታች እንደ ክትር ክብ ሁኖ ከላይ እንደ ጉልላት በቅርጽ የወጣ ነው። ይህ የጥምጥሙ ወደ ላይ ጉልላት መስሎ መወጣቱ የሊቅነቱ እና የዕውቀቱ መገለጫ ነው። ጉልላት ከቤተ ክርስቲያን ጫፍ እንደሚሆን ሁሉ የጎንደር ሊቃውንትም የማኅበረሰቡ ራስ መኾናቸውን ይተረጉማል። ጉልላት የቤተ ክርስቲያኗ መደምደሚያ መቋጫ እንደኾነ ሁሉ የጎንደር ሊቃውንቱም የጎንደር ማኅበረሰብ ትልቁ እርከን መኾናቸውን ይተረጉማል። ይህ ከሊቃውንቱ ክብር ዐልፎ የጎንደር ማኅበረሰብ ለዕውቀት የሚሠጠውን ልዕልና ያዘክራል። በመሆኑም የሊቃውንቱ አጠማጠም እና የቤተ ክርስቲያን ጉልላለት ዙረው የሚገጥሙ ናቸው።



*(የጎንደር ሊቃውንትን አጠማጠም የሚያሳይ ፎቶ 2013 ዓ.ም)*

ሌላው ሊቃውንቱ በጸናጽል እና መቋሚያ አያያዞች የየራሳቸው ሥርዓት እና ጥበብ አላቸው። በጸናጽል ጊዜ የጎንደሬው አቋቋም በመሪነት የሚወስድ ሲኾን በዘንግ ጊዜ ደግሞ የተክሌው አቋቋም ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከፊት ወደ ኋላ፣ ከኋላ ወደ ፊት፣ ከላይ ወደ ታች እና ከታች ወደ ላይ የሚለውን የመቋሚያ ወይም የዘንግ ሥራ በበላይነት የተክሌ አቋቋም ይመራዋል። የጸናጽሉን የበላይነት ደግሞ የጎንደሬ አቋቋም ሊቃውነት ይከውኑታል።



*(በጎንደር ጥምቀት ሊቃውንቱ በሥርዓተ ቁመት ላይ ሲያስረግጡ 2012 በአጥኝው የተነሣ ፎቶ ግራፍ)*

በጥምቀት ክብረ በዓል የሊቃውንቱ በኅብረት አረጋገጥ፣ መቋሚያ እና ጸናጽል አያያዝ አንድም የጎንደርን ማኅበረሰብ መደጋገፍ፣ መረዳዳት፣ መተሳሰስብ እና አንዳቸው ለሌላቸው

"ጥርስና ከናፍር ተደጋግፎ ያምራል" እንደሚባለው የኅብረታቸውን እና የምግባራቸውን አንድነት የሚያዘክር ነው። ከሃይማኖታዊ አንድምታው አኳያ ደግሞ መቋሚያ መደገፊያ ሲኾን ድጋፍ ደግሞ ጌታ እየሱስ ክርስቶስ ነው። ተምሳሌቱም አምላክ ከሰማየ ሰማያት መምጣቱንና ከድንግል ማርያም መወለዱን የሚያጠይቅ ነው። መቋሚያው ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከግራ ወደ ቀኝ፣ መመላለሱ አይሁድ አምላክን በምክረ ቀያፋ እና ሐና ከጲላጦስ ወደ ሔሮድስ እና ከሔሮድስ ወደ ጲላጦስ የተመላለሰበትን የሚያጠይቅ ነው። ጸናጽሉ ደግሞ የጽፋቱ ምሳሌ ነው (መ/ር ሰሎሞን ረዳ 03/05/2012 ቃ.መ)። እንደዚሁም አባ ገብረ ሥላሴ ስለ ሥርዓተ ቁመት እና መቋሚያ ተምሳሌት ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *የካህናቱ ክዋኔ በበለጠ የሚያብራሩ ሊቃውንት ቢኖሩም ምስጋና ከመላእክት የመጣ ነው። መቋሚያ የጌታችን የዕፀ መስቀሉ ተምሳሌት ነው። ከአሲቶስጥራ እስከ ቀራንዮ ድረስ ደፋ ቀና እያለ የደረሰበትን እና ከሐና ወደ ቀያፋ ለሰው ልጆች ሲል የተንገላታበትንና የተመላለሰበትን የሚመለከትና ያን ለማሰብ ነው። ለኛ ቆስለኸል፣ ደክመኸል የሚለውን የሚመለከት ነው። የሥጋና የመለኮትን መዋሐድ ይመለከታል። መቋሚያ መመርኮዣ ነው ምርኩዝ የሚያቆምና የሚያጸና ነው። ተጠመቀ፣ ወረደ፣ ሞተ፣ ተነሣ የሚል አንድምታ አለው* (አባ ገብረ ሥላሴ 03/06/11 ቃ.መ)።

መረጃው እንደሚያረጋግጠው መቋሚያ ከላይ ወደ ታች እና ከቀኝ ወደግራ መዝመም እና የዝማሜው ሥርዓት መነሻው ለሰው ልጆች ሲል አምላክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በቀራንዮ አደባባይ የከፈለውን መከራ የሚያዘክር ነው። ይህ ሃይማኖታዊ መነሻ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሚያስተላልፈው አንድምታ አለ። ይህም ሰዎች በመካከላቸው ፍቅር አንድነት፣ መተሳሰብና መግባባት እንዲኖራቸው ያስተምራል። አንድም ጥምቀት የሊቃውንቱ ማኅበራዊ ልዕልና ማሳያ ነው። ሊቃውንቱ በጥምቀት ክብረ በዓል የሚያደርጉት የቁመት ሥርዓት ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ አንድምታ አለው። ሃይማታዊ አንድምታው የኢየሱስ ክርስቶስን ተግባር በቁመቱ ማሳየት ነው። ማኅበራዊ አንድምታው ደግሞ ሊቃውንቱ ከጎንደር ማኅበረሰብ ጋራ የሚኖራቸውን ግንኙነት የሚያሳይ ነው። ሊቃውንቱ ይህን የቅዱስ ያሬድ ቁመት በሚቆሙበት፣ በሚያስረግጡበትና በሚከውኑበት ወቅት ከፍ ያለ የዕውቀት ልዕልና በጎንደር እንዲታይ ያደርጋል።

ይህ ሥርዓት በጎንደር ከተማ ያለው የሊቃውንት ማስመስከሪያ ጉባኤዎችና ሊቃውንቱ እንዲቀጥሉ ያደርጋል። ሊቃውንቱ በማሕሌት ተወስነው፣ በሌሊት ያደርጉት የነበረውን የቁመት ሥርዓት በአደባባይ እና በሕዝብ ፊት እንዲቆሙት ጥምቀት ዕድል ይሰጣል። በዚህ ምክንያት በማኅበረሰቡና በጎንደር ሊቃውንት መካካል ከዘወትሩ በተለየ መልኩ መተዋወቅና

መቀራረብን ይፈጥራል። ማኅበረሰቡ በሊቃውንቱ የቁመት ክዋኔ በመመሰጥ፣ በመማረክ እና ዕውቀትን በማድነቅ እንዲሁም ለዕውቀት ቦታ በመስጠት የጎንደርን የሊቃውንት መዲናነት ያስቀጥላል (አባ ገብረ ሥላሴ 03/06/11 ቃ.መ)።

## 5.2. የካህናት ክዋኔ እና አንድምታ በጎንደር ጥምቀት

በ10/05/2011 በጥምቀቱ ዋዜማ ከአጣጣሚ ሚካኤል ተነሥተን ወደ ዋናው ማንኪት ወደሚገኘው ባሕረ ጥምቀት ታቦታቱን እያጀብን በመምጣት ላይ ነበር። በዚህ ዕለት ቀሳውስቱ በተለያዩ ኅብረ ቀለማት ባሸበረቁ የታቦት አልባሳት ለበሰው በየሥራ ድርሻቸው ይሳተፋሉ። ሊቀ ጳጳስ፣ ጳጳስ፣ ኤጲስ ቆጶስ፣ ቆጶስ፣ ቆሞስ፣ ቄስ እና ዲያቆን የመሳሰሉ የሥልጣነ ክህነት ተዋረዶች አሏቸው። በሥርዓተ ቅዳሴ ኹለት ቄስና ሦስት ዲያቆናት የሚያስፈልጉ ሲኾን ደረጃቸውም በቅደም ተከተል ገባሬ ሠናይ ቄስ፣ ንፍቅ ቄስ፣ ገባሬ ሠናይ ዲያቆን፣ ንፍቅ ዲያቆን እና አናጉንስጢስ ዲያቆን ተብለው ይጠራሉ። እነዚህ ልዑካን በሥርዓተ ጥምቀቱ የራሳቸው ሚና አላቸው። በማንኪት ታቦት ማደሪያ በማኅሌቱ ሥርዓት ላይ ሥርዓተ ቅዳሴ፣ ወንጌል፣ ኪዳንና በመጨረሻም የዋዜማው ፍጻሜ የኾነውን የባሕረ ጥምቀቱን ቅዳሴ ያሳርጋሉ።

ቀሳውስቱ በጎንደር ጥምቀት ተሳትፏቸው መንፈሳዊነት ያለው ኹኖ ከከበሮና ከጸናጽል፣ ከሽብሻቦና ከመረግድ ይልቅ በቅዳሴና በሰዓታት ላይ ያተኮሩ ናቸው። አለባበሳቸው እጅግ ያማረና በኅብረ ቀለም ያሸበረቀ ነው።



(ታቦታቱና ቀሳውስቱ በማንኪት ታቦት ማደሪያ 2011)

የቀሳውስቱ አለባበስና ተምሳሌት የ24ቱ ካህናተ ሰማይ ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በመንበረ ልዑል ኪሩቤልና ሱራፌል አጠገብ ኹነው ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ እያሉ ያለ ማቋረጥ እና ያለ ዕረፍት ለእግዚአብሔር የሚያደርሱትን ምስጋና ይመለከታል፡፡ በዚህም ቀሳውስቱ የእነዚህ ተምሳሌት በመሆን ምእመኑን ከአምላክ ጋራ የሚያገናኙ ናቸው ተብሎ ይታመናል፡፡ አንድም የቀሳውስቱ ሕብረ ቀለማት የጎንደርን ማኅበረሰብ የሚወክል ነው፡፡ የጎንደር ማኅበረሰብ የሃይማኖት፣ የብሔር፣ የዕውቀት፣ የዕድሜ፣ የጾታ፣ የሊቃውንት፣ የሹማምንት፣ የምእመን ሕብረ ቀለማት ድምር ነው፡፡ በመኾኑም የካህናቱ ልብሰ ተክህኖ ኅብረ ቀለማት የጎንደርን ማኅበረሰብ አብሮነት ጌጥ፣ ውበት እና መታደል ያዘክራል (አባ ገብረ ሥላሴ 03/06/11 ቃ.መ)፡፡

ማኅበረሰቡ ለሊቃውንቱ ከዕውቀት ጋራ አያይዞ የሚሰጠው ክብር ያክል ለካህናቱ የሚሰጠው ክብር ደግሞ ከሥልጣነ ክህነት ጋራ የተያያዘ ነው፡፡ ሥልጣነ ክህነትን የሚረዳበት መንገድ በሥጋዊና መንፈሳዊ ግልጋሎት ነው፡፡ ቀሳውስቱ የታመመውን በማጥመቅ ከበሽታ ይፈውሳሉ፡፡ ክርስትና በማንሳት ስመ ክርስትና ሀብተ ውልድና ያስገኛሉ፡፡ ጸላእያን አጋንንትን እና መናፍስትን በጸሎታቸው ያስራሉ ተብሎ በማኅበረሰቡ ዘንድ ይታመናል፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ ካህናቱን ዐቃቤ ሥጋ እና ዐቃቤ ነፍስ አድርጎ ይመለከታቸዋል (አባ ገብረ ሥላሴ 03/06/11 ቃ.መ)፡፡

በሌላ መልኩ ደግሞ እነዚህ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ቀሳውስት የነፍስ አባት በመሆን፣ በመናዘዝ በመገሠጽ እና በማስተማር ነፍስን ወደ ገነት እንደትገባ መራሔ ናቸው ብለው ያምናሉ፡፡ በጥምቀት ዕለት ምእመኑ ሕፃናቱ ጉልበት እየሳሙ መስቀል ይሳለማሉ፡፡ የጥምቀቱን ጠበል ተባርኮ የሚረጭ በካህናቱ ነው፡፡ በቀሳውስቱና በምእመኑ ያለው ግንኙነት ከልጅና አባት ጋራ የሚደረግ መስተጋብር ይመስላል፡፡ ምእመኑ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ይጠመቃሉ፤ መስቀል ይሳለማሉ፤ በመጨረሻም ይፍቱኝ ይላሉ[59] (አባ ገብረ ሥላሴ 03/06/11 ቃ.መ)፡፡ በዚህ ጊዜ በካህናቱና በምእመኑ መካከል የሚደረገው የጥምቀት ግንኙነት የመዳን፣ የመፈወስ እና የመንጻት ነው፡፡ ምእመኑ ከኀጢአታቸው ኹሉ ወይም ከሠሩት ክፉ ድርጊት በጥምቀት ጠበል እንደተፈወሱ ስለሚሰማቸው በውስጣቸው የመዳን እና ነጻ የመውጣት ዕረፍት የማግኘት ዕድል ይዘው ይመለሳሉ (አባ ገብረ ሥላሴ 03/06/11 ቃ.መ)፡፡

[59] ምእመኑን ተከትለው ቀሳውስቱ የሚሰጡትን ስርየት ቃል ከሥልጣነ ክህነት ጋራ ተያይዞ አስተምህሮው ስለሚከለከል ለማካተት አልቻልኩም፡፡

በጎንደር ጥምቀተ ባሕር ከመፌወስ ጋራ በተያያዘ ጳጳሱ ከባረኩትና ከተረጨ በኋላ ከዛፍ ላይ እየዘለሉ ወደ ጥምቀተ ባሕሩ ገንዳ ይገባሉ፡፡ የተጠማቂው ቁጥርና የዋናተኛው ቁጥር በውል ስለማይታወቅ አንዳንድ ጊዜ በመዋኛው ገንዳ ውስጥ የመጨናነቅ እና የመታፈን ኹኔታዎች ያጋጥማሉ፡፡



*(የጸበል ርጭት ሥርዐት በጎንደር ጥምቀት 2013)*

### 5.3. የሰንበት ተማሪዎች ክዋኔ በጎንደር ጥምቀት

የጎንደርን ጥምቀት ከሚያደምቁትና ከሚሳተፉት የማኅበረሰብ ክፍሎች መካካል የሰንበት ትምህርት ቤት መዘምራን ከፍ ያለ ድርሻ አላቸው፡፡ ይህን በተመለከተ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *የሰንበት ትምህርት ቤት ዘማርያን እየዘመሩ ከእነሱ በኋላ ኹነው ደግሞ ወጣቶቹ ሆ እያሉ ለጥምቀት በዓል የሚገባውን ሆታ ማለት ነው፡፡ ሴቶች እልል እያሉ ከጥምቀተ ባሕር አንሥቶ እስከ መስቀል አደባባይ ወይም እስከ ዐፄ ፋሲል ቤተ መንግሥት ድረስ ታቦታቱ ሲወርዱም ሲመለሱም ያለው የሕዝብ ብዛትና ሆታው የእልልታው ድምቀት ህዝቡን አንድ አድርጎ ገፋኸኝ ገፋሸኝ አይባባልም፡፡ የፍቅር በዓል ነው፡፡ እንዳውም ፍቅር የሚገዛበት በዓል ነው፡፡ ተደጋግፎ አንዱ ቢገፋው እንኳንሥ ስቆ ተሣሥቆ ነው እንጅ በፍቅር የሚለያይ መጣላት የለም፡፡ ጠብን በጥምቀት በዓል ወደ ፍቅር የሚለወጥበት ተለውጦ የምናይበት በዓል ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

በ05/10/11 ከጥምቀቱ ዋዜማ ጀምሮ ባደረግኩት ምልከታ የሰንበት መዘምራን እየዘመሩና እያሸበሸቡ እና ታቦታቱን እየከበከቡ ወደ ጥምቀተ ባሕሩ አውርደዋል፡፡ እኔም ከካህናቱ፣ ከሊቃውንቱ እና ከሰንበት ዘማርያኑ ወጣ ገባ እያልኩ ምልከታዬን ማካሄድ ቀጥያለሁ፡፡ እነዚህ የሰንበት ዘማርያን እና ዘማርያት ከቀሳውስቱና ዲያቆናቱ ከሊቃውንቱና መዘምራኑ በተለየ መልኩ በዕድሜ ደረጃ ሲታዩ ወጣቶች ናቸው፡፡ ሴቶቹ የሰንበት ዘማርያት በሰንበት ትምህርት ቤቱ በማኀበር የተሰፋ እና የመስቀል ምልክት ያለበት ቀሚስ ይለብሳሉ፡፡ ሴቶቹ እራሳቸውን በነጭ ሻሽ ይሸፍናሉ፡፡ ወንድ ወጣቶች ደግሞ እንደ ሴቶቹ መዘምራን ሁሉ በማኀበሩ የተሰፋ የመስቀል ምልክት ያለበት ቀሚስ ይለብሳሉ፡፡ ወንዶቹ መዘምራን ራሳቸውን እንደ ሴቶቹ በሻሽ አይሸፍኑም፡፡

የሴቶቹ በሻሽ ራሳቸውን ማሰራቸውና መሸፈናቸው አንድም ሃይማኖታዊ መነሻ፣ አንድም ማኀበረሰባዊ ትርጉም አለው፡፡ ሃይማኖታዊ አንድምታው በዐይን መመልከትን፣ በልብ ማሰብን እና በኀልዮ ኀጢአት መውደቅን መከልከል ነው፡፡ ይህም ከፈቃደ ሥጋ እየተጠበቁ፣ በድንግልና በንጽሕና ፈጣሪያቸውን እያገለገሉ መኾናቸውን የሚያጠይቅ ነው፡፡ ማኀበረሰባዊ አንድምታው ደግሞ በዚህ ማኀበረሰብ ውስጥ የሴቶች መሸፈን ቀድሞ ከአባቶች የነበረ እና ከእቴጌዎቹ የቀጠለ ነው፡፡ በጎንደር ቤተ መንግሥት እቴጌዎቹ በዐይነ ርእግብ ተሸፍነው፣ ደንገጡር አስከትለው ይወጡ ነበር፡፡ የጎንደር አካባቢ ማኀበረሰብ ከፍ ያለ ክብርና ቦታ ያላቸውን ሰዎች መሸፈን እና መጋረድ የቆየ ልማድ አለው፡፡ በመኾኑም የሴቶች በሻሽ መሸፈን ይህን ማኀበረሰባዊ ትውፊት የሚያዘክር ነው (ዘማሪት ስንዱ ወርቁ 12/05/2011 እና መ/ር እንባቆም 10/05/13 ቃ.መ)፡፡

እስካሁንም ድረስ በጎንደር አካባቢ ሴት ሙሽሮች ተሸፍነው ወደ ጫጉላ ይገባሉ፡፡ በጎንደር ማኀበረሰብ ዘንድ መሸፈን ለሴቶች የበለጠ የመድመቅ፣ የማጌጥ እና ከፍ የማለት ማኀበረሰባዊ ቅቡልነት ያለው ባህል ነው፡፡ ሴቶች የሚዋቡበት ሻሽ፣ ቀሚስ፣ መቀነት እና መሰል የጥምቀት አልባሳት ለልጃ ገረዶቹና ለዘማርያኑ የክብርና የልዕልና ፈርጥ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የከበረ እና ውድ ነገር ኹል ጊዜ በምስጢር በድብቅ እንጅ ተጋልጦ፣ አፍጥጦ እና አግጥጦ አፍኣ አይወጣም፡፡ በጥምቀት ዐውድ ሴት ዘማርያት መሸፈናቸው አንድም የንጽሕናቸው፣ አንድም የማኀበራዊ መስተጋብራቸው ማጠየቂያ እንጅ ገደብ መጣያ አይደለም (ዘማሪት ስንዱ ወርቁ 12/05/2011 ቃ.መ እና መ/ር ዳዊት ስራው 03/06/12 ቃ.መ)፡፡

የሰንበት ዘማሪዎች በዝማሬ ደረጃ ጸናጽል፣ መቋሚያ፣ ከበሮ እና ቃለ እግዚአብሔሩን በመሳተፍ እኩል በቅብብሎሽ ወይም በተራ ያስኬዳሉ፡፡ ወንዶቹ ዘማሪዎች ከሴቶቹ በተለየ ወይም በተሻለ መልኩ የሚዘምሩት፣ የሚወርቡት፣ የሚቸበችቡት እና የሚያስረገጡት ክዋኔ የለም፡፡ እጅግ እኩል በሆነ መልኩ የጸናጽል፣ የመቋሚያ፣ የሽብሻቦ እና የወረብ ክዋኔ በእየተራ ያቀርባሉ፡፡ በጎንደር ጥምቀት በወንድና ሴት ዘማሪዎች የሚከወን የሰንበት ዘማሪዎች እንቅስቃሴ ቀልብን እጅግ ይስባል፡፡ በዕለተ ጥምቀቱ የሰንበት ዘማርያን እንደ ካህናቱና ሊቃውንቱ ኹሉ የራሳቸው የቦታ አደረጃጀት አላቸው፡፡ ደረጃቸው ከታቦቱ፣ ከቀሳውስቱ እና ከሊቃውንቱ ቀጥሎ በምእመኑና በሊቃውንቱ መካከል ያለውን ቦታ ይሸፍናል፡፡



*(በጎንደር ጥምቀት የሰንበት ዘማርያን/ት በፒያሳ መስቀለ አደባባይ ሲያስረግጡ 2013 ዓ.ም)*

በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል የበርካታ አብያተ ክርስቲያናት ዘማሪዎች ይሳተፋሉ፡፡ እኔ ባደረግኹት ምልከታ የአጣጣሚ ሚካኤል የሰንበት መዘምራን፣ የአደባባይ ኢየሱስ፣ የፊት አቦ፣ የፊት ሚካኤል፣ የአባጃሌ ተ/ሃይማኖት፣ የአቡን ቤት ግቢ ገብርኤል፣ የእልፍኝ ጊዮርጊስ እና የመንበረ መንግሥት መድኀኔዓለም የሰንበት መዘምራን እና ዘማርያት በክብረ በዓሉ ተሳትፈዋል፡፡ በሰንበት ዘማርያን እና ዘማርያት መካከል የወንዶች እና የሴቶች ተዋጽኦ እኩል መኾን አንድም የጾታ እኩልነትን ያረጋግጣል፤ አንድም ወንድ ያለ ሴት፣ ሴት ያለ

ወንድ ለሥኬት መብቃት እንደማይቻል ያዘክራል፡፡ በዚህ መልኩ በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የሰንበት ዘማርያን ክዋኔ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሴቶች እና ወንዶች አብሮ መሥራት፣ እኩልነትን ያለማምዳል፣ ያስተምራል፤ ያሰርጻል፡፡

## 5.4. የልጆች[60] ተሳትፎ በጎንደር ጥምቀት

ልጆች በጎንደር ጥምቀት መዘጋጀት የሚጀምሩት ከመድረሱ ወር ቀደም ብለው ነው፡፡ ከወር ቀደም ብሎ የጥምቀት ግምግምታ ሲሰማ ወንድ ልጆች ዐዲስ እጀ ጠባብ፣ መብሩቅ ኮትና ሱሪ እንዲገዛላቸው ወላጆቻቸውን ይወተውታሉ፡፡ አንዳንድ ልጆች ጥምቀትን ታሳቢ በማድረግ ደሮ አርብተው እና ቀጤማ ዐጭደው በመሸጥ፣ ጌሾ አሳድገው እና ቀርሚያ ለቅመው ባገኙት ገንዘብ ጫማ ወይም ኮት ሊገዙ ይችላሉ (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡

ወንድ ልጆች በጥምቀት በዓል ላይ ጥሩንባ በመንፋት፣ ፊኛ በመያዝ፣ በየደረሱበትና በየአለፉበት መንገድ የሚሸጡ መጠጦችን እና ምግቦችን እየገዙ ይቀማምሳሉ፡፡ በአብዛኛው የልጆች ተሳትፎ በጥምቀቱ ክዋኔ የመመልከት ተግባር ይበዛዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው የጥምቀት ክብረ በዓል ስለአካባቢቸውና ስለ ማኅበረሰቡ ማንነት ዕውቀትና ግንዛቤ የሚያገኙበት ትምህርት ቤት መኾኑን ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ልጆች ከዋናው ሆታ በመራቅ እና በቅርብ ርቀት በመኾን ዘፈኑን፣ እስክስታውን ጭፈራውን እና ወረቡን በተመስጦ ይከታተላሉ፡፡ የጥምቀቱን ፈርጀ ብዙ ክዋኔዎች ከቻሉ በራሳቸው ዐቅም፣ ካልቻሉ ደግሞ በወላጅና በቅርብ ዘመድ ታቅፈው ወይም አሽኮኮ ተብለው ይመለከታሉ፡፡ ልጆች ነፍስ ሳያውቁ ጀምሮ በአንቀልባ እና በዕቅፍ ጀምረው የጎንደርን ጥምቀት ያከብራሉ፡፡ በዚህ ኺደት ውስጥ የማኅበረሰቡን ትውፊት እየተማሩ ያድጋሉ፡፡ በመኾኑም የጥምቀት ክብረ በዓል ለልጆች የአእምሮ ማስሊያ፣ የዕሴት ማስተማሪያ እና የአካባቢ መገንዘቢያ በመኾን ያገለግላል፡፡ ይህን በተመለከተ ወ/ሮ ፀሐዬ ካሳ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *እኔን መቼ ነው የጎንደርን ጥምቀት ያወቅሽው ብትለኝ በዚህ ጊዜ አልልህም፡፡ እናትና አባትሽን መቼ ነው ያወቅሻቸው እንደ ማለት ነው፡፡ እናቴ ነፍሰጡር ኹናም ጥምቀት አትቀርም፡፡ ከወለደችኝ በዛኅል አንቀልባ አዝላኝ ሳውቅም አስከትላኝ ከባልንጀሮቿ ጋራ*

[60] እነዚህን የጥምቀት ተሳታፊዎች በእድሜ ቁርጥ ያለ መስፈርት አላወጣላቸውም፡፡ በዐይነት ስለካቸው ከእናት እቅፍ የወረዱትን እና ራሳቸውን ችለው ደግሞ የማየከውኑትን ለማለት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ከፍ ያሉትን ልጆች አነስ ያሉትን ደግሞ ሕፃናት እያልኩኝ ተጠቅሜያለሁ፡፡

*ጥምቀት እንሄድ ነበር። የጥምቀት ጭምጭምታ ሲሰማ እንቅልፍ አንተኛም። በጣም ልጆች ሳለን የምንንን ነን። ቅጡ ነው የሚጠፋን። ከዘፈኑ፣ ከአቡኑ፣ ከሆታው፣ ከግናው፣ ከፈረሱ፣ እንዲያው ዝም ብለን እንደ ሸማኔ መወርወሪያ ስንባክን ነበር የምንውል። ተወኝ የጎንደርን ጥመቀት "ኩታራ" ኹነን እና አሁን እንዲያውም የያኔው ትዝታ ይበልጣል። ኹሉ ነገር ነው የሚያስደስተን። ጠፍተን እናመሽ ነበር። "ሞረሽ"[61] ተብለን ነው ሲመሽ እምንገባ። የአንድ ኩታራ አባት የሌላውን ልጅ ይጠብቃል። በጥምቀት ኩታራ አይከለከልም። ለጥምቀት ነፍሳችን ነው የሚወጣለት (ወ/ሮ ፀሐዬ ካሳ 08/12/ 2011 ቃ.መ)።*

ቃለ መጠይቁ እንደሚያስረዳው የጎንደር ጥምቀት ሕፃናት ርስ በርሳቸው ለመተዋወቅና ጓደኝነት ለመመሥረት አንድ ብለው የሚጀምሩበት ምዕራፍ ነው። የጎንደር ጥምቀት ለሕፃናት ግንባታ ያለውን ፋርጀ ብዙ ግልጋሎት ወ/ሮ ፀሐዬ ያስረዳሉ። ወ/ሮ ፀሐዬ እንደሚያስታውሱትና አኹንም ድረስ የቀጠለው የጎንደር ጥምቀት ለነዋሪዎቹ በዚህ ጊዜ ጀምሬ ዐየሁት ማለት እንደማይቻል ነው። የወሮ ፀሐዬ መረጃ በጥምቀት ዕለት አጥኚው በምልከታ ካየውና ካስተዋለው ጋራ ተመሳስሎ ያለው ነው። በምልከታ ባረጋገጥኩት መሠረት የጎንደር ጥምቀትና የሕፃናቱ መስተጋብር ከእናት ዕቅፍ የሚጀምር ቀዳሚ ዕሴት ነው። ልጆቹ ለአንድ አፍታ እንኳን አያርፉም። ከዚህ ታይተው ከዚያኛው በሚያደርጉት መባከን መረጃ አቀባዩ "የሸማኔ መወርወሪያ እንመስል ነበር" ያሉት ማንጸሪያ የሚሠምር ነው። የጎንደር ጥምቀት ባለው ፋርጀ ብዙና ኀብር ክዋኔ ምክንያት ሕጻናቱን ከአንድ ቦታ ተረጋግተው አይመለከቱም። የተለያየው የጥምቀት ክዋኔ ያመለጣቸው ስለሚመስላቸው በሩጫና በጥድፊያ ከየክዋኔው ዘውግ እየደረሱ ይዘግናሉ። በዚህ ምክንያት የጎንደር ጥምቀት ልጆች የማኅበረሰቡን ዕሴት የሚማሩበት፣ ክፉና ደጉን የሚለዩበት፣ የማኅበረሰቡን ዕሳቤ በትንሽ በትንሹ የሚረዱበት ነው። ይህን ለማድረግ የስሜት ሕዋሳታቸውን ተጠቅመው ዕያዩ፣ እየሰሙ፣ እየዳሰሱ እና እየቀመሱ ግንዛቤ ያገኙበታል። መረጃ አቀባዩ እንዳስረዱኝ በጎንደር ባህል የጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ሕፃናት አይከለከሉም። ይህ ባህላዊ ሥሪት ሕፃናት የማኅበረሰቡን ባህል እና ዕሴት እንዲረዱ ያስችላቸዋል።

ወንድ ልጆች በጥምቀቱ ዕለት ቁርጥ፣ ቁርጥ ሠርተው ጎንደርን የሚወክሉ የተለያዩ የባህል አልባሳት ይለብሳሉ። ሴቶቹ ደግሞ የጎንደርን ጥልፍ ቀሚስ ለብሰው የጥምቀትን በዓል ያከብራሉ። በዚህ አከባበራቸው ተመስጨ ወደ አክባሪዎቹ ልጆች ጠጋ ብየ በስሱ ማናገር

[61]"ሞረሽ" በዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ በምሽት ሰው የሚጠራበት ስም ነው። ከመሸ በኋላ ሰው በስሙ አይጠራም። ጠላት ወዳጅ ይኖራል። ሰይጣን ይለከፈዋል ተብሎ ይታመናል። በደፈናው ሞረሽ ተብሎ ነው የሚጠራ። እናም የአምሽ ሰው መጠሪያ ስም ነው (ወ/ሮ ፀሐዬ ካሳ *08/12/ 2011 ቃ.መ)።*

ጀመርኩኝ። ይህን ያህል በወጥነት የሚጠቀስ ባይሆንም በአጥኚው አረዳድ ልጆች ጥምቀትን ከምንም በላይ እንደሚወዱት፣ በጣም የሚስባቸው ደግሞ ከእነሱ በዕድሜ ከፍ ያሉትን ልጆች እንደየፆታቸው መምሰል እንደኾነ ተረድቻለሁ። በርግጥ ከልጆች ጋራ ቤተሰቦቻቸው እናቶች፣ አባቶች፣ እኅት እና ወንደሞቻቸው ይከተሏቸዋል። ጥምቀቱ ደመቅ ሲል ግን ልጃ ገረዶችና ወንድ ወጣቶች በጥምቀቱ ስለሚማረኩ በአስተማማኝ ኹኔታ ልጆችን የመያዝ ኀላፊነት አይጣልባቸውም። ከመረጃ አቀባዮች በተጨማሪ በአጥኚው ምልከታ እናቶች ትልቁን ኀላፊነት ሲወስዱ ይስተዋላል።

ሕፃናት ልጆች በአብዛኛው ቡድን የሚመሠረቱት ከመጡበት ሰፈር የሚቀዳ ነው። የዚያ ሰፈር ወይም ጎጥ ልጆች እየተባሉ ይጠራሉ። አጥኚው ባረጋገጠው መሠረት የአጣጣሚ ሚካኤልን ልጆች፣ የመንበረ መንግሥትን መድኀኔዓለምን ልጆች፣ የማራኪ ልጆች፣ የእልፍኝ ጊዮርጊስን ልጆች፣ የጃን ተከል ልጆች እና እንደዚሁም የአየር ማረፊያ ልጆች በቡድን፣ በቡድን ኹነው ሲኼዱና ሲመለሱ ለመመልከት ችያለሁ። ልጆቹ ወደ እየቤታቸው ሲመለሱ ከጥምቀቱ የቀሰሙትን የእስክስታ፣ የጭፈራ ክዋኔ ታቦታቱን በመጥራት እንደገና ለመድገም እና ለመከወን ጥረት ያደርጋሉ። በዚህ ኺደት ሕፃናት በጎንደር ጥምቀት አካባቢቸውን ማኅበረሰቡን እና ባህላቸውን እየተረዱ ያድጉበታል።

### 5.5. የልጃ ገረዶች ክዋኔና አንድምታው በጥምቀት

በጎንደር ጥምቀት ከሚገኙ ታዳሚዎች መካከል ያላገቡ ልጃገረዶች ትልቅ ቦታ አላቸው። ልጃ ገረዶቹ በአብዛኛው ከባህሉ አኳያ የማፈር እና የመሽኮርመም ገጽታ ይታይባቸዋል። ከጥምቀቱ ዋዜማ ጀምሬ እስከ ዕለተ ጥምቀት ድረስ በልጃገረዶች ክዋኔ ላይ ምልከታ አካሂጃለሁ። ይህን ምልከታዬን ለማረጋገጥ ስለ ጎንደር ልጃገረዶች አለባበስና አከባበር በተመለከተ ለአቶ ልዕልና ኀይለ መስቀል ላቀረብኩላቸው ቃለ መጠይቅ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *ሴቶች ጥልፍ ከሙሉ ሸማ የተሰራ ሁኖ በጥልፍ የተሰራ ሙሉ እጅጌ ያለው እጅጌው አንገር አለው አንገሩና ልብሱ በዕድሜ ባገባና ባላገባ ተብሎ ይለያያል። ልጃ ገረዶች ከኾኑ ብዙ ጌጥ የበዛበት ጥልፎ ያደርጋሉ በተለይ ትክሻቸው አካባቢ። ከደረት በኩልና ትክሻ አካባቢ በጣም የተዋበ ነው የሚኾኑ የልጃ ገረዶች ጥልፍ ቀሚስ። ያገቡትና ቤት የመሠረቱት እናቶች ጥልፍ ብዙም ጌጣጌጥ የለውም። አምረው ተውበው የሚታይበት ጊዜ አልፏል። በሰከነ ሕይወት ወልደው የሚያሳድጉበት ኹኔታን የሚገልጹበት የሚያሳዩበት ነው አለባበሳቸው (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011)።*

መረጃ ሰጭዬ እንደሚያስረዱት እና አጥኚው በምልከታ እንዳረጋገጠው ያላገቡ ልጃ ገረዶች ሙሉ እጅጌ ያለው የጎንደር ቀሚስና አበባ መሰል ጌጥ የበዛበት ጥልፍ ቀሚስ ከተዋበ መቀነት ጋራ ይለብሳሉ፡፡ ይህ ጌጣጌጥ የበዛበት አለባበስ የወጣትነት፣ የማማር እና የመዋብ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ አበባ ገና ለፍሬ ያልበቃ በቀለማቱና በመዓዛው ንቦችን እና ቢራቢሮዎችን እንደሚሰብ ኹሉ ወጣት ሴቶችም ተመልካቾቻቸውን ይማርካሉ፡፡ የልጃ ገረዶቹ ጌጥ መብዛት አበባነትን፣ እንቡጥነትንና ዐዲስነትን የሚያዘክር ነው፡፡ በዚህ መልኩ ልጃ ገረዶችና አበባ ተመሳስሎ አላቸው (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡



*(በጥምቀት ክብረ በዓል ልጃ ገረዶች አበባ መሰል ጥልፍ ቀሚስ ለብሰው ሲያከብሩ 2013)*

ልጃ ገረዶቹ ከመሰል ጓደኞቻቸው ጋራ በአንድ ላይ በመኾን እጅብ ብለው በዐማረና በደመቀ መልኩ የጥምቀትን በዓል ያከብራሉ፡፡ በጥምቀት ዐውድ ላይ እንደተመለከትኩት እነዚህን በአንድ ላይ አምረው የሚያከብሩ ልጃ ገረዶች ወጣት ወንዶች እያጀረጀሩ ይከተሏቸዋል፡፡ በልጃ ገረዶች ላይ ከግራና ቀኝ የሚያጀረጅረው ወጣት ግፊያና አንዳንዴም በዐይን የመጎንተል እና ሎሚ የመወርወር ኹኔታ ይስተዋላል፡፡ ሎሚ አንድም የውበት፣ አንድም፣ የመድኀኒት፣ አንድም፣ የጥሩ መዓዛ፣ አንድም፣ የኀይል ተምሳሌት ነው፡፡ በዚህ መልኩ ሎሚ አንድም

የጎንደርን ልጃ ገረዶች ውበት ይጠቁማል፤ አንድም የፍቅርን መዓዛ ይተሩማል፤ አንድም የጎንደርን ማኅበረሰብ ኀይለኛነት፣ ቆፍጣናነት፣ መፍትሔ ዐዋቂነት ያዘክራል፤ አንድም የጥምቀትን መድሐኒትነት እና አዳኝነት ይተረጉማል (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡

በወጣት ሴቶችና ወንዶች በጥምቀቱ ክዋኔ ላይ የመቀራረብ፣ የመሽኮርመም፣ የማፈር፣ እዩኝ እዩኝ የማለት ከውበትና ወጣትነት ጋራ የሰምሩ እና የተዛነቁ ግንኙነቶች አሏቸው፡፡ በኹኔታው የመተንኮስ መይም የመተናኮል ነገር ዓይኑር እንጅ በልጃ ገረዶቹ የሚማረኩት እና አጃቢ ኹነው ልጃገረዶቹን ሲከተሉ የሚውሉ ጎረምሳዎች[62] ብዙ ናቸው፡፡ የጎንደር ጥምቀት ልጃገረዶቹ ከጓደኞቻቸው ጋራ ተጠራርተው በማኅበር እንጅ ብዙ ጊዜ በተናጠል አይኼዱም (ወ/ት ገነት ጌታሁን 11/05/11 ቃ.መ)፡፡

መረጃ አቀባዬ የመጣችው አምባ ከሚባለው የገጠሩ ክፍል ነው፡፡ በዚህም ከጓደኞቿ ጋራ በአለላ የተሰፋ አገልግል ይዛለች፡፡ ከጓደኞቿ ጋራ አንድ ዐይነት የባህል ቀሚስ የለበሱ ሲኾን ያገኘኋቸው በአንድ ላይ እያከበሩ ነበር፡፡ እኔም ከጓደኞቿ ጋራ ከየት አካባቢ እንደመጡ እና አለባበሳቸው ምንን እንደሚወክል ለገነት ጌታሁን ላቀርብኩላት ቃለ መጠይቅ ተከታዩን መረጃ ሰጥታኛለች፡፡ *"እኛ የመጣነው ከአምባ ነው፡፡ የራሳችን አለባበስ፣ አጊያጊያጥ ይዘን አገልግል ይዘን ነው ጥምቀትን የምናከብር ይህን የምናደርገው ባህላችን ስለኾነ ጥምቀትን ለማክበር ነው" (ገነት ጌታሁን 11/05/2011 ቃ.መ)፡፡*

ልጃ ገረዶቹም ኾኑ ሌሎች የጥምቀት አክባሪዎች እንደየጎጣቸው እና አካባቢያቸው የተለያየ ነው፡፡ ጎንደር ከተማ ውስጥ እና ገጠሩ ያለው የልጃ ገረዶች አለባበስ በቀሚስ በኩል አንድ ዐይነት ቢኾንም በአገልግል መያዝ፣ በሥሬት እና በእጅ አንባር የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ጌትነት አመራ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ *"በጥምቀት ቀን ልጃገረዶች አገልግል መያዝ ከጥንት ከአባቶቻችን ጀምሮ የነበረ ነው፡፡ ከእናቶቻችን አገልግሉ ምግብ ይቀመጥበታል፤ አገልግሉ የሰው ልጅ ነው የሚመስለው፤ አሰፋፉም ምኑም ይማርካል እኮ ውቢቷ ጎንደር ተባለችውን የሚመለከት ነው፡፡ አንግተውት ነው የሚኼዱት" (ጌትነት አመራ 13/05/2011 ቃ.መ)፡፡*

የገጠሩ ክፍል ልጃገረዶች የተለያየ ሳዱላ የራስ አሠራር ያላቸው ሲኾን አገልግልና የእጅ አምባር ያደርጋሉ፡፡ የጸጉር አሠራራቸው ልጃ ገረዶቹ ያልታጩ፣ ያለገቡ እና የአገቡ

---

[62] ይህ የጎረምሶች ልጃ ገረዶችን ተከትሎ ሲያጀረጅሩ መዋል ምን እንደገጠመኝ በመስክ ተሞክሮዬ ላይ ገልጬዋለሁ፡፡

መኾናቸውን የአካባቢው ማኅበረሰብ በሚረዳው እና በሚያሳይ መልኩ ነው፡፡ የጸጉር አሰራር ቁንጮና ጋሜ ሁና ጋሜው ጠባብና ቁንጮው ሰፊ ከሆነ ያልታጨች ልጃገረድ መሆኗን ይጠቁማል፡፡ ይህም ጋሜው የዐዋቂነት ምሳሌ ቁንጮው ሳዱላው ደግሞ የልጅነት ምሳሌ ነው፡፡ ይህ እያደገ መጥቶ ጋሜው እየሰፋ፣ እየሰፋ ከኼደና ከገጠመ ያገባች መሆኗን ይገልጻል፡፡ አገልግሉ በአለላ የተንቆጠቆጠ ሲኾን ልጃ ገረዶች የሚያዝሉት ነው፡፡ ይህም ልጃ ገረዶችን የወደፊት መልካም እድል የሚመኙበት ነው (ቄስ ባየው አበራ 16/05/2011 ቃ.መ)፡፡

ይህ የአለላ አገልግል ሌላ መንፈሳዊ አንድምታም አለው፡፡ መንፈሳዊ አንድምታው አገልግል የቅደስት ድንግል ማርያም ተምሳሌት ነው፡፡ በውስጡ ያለው ምግብ ደግሞ ምግበ ነፍስ የኾነው የኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት ነው (ቄስ ባየው አበራ 16/05/2011 ቃ.መ)፡፡ ይህን በተመለከተ መ/ር ዳዊት ሥራው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *በዚያን ሰዓት ልጃገረዶች በበዓሉ አምሮባቸው የሚታዩ ናቸው፡፡ አለላ አገልግል ኮረዳዎች ያላገቡት የሚይዙት ሲኾን ለመታጨት ለመፈጨት፣ የሚያበቃቸው ነው፡፡ ሌላው አገልግሉ ጌጣጌጥ ያለው መኾኑ የጎንደርን ውብነት የሚወክል ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃልም አለው፡፡ "አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ"[63] እንዳለው ጥምቀትን የሚወክል ነው፡፡ በጥምቀት መሶቡ የእመቤታችን ኅብስቱ የእየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት ነው (መ/ር ዳዊት ሥራው፣ 12/19/2011)፡፡*

መረጃው እንደሚያሳየው የጎንደር አለላ አገልግል አንድም ጎንደርን፣ አንድም የጎንደር እናቶችን ይተረጉማል፡፡ የአገልግሉ ማማር እና ውብነት የጎንደርን ውብነት ሙሽራነት የሚተረጉም ነው፡፡ ጎንደርን ከሙሽራ ጋራ የማገናኘት ሁኔታ በስፋት ይታያል፡፡ ይህን እውነታ በጎንደር ጥምቀት ዘፈን ጭፈራ ላይ የተቀነቀነውን ቃል ግጥም ያረጋግጣል፡፡

*አረጀሽ እያለ ሰው ኹሉ ሲያሙሽ*
*ጎንደር ሙሽራ ነሽ ይሰፋል ልብስሽ፡፡*
*(አዝማሪ ቸኮል* 12/05/2012*)፡፡*

ቃል ግጥሙ አንድም የጎንደርን ጥንታዊነት አንድም የጎንደርን ወጣትነት የሚተረጉም ነው፡፡ እነዚህ ኹለት ሙሽራ እና እርጅንና ተቃራኒ የሚመስሉ እንዴት ሊስማሙ ይችላሉ የሚለው ጥያቄ መነሣቱ አይቀሬ ነው፡፡ ጎንደር እንዴት የእርጅና እና የሙሽርነት ሰብእና ተሰጣት የሚለው ጥያቄም ይመዘዛል፡፡ ጎንደር በእርጅና መመሰሏ የታሪክ፣ የጥንታዊ ትውፊት፣

[63] "መሶበ ወርቅ አንቺ ነሽ" (ትርጉም የእኔ)

የባህላዊ እና መንፈሳዊ ዕውቀት ባለቤት መሆኗን ለመዘከር የቀረበ ነው፡፡ ሌላውና በቃል ግጥሙ ገዝፎ የወጣው የጎንደር ሙሽርነት ነው፡፡ ጎንደርን ሙሽራ ከሚያደርጓት መካከል አንዱና ዋናው የጎንደር ጥምቀት ነው (ቄስ ባየው አበራ 16/05/2011 እና ሊቀ መኳስ[64] ደርበው ድሌ 05/12/2011 ቃ.መ)፡፡

ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ #4 አድባራትና የጥምቀት ክብረ በዓል ጎንደርን ኹል ጊዜ ሙሽራ እንድትሆን ያደርጓታል ይላሉ፡፡ የሙሽርነት ባሕርይ መከበር፣ ማጌጥ፣ መዋብ፣ መደሰት፣ ወጣት መሆን ነው፡፡ የሕዝቧ ማማር፣ የዐጸዷ መለምለም፣ የግንቦቿ ከፍ ብለው መታየት እና የጥምቀት ክብረ በዓል ተዳምረው ጎንደርን ከሙሽራ መዋብ ጋራ ያመሳስሏታል፡፡ ዘመናት እና ወራት በዘመን መለወጫ እየታደሱ ኹል ጊዜ ከእርጅና ነጻ እንደሚሆኑ ሁሉ ጎንደርም በጥምቀት ክብረ በዓል እየታደሰች ኹል ጊዜ ወጣትነቷን ሙሽርነቷን ታረጋግጣለች (ቄስ ባየው አበራ 16/05/2011 እና ሊቀ መኳስ[65] ደርበው ድሌ 05/12/2011)፡፡

የጎንደርን ሙሽርነት ለመመስከርና ለመዘከር ልጃገረዶች በጥምቀት ዕለት በተለያዩ ቀለማት ባለው ግራምጣና አለላ የተሰፋ ሙዳይ ቅቤ ቅል በመያዝ በአንባርና በድሪ አጊጠው ይውላሉ፡፡ የጎንደርን አገልግል በተመለከተ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *አገልግል የጥንቱ ኢትዮጵያ ባህል ነው፡፡ አገልግል ሙሽራ ስትዳር ቅቤቅል፣ ሙዳይ አገልግል፣ ወስፌ፣ መርፌ፣ ይህን ኹሉ ይዛ ነው የምትሄድ ወደ ባሏ፡፡ የሙሽሪት መለያ ነው፡፡ እና የጥምቀት በዓል ሲከበር ይህን ወጣቶች ሴቶች ይዘው ነው የሚያከብሩት፡፡ ሙዳይ ይዘው አገልግል ዐዝለው ቅቤ ቅል ይዘው በጥምቀቱ ይታያሉ፡፡ እና ፈረንጆቹ ይህን ኹሉ ሙሉ በሙሉ ደስ ስለሚላቸው በተለይ ሴቶቹ አገልግሉን ያዝላሉ የቅቤ ቅሉን ይይዛሉ ከአለባበሱ ጋራ አብሮ ስለሚሄድ ማለት ነው፡፡ እና ይህን እያንዳንዱ ይገዛሉ፡፡ ይሀ ኹሉ ገቢ ነው የልማት ምንጭ ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

መረጃው እንደሚያስረዳው በጎንደር ጥምቀት የሚሳተፉት ልጃ ገረዶች ልክ በሙሽራ ጊዜ የሚለበሰው እንደ ቅቤ፣ ቅል፣ ሙዳይ፣ ወስፌ፣ መርፌ እና መሰል መዋቢያዎች አልባሳት እና መሰል መጊያጊያጫዎችን በመጠቀም ያከብሩታል፡፡ ጌጣጌጦቹ እና መዋቢያዎቹ የጎንደርን ማኅበረሰብ የሚተረጉሙ ናቸው፡፡ ቅቤ ቅል እና ሙዳይ የጎንደርን እናቶች እና ልጃ ገረዶችን ይተረጉማሉ፡፡ ቅቤ ቅል ወዙ የሚቀዳ እና የዐማረ ሲኾን ይህ የቅቤ ቅል ውበት ከጎንደር ልጃ ገረዶች ውበት ጋራ ይፎካከራል፡፡ ከቅቤ ቅሉ የሚገኘው ቅቤ ደግሞ ቢቀቡት የሚያወዛ፣ ቢመገቡት የሚስማማ ነው፡፡ ከጎንደር ወይዘሮዎች የሚገኘው ትውልድም እንደዚሁ አንድም

[64] የአዝማሪዎች የዓለም አጫዋች የበላይ ማእረግ ነው ደርበው ድሌ (05/12/2011 ቃ.መ)

በሊቃውንቱ፣ አንድም በሹማምንቱ፣ አንድም በግብርናዉ፣ አንድም በውትድርናዉ የሚሳተፉ መሆናቸውን ያዘክራል፡፡ ሙዳይ ወይም አገልግል የሚባለው ስፌት የመዋቢያ ጌጣጌጦች መያዣ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከጎንደር እናቶች ጋራ ይፈካከራል፡፡ ሙዳይው ወይም አገልግሉ በውስጡ የሚይዛቸው ቢልቃጥ፣ መርፌ፣ ወስፌ፣ ምላጭና ክር ደግሞ በእናት የተገኙትን የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ይተረጉማል (መቶ አለቃ ሞላ እድማሱ 12/05/13፣ መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ እና መ/ር ዳዊት ስራው 03/06/2012 ቃ.መ)፡፡

መርፌ ደግሞ የጎንደር አካባቢ የሀገር ሽማግሌዎችን ይተረጉማል፡፡ የጎንደር አካባቢ ሽማግሌዎች እና ነገር ዐዋቂዎች ናቸው፡፡ ሰዎች በተጣሉ እና ማኅበራዊ ችግር በአጋጠመ ጊዜ ቀዳዳውን አጥብበው፣ ክፍተቱን ሞልተው ለችግር መፍትሔን፣ ለጠብ እርቅን ያወርዳሉ፡፡ መርፌ የተቀደደውን በመስፋት፣ የተዛነፈውን በማስተካከል ርቃን ይሸፍናል፡፡ መርፌ ለመስፋት ክር እንደሚያስፈልገው የአገር ሽማጌሌዎችም እርቀ ሰላም ለማውረድ ቃል ይጠቀማሉ፡፡ በዚህም ከሽማግሌዎቹ አንደበት የሚወጣው ቃል እና ከመርፌው የሚመዘዘው ክር ተመሳስሎ አላቸው፡፡ ማኅበረሰባዊ ርቃን የሚባለው አንድ ግለሰብ በማኅበረሰቡ መዋቅር ውስጥ ማኅበረሰቡ ያወገዛቸውን ድርጊቶች ሲተላለፍ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የሰብእና እና የማኅበረሰብ መንጠፍ ሊያጋጥመው ይችላል፡፡ በተለይ በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ በትዳር መባለግ፣ "ዲቃላ" መውለድ እና ጥቁር ደም የመሳሰሉት ማኅበረሰባዊ ርቃን የሚያስከትሉ ናቸው፡፡ ግለሰቦች እንደዚህ ያለ ነውር ሲገጥማቸው ሽማጌሌዎች "ውሾን ያነሣ ውሾ" በማለት ነገሩ ተከድኖ እንዲቀር ያደርጋሉ፡፡ ይህ ተግባራቸው በማኅበረሰቡ ውስጥ ርቃኑን ቁሞ የነበረው ግለሰብ ማኅበራዊ ልብስ እንዲለብስ ያደርጉታል፡፡ በዚህ መልኩ መርፌ እና ወስፌ እነዚህን የማኅበረሰብ ክፍሎች ይወክላሉ፡፡

ወስፌ እንደ መርፌ ሁሉ የጎንደርን የሀገር ቀንድ ሽማግሌዎች ይወክላል፡፡ ሽማግሌዎቹ በአንድ በኩል ነገር ዐዋቂ በመሆናቸው "እነ እከሌ እንዳሉት፣ እነ እከሌ እንዳቆዩት" የሚባል ቋሚ ባህላዊና ማኅበራዊ ድንጅቶችን ያስቀምጣሉ፣ ወስፌም እንደ ስፌት፣ ወዲላ፣ እና መቀነቻ የመሳሰሉትን ብዙ ጊዜና ዘመን የሚሻገሩትን ባህላዊ ቁሶች ለመስፋት ያስችላል፡፡ የወስፌውና የመርፌ ሹልነት ከሽማግሌዎቹ ነገር ዐዋቂነት እና ብልህነት ጋራ ይፈካከራል፡፡ ሽማግሌዎቹ ነገር ሲያግሙ እና አገር ሲያቆሙ መሳሪያ ታጥቀው፣ ጨንገር ቆርጥው አይደለም፡፡ የሽማግሌን ቃል ንቆና ረግጦ የሚሄድ ግለሰብ ስንዝር አይራመድም የሚል እምነት በማኅበረሰቡ ልቡና ውስጥ ትክልት ነው፡፡  በዚህ መልኩ የሽማግሌ ቃል እና

የመርፌ ሹልነት ተመሳሳይ ናቸው። ሽማግሌ ከጉዳይ እና ነገር ዐዋቂነት ጋራ ያለውን ከፍታ ለማሳየት በጎንደር ማኅበረሰብ "ሰማይ ተቀደደ ቢሉት ሽማግሌ ይሰፋዋል ይባላል" ይህ የሽማግሌን ሁለንተናዊ መፍትሔ አምጭነት፣ ችሎታና ተሰጥኦ የሚያጠይቅ ነው። በዚህም ወስፌና መርፌ የጎንደርን የሀገር ሽማግሌዎች ይወክላሉ (መቶ አለቃ ሞላ እድማሱ 12/05/13 እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ ቃ.መ)።

እንደዚኹም በሙዳይው ውስጥ የሚገኘው ሌላው ቢልቃጥ ነው። ቢልቃጥ በውስጡ የሽቱ መያዣ ነው። ይህ ቢልቃጥ የጎንደርን ሊቃውንት እና ካህናት ይወክላል። ሊቃውንቱ ሰማየ ሰማያት የሚደርስ ሰውን ከፈጣሪ የሚስታርቅ የቃለ እግዚአብሔር ባለቤቶች ናቸው። እነዚህ የጎንደር ካህናት ዕውቀታቸው ከሽቱው ጋራ ሥልጣናቸው ደግሞ ከብልቃጡ ጋራ ይፈካከራል። የሊቃውንቱ ሥርዓተ ቁመት በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ሲታዩ በክዋኔው ውስጥ ልብን የመመሰጥ፣ ቀልብን የመስረቅ እና አልጫውን የማጣፈጥ ዐቅም አለው። ሽቱውም በመዓዛው ውበት አፍንጫን ሰርቆ ጥሩ መዓዛ እንዲተነፍስ ያደርጋል። በዚህም የጎንደር ሊቃውንቱ በጎንደር ጥምቀት የሚያደርጉት ቁመት፣ ቅኔና ወርብ ከቢልቃጡ ሽቱ ጋራ ይፈካከራል (መቶ አለቃ ሞላ እድማሱ 12/05/13፣ መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ እና መ/ር ዳዊት ሥራው 03/06/2012 ቃ.መ)።

ቢልቃጡ ደግሞ ከሥልጣነ ክህነት ጋራይመሳሰላል። ቢልቃጥ ወድቆ እንደማይነሣና ጥንቃቄ እንደሚፈልግ ኹሉ ሥልጣነ ክህነትም በንጽሕና በጥንቃቄ መያዝ እንዳለበት ከወደቁ ተመልሰው የማይጠገኑ ናቸው። ይህም የቢልቃጡን እና የሥልጣነ ክህነትን ተመሳስሎ ያጎላዋል። የሥልጣነ ክህነት ሹመት ከሰማይ ስለሆነ እንደገና የሚታገም፣ የሚጠገን እና የሚመለስበት ዕድል የለውም። ቢልቃጥም ሥሪቱ ከብርጭቆ ስለሆነ ከተሰበረ ተጠግኖ ለአገልግሎት አይበቃም። ለብርጭቆ ውደቀት ጠላቱ እንደሆነ ኹሉ ለሥልጣነ ክህነትም ኀጢያት ጠላቱ ነው። በመኾኑም ቢልቃጥና ክህነት ተመሳስሎ አላቸው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/11፣ መቶ አለቃ ሞላ እድማሱ 12/05/13 እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ 12/05/13 ቃ.መ)።

ሌላው በሙዳይው ውስጥ የሚገኘው ምላጭ ነው። ምላጭ የጎንደርን ነገሥታት እና የወታደሩን የማኅበረሰብ ክፍል ይተረጉማል። ይህ የወታደሩ የማኅበረሰብ ክፍል ጎንደርን እና ማኅበረሰቦቿን የመጠበቅ ሥልጣንና ኀላፊነት አለበት። በዚህ መልኩ ከምላጭ ጋራ

ይፈካከራል። ምላጭ እባጭን የማስተንፈስ፣ ጸጉርን የመላጨት፣ ማስሪያ እና ጥፍር የመቁረጥ አገልገሎት ይሰጣል። የተጠቀሱት እንደ እባጭ ያሉ በሽታዎች በማኅበረሰቡ ዘንድ አስቸጋሪዎች ናቸው። ጠጉርና ጥፍርም በዓዳዎች ናቸው። እነዚህ በዓዳዎች ከበዓዳ ወራሪ ጋራ ይፈካከራሉ። ምላጭ እባጭ በማስተንፈስ፣ ጥፍር በመቆረጥ፣ ጸጉር በመላጨት ሰዎችን ይታደጋል። የጎንደር ነገሥታትም የጎንደርን ውጫዊ ኀይሎች በመገዳደር ማኅበረሰቡን ይታደጋሉ። በመኾኑም የምላጩ ስለት እና የነገሥታቱ ኀይል ተፈካካሪዎች ናቸው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/11 እና መ/ር ዳዊት ስራው 03/06/2012 ቃ.መ)።

እነዚህ ከላይ የተፈከሩት ምላጭ፣ መርፌ፣ ወስፌ፣ ብልቃጥ በአንድ ላይ የሚገኙት በአገልግል ውስጥ ነው። ይህ አገልግል አንድም የእናቶች አንድም የጎንደር ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል። የእነዚህ ማኅበረሰብ ክፍሎች መገኛ እናት እንደሆነች ኹሉ የእነዚህ ቁሳቁሶች ሰብሳቢ በጥምቀት ዕለት የተያዘው አገልግል ነው። በዚህ መልኩ እናትና የጎንደር አገልግል ይፈካከራሉ። አንድም አገልግሉ የጎንደር ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል። ሽማግሌዎች፣ ነገር ዐዋቂዎች፣ አርሶ አደሮች፣ ነጋዴዎች፣ ሊቃውንቱ እና ነገሥታቱ ኹሉ መገኛቸው ጎንደር ውስጥ ነው። የእነዚህ የተለያዩ ማኅበረሰቦቹ መታቀፊያ ጎንደር እንደሆነች ኹሉ የባህላዊ መጋጊያጫ መሣሪያዎቹ መታቀፊያም አገልግሉ ነው። በዚህ መልኩ በጥምቀት ክብረ በዓል በልጃ ገረዶች እና እናቶች የሚያዘው አገልግል ጎንደርን እና የጎንደርን እናቶችን ይተረጉማል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/11፣ መቶ አለቃ ሞላ እድማሱ 12/05/13 እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ ቃ.መ)።

በጎንደር ጥምቀት የሚሳተፉ ልጃ ገረዶች ከጥምቀቱ ሃይማኖታዊ በረከት በተጨማሪ ነጻነት የሚያገኙበት ነው። በጥምቀት ለምን በዚህ ኼድሽ፣ ለምን በዚህ ወጣሽ፣ ለምን በዚህ ወረድሽ፣ ለምን ይህን ዘፈንሽ የሚል ተቃውሞ ከቤተሰብ ኾነ ከማኅበረሰቡ አይነሣም (አገሬ መሳፍንት፣ 11/05/ 2011 ቃ.መ)።

የጥምቀት ዕለት ጥር 11/ 2011 ዓ.ም እጅብ ብለው ጥምቀት ውለው ወደ ማራኪ ከሚመለሱት ልጃ ገረዶች መካከል ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ የኾነችውን አገሬ መሳፍንትን[66] ቃለ መጠይቅ አቅርቤላታለሁ። እሷም የጥምቀት ዕለት ከማንኛውም ጊዜ የበለጠ ያለ ከልካይ ጓደኞቿን የምታገኝበት፣ የምትዘፍንበት፣ የምትጨፍርበት፣ በሙሉ ነጻነት የምትደሰትበት

---

[66] ልጃ ገረዷን ለመጠየቅ ከእሷ በተጨማሪ ዐብሯት የነበረውን ታላቅ ወንድሟን አስፈቅጄ ነው። ስለሆነም ፍጹም ነጻ ናቸው ማለት አይቻልም።

ጊዜ እንደሆነ በቃለ መጠይቁ አስረድታኛለች፡፡ መረጃ ሰጭዬ በተጨማሪም በአዘቦት ጊዜ ልጃ ገረዶች ላይ የቤተሰብ ቁጥጥር መብዛቱና ከዚህ በተጨማሪ የአከባቢ ወጣቶች ትንኮሳ፣ የአዛውንቶች ትችት ከፍተኛ መሆኑን እንደሚከተለው አስረድታኛለች፡፡

*"ሴት ልጆች ጭምት እንዲኾኑ ይፈለጋል፡፡ አንዲት ልጃ ገረድ የቅርብ ሰው ካልሆነች በቀር በሰርግ፣ በክርስትና፣ በማኀበር ብትዘፍን፣ እስክስታ ብትወርድ እና አምራ ብትወጣ እብዲት፣ ቀልበ ቀላል እና አሳዳጊ የበደላት መባሏ አይቀርም፡፡ ብሶታችን ለመግለጽ በጥምቀት እና በሰርግ ወቅት ጭምትነትን ለመቃወም "እብዲት እብዲት አሉኝ ሙሪት*[67] *ሙሪት፣ መቼ ተወልጀ መቼ ልጨምት" እያልን እናንጎራጉራለን"* (*አገሬ መሳፍንት*፣ 11/05/ 2011 *ቃ.መ*)፡፡

ከላይ የተሰጠውን መረጃ ስንመለከት የጎንደር ጥምቀት ለሴት ልጆች ከዘወትሩ የተለየ ነጻነትን የሚያጎናጽፍ መሆኑን አመላካች ነው፡፡ በጥምቀት ዕለት ሴት ልጅ ብትዘፍን ብታቀነቅን፣ ብትጫወት እና ብትቃለድ እንደቀደመው ጊዜ እብዲት እና ሙሪት አትባልም፡፡ በጥምቀት ቀን ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል በመኾኑ ዐይተው ያደንቃሉ፤ ወይም ለአጭት ሽማግሌ ይልካሉ እንጂ ወጣቶቹ እንደዘወትሩ ለተለየ ጥቃት በልጃ ገረዶች ላይ አይከጅሉም፡፡ በዚህ መክንያት ልጃ ገረዶች ከጓደኞቻቸው ጋራ በኅብረት በመውጣት እንደ ልባቸው አንገታቸውን አሳይተው፣ እንደየ ችሎታቸው ዘፍነውና አመስግነው ለዓመቱ ተሥእለው የሚገቡበት በዓል ነው (*አገሬ መሳፍንት*፣ 11/05/ 2011 እና *ዋለልኝ ደስታ*፣ 20/ 05/ 2011 *ቃ.መ*)፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የልጃገረዶች ክዋኔ አለባበስ እና አጊያጊያጥ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሴቶችን ቦታ እና እማዊ ሥርዓቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ሴት በዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ብልኅ እና ለችግር መፍትሔ አምጭ ተደርጋ ትወሰዳለች፡፡ በተግባርም ዐፄ ቴዎድሮስ አጣብቂኝ ወስጥ ሲገቡ ማምለጫ መንገድ ከእቴጌ ተዋበች ያገኛሉ፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ የሴትን ብልኅነት እና መላ ሰጭነት የሚያረጋግጡ ተረቶች እና አፈ ታሪኮች በብዛት ይነገራሉ፡፡ አንድም የልጃ ገረዶች ክዋኔ እማዊ ሥርዓቱን የሚወክል ነው፡፡ በልጃ ገረዶቹ ክዋኔ የወጣቶቹን ግፊያ ይለዘባል፤ ክዋኔው ቅርጽና ውበት ይይዛል፡፡ በርካታ ታደሚዎች በልጃ ገረዶቹ ክዋኔ፣ አለባበስ እና አጊያጊያጥ የሚማረኩ እና የሚወድቁ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንት ዐይናቸውን ተክለው፣ ጆሯቸውን ሰጥተው ከልጃ ገረዶቹ ላይ ይውላል፡፡ ይህ ኹኔታ ሲታይ ሰዎች ባይኾኑትም

[67] ለያዥ ለገራዥ የአቃተ፣ ነውር እና ጸያፍ ያለየ፣ ለባህልና ህግ ያልተገዛ (መ/ር ዳዊት ሥራው 03/06/2012 ቃ.መ)፣

እማዊ ሥርዓቱን የሚመኙት ይመስላል፡፡ በዚህ መልኩ የልጃ ገረዶች ክዋኔ፣ አልባሳት እና አጊያጊያጥ አንድም ማኅበረሰባዊ ተሳትፏቸውን፣ አንድም እማዊ ሥርዓቱን የሚወክል ነው፡፡

### 5.6. የእናቶች ክዋኔ እና አንድምታው በጎንደር ጥምቀት

በጎንደር ጥምቀት በዓል ከሚታደሙት ምእመናን መካካል የአገቡ ሴቶችም ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የአገቡ ሴቶች በጥምቀቱ በዓል ላይ የመዝፈን፣ የማቀንቀን፣ እስክስታ የመውረድና ታቦቱን የማክበር ሥርዓት አላቸው፡፡ አለባበሳቸውና የጸጉር አሠራራቸው የአገቡ ሴቶች ከአላገቡት ይለያሉ፡፡ ይህን ሐሳብ በተመለከተ አቶ በሪሁን አካላትን ጠይቄያቸው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *የጥምቀት ሹርባ ነው እሚሠራው ሹርባ ነው፡፡ ሚለበስም ነጠላ ነው፡፡ ርባን ነበር ድሮ ወጣቶች፡፡ ድሪ፣ ቀሚስ፣ መስቀል፣ ድኮት ስታየው ሳዱላው ልዩ ነው፡፡ ሳዱላ ዕድሜዋን እየለካህ ድርብ ሳዱላ አለ፡፡ ከፍ ስትል እተደረበ ይኼድና እየጠበበ መጥቶ እስክትዳርድረስ ይሠራል፡፡ ሳዱላው ሲደፈን እማውራ ኹናለች (አቶ በሪሁን አካላት 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡*



(አቶ በሪሁን አካላት 12/12/2011 በቃለ መጠይቅ ላይ)

አቶ በሪሁን አካላት ካላቸው ዕድሜ እና ልምድ ተነሥተው ወደ ኋላ በትዝታ ከሰጡት መረጃ እንደምንረዳው በጥምቀት ክብረ በዓል ያገቡ ሴቶች ካላገቡት ልጃገረዶች የሚለዩበት

የራሳቸው የኾነ የጸጉር አሠራር ባህል አላቸው፡፡ አንዲት ልጃ ገረድ በሳዱላ የጸጉር አሠራር ከተሠራች እና በጥምቀት ክብረ በዓል ከዋለች ያልታጨች መሆኗን አመላካች ነው፡፡ ጸጉሯ ሙሉው ድፍን ሥሬት፣ አለባሶ እና አሳ ሥሬት ከሆነ ደግሞ ያገባች መሆኗን ያሳውቃል (መልሽው ጌጡ፣ 12/ 05/ 2013 እና አቶ በሪሁን አካላት 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡

ይህ የጸጉር አሠራር ያገባቻውን ካላገባቻው በመለየት ለእጭትና ለጋብቻ የሚያመቻች ከመኾኑ ባሻገር ኀላፊነትንም ጭምር ይተረጉማል፡፡ የአገባቸው ሴት የጸጉር አሰራር ድፍን እና ክቡ መሆን ኀላፊነትን የመረከብ ዐቅም ያላት መሆኗን ያረጋግጣል፡፡ በዚህ የጸጉር የአሠራር የተዋበች ሴት በጥምቀት ዕለት ወጥታ ስትታይ ቤት እየመራች፣ ልጆች እያሳደገች መሆኗ በተመልካቾች ዘንድ ይታወቃል፡፡ ሌላው በጎንደር ጥምቀት ሴቶች ለየት ያለ የቀሚስ አለባበስ ሥርዐት አላቸው፡፡ የጎንደር ሴቶች ቀሚስ በጥልፍ ደረጃ እኩል 13 ጥልፍ ያለው ይሁን እንጂ ያገቡ ሴቶች ቀሚስ ካላገቡት ይለያል፡፡ የአገቡት ሴቶች ቀሚስ ከፊት በኩል በደረት የሚወርደው እና ዘርፋዘርፍ ያለው ጌጥ አበባ መሰል ቅርጽ የለውም፡፡ በዚህ መልኩ ጌጣጌጡም እንደ ልጃ ገረዶቹ የበዛ አይደለም (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/11፣ መልሽው ጌጡ፣ 12/ 05/ 2013 እና አቶ በሪሁን አካላት 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡

የአገቡ ሴቶች አበባ መሰል ቅርጽ እና ጌጣጌጥ የበዛበት ቀሚስ አለመልበሳቸው ምን ትርጉም አለው የሚል ቃለ መጠይቅ ለአቶ ልዕልና ኀይለ መስቀል አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም *"ያገቡትና ቤት የመሠረቱት እናቶች ጥልፍ ብዙም ጌጣጌጥ የለውም፡፡ አምረው ተውበው የሚታይበት ጊዜ አልፏል፡፡ በሰከነ ሕይወት ወልደው የሚያሳድጉበት ኹኔታን የሚገልጹበት የሚያሳዩበት ነው አለባበሳቸው"* (ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011) የሚል መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

ከላይ እንደተገለጸው የአገቡ ሴቶች በጎንደር ጥምቀት የተለየ አለባበስ አላቸው፡፡ የእነዚህ ሴቶች አለባበስ መለየት ሎሚ እንዳይወረወርባቸው፣ የፍቅር ፍላጎት ያለው ወጣት በትዳር ዓለም ያለች መኾኗን ተረድቶ ሐሳቡን እንዲያስተካክል ያስችለዋል፡፡ በጎንደር ጥምቀት የአገቡ ሴቶች በጥምቀቱ ዐውድ ውስጥ ከዚያም ከዚያም እየተመላለሱ የመሳተፍ ዕድላቸው የተወሰነ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ተጨማሪ ኀላፊነት ያለባቸው በመኾኑ ወደ ልጆቻቸው፣ ወደ ቤታቸው የሚመለከቱበት ኹኔታ መኖሩ ነው (የሽ ደሴ 21/11/2011 እና ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 ዓ.ም)፡፡

እናቶች በጎንደር ጥምቀት “ለጥምቀት ያልኾነ ቀሚስ ይበጣጠስ” እንደሚባለው ዋናው ልዩ ኹነው አሸብርቀው የሚውሉበት አልባሳት የጎንደር ቀሚስ ነው። ይህ ቀሚስ ራሱን ችሎ የጎንደር መለያ እና መታወቂያ ነው። ቀሚሱ በታዋቂ የጎንደር ጠላፊዎች የተጠለፈ ነው። ጥልፉ በአብዛኛው የመስቀል ቅርጽ ያለው ነው። የመስቀሉ ብዛት ደግሞ ዐሥራ ሦስት ነው። መስቀሉ ከላይ ቢለያይም ከሥር መነሻው አንድ ኹኖ መልኩ ጸዐዳ ነው። ይህ የጎንደር ቀሚስ የተለያዩ አንድምታዎች አሉት (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ 15/11/11፣ መልሸው ጌጡ፣ 12/ 05/ 2013 እና አባ በሪሁን አካላት 12/12/2011 ቃ.መ)።

የጥልፉ ዘርፋዘርፉ የጎንደርን የተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች እና ልዩነቶችን እንዴት ይወክላል? የሚለውን እና የቀሚሱ ጥልፍ 13 የመሆን ትርጓሜ እንዲያስረዱኝ ለሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር። እሳቸውም ቀጣዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *እናቶቻችን እና እኅቶቻችንም እንዲሁ የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ አለ። ወደ ፲፫ መስቀል አለው። የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ ፲፫ ጥልፍ አለው። በቀኝና በግራ እጅጌ ላይ በኋላ እና በፊት ሲቈጠር ፲፫ ነው ፲፫ቱ የሕማማተ መስቀሉ ምሳሌ ነው። ልብሱ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በተሰቀለ ጊዜ መከራው ብዙ ሲኾን በተለይ ግን ፲፫ቱ ሕማማተ መስቀል ይነገራሉና በዚያ ልክ ነው የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ መስቀሉ ፲፫ የኾነበት አምሳል ነው። ጠላፊዎቹም ራሱ ይህን ምስጢር የተረዱ ናቸው ማለት ነው። ለባሾቹ ደግሞ ይህን ሲያደርጉ ጌታችን በወንጌል ሲያስተምር በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲ ላይ “ዘኢጾረ መስቀለ ሞትየ ኢይፀመደኒ” “መስቀሌን ተሸክሞ ያልተከተለኝ እኔን ሊያገለግል አይገባም” ብሎ አስተምሯልና ጥልፍ ቀሚስ ለብሰው የሚከተሉትም የወንጌልና የመጽሐፍ ቅዱስ ፈጻሚዎች ናቸው ማለት ነው። እና ኹሉም በምስጢር የተያዘ ነው። በዓሉ በዚህ መልኩ ይከበራል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)*

የቀሚሱ ነጭ መሆን በጎንደር ጥምቀት ከቂም በቀል ነጻ መሆንን፣ ሥጋዊና መንፈሳዊ ንጽህናን የሚወክል ነው። ይህም በጥምቀት ዕለት የሚሳተፈው ማኅበረሰብ ከቂምና ከበቀል የጸዳ እንዲሆን ይፈለጋል። ነጭ ጥቁርን እንደሚጠላ ኹሉ፣ የጎንደር ጥምቀትም በቀልን ይጠላል። ይህም የጥምቀት ክብረ በዓልን ምክንያት በማድረግ ማኅበረሰቡ ከጥላቻና ከጠብ እንዲርቅ ያደርጋል። የጎንደር ቀሚስ ጥልፍ የመስቀል ቅርጽ መሆኑ ደግሞ የጥምቀት በዓል መነሻ የክርስትና ሃይማኖት መሆኑን የሚያዘክር ነው። የጥልፉ መስቀል ብዛት ዐሥራ ሦስት መሆኑ ደግሞ ጌታችን መድኀኒታችን እየሱስ ክርስቶስ በመልዕልተ መስቀል ላይ

ሰውን ለማዳን የተቀበላቸውን ዐሥራ ሦስት[68] ሕማማት መስቀል ያዘክራል፡፡ ጥልፉ ከላይ መነሻው አንድ ሁኖ ከታች መስቀሎቹ እየሰፉና ርስ በርሳቸው የመያያዛቸው ምክንያት ደግሞ የጎንደርን ማኅበረሰብ ትስስር የሚተረጉም ነው፡፡ የጥልፎቹ ርስ በርስ መያያዝና መጋመድ የመማኅበረሰቡን ዝምድና፣ የጋብቻ፣ የአበልጅ እና ወዳጅነት ማኅበረሳባዊ ትስስርን ይተረጉማሉ፡፡ አንድም የነገሥታቱን፣ የሊቃውንቱን፣ የልጃ ገረዶቹን፣ የወይዛዘዝርቱን፣ የምእመናቱን፣ የወለቃና የቤተ እስራኤሉን ትስስር እና ግንኙነት ያስረዳል፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ የጎንደርን ማኅበረሰባዊ ግንኙነት፣ ማኅበረሰባዊ ስብጥር እና ተግባቦት የሚያሳይ ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011፣ ልዕልና ጎይለ መስቀል 12/12/2011 እና በሪሁን አካላት 12/12/2011ቃ.መ)፡፡

ሌላው እናቶች በጎንደር ጥምቀት አምላካቸውን አካባቢቸውን እና የጥምቀትን ልዕልና የሚያዘክሩ ዘፈኖችን ያቀነቅናሉ፡፡ ስለት ከደረሰላቸውም በተሳሉት ልክ በሽብሻቦ እና በእልልታ ደስታቸውን ይገልጻሉ፡፡ በጎንደር ማኅበረሰብ ዘንድ በጥምቀት ዕለት በጠና ካልታመመ፣ ካለታሰረ ወይም ከዐቅም በላይ የሆነ ነገር ካላገጠመው በቀር በቸልተኝነት ከቤት መዋል እንደ ትልቅ ጥፋት ይቆጠራል፡፡ ይህን በተመለከተ ጥር 11 ቀን 2011 ዓ.ም የጥምቀት ዕለት ወ/ሮ የዝና ተሻሜ ቀጣዩን ቃል ግጥም ስታቀነቅነው[69] በመቅረጸ ድምጽ በማስቀረት ወደ ማስታወሻየ አስፍሬዋለሁ፡፡

*ከቤት ይውላል ሞኛ ሞኙ፣*<br>*ከቤት ይውላል ሞኛ ሞኙ፣*<br>*እናትና ልጁ ካንድ ላይ ሲገኙ፡፡*<br>*ከቤት ይውላል ሞኛ ሞኙ፣*<br>*ከቤት ይውላል ሞኛ ሞኙ፣*<br>*እናትና ልጁ ካንድ ላይ ሲገኙ፡፡*<br>*(የዝና ተሻሜ በ11/05/2011 ያቀነቀኑት)፡፡*

የዚህ ቃል ግጥም ይዘት በጥምቀት ዕለት የማይሳተፉትን የማኅበረሰብ አካላት በሞኝነት የሚፈርጅ ነው፡፡ ይህን ቃል ግጥም ለምን እንደመረጠችውና እንደዘፈነችው ቃለ መጠይቅ አድርጌለታለሁ፡፡ እሷም *"በጥምቀት ከቤት የሚውል ጤነኛ አይደለም፡፡ አስገዳጅ ነገር ገጥሞት ካቅሙ በላይ ካልኾነ በቀር ለጥምቀት ያልኾነ ቀሚስ ይበጣጠስ"* ነው በማለት አስረድታኛለች፡፡ አቀንቃኟ የዘፈነችውን ግጥም በሌላ የዘፈን አቀንቃኝም ሲደገም አዳምጫለሁ፡፡ "እናትና ልጁ

---

[68] የፋሲል ግምብም 13 በሮች አሉት ይህ የሚያሳየው ስለ ሕማማተ መስቀሉ በማኅበረሰቡ ዘንድ የነበረ እና የቆየ ዕውቀት መኖሩን አመላካች ነው፡፡
[69] የመረጃ ሰጭዎቸን የዕድሜ ደረጃ እና ማዕረግ ተከትዬ አንቱ እና አንተ፣ አንቺ ልል እችላለሁ፡፡

በአንድ ላይ ሲገኙ" የሚለው ቃል ግጥም አንድም በጥምቀቱ የሚገኘውን የሕዝብ ብዛት የሚገልጽ ነው። የጎንደር ጥምቀት በጎንደር አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች እኅትና ወንድም፣ እናትና አባት፣ አክስትና አጎት፣ አለቃና ምንዝር፣ ሊቅ እና ጨዋ በአጠቃላይ ነጭ ሰው[70] የሚገኝበት መሆኑን የሚያስረዳ ነው (ሙሉ በዜ 21/11/2011፣ የትዋለይ ሹሜ 21/11/2011 እና መ/ር ዳዊት ሥራው፣ 12/19/2011 ቃ.መ)። ሌላው የቃል ግጥሙ አንድምታ እናትነትን የሚተረጉም ነው። እናት ከልጇ ጋራ ከሆነች ልቦናዋ አይደነግጥም፤ ሐሳቧ አይበተንም። ኹሉ ነገር ሙሉ ይሆናል ማለት ነው።

ይህን ቃል ግጥም በተመለከተ መ/ር ዳዊት ሥራውን ጥያቄ አቅርቤላቸው እንደሚከተለው አብራርተውልኛል። *"የጥምቀት በዓል ነጻነትን የሚሰብክ ነው። ሃይማኖታዊ መነሻው ነጻነትን ማወጅ እስከኾነ ድረስ ሥጋዊና መንፈሳዊ ነጻነትን የሚመለከት ነው። በዚህ ቀን አሽከር፣ አለቃ፣ ምንዝር በአንድነት የሚያከብሩት ነው። በነጻነት ከአረጋውያን እስከ ሕፃናት አይቀርም"* (መ/ር ዳዊት ስራው 19/12/2011 ቃ.መ)።

"እናት ልጅ ባንድ ላይ ሲገኙ" የተባሉት አንድም ታቦታቱ ናቸው። በጥምቀተ ባሕሩ የወረዱት ታቦታት እመቤታችን ድንግል ማርያም እና ልጇ ኢየሱስ ክርስርቶስ በታቦት ማደሪያው የጥምቀት ዕለት በአንድ ላይ የመገኘታቸው ምሳሌ ነው። የግምጃ ቤት ማርያም እና የአደባባይ ኢየሱስ በአንድ ላይ የሚገናኙበት ጥምቀት የነጻነት፣ የሰላም፣ የድኅነት፣ የፍቅር፣ በአጠቃላይ ኹሉ ነገር ምሉዕ የኾነበት ዕለት መሆኑን ያዘክራል። በመኾኑም በዚህ ዕለት መገኘት አንድም መንፈሳዊ በረከትን የመቀበል፣ አንድም ሥጋዊ ትፍሥሕትን የማግኘት ዕለት ተደርጎ ይወሰዳል (ደስታ አሻግሬ 21/11/11፣ አወቀይ እንየው 21/11/2011 እና መ/ር ዳዊት ሥራው፣ 12/19/2011 ቃ.መ)።

### 5.7. የወጣት ወንዶች ክዋኔ እና አንድምታ በጎንደር ጥምቀት

ወጣቶች የጥምቀትን ክብረ በዓል በጭፈራ፣ በሆታ፣ በግና እና በመሳሰሉት የማክበሪያ ስልቶች በደመቀ ኹኔታ ያከብሩታል። የወጣቱ የጥምቀት አከባበር ከብዛቱ፣ ከኀይሉና ከሥርዐቱ አኳያ አንዳንድ ጊዜ ኀይል የተቀላቀለበት ወደ ጉልበት መፈተሻ እና ወደ መሳሰሉ ጉዳዮች የሚያመራበት ኹኔታ አለ። በዚህ ጊዜ ከአዛውንቱና ከወጣቱ የተመረጡ ለአገልግሎት የተሰለፉ ለታቦት ምንጣፍ የሚጥሉ፣ ቁጤማ የሚጎዝጉዙ እና ሰላሙን የሚያስከብሩ ወጣቶች የብዙኃኑን ወጣት ግፊያና የኀይል ሆታ እንዲበርድና ወግ ይዞ

[70] የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ለቁጥር የሚያዳግትን ህዝብ በዚህ መልኩ ይጠራዋል (መ/ር ዳዊት ሥራው 12/19/2011)

እንዲኼድ ያደርጋሉ (ስንታየሁ ሙጩ 12/05/13፣ ደረጀ ስመኝ 12/05/13፣ ዋለልኝ ደስታ፣ 20/05/2011 ቃ.መ)፡፡

በጥምቀቱ ዕለት የወጣቶች ሆታ ታቦት ሲነሣና ሲገባ የተለየ ድምቀት አለው፡፡ ታቦት ሲነሣ የሆታው መድመቅ ተምሳሌት የሰው ልጅ ከዲያብሎስ ዳኛ ከዐልጋ ቁራኛ ነጻ የኾነበትን እና የእግዚአብሔር ልጅነት ማግኘትን የሚተረጉም ነው፡፡ ሰው ወድቆ የመነሣቱ እና ታሞ የመዳኑ ተምሳሌት ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ሆታው ብቻ ሳይኾን የሊቃውንቱ ወረብም፣ የሰንበት ተማሪዎቹ ዝማሬም፣ የእነማሆይ እልልታም፣ የሕፃናቱ ውርውርታም ይደምቃል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 እና ዋለልኝ ደስታ፣ 20/05/2011 ቃ.መ)፡፡

ታቦቱ ሲገባ የሚታየው የጥምቀት ድምቀት እና ማሸብረቅ ደግሞ ቤተ ክርስቲያን የኢየሩሳሌም ሰማያዊት ተምሳሌት መሆኗን የሚያዘክር ነው፡፡ በተጨማሪ ታቦቱ ወደ መንበረ ክብሩ ሲገባ የሚኖረው የጥምቀት ድምቀት፣ የሮኬት ተኩስ፣ የሆታ እና የጭፈራ ድምቀት የሰው ልጅ በጥምቀት ወደ ዘላለማዊ ነጻነት የተሸጋገረበትን እና መንግሥተ ሰማያትን ተስፋ የማድረግ ምሳሌ ነው፡፡ ስለዚህ የጎንደር ጥምቀት በሥርዓትና በወግ የሚከወን በረከተ ሥጋ እና በረከተ ነፍስ የሚገኝበት እንደሆነ በማኅበረሰቡ ዘንድ ይታመናል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 እና ዋለልኝ ደስታ፣ 20/05/2011 ቃ.መ)፡፡

ሌላው ከባሕረ ጥምቀቱ ያደሩት ታቦታት ሲነሡ ጥምቀቱ የሚከብረው በባሕረ ዮርዳኖስ ተጥሎ የነበረውን ዕዳ ደብዳቤ "እንደ አምላክነቱ አቅልጦ እንደሰውነቱ ረግጦ" ያጠፋበትንና አዳምን ነጻ ያወጣበትን የሚያዘክር ነው፡፡ ጥምቀት የድል አድራጊነት፣ የአሸናፊነት፣ የደስታና የሐሤት ተምሳሌት ነው፡፡ ከዚህ መነሻነት የጎንደር ወጣቶች የጎንደርን ጥምቀት የሚያከብሩበት አግባብ የደመቀ ነው፡፡ በሆታው ላይ የሚሳተፉ ወጣቶች በላብ ተጠምቀው፣ አደግድገው እና ታጥቀው ራሳቸውን ለጥምቀት በረከት አሳልፈው ሲሰጡ ይስተዋላል፡፡ ይህን በተመለከተ ስለ ጎንደር ጥምቀትና ወጣቱ ክዋኔ አቶ ጌትነት አመራ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *በዓሉን በጣም ነው የሚያከብረው ወጣቱ ምንጣፉን በማንጠፍ ሆ በማለት፣ በሆታ፣ በጭፈራ፣ በጣም የተለየ በጎንደር ክፍለ ሀገር በስሜት በፍቅር ነው የጎንደርን ጥምቀት የሚያከብረው፡፡ ቀጣይም እንደዚህ ያለ የእናት የአባቶቻችን አለባበስ ባህል በመያዝ ይህንን ነገር በጣም እንደምናከብረው አዛውንቱን፣ ወጣቱን፣ ቀሳውስቱን በአንድ ላይ በመያዝ በአንደነት የምናከብረው ነው (ጌትነት አመራ 13/05/2011 ቃ.መ)፡፡*

ቃለ መጠይቁ እንደሚያስረዳው ወጣቱ የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን የጎንደርን ጥምቀት ያከብራሉ፡፡ ወጣቶቹ ለአምላካቸው ስለት ሲገቡም እንደየችሎታቸውና ፍላጎታቸው ነው፡፡

አንዳንዶቹ የዛሬ ዓመት አድርሰንና ምንጣፍኽን በማንጠፍ፣ ቀጤማኽን በመጎዝጎዝ፣ መንገድኽን በመጥረግ አገለግልኻለሁ በማለት ስለት ይሳላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ከዓመት ዓመት አድርሰንና እስክስታ በመውረድ፣ ዘፈን በመዝፈን፣ በሆታና በእልልታ ከብክበን እናስገባኻለን ይላሉ፡፡ ሁሉም ቢሆን እንደየራሳቸው የሠመረላቸውን ስለት ተከትለው ጥምቀትን ያከብራሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ወጣቶቹ ከጸጥታ ማስከበሩም ኾነ ከሆታ እና ጭፈራም አይለዩም፡፡

ይህን በተመለከተ ለአቶ ጌትነት አመራ የጥምቀት ዕለት ወጣቶች በሆታና በዳንኪራ የተለያዩ ዘፈኖችን በመዝፈን የጥምቀትን ክብረ በዓል እያከበሩ ተመልክቻለሁ፡፡ ይህ አከባበር በጎንደር ምን አንድምታ አለው? የሚል ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም ተከታዩን ማብራሪያ ሰጥተውኛል፡፡

> *ኧረ በስመ አብ የዚያን ቀን ጥሩ አስታወስከኝ እንዲያውም የገበሬ ልጅም ከቤት አይውልም፡፡ አባትየው ነው ከብት ሲጠብቅ የሚውል፡፡ ብትር፣ ብትሩን ይዞ ሆ ብሎ ነው ገጠሩ፣ ራሱ ገጠሩ ወደ ጥምቀቱ የሚኼደው፡፡ ከብቱን ራሱ አባቱ፣ አባቱ ነው ከብት የሚጠብቅ፣ እንዴት ብሎ ከቤት ይውላል ሌላው ነጉዶ ነው የሚሄደው፡፡ በዚያች ቀን ኺዶ ወጣቱ ጥምቀትን ካላየ እሽ አይልም፡፡ ጦርነት ነው የሚያነሣ፡፡ ከአባት ከእናቱ ጋራ እናት አባቱም እነሱ ደግሞ የኛን ይረከቡ እያሉ ያስኼዳሉ፣ ይፈቅዱላቸዋል (ጌትነት አመራ 13/05/2011 ቃ.መ)፡፡*

አቶ ጌትነት አመራ ጎንደር በሰሚው ቅዱስ ሚካኤል በሰበካ ጉባዔነት እያገለገሉ ያሉ ናቸው፡፡ ከኩተት እስከ ሽበት በጎንደር ከተማ መኖራቸው የጥምቀት በዓል በጎንደር ምን እንደሚመስል አሳምረው እንዲያውቁት ረድቷቸዋል፡፡ በመኾኑም የጥምቀት በዓል በጎንደር ልዩ መኾኑን አስረድተውኛል፡፡ በትዝታ ወደ ኋላ መለስ ብለው በማስታወስ የጎንደር ጥምቀት ከምድር በላይ ያለ ወጣት አፈር ካልተጫነው በቀር ወጣቱ ሳያከብር እንደማይውል ያላቸውን ግንዛቤ ነግረውኛል፡፡ የአቶ ጌትነት መረጃ እንደሚያስረዳው ወጣቱ በጥምቀት ቀን አዝመራ ጠብቅ፣ ነዶ ሰብስብ፣ ከብት አግድ አይባልም፡፡ ይህን የሚል ወላጅ ካለ እንኳን የሚፈረድ በወላጅ ነው፡፡

በተጨማሪም ለመ/ር ሰሎሞን ረዳ ስለ ወጣቱና የጎንደር ጥምቀት ግንኙነት ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ *"ወጣቱ በመስቀልና በጥምቀት ትንግርት፣ ትንግርት ነው ብታይ፡፡ ወጣቱ በጣም ነው ደስ የሚልኽ ታቦቱ ሲወጣ መንገዱን ይጠርጋል፤ ያዘጋጃል፡፡ አሁን ደግሞ ምንጣፍ ይጥላል፡፡ እየጣለ ደከመኝ፣ አመመኝ አይልም፡፡ ገና ታቦቱ*

*ሲወጣ በደስታ ደስታ ታቦት መቼ ነው የሚወጣ እያለ ከታራው ኹሳ ይጠይቀናል" (መ/ር ሰሎሞን ረዳ* 16/05/2011 *ቃ.መ*)፡፡

ወጣቶች በዚያን ቀን የሚማርካቸውና የሚስባቸው ነገር ብዙ ነው፡፡ በተለይ የተለያዩ አካባቢዎች የጭፈራ ስልቶች በጥምቀት ስለሚቀርቡ ወጣቶቹን ይመስጣቸዋል፡፡ የአቀንቃኞቹ ድምፅ፣ የልጃ ገረዶች ውበት፣ የታቦታቱ ግርማ ሞገስ፣ የሊቃውንቱ ያሬዳዊ ዜማ፣ የካህናቱ ዕፀ መስቀል፣ ጥላ፣ ጽና፣ መጎናጸፊያ እና ኅብረ ቀለማት ተጃምለው የወጣቱን ብሎም የማኅበረሰቡን ቀልብ ይስባሉ (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሀዲስ 15/11/11፣ ስንታየሁ ሙጬ እና ደረጀ ስመኝ 12/05/13 *ቃ.መ*)፡፡

በጥምቀት ክዋኔ ላይ የተመለከትኳቸውን የተለያዩ የአለባበስና የአጨፋፈር ስልቶች በተመለከተ በጥምቀቱ ክብረ በዓል ላይ የአጨፋፈርና የአለባበስ ልዩነት ይታያል፡፡ ወጣቶቹም በእነዚህ ጭፈራዎች በጣም ይሳተፋሉ፡፡ የዚህ ምክንያት ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ለአቶ ልዕልና ኀይለ መስቀል አቅርቤላቸው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *አዘፋፈኑን አጨፋፈሩን በሚመለከት ጎንደር የራሱ የኾነ ዜማ፣ ምት፣ ስልትና ዕውቀት አለው፡፡ የጎንደር አካባቢ የስልተ ምቱ አንድ ዐይነት ቢኾንም የአጨፋፈር ልዩነቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ የደንቢያ አለ፣ መኻል ጎንደር፣ ወገራ፣ ራሱን የቻለ ወደ ጥምቀት ሲመጡ የአካባቢያቸውን የጎንደርኛ አጨፋፈር ይዘው ይመጣሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ጎንደር በአጨፋፈር ስብጥር የኾነ ስልት አላት፡፡ የአጨፋፈር ስልቱ አንገር፣ አንጓ በአንጓ የሚሉት አለ፡፡ ዋንጫ ልቅለቃ የሚሉት አለ፡፡ ስለዚህ በጥምቀት ክብረ በዓል እነዚህ ኹሉ የጭፈራ ዐይነቶች ይታያሉ (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011)*

ከላይ የተሰጠው መረጃ እንደሚያስረዳው የጎንደር ጥምቀት ከተለያዩ አካባቢ የሚመጡ ተወላጆች የየራሳቸውን የአዘፋፈን ስልትና ምት ይዘው ይመጣሉ፡፡ እነዚህ የተለያዩ የአጨፋፈር ስልትን ተከትለው የሚከወኑ ጭፈራዎች ማራኪነት አላቸው፡፡ የደንቢያ ወጣት የመሃል ጎንደርን፣ የመሃል ጎንደር ደግሞ የደንቢያን የአዘፋፈን ስልትና ለዛ መመልከት ያስደስተዋል፡፡ የወገራውን ደግሞ የበለሳው፣ የጎንደርና የደንቢያው ወጣት ሰፍ ብሎ ይመለከተዋል፡፡ የበለሳ የጓህላና የአርባያ አካባበቢ ጭፈራዎች ከሰውነት ወደ ላይ የሚመነጠቅ የእስክስታ ዓይነት ነው፡፡ ይህን የአጨፋፈር ስልት ከሕፃናት ጀምሮ እስከ ዐዋቂ ድረስ ይወዱታል፡፡

የወጣቶቹ የዘፈን አወራረድ እንዳለ ሁኖ በጣም ልብ የሚሰርቅ ግን የእስክስታ አወራረዳቸው ነው፡፡ የዋንጫ ልቅለቃ የሚባለው የእስክስታ ዓይነት ከወገብ ያለው አወራረድ እና የእጅ

እንቅስቃሴ ከዋንጫ ልቅለቃ ጋራ የሚመሳሰል ነው፡፡ አንዳንድ በአንዳንድ ደግሞ በመካከሉ የተወሰኑ የሰከንድ ዐይነት ረፍቶችን በመውሰድ የሚደረግ የእስክስታ ዐይነት ነው፡፡ እነዚህ የእስክስታ ዐይነቶች በጎንደር ጥምቀት በወጣቱ የሚከወኑ እና በወጣቱ የሚወደዱ ናቸው፡፡ (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011፣ ስንታየሁ ሙጨ እና ደረጀ ስመኝ 12/05/13 ቃ.መ)፡፡

በጥምቀት የሚከወኑ እስክስታዎችን ሕፃናትና ልጆች ከጥምቀቱ ክብረ በዓል ተመልክተው በመኼድ ከጥምቀት በኋላ ይለማመዷቸውና በዓመቱ ችለው ይመለሳሉ፡፡ የጎንደር እስክስታ ተመልካቹን የመሳብና የመማረክ ኀይል አለው፡፡ በዚህ ምክንያት ከሃይማኖታዊ ዋጋው ባሻገር የክዋኔውን ውበት ለማየትና ለመመልከት የሚመጡት ብዙ ናቸው (ጌትነት አመራ 13/05/2011 ቃ.መ)፡፡

በዙብል፣ በምንትዋብ፣ በፒያሳ፣ በአውቶ ፓርኩ፣ በመንበረ መንግሥት መድኀኔዓለም፣ በአባጃሌ እና በእልፍኝ በ2011፣ በ2012 እና በ2013 ዓ.ም በጥምቀት ክብረ በዓል ዕለት ባደረግኩት ምልከታ እና በቃለ መጠይቅ ባረጋገጥኩት መሠረት የዳንኪራው ክዋኔ የፍክክር፣ የውድድርና የአሸናፊነት መንፈስ ይዞ ከየአካባቢው የሚመጣ በመኾኑ ትልቅ የኾነ ድምቀት አለው፡፡ ዳንኪራ መቺዎቹ ግና ብትር የያዙ ናቸው፡፡ ይህን ብትር ወደላይ በማውጣት ግጥሙ እስኪያልቅ ጎንበስ ቀና ሲሉ ይቆዩና ግጥሙ ሲያልቅ ወደ ላይ ወደ ላይ ይዘላሉ፡፡ ይህ ዝላይ ዐልፎ ዐልፎ በሩጫና በግፊያ መልክ ስለሚኾን ተመልካቾች የሚፈሩበት ኹኔታ አለ፡፡ በዚህ ምክንያት ልጆች በዛፍ፣ በዐጥር እና በግንብ ላይ ወጥተው ይመለከቱታል፡፡ ሕፃናት ደግሞ በእናታቸው ጫንቃ ወይም በአባታቸው ትክሻ ኹነው ዳንኪራውን ይከታተላሉ (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.ሙ)፡፡

እነዚህ የዳንኪራው ሥርዓት የራሱ ትርጉም አለው፡፡ መጀመሪያ ጎንበስ ቀና የሚሉት የአክብሮት ምሳሌ ነው፡፡ አምላካቸውን ከዚህ ዕለት ያደረሳቸውን ፈጣሪ ታቦታቱን እጅ የመንሣት ምሳሌ ነው፡፡ መጨረሻ ወደ ላይ ወደ ላይ የሚዘሉት ደግሞ ቀጣዩን ዓመት ተስፋ የማድርጋቸው፣ የእድገትና ከፍታ ተምሳሌት ነው፡፡ ክርሞ በማንኛውም መልኩ አሁን ካሉበት ጨምረውና አድገው፣ አብበው፣ አፍርተው እንዲመጡ የመልካም ምኞት መግለጫ ነው፡፡ የጥምቀት ክብረ በዓል ያላጨት አጭተው፣ ያልተዳሩት ተድረው፣ የተዳሩት ወልደው ለቀጣዩ ዓመት ያደርሳቸው ዘንድ ወደ አምላክ ምስጋናቸውን በማስታኮት[71] የሚያቀርቡበት

[71] ማሳረግ፣ ማሳሰብ ማለት ነው (ቄስ ባየው አበራ)፡፡

ዕለት ነው (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ እና በሪሁን አካላት 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡

በጥምቀት የሚያዘው ዱላ ሽልም ግና ይባላል፡፡ ይህ ሽልም ግና አመጣጡ አምላክ በቤተ ልሔም በተወለደ ጊዜ እረኞች ግና ተጫውተው ነበር፡፡ ይህ የግና ሥርዐትም ያንን ለማዘከር የቆመ ነው፡፡ አንድም ሽልም ግና ማኅበረሰባዊ እና የጥምቀትን ምስጢር ወክሎ የመጣ ነው፡፡ አንድም  የጎንደርን ማኅበረሰባዊ መልክ፣ ውበት እና ግብር ይወክላል፡፡ የሽልም ግናው ነጭ እና ጥቁር መሆን የጎንደር ማኅበረሰብ እና በጎንደር ጥምቀት የሚታደመው ሰው አንዱ ቀይ አንዱ ጠይም አንዱ ጥቁር መሆኑን ያዘክራል፡፡ የሽልም ግናው ውበት ደግሞ ኀራማይሌ መልክ ያለው ማኅበረሰብ ያለውን ማማር ያዘክራል፡፡ ሌላው በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን ሠናይ እና እኩይ ተግባራት ይወክላል፡፡ በዚህም ነጩ የሠናይ ተግባር ምሳሌ ሲኾን ጥቁሩ ደግሞ የእኩይ ተግባራት ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህ መልኩ የግናው ነጭና ጥቁር መኾኑ ነጩ ደስታን ጥቁሩ ደግሞ መከራን ይተረጉማል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/11 ቃ.መ፣ መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ እና ዳዊት ስራው፣ (12/19/2011 ቃ.መ)፡፡

አንድም ግና ጥምቀትን ወክሎ የመጣ ነው፡፡ የአዳም እዳ ደብዳቤ እና ዮርዳኖስ በጥምቀት እንደተገኙ ኹሉ ጥቁሩ እና ነጩ ቀለማትም በገናው ላይ ይገኛሉ፡፡ ጥቁሩ የዲያቢሎስ ዕዳ ደብዳቤ ሲኾን ነጩ የክርስቶስ ጥምቀት እና ግናው ደግሞ የዮርዳኖስ ተምሳሌት ነው፡፡ በግናው እንቁር እንደሚለጋ ሁሉ ክርስቶስ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ የአዳም እዳ ደብዳቤ ተሸሯል፡፡ በዚህ መልኩ ሽልም ግና ከጎንደር ማኅበረሰብ እና ከጥምቀት ክብረ በዓል ጋራ ተፈካካሪ ነው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ የግናው ዥጉርጉር መሆን ደስታና ሀዘን፣ ልደት እና ሞት፣ የሚፈራረቁበትን ማኅበረሰብ ዥጉርጉር ሕይወት የሚተረጉም ነው፡፡ (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/11 ቃ.መ፣ መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ እና ዳዊት ስራው፣ (12/19/2011 ቃ.መ)፡፡

### 5.7.1. የወጣቶች "አይብላሆ መኔ"[72] ክዋኔ ሥርዓት

[72] ሳብአለ ውሎ፣ አይ ሎጋ ሽቦ፣ ኧረ በሬው ና፣ ተው ግሽ የሚሉ የዚሁ ዐይነት ዜማ ምት ያላቸው የዳንኪራ ዐይነቶችም አሉ፡፡ የግሸን ነገር ብትሰማ ዝግራ ልጆቿን ሸጣ ገዛች ውጅግራ፣ የግሸን ነገር ብትሰማ ቆቅ ልጆቿን ይዛ አለች ድብቅ፣ የግሸን ነገር ብትሰማ ጦጣ ልጆቿን ይዛ ገባች ሽምጠጣ ወዘተ የሚሉ ቃል ግጥሞች ይከወናሉ (አቶ መርሻ ጌትነት 15/ 06/12 ቃ.መ እና መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ.)፡፡

ወጣት ወንዶቹ “አይብላሆ መኔ” እያሉ ከፍተኛ ሆታ ያካኺዳሉ፡፡ በዚህ ሆታ ላይ ስለ እርጅና ስለ አካባቢ እና ስለ ዐብሮነት ዕሳቤዎች ይገለጹበታል፡፡ ሆታው “አይብላሆ መኔ” የሚል መጠሪያ አለው፡፡ በሆታው ክዋኔ ላይ ግጥሙን የሚገጥመው እና ሆታውን የሚመራው “ሆታ አውጭ” ይባላል መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ)፡፡

በ11/05/ 2012 በምልከታዬ ያስተዋልኩት ሆታ አውጭ ደስታው ፈንታው ይባላል፡፡ ወጣቶቹ ከጭፈራቸው ብዛት እና ከፀሐይው ድምቀት የተነሣ በላብ ተዘፍቀዋል፡፡ የሆታው ክዋኔ የራሱ ሥርዐት አለው፡፡ መጀመሪያ ቀለል ባለ መልኩ ከላይ ወደታች ከወገብ ሸብረክ እየተባለ ዳንኪራው ይመታል፡፡ ከዚያ ሞቅ እያለ ወደ ቀኝ እና ወደ ግራ የሚደረግ ሲኾን በመጨረሻ በሞቀና በደመቀ መልክ በከፍተኛ ትንቅንቅ ወደላይ ወደ ላይ በመዝለል የሚከወን ነው፡፡ በአብዛኛው የሆታ አደረጃጀት አካባቢን፣ ዕድሜን፣ ጾታን እና ዝምድናን ማዕከል ያደረገ ነው፡፡ በዚህ አደረጃጀት ምክንያት ሆታ የአንዱ አካባቢ ሆተኛ[73] ከሌላው አካባቢ ሆተኛ ጋራ ፍክክር እና ውድድር ይካኼድበታል (አቶ መርሻ ጌትነት 15/ 06/12 ቃ.መ.፣ መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ. እና ደስታው ፈንታው 11/05/12 ቃ.መ.)፡፡

የሆታው ክዋኔ እና የክዋኔው ግጥም በአብዛኛው የመወለድ፣ የመኖርና የመሞት ዕጣ ፈንታዎችን የሚያዘክር ነው፡፡ በጎንደር ማኅበረሰብ ልጅ በተወለደ ጊዜ እልል ዘጠኝ እና እልል ዐሥር ተብሎ በደስታ የመቀበል ነባር ልማድ አለ፡፡ በዚህ መልኩ ከላይ ወደታች ቀለል ባለ መልኩ የሚደረገው የሆታ ክዋኔ ካለ መኖር ወደ መኖር የተገኘበትን የሰው ልደት የሚያዘክር ነው፡፡ ይህ ኺደት የደስታ በመሆኑ ቀለል ያለና የለዘበ ክዋኔ ነው (አቶ መርሻ ጌትነት 15/ 06/12 ቃ.መ፣ መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ. እና ደስታው ፈንታው 11/05/12 ቃ.መ.)፡፡

ኹለተኛው የሆታ ክፍል ደግሞ ጠንከር ባለ መልኩ ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደ ቀኝ የሚደረግ የሆታ ዐይነት ነው፡፡ ይህ ሆታ በጎንደር ማኅበረሰብ ውስጥ ሰዎች ለዐቅመ አዳም እና ለዐቅመ ሔዋን ከደረሱ በኋላ ያሉባቸውን ኃላፊነቶች፣ እንቅስቃሴዎች እና ሕይወትን ለመምራት የሚደረገውን ኺደት ይተረጉማል፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ ከግራ ወደ ቀኝ የሚደረገው እንቅስቃሴ የሰዎችን ስኬት የሚተረጉም ነው፡፡ ሰዎች በኑሮአቸው ውስጥ ኹል ጊዜ በስኬት ጎዳና አያልፉም፡፡ ለዚህም ከቀኝ ወደ ግራ የሚደረገው እንቅስቃሴ የሰዎችን በችግር ማለፍ የሚተረጉም ነው፡፡ በመኾኑም ከቀኝ ወደ ግራ እና ከግራ ወደ ቀኝ

[73] በሆታው የሚሳተፉት ቡድኖች መጠሪያ

የሚደረገው የሆታ ሥርዐት የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ በደስታና በሐዘን የተገመደ ሕይወትን የሚመራ፣ በሠናይ እና እኩይ ተግባር የሚያልፍ መሆኑን ያዘክራል (መ/ር ፈቃድ ቀለመ ወርቅ 15/06/12 ቃ.መ)፡፡

ሌላው እና የጉልበት ሚቃ ያለው የሆታ ክዋኔ ወደላይ፣ ወደ ላይ የሚደረገው ሆታ ነው፡፡ ይህ ትንቅንቅ ሰዎች በዚህ ዓለም ሲንገላቱም ሲደሰቱም የግራ እና ቀኝም መንገድ ሲጓዙ ኖረው ከዚህ ዓለም በሞት የሚለዩበትን ኺደት ይተረጉማል፡፡ ወደላይ መዝለሉ ደግሞ ነፍስ ወደ ሰማይ ትኼዳለች ተብሎ ስለሚታሰብ የዚያ ምሳሌ ነው፡፡ ኀይልና ሚቃ መኖሩ የአካባቢው ማኅበረሰብ ሞትን የሚረዳበት መንገድ "ይብላኝ፣ ክፉ ሥራ" በሚል ስለኾነ የሐዘን መግለጫ ነው (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ.፣መ/ር ዳዊት ስራው፣ 06/06/2011 ቃ.መ እና መ/ር ፍቃድ ቀለመወርቅ 15/06/12 ቃ.መ)፡፡

ሌላው የሆታው ሥርዐት መ/ር ዳዊት እንዳስረዱኝ ከማኅበራዊ አንድምታው በተጨማሪ ሃይማኖታዊ አንድምታም አለው፡፡ ከላይ ወደ ታች የሚደረገው ሥርዐት በመጀመሪያ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም የመወለዱ ምሳሌ ነው፡፡ ከግራ ወደቀኝ እና ከቀኝ ወደ ግራ የሚደረገው ሆታ ደግሞ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በተሰቀለ ጊዜ ከጲላጦስ ወደ ሔሮድስ፣ ከሔሮድስ ወደ ፒላጦስ የተመላለሰውን እና አይሁድ የአንገላቱትን ተምሳሌት ያዘክራል፡፡ እንደዚሁም የመጨረሻው ወደ ላይ ወደ ላይ መዝለሉ የክርስቶስን ዕርገት እና በመጨረሻ ወደ ታች መውረዱ ዳግመኛ ለፍርድ እንደሚመጣ የሚተረጉም ነው (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ. እና መ/ር ዳዊት ሥራው፣ 06/06/2011 ቃ.መ.)፡፡

በመኾኑም የሆታው ሥርዐት ማኅበረሰባዊ፣ ሰዋዊ እና ሃይማኖታዊ አንድምታዎችን የያዘ ነው፡፡ የጎንደርን የጥምቀት ሆታ በተመለከተ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ *"ማኅበረሰቡ ደስ እያለው በጥምቀት በዓል ወጣቶቹ ወንዶቹ ጥንታውያን አለባበስ በመልበስ ዐብረው በአንድ ላይ ሆ በማለት ከሊቃውንቱ በኋላ ሥርዓት ባለው መልኩ የሰንበት ትምህርት ቤት ዘማርያን እየዘመሩ፣ ከእነሱ በኋላ ሁነው ደግሞ ወጣቶቹ ሆ እያሉ ለጥምቀት በዓል የሚገባውን ሆታ ያደርሳሉ" (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ.)፡፡* ሆታው በአብዛኛው የጉልበት ዐቅም ባለቸው ወጣት ወንዶች የሚከወን ነው፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ የጥምቀትን ሆታ፣ የዐውድማን ትግል እና የሰርግን ንጥቂያ እንደ ጥንካሬ መፈተሻ አድርጎ

ይወስደዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የጥምቀት ሆታ የጎንደርን ማኅበረሰብ የልደት፣ የጋብቻ፣ ሞት የደስታ፣ የሐዘን፣ የኀይል፣ የጀግንነት እና መሰል ማኅበረሰባዊ ሕይወትን የሚተረጉም ነው፡፡

### 5.7.2. በወጣቶች የሚቀነቀኑ የሆታ ቃል ግጥሞች ክዋኔና አንድምታ

የጎንደር ጥምቀት የሆታ እንቅስቃሴ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ማንነት እንደሚያሳይ ኹሉ በሆታው ላይ የሚቀነቀኑት ቃል ግጥሞችም አካባቢያዊ አንድምታ አላቸው፡፡ በዚሁ ሆታ ላይ ደስታው ፈንታው የተባለ ወጣት ተከታዩን ግጥም እያወረደ ሆታውን ሲመራው በምልከታዬ አስተውያለሁ፡፡ ደስታው ፈንታው በየ ዓመቱ የጥምቀት በዓል ላይ ሆታ ያወርዳል፡፡ ከደስታው ፈንታው ጋራ በ2011 ዓ.ም በተጨማሪ በ2013 ተገናኝተናል፡፡ በ2013 ዓ.ም. የፎቶ ማናሣት ተግባረ አካሂጃለሁ፡፡ ከታች የተጠቀሱትን ቃል ግጥሞች በክብረ በዓሉ በየዓመቱ እየተደጋገሙ የሚከወኑ መኾናቸውን ባደረግኩት የሦስት ዓመት ተከታታይ ምልከታ አረጋግጫለሁ፡፡

*አይብላሆ አይብላሆመኔ (ከዋኝ)*
*አይብላሆመኔ (ተቀባይ)*
*አይብላሆ እስኪ ልነሳና (ከዋኝ)*
*አይብላሆመኔ(ተቀባይ)*
*አይብላሆ ልበል ወለሽ ወለሽ (ከዋኝ)*
*አይብላሆመኔ (ተቀባይ)*
*አይብላሆ እርጅና መጣ አሉ (ከዋኝ)*
*አይብላሆ መኔ (ተቀባይ)*
*አይብላሆ ያውቃቢ የለሽ (ከዋኝ)*



*(ወጣቶች በአይብላሆመኔ ሆታ ላይ 2013)*

ከግጥሙ መልእክት በፊት "አይብላህ ወመኔ" የሚለው አዝማች ራሱን የቻለ መልእክት አለው። የዚህ መልእክት አይብላህ ወመኔ በዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ መበላትን፣ መጋለጥን፣ መውደቅን፣ መሸነፍን የሚተረጉም ነው። ለምሳሌ "እኂው በላኝ፣ ስለት በላኝ፣ ውሐ የበላው ጨው"ወዘተ የሚሉትን ፈሊጣዊ ንግግሮች ብንውስድ ውሐ በላኝ በውሐ መጥለቅለቅን እና ለአደጋ መጋለጥን፣ ሌባ በላኝ በሌባ መበርበርን፣ ውሐ የበላው ጨው ደግሞ ከንቱነትን የሚተረጉሙ ናቸው። ከዚህ በመነሣት "አይብላህ ወመኔ" የሚለው ቃል ለቀማኛ፣ ለሽፍታ፣ ለወመኔ እና ለማትገዳደረው ባላንጣ አሳልፎ አይስጥህ የሚለውን ይተረጉማል። ከግጥሙ በፊት "አይብላህ ወመኔ" የሚለው ቃል መምጣቱ ለፈጣሪ የሚደረገውን ልመና ይመለከታል። ወመኔ ታግሎ የሚጥል እና ሞግቶ የሚረታ የሚሉትን ቃሎች ይተረጉማል። በዚህም ማኅበረሰቡ ወመኔን ከሌባና ከቀማኛ ባለፈ ለሞትና ለእርጅና ምሳሌ አድርጎ ይወሰደዋል (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ. እና ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/12 ቃ.መ.)።

እርጅናና ሞትን ታግሎ የጣላቸው፣ ሞግቶ የረታቸው የለም። እርጅና እና ሞት አመክንዮ አይቀበሉም። ሌላው "አይብላህ ወመኔ" የብይን ምሳሌ ነው። የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ከነገሥታቱ ጀምሮ ለብዙ ዘመናት በፍርድ ኺደት ውስጥ ያለፈ ማኅበረሰብ ነው። የፍርድ ሥርዐቱ ከሚጣመምበትና ከሚወላገድበት የወለደውን ቢያጣ ይሻለዋል። ለፍትህ ያለው ዕሳቤ ከፍተኛ በመኾኑ "የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ" እና "በፍርድ ከኼደች በቅሎዬ ያለ ፍርድ የኼደችው ዶሮየ ቆረቆረችኝ" እያለ የፍርድ ሚዛናዊነትን ለማስጠበቅ ጥረት ያደርጋል። ለዚህም ያለ ፍርድ የሚደረግን ብይን ይቃወማል (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ.፣ ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/12 ቃ.መ. እና መ/ር ፈቃድ ቀለመወርቅ 15/06/12 ቃ.መ.)።

በተፈጥሮ ሕግ እንጂ በምክንያት የማይመራውን እርጅና እና ሞት "ወመኔ" ይለዋል። ስለዚህ አይብላኽ ወመኔ እንደ አዝማች ኾኖ የአይብላኽ ወመኔው እና የዳንኪራው ማስኬጃ በመኾን ተደጋግሞ ይነሣል። በየ አይብላህ ወመኔው መካከል "እንጃ እና እምቢ" የሚሉ ቃላት ይደጋገማሉ። እነዚህ "እምቢ እና እንጃ" የሚባሉት ቃላት የጎንደርን ማኅበረሰብ ለመግለጽ የቆሙ ናቸው። የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ ባላንጣውን በዋዛ አያየውም፤ በጥቁር ደም ከተቃባ መብረጃው ሩቅ ነው። አትንኩኝ ባይነቱን ለመግልጽ "እንጃ" የሚለውን ቃል በየ አዝማቹ ደጋግሞ ይጠቀማል (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/12 ቃ.መ.፣ መ/ር ፍቃድ ቀለመወርቅ 15/06/12 ቃ.መ.)።

"እንጃ" የሚለው ቃል እንደዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ እና እንደ አይብላሆመኔ ዐውድ አሻፈረኝን፣ አለ መቀበልን፣ አለ መንበርከክን፣ አለ መፍራትን፣ አትንኩኝ ባይነትን እና እጅ አለ መስጠትን ይተረጉማል። የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ ከባላንጣ በተጨማሪ እርጅናን የሚሞግቱ የሚተቹ እና የሚያወግዙ ቃል ግጥሞችን ጭምር በጥምቀት ክብረ በዓል እንደሚከተለው ያቀነቅናል።

*እስኪ ልነሣና ልበል ወለሽ ወለሽ*
*እርጅና መጣ አሉ ያውቃቢ የለሽ*
*(ደስታው ፈንታው 11፣ 05/ 2011 ዓ.ም ሆ ያለው)።*

የዚህ ግጥም ዋና መልእክት እርጅናን መቃወም ነው። እርጅና አባሮ መያዝን፣ ተይዞ መንጠቅን፣ ታግሎ መጣልን የሚገታ በአንጻሩ እጅ መስጠትን፣ መንበርከክን፣ ወደ ኋላ በትዝታ መናወዝን የሚያስከትል ነው። የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ "ማርጀት" የሚለውን ዕሳቤ ከሞት በላይ ይመለከተዋል። የዓለሙትን እና የአሰቡት ለማድረግ ተቀምጦ መነሣትን፣ ተነሥቶ መቀመጥን የሚከለክል፣ በሕይወት እያሉ ዐይንን የሚያደራ፣ ጀሮን የሚደፍን፣ ጉልበትን የሚያርድ ባላንጣ ነው። በዚህ ምክንያት ማኅበረሰቡ እርጅናን አጥብቆ ይጠላዋል። ለዚህ ማጠየቂያ ይሆን ዘንድ "እንኳን መሞት ማርጀት አለ" የሚል ብሂል እያነሣ እርጅና[74] ከሞት የከፋ ዕጣ ፈንታ እንደሆነ ያረጋግጣል (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/13 ቃ.መ.፣ ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/12 ቃ.መ. እና መ/ር ፈቃድ ቀለመ ወርቅ 15/06/12 ቃ.መ.)።

በዚህ ጉዳይ ደስታው ፈንታውን እርጅናን እንዴት ታየዋለህ የሚል ጥያቄ አንስቸለት ነበር። እሱም *"እርጅናን ከሞት በላይ እፈራዋለሁ። የአገሬ ሰው "እንኳን መሞት ማርጀት አለ" ብሎ የል"* (ደስታው ፈንታው 11፣05/2011 ቃ.መ) የሚል ዐጭር መልስ ሰጥቶኛል። በመኾኑም የሆታው ቃል ግጥም የጎንደር ማኅበረሰብ ፍልስፍና መገለጫ ነው። ይህንኑ የእርጅና እና የሞት ዕሳቤን የሚገልጽ ቃል ግጥም እንደሚከተለው ቀርቧል።

*አይብላሆ፣ አይብላሆ ወመኔ፣*
*እንጃ፣*
*አይብላሆ ወመኔ።*
*አይብላሆ ኸረ ኅበዝ፣ ኅበዝ፣*
*እንቢ፣*
*አይብላሆ ወመኔ።*

---

[74]እርጅና እንደየ አውዱ እና ከአካላዊ ጥንካሬ ጋራ ያለውን እንጂ ከመንፋሳዊነት፣ ከዕድሜ ባለጸግነት፣ ከጽድቅ መሻት እና ከመመረቅ ጋራ ከሆነ ደግሞ አነደ ፈጣሪ ምርቃት ተደርጎ ወሰዳል። ይህም በጥናቱ ከመቅሰፍት ጋራ ተያያዞ ትንታኔ ተሰጥቶበታል።

*አይባላሆ ኀበዝ ይብላኝልህ፣*
*እንጃ፣*
*አይብላሆ ወመኔ፡፡*
*አይብላሆ እርጅናውም መጣ፣*
*እንቢ፤*
*አይብላሆ ወመኔ፡፡*
*እንጃ፤*
*አይብላሆ ወመኔ፡፡*
*አይብላሆ ሞቱም አይቀርልህ፣*
*እንቢ፣*
*አይብላሆ ወመኔ፡፡*
*(ደስታው ፈንታው 11፣05/2011 ዓ.ም ሆ ያላው)፡፡*

ከላይ የተጠቀሰው የጥምቀት ሆታ ማኅበረሰቡ ተፈጥሮን የሚሞግትበት እና የሚተችበት መሣሪያው ነው፡፡ "ይብላኝልህ" የሚለው ቃል ሰው አምሮና ተውቦ፣ ተፈጥሮና ኑሮ ለእርጅና መጋለጡን ዐለፍ ሲልም ለሞት የተገባ መኾኑን በመሞገት ስሜቱን የሚገልጽበት ቃል ግጥም ነው፡፡ የቃል ግጥሙ ጭብጥ ወጣቱ በወጣትነት እና በእሳትነት ጊዜው አላግባብ የሆነ ጮቤ እንዳይረግጥ ከፊቱ ያሉት የእርጅና እና የሞት ዕጣ ፈንታዎች ይነገሩታል፡፡ እነዚህ የሆታ ግጥሞች የበረታው የኮሰሰውን፣ ሀብታሙ ድሀውን፣ መሪው ተመሪውን፣ ባለ ጊዜ ጊዜ የጣለውን "ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል" እንዳይኾን ሚዛን የሚያደላድሉ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ትውልዱ እርጅናን እና ሞትን ዕያሰበ በተራመደ ቁጥር ለማኅበሩ ዕሴት፣ ደንብ፣ ሕገጋትና ሃይማኖት ተገዥ ይኾናል፡፡ ተገዥ በሆነ ቁጥር ደግሞ የተረጋጋ ማኅበረሰብ ይፈጥራል፡፡ ለዚህም ከላይ የተወሰደው ቃል ግጥም በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል እየተከወነ ወጣቱን ያስተምራል፡፡ እነዚህ የእርጅና እና የሞት ይዘት ያላቸው ቃል ግጥሞች ለወጣቱ አንድም መምከሪያ አንድም ማስፈራሪያ በመሆን የማኅበረሰቡን የኀይል ሚዛን ይገራሉ፡፡

በዚህ የሆታ ግጥም በዋናነት እንቢ እና እንጃ የሚሉት ቃላት ተደጋግመው በአዝማጅ የተጠቀሱ ናቸው፡፡ እነዚህ ኹለት ቃላት ያላቸው ማኅበራዊ አንድምታ ምን እንደሆነ ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌን ጠይቄአቸው ነበር፡፡ እሳቸውም ተከታዩን ዐጭር መልስ ሰጥተውኛል፡፡ "ይህ ፎከታም ሲመጣ ይምጣ እንጂ፣ አሜን ብሎ ማን ይቀበለዋል እርጅናንም ሞትንም" (ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ፣ 03/06/ 2012 ቃ.መ) በማለት በሰውኛ ዘይቤ ሞትን እና እርጅናን ጎንትለውታል፡፡

ከዚህ ላይ ኹለት አንኳር ጉዳይ ማንሣት ተገቢ ነው፡፡ እነሱም አንድም ጥንካሬ አንድም ሙግት ናቸው፡፡ በማኅበረሰባዊ ጎራ ውስጥ ማሸነፍና መሸነፍ የነበረ፣ ያለ እና የሚኖር ሐቅ ነው፡፡ ቢኾንም "ታሞ እንጅ ፈርቶ የሞተ የለም" እንደተባለው "እንቢ" እና "እንጃ" የሚሉት ቃላት ለማኅበራዊ ጥንካሬው ማስኬጃ፣ ለተፈጥሮ ዕጣ ፈንታው መሞገቻ አድርጎ ይጠቀማቸዋል፡፡ በሌላ መልኩ በጥምቀት ሆታ ተደጋግመው የተነሡት "እንቢ እና እንጃ" የሚሉት ቃላት በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ ከአካባቢያዊ ደም መመላለስ እና ቂም በቀል ወጥቶ ሰፋ ባለ መልኩ ሃይማኖት ከሚያስቀይር፣ ባህል ከሚያጠፋ፣ ስመ ክርስትና ሀብተ ውልድና ከሚያጎድል ባላንጣ እና የውጭ ወራሪ ኀይል[75] እንቢ የማለቱ ተምሳሌቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ይህን በተመለከተ ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ቀጣዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ "*ያን ጊዜ "እንቢ እና እንጃ" ባንል ኑሮ ድርቡሾች ዐፄ ዮሐንስን መተማ ላይ ጥለው ጎንደርን ሲያቃጥሉ እጅ እንሰጥ ነበር፡፡ እንቢ በማለታችን ግን ለጊዜው ቢጎዱንም አሸንፈን #4ቱን የአባቶቻችን አድባራት አስጠብቀን እንኖራለን፡፡ የመጣውን ኹሉ ሲያሸንፍ ያሸንፍ እንጂ ተደቁሶ እጅ መስጠት ተገቢ አይደለም" (ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ፣ 03/06/ 2012 ቃ.መ)*፡፡ ስለኾነም በግጥሙ ውስጥ ያሉት እንቢ እና እንጃ የሚሉት ቃላት የማኅበረሰባዊ ትስስሩ ማጠንከሪያ ጉልበት ናቸው፡፡ ይህ ወኔው ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ ጠንካራ ማኅበረሰባዊ ግንባታው እንዲቀጥል ተደጋግሞ በሚመጣው የጥምቀት ክብረ በዓል ላይ በሆታ ላይ እየተከወነ ይተላለፋል፡፡

በሌላ መልኩ በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የሚከወኑት የወጣቶች የሆታ ግጥሞች ጓደኛ ተኮር ናቸው፡፡ በጥምቀቱ ክብረ በዓል ያልተገኘ ጓደኛቸው ለወጣቶቹ ምን ያክል እንደሚያሳስባቸውና እንደሚናፍቃቸው ያስታውሱበታል፡፡ ደስታው ፈንታው ያቀነቀነው ተከታዩ ቃል ግጥም ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

*አጣማጄን ሲያጣ እንቧ ይላል በሬ፣*
*ያምስጋን ገደፋው የት ኺዶ ነው ዛሬ፡፡*
*(ደስታው ፈንታው 11/05/2011 ዓ.ም ሆ ያለው)*

ለደስታው ፈንታው ይህን ሆታ ያወጣኸው[76] እና በሆታው ላይ የጠቀስከው ሰው ምንድን ነው? ብዬ ከሆታው በኋላ ላቀረብኩለት ጥያቄ ተከታዩን መልስ ሰጥቶኛል፡፡ "*በጥምቀት ቀን*

[75] ግብጾች እና ድርቡሾች በጎንደር አካባቢ ያደረጉትን ጦርነት ለማዘከር የቀረበ ነው፡፡ እንደዚሁም በሃይማኖት ዙሪያ በጎንደር አካባቢ በ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ከጻጋዎች እና ከሚሲዮናዉያን ጋራ የነበረውን ሙግት፣ ትችት እና ክርክር ለመግለጽ የቆመ ነው፡፡ (ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/12 *ቃ.መ*)፡፡

[76] ከዋኙ በአካባቢው ማኅበረሰብ ከዋኝ ሳይኾን "ሆታ አውጭ" ተብሎ ይታወቃል፡፡

*የምትወደው ጓደኛኽ ከተለየኽ በጣም ነው የሚከፋኽ። ጥምቀት እኮ በዓመት የሚመጣና ስለት ከርሞ አድረስን ብለን የምናቀርብበት ነው። ይህ ጓዳኛችን ባለፈው ሠኔ ወጥቶ በመተማ አድርጎ ወደ ሱዳን ኼዶ አልተመለሰም። በጣም ነበር የሚያደምቀው" (ደስታው ፈንታው 11/05/2011 ቃ.መ.)።*

የቃል የግጥሙ አንድምታ ሰው ያለ ጓደኛ ባዶ መሆኑን በማዘከር የሰዎችን መዋደድ የሚዘክር ነው። ለዚህ ማንጸሪያ ይሆን ዘንድ በበሬው መግባቢያ መሠረት መጥራት ይሁን መናፈቅን በሚገልጽ መልኩ "እንቧ" ብሎ ይጮኻል። እንኳ ሰው እንስሳው በደመ ነፍሱ አጣማጁን ይፈልጋል እያለ የጓደኝነትን አስፈላጊነት ይገልጻል። ለሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ አጣማጅ ምንድን ነው? የሚል ጥያቄ አንስቼላቸው ነበር። እሳቸውም ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *አጣማጅ ማለት በሬና ገበሬን ዕይ በሬዎቹ ኹለት ናቸው። የግራና የቀኝ በሬ እነዚህ ኹለቱ አንደኛው ወደኋላ፣ አንደኛው ወደፊት አንደኛው ወደ ቀኝ አንደኛው ወደ ግራ ካሉ ዕርሻው አይታረስም። ከንቱ ድካምና ልፋት ነው። ለዚህ በሬዎቹ በዐቅምም፣ በሙያም ተመሳሳይ መኾን አለባቸው። በዚህ ጊዜ ገበሬው ከበሬው ተስማምቶ ባሕር የመሰለ አዝመራ ያበቅላል። ይህ አጣማጅ በኛ በጎንደሬዎች ሰውም አጣማጅ አለው በጦርሜዳ፣ በጎራ፣ አገር ስትቸገር አጣማጁን ይዞ ነው ጎራውን የሚያስከብር። ወደፊትና ወደኋላ ካለ መማረኩ ነው። የጥይት ድምፅ ሲሰማ ጭንቅ ሲኾን ጥሎ የማይሸሽ ማለት ነው አጣማጅ።*
>
> *አልቢን ምንሽሩ ሲውል ከሰው ገላ፣*
> *ቀዩ ሰው ሲጠቁር ጥቁሩ ሰው ሲቀላ*
> *ልብ አይታመንም እንኳን ባልንጀራ*
> *እንኳን ባልንጀራ ጥሎ የሚሸሸው*
>
> *ልብ አይታመንም ዐብሮ እሚበላሸው ይባላል ወንድም። አጣማጅ ማለት አብሮ የሚሞት በማለት ነው (ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/2012 ቃ.መ)።*

መረጃው እንደሚያስረዳው በጥምቀት ላይ አይብላሆ መኔ የሚገጠሙ ግጥሞች የአካባቢው ማኅበረሰብ ማንነት መገለጫዎች ናቸው። በሌላ የሆታ ክዋኔ ላይ ደግሞ እንደዚሁ ፈሪ እና ሰነፍን፣ ወስላታ እና ቦዘኔን የሚያወግዙ ግጥሞች ሲከወኑ ሰምቻለሁ። ከእነዚህ ግጥሞች መካካል ደነቀው ማሩ ተከታዩን ቃል ግጥም አቀንቅኗል።

> *ይወለድና አንዳንድ አምበልጋ*
> *ሲያፈርስ ይውላል የእመጫት ዐልጋ*
> *(ደነቀው ማሩ 11/05/2012 ሆ ያለው)*

ይህን የሆታ ግጥም የአካባቢው ማኅበረሰብ ሰነፍ ሰውን የሚጠላ መሆኑን የሚተረጉም ነው። አንድም ሲያፈርስ ይውላል የእመጫት ዐልጋ የሚለው ስንፍናን የሚገልጥ ነው። ወንድ ልጅ ሠርቶ፣ ዐርሶና ዐፍሶ፣ ነግዶና አትርፎ፣ ቤቱን መምራት አለበት። ቃል ግጥሙ ሲያፈርስ ይውላል የእመጫት ዐልጋ የተባለው በቁሙ "ዐልጋ ማፍረስን" የሚገልጽ አይደለም። ከዚህ ይልቅ ከቤት መዋልን፣ ሥራ አለመስራትን፣ ቦዘኔነትን እና ሥራ

ፈትነትን የሚተረጉም ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አንድ አባውራ ከቤት እየዋለ ከዐራስ እናቶች ጋራ ያለችውን ልም እህል እሚመገብ ከኾነ የተወለደው ሕፃን የሚያድግበት አያገኝም (ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/12 ቃ.መ)፣ መ/ር ፈቃድ ቀለመ ወርቅ 15/06/12 ቃ.መ፡፡

የጎንደር ማኅበረሰብ በብዙ ማኅበራዊ መዋቅሮች እና ሥራቶች የተገነባ ነው፡፡ ከማኅበራዊ መዋቅሮቹ ውስጥ ትልልቅ የሆነ የኹለትና የአራት ቀን የዐዳር ማኅበር፣ የክርስትና፣ የዓመት በዓል እና የሰርግ የመሳሰሉ ትልልቅ ድግሶች አሉበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእግዜር እንግዳ የመቀበል ልማድ አለው፡፡ በዚህ ማኅበራዊ መዋቅሩ ውስጥ ጠላ ጠምቆ፣ እንጀራ ጋግሮና ሙክት አርዶ የሚያስተናግድባቸው ጊዜያቶች ብዙ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ሰፋፊ ድግሶችና ለእንግዳ መቀበያ የሚውል በርከት ያለ ጥሪት ያስፈልገዋል፡፡ የገጠሩ ማኅበረሰብ ዋናው የገቢ ምንጭ የተመሠረተው ግብርና ላይ ነው፡፡ የከተማው አካባቢ ማኅበረሰብ ደግሞ በንግድ ተግባር ኑሮውን ይገፋል፡፡ እነዚህ ኹለቱ ሥራዎች ከቤት በመዋል የሚሠሩ አይደሉም፡፡ በመኾኑም ከላይ የተቀነቀነው ቃል ግጥም ስንፍናን የሚያወግዝ እና ሥራን የሚያበረታታ ነው (ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/12 ቃ.መ)፣ መ/ር ፈቃድ ቀለመ ወርቅ 15/06/12 ቃ.መ፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ በጎንደር ጥምቀት ሆታ ላይ የሚከወኑት ቃል ግጥሞች የሰውን ልጆች ዕጣ ፈንታ እና ሕይወት የሚያስረዱ ናቸው፡፡ ማኅበረሰቡ እኩይ ብሎ የፈረጃቸውን እንደ ጥቃት፣ ስንፍና፣ ጥላቻ፣ ዝሙት፣ ስርቆት እና የፍርድን መንሸኳረር የሚያወግዙ ናቸው፡፡ በአንጻሩ ሠናይ ተግባራት የሚላቸውን ተግቶ መሥራትን፣ ሀገር መጠበቅን፣ ጀግንነትን፣ ዐብሮነትን እና ማኅበረሰባዊ መዋቅሮችን የሚያለመልሙ ናቸው፡፡

እንዲኹም የወጣት ወንዶች ክዋኔ የአባዊ ሥርዓቱን የሚወክል ነው፡፡ የሆታው ገፊያ እና ልጊያ የአባዊ ሥርዓቱን የኀይለኝነት እና የበላይነት ምኞት ይተሩማል፡፡ የሎሚ ውርወራው እና የልጃ ገረዶች ጉንተላው ደግሞ የተቃራኒ ጾታ ምኞቱን የሚያዘክር ነው፡፡ ከዚህ ላይ አባዊ ሥርዓቱ እና እማዊ ሥርዓቱ ለምን በወጣት ወንዶች እና ሴቶች ክዋኔ ተወከለ የሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም፡፡ ይኹን እንጅ ሕፃናት እና ልጆችን “ለመብል ያልታገሱ፣ ለሥራ ልደረሱ” የሚለው ብሂል ይጸናባቸዋል፡፡ አረጋውያንን ደግሞ “ልጣቸው የተራሰ፣ መቃብራቸው የተማሰ” የሚለው ንግር ከሃላፊነት ያስወጣቸዋል፡፡ በመኾኑም ሥርዓቶቹ በወጣቶቹ መወከላቸው ተገቢ ይኾናል፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ አንድም ሐልዮ፣ አንድም ነቢብ አንድም ገቢር አንድም ውሕደት አንድም ዑደት የሚሉትን መስመሮች የተከተለ ነው። ሐልዮ የሚለው ቃል በጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ ውክልናን፣ ትእምርትን፣ ፍካሬን፣ ምናብን፣ ሃይማኖትን፣ ረቂቅ እና ጻናን ዕሳቤዎችን የወከለ ነው። ነቢብ፣ በጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ላይ በአንደበት የሚዜሙትን ዜማዎች፣ ዝማሬዎች፣ እልልታዎች፣ ዘፈኖች፣ ኾታዎች፣ አይብላኾ መኔዎች፣ ቃል ግጥሞች እንዲኹም ስለ ጥምቀት ክብረ በዐዓል የሚነገሩትን አፈ ታሪኮች እና ምልኪዎች ይወክላል።

ገቢር በጥምቀቱ ክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ የሚጨበጥን፣ የሚዳሠሥን፣ ዘወትርን፣ የዕማሬን እና መሰል ታዋቂ፣ ተጨባች እና ተዳሳሽ ነገሮችን የሚወክል ነው። በዚህ በታወቀው እና በዘወትሩ ነገር ላይ ሐልዮ እና ነቢብ ሲዋሐዱ የነበረውን ዘወትራዊ ወደ ብርቃዊ፣ ዓለማዊ ወደ ሰማያዊ፣ ሥጋዊ ወደ መንፈሳዊ በመቀየር የሕይወት አሰልችዎች እንዲለዝቡ እና አልጫዎች እንዲጣፍጡ ያደርጋል።

ውሕደት በጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ ከሐልዮ ከነቢብ እና ከገቢር በኋላ በማኅበረሰቡ ልቦና የሚገኘውን ይደረግልኛል፣ ተደርጎልኛል ውጤት የሚመለከት ነው። ዑደት ደግሞ ውሕደት ተብሎ የተወከለው የጥምቀት ክብረ በዓል ሀላፊ እና ረጋፊ እንዳይኾን፣ የአሰልችነት፣ የእርጅና እና የሞት ዕጣ ፈንታ እንዳይገጥመው የሚያደርግ ነው። ዑደት ቦታን እየጠቀሰ፣ ዓመታትን እየመለሰ ውሕደትን ያስቀጥላል። የሐልዮ፣ የነቢብ እና የገቢር ውሕደት እና ዑደት በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ሲታይ ምን ይመስላል? የሚለው ጥያቄ እንደሚከተለው የሚገለጽ ነው። ውሐ በቁሙ ለንጽሕና፣ ለመስኖ ሥራ፣ ለጭቃ ማቡኪያ እና ለጥም ማርኪያ የሚውል ነው። ወደ ጥምቀተ ባሕሩ ተጠልፎ የገባው የቀሐ ውሐ ሐልዮ እና ነቢብ የኾነው ጸሎት ሲጨመርበት ጥንት የነበረውን ዘወትራዊነት ውሐ ይለቅና የሐልዮ የነቢብ እና ገቢር ውሕደትን ይፈጥራል። በዚህ ጊዜ “ጸበል ሲያዩት ውሐ ይመስላል፣ ካህን ሲያዩት ሰው ይመስላል” የሚለውን ብሒል ያሰገኛል። በዚህ መልኩ ጥምቀተ ባሕሩ ዘወትራዊን ውሐ ይለቅና ወደ ጸበልነት፣ ፈዋሽነት፣ አዳኝነት ይለወጣል። ሌላው መስቀል፣ ጸናጽል፣ መቋሚያ፣ መርከብ፣ ከበሮ፣ አልበሳት፣ ጥላ፣ ጥና እና መሰል ቁሳዊ ባህሎች ሥሪታቸው ገቢር ነው። ጥንት የነበረው ሐልዮ እና አኹን የሚነበነበው ነቢብ ሲያድርባቸው ደግሞ በሚሸከሙት ውክልና የደኅነት እና የፈውስ ንዋዬ ቅድሳት ይኾናሉ።

ከቦታ አንጻር ደግሞ ዓመቱን ሙሉ ማንኪት ከአዘዞ፣ አዘዞ ከማንኪት አያንሱም፤ አይበልጡም፤ ይኹን እንጂ ጥምቀት ሲመጣ ባሕረ ጥምቀቱ ማንኪት በሰው ተሞልቶ ይቀደሳል፡፡ ሰው ቦታን ይቀደሳል፤ ቦታም ሰውን ይቀድሳል፡" እንዲሉ፡ ይሕም በዐዋዲ መርነት እየተመለሰ ሲቀደስ እና ሲወደስ ይኖራል፡፡ ሌላው ተጠቃሽ ጉዳይ ጊዜ ነው፡፡ የዘወትሩ ጊዜ ሲታሰብ ያው የተለመደ እና አሰልች ነው፡፡ ይህ የተለመደው ጊዜ በሐልዮ እና ነቢብ በጥምቀት ሀልዮ እና ነቢብ ሲባረክ ያች ዕለት ቅደስና እና ልዕልና ይኖራታል፡፡ በዚህ መልኩ ጥምቀት እና ጊዜ ሲዋሐዱ የጥምቀትን ክብረ በዓል ያስገኛሉ፡፡ ይህች ዕለትም በጥምቀት ክብረ በዓል ምክንያት ከዘወትሩ ቀናት የተለየች እና የተባረከች ለሰዎች ድኅነት የምታስገኝ ትኾናለች፡፡ ስለኾነም የክዋኔ ሐልዮ፣ ነቢብ እና ገቢር ውሕደት ዐዲስ ነገርን ማስገኘት ነው፡፡ ይህ ዐዲስ ነገር ደግሞ የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ ነው፡፡

# ምዕራፍ ስድስት፡- የጥምቀት ክብረ በዓል ያለው ማኅበራዊ አንድምታ እና መስተጋብር በጎንደር

በዚህ ሥር የተተነተኑት ማኅበራዊ ፋይዳዎች በኹለት ክፍል የተዋቀሩ ናቸው። አንደኛው ክፍል በጥምቀት ክብረ በዓል ዐውድ የሚገለጹ ክዋኔዎች አንድምታ እና ማኅበራዊ ፋይዳዎቻቸው የሚለው ነው። በዚህ ሥር የተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮችን የማቀራረብ ፋይዳ፣ ማንነትን የማስቀጠል ፋይዳ፣ ታሪክን እና አፈ ታሪክን የመዘከር ፋይዳ፣ የግብረ ገብነትን እንዲቀጥል የማድረግ ፋይዳ እና ከቤተሰቦቻቸው የተለያዩ ማኅበረሰቦችን የማገናኘት ፋይዳ የሚሉት ነጥቦች የተካተቱበት ነው።

ኹለተኛው ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚነገረው ትረካ ማኅበራዊ ፋይዳ ነው። በዚህ ሥር ደግሞ ስለ ጎንደር ጥምቀት አመጣጥ የሚነገሩ አፈ ታሪኮች አንድምታ እና ማኅበራዊ ፋይዳዎች፣ ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚነገሩ ሃይማኖታዊ ትረካዎች አንድምታ እና ማኅበራዊ ፋይዳዎች እና ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚነገሩ የምልኪ ትረካዎች አንድምታ እና ማኅበራዊ ፋይዳዎች የሚባሉት ንኡሳን አርእስት ተተንትነው የቀረቡበት ክፍል ነው።

## 6.1. በጥምቀት ክብረ በዓል ዐውድ የሚገለጹ ክዋኔዎች አንድምታ እና ማኅበራዊ መስተጋብር

### 6.1.1. የተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮችን ማቀራረብ

የጎንደርን ጥምቀት ክብረ በዓል በአካባቢው የሚኖሩ የእስልምና ሃይማኖትና የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮች ከኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ጋራ ዐብረው ያከብሩታል። እነዚህ ማኅበረሰቦች በዓሉን ማክበር ብቻ ሳይኾን በጎረቤቶቻቸው፣ በወዳጆቻቸውና በጓደኞቻቸው ቤት ውስጥ በመጠራራት በድግስ ሥርዐቱ ላይ ተጋብዘው ጸበለ ጻድቅ ይቀምሳሉ። ይህን በተመለከተ ሙሔ ሰዒድ የተባለ መረጃ አቀባዬ ቀጣዩን መረጃ ሰጥቶኛል።

> *ማኅበራዊ ትስስሩ እንኳን ከዚህ ጎንደር ውስጥ ሙስሊምና ሌላም እምነት ተከታዮች ይቅርና ከውጭ ድረስ መጥተው የሚያዩትም ቱሪስቶች እንዳሉ ይታወቃል። እንደገና የጎንደርን ጥምቀት ለማየት ሃይማኖት ይገድበዋል ብዬ አላስብም፤ ምክንያቱም ይህ ባህላችን የኹላችንም በዓል ኹኔታ ስለኾነ በሃይማኖቱ እኔ የእስልምና ሃይማኖት ብከተልም ኢትዮጵያዊ በዓል እና ቅርስም ስለኾነ እኔ በተለየ ኹኔታ ነው የማየው የጎንደርን ጥምቀት እንደራሴም እንደኀብረተሰቡም ጥምቀትን ደስ ብሎን ነው የምናየው (ሙሔ ሰዒድ 16/05/2011 ቃ.መ)።*

መረጃው እንደሚስረዳው የጎንደር ጥምቀት ማኅበረሰባዊ መስተጋብሩ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ ነዋሪ የኾኑት የሙስሊምና የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የሚገናኙበት በዓል ነው፡፡ በዚህ በዓል ላይ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሚታደምበት ዋናው ምክንያት ከሃይማኖቱ ባለፈ በጥምቀት ዕለት የሚታየውና የሚደረገው ክዋኔ ማኅበረሰባዊና ባህላዊ ይዘት ያለው መኾኑ ነው፡፡ በጥምቀት ዕለት የሚለበሰው አልባሳት፣ የሚጨፈረው ጭፈራ፣ የሚቀነቀነው ቃል ግጥም፣ የሚካሄደው ግብይት፣ የሚከወነው ባህልና ዕሴት የአንድ ሃይማኖት ተከታዮችን ዕሴት ብቻ የሚገልጽ አይደለም፡፡ ከዚህ ይልቅ በጎንደር ባህልና የጎንደርን ማኅበረሰብ የሚወክሉ ድርጊቶች ስለሚፈጸሙ ሁሉም ማኅበረሰብ የኔ ብሎ ይቀበላቸዋል፡፡ በዚህ ምክንያት በየዓመቱ የጥምቀትን በዓል በጋራ ያከብሩታል፡፡ በዚህ ተሳትፎ ውስጥ ከተሳትፎው ባለፈና በላቀ መልኩ በኦርቶዶክስ፣ በእስልምናና በአይሁድ አማኞች ዘንድ የርስ በርስ መገናኘትን እና ጥብቅ ዝምድናን ይፈጥራል፡፡ ይህ ማኅበራዊ ትስስር እና ዝምድና የግብይት፣ የንግድ ልውውጥን እና የባህል ትስስርን በመፍጠር በሃይማኖቶች መካካል መቻቻልን ይፈጥራል (ቦሴ ወንድማገኝ 28/11/11 *ቃ.መ*[77]፤ ጀጃው ያለው 28/11/11 *ቃ.መ*)፡፡

በጎንደር ጥምቀት በሽመና *ሥራ* ውጤቶች በሆኑት ቀሚስና ባህላዊ አልባሳት ሽያጭ ላይ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ከክርስትና ሃይማኖት ተከታይው ከፍ ያለ ተሳትፎ አላቸው፡፡ ቤተ እስራኤሎችም በእደ ጥበባት፣ በሸክላ *ሥራ* እና በቅርጻቅርጽ ግብይት ላይ ተጠቃሚነታቸው ላቅ ያለ ነው፡፡ ይህ የጋራ ተጠቃሚነት ደግሞ የጥምቀትን ክብረ በዓል የጋራ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በመኾኑም የጎንደር ጥምቀት በጎንደር አካባቢ የሚኖሩ የኦርቶዶክስ፣ የእስልምና እና የአይሁድ ቤተ እስራኤል እምነት ተከታዮች እንዲግባቡና ተቀራርበው እንዲኖሩ ትልቅ ማኅበራዊ ፋይዳ አለው (ቦሴ ወንድማገኝ 28/11/2011 *ቃ.መ*[78]፤ ጀጃው ያለው 28/11/2011 *ቃ.መ*)፡፡

ይህን በተመለከተ የጥምቀት በዓል ላይ የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ሲሳተፉ አይቻለሁ፡፡ ይህ ማኅበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል? የሚል ጥያቄ ለአቶ ጌትነት አመራ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ *"ይህ በእውነቱ እኔ እንዳየሁት ሙስሊምም ቢኾን*

---

[78] በተመሳሳይ ቀናት ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ተጠኚዎች ተመሳሳይ መረጃ ከሰጡ በፊደል ቅደም ተከተል ተራ ይጠቀሳሉ፡፡

*ተደስቶ ነው የሚውለው፣ አሸብርቆ ወጣቱ የሙስሊም ሴቶች ወጣቶች አዛውንቶች በባህላቸው ዐብረው ተደስተው ነው የሚውሉ። በአካል ስላየኹት ነው" (ጌትነት አመራ 13/05/2011 ቃ.መ)።*

የአቶ ጌትነት መረጃ የጎንደር ጥምቀት የአንድ ወገን ብቻ ሳይኾን የሙስሊም ልጃ ገረዶችና ወጣቶች ዐብረው አሸብርቀው የሚያከብሩት በዓል መኾኑን የሚያጸና ነው። በጥምቀት በዓል የሚታየው ክዋኔ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት መገለጫ ብቻ ሳይሆን የጎንደርን ማኅበረሰብ ባህል የሚመለከት ነው። ይህ ባህልና እሴት ደግሞ የሁሉም ነዋሪዎች ሀብት በመኾኑ በአንድ ላይ ያከብሩታል። ስለ ጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል አካታች፣ ሳቢና ማራኪ ያደረገው ጉዳይ ምን እንደኾነ ለወጣት ሙሔ ሰዒድ ላቀረብኩለት ጥያቄ የሚከተለውን መረጃ ሰጥቶኛል። *"የሚመስለኝ ከዚህ ከ44ቱ ታቦታት ይባላል 44ቱ ታቦታት ሲባል የእያንዳንዱ ሌላ ቦታ ላይ አንድ ወይም ኹለት ብቻ ነው የሚያድርገው ታቦት ማደሪያ ከዚህ ግን ቢያንስ ርግጠኛ ባልኾንም ከ፳፣ከ፰፣ ከ፴ ያላነሱ ከአንድ ላይ ያድራሉ። በዚህ ጥምቀቱን ልዩ ያደርገዋል" (ሙሔ ሰዒድ 16/05/2011 ቃ.መ)።*

ከዚህ ላይ የምንረዳው የጎንደርን የጥምቀት ክብረ በዓል አመጣጥ ታሪክና ምንነት የሚረዱት ክርስቲያኖቹ ብቻ ሳይሆኑ ሙስሊሞቹም ግንዛቤ እንዳላቸው የሚያስገነዝብ ነው። ይህ ግንዛቤ ድንገት የመጣ ሳይሆን የሙስሊም ማኅበረሰቦች ከክርስቲያኑ ጋራ በሚያደርጉት የጥምቀት ተሳትፎ እና የቆየ ግንኙነት እየዳበረ የመጣ ማኅበራዊ ዕሴት መኖሩ ነው። የጎንደር ሙስሊሙ ኅብረተሰብ ስለ ጎንደር ጥምቀት አመጣጥ፣ ታሪክና ስለ አርባ አራቱ አድባራት ጭምር ግንዛቤ እና ዕውቀት አላቸው። ይህ ዕውቀት የጋራ ማንነትን እና ባህላዊ ዕሴትን የሚያሳድግ በመኾኑ ማኅበረሰቦች ተግባብተው እንዲኖሩ ያስችላል። ይህን በተመለከተ ወጣት ሙሔ ሰዒድ ተከታዩን መረጃ ሰጥቶኛል።

> *ስሜ ሙሔ ሰዒድ እባላለሁ እምኖረው በጎንደር ክፍለ ከተማ ነው። እና ስለ መስቀል ጥምቀት ኹኔታ ብዙ ደስ የሚሉ ነገሮች አሉት። ያው እኔ በሃይማኖቴ ሙስሊም ነኝ። በጥምቀቱ የሚታየው ነገር አለባበሱ፣ በዝማሬ ነው የሚያከብሩት። እኔ የምኼድበት ዋናው ምክንያት በዓሉን በተለየ ኹኔታ ለማየትና ክብረ በዓሉ ስለሚስበኝ። በዓሉን የሚያከብሩት ከአለባበሳቸው ይጀምራል። አለባበሱ በጣም ደስ የሚል ነው። በማንኛውም ሰዓት የሚለበሰው ልብስ ሳይሆን ወንዶችም ሴቶችም በጥምቀቱ ከተራው ጊዜ የሚለብሱት አለባበስ ለየት ይላል። በየ ራሳቸው ግሩፕ የተለያየ ልብስ እነሱን የሚመስል ነው የሚለብሱ። ጥምቀት ስውልና ያንን ሳይ የበለጠ ውስጤ በጣም ደስ ይለኛል (ሙሄ ሰኢድ 16/05/2012 ቃ.መ)።*

የሙሔ ሰዒድ የእስልምና እምነት ተከታይ ቢኾንም የጎንደርን ጥምቀት በየዓመቱ ይታደማል። በዚህ መረጃ መሠረት የጎንደር ማኅበረሰብ አለባበስ ከጥምቀት በዓል ጋራ የተለየ ትርጉምና መልእክት አለው። የጥምቀት ታደሚዎች በየ መጡበት ቡድን መገለጫ እነሱን የሚገልጽ የአለባበስ ሥርዓት አላቸው። ይህ ሥርዓታቸው እና የጥምቀት ክዋኔ ስለሚስባቸው የሃይማኖት ልዩነት ሳይገድባቸው በየዓመቱ እየመላለሱ በዓሉን ያከብሩታል። ይህን በተመለከተ መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል። *"ብዙ ጊዜ በጎንደር ጥምቀት በተለየ መልኩ ደግሞ የሚታየው የሃይማኖቶች ማለት የሙስሊም ሃይማኖት ማኅበረሰቦች አስፓልት ጠርገው አጥበው ምን ብለው ያው ተሳትፎ ያደርጋሉ። ያ ምንድን ነው የአካባቢው ማኅበረሰብ ፍቅር የኾነ ተፈጥሮ ባሕርይ እንዲኖረው ያደርጋል"* (መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ 19/01/12)።

ጠቅለል ባለ መልኩ የጎንደር ጥምቀት የክርስትና፣ እስልምና፣ አይሁድና የሌሎችም እምነት ተከታዮች በአንድ ላይ ኹነው የሚያከብሩት መሆኑን የሚያረጋግጥ መረጃ ነው። ይህ የክብረ በዓል አካኼድ ከሃይማኖታዊ ጉዳዩ በበለጠ ማኅበረሰባዊ፣ ሰዋዊ እና ባህላዊ ይዘቱ የሚልቅ መኾኑን ያመላክታል። በዚህ መልኩ የጎንደር ትምቀት የተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮችን በማገናኘት እና በማቀራረብ ዐብሮነታቸው እንዲቀጥል በማድረግ ኹነኛ ማኅበራዊ ፋይዳ አለው።

### 6.1.2. ሀገረሰባዊ ዕውቀትን እና ሀገራዊ ማንነትን ማስቀጠል

የጎንደር ጥምቀት ለአካባቢው ማኅበረሰብ ሀገረሰባዊ ዕውቀትን እና ሀገራዊ ማንነትን በመዘከር ከፍ ያለ ግልጋሎት አለው። የጎንደር ጥምቀት ለሀገረሰባዊ ዕውቀት እና ለሀገራዊ ማንነት ያለውን መስተጋብር እና ፋይዳ በተመለከተ ለአቶ ልዕልና ኀይለ መስቀል ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር። እሳቸውም ተከታዩን ሰፋ ያለ መረጃ ሰጥተውኛል።

> *በዓሉ ጎንደር ላይ በተለየ ኹኔታ ስለሚከበርና ልዩ ገጽታ ስላለው የተለየ የሚያደርጉት ብዙ ገጽታዎች የአለባበስ፣ በወቅቱ የአመጋገቡ፣ ጭፈራው፣ ሥነ ሥርዓቱ ከሌላው አካባቢ ከፍ ያለ ስለሚያደርገውና ስለሚጎላ ይህን ክብረ በዓል ለመታደም ከውስጥም ከውጭም በርካታ ሕዝቦች ይታደማሉ። አዘፋፈኑን አጨፋፈሩን በሚመለከት ጎንደር የራሱ የሆነ ዜማ፣ ምት፣ ስልትና ዕውቀት አለው። የጎንደር አካባቢ የስልተ ምቱ አንድ ዐይነት ቢኾንም የአጨፋፈር ልዩነቶች አሉ። ለምሳሌ የደንቢያ አለ፣ መኻል ጎንደር፣ ወገራ፣ ራሱን የቻለ ወደ ጥምቀት ሲመጡ የአካባቢያቸውን የጎንደርኛ አጨፋፈር ይዘው ይመጣሉ። ከዚህ አንጻር ጎንደር በአጨፋፈር ስብጥር የኾነ ስልት አላት። የአጨፋፈር ስልቱ አንገር፣ አንጓ በአንጓ የሚሉት አለ። ዋንጫ ልቅለቃ የሚሉት አለ። ስለዚህ በጥምቀት ክብረ በዓል እነዚህ ኹሉ የጭፈራ ዐይነቶች ይታያሉ። አለባበሱን በሚመለከት ግን ጎንደር የራሱ ወጥ የኾነ*

*የአለባበስ ስልት አለው። ሸማ ለባሽ ሕዝብ፣ ነጭ ለባሽ ሕዝብ ነው የሚባለው (ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011 ቃ.መ)።*

ቃለ መጠይቁ እንደሚያስረዳው የጎንደር ጥምቀት የጎንደር መገለጫ የሆነው ሀገረሰባዊ ዕውቀት እና ማንነት እንዲጠበቅ ያደርጋል። የጎንደር ጥምቀት አንድ የኾነ የአጨፋፈር ስልት አለው የሚባለው የጎንደር መገለጫ የኾነው የእስክስታ እና የአጨፋፈር ስልት መኖሩ ነው። ይህ ስልተ ምት ደግሞ ወረዳዎች እንደገና የየራሳቸው የአካባቢ የጭፈራ ስልት አላቸው። በጎንደር ጥምቀት እነዚህ ወረዳዎች ጭፈራዎቻቸውን እና የእስክስታ ምት ስልቶቻቸውን ይዘው ይታደማሉ። በጎንደር ጥምቀት የደንቢያ ጭፈራ፣ የወገራ ጭፈራ፣ የበለሳ ጭፈራ፣ የጠዳ ጭፈራ፣ የሚባሉ የአጨፋፋር ዓይነቶች ይከወናሉ። የዋንጫ ልቅለቃ፣ የአንገር እና የአንጓ በአንጓ ጭፈራዎች ከየ ወረዳው የሚመጡ ሲኾን እነዚህ በአንድ ላይ የጎንደር ጭፈራ ተደርገው ይወሰዳሉ። ጭፈራዎቹም የጎንደር መገለጫዎች ናቸው። በመኾኑም የጎንደር ጥምቀት ለእነዚህ ሀገረሰባዊ ዕውቀቶች የመከወኛ ዐውድ በመኾን ከዘመን ዘመን እንዲቀጥሉ እና እንዲሻገሩ ያደርጋል።

እነዚህ የመንጥቅ፣ የአንጓ በአንጓ እና የዋንጫ ልቅለቃ እስክስታዎች የአካባቢውን ማኅበረሰብ የውትድርና፣ የአጨዳ፣ የእርሻ፣ የቅልጥፍና የዳገት መውጣት፣ የቁልቁለት መውረድ፣ ጀግንነትን፣ ማግኘትን እና ማጣትን የመሳሰሉ ማኅበረሰባዊ ሕይወትን የሚያሳዩ ናቸው። አንድም የእስክስታው ለሰስ፣ሞቅ ደመቅ እና በመጨረሻም እንደ መጀመሪያው ለዘብ ያለ ቅርጽ መያዛቸው ልጅነትን፣ ወጣትነትን እና እርጅናን የሚተረጉሙ ናቸው። በመኾኑም የጎንደር እስክስታ የጎንደርን ማኅበረሰብ ሕይወት የሚጠቁሙ ናቸው (ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011 ቃ.መ)።

ሌላው የጎንደር ባህላዊ ትውፊት የአለባበስ ሥርዓታቸው ነው። ጎንደሬዎች በጥምቀት ዕለት የራሳቸው የኾነ የአለባበስ ሥርዐት አላቸው። እነዚህ ማኅበረሰቦች በአብዛኛው የሚታወቁት ነጭ፣ ለባሽ፣ ሸማ ለባሽ በመኾናቸው ነው። በጥምቀት ክብረ በዓል በአብዛኛው ከነጭ ልብስ ላይ ከግራ ትክሻ ወደ ቀኝ በሰያፍ መሥመር በቀይ ቀለም ቦርቀቅ ብሎ የተሠመረ ልብስ በሌላ አጠራር ጃኖ ተብሎ የሚጠራውን ልብስ ወንዶቹ ይለብሳሉ። ይህ ልብስ የጎንደር መገለጫ ሲኾን የዕሴት እና የማንነት መገንቢያ ተደርጎ ይወሰዳል (ልዕልና ኀይለ መስቀል፣ 12/12/2011 ቃ.መ)።

የሸማው ቀይ ክፍል ከነገሥታቱ ጋራ የተያያዘ ታሪካዊ እና ከክርስቶስ ስቅለት ጋራ የተያያዘ ሃይማኖታዊ አንድምታ እንዳለው ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ ያስረዳሉ። ጎንደር ነጭ ለባሽ

መኾኑ እና በጥምቀት ዕለት ነጭ መልበሱ የጥምቀትን ንጽሕና የሚገልጽ ነው። ሰዎች በጥምቀት ዕለት ከቂም ከበቀል፣ ከተንኮልና ከክፋት ነጻ ኹነው የሚያከብሩበት መኾኑን ያዘክራል። በነጭ ልብስ ላይ ከግራ ወደ ቀኝ የተሠመረው ቀይ ክፍል ደግሞ ነገሥታቱ ድሮ የሚለብሱት እንደ ነበር ይገልጻሉ። የሚለብሱበት ምክንያት ቀዩ ክፍል የመሥዋዕትነት ምሳሌ ነው። ነገሥታቱ ለሀገራቸው እና ለሕዝባቸው ሲሉ የሚመጣውን ማንኛውንም መስዋዕት ለመክፈል ዝግጁ እንደ ነበሩና እንደ ከፈሉ ያጠይቃል። ለሀገራቸው ሲሉ ዐፄ ገላውዲዎስ፣ ዐፄ ቴዎድሮስ እና ዐፄ ዮሐንስ የከፈሉትን መሥዋዕት ማዘከሪያ ተደርጎ ይወሰዳል።

ቀዩ ጃኖ ከቅርበትም ይኹን ከርቀት ሲመለከቱት ከአፎቱ የተመዘዘ ወይም ከሰገባ የወጣ ሰይፍ ይመስላል። በወቅቱ ነገሥታቱ ጠላቶቻቸውን ድል ያደርጉበት የነበረው መሣሪያም ሰይፍ ነው። ሰይፍ ደግሞ የጎንደር ነገሥታት የጀግንነት መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል። ንጉሡ "ክተት ሰራዊት፣ ምታ ነጋሪት" ብሎ ሲወጣ ጠላትን አሳፍሮ የሚመልስ መኾኑንና የሚያዘክር ነው። ጃኖው ሲመለከቱት ሰገባው በግራ እጅ እና ሰይፉ በቀኝ እጅ ሲመዘዝ እና ከአፎቱ ሲወጣ ለቅጽበት የሚያሣይ ነው። ይህም የነ ዐፄ ቴዎድሮስን ግብር የሚያዘክር ነው። በመኾኑም ጃኖ የጎንደር ሕዝብ እና ነገሥታት ለሃይማኖቱ፣ ለሀገሩ እና ለክብሩ መሥዋዕት የተቀበለበት ድርሳን ተደርጎ ይወሰዳል (ሊቀ ሊቃውንተ ዕዝራ ሐዲስ 2011 ቃ.መ)።

ሌላው በጎንደር ጥምቀት የሚቀነቀነው ኢትዮጵያዊ ማንነት ነው። በጥምቀቱ ዕለት ከታቦታቱ፣ ከሥዕል አድናውና ከሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ጋራ የተለያዩ ሥዕላት ዐብረው ይወጣሉ። ከእነዚህ መካከል አንዱ የኢትዮጵያ ካርታ ነው። ይህ ካርታ ዐብሮ በጥምቀት ቀን መውጣቱ ምን አስተምህሮ አለው? ብዬ ለሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የጎንደር ጥምቀት ከጎንደር ዐልፎ ኢትዮጵያዊ፣ አፍሪካዊና ዓለማቀፋዊ ይዘት ያለው መኾኑን እንደሚከተለው ገልጸውልኛል። *"ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር" ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ተብሏል። ይህ ማለት ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ሀገር መኾኗን እንዳውም ንግሥተ ሳባ አይሁዶችን ታሳፍራቸዋለች። የጎንደር ጥምቀት ጎንደሪያን ኢትዮጵያውያን ማንነታቸውን የሚያሳዩበት ነው። ጥምቀት ከሃይማኖታዊ ጋራ ሀገርንም የሚያሳውቅ፣ ለዓለም ክፍል የሚያስተዋውቅና ኢትዮጵያዊ ማንነቱን በአደባባይ ለዓለም የማሳወቂያ አደባባይ ነው"* (ሊቀ ሊቃውንተ ዕዝራ ሐዲስ 2011 ቃ.መ)።

በጥምቀት ዕለት የኢትዮጵያ ምስልና፣ ሰንደቅ ዓላማ የሚወጡት ጎንደር ማንነት ከጎንደር ዐልፎ ኢትዮጵያዊ መሆኑን የሚያዘክር ነው። የሰንደቅ ዓላማ እና የኢትዮጵያ ካርታ በጥምቀቱ ላይ ወጥተው መታየታቸው የጎንደር አካባቢ ሕፃናት እና ወጣቶች በቀላል መንገድ ማንነታቸውን እያወቁ እንዲመጡ የማስቻል ዐቅም አለው።



(የኢትዮጵያ ካርታ እና ሠንደቅ ዓላማ በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል 2011)

### 6.1.3. ከቤተሰቦቻቸው የተለዩ ማኅበረሰቦችን ማገናኘት

የጎንደር ጥምቀት ከአካባቢው ርቆ ለሥራ ጉዳይ ይኹን በስደት ከሀገር ውጭ የሚኖሩ ተወላጆች ከቤተሰቦቻቸው ጋራ የሚገናኙበት ክብረ በዓል ነው። የዚህ አካባቢ ማኅበረሰቦች ለሱዳን[79] ቅርብ በመኾናቸው ምክንያት ለሥራ ጉዳይ መተማን አቋርጠው ወደ ሱዳን ይኼዳሉ። ወደ ሱዳን ኺደው በሥራ ከቆዩ በኋላ የጥምቀትን በዓል ምክንያት በማድረግ ወደ ጎንደር ይመለሳሉ። የጎንደር ጥምቀት ሲቃረብ እና ሲበሠር የጠፋ፣ የራቀና የተሰደደ ዘመድ ይመጣል ተብሎ ይታሰባል። በዚህ ምክንያት የጥምቀት ክብረ በዓል መቃረብን ተከትሎ በማኅበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ደስታን ይፈጥራል (ዓለም ሰገድ በለጠ፣ 10/11/2011 ቃ.መ.፣ እቴኑ መኮነን 18/05/12 ቃ.መ እና ደጅጥኑ ሥንቁ 18/05/12 ቃ.መ.)።

በደርግ ዘመነ መንግሥት ከቀይ ሽብር እና ተመሳሳይ የፖለቲካ ችግሮች ጋራ በተያያዘ ኹኔታ የአካባበው ማኅበረሰብ ወደ አሜሪካና አውሮፓ ሀገራት በመኼድ ይኖራሉ። እነዚህ የአካባቢው ተወላጆች ምንም ቢኾን የጥምቀት በዓል ሲደርስ ጎንደርን ያስታውሳሉ።

---

[79] *በምዕራፍ ዐምስት ውስጥ የጎንደር ወጣቶች በብዛት ወደ ሱዳን እንደሚኼዱ እና የጥምቀት ካልተመለሱ "አጣማጁን ሲያጣ እንቧ ይላል በሬ፣ ያምስጋን ገደፋው የት ኺዶ ነው ዛሬ።" (ደስታው ፈንታው 11/05/2011 ዓ.ም) ተብሎ እንደሚያቀንቅንላቸው እና የጥመቀት ዕለት ያለ ክፉ ነገር ጎንደር እንዳማይቀር ተገልጿል።*

በመኾኑም በጥምቀት ሰሞን ከምንጊዜው በበለጠ በውጭ ሀገር የሚኖሩ የአካባቢው ተወላጆች ወደ ጎንደር ይመጣሉ (ዓለም ሰገድ በለጠ፣ 10/11/2011 *ቃ.መ*፣ እቴኑ *መ*ኮነን 18/05/12 *ቃ.መ* እና ደጅጥኑ *ሥን*ቄ 18/05/12 *ቃ.መ*)።

ግለሰቦቹ የሚመጡበት ምክንያት አንድም በሕይወት እያሉ የጎንደር ጥምቀት የቀደመ ትዝታ ስለሚያጭርባቸው ለመታደም በማሰብ ነው። አንድም የጎንደር ጥምቀት በየ ዓመቱ ቃል እየገቡ ስለሚኼዱ እንደ ስለት በመውሰድ ነው። አንድም የአካባቢው ማኅረሰብ በጥምቀት ክብረ በዓል የቀረ ዘመድ ካለ ትልቅ ሀዘን የማስገባት ነገር ስላለ እግዚአብሔርን ሳይከፋው ዘመዶቻችን አሳዝነን አንውልም ብለው በማሰብ ነው። በእነዚህ ምክንያቶች በውጭ ሀገር የሚኖሩ የአካባቢው ተወላጆች በዚህ ቀን መጥተው ጥምቀትን አክብረውና ዘመዶቻቸውን አግኝተው መኼድ ይፈልጋሉ። በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት የጠፋውን፣ የተሰደደውን እና ከሀገር የራቀውን ማኅበረሰብ በማገናኘት በኩል ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አለው (ዓለም ሰገድ በለጠ፣ 10/11/2011 *ቃ.መ.*፣ እቴኑ *መ*ኮነን 18/05/12 *ቃ.መ.* እና ደጅጥኑ *ሥን*ቄ 18/05/12 *ቃ.መ.*)።

እንደዚሁም በርካታ ልጃ ገረዶች በዐዲስ አበባ ከተማ በተለያዩ *ሥራ*ዎች በመሠማራት ኑሯቸውን ይገፋሉ። እነዚህ በዐዲስ አበባ የሚኖሩ ልጃ ገረዶችና ወጣቶች በየዓመቱ የጎንደርን ጥምቀት ያከብራሉ። የዐዲስ አበባ ልጃ ገረዶችን እና የጎንደርን ጥምቀት መስተጋብር በተመለከተ አቶ ጌትነት አመራ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *ዐዲስ አበባ የሚኖሩ ልጆቻችን፣ በመንግሥት ሥራም ኾነ በቤት ሠራተኝነት የሚኖሩት ኹሉ ብዙ ጊዜ ቢለዩንም ተስፋ የምናደርግ ጥምቀት ሲደርስ ነው። ጥምቀትን መጥተው አክብረው ይኼዳሉ። ለታቦቶቱ ጥላ፣ ጧፍ፣ መጎናጸፊያ፣ ምንጣፍ፣ መጋረጃውን እየገዙ ስለት ያቀርባሉ። እንደቻሉት ለቤተሰቦቻቸውም ኩታውን፣ ነጠላውን፣ ቀሚሱን፣ ካባውን፣ ባትተኹለቱን ግዝተው ይሰጣሉ። ውጭ የሚኖሩትም በአብዛኛው በጥምቀት ነው የምንገናኝ ጥምቀት ካለፈ ጥምቀትን ተስፋ ማድረግ ነው እንጂ ብዙም በውጭም በውስጥም የሚኖረው ወገን ከወገኑ የሚያገናኝ ጥምቀት ነው። የጥምቀት በዓል ያለ ዐሳር[80] ነገር ቀርቶ አይቀርም ወገኑ (ጌትነት አመራ፣ 7/11/2011 ቃ.መ.)።*

ከዚህ መረጃ እንደምንረዳው የጎንደር ጥምቀት ከቤተሰብ የተለዩትን የአካባቢው ተወላጆች በማገናኘት በኩል ፋይዳው ላቅ ያለ እንደሆነ የሚያሳይ ነው። እንደ አካባቢው ማኅበረሰብ እምነት አንድ ተወላጅ በማንኛውም ጊዜና በማንኛውም ቦታ በሥራና በተለያዩ ጉዳዮች ኺዶ ሊኖር ይችላል። በጥምቀት ክብረ በዓል ግን ያለ ጭንቅ ነገር ጎንደርን ሳይረገጥ አይውልም የሚል እምነት አለ። ይህ እምነት ደግሞ በሚጠብቀው ቤተሰብም ሆነ በውጭ በሚኖረው

---

[80] ክፉ ነገር፣ ድንገተኛ፣ ያልታሰበ ነገር ማለት ነው (ጌትነት አመራ፣ 7/11/2011 *ቃ.መ*)።

ሰው ተቀባይነት ያገኘ የቆየ ልማድ ነው። በዚህ ምክንያት በዐዲስ አበባ የሚኖሩ በርካታ ከሰው ቤት ተቀጥረው የሚሠሩ ሴት ልጆች በዚህ ዕለት እንደምንም አጣጥመው ከቤተሰቦቻቸው ጋራ ተደስተው ለመዋል ሲሉ ወደ ጎንደር ጥምቀት ይታደማሉ።

አሠሪዎቻቸው ሠራተኞቹን በጎንደር ጥምቀት ሰሞን በብዛት የመፍቀድ ባህል እየዳበረ መጥቷል። ይህ ልማድ በዐዲስ አበባ ዘንድም ተቀባይነት ያገኘ በመኾኑ የጥር ወር ሲገባ ወደ ጎንደር እንደሚኼዱ ታውቆ ዝግጅት ያደርጋሉ። ለሠራተኞቹ የጎንደር ጥምቀት ትልቅ የኾነ ሐሤት እና ደስታን ስለሚያጎናጽፋቸው አጥብቀው ይወዱታል። ዓመቱን ሙሉ በሰው ቤት ሢሰሩ የቆዩ ልጃ ገረዶች በጎንደር ጥምቀት ሰሞን ተውበውና አምረው እንዲውሉ ያስችላቸዋል (ትግሥት ዓባይነው 23/05/12 ቃ.መ.)።

የጎንደር ጥምቀትና በዐዲስ አበባ የሚኖሩት ልጃ ገረዶች ግንኙነት በበዓል ማክበር ላይ የተወሰነ ብቻ አይደለም። ከዚህ ባለፈ ነጻ መሆንን፣ አምሮ መውጣትን፣ ውበት ማድነቅን እና የማኅበረሰቡን ዕሴት መማርን ያስገኝላቸዋል። ዓመቱን ሙሉ በአጥርና በግድግዳ ተወስነው የኖሩትን የቤት ሠራተኞች በነጻነት ከማኅበረሰቡ እና ውጭ ከሚኖሩት የጎንደር ተወላጆች ጋራ በአንድ አደባባይ የመዋል ዕድልን ይፈጥርላቸዋል (ትግሥት ዓባይነው 23/05/12 ቃ.መ.)።

በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት የማኅበረሰባዊ መዋቅር ልዩነትን በማለዘብ እና ማኅበረሰባዊ እኩልነትን በማረጋገጥ ላቅ ያለ ፋይዳ አለው። ይህን የጎንደር ጥምቀትን እና በዐዲስ አበባ የሚኖሩ ልጃ ገረዶችን በተመለከተ መ/ር ዳዊት ሥራው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *አንድ አባ መኳንንት በድብቅ ስማቸው "ጀብጀብ" የሚባሉ ሰው ነበሩ። እሚናገሩት እንደፈለጋቸው ነው። በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ከታቦት ማደሪያው ከዐዲስ አበባ የመጡ በርካታ የሚያምሩ ልጃ ገረዶች በባሕረ ጥምቀቱ አበባ መስለው ታጅበዋል። ለተመልካቾቻቸው በጣም ያምራሉ። ልጃ ገረዶቹ ከጥላው ሥር ታቦት እስኪነሳ ለብቻቸው እጅብ ብለው ተቀምጠዋል። በዚህ ጊዜ አባ መኳንንት "ጀብጀብ" በአጠገባቸው ሲያልፉ እንደ አካባቢው ማኅበረሰብ እና እንዳስለመዷቸው ሕግ እነዚህ ልጃ ገረዶች ሳይነሱላቸው ቀሩ። በልጃ ገረዶቹ ድርጊት እንደመናደድ ያሉት "ጀብጀብ" "የጎንደር እመቤቶች የዐዲስ አበባ "ገረዶች" ጤና ይስጥልኝ" ብለው ሸነቆጧቸው (መ/ር ዳዊት ሥራው 7/11/2011 ቃ.መ)።*

ይህ መረጃ የሚያሳየው ጀብጀብ ልጃገረዶቹ ባለመነሣታቸው እና በላ ማክበራቸው ቢናደዱም በጥምቀት ዐውድ ለተመለከቷቸው ልጃ ገረዶች ውበት ከልባቸው የመነጨ የምስክርነት ቃል ሰጥተዋል። ይህ መረጃ ልጃ ገረዶቹ በዐዲስ አበባ በሰው ቤት ተቀጠወረው እንደሚሠሩ ይጠቁማል። በሠራተኝነት ሕይወት የሚኖሩት ልጃገረዶች በጎንደር ጥምቀት ሲታደሙ በአንድ አፍታ ከሠራተኝነት ወጥተው ወደ እመቤትነት መቀየራቸውን አባ ጅብጀብ

ይመሰክራሉ። በመኾኑም የጎንደር ጥምቀት በተለያዩ ቦታዎች የሚኖሩ ሰዎችን ከቤተሰቦቻቸው ጋራ ማገናኘት ፋይዳው እንደተጠበቀ ኾኖ በዝቅተኛ ሕይወት ለሚኖሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ከላይኛው የማኅበረሰብ ክፍሎች ጋራ በማቀራረብና ሰብአናቸውን ከፍ በማድረግ በኩል ሚናው የላቀ ነው።

### 6.1.4. የባህላዊ አልባሳት ቀለማት እና ምልክቶች ማኅበራዊ መስተጋብር

በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል በአልበሳት ላይ የሚታዩ ቀለማት የተለያዩ ማኅበረሰባዊ አንደምታዎች አሏቸው። ይህን በተመለከተ መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ ቀጣዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *የጎንደር ጥምቀት አለባበሶቹ መልክታዊ ናቸው። የሚነዷቸውን መኪና ነኮች፣ መርከብ ነኮች፣ እንደዚህ የመላእክት ቅርጽ ያላቸው እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የኾኑ ሰው ማንም ወንጌል ሳያስተምረው የሚደረጉትን እንቅስቃሴ በማየት ብቻ እንዲገባው ያደርጋሉ። ለምሳሌ መስማት የተሳናቸው ዜጎች እራሱ ያንን በማየት የጎንደርን ጥምቀት አንድምታው ምን እንደኾነ የሚረዱበት ለኹሉም ማኅበረሰብ ማየት የተሳናቸው በጆሮ ሲሰሙት ከዝማሬው ጋራ መስማት የተሳናቸው ደግሞ በማየት ብቻ የሚተረጐም ትልቅ ታሪክ ያለው ነው። የጎንደር ጥምቀትና መንፈሳዊውም ዕይታ ለየት የሚያደርገው ይህ ነው (መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ 19/01/12)።*

በመኪናዎች፣ በባጃጆችና በታክሲዎች ላይ መንፈሳዊ አንድምታ ማኅበረሰባዊ መዋቅር ያላቸውን ጥምቀት ለሰዎች ድኅነት የተሰጠ መሆኑን የሚያሳዩ ጥቅሶችና ምልክቶች በጎንደር ጥምቀት ሰሞን ይስተዋላሉ። ሌላው በጥምቀት በዓል ላይ የነገሥታቱን የሚወክሉ ምስሎች እና የአድባራቱን የሚወክሉ ሥዕለ አድኅኖዎች ይወጣሉ። እነዚህን በማየት መስማት የተሳናቸው ሳይቀሩ የጎንደርን ጥምቀት በበቂ ግንዛቤ እንዲረዱት ያስችላቸዋል። በመኾኑም ማየት የተሳናቸው በድምፅ በሚደረገው ዝማሬና ሆታ ጥምቀቱን መረዳት ሲችሉ መስማት የተሳናቸው ደግሞ በቅርጻቅርጾቹ እና በአካል እንቅስቃሴዎቹ የጥምቀትን በዓል ክዋኔ ይረዱታል። ይሕም የጥምቀት ክብረ በዓል ሰው ለኾነ ኹሉ ያለውን ተደራሽነት አመላካች ነው።

እንደዚሁም በጎንደር ጥምቀት በጥምጣም፣ በመቀነት፣ በቀሚስና መሰል አልባሳት ላይ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማት ይበዛሉ። እነዚህ ቀለማት በአልባሳት ላይ ብቻ የሚቀሩ አይደሉም። የጎንደር አብያተ ክርስቲናትና በጥምቀተ ባሕሩ ማክበሪያ ላይ ለባሉ ማድመቂያ ተግባር ላይ ይውላሉ። እንደዚህም የተለያዩ የቤት ግድገዳዎች ላይ የተሣሉ ምስሎች እና ሥዕለ አድኅኖዎች የተለያዩ ኅብረ ቀለማት ይታይባቸዋል። እነዚህ የተለያዩ ቀለማት በጎንደር

ማኅበረሰብ እና በጎንደር ጥምቀት የተለየ መገለጫ ይኖራቸው እንደሁ አንድምታቸውን ለመረዳት ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራን ጠይቂያቸው ተከታዩን ሰፋ ያለ መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ቀይ፣ ብጫ፣ አረንጓዴ በአንድ ላይ ሲለበስ የኢትዮጵያ ባንዲራ[81] ነው፡፡ አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ዘጠኝ ላይ እግዚአብሔር አምላክ ኖኅን ዳግመኛ ዓለምን በንፍር ውሐ እንዳያጠፋው ‹‹እሠይም ቀስተየ በውስተ ደመና›› ብሎ በደመና ላይ ምልክት አሳያለሁ ቀይ፣ ብጫ አረንጓዴ ብሎ ለኖኅ የሰጠው ቃል ኪዳን ነውና የኢትዮጵያ ባንዲራ የኖኅ ቀስተ ደመና ነው፡፡ በአንድ ላይ ሲለበስ ቀይ፣ ቢጫ አረንጓዴ ይባላል፡፡ በተናጠል ቀዩ ሲለበስ ጃኖ ይባላል፡፡ በየብቻ ሲለበስ ለየራሱ ኹሉም ሸማ ይባላል፡፡ አረንጓዴ፣ ጃኖ ለብቻ፣ ቀይ ጃኖ ለብቻ፣ ብጫው ጃኖ ለራሱ ይኾንና ስሙ ጃኖ ይባላል፡፡ በአንድ ላይ ሦስቱ ሲገናኙ የኢትዮጵያ ባንዲራ ይሆናል፡፡ ቀይ፣ ብጫ፣ አረንጓዴ፣ ነጭ የዐራቱ የሥጋ ባሕርያት ምሳሌ ናቸው፡፡ አንዱ ነፋስ፣ እሳት፣ ውሐ፣ መሬት ነው፡፡ ቀዩ የሳት ምሳሌ ነው፡፡ የሰው ኀይሉ በእሳት ነው፡፡ እና የኀይል ምሳሌ ነው፡፡ እነ ዐፄ ቴዎድሮስ ኀያላን የኀይል መገለጫ ነው፡፡ እነ ዐፄ ቴዎድሮስ ለብሰው የሚታዩት የሚጠመጥሙት ጃኖ ነው፡፡ ከአራቱ ባሕርያት አንዱና ኀይለኛው እሳት ነው እሳት ደግሞ ሲያዩት ቀይ ነው፡፡ እና ቀዩ የእሳት ምሳሌ የጀግንነት፣ የኀይል ምሳሌ ስለሆነ እሱን ይለብሱታል፡፡ ብጫው የልምላሜ የመሬት ምሳሌ ነው፡፡ ነጩ የውሐ ምሳሌ ነው፡፡ እንደገና ወደ መንፈሳዊው ስንገባ ደግሞ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ለነፍሳችን ድኅነት እንዲኾን ተሰጥቶናል፡፡ ሥጋውን ሰጥቶናል፣ ደሙን ሰጥቶናል፡፡ ቀዩ የደሙ ምሳሌ ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

ከላይ የተሰጠው መረጃ እንደሚያሳየው በጎንደር ጥምቀት የሚለበሰው ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ ቀለማት ያላቸው አልባሳት በማኅበረሰቡ ዘንድ በርካታ ትርጉም አላቸው፡፡ ቀይ፣ ቢጫ አረንጓዴ በአንድ ላይ ሲለበስ ኢትዮጵያዊነትን ይተረጉማል፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት ከጎንደር ዐልፎ የኢትዮጵዊነት መገለጫ መኾኑን ያሳያል፡፡ ይህም ከውጭ የሚመጡት ቱሪስቶችና ጎብኚዎች በጎንደር ጥምቀት በመታደም ኢትዮጵዊነትንም እንዲዳሠሡ እና እንዲረዱ የማድረግ ዐቅም አለው፡፡

ሌላው ቀይ፣ ቢጫ አረንጓዴ አምላክ ዳግመኛ ምድርን ብንፍር ውሐ አላጠፋም የሚል ቃል ኪዳን የገባበት ምሳሌ ነው፡፡ ይህ ምሳሌ የይቅርይባነት ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመኾኑም በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ የጥምቀት ሰሞን በደል ቢኖር እንኳን ይቅር የማለትን ልማድ ያዘክራል፡፡ በዚህ መልኩ አረንጓዴ፣ ቢጫ ቀይ ቀለማት ያለበት ልብስ የሀገር እና ይቅርባይነት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህ መልኩ አረንጓዴ፣ቀይ ቢጫ ልብስ

[81] እሳቸው ባንዲራ ይበሉት እንጂ ሠንደቅ ዐላማ ለማለት ነው፡፡

በማኅበረሰቡ ውስጥ አንድም ሀገር ወዳድነት አንድም ይቅር ባይነት እንዲለመልም ያደርጋል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡

እነዚህ አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀይ ቀለማት በተናጠል ባላቸው ትርጉም የጎንደርን አካባቢና ጥምቀትን የሚገልጹ ሥጋዊና መንፈሳዊ አንድምታዎች አሏቸው አረንጓዴ የልምላሜና የተክል ዛፍ የደን ምሳሌ ነው፡፡ በዚህ ምሳሌ መሠረት የጎንደር የጥምቀት መውረጃ ቦታ አብያተ ክርስቲያናትና የነገሥታቱ መናገሻዎች በደን የተሸፈኑ ናቸው፡፡ ወጣቶቹ ይህን መልበሳቸው ቤተ ክርስቲያኗ ለደን ያላትን ትኩረት የሚያዘክር ነው፡፡ ሌላው ቢጫ ነው ቢጫ የአበባ እና የተስፋ ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ የጥምቀትን በዓል የሚያከብረው ቀጣይ የተሻለ ጊዜና ተስፋ በመሠነቅ ነው፡፡ እነዚህ ተስፋዎቹን በመያዝ በየ ዓመቱ የጥምቀትን በዓል ያከብሩታል፡፡ ሌላው ቀይ ጃኖ[82] ነው፡፡ ይህ ጃኖ የጎንደር ማኅበረሰብ ከጀግንነት ጋራ አያይዞ የሚመለከተው ነው፡፡ መረጃ ሰጭዬ እንደሚያስረዱት የጎንደር ነገሥታት ዐፄ ቴዎድሮስን ጨምሮ ቀይ ጃኖ ይለብሱ ነበር፡፡ ጃኖ የጅግንነት፣ ወጣትነትና የጉብዝና ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እንደዚሁም ሌላው ነጭ ልብስ ሲኾን ይህ ልብስ በጥምቀት ከጠብና ከጥላቻ ነጻ መሆንን የሚያስረዳ ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡

የጎንደር ማኅበረሰብ የጃኖ ምልክት ያለበትን ባህላዊ ልብስ ገና ከሕፃንነት ጀምረው ልጆቻቸውን እያለበሱ የማሳደግ ባህል አላቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ወጣት ደረጃ ላይ ሲደርሱ በራሳቸው ፈቃድ ጃኖ በመልበስ የጥምቀትን በዓል የሚያከብሩ የአካባቢው ወጣቶች ብዙ ናቸው፡፡ በዚህ ጃኖ ሃይማኖታቸውን፣ ጀግንነታቸውን፣ ዕሴታቸውን እና ፍልስፍናቸውን ያስቀጥሉበታል፡፡

[82] አገር በቀል ዕውቀቶች እና ማንነት መገለጫ በሚለው ንኡስ ርእስ ላይ በይበልጥ ተብራርቶ ቀርቧል፡፡



*(የጎንደር ወጣቶች ጃኖ በመልበስ የጥምቀትን በዓል ሲያከብሩ የሚሳይ 2013 ዓ.ም.)*

በሌላ መልኩ እነዚህ ቀለማት መንፈሳዊ አንድምታም አላቸው፡፡ ቀዩ የኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ ተሰቅሎ ለሰው ልጆች ድኅነት የሰጠውን እና የከፈለውን ዋጋ የሚያመላክት ነው፡፡ ነጩ ልብስ ደግሞ የውሐ የጥምቀት ምሳሌ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴና ቀይ የአራቱ ባኅርያተ ሥጋ ምሳሌዎች እንደኾኑ ያስረዳሉ፡ በመኾኑም በጥምቀት ዕለት የሚለበሱት የቀለማት ኅብር የጎንደርን ማኅበረሰብ አንድነት እምነት፣ ዕሴት እና ፍልስፍና የሚያሳዩ ማኅበራዊ ፋይዳዎች አሏቸው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ 15/11/2011 ቃ.መ፣ እማሆይ ጠጋ ደጀን 03/13/11 ቃ.መ)፡፡

## 6.2. ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚነገሩ ታሪኮች እና አንድምታቸው

በዚህ ሥር ስለ ጎንደር ጥምቀት እና ስለ ነገሥታቱ የሚነገሩ አፈ ታሪኮች ግንኙነት፣ አንድምታ እና ማኅበራዊ ፋይዳዎች፣ ስለ ጥምቀት ክብረ በዓል የሚነገሩ ሃይማኖታዊ ታሪኮች አንድምታዎች እና ማኅበራዊ ፋይዳዎች እና ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚነገሩ የሚት ትረካዎች አንድምታ እና ማኅበራዊ ፋይዳዎቻቸው የሚሉት ነጥቦች ተተንትነው ቀርበውበታል፡፡

### 6.2.1 ስለ ጎንደር ጥምቀት እና ነገሥታቱ ግንኙነት የሚነገሩ ታሪኮች (narratives)[83] እና ማኅበራዊነት

የጎንደር ጥምቀት ከማኅበራዊ ፋይዳው አንዱ የማኅበረሰቡን ታሪክ ዘክሮ ለትውልድ የሚያስተላልፍ በዓል መኾኑ ነው፡፡ በዓሉ ታሪክን ለትውልድ የሚያስተላልፈው ጥምቀት በጎንደር እንደዚህ ነበር፤ በእነዚህ ይከበር ነበር፤ እነ እከሌ በዚህ መልኩ ያከብሩት ነበር እና መሰል የነበሩ እና ያለፉ ታሪኮችን እያነሣ ለትውልዱ በማስታወስ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ሌላው የጎንደር ጥምቀት ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው እንደተባለው "ነገሥታቶቹ ክተት ሰራዊት፣ ምታ ነጋሪት" ብለው እንደ ዐዋጅ የሚደግፉት ነበር፡፡ ይህንን ሊቃውንቱን ግብዣ የሚጋብዙት ኹሉን ነገር የሚያደርጉት ነገሥታቶቹ ነበሩ፡፡ ከነገሥታቶቹ ከአባቶቹ የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የሀገር መሪዎች ራሱ እንደ ሀገር መሪ እንደፖለቲካ ሳያዩት እንደ ታሪክ እንደ ቅርስ አውርደው ለትውልዱ ሰጥተዋል፡፡ ዛሬ ምንም የታሪክ መሸዋወድ፣ የታክ ምዝበራ፣ የታሪክ ስርቆት፣ የአሻራ ስርቆት ቢኖርም እንኳ ይህ ታሪክ የማይሰረቅ ነው፡፡ ጎንደርነትን የጎንደርን ታሪክ የጎንደርን ባህል ሰርቆ መውሰድ አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ባህሉ የሚዳሠሥ ስለሆነ፡፡ ባህሉ ወደ ትውልዱ ወርዶ ኹሉም ትውልድ ከእነዚህ፣ ከእነዚህ ከሕፃናቹ ጀምሮ እያንዳንዱ በቅብብሎሽ እያስተላለፈው ያለው ታሪክ ነውና የጎንደር ጥምቀት በዚህ የሚገለጽ አይደለምና ይህን ይመስላል በኔ በኩል (መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ 19/01/12)፡፡*

ከላይ የተጠቀሰው መረጃ የጎንደር ጥምቀት በነገሥታቱ ዘመን በምን መልኩ ይከበር እንደነበር የሚያዘክር ነው፡፡ ከዚህ በመነሣት የጎንደር ጥምቀት በነገሥታቱ ዘመናት ከማኅበራዊ እና ሃይማኖታዊ በዓሉ ባሻገር የሀገሪቱ የመንግሥት በዓል እንደ ነበር ያስረዳል፡፡ የመንግሥት በዓል በመኾኑ ነገሥታቱ "ክተት ሰራዊት፤ ምታ ነጋሪት" ብለው ያከብሩት ነበር፡፡ ይህ ክተት ሰራዊት እና ምታ ነጋሪት የሚለው ቃል በዓሉ መንግሥታዊ በዓል እንደ ነበር አረጋጋጭ ነው፡፡ ይህ ትረካ በጥምቀት ክብረ በዓል እና በመንግሥት መካከል የነበረውን መስተጋብር እንደ ታሪክ ነጋሪና መስካሪ ኾኖ ያገለግላል፡፡ በአለፉት ዘመናት ሃይማኖት፣ መንግሥት እና ሕዝብ የነበራቸውን መስተጋብር ለአኹኑ ትውልድ በማስተላለፍ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ይህን በተመለከተ አባ ገብረ ሥላሴ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ጎንደር በአብዛኛው ክርስቲያን ነው፡፡ ከነገሥታቱ ጥንካሬ የተነሣ ጥምቀቱም ከዚያ ጀምሮ የደመቀ ኾነ፡፡ የነግሥታቱ ቀናኢነትና ጥንካሬ ከዚያ ጀምሮ ጥምቀት በዓል በእግዚአብሔር ፈቃድ እየደመቀ መጣ፡፡ እንደ ምሳሌ ዐፄ ኢያሱን ብንወስድ ታቦት እስከመሸከም የደረሱ*

[83] "History" የሚለውን ቃል የሚመለከት እንዳልሆነ ለመጠቆም ነው እንግሊዘናውን የተጠቀምኩት፡፡ አንድም ትረካ የሚለውን ቃል ላላመጠቀም ነው ታሪክ የሚለውን ቃል የመረጥኩት፡፡

*ንጉሥ ናቸው። ጻደቁ ዮሐንስም ሰሌን ሠርተው ለምግባቸው የሚጠቀሙ ጻድቅ ናቸው፤ ከሚገበረው አይደለም የሚጠቀሙት፤ የሚገበረውን ለሕዝቡ ነበር የሚያውሉት። ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ማኅበረሰቡን አካባቢውን ቀርጸውታል። ከዚህ ተነሣ ኹሉም የዚህ ተሰጥኦ ስላለው የጥምቀት በዓል እየደመቀ፣ እየደመቀ፣መጥቷል። ሊቃውንቱም የአቋቋም፣ የቅዳሴ፣ የቅኔው በተለይ የአቋቋሙ 24 ሰዓት ቢጮኹ ቢጮኹ አይደክሙም። በዚህ መልኩ ጥምቀቱን የጎላ ያደርገዋል (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)።*

ከዚህ መረጃ የምንረዳው የጎንደርን ነገሥታት የአገዛዝ ሥርዓት ከሃይማኖቱ እና ከጥምቀት በዓል ጋራ የነበራቸው ቁርኝት ጥብቅ መኾኑን ያጸናል። በወቅቱ እንደነጻድቁ ዮሐንስ ያሉ የጎንደር ነገሥታት ሥልጣነ ክህነት የነበራቸው እና ራሳቸውን ዝቅ አድርገው የሚኖሩ እንደነበሩ ለአኹኑ ትውልድ ያስረዳል። ሥልጣነ ክህነት ካላቸው ነገሥታት መካከል ዐፄ ኢያሱ ተጠቃሽ ናቸው። ዐፄ ኢያሱ ከንግሥና ዐልፈው ታቦት ይሸከሙ እንደ ነበር እና በጎንደር ጥምቀት ታቦት በመሸከም ጭምር ያገለግሉ እንደነበር መረጃው ያረጋግጣል። የጎንደር ሥልጣንና ቤተ ክህነት የሚቀራረቡበት ምክንያት ጎንደር የሊቃውንት ሀገር ስለሆነች በዚሁ ክፍል ውስጥ የተማሩት ግለሰቦች የኹለቱንም ተግባር እና ሃላፊነት የሚወስዱ መሆናቸው ነው። በዘመኑ ጎንደር የዕውቀት ማእከል እንደ ነበረችም መረጃው ያስረዳል። በዚህ ኹኔታ ከቤተ ክህነት የመጡት ነገሥታት ለቤተ ክርሲቲያን ቅርብ ስለነበሩ በጥምቀት በዓል ታቦት በራሳቸው፣ ቃጭል በጥርሳቸው ተሸክመው ያገለግሉ ነበር (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)።

ከጎንደር ነገሥታት መካከል ጻድቁ ዮሐንስ በዘመነ ንግሥናቸው ከቤተ ክርስቲያን እና ከማኅበረሰቡ የሚሰበሰበውን ግብር ለመንግሥት ማስኬጃ እንጂ ለራሳቸው ፍጆታ አይጠቀሙም ነበር። ንጉሡ ለራሳቸው ፍጆታ የሚሆን በዘመኑ ከነበረው የገቢ ምንጭ አንጻር ሰሌን ሰርተው ጭራ ቆንነው በመሸጥ ይተዳደሩ ነበር (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)። የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል የነበረውን ታሪክ ለአኹኑ ትውልድ በመንገር ሕዝባቸውን የሚወዱ ገዢዎች እንዲገኙ ያስተምራል። የአኹኑ ሹማምንት ለካ እንዲህ ያለም ነበር ብሎ ራሱን ቆም ብሎ እንዲፈትሽ እድል ይሰጣል። ጻድቁ ዮሐንስ ከስሙ እንደሚያመለክትው የጻድቅነት ክብር ሊያገኙ የቻሉት ሕዝባቸውን እና አምላካቸውን በማክበራቸው ነው። ከማኅበረሰቡ የተሰበሰበውን ግብር ለግል ፍጆታ አለ ማዋላቸው የዚህ ማረጋገጫ ነው። በመሆኑም የጎንደር ጥምቀት እነዚህን ጠቃሚ ታሪኮች በመዘከር እና በመንገር ትውልዱ እንዲማርበት ያደርጋል። ከዚህ ላይ የሚያሣየው ከመነሻው ከታሪካዊ አመጣጡ ጀምሮ

የጎንደር ጥምቀት፣ የጎንደር ነገሥታት፣ የጎንደር አብያተ ክርሲቲያናት እና የጎንደር ቤተ መንግሥታት የማይለያዩ ሥሪቶች በመኾናቸው አንዳቸው ሲነሡ የአንዳቸው ሐረግ ዐብሮ የሚመዘዝ መኾኑ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የጎንደርን ጥምቀት ታሪክ በመዘከር እና በማስተማር ከፍተኛ ፋይዳ አለው፡፡ ይህን በተመለከተ የጎንደር ጥምቀትና የጎንደር ነገሥታት ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል የሚለውን ጥያቄ ለአባ ገብረ ሥላሴ አቅርቤላቸው ተከታዩን ማብራሪያ ሰጥተውኛል፡፡

> *ጉልሕ የሚያደርገው አንደኛ አቀራረጹ ከአጤ[84] ፋሲል ጀምሮ 17ቱ ነገሥታት ዐብረው ቀርጸውታል፡፡ ተውልድ መሪውን ይመስላል፡፡ መምህሩ ከጎበዘ ተማሪውም እንደዚያው ነው፡፡ እነዚያ ነገሥታት ከቀረጹት ጥምቀተ ባሕሩን፣ አብያተ ክርስቲያናቱ እነ ቁስቋምን፣ ደብረ ብርሃንን ስናይ የጎንደር ጥምቀት ከጥንታዊ አንሥቶ የጎንደር መገለጫ ኹኖ የመጣ ነው፡፡ ቤተ መንግሥቱ አብረው ከመንግሥታቸው በላይ ነበር የሚያዩት በዚህ በጣምራ ተመሠረተ ስለኾነ ኹሉም የኔባይነት እንዲሰማ አድርጎታል፡፡ ለዚህ ነው ጎንደር የሚለየው (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)፡፡*

የጎንደር ጥምቀት የጎንደር መገለጫ ነው ሲባል የጎንደር ታሪካዊ ትውፊታዊ፣ ሃይማኖታዊ እና ማኅበረሰባዊ ጉዳዮች በሙሉ በጎንደር ጥምቀት የሚዘከሩበት ማሕቀፍ መኾኑ ነው፡፡ ለዚህም በነገሥታቱ የተመሠረቱት እነ ደብረ ብርሃን ሥላሴ፣ ማንኪት እና ቁስቋም ለዚህ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ በጣምራ ተብሎ እንደተገለጸው ነገሥታቱ ቤተ መንግሥቱን እና ቤተ ክህነቱን ወይም ዙፋኑንና አርባ አራቱን በአንድ ላይ ያስኬዱ እንደነበር ያስረዳል፡፡

በዚህ ንቁ ተሳትፎ ነገሥታቱ በሕዝብ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነትን ከማግኘታቸው በተጨማሪ የእነሡ ታሪክና ጥሩ ሥራ እስካሁንም ድረስ በጎንደር ጥምቀት እየተዘከረ እንዲኖር አድርጎታል፡፡ ይህ የሚያሣየው ቤተ መንገሥትና ቤተ ክህነት የአንድ ሳንቲም ኹለት ገጽታዎች እንጂ ተነጣጥለው እና አንዱን ጥሎ አንዱን አንጠልጥሎ የሚደረግ ጉዞ እንዳልነበር ያሳያል፡፡

ስለሆነም የጎንደር ጥምቀት ለጎንደር ማኅበረሰብ ክብረ በዓል ማክበርና ሃይማኖታዊ ግዴታን መወጣት ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም ጥምቀት ሲነሣ አጠቃላይ የጎንደር ታሪካዊ አመሠራረት፣ እድገት፣ ኺደትና አኹን የደረሰችበት ኹኔታ ምን እንደሚመስል የሚያሣይ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ከሃይማኖታዊ ተግባሩ በተጨማሪ እንዴት የታሪክ ማኅደር ኹኖ ሊያገለግል ቻለ? የሚል ጥያቄ ለአባ ገብረ ሥላሴ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

[84] መረጃ ሰጪዩ ዐፄ ለማለት የተጠቀሙት ቃል ነው፡፡

*ይህ የጎንደር ጥምቀት በተለያየ ኹኔታ ከመንፈሳዊነቱ በስተጀርባ የጎንደር ጥምቀት እንደታሪክም ስናየው ደግሞ ነገሥታቶቹ አክብረውት ዘውዳቸውን ዝቅ አድርገው ታቦት አጅበው፣ ሰራዊቱ ታቦቱን ተንከባክቦ መንፈሳዊነት ማጥመቂያ፣ ቤተ መቅደስ፣ ባሕር ማጥመቂያ ሠርተው ባህሉን ጠብቀው የሚኼዱበት ኹኔታ ነበረ፡፡ አኹንም ያለው ያው ነው፡፡ ኹለተኛ ደግሞ የጎንደር ጥምቀት በተለያዩ አድባራት ነው የሚሸፈነው፡፡ ማለት ለምሳሌ የአደባባይ ኢየሱስ ዘንድሮ ጥምቀቱን አክብሮ ከኾነ ቀጣይ ደግሞ አመራሩ፣ አሠራሩ ወይ ባባጃሌ ተክለሃይማት ይውላል፡፡ ወይ በመንበረ መንግሥት እያለ አድባራቶቹ እንደ ዕቁብ እየተጣጣሉ በረከቱን የሚሳተፉበት እኔ እሠራ እኔ አደርግ እያሉ፡፡ በረከቱን የሚወስዱበት አለ፡፡ የጎንደር ጥምቀት ይኽ ብቻ አይደለም፡፡ #4ቱም አድባራት ላይ ከዚያ ላይም ደግሞ ሥናየው #4ቱ እንደ አንድ አድርገው ወይም ደግሞ እንደ ተወሰኑ አድርገው በአንድ ላይ አውርደው የሚያውሉበት ደሞ ትልቅ ትርጉም አለው፡፡ ከሌሎቹ ሀገራት ወይም ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት የጎንደር ጥምቀት ለየት የሚያደርገው ይህ ነው (መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ 19/01/12)፡፡*

ከላይ የተጠቀሰው መረጃ እንደሚያስረዳው የጎንደር ጥምቀት ለመድመቁ፣ ለመቀጠሉ፣ የቱሪስት መስሕብ እና ለዚህ አሁን ላለበት ደረጃ የደረሰው ባለው የመነሻ ታሪክ ነው፡፡ በጎንደር ጥምቀት ታሪክ ነገሥታት ዘውዳቸውን አውልቀው[85] ከታችኛው ማኅበረሰብ ጋራ ያከብሩት ነበር፡፡ በዚህ የታሪክ ማኅደር ውስጥ አሁንም ድረስ በከተማዋ ያሉ ተሿሚዎች የጥምቀትን በዓል ዝቅ ብለው ከምእመኑ ጋራ አብረው የሚከብሩበት የተለመደ ትውፊት እንዲኖር አድርጎታል (መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ 19/01/12)፡፡

ሌላው ነገሥታቱ የራሳቸውን የአስተዳደር ሥራ ሲሰሩ መንፈሳዊ ተግባርም ጭምር የሚካኼዱ መኾናቸው ነው፡፡ በዚህም ቤተ መንግሥት ሲያንጹ የመጠመቂያ ጥምቀተ ባሕርም አብረው ገንብተዋል፡፡ ይህ አካኼዳቸው መንፈሳዊና ሥጋዊ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ባህላዊ ዕሴቶች በጎንደር ጥምቀት እንዲጋመዱ አስችሏል፡፡

ይህ ዕሴት እስካሁንም ድረስ ቀጥሎ የጥምቀቱን ድግስ በየዓመቱ ቤተ መንግሥት መድኀኔዓለም፣ አባጃሌ፣ ፊት አቦ፣ እያሉ በየ ተራ የሚያስከብሩበት ዑደታዊ ትስስር አላቸው፡፡ በዚህም አንዱን ዓመት አንዱ ሲያስተዳድር ቀጣዩን ዓመት ደግሞ ሌላኛው ያስተዳድራል፡፡ በዚህ የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ የጥንቱ የአስተዳደር ሥርዐት ይከወናል፡፡ ይህ ትውፊታዊ ሥርዓት በየ አድባራቱ እና በየ ማኅበረሰቦቹ ዘንድ የኔ ባይነት ስሜት እንዲጎናጸፉ አስችሏል (መላከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ 19/01/12)፡፡

[85] ለጥምቀት ዕለት እንጅ ይህ ዘውድ አውልቆ፣ ዝቅ አድርጎ እና አደግድጎ ከምእመን ጋራ መዋል በነገሥታቱ ዘንድ በዋዛ የሚታይ ጉዳይ አልነበረም (መ/ር ዳዊት ስራው) ፡፡

ይህን በተመለከተ አቶ ጌትነት አመራን የጎንደር ጥምቀትና ጎንደር ያለው ታሪክ እስከምን ድረስ ነው? የሚል መጠይቅ አቅርቤላቸው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *የጎንደር ታሪክ እኮ አሁን የሚነገር አይደለም፡፡ የቆየ እኮ ነው፡፡ አያት ቅማንቶቻችን ናቸው ያቆዩን፡፡ እኛ ደግሞ እነሱ ያቆዩንን ይበልጥ ለማሻሻል ነው የኔ ወንድም፡፡ እነሱማ አስረክቡ እኮ ብዙ ብዙ ነገር አድርገው ኼዱ እኮ እነሱማ፡፡ የነሱን ምልክት አድርገው አሳይተው መሠረት ጥለው ኺደዋል ያን መሠረት እንዳይፈርስ ነው እኛ ማድረግ ያለብን፡፡ ጎንደርና ጥምቀት ትስስራቸው በዚያች ዕለት ከአባት ከእናታችን የወረስነው ስለኾነ በዚያች ዕለት ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ተባብሎ ሆ ብሎ ነው የሚኼደው ወደ ጥምቀተ ባሕሩ፡፡ አውራው እንደተነካ ንብ ማንም ገላጋይ የለውም ጥምቀት ኺድ የሚለው የለም በራሱ ፍላጎት በወኔ ከዓመቱ አድረስኝ እያለ ነው ተነስቶ የሚኼድ (ጌትነት አመራ 13/05/2011 ቃ.መ)፡፡*

ከላይ የተወሰደው መረጃ የሚያረጋግጠው የጎንደር ጥምቀት ከአባቶች የተወረሰ እና የቃል ኪዳን ዐደራ ያለበት መኾኑን ነው፡፡ የጎንደር ማኅበረሰብ ከአያትና ቅደመ አያት ለሚወረስ ታሪክ ይኹን ትውፊት ትልቅ ቦታ ይሰጣል፡፡ ከዚህ አኳያ የጥምቀት በዓል አከባበርና ሥርዓት ከጥንት ከአያት ቅድመ አያት የመጣ በመሆኑ አከባበሩም ያንኑ የጎንደርን የጥንቱን ሥርዓት በሚያሳይ መልኩ ነው፡፡ ለዚህም አለባበሱ፣ አደጋገሱ፣ አነጋገሩና መሰል የጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔዎች በየ ጊዜው የሚለዋወጡ ሳይኾኑ የጥንቱን የአባቶችና የእናቶችን ታሪክ በሚዘክር መልኩ ነው፡፡ መረጃው በዋናነት የሚያስረዳውም የጎንደር ጥምቀት እና የጎንደር ታሪክ ያላቸውን ዝምድና በጎንደር የሚገለጡ መኾናቸውን ነው፡፡ ስለኾነም "ከእናት አባቶቻችን በወረስነው መልኩ አውራው እንደተነካ ንብ ወጥቶ ማኅበረሰቡ ያከብረዋል" የሚል መረጃ አቶ ጌትነት አመራ ሰጥተውኛል፡፡ የጎንደር ጥምቀት ከእናት አባት የተወረሰ መሆኑ የጥምቀቱን የሕዝብ ብዛት፣ የክዋኔ ኹኔታ፣ የሆታውና የዝማሬውን መጠን፣ የጭፈራውን እና የክዋኔው ድምቀት እንዲቀጥል አስችሏል፡፡ አውራው የተነካ ንብ ከቀፎው አይቀርም፤ የጎንደር ጥምቀት ዕለትም ሰው ከቤቱ አይውልም፤ ሆ ብሎ ወጥቶ ነው የሚያከብረው፡፡ ይህ የአከባበር ሥርዓት ደግሞ ትናንት የመጣ ዛሬ የተጀመረ ሳይሆን ከጥንት ከአያት ቅድመ አያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ፣ የቆየ እና የተወረሰ ትውፊት መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ስለሆነም የጎንደር ጥምቀት የነገሥታቱን፣ የአስተዳደሩን፣ የማኅበረሰቡን፣ ዕሴት፣ ትውፊቱን እና ታሪኩን በመዘከር ያለው ማኅበራዊ ፋይዳ የጎላ ነው፡፡ በሌላ ጉዳይ ሊወቃቀሱ እና ሊነቃቀፉ ይችላሉ እንጅ በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ጊዜ ምእመኑ፣ ሊቃውንቱ እና ሹማምንቱ ስምሙ ናቸው፡፡ ይህ ስምምነት ዘላቂ ሊሆን የቻለበት

ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚተረከው የቆየ ታሪክ ነው፡፡ በመኾኑም የጥምቀት ክብረ በዓል ሹሙን ከሙስና፣ ምእመኑን ከጽሞና እና ሊቃውንቱን ከድንቁርና ይከላከላል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡

### 6.2.2. ስለ ጥምቀት ክብረ በዓል የሚነገሩ ሃይማኖታዊ ታሪኮች እና ማኅበራዊ አንድምታቸው

የጎንደርን ጥምቀት ከፍ ከሚያደርጉት መነሻ ምክንያቶች መካከል አንዱ የጥምቀት አመጣጥ ሃይማኖታዊ አንድምታ ነው፡፡ ይህን በተመለከተ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ቀጣዩን ሰፋ ያለ መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *በሕገ ኦሪት እግዚአብሔር የወደዳትና የመሰከረላት ስለኾነ ኢትዮጵያ ይከበራል በጥንታዊዉና በሕገ ወንጌሉ እንደተጻፈ ታቦታቱ እየወረዱ ድንኳን እየተተከለ ወንዙ እየተባረከ ሕዝበ ክርስቲያኑ በዓሉን እያከበረ ይገኛል፡፡ ሥርዓቱ ኹሉም ይከበራል፡፡ ታቦታት ይወርዳሉ፤ ለምን ይወርዳሉ ቢባል በመጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ ምዕራፍ ፫ እንደተጻፈው ኢያሱ እስራኤልን ይዞ ወደ ምድረ ርስት ወደ ኢየሩሳሌም ሲኼድ የዮርዳኖስ ወንዝ ተከፍሎላቸው በደረቅ ታቦታቱን ለተሸከሙ ካህናት ጸላቱን አስይዞ ነበር፡፡ ለማየ ዮርዳኖስ ትንቢት ተነግሯል፡፡ "ምንተ ኮንኪ ባህር ዘጉየይኪ ወአንተኒ ዮርዳኖስ ዘገባይከ ድኅሬከ" ዮርዳኖስ ወደ ኋላ ተመለስክ፤ ለምንድን ነው? ለምን ሸሸህ? መጀመሪያ በኢያሱ ዘመን ታቦቱ ወደ ወንዝ ወርዶ ዮርዳኖስ ሲሻገር ወንዙ ታቦቱን አክብሮ እንደተከፈለላቸውና በደረቀ እንደተሸገሩ የሚያጠይቅ ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

ከላይ የተጠቀሰው መረጃ የጥምቀት አመጣጥ ከሐዲሳት በፊት በዘመነ ኦሪት ትንቢት ይነገርለትና አንዳንድ ተግባራትም ይፈጸሙበት እንደነበር የሚያስረዳ ነው፡፡ በዚህም በዘመነ ኦሪት ኢያሱ የተባለ የእስራኤል ንጉሥ እስራኤላውያንን ከግብጽ ነጻ አውጥተው ይዘው ወደ ሀገራቸው በገበቡት ወቅት በዮርዳኖስ ወንዝ ተፈትነው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ኢያሱ ታቦታት ተሸክመው ይኼዱ ስለነበር ለታቦታቱ ሲል የዮርዳኖስ ወንዝ ሙላት በልክ ኾኖ መሻገራቸው ያለው ሃይማኖታዊ አንድምታ ነው፡፡ ይህ ሃይማኖታዊ አንድምታ አሁን እየተከበረ ላለው ጥምቀት እንደ ትውፊት ሁኖ ያገለግላል፡፡ ትውፊትነቱ ለታቦታቱ እና ለሰዎች የሚሰጥ ክብር ነው፡፡ ይህ ክብር አሁንም በጥምቀት ሥርዓት ላይ ከፍተኛ ማኅበረሰባዊ መከባበርን፣ መተሳሰብንና መተጋገዝን ፈጥሯል፡፡ ሕይወት አልባ የኾነው ውሐ ለፈጣሪው ያደረገውን መገዛት በመውሰድ የአሁኑ ማኅረሰብ ፈጣሪውን እንዲያውቅና እንዲያከብር እንደ መነሻ ኹኗል፡፡ ይህ የጥምቀት ታሪክ በኢያሱ ዘመን እስራኤላውያንን በማኅበር ከግዞት ወደ

ነጻነትና ወደ ምድረ ርስት አሸጋግሯል፡፡ እስከ ዮርዳኖስ መሻገሪያ ድረስ እስራኤላውያን በሥጋትና በፍርሀት ነበሩ፡፡ ከተሻገሩ በኋላ ግን እስራኤል ወደምተባለው ምድረ ርስት ገብተዋል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡

በመኾኑም የጥምቀት ክብረ በዓል ከጨለማ ወደ ብርሃን፣ ከግዞት ወደ ነጻነት፣ ከችግር ወደ ጥጋብ፣ ከባይታወር ወደ ቤተኛ የሚደረግ ሽግግር ነው፡፡ በዚህ ምክንያት በማኅበረሰቡ ዘንድ ጥምቀት የመዳን፣ ነጻ የመውጣትና የሐሤት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ እስራኤላውያን በአንድነት በኅብረት ያደርጉት የነበረው ጉዞ እና ወደ ሀገራቸው መመለስ ደግሞ ጥምቀት ከማኅበራዊ አንድምታ ጋራ ያለውን መስተጋብር ያሳያል፡፡ የኦሪቱ ኢያሱ የጎንደርን ቀሳውስት፣ ሊቃውንት እና ሹማምንት ሲወክል፣ እስራኤላውያን ደግሞ የጎንደርን ማኅበረሰብን ወክለው የቆሙ ናቸው፡፡ ኢያሱ ከእስራኤላውያን ጋራ የዮርዳኖስን ባሕር በሰላም ተሻግሮ ወደ ሀገሩ እንደገባ ኹሉ በጎንደር ጥምቀትም የጎንደር ሊቃውንት፣ ነገሥታትና ማኅበረሰብ ወደ ደስታ፣ ሐሤት እና ማኅበረሰባዊ ተግባቦት ይሸጋገራሉ (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡

ስለ ጥምቀት በኦሪት ዘመን ጀምሮ እየተነገረና ትንቢት እየተሰጠ መጥቶ በሐዲስ ኪዳን ትንቢቱ ተፈጽሟል፡፡ ይህ የተፈጸመው ትንቢትና የጎንደር ጥምቀት ያለውን መስተጋብር ለመረዳት ሊቀ ሊቃውንትን ዕዝራን ጠይቄያቸው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *በኋላ ግን መድኀኔዓለም ክርስቶስ ከድንግል ማርያም በድንግልና ተፀንሶ በድንግልና ተወልዶ፣ ያለ ዘርዐ ብእሲ፣ ያለ ሩካቤ፣ ያለ አባት ከድንግል ማርያም በነቱም ድንግልና ተፀንሶ፣ በነቱም ድንግልና ተወልዶ፣ በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ እንደሚጠመቅና ታቦቱ የወረደባት፣ ታቦቱ የተሻገረባት፣ ለአማናዊ ለእውነተኛው መድኀኔዓለም ክርስቶስ እንዲሁ መጠመቂያ የመጠመቂያ ወንዝ እንደምትኾን ትንቢት አስቀድሞ እንደተናገረ መድኀኔዓለም ክርስቶስ በዮርዳኖስ ተጠምቋል፡፡ ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን ታቦታቱን ወደ ወንዝ ይዛ የምትወርደው መድኀኔዓለም ወንዝ ወርዶ እንደተጠመቀ ዛሬም ጥምቀት በዓል ሲከበር ጽላቱ ይወርዳል፡፡ ኹለት ነገሮች አሉ፡፡ አንደኛ በዘመነ ኢያሱ የነበረው ኢያሱ ታቦቱን ጽላቱ ዮርዳኖስን ሲሻገር የተደረገ ታምር ስላለ ነው፡፡ ኹለተኛው ደግሞ ያለም ቤዛ፣ ያለም መድኀኒት ኢየሱስ ክርስተስ በዮርዳኖስ ወንዝ ስለተጠመቀ ከወንዝ ወርደን ከወንዝ አድረን በዓሉን የምናከብረው በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈው በኹለቱ ነገሮች ነው፡፡ በኦሪትና በሕገ ዐዲስ በኦሪት በእነ ኢያሱ በሕገ ዐዲስ በወንጌል ራሱ ባለቤቱ መድኀኔዓለም ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጥቶ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ዮርዳኖስ ተጠምቆ አብ የምወደው ልጀ ይህ ነው ብሎ ሲመሰክር፣ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ የሥላሴ አንድነት ሦስትነት የታየበት በዓል ነውና*

*ኢትዮጵያ ታቦቱንም ይዛ የምትወርደው ለዚህ ነው፤ ጥምቀቱን የምታከብረው ለዚህ ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)።*

የኢትዮጵያ፣ ብሎም የጎንደር ጥምቀት አከባበር የብሉያትና የሐዲሳት መነሻ አለው። ይህ መነሻ በኦሪት ለኢያሱ የተደረገለት ድኅነት ሲኾን በሐዲሳት ደግሞ ሲነገር የኖረው ትንቢት ተፈጽሞ ኢየሱስ ክርስቶስ የጥምቀትን ሥርዓት የሠራበት ነው። በዚህ ምክንያት መረጃው እንደሚያሳየን የጥምቀት አንድምታ ሰዎችና አምላክ በአንድ የተገናኙበት ዕለት ነው። በዚህ ዕለት ወልድ በማየ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ሲጠመቅ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል መጥቶ በወልድ ላይ ሲቀመጥና ከሰማየ ሰማያት "የምወደው ልጄ ይህ ነው" የሚለው ቃል ሲመጣ ሦስቱ ሥላሶች በአንድ የተገኙበትን ምስጢር ያዘክራል። ይህም ርግብ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌና ቃል ደግሞ የአብ ምሳሌ ከወልድ ጋራ የአደረጉት መገናኘት ነው።

በዚህ መገናኘት ውስጥ ማኅበረሰባዊ የኾነ ፍቅር እና ዕርቀ ሰላም የሚገኝበት ነው። በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት መነሻው ሃይማኖታዊ ሲኾን ስለ ሃይማኖታዊ አመጣጡ የሚደረገውና የሚነገረው ትረካ ማኅበራዊ አንድነቱ እንዲጠነክር፣ ፍቅር እና መተሳሰብ በሰዎች ዘንድ እንዲኖር ያደርጋል።

### 6.2.3. ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚነገሩ የሚት ትረካዎች አንድምታ እና ማኅበራዊ ፋይዳዎቻቸው

ስለ ጎንደር ጥምቀት ማኅበራዊ ግንኙነት መጠንከር ምክንያት አንዱ ስለ ጥምቀቱ የሚነገረው ሚት እና አፈ ታሪክ ነው። ከታሪኮቹ መካከል መለኮታዊ ቀርጽ፣ የነገሥታት አፈ ታሪክ፣ ጥንታዊነት እና ሚት መኾናቸው ነው። ይህን በተመለከተ አባ ገብረ ሥላሴ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *ጥምቀት በጎንደር ለየት ያለ ነው። ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። እግዚአብሔር የፈቀደውን ከፍ ያደርጋል። የጎንደር ጥምቀትም እንደዚህ ነው። በመጀመሪያ ከተማው ሲመሠረት በነማንና እንዴት እንደተመሠረተ መመልከቱ ተገቢ ነው። ጎንደር ማርና ወተት የሚፈልቅባት ተብሎ በፈጣሪ የተነገረላት አገር ናት። ዋናውየ መሠረቱ ይህ ነው። እግዚአብሔር አምላክ ለሙሴ ሕዝቤን ማርና ወተት ወደምታፈልቀው ወደ ከንዓን ምድር ይዘኽ ትገባለህ እንዳለው ኹሉ ጎንደርንም በቅዱሳኑ አማካይነት ማርና ወተት የምታፈልቅ ነች ብሎ ገልጿል። ማርና ወተት የተባለው ቀጥታ የሥጋ ሳይኾን ምግበ ነፍሱንም የሚጨምር ነው። ነፍስን የሚያለመልመው ቃለ እግዚአብሔር ነው* (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 *ቃ.መ*)።

ከላይ የተወሰደው መረጃ እንደሚያሳየው የጎንደር ጥምቀት ለየት ከሚልባቸው መልኮቹ አንዱ ቀደምት አንሥቶ እየተነገረና እየተተረከ የመጣው ታሪክ ነው። አባ ገብረ ሥላሴ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ደረጃ ከፍ ያለበትን ምክንያት ሲያብራሩ “እግዚአብሔር የፈቀደውን ያደርጋል” የሚል አምላካዊ መነሻ አላቸው። ይህ ቃል ማኅበረሰቡ የጎንደርን ጥምቀት እግዚአበሔር መርጦ ያላቀውና የመረጠው ነው ብሎ እንዲያምን አድርጎታል።

ጥምቀት ይዘቱና መነሻው ኢየሱስ ክርስቶስ በባሕረ ዮርዳኖስ መጠመቅ ነው። የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ጥምቀት በጎንደር ለየት ባለ መልኩ እንዲከበርና እንዲደምቅ ያደረገው ከእግዚአብሔር የተሰጠ ጸጋ ነው የሚል ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ምልኪያዊ ታሪክ አላቸው። ይህም ለጎንደር ጥምቀት እና ማኅበራዊ ትስስሩ መጎልበት የላቀ ፋይዳ አለው። ይህ ምልኪያዊ ቃል በአክባሪዎቹ ዘንድ አንድም አንዳች ክብር ይደረግልናል የሚል እምነት በልባቸው ውስጥ ያሳድራል፤ አንድም ቅጣት ያስከትላል የሚል ሥጋት ያጭራል። ኹለቱም ምክንያቶች ማኅበረሰቡ የጎንደርን ጥምቀት በመከባበር እና በመተሳሰብ እንዲያከብሩት የሚያደረጉ መደላድሎች ናቸው። ሌላው “ጎንደርንም በቅዱሳኑ አማካይነት ማርና ወተት የምታፈልቅ ነች ብሎ ገልጿል” የሚለው ቃል ነው። ይህ ቃል ጎንደር ከሌሎች አካባቢ የተለየችና የተመረጠች ቦታ እንደኾነች የሚያጸና ነው። ጎንደር ማርና ወተት የሚፈልቅባት ናት የሚለውን ዐረፍተ ነገር አባ ገብረ ሥላሴ ከምናውቀው ማርና ወተት ከፍ ያለ “ምግበ ሥጋና ምግበ ነፍስ” ነው በሚል ተርጉመውታል።

ምግበ ነፍስ እና ምግበ ሥጋ የሚለው ቃል ትርጉም የሚሻው በመሆኑ ለአባ ገብረ ሥላሴ ጥያቄ አቅርቤላቸው ተከታዩን ማብራሪያ ሰጥተውኛል። ምድራዊ ሕይወት የተባለው ከሕፃናት እስከ ዐዋቂ፣ ከሴት እሰከ ወንድ፣ ከወጣት እስከ ልጃ ገረድ በጥምቀት በዓል የሚሳተፉት ታዳሚዎች የሚደረግላቸውን ስኬት የሚተረጉም ነው። ከዚህ ላይ ወልዶ መሳምን፣ አሽቶ መቃምን እና መሰል ምድራዊ ስኬቶችን ይመለከታል። የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ የጎንደርን ጥምቀት በማክበሩ ይዞለት የሚመጣ መልካም በረከት እንዳለ ያምናል። ከእነዚህ በረከቶች መካካል ፈተና የማለፍ፣ ዐርሶ የማፈስ፣ ነግዶ የማትረፍ፣ ታግሎ የመጣል፣ ተይዞ የመንጠቅ ተሟግቶ የመርታት፣ ታስሮ የመፈታት፣ ዕድሎችን ማስገኘት ነው። በዚህ ምክንያት የጎንደር ጥምቀት እንደ ምግበ ሥጋ ተደርጎ ይወሰዳል (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)።

ሌላው ምግበ ነፍስ የሚለው ቃል ነው፡፡ ጎንደር ምግበ ነፍስ ናት ስትባል ከሥጋዊና ከሰዎች አእምሮ ራቅና ረቀቅ ያሉ ከኅሊና በላይ የኾኑ ዕሳቤዎችን የሚመለከት ነው፡፡ የነፍስ ጉዳይ ማኅበረሰቡ እንዲያስብ እና እንዲያንሰላስል፣ እንዲቀበል እና እንዲሰጥ ከሚያደርጉ ጉዳዮች አንዱ ነው፡፡ በመኾኑም በታሪኩ ውስጥ የጎንደር ጥምቀት የሚሰጠው ማር እና ወተት ከምግበ ሥጋ ዐልፎ ምግበ ነፍስ ነው ሲባል ያለውን ማኅበራዊ ቦታ ከፍ ያደርገዋል፡፡ በዚህ ታሪክ ውስጥ የጎንደርን ጥምቀት በማክበር ሰዎች የነፍስን ምግብ ያገኛሉ፡፡ በዚህ በፈቃደ እግዚአብሔር የመጣው የጎንደር ቅድስና እያደገ መጥቶ ነገሥታቱ ላይ ይደርሳል፡፡ ይህን በተመለከተ አባ ገብረ ሥላሴ ቀጣዩን መረጃ አክለዋል፡፡

> *ጎንደር መጀመሪያ "ወይነግሥ" የሚል ትንቢት ስለነበር ያ ትንቢት ነው፡፡ ከዐፄ ሱስንዮስ፣ ከዐፄ ፋሲል አባት ጀምሮ ከዚያም በፊት ይነገር ነበር፡፡ ትንቢቱ የተገለጠው ግን ለዐፄ ፋሲል ነው፡፡ በፈረሳቸው አማካይነት ከዚህ ቦታ ላይ ከጎመንጌ ተነስታ ቤተ መንግሥቱ ላይ ጠበል ነበር ከዚያ ላይ ፈረሷን አገኟት፡፡ ከዚያ ቦታ ባንታዊ አግኝተው ወይነግሥ የተባለችው ይቺ ነች አሏቸው፡፡ ሰባት ቀን ግብዣ አድርገው ባህታዊ አንድ ትልቅ ቦታ መጥተው ቤተ መንግሥቱ ከተሰራ በኋላም የመዝመም አቅጣጫ አሳይቶ ነበር፡፡ አባ ተስፋ ማርያም የሚባሉ አንድ ታላቅ ቦታ ባንታዊ መጥተው ቤተ መንግሥቱ እንዴት መጽናት እንዳለበት እነ ፊት ሚካኤል፣ ፊት አቦ እና እልፍኝ ጊዮርጊስ መተከል እንደለባቸውና በዚህም ቤተ መንግሥቱ ጸና፡፡ ማርና ወተት የተባለው ትንቢት እንዲፈጸም የወንጌል ተርጓሚ ወጡ ከዚያ በኋላ ጎንደር የሊቃውንት የአቋቋም፣ ቅኔ የትርጓሜ ማዕከል ኾነች፡፡ ከኹሉም በፊት የተሻለ በሃይማኖቱ የጸና ኾነ (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ.)፡፡*

ይህ መረጃ የጎንደርን ልዕልና የሚያዘክር ነው፡፡ ጎንደር ቀድሞ ትንቢት ተነግሮላታል የሚለው ቃል ለትልቅነቷ ሚዛን የሚደፋ ነው፡፡ "ወይነግሥ" የሚለው ትንቢት ቀድሞ እየተነገረ መምጣቱ በዚህ ማኅበረሰብ ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው፡፡ ስለ አምላክ "ይወርዳል፤ ይወለዳል" ቀድሞ በነቢያት ትንቢት ይነገር ነበር፡፡ ይህ ትንቢት ደርሶ አምልክ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ፣ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ሥርዓተ ጥምቀትንንና መሰል የሰው ልጆችን ድኅነት ሠርቷል፡፡ ስለኾነም የሚነገር ትንቢት ቀድሞ የተቈረጠለት በአምላክ ዘንድ የታቀደና የማይቀር እንደኾነ ይታመናል፡፡

ቀደም ብለው ዐፄ ሰርጸ ድንግል እና ዐፄ ሱስንዮስ፣ በእንፍራዝ የጉዛራን ቤተ መንግሥት ለማቆም ሞክረው ነበር፡፡ ይኹን እንጂ ትንቢት ተነግሮ፣ ዘመን ተቆጥሮ ስለ አልመጣ ቤተ መንግሥቱ ሊቆም እና ሊጸና አልቻለም፡፡ በመጨረሻ ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ የዐፄ ፋሲል ፈረስ ከጎመንጌ ተነሥታ ቤተ መንግሥቱ ላይ ካለው ጸበል ዐፄ ፋሲል አገኟት፡፡ በዚሁ ቦታ

ባኅታዊ ይኖሩ ነበር። እኒህ አባት ለዐፄ ፋሲል "ወይነግሥ" የተባለቸው ቦታ ይህች ነች አሏቸውና ትንቢቱ ተፈጽሞ የጎንደር ቤተ መንግሥት ጸንቶ ቆመ። ቀድሞ ይነግሣል የሚለው ቃል ይነገር ስለነበር ትንቢቱን ተከትሎ እና ዘመን ተቀምሮ የመጣው የጎንደር ንግሥና በማኅበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ተቀባይነት አግኝቷል (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)።

ይህ ምልኪ እና አፈ ታሪክ የተቃየጡበት ንግር የጎንደር ጥምቀት፣ ነገሥታት እና የጎንደር አመሠራረት ከሰው ሳይሆን ከአምላክ ዘንድ የተሰጠ መሆኑን የሚያዘክር ነው። ለዚህም ማስረጃ ይሆን ዘንድ ትንቢት ተነግሮና ተቆርጦ የነበረና ትንቢቱ ደግሞ በሰው አእምሮ ብቻ ሳይኾን በፈረስ ጭምር ይገለጥ እንደነበር አፈ ታሪኩ ያስረዳል። ፈረስ የተመረጠበት ምክንያት የጎንደር ነገሥታት ለንግሥና እና ለጦር ሜዳ ውሎ ፈረሶችን ይጠቀምባቸው ስለ ነበር ነው። አንድም ፈረስ ከሰማዕታት ተጋድሎ እና ንግሥ ጋራ የተቆራኘ ክብር አለው። ፈረሷ በጎንደር ቤተ መንግሥት መገኘቷ የዚሁ ምሳሌ ነው። የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ በቅሎና ፍየልን የኀጥኣን፣ ፈረስን የቅዱሳን ተጋድሎ ማስፈጸሚያ እና በግን ደግሞ የጻድቃን ተምሳሌት አድርጎ ይወስዳቸዋል (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)።

በዚህ ምክንያት በፈረስ አማካይነት ትንቢቱ መፈጸሙንና የጎንደር ንግሥና መጀመሩ የጎንደርን ቅድስና ከሥጋዊ ወደ መንፈሳዊ ከፍታ ያወጣዋል፤ ሌላው የበቁት ባሕታዊ ናቸው። እኒህ ባሕታዊ በጎንደር ቀድመው መገኘታቸው የጎንደርን ቅድስና እና ንጽሕና ላቅ እንዲል ለማስቻል መንገድ አደላዳይ ናቸው። ከዚህ በመነሣት ማኅበረሰቦቹ የጎንደር ጥምቀት ከአርባ አራቱ ታቦታት ጋራ ተያይዞ የተቀደሰ ቦታ እንደኾነ እንዲያምኑ አድርጓል። ይህ የቅድስና እምነት የጎንደርን ጥምቀት ለየት እና ደመቅ ብሎ እንዲከበር አድርጎታል። በዚህ ቅዱስ ቦታ የሚከበረው ጥምቀት ማኅበረሰባዊ ፍላጎቱ፣ ቁሳዊ ይዘቱ እና መንፈሳዊ መሠረቱ ይጨምራል። በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ማኅበራዊ ትስስሩ እንዲጠብቅ እና መንፈሳዊ ይዘቱ እንዲጸና አስችሎታል።

የአካባቢው ማኅበረሰብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወደ ራሱ በመውሰድ "ሰው ቦታን ይቀድሳል፤ ቦታ ደግሞ ሰውን ይቀድሳል" የሚል ብሂል አለው። ይህ ብሂል ሰውና ቦታ የማይነጣጠሉ፣ አንዳቸው በሌላቸው የሚገለጹ መሆናቸውን ያስረዳል። በዚህ መልኩ ጎንደር ከፍ በማለቷ በውስጧ ያሉት #4ቱ አድባራትና የጥምቀት ክብረ በዓል ከፍ ይላል። በክብረ በዓሉ የሚሳተፉ

ምእመናንም ከፍ ያለ ክብር አግኝተው እንደተመለሱ ያምናሉ፡፡ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓልን በረከት ለማግኘት ማኅበረሰቦች ከተለያዩ ቦታዎች በመምጣት ቡራኬ አግኝተው መመልስ እንዳለባቸው ያምናሉ፡፡ በዚህም በጎንደር ጥምቀት የሚታደመው ማኅበረሰብ የሚያስበውና የሚመኘው ነገር ተደርጎልኛል ብሎ በማመን ተስፋ እንዲያደርግና ሕይወቱን ተረጋግቶ እንዲመራ ያደርጋል፡፡ ሌላው ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚተረከው ታሪክ የጎንደር ጥምቀት ኢየሱስ ክርስቶስ ከተጠመቀበት ዮርዳኖስ ጋራ ተፎካካሪነት አለው የሚል ነው፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ልዕልና ኀይለ መስቀል ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ከእስራኤል ሀገር ጋራ የምንመሳሰልበት አንደኛው ይህ ነው፡፡ ዮርዳኖስ ወንዝ ያለው እስራኤል ነው፡፡ ያንን ለመዘከር ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበትን ቦታና ዕለት በመዘከር እኛም ተመሳሳይ ወንዝ የሚመስል መዋኛ ማንም አገር መሰል መዋኛ ባልገነባበት ምንአልባትም ባላወቀበት ዘመን እኛ ገንብተናል፡፡ በዚህም ጥሩ ትስስር እንዲኖረን ያስችላል፡፡ ታሪካዊ ዳራው ጥምቀት የጌታችን የመድኀኒታችን የእየሱስ ክርስቶስን ያደረገውን መጠመቅ ማስታወስና መዘከር ነው፡፡ አስተምህሮ አለው፡፡ በጎንደር ጥምቀት በዓል ከዚህ ጀምሮ ተከበረ የሚባልበት የለም፡፡ ግን ከዐፄ ፋሲል ቀደም ብሎ እና ጎንደር በዐፄ ፋሲል ተጀመረ ተብሎ ስለሚታሰብ ከ1628 ጀምሮ ነው ጎንደር የሚያነሳው፡፡ ግን ጎንደር ከዚያ በፊትም የከተማ ቅጥ የነበራት አካባቢ ናት፡፡ ጎንደር ታሪካዊ ዳራዋ የተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሲራራ ንግድ ይካኼድባት ስለነበር ጎንደር ከዚያ በፊትም ከተማ ናት፡፡ ያኔም ጥምቀት ይከበር ነበር፡፡ የፋሲል መዋኛ መገንባቱ የጥምቀትን በዓል በጎንደር ይበልጥ አጎላው፡፡ ዕሴት ሰጠው (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011)፡፡*

ከላይ የተሰጠው መረጃ የጎንደር ጥምቀት ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበትን ዮርዳኖስን ተክቶ የቆመ እንደኾነ ተገልጿል፡፡ ክርስቶስ የተጠመቀበት ቦታ ዮር እና ዳኖስ በሚባሉ ኹለት ወንዞች መካካል ነው፡፡ እንደዚሁም የጎንደር ባሕረ ጥምቀት ደግሞ በቀሐ እና አንገረብ መንዞች መካካል ማንኪት በሚባለው ቦታ የከተመ ነው፡፡ የጎንደሮቹ ቀሐና አንገረብ፣ የእስራኤሎቹ ዮር እና ዳኖስ የተባሉት ወንዞች ተፈካካሪ ናቸው፡፡ የጎንደሩ ባሕረ ጥምቀት ማንኪት ደግሞ ክርስቶስ የተጠመቀበትን ዮርዳኖስን ይወክላል፡፡ ይህ የወንዞች እና የባሕረ ጥምቀት ተመሳስሎ የጎንደርን ጥምቀት ቅድስና እና ማኅበረሰባዊ ቅቡልነት ያስጠብቃል፡፡ አንድም በቅድስናው አንድም በማኅበረሰባዊ ቅቡልነቱ ምክንያት ወደ እስራኤል የሚያደረገውን ጉዞ ያስቀራል፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት የኅብረተሰቡን ድካም ከማስቀረቱ በተጨማሪ የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር በማድረግ ፋይዳው ላቅ ያለ ነው (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011)፡፡

ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚሰጠው ታሪክ በብዙ መልኩ የጥምቀቱን ክብረ በዓል እንዲያድግና ማኅበረሰባዊ ትስስሩ እንዲጠነክር የማድረግ ዐቅም አለው፡፡ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ተከታዮች የክርስቶስን ልደት፣ ጥምቀትና ስቅለት የተፈጸመባቸውን ቅዱስ ቦታዎች ለማየት እና በረከት ለማግኘት ረጅም ጉዞዎችን ያደርጋሉ፡፡ የጎንደር ጥምቀተ ባሕር ዮርዳኖስን እንዲተካ ኾኖ መሠራቱ የነበረውን የጉዞ ወጭ እና ድካም ቀንሶለታል፡፡ አኹን አኹን ማኅበረሰቡ ወደ ጎንደር ጥምቀት ሲመጣ ዮርዳኖስ እንደኼደ በማሰቡ ከፍ ያለ የማኅብረሰብ ትስስር እና የነፍስ ልዕልና እንዲሰማው አድርጎታል፡፡

በዚህም ማኅበረሰቡ ወደ ዮርዳኖስ በረከት ለማግኘት ሲኼድ የሚያወጣውን የጉልበት፣ የጊዜና የገንዘብ ወጭ ያስቀራል፤ በምትኩ ጎንደር በማኅበረሰባዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ እድገት እንዲነቃቃ ያደርጋል፡፡ የጎንደር የጥምቀት የዮርዳኖስ ወንዝ ነው የሚል እምነት በማኅበረሰቡ ልቦና ውስጥ በመሥረጹ ምክንያት ከዓመት ዓመት ማኅበረሰባዊ ትስስሩ እንዲጠነክር አድርጓል፡፡ ስለኾነም ስለ ጎንደር ጥምቀትና ስለጎንደር ቦታ የሚደረገው የታሪክ እና የሚት ነገራ የጥምቀቱን ክብረ በዓል ከፍ ከማድረጉም በላይ ፈርጀ ብዙ ማኅበረሰባዊ ጠቀሜታዎች በሀገር ውስጥ እንዲመጡ አስችሏል፡፡ የጎንደር ጥምቀት ድምቀት እና ማኅበራዊ ትስስር ጥንካሬ የሚቀዳው ከቦታው አቀማምጥ፣ ከሚነገረው ታሪክ፣ ከነገሥታቱ እና አርባ አራቱ አድባራት ታሪክ እና ከባሕረ ጥምቀቱ ቦታ ነው፡፡ ቀድሞ በትንቢት የመጣ እንደኾነ የሚነገረው ትውፊታዊ ታሪክ የጎንደርን ጥምቀት ከፍ እንዲል እና ማኅበረሳባዊ ተግባቦቱ እንዲጠነክር አስችሎታል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት፡- የጎንደር ጥምቀት ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ እና አንድምታው

የጎንደር ጥምቀት በዋናነት ፎክሎራዊ የሆኑ የባህል አልባሳት ንግድ፣ የባህል መጠጥ ቤቶች ንግድ፣ የምግብ ቤቶች ንግድ፣ የእደ ጥበባት ንግድ፣ የባህል ቁሳቁሶች ንግድ፣ የባህላዊ ጭፈራዎች ፌስቲባል እና በንዋየ ቅድሳት ሽያጭ ምጣኔ ሀብቱ የሚደገፍበት ወቅት ነው፡፡ ከፎክሎራዊ ንግዶቹ በተጨማሪ የሴቶች ውበት ሳሎን ንግድ ንግድ በጥምቀት ሰሞን ከወትሮው የተለየ ገቢ የሚያስገኙ ናቸው፡፡ የፎክሎር ገበያ የማይነጥፍ እና ሁለንተናዊ ከመኾኑ በተጨማሪ በገንዘብ ከሚሰላው በላይ የባህል ስሌቱ ስለሚበልጥ ይህ ምዕራፍም በዋናነት በፎክሎራዊ ንግዶች በሚመሠረተው ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ ላይ ትኩረት ሰጥቶ ተጠንቷ፡፡

### 7.1. በጥምቀት ክብረ በዓል የባህል አልባሳት ንግድ እና ምጣኔ ሀብት

የጎንደር ጥምቀት በዕደ ጥበባት፣ በጥልፍ፣ በሽመና፣ በስፌት፣ በባህላዊ አልባሳት በቀሚስ፣ በመብሩቅ፣ በመቀነት፣ በሸማ፣ በጃኖ እና መሰል ባህላዊ ውጤቶችን በመሸጥና በመግዛት ትልቅ ምጣኔ ሀብታዊ ማኅበረሰብ ይፈጥራል፡፡ ጥምቀትን አስመልክቶ የሚደረገው የገበያ ትስስር የሃይማኖትን፣ የብሔርና የእምነት አብሮነትን የሚያጠናክር ነው፡፡ በዚህ ገበያ ውስጥ ሙስሊም፣ ክርስቲያን፣ አማራው፣ ትግራይው፣ ቅማንቱ፣ ቤተ እስራኤሉና ሌሎችንም የማኅበረሰብ ክፍሎች የጋራ ጥቅምና ትስስር የሚፈጥሩበት ነው፡፡ ይህን የጎንደርን ገበያ የባህል አልባሳት ትሰስስር በተመለከተ አባ በሪሁን አካላትን ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ *"የጎንደር ገበያ የሚደራው በጥምቀት ነው፡፡ ነጭ እጀ ጠባብ፣ ነጭ ሸሚዝ፣ ጎንደር ደስ የሚልህ በጥምቀት ዓመት በዓል አበባ መስሎ ነው የሚወጣ፡፡ የአገር ባህል ነው የሚለብሱ ቱሪስቶች ሲመጡ ባህሉን ነው የሚያዩ" ( አባ በሪሁን አካላት 11/11/2011)፡፡*

የጎንደር ገበያ ዓመቱን ሙሉ ካሉት ወቅቶች በጥምቀት ሰሞን ከፍ ያለ የገበያ እንቅስቃሴ መኖሩን የአባ በሪሁን መረጃ አመላካች ነው፡፡ የገበያ አንቅስቃሴው በምጣኔ ሀብተት ደረጃ የአንድ የሃይማኖት ተከታይን እና የአንድ ወገንን ብቻ የሚጠቅም አይደለም፡፡ ማንኛውም በዘርፉ የተሰማራ የኅበረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ውስጥ በጎንደር ጥምቀት ምጣኔ ሀብቱና ማኅበራዊ ትስሰሩ ዞሮ የሚገጥምምበት፣ ተፈላልጎ ሚቧደንበት ነው፡፡ ከሸማቃ ወይም ከሽመና ሥራ ጋራ በተያያዘ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ይበልጥ ዕውቀት

አለው። የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ባለው የሽማ ሥራ ዕውቀት እና የግድ እንቅስቃሴ ምክንያት በጎንደር ጥምቀት ሰሞን ላቅ ያለ የገበያ ተሳትፎ አለው (ሙሔ ሰዒድ 16/05/2012 ቃ.መ)። ይህን የሙሔ ሰዒድን መረጃ እና የእኔን ምልከታ በመጨመር ስለ ባህላዊ አልባሳት ንግድ እና ስለ ሙስሊሙ ማኅበረሰብ ለልዕልና ኀይለ መስቀል ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር። እሳቸውም ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ሽማ በመሸጥ ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋራ መቀራረብን በመፍጠር ትልቅ ፋይዳ አለው። በጎንደር ያሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች በጥምቀት ሰሞን በስራ ይጠመዳሉ ትልቅ የሆነ የገበያ ትስስር አለ። በተለይ በሽመናው፣ በጥልፉ፣ በጌጣጌጡ፣ በሆቴል የተሰማራው፣ የተለያየ እምነት ተከታይም ቢሆን እጅጉን የሚጠቀምበት ጊዜ ነው። በዚህም የጥምቀት በዓል እንዲነካባቸው አይፈልጉም። በዚህም ማህበረሰቡ እንዲቻቻልና አብሮ እንዲኖር ያደረገው ዋናው ጥምቀት ነው። እንደክርስቲያኑ ሁሉ የጥምቀት በዓል ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገር ማኅበራዊ ትስስርንም ስለሚፈጥር በዓሉን የጋራ ሀብት አድርጎ የመውሰድ የጋራ ስሜቱ አላቸው። ማኅበራዊ ትስስሩ የጎለበተ እንዲሆን ያደርጋል (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011)።*

ከላይ የተሰጠውን መረጃ ስንመለከት በጥምቀት ሰሞን የጎንደር ገበያ መድራት እና የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ተሳትፎ የላቀ መሆኑን አረጋጋጭ ነው። በተለይ የሽመና ሥራ፣ የጥልፍ ሥራ፣ የጥበብ እና የጥሩር ሥራ ላይ የሙስሊሙ ማኅበረሰብ ክፍል የሚያደርገው ግብይት ከፍተኛ ነው። ይህ የገበያ ትስስር ውጤት የጥምቀትን ክብረ በዓል የሙስሊሙ ማኅበረሰብ የሚሳተፍበት እና ገቢውን የሚያሳድግበት እንዲኾን አስችሎታል። በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት ምጣኔ ሀብት የሚለካው ግለሰቦች በሚከተሉት ሃይማኖት ሳይኾን ባለቸ ዕውቀት እና ጥበብ የሚመነጭ ነው። ይህ ደግሞ ሀገረሰባዊ ዕውቀትና ጥበብ እንዲያድግ እና የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ኹለንተናዊነትም ያረጋግጣል።

የጎንደር ጥምቀት የባህል አልበሳት አዛውንቶች፣ ሕፃኖች፣ ወጣቶች፣ እናቶች፣ አባቶች፣ ልጃ ገረዶች እና ዐልፎ ዐልፎም ቱሪስቶች ጭምር ለብሰውት ተመልክቻለሁ። ይህም የጎንደር የባህል አልበሳት ከባለቤቶቹ አልፎ የውጭ ሃገራትን ቀልብ እየሳበና እየተወደደ ያለ መኾኑን የሚያረጋግጥ ነው። በጥምቀት ክብረ በዓል እንደተመለከትኩት የውጭ ዜጎች የጎንደርን ጥልፍ ቀሚስ፣ መቀነት፣ ሻሽ ግዝተውና ለብሰው[86] ይታያሉ። መልበስ ብቻ ሳይሆን ከአናቶችና ከልጃ ገረዶች ጋራ አብረው ይጨፍራሉ (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/11 ቃ.መ.)፣ ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 እና ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን 12/05/13 ቃ.መ.)።

---

[86] ምዕራፍ ዘጠኝ የቱሪስት መስሕብ እና ፋይዳው በሚለው ላይ በፎቶ ተደግፎ ቀርቧል።

የልብስ ገበያው ከጥምቀቱ ቀደም ብሎ እስከ ጥምቀቱ ዕለት እና ከጥምቀት በኋላም ለአንድ ወር ያክል ይቀጥላል፡፡ በአረንጓዴ፣ በቢጫ እና በቀይ ቀለማት የተሠሩ የአንገት ፎጣዎች እና የጎንደር ጥልፍ ቀሚሶች በብዛት ይለብሳሉ፡፡ በ2013 ባደረግኩት ምልከታ በጥምቀተ ባሕሩ እና በፒያሳ አካባቢ ከጥምጣም አልፎ እንደ ኩታ ተለብሶ ተመልክቻለሁ፡፡ ወጣት ምስጋን ሞላ በባሕረ ጥምቀቱ ለብሶት አግኝቸዋለሁ፡፡ እኔም ስንት ገዛኸው? ለምን በጥምቀት ቀን እንደኩታ ለበስከው? የሚል ጥያቄ አቅርቤለት ነበር፡፡ እሱም *"የገዛኹት አንድ ሺህ አምስት መቶ ስልሳ ብር ነው፡፡ የሚሠራው ጎንደር እና በጣና ገዳማት አባቶች ናቸው፡፡ እኔም ይህን በጥምቀት ውድ ቢኾንም ለብሸ አገሬን አስተዋውቅበታለሁ፡፡ በጣም ነው ደስ የሚለኝ ይህን አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀይ ስለብስ (ምስጋን ሞላ 11/05/2013 ቃ.መ.)* የሚል መልስ ሰጥቶኛል፡፡





*(ምስጋን ሞላ እና ጠጁ ታምሬ ከግራ ወደ ቀኝ በጎንደር ጥምቀተ ባሕር 2013)*

በጥምቀት የሚሸጡት እና የሚለብሱት ባህላዊ አልባሳት ከገንዘብ ማስገኘት ዐልፎ ማንነትን ማሳወቂያ ናቸው፡፡ እነዚህ አረንጓዴ፣ ብጫ እና ቀይ ቀለማት የኢትዮጵያ ባንዲራ ሲኾኑ ከባንዲራውም ዐልፎ የበጎ ነገር የቃል ኪዳን ምልክቶች ናቸው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ

15/11/11 *ቃ.መ.*፤ ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 እና *ዲያቆን* ፍስሐ *መሥፍን* 12/05/13 *ቃ.መ.*)፡፡

የሰው ልጆች በኖሕ ዘመን አምላካቸውን አብዝተው ይበድሉ ስለነበር በንፍር ውሐ ቀጣቸው፡፡ ይህ ቅጣት ዳግመኛ እንዳይፈጸምና ምድርን በንፍር ውሐ እንዳላጠፋት በሰማይ ምልክት አደርጋለሁ ብሎ በመናገሩ በዝናም ወቅት የምናየው ቀስተ ደመና ከዚህ የመጣ ነው የሚል እምነት አለ፡፡ ቀይ፣ ቢጫ አረንጓዴ ቀለም ከሰንደቅ ዓላማ ባለፈም የሰው ልጆችና አምላክ ቃል ኪዳን መግባቢያ ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ይህ ቃል ኪዳን በማኅበረሰቡ ዘንድ ዳግመኛ አልጠፋም ብሎ የመረጋጋት፣ የመዳን እና የመንጻት ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 እና ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን 12/05/2013 *ቃ.መ.*)፡፡ የጥምቀትን ገበያ እና የባህል አልባሳትን ትስስር በተመለከተ ለአባ በሪሁን አካላት ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *የጎንደር ገበያ የሚደራው በጥምቀት ነው፡፡ ነጭ እጀ ጠባብ፣ ነጭ ሸሚዝ፣ ጎንደር ደስ የሚልህ በጥምቀት ዓመት በዓል አበባ መስሎ ነው የሚወጣ፡፡ የሀገር ባህል ነው የሚለብሱ፤ ቱሪስቶች ሲመጡ ባህሉን ነው የሚያዩ፡፡ አንዲት ሕንዳዊት[87] ቱሪስት ከመድረኩ ላይ ኾና ከእናቷ ጋራ ጨቅላዋን የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ ለብሳ ዐየቻት፡፡ ያች ልጅ የት እና የት ነው ያለችው መሰለህ፡፡ ያች ጨቅላ እንዲኸ፣ እንዲኸ ስትል ስታያት ስንቱን ሰው ሠንጥቃ መጥታ ዐቅፋ ሳመቻት፡፡ ቱሪስቶች ሲመጡ ቀሚስ ያለበሰውን አይወዱትም፡፡ ቱሪስቱ ሱሪ ለባሹን ትክ ብሎ አያየውም (በሪሁን አካላት 11/11/2011)፡፡*

የተለያዩ የባህል አልባሳት ነጭ እጀ ጠባብ፣ ነጭ ባት ተኹለት ወንዶቹ አባቶች፣ ወጣቶችና ሕፃናት የሚለብሱት ነው፡፡ የጎንደር ነገሥታት እና ይለብሱት የነበረ እንደዚሁም በባህል ጥልፍ ቀሚስ ደግሞ ልጃ ገረዶችና ወይዛዝርት አሸብርቀው ይወጣሉ፡፡ ይአቶ በሪሁን እንደሚያስረዱት ፈረንጆቹ የባህል ልብስ ቀሚስና መቀነት የለበሱት ሴቶች እንደሚማርኳቸው የሚገልጽ ነው፡፡ ለዚህ ማስረጃም የባህል ቀሚስ የለበሰችውን ሕፃን አግኝታ ያቀፈቻትና የሳመቻትን ሕንዳዊት በምሳሌነት ያነሣሉ፡፡ በመረጃ ሰጭየ ግንዛቤ ሕንዳዊቷ የተማረከችው በሕፃኗ ቀሚስ አለባበስ፣ በጭፈራዋ እና በጎንደር መዋቢያ በማጌጧ ነው፡፡ እነዚህ ከውጭ የመጡ ቱሪስቶች የሚማረኩት በጎንደር አገርኛ ውበት፣ ከአለባባስ እስከ አመጋገብ፣ ከአጨፋፈር፣ እስከ ሥነ ሥርዓትና ግብረ ገብነት ኹሉ በሚከወኑት የጥምቀት ክዋኔዎች እንደኾነ አባ በሪሁን አከላት በቃለ መጠይቁ ነግረውኛል፡፡ በዚህ መልኩ

[87] *መረጃ ሰጭዎቸ ቱሪስቶቹን ፈረንጅ እና ሕንዳዊ እያሉ የሚጠሩበት ሁኔታ አጋጥሞኛል፡፡ ዋናው ጉዳይ ከውጭ የመጡትን ቱሪስቶች ለመግለጽ ስለሆነ ለመግባባት አልተቸገርኩም፡፡*

የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ለሸማ ሠሪዎች፣ ሸማ ሻጭዎች እና ሸማ ጠላፊዎች ከፍተኛ የሆነ የገቢ ምንጭ ያስገኝላቸዋል፡፡ አቶ ደሴ እምሩ በሽመና ሥራ የሚተዳደሩ ናቸው፡፡ ግለሰቡ ስለ ጎንደር ጥምቀት እና ሸማ ሠሪዎች ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

*በጥምቀት ሰሞን የሽመና ሥራ ወረፋው አይጣል ነው፡፡ በሸሚያ ነው የሚያሠራው በዚህ ሥራ ሰው የጥምቀት በዓል ሊደርስ ኹለት ወር ቀደም ብሎ ገበያው ይደራል፡፡ ከዚህ ቀን ጀምሮ ሸማ ሠሪዎች ሌሊት በመብራት ሳይቀር የሽመና ሥራ ሲሠሩ ያድራሉ፡፡ ቀለሙ፣ ድሩ፣ መህኑ፣ እና ዝሀው ሁሉ በጥምቀት ሰሞን ይፈለጋል፡፡ የሽመና ሥራው ይህን ኹለት ወር ይዞ እስከ የካቲት ሦስት ወር ድረስ ምንም አይል (አቶ ደሴ እምሩ 03/06/12 ቃ.መ)፡፡*

በጥምቀት ሰሞን ሸማ ሠሪዎች ከዕለት ጉርሳቸው ዐልፈው የዓመት ልብሳቸውን እና የዓመት ቀለባቸውን የሚከስቡበት ጊዜ ነው፡፡ የጎንደር አካባቢ ሸማ ሠሪ በጎንደር ጥምቀት ሰሞን በሰክሰክ *ሥራ*[88] አማካኝነት፣ ከወገራ፣ ከፎገራ፣ ከደራ፣ ከበለሳ፣ ከእብናት፣ ከቋሊሳ፣ ከመቀጣዋ፣ ከከምከም፣ ከሊቦ፣ ከውዶ፣ ከእንፍራዝ እና ከመሰል ቦታዎች ጭምር በመምጣት ሸማ ይሠራሉ (ደሴ እምሩ፣ 12/05/2012 *ቃ.መ*)፡፡ የጎንደር ጥምቀት በሽመና *ሥራ*ው በጎንደር ሸማኔዎች ብቻ የተገደበ አይደለም፡፡ ደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብ ጎንደር፣ ሰሜን ጎንደር፣ ማእከላዊ ጎንደር የሚኖሩትን ሸማኔዎች ኹሉ ተጠቃሚ ናቸው፡፡ ይህን በተመለከተ የሱፍ ወርቁ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

*የሱፍ ወርቁ እባላለሁ፡፡ የምኖረው መቀጣዋ ወረዳ አዲያ ቀበሌ ደረኮድ ጎጥ ነው፡፡ ታኅሣሥ ሲያብት ሸማቃዬን ጠቅልዬ ወደ ጎንደር ነው የምጠጋ፣ በዚህ ሰክሰክ ሥራ ምግብና መጠጥ ራሳቸው ችለው ያሠሩናል፡፡ ገበያው በየወቅቱ ይለያያል፡፡ ቢኾንም በዚህ ሰሞን ግን ከወትሮው ከነበረው ገበያ በእጥፍ ይገኝዋል፡፡ ዝኃውን፣ መበዘቂያውን፣ ቀለሙን፣ ጥለቱን ችለው እኛ እጅ ስራውን ብቻ ነው የምንሰራ ጋቢ፣ ቀጭን ኩታ፣ መቀነት፣ ነጠላና ሻሽ ነው፡፡ መቀነትና ቀጭን ኩታ ስንሰራ ብሩ ያክላል፡፡ ቀጭን ኩታው ጥበብ እና ጉብጉብ ከሆነ ደግሞ ብሩ እንኝርቅ[89] ነው፡፡ መቸም የዓመት ቀለቤን በእሦስቱ ወር ነው ይዠ እምመለስ ከወትሮው ይሻላል (የሱፍ ወርቁ፣ 03/05/12 ቃ.መ)፡፡*

መረጃ ሰጭዬ እንዳስረዱት ሰክሰክ ሠሪ የሚጠቀመው በዚህ በሰሙነ ጥምቀት ነው፡፡ ጥቅሙ በተለይ የጥበብ *ሥራ* የሚችሉ ሸማኔዎች መቀነት በብዙ ጥበባት እና ኩታ ደግሞ በጉብጉብ ስለሚሠራ ከፍ ያለ ገንዘብ ያስገኝላቸዋል፡፡ የጎንደር ማኅበረሰብ በጥምቀት ሰሞን፣ ጥሩር፣

---

[88] ደሴ እምሩ እና የሱፍ ወርቁ እንደነገሩኝ ስክሰክ *ሥራ* ማለት ሸማኔዎች አካባቢያቸውን ለቀው ኺደው የሽመና *ሥራ* ውድ ወደሆነበት አካባቢ በመኼድ ለተወሰነ ወራት የሚደረግ የሸማ *ሥራ* ነው፡፡ አኹን አኹን ግን የባህላዊ ልብስ ለባሽ ከጥምቀት ውጭ እየቀነሰ በመምጣቱ ሰክሰክ *ሥራ*ው እየተቀዛቀዘ መጥቷል፡፡

[89] በአካባቢው ማኅበረሰብ የተለመደ ቃል ሲኾን ትርጉሙም ትረፋማ እና ብዙ ማለት ነው (የሱፍ ወርቁ 2012 *ቃ.መ*)

ጉብጉብ እና ጥበብ ኩታ በውድ እየገዛ መልበሱ አንድም አምላክ ሰውን ከፈጠረበት ሰውን ያዳነበት ጥበቡ መብለጡን ለማዘከር፣ አንድም የጥምቀትን የማዳን ጥበብ ለማስታወስ ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011፡፡

የጎንደር የባህል አልባሳት ከሸማ ሠሪዎች ዐልፎ የባህል አልባሳት ነጋዴዎችንም በበምጣኔ ሀብቱ ያሳትፋል፡፡ የጎንደር የባህል አልባሳት ነጋዴዎች በተለይ ከእንፍራንዝ፣ ከደብረታቦር፣ ወረታ፣ ዐዲስ ዘመን እና መሰል ቦታዎች አልባሳትን በጅምላ በመረከብ ወደ ጎንደር አምጥተው የጥምቀት ሰሞን ይሸጣሉ፡፡ በጎንደር ከተማ የአዘዞ ገበያ መደብሮች፣ የአራዳ ገበያ አዳራሾች በርካታ የባህል አልበሳት ይሸጥባቸዋል፡፡ በጥምቀት ሰሞን ነጋዴዎች ከፍተኛ የኾነ የባህል አልባሳት ገበያ አላቸው፡፡

እንደ ሸማ ሠሪዎቹ ኹሉ ነጋዴዎቹም ከዓመቱ ገበያ ባልተናነሰ ጥምቀት ግም ግም ሲል ጀምሮ የጥር ወራት ገቢያቸው ይደራል፡፡ የጎንደር ጥምቀት ተሳታፊ ኹሉ በዐዲስ ልብስና በባህል ልብስ አሸብርቆ የመዋል ልምድ አላቸው፡፡ ይህን ተከትሎ የጥምቀት ተካፋይ እና አክባሪው ማኅበረሰብ የባህል ልብስ ሲገዛ ገበያው ይደራል፡፡ በዚህ ምክንያት ነጋዴዎች ትርፋማ ይኾናሉ (ወ/ሮ ሞሚና አሕመዴ 03/05/2012 ቃ.መ)፡፡

በሌላ በኩል በአራዳ ገበያ የወንዶች የባህል ልብስ ሰፊና ሻጭ የኾኑት አቶ ፋሲል በሪሁን እና በሥራቸው የሚገኙ ዐምስት ልብስ ሰፊዎች በመደብሩ ውስጥ በሥራ ተጠምደው አግኝቻቸዋለሁ፡፡ በጥምቀት ሰሞን በዚህ ቦታ ልብስ እሚሰፉ እና እሚያሰፉ ብቻ ሳይሆን እሚጠልፉና እሚተኩሱም ጭምር በጥድፊያ ሥራዎቻቸውን ሲያከናውኑ ተመልክቻለሁ፡፡ እንደዚኹም በተለያዩ የባህል ልብስ ስፌቶች ውስጥ በማኅበር፣ በማኅበር ኹነው እነሱን በሚገልጽ መልኩ ምልክቶች ያሉባቸውን የባህል አልባሳት የሚያሰፉ ደንበኞችን ተመልክቻለሁ፡፡ አቶ ፋሲል በርካታ የሕፃናት እና የዐዋቂ ልብስ ከመደብሩ ውስጥ በመሸጥ ላይ እያሉ ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኝነታቸውን ጠይቄቸው ነበር፡፡ እሳቸውም ከወቅቱ የገበያ ጥድፊያ ጋራ ተያይዞ ለዐጭር ቃለ መጠይቅ ፈቅደውልኛል፡፡ በዚሁ መሠረት ለአቶ ፋሲል በሪሁን በጥምቀት ሰሞን ስላለው የባህል አላባሳት ሽያጭ እና ግብይት ጥያቄ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም የጎንደር ጥምቀት ሰሞን ከፍተኛ የሆነ የባህል አልባሳት ግብይት መኖሩን ነግረውኛል (ፋሲል በሪሁን 04/05/12 ቃ.መ.)፡፡ የጥምቀት ክብረ በዓል ሰሞን ስለሚኖረው የገበያ ኹኔታ ለሊቀ ሊቀውንት ዕዝራ ላቀረብኩላቸው ቃለ መጠይቅ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

*ያን ጊዜ እደ ጥበባት ያላቸው ሸማ እሚሠሩ ሰዎች ገበያቸው እንዴት ነው ሐበሻው ፈረንጁ የሐበሻውን ልብስ እየገዛ ስለሚለብስ ዕጥፍ ይጨምራል፡፡ ባለ ሆቴሎች ዐልጋ ውድ ነው ያን ጊዜ አይገኝም፡፡ ብዙ ገቢ አለ፡፡ መጠጥ ምን እና በእውነቱ ሳስበው ለጎንደር ብቻ አይደለም፡፡ ለኢትዮጵያ በሙሉ የገቢ ምንጭ ነው፡፡ እንዲያውም እስካሁን ድረስ በዩኒስኮ ሳይመዘገብ[90] መቆየቱ ለነጋዴውም፣ ለገበሬውም፣ ለአምራቹም፣ ለሸማ ሠሪውም፣ ለመስቀል ወርቅ፣ ጌጣጌጥ ለሚሠሩ፣ ሸማ ለሚሠሩት፣ ለግብርና፣ ለቱሪዝም ለዚህ፣ ለዚህ ኹሉ የገቢ ምንጭ፣ የመሠረተ ልማት ነው፡፡ በዓሉ ሃይማኖታዊ በዓል ተደርጎ ብቻ መወሰድ የለበትም፡፡ መስሕብነት ያለው ማን ነው መባል አለበት፡፡ ዓለማቀፋዊነት ያለው የቱሪስት መስኅብ ጥምቀት ኹለተኛ ገቢ የሚያስገኝ ማን ነው? መባል አለበት፡፡ በጥምቀት በዓል ኹሉም ክብር ያገኛል፡፡ ቤቶቹን ኹሉ ጥምቀት ነጻ ያወጣቸዋል፡፡ ቀለም ይቀባሉ፤ ይጸዳሉ፡፡ እንዲያውም የጎንደር ጥምቀት ምን ልበልህ ለኹሉም፣ ለኹሉም መሠረት ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

እንደ ሸማ ሠሪዎች ኹሉ የባህል ልብስ ሰፊዎችና ጠላፊዎችም በጎንደር ጥምቀት ኪሳቸውን የሚሞሉበት ወቅት ነው፡፡ *"የጎንደር ጥምቀት ሰሞን ልብስ ስፌትና ጠላፊ፣ ሸማኔ "ወፌ በረረች" ነው* (ደጉ አለቤ፣ 20/04/2012 *ቃ.መ*)፡፡ ደጉ አለቤን ያገኘኋቸው የወንዶች የባህል አልባሳት እየሰፉ ነው፡፡ የጎንደርን ጥምቀትና በባህል አልባሳት ላይ የተሰማሩትን፣ ነጋዴዎች፣ ሸማኔዎች፣ ልብስ ሰፊዎች፣ ጠላፊዎች ቀኑ ሳይታወቃቸው እንደሚመሽና ሌሊቱ ደግሞ ሳይታወቃቸው እንደሚነጋ አስረድተውኛል፡፡ እነዚህ ባለሞያዎች አንዳቸው ላንዳቸው ተደጋጋፊ በመኾን በባህል አልባሳት ከፍተኛ የሆነ ገቢ በጥምቀት ሰሞን ያገኛሉ፡፡ ሸማ ሠሪው የሠራውን ሸማ ነጋዴው ይረከበዋል፡፡ አንዳንዴም ራሱ ይሸጠዋል፡፡ ጥልፍ ጠላፊዎችም አንዳንዴም ተቀጥረው ሌላ ጊዜም ከነጋዴው፣ ከሸማ ሠሪውና ከልብስ ሰፊው ተረክበው በመጥለፍ አትርፈው ለተጠቃሚው ይሸጣሉ (ወ/ሮ ሞሚና አሕመዴ 03/05/2012 *ቃ.መ* እና ደጉ አለቤ፣ 20/04/2012 *ቃ.መ*)፡፡

የጎንደርን የባህል አልባሳት የአካባቢው ምእመን ብቻ የተገደበ አይደል፡፡ ለጉብኝት የመጡት ፈረንጆችም ጭምር እየገዙ ይለብሱታል፡፡ በተለይ ሴት ፈረንጆች የጎንደርን ጥልፍ ቀሚስ ከጥበብ መቀነት ጋራ በውድ ዋጋ ገዝተው በጥምቀቱ ክብረ በዓል የጎንደርን ወይዛዝርት መስለው ይውላሉ (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 *ቃ.መ*)፡፡ የባህል አልባሳት የጥምቀት ሰሞን በጎንደር ገበያዎች ውስጥ በስፋትና በብዛት በደራ መልኩ ይገበያያል፡፡ የባህል አልባሳት ከሱቅ መደብሮች በተጨማሪ በታየ በላይ ሆቴል፣ በዐፄ ቴዎድሮስ አየር ማረፊያ እና መሰል ለቱሪስት ምቹ በኾኑ ቦታዎች ጭምር በብዛት ይሸጣሉ፡፡ ይህን

---

[90] *ቃለ መጠይቁ የተደረገው የጥምቀት ክብረ በዓል በዩኒስኮ ከመመዝገቡ ቀደም ብሎ ስለነበር ነው፡፡*

የጥምቀት እና የባህል አልባሳትን ግንኙነት በተመለከተ *"ያለ ጥምቀት ልብስ የላቸው ያለ ፋሲካ ድግስ የላቸው"* ተብሎ ተተርቷል (ደጉ አለቤ 20/04/2012 *ቃ.መ*)፡፡ ይኸም በጥምቀት ሰሞን ያለውን የባህል አለባሳት ግብይት ድምቀትና ስፋት የሚያሣይ ነው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ በሰሙነ ጥምቀት የሚካሄደው የባህል አልባሳት ንግድ የጎንደርን ምጣኔ ሀብት በመደገፍ በኩል ብቻ ሳይሆን የጎንደርን ማንነት በመግለጥ እና በማስተዋወቅ በኩልም ወሳኝ ሚና አለው፡፡

## 7.2. በጥምቀት ክብረ በዓል የባህል መጠጥ ቤቶች ንግድ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ እና አንድምታቸው

በጎንደር ከተማ የጥምቀት ሰሞን ከፍተኛ የኾነ የመጠጥ ፍጆታ አለ፡፡ በዚህ ወቅት ባህላዊ መጠጦች ጠጅና ጠላ ከቤት አልፎ በየ አደባባይው ይሸጣሉ፡፡ በጎንደር ከተማ በተለይ በአዘዞ አካባቢ በዚህ ሰሞን በርካታ የጠላ ቤቶች ጥሩ ገቢ የሚያገኙበት ወቅት ነው፡፡ አንድ ጣሳ ጠላ በ7[91] ብር ሒሳብ ይሸጣል፡፡ አዘዞ አካባቢ በጠላ ሽያጭ የሚተዳደሩ ነዋሪዎች በርካታ ናቸው፡፡ ጧት፣ ጧት አዘዞ ኮረፌ ጠላ የሚሸጥባት ሲኾን ከረፋድ ጀምሮ ደግሞ ጥሩ ጠላ ይሸጣል፡፡ የጥምቀት ሰሞን ከገጠር አካባቢ የሚመጣው ማኅበረሰብ በርካታ በመኾኑ ምክንያት የጠላ ገበያ በሰፊው ይካኼዳል፡፡

በጎንደር ጥምቀት ሰሞን ዋናው እና ተጠቃሹ መጠጥ ጠጅ ነው፡፡ የጠጅ ቤቶቹ ከሚኖሩበት አካባቢ በተጨማሪ የጥምቀት ዋዜማ በባሕረ ጥምቀቱ አጠገብ ያሉ ቦታዎችን ተከራይተው ይሸጣሉ፡፡ በዚህ ወቅት ሽያጩም ቢኾን ከወትሮው የተለየ ነው፡፡ በ11/05/12 ዓ.ም ከባሕረ ጥምቀቱ ቀይቸ ይህንኑ የደራውን የባህል መጠጥ ለማጥናት ምልከታዬን ቀጠልሁ፡፡ በዚሁ ቀን ከምሽቱ 1፡00 አካባቢ ብዙ ጠጅ ቤቶችን ተዘዋውሬ ከተመለከከትኩ በኋላ ከአውቶፓርኩ በላይ ካለው ጠጅ ቤት ገብቸ ታዲሚያለሁ፡፡ ጠጅ ቤቱ ውስጥ ከጠጅ በተጨማሪ ብርዝ ይሸጣል፡፡ ለኔ አንድ ብርሌ ብርዝ ይዣለሁ፡፡ ቤቱ አልበቃ ብሎ ሰው ውጭ ላይ ተቀምጦ ይስተናገዳል፡፡ አዝማሪው ሁሉንም እያነሣሣ የጎንደርን ዘፈን እየዘፈነ በመጫወት ላይ ነው፡፡ በዚኽ ወቅት ባደረግኩት ምልከታ አንድ ጠርሙስ ጠጅ 80 ብር ይሸጣል፡፡ በብርሌ ደግሞ 40 ብር ይሸጣል፡፡ ይህን ተመልክቸ ለባለ ጠጅ ሻጭዋ ወ/ሮ ፀሐዬ ካሳ በ10/05/12 *ቃለ መጠይቅ* አድርጌላቸው ነበር፡፡ እሳቸው የዘወትሩን ገበያ ምን እንደሚመስል ዋጋውን

---

[91] ይህ መረጃ በተሰጠበት በ2011 ዓ.ም የነበረውን ነው፡፡ ቁጥሩ ከወቅት ጋራ የሚሄድ እንጅ ቋሚ አይደለም፡፡

ባይነግሩኝም ልዩነት እንዳለው ግን አጫውተውኛል፡፡ በቂ መረጃ ለማግኘት ካጠገቤ ካሉት ከነ ካሳው መኳንንት ከተባሉት ጎልማሶች ጋራ መጠያየቅ ጀመርኩኝ፡፡ እነ ካሳው እንዳስረዱኝ እና እንደነገሩኝ ከሆነ ዛሬ ዓመት በዓል ስለኾነ የደስደስ ነው ብለን እንጅ በዘወትሩ 40 ብር ነው የሚሸጥ ብለውኛል፡፡ በዚህ ጠጅ ቤት ውስጥ ማን እንደጋበዘ ሳይታወቅ ኹሉ እየዞረ የሚቀዳበት ኹኔታ ተመልክቻለሁ፡፡ ይህ ለምን ይኾናል ብየ ለነ ካሳው ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የጥምቀት ዕለት ድኀውም ሀብታሙም ደስተኛ እንዲኾን ነው የሚል መልስ ሰጥተውኛል (ካሳው መኳንንት 10/05/12 ቃ.መ)፡፡

ጠጅ የጎንደር መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል ጠጅ ከውሐ፣ ከብቅል፣ ከጌሾ እና ከማር ይዘጋጃል፡፡ ይህም የሰውን ባሕርያተ ሥጋ ይተረጉማል፡፡ ጠጅ የማር እና ጌሾ ውጤት መኾኑ ሰው የሰናይ እና እኩይ ግብር ውጤት መኾኑን ዘክራል፡፡ አንድም ጌሾው በዮርዳኖስ የተጣለውን የአዳምን እዳ ደብዳቤ ያዘክራል፡፡ ማሩ አንድም የጥምቀትን ጣፋጭነት፣ ምግበ ሥጋ፣ ምግበ ነፍስ መኾኑን ይተረጉማል፡፡ በማሩ የጌሾው ምሬት መወገድ እና የጠጅ መጣፈጥ እንዲኹም በጥምቀት የአዳም እዳ ደብዳቤ መደምሰስ እና ሰው ነጻ መውጣት ተፈካካሪዎች ናቸው፡፡ ማሩ አንድም የሊቃውንቱን ቃለ እግዚአብሔር ይተረጉማል፡፡ አንድም የነገሥታቱን ግብር የማብላት ርኅራኄ፣ አንድም ድሃ ተበደለ ፍርድ ጎደለ የሚለውን ፍትሕ ይተረጉማል፤ አንድም ጌሾው ደንበር ዘለሉን ከታች ባት፣ ከላይ አንገት የሚቀጡትን ያዘክራል፡፡ የጠጅ ተጥሎ መነሣት ደግሞ አንድም ትንሣኤ ሙታንን፣ አንድም ወድቆ መነሣትን፣ አንድም ተዋርዶ ክፍ ማለትን ይተረጉማል፡፡ ይህም ከዐፄ ኢያሱ፣ ከጻድቁ ዮሐንስ፣ ከዐፄ በካፋ እና ከዐፄ ቴዎድሮስ ተዋርዶ የመነሣት ንግሥና ጋራ ይፈካከራል፡፡ በመኾኑመ ጠጅ የጎንደር ማኅበረሰብ፣ ነገሥታት እና ሃይማኖት መገለጫ ነው (አባ ገብረ ሥላሴ 16/05/12 ቃ.መ)፡፡

በመኾኑም የጠጅ መጣል በጎንደር ከተማ ከጥንት ከነገሥታቱ ጀምሮ የነበረ እና የመጣ ነው፡፡ በነገሥታቱ ዘመን ለምስለኔው፣ ለጭቃው፣ ለንጉሡ፣ ለሊቃውንቱና ለመኳንንቱ እንደየ ተዋረዱ ጠጅ ተጥሎ በቤተ መንግሥቱ ግቢ ውስጥ ግብዣ ይደረግ ነበር፡፡ ግብዣው ከጦር ሜዳ ሲመለሱ እና እንደ ጥምቀት ባለ ክብረ በዓል ይካኼድ ነበር፡፡ ይህን ተከትሎ የጎንደር ጠጅ በጥምቀት ሰሞን በአዘዞ፣ በጠዳ፣ በማራኪ፣ በፒያሳ፣ በአራዳ አካባቢ በተጠናከረ ኹኔታ ይሸጣል (ካሳው መኳንንት 1005/ 2012 እና አባ ገብረ ሥላሴ 16/05/12 ቃ.መ)፡፡

አዘዞ አካባቢ ከአባታቸው ጀምሮ ጠጅ በመጣልና በመሸጥ የሚታወቁት ወ/ሮ ፀሐይነሽ ካሳ የጎንደርን ጠጅና ጥምቀት በተመለከተ ከፍ ያለ ቁርኝት ያላቸው መኾኑን ገልጸውልኛል። *"የሚጣለው ጠጅ አራት ዐምስት ዳቤ ማር፣ የጌሾው፣ የብቅሉ ድሮ በጋን እና በዕንጨት ደምበኛ ይጣል ነበር። በዚኽ የተጣለው ጠጅ አካባቢው አልባብ አልባብ ይሸታል" (ወ/ሮ ፀሐይነሽ ካሳ 12/05/12 ቃ.መ)።* ይህን *ታሪካዊ አመጣጥ* ተከትሎ አኹንም ድረስ ከደምቢያ፣ ከወገራ፣ ከማክሰኚት፣ ከሚካኤል ደብር፣ ከሎዛ አካባቢ መጥቶ የጎንደርን ጥምቀት ሲያከብር የዋለው የማኅበረሰብ ክፍል ጠጅ ቤት ገብቶ በጎንደር ጭፈራ ሌሊቱን ሙሉ እየጠጣ እና እየተጫወተ ያነጋል። በዚህ ጠጅ ቤት ያላቸው እና በጠጅ ንግድ የሚተዳደሩ የማኅበረሰብ ክፍሎች ጥሩ ገቢ የሚገኙበት ጊዜ ነው። በጥምቀት ክብረ በዓል ጠጅ በብዛት እና በውድ ስለሚሸጥ የጠጅ ሻጮቹ ገቢ ያድጋል። ከዚሁ ጎን ለጎን ደግሞ ባህላዊ የሆነው የጠጅ ሙያ እንዲቀጥል እና እንዲያድግ በማድረግም አስተዋፅዖ አለው (ካሳው መኳንንት 10/05/12 ቃ.መ እና አባ ገብረ ሥላሴ 16/05/12 ቃ.መ)።

### 7.3. በጥምቀት ክብረ በዓል የምግብ እና አልጋ ቤቶች ንግድ ምጣኔ ሀብት

ጎንደር ከታችኛው ሽሮ ቤት ጀምሮ ደረጃቸውን የጠበቁ ባለ ኮከብ ሆቴሎች የሚገኙባት ከተማ ናት። የሽሮ ቤቶች በጥምቀት ሰሞን ጥሩ ገበያ ያገኛሉ። በጥምቀቱ የሚሳተፈው ማኅበረሰብ ከሀብታም እስከ ድሐ በመኾኑ የታችኖቹን ሽሮ ቤቶች በዚያን ዕለት እንደ ዐቅሙ የጥምቀቱ ታዳሚ ይገዛቸዋል። በእነዚህ ሽሮ ቤቶች ምግብ ብቻ ሳይኾን ወለልም ጭምር በማከራየት የጥምቀት ሰሞን ገቢያቸውን ይደጉማሉ። *"በጥምቀት የጎንደር ሞያ የሚለካበት ዶሮ ወጥ በለው፣ ጠጁ በለው፣ ጠላው በለው የተለያዩ ምግቦች ነው የሚቀርቡ የጎንደር ባህላዊ ምግቦች ፈረንጆች ሲመጡ በጣም ይወዱታል። በቃ ፈረንጆች ሲመጡ በውነት እየሮጠ፣ እህ፣ እህ እያሉ ያን ለመቅመስ ይጓጓሉ" ጌትነት አመራ (13/05/2011 ቃ.መ)።*

በአዘዞ አካባቢ ባለ ሽሮ ቤት ሲኾኑ ዳቦ በመጋገርና በመሸጥ የሚተዳደሩትን ወ/ሮ አዳነች ደጀኔን በ11/05/12 ከጥምቀት መልስ ኹለት ልጆቻቸውን፣ ታናሽ እኅታቸውን እና አንዲት መድኀኒት የምትባል ጎረቤታቸውን ጨምረው በሥራ ተጠምደው ነው ያገኘኋቸው። ቤቱ በየ ዐይነት፣ ሽሮ ፈሰስ፣ እንጀራ በአዋዜ፣ እንጀራ በሰላሱት፣ እንጀራ በተልባ፣ እንጀራ በዕልበት፣ እንጀራ በስልጆ እና እንጀራ በዕርጎ ይሸጥበታል። ቤቱ አልበቃ ብሎ ታዛው ኹሉ በእንግዳ ተከቧል። ከታች ከላይ ይላሉ። እኔም ትንሽ ጊዜ ወስጄ መመልከትና ቃለ መጠይቅ

ማድረግ በመፈለጌ በቦታው ታድሜአለሁ፡፡ በዚህ ኹኔታ እየተመለከትኩኝ እንደቆየሁ ወጣት ኮተኞች፣ ሆታ ሲያወጡ የዋሉ ወደ ወ/ሮ አድና ቤት ገብተው ሲስተናገዱ መመልከት ችያለሁ፡፡ በዚህ ሁኔታ ወደ 12 ሰዓት ላይ ወ/ሮ አድና በየዓይነትና በአጠቃላይ የተዘጋጀውን ምግብ ሸጠው ጨረሱ፡፡

ለቃለ መጠይቁም ፈቃደኝነታቸውን ጠይቄ ይሁንታቸውን አግኝቻለሁ፡፡ እኔም የጥምቀት በዓል ከገቢያቸው ጋራ ያለውን ግንኙነት ጠየቅኋቸው፡፡ እሳቸውም እንደሚከተለው አስረድተውኛል፡፡ *"የጥምቀት ሰሞን የሚያጥረን ጉልበት ነው እንጂ ገበያው ውብ ነው፡፡ የያዝነው ኹሉ ይኼዳል፡፡ ያው አንድ ወቅት መኾኑ ነው እንጂ፡፡ አኹን እኽል ውሐውን ጨርሰን ባዶችን አንቀመጥም ማታ እንደ ዐቅማቸው ወለል የሚያድሩ እንግዶች ይመጣሉ" (ወ/ሮ አድና ደጀኔ 11/05/12 ቃ.መ)፡፡*

ይህ መረጃ የጎንደር ጥምቀት በትንሽ ዐቅም ለሚተዳደሩ ሽሮ ቤቶችም ጭምር ጥሩ የገቢ ምንጭ የሚያስገኝላቸው መኾኑን ያረጋግጣል፡፡ ምግብና መጠጥ ቢያልቅ እንኳን ወለል[92] ለማደሪያ የሚያከራዩበት ኹኔታም አለ፡፡ ጎንደር ከመካከለኛ ሆቴሎች ጀምሮ ደረጃቸውን የጠበቁ ባለ ኮከብ ሆቴሎች የሚገኙባት ከተማ ናት፡፡ በዚህች ከተማ ያሉ ሆቴሎች የጥምቀት ሰሞን ትልቅ ገበያ አላቸው፡፡ ሆቴሎቹ በከተማው ባህልና ቱሪዝም ተለይተው ከውስጥ እና ከውጭ ሀገር ለሚመጡ ለእንግዶች በጥሩ ዋጋ የሚከራዩበት ኹኔታ ብዙ ነው፡፡

ከሀገር ውስጥ ባለ ሀብቶች፣ ባለ ሥልጣናት፣ ምሁራን፣ ዘማርያን፣ ሊቃውንተ ቤተ ክርቲያን ጥምቀትን ለማክበር በጎንደር ይታደማሉ፡፡ እነዚህ ከሀገር ውስጥ የመጡ እንገዶች የጥምቀትን በዓል በሰላም ተስተናግደው እንዲኼዱ ሆቴሎቹ የምግብ እና የምኚታ አገልግሎት በመስጠት በኩል ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡ ሌላው የምጣኔ ሀብት ደጋፊዎች ከተለያዩ የአፍሪካ፣ የአውሮፓ፣ የአሜሪካ፣ የእስራኤል እና መሰል ሀገራት የሚመጡ ቱሪስቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ቱሪስቶች ከሀገር ውስጡ እንግዶች በተሻለና ከፍ ባለ ታሪፍ መሠረት የምግብና የመኝታ አግልግሎት ተጠቃሚ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት ሆቴሎቹ ከፍ ያለ ገቢ ያገኛሉ፡፡ በተለይ እንደ ፍሎሪዳ ሆቴል፣ ኤጅ ሆቴል፣ ታየ በላይ ሆቴል፣ ቋራ ሆቴል፣ ጎሐ ሆቴል፣ ዴን ማርክ ሆቴል ያሉት በጥምቀት ሰሞን ትልቅ የሆነ የምግብና የዐልጋ አገልግሎት የሚሰጡ ናቸው፡፡

[92] ዐልፎ ዐልፎ ካልኾነ በቀር ዘመድ አዝማድ ነው ሲጨፍርበት የሚያድር፡፡

የጎሐ ሆቴል ከቡልኮ ተራራ አናት ላይ የተገነባ በመሆኑ የጎንደርን ከተማ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡፡ እንደ ጎሐ እና ታዬ በላይ ያሉ ሆቴሎች የጎንደርን ባህላዊ ግንብ በሚያሳይ መልኩ በዕንቁላል ግንብ የታነጹ ናቸው፡፡ በእነዚህ ሆቴሎች ሀገረሰባዊ ጭፈራ፣ ሀገረ ሰባዊ ዳንስ እና ሀገረ ሰባዊ ዘፈን በጥምቀት ሰሞን ይታይባቸዋል፡፡ የጎንደርን ጭፈራ፣ እስክስታ፣ ዘፈን እና አጊያጊያጥ ለማየት ሲሉ ቱሪስቶች እነዚህን ሆቴሎች በጣም ይወዷቸዋል፡፡ በመኾኑም የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ባለ ሆቴሎቹ እና ባህላዊ ጭፈራ ተሳታፊዎቹ ከፍ ያለ ገቢ የሚያገኙበት ወቅት ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ፣ ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 እና ንጋቱ ችሎቴ 21/12/ 2011 ቃ.መ)፡፡

በጥምቀት ሰሞን የሆቴሎቹ ግብይት ከዘወትሩ በተሻለ መልኩ በመጠንም ሆነ በዋጋ ከፍ ያለ እንደኾነ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ባለ ሆቴሎች ዐልጋ ውድ ነው፤ ያን ጊዜ አይገኝም፡፡ ብዙ ገቢ አለ፡፡ መጠጥ ምን እና በእውነቱ ሳስበው ለጎንደር ብቻ አይደለም፡፡ ለኢትዮጵያ በሙሉ የገቢ ምንጭ ነው፡፡ ቤቶቹን ኹሉ ጥምቀት ነጻ ያወጣቸዋል፤ ቀለም ይቀባሉ፤ ይጸዳሉ፡፡ እንዲያውም የጎንደር ጥምቀት ምን ልበልህ ለኹሉም፣ ለኹሉም መሠረት ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

በጥምቀት ሰሞን ሆቴሎች ከዘወትሩ በተለየ ውድ በመኾናቸው ባለቤቶቹ ጥሩ ገቢ የሚያገኙ መኾኑን መረጃው ያረጋግጣል፡፡ “ቤቶቹን ኹሉ ጥምቀት ነጻ ያወጣቸዋል” የሚለው ዓረፍተ ነገር ምን ለማለት እንደሆነ ማብራሪያ እንዲሰጡኝ ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራን በ(15/11/2011) ጠይቄያቸው ነበር፡፡ እሳቸውም “*በጥምቀት ቀን አቧራ ለብሶ የነበረው ቤት፣ ተሰነጣጥቆና ወለሉ ነፍሎ የነበረው ኹሉ ወለሉ ይስተካከላል፣ ግድግዳው ይለሰናል፤ በዚህ ብቻ አያበቃም አቧራው ተራግፎ የሸረሪቱ ድር ጸድቶ ቀለም ይቀባል፡፡ በአጠቃላይ ይዋባል*” የሚል ማብራሪያ ሰጥተውኛል፡፡ ከእሳቸው ቃለ መጠይቅ እና ከአጥኚው ምልከታ በመነሣት ጥምቀት በአንድም ኾነ በሌላ መልኩ የገበያ ትስስሩ፣ የሥራ ዕድል ፈጠራው፣ የምጣኔ ሀብት ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው፡፡ በመኾኑም በጥምቀት ሰሞን ከምግብ እና ከዐልጋ ቤቶች በተጨማሪ የቤት ቀለም ሻጭዎች፣ የልስን ጭድና ጭቃ አቡኪዎች፣ ቤት ለሳኞች፣ ቀለም ቀቢዎች እና ዐናጺዎች ኹሉ ጥሩ ገቢ የሚያገኙበት ወቅት ነው፡፡

## 7.4. በጥምቀት ክብረ በዓል የሴቶች የውበት ሳሎን[93] ንግድ

የጎንደር ጥምቀት በንግዱ ዓለም ከፍተኛ እንቅስቃሴ ከሚታይባቸው መስኮች አንዱ የሴቶች የውበት ሳሎን ነው፡፡ ይህ የኾነበት ዋናው ምክንያት የጎንደር ጥምቀት በአብዛኛው ሴቶች አምረው የሚውሉበት ክብረ በዓል መኾኑ ነው፡፡ ሴቶች በተለይም ልጃ ገረዶች ዐምረውና ተውበው የሚውሉበት በዓል በመኾኑ በሴቶች የውበት ሳሎን ንግድ የተሠማሩ ግለሰቦች ከመቼውም በበለጠ ትርፋማ ይኾናሉ፡፡ እነዚህ የንግድ ቤቶች ጥምቀት ቀረብረብ ባለ ቁጥር ፋታ ያጣሉ፡፡ በዚህ ቀን ሥሬት ከሚሠሩት ባህላዊ አሠራርን ከሚከተሉት የገጠር ልጃ ገረዶች ውጭ የከተማውና ከዐዲስ አበባ አካበቢ የሚመጡት ልጃ ገረዶች በአብዛኛው ተኩስና የተለያዩ ቅርጾች ያለቸው የሥሬት ዐይነቶች ይሠራሉ፡፡

ከወንዶች በተለየ በጎንደር ጥምቀት ሴቶች ዐምረው የሚውሉበት ምክንያት ከግለሰቦች ከፍ ባለ መልኩ በተሰጣቸው ሀገራዊ እና ማኅበረሰባዊ ትእምርት ነው፡፡ የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ሴቶች አንድም የጎንደር፣ አንድም ኢትዮጵያ ተምሳሌት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ የጎንደር ማኅበረሰብ ደግሞ ከሀገሩ፣ ከርስቱ እና ከሚስቱ በላይ የሚኾንለት ያለ አይመስልም፡፡ እነዚህን ሀገርን፣ ርስትን፣ እናትን እና ሚስትን ወክለው የሚገኙ በመኾናቸው በጥምቀት ክብረ በዓል ለሴቶች የተለየ ክብር ይሰጣል፡፡ በመኾኑም የሴቶች መዋብ እና ማማር በማኅበረሰቡ ዘንድ ሙሉ በኩለሄ ነው ተብሎ ይታመናል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 11/15/11 ቃ.መ)

በጥምቀት ሰሞን በውበት ሳሎኑ ውስጥ ከጎንደሬ ሥሬት በተጨማሪ ማጠብ፣ መፈረዝ፣ መተኮስ እና ማድረቅ የመሳሰሉ ሥራዎች ይከናወናሉ፡፡ ባለ ሳሎን ቤቶች ለእነዚህ ተግባራት ተጨማሪ ባለሙያ ያስፈልጋቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ የጥምቀት ክብረ በዓል የሥራ ዕድል በመፍጠር ዐዳዲስ ባለሙያዎች እንዲቀጠሩ ዕድል ይሰጣል (ዐወቀ ዋጋው 03/06/12 ቃ.መ፤ ደጅይጥኑ ሥንቁ 18/05/12 እና ገዳሙ ዓለሙ 03/06/12 ቃ.መ)፡፡

---

[93]በጥምቀት ሰሞን በአብዛኛው የሚዋቡት ሴቶች ናቸው፡፡ በመሆኑም በሴቶች የውበት ሳሎን ጥድፊያ የሆነ ሥራ መኖሩን በምልከታዬ አረጋግጫለሁ፡፡ ይህ የሚያሳየው ሴቶች በጎንደር ጥምቀት የተለያዩ የጸጉር አሰራሮችን ተሠርተው ጥምቀቱን የሚታደሙ መሆናቸውን ነው፡፡ የወንዶች የጸጉር ቤቶች ከዘወትሩ ለየት ያለ ገበያ ቢኖርም የሴቶቹን የውበት ሳሎን ያክል የደራ አይደለም፡፡ በመሆኑም በጥናቱ የሴቶቹን የውበት ሳሎን ለትንተና ተመርጧል፡፡

ጥር 8/2012 ዓም በጎንደር ማራኪ ክፍለ ከተማ ቀበሌ ዐሥራ ስምንት በሚገኙ ሦስት የውበት ሳሎን ቤቶች ምልከታ አድርጌ ነበር፡፡ ምልከታ ባደረግኩበት ወቅት ከአለባቸው የሥራ ብዛትና ጥድፊያ የተነሣ ባለቤቶቹ ለኔ ጊዜ ሰጥተው ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ዕድል ባላገኝም ከውጭ የሚገቡትን እና የሚወጡትን መረጃ መጠየቅ እንደምችል ፈቅደውልኝ ነበር፡፡ ከእነዚህ በአንደኛው ውበት ሳሎን ሰልፍ ይዘው ወረፋ ከሚጠብቁት መካከል ተማሪ የሻረግ ታፈስን ቃለ መጠይቅ አድርጌላት ነበር፡፡ እሷም ተከታዩን መረጃ ሰጥታኛለች፡፡

> *ከዚህ የመጣኹት ጧት ሦስተ ሰዓት ላይ ነው፡፡ አኹን ዘጠኝ ሰዓት እየኾነ ነው፡፡ ሌሊት ነው ቀድመውኝ ተሰልፈው ያገኘኋቸው፡፡ ከውስጥ የሚሠሩት ብዙ ናቸው፡፡ ደንበኛ በመብዛቱ እስካሁን አልደረሰኝም አኹንም ብዙ ሴቶች አሉ፡፡ አስከ ምሽቱ ቆይቼ ነው የሚደርሰኝ፡፡ ከዚሁ ስንቃቃ ምሳም አልበላሁም፡፡ ወረፋው ሌሊቱን ሙሉ ነው፡፡ ጥምቀት ሲደርስ ከቤት የሚያደር የለም ግማሹ ጸጉሩን ሊሠራ ግማሹ፣ ጠላ ጠመቃ፣ ግማሹ እንጀራ ጋገራ፣ ጥድፊያ ነው፡፡ ውድ ነው የምንከፍለው ዛሬማ መቼ በደረሰኝ ነው እንጅ ለገንዘብ ማን ዐስቦ፡፡ እነሱም ዐይናቸው ቆርፍዶ እንቅልፍ አያየዩም፡፡ እኛስ ላንድ ቀን ነው፡፡ እነሱ ሳምንቱን ሙሉ (የሻረግ ታፈስ፣ 08 /05 /2012 ቃ.መ.)፡፡*

ከላይ የተወሰደው መረጃ በጎንደር ጥምቀት የሴቶች የውበት ሳሎን ያለውን የሞቀ ገበያ የሚያስረዳ ነው፡፡ በጎንደር ጥምቀት ከባህላዊ አልባሳት ቀጥሎ ሴቶች ከሚዋቡባቸው መንገዶች አንዱ የጸጉር አሠራርና አጊያጊያጥ ነው፡፡ በጥምቀት ዕለት ጸጉሯን ሳትሠራ ወይም ሳትተኮስ የምትውል ልጃገረድ ያለች አይመስልም፡፡ ይህ ኹሉ ጸጉር ተኩስ ደግሞ በጎንደር ከተማ በሚገኙ የሴቶች የውበት ሳሎን እና ባህላዊ ጸጉር አሠራሮች የሚከናወን ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ጥምቀት ቀረብረብ ሲል መረጃው እንደሚያስረዳን ልጃ ገረዶች እናቶችና ያገቡና ያላገቡ ሴቶች በጧት ተነሥተው እስከ ምሽት ድረስ ወረፋ ይጠባበቃሉ፡፡

በሴቶች ውበት ሳሎን ውስጥ አብዛኛው በሚባል ደረጃ የሚሠሩት የሚሳተፉት ሠራተኞች እና የውበት ሳሎኖቹ ባለቤቶች ሴቶች ናቸው፡፡ በጥምቀት ክብረ በዓል ሰሞን የውበት ሳሎን ገበያ መድራቱ ለሴት ልጆች ያለውን ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ ከፍ የሚያደርግ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የጥምቀት ክብረ በዓል ሰሞን በውበት ሳሎን ሴቶች የሥራ ዕድል ይፈጠርላቸዋል፡፡ ከሌላው ጊዜ የተሻለ የምጣኔ ሀብት ባለቤት እንዲኾኑ ያስችላል፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት በነጻነት፣ በምጣኔ ሀብት፣ በሥነ ልቡና እና መሰል ተሳትፎዎች ሴቶች እንዲበረታቱ ያደርጋል፡፡ የጸጉር አሰራሩም በአብዛኛው የጎንደር ልጃ ገረዶችን የሚገልጽ ነው፡፡ በአብዛኛው የውበት ሳሎን ከጸጉር ተኩሱ በተጨማሪ አፈሳሶ፣ አሳ ስሬት፣ ሳዱላ እና ጋሜ የሚባሉ ባህላዊ የጸጉር አሠራሮች ይተገበራሉ፡፡ ይህ ኹኔታ ከገንዘብ ማግኘታቸው

በተጨማሪ የጎንደርን  ባህላዊ የጸጉር አሰራር እንዲቀጥል ያስችላል፡፡ በጥምቀቱ ተሳትፎ ውስጥም ቢሆን ከወንዶች ላቅ ባለ መልኩ ለሴቶች የሚሰጠው እድል ሲታይ የጎንደር ጥምቀት ከፍ ያለ ድርሻ አለው (ቦሴ ውብሸት 28/11/11፣ የሻረግ ታፈስ፣ 08 /05 /2012 ቃ.መ. እና አክሊል አሰፋ 03/06/12 ቃ.መ.)፡፡

### 7.5. በጥምቀት ክብረ በዓል የእደ ጥበባት ባህላዊ ቁሶች ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ እና አንድምታቸው

በጎንደር ጥምቀት ምጣኔ ሀብቱ ከፍ ከሚልላቸው ግለሰቦች መካከል በእደ ጥበብ ሙያ የተሠማሩ ግለሰቦች እና ነጋዴዎች ናቸው፡፡ የብርና የወርቅ አንጥረኞች ሥራዎቻቸው በጥምቀት ሰሞን በጣም ይሸጣሉ፡፡ ዋጋቸውም ቢኾን ከዘወትሩ ዋጋ ከፍ ያለ ነው፡፡ የጎንደር ልጃ ገረዶች እና ወይዛዝርት የአንገት የብርና የወርቅ ጌጣጌጦች፣ ወይም ወርቅ መሰል ጌጣጌጦችን ለጸጉራቸው ማሠሪያ፣ ለጆሮ ጉትቻ፣ ለአንገት ማስጌጫ ይጠቀሙባቸዋል፡፡ እነዚህ ጌጣጌጦች በአልቦ መልክና በድሪ መልክ ከወረዳ የመጡ ሴቶች ይጠቀሙባቸዋል፡፡ አልቦ በእግር ቁርጭምጭሚት የሚገባ ሲኾን ያገቡ ሴቶች የሚያጌጡበት ባህላዊ ማስጌጫ ነው፡፡ የአገቡ ሴቶች አልቦ የማድረጋቸው ምክንያትና ከእግር ላይ መታሰሩ የትዳር ተምሳሌት ነው፡፡ የአገባች ሴት በሚኖራት የትዳር መምራት፣ የልጆች ማሳደግ ኀላፊነትን የሚገልጽ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የአገባች ሴት ያላት እንቅስቃሴ የተገደበና የተመጠነ መኾኑን ይተረጉማል (ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 ቃ.መ. እና አክሊል አሰፋ 03/06/12 ቃ.መ.)፡፡

አልቦ በአብዛኛው የሚሠራው ከብር ነው፡፡ ነጭ ቀለም ያለው ኹኖ እግር ላይ ውበት ይሰጣል፡፡ ብር የትዳርን ክብር የሚያመለክት ነው፡፡ ብር የከበረ ማዕድን እንደመኾኑ ትዳርም ትውልድን የሚያስቀጥል የከበረ ጸጋ ነው፡፡ ነጭ መሆኑ ደግሞ በትዳር መካከል መተሳሰብን፣ መተጋገዝን እና መታማመንን የሚያሳይ ነው፡፡ በመሆኑም የእደ ጥበባት ሥራዎች ከጌጣጌጥነታቸው ባለፈ የአካባቢው ማኅበረሰብ ዕሴት እና ሥርዓት ተምሳሌቶች ናቸው (ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 ቃ.መ.)፡፡ ከአንጥረኞች ተቀብለው የሚሸጡ ነጋዴዎች በጥምቀት ሰሞን ትልቅ የኾነ ገቢ ያገኛሉ፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ልዕልና ኀይለ መስቀል ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ከእደ ጥበብ ምርትና ሽያጭ ቅድም ያልኳቸውን ጌጣጌጦች ከመዳብ፣ ከብር፣ ከወርቅ የሚሠሩ ጌጣጌጦች እንደ ድሪ እንደ አልቦ ኹሉ በዚህ ወቅት ይሸጣሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ*

*ኹሉ አቅራቢዎቹ ተጠቃሚ ናቸው። ሌላው ሸቀጣ፣ ሸቀጥ ኹሉ በዚህ ወቅት ይሸጣሉ። ስለዚህ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ በጣም የሰፋ ነው (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011)።*

መረጃው እንደሚያስረዳው በጎንደር ጥምቀት የእደ ጥበባት ውጤቶች በብዛት እንድሚሸጡና በዚህም ለሻጭ ግለሰቦች የምጣኔ ሀብት ገቢ ያስገኙላቸዋል። በ11/05/13 በጥምቀት ዋዜማ ጀምሮ ታቦታት እስኪነሣ ድረስ የጥምቀቱን መመለሻ መንገድ ተከትሎ በርካታ የኾኑ ጌጣጌጦች ተዘርግተው ይሸጣሉ። ከእነዚህ መካካል እኔ ወደ ተወሰኑት ጌጣጌጥ መሸጫዎች በመቅረብ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ። ከእነዚህ መካካል ወጣት ብርሃ እሸቱ እና ወጣት ዘውዱ በየነ በ11/05/11 ዮብል አጠገብ ዘርግተው በአረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀይ የተሸመኑ ሸማዎችን፣ መስቀል ያለባቸው የአንገት ማተቦችን፣ መስቀል እና የእጣት ቀለበቶችን እየሸጡ አግኝቻቸዋለሁ። እነዚህ ወጣቶች ከላሊበላ ላስታ እንደመጡ እና በጌጣጌጥ መሸጥ እንደሚተዳደሩ አጫውተውኛል። ጌጣጌጦቹ በዋናነት በልደት ላሊበላ እና በጥምቀት ደግሞ ጎንደር ጥሩ የኾነ ገብያ እንደሚያገኙ አስረድተውኛል።

እነዚህ ቀለበቶች፣ መስቀሎች፣ አልቦ እና የድሪ ጌጣጌጦች በጥምቀት ሰሞን በሱቆች፣ በመንገድ ተዘርግተው እና በእንቅስቃሴ ይሸጣሉ። እነዚህ ጌጣጌጦች ወርቅ ቤት ወርቅ ፈላጊው፣ ብር ቤት ብር ፈላጊው እንደዚሁም በተለያዩ ቦታ መዳብ ፈላጊው ይሸምታቸዋል። በዚህ መልኩ የጌጣጌጦቹ ሥሪት ከወርቅ፣ ከብር እና ከመዳብ ነው። እነዚህ የወርቅ፣ የብርና የመዳብ ጌጣጌጦች የጎንደርን ማኅበረሰብ መዋቅር የሚተረጉሙ ናቸው። የጎንደር ማኅበረሰብ የሊቃውንት፣ የነገሥታትና የማኅበረሰብ ታሪካዊ መዋቅር ያለው ነው። እነዚህ የመዋቢያ ጌጣጎጦች፣ መቋሚያዎች፣ ጸናጽል፣ ከበሮና መሰል ንዋየ ቅድሳት ከወርቅ፣ ከብርና ከመዳብ ማዕድናት መሠራታቸው የጎንደርን የሊቃውንት፣ የነገሥታትና የሕዝብ መዋቅር ያሳያሉ ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 ቃ.መ)።

ወርቅ በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ የሊቃውንቱ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል። የጎንደር ማኅበረሰባዊ ሥሪት ለሊቃውንት የሚሰጠው ቦታ ከፍ ያለ ነው። ማኅበረሰቡ ሊቃውንቱ "እንዳሉት" የሚል አብነትን እየጠቀሰ የተጣላን ያስታርቅበታል፤ የሸፈተን ይመልስበታል። ሊቃውንቱን እና ካህናቱን አንድም የነገሮች መፍቻ ጠቢብ እንድም ከአምላክ የሚያገናኝ ቅዱስ አድርገው ይመለከቱታል። በዚህ ምክንያት ሊቃውንቱን በወርቅ መስሎ ያያቸዋል (ቄስ ደስታው አለሙ 15/05/12 ቃ.መ)።

ማኅበረሰቡ የወርቅን ባህርይ ለሊቃውንቱ በመስጠት ሊቃውንቱን ያነጽርበታል፡፡ ወርቅ መፈተን፣ ማለፍ እና መከበር ባሕርይው ነው፡፡ ሊቃውንቱም በረጅሙ መንፈሳዊ ትምህርት ውስጥ "በእንተ ስማ ለማርያም" ብሎ ዝካሪ እየለመነ ከውሻ ጋራ መፋለሙን ተፈትኖ ያልፋል፡፡ ወርቅ በእሳት ካልተፈተነ ወርቅነቱ አይረጋገጥም፤ ሊቃውንቱም በትምህርት ኺደት ካልተፈተኑ ሊቅ ለመሆን አይበቁም፤ በዚህ መልኩ የወርቅ እና የሊቃውንት መፈተንም፣ መከበርም ተፎካካሪ ናቸው፡፡ እነዚህ የጎንደር ሊቃውንት በማኅበረሰቡ ዘንድ የተከበሩ ናቸው፡፡ ክብራቸው ከአለባበሳቸው፣ ከአጠማጠማቸው እና ከቃለ እግዚአብሔራቸው ጋራ ስምሙ ነው፡፡ ወርቅ በጌጥ እና በፈርጥ ሰዎችን እንደሚያደምቅ ኹሉ ሊቃውንቱም በቃለ እግዚአብሔር ጎንደርን ያደምቃሉ፡፡ በዚህ መልኩ ወርቅ የሰው ማድመቂያ ሲኾን ሊቃውንት የእግዚአብሔር ዐይኖች ናቸው፡፡ ስለኾም የወርቅ ፈርጥ እና የሊቃውንቱ ቃለ እግዚአብሔር ተፎካካሪ ናቸው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/11 ቃ.መ. እና ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 ቃ.መ)፡፡

ሌላው የብር አንድምታ ነው፡፡ ብር በጎንደር ማኅበረሰብ የሹማምንቱና የነገሥታቱ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የብር ጌጥ ሰዎችን በማድመቅ አኳያ ከወርቅ ቀጥሎ የሚታይ ነው፡፡ ይህ በማኅበረሰቡ መዋቅር ውስጥ ያለውን መዋቅራዊ ቦታ ይተረጉማል፡፡ ከማኅበረሰባዊ አገልግሎት አኳያ የነገሥታቱም አስተዋፅኦ ጎንደርን በመገንባት፣ ማኅበረሰቡን በማገልገልና ሚናው የጎላ ነው (ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 ቃ.መ፣ ዳዊት ሥራው፣ (12/19/2011 ቃ.መ)፡፡

ሌላው መዳብ ነው፡፡ መዳብ ከወርቅና ከብር ቀጥሎ የሚመደብ የማዕድን ዐይነት ነው፡፡ በወርቅና በብር የሚሠራው ንዋየ ቅድሳትና ጌጣጌጥ በመዳብ ይሠራል፡፡ ንዋየ ቅድሳቱም በሚሰጠው አገልግሎት እኩል ነው፡፡ ከዚህ ላይ አንድ በወርቅ፣ በብርና በመዳብ የተቀረጸን መስቀል መውሰድ ምሳሌውን የሚያጸና ነው፡፡ ይህ መስቀል በዋጋ ውድነት የሚለይ ካልሆነ በቀር አጋንንትን በማባረር፣ ሕሙማንን በመፈወስ እና ኀጢአትን በማስተስረይ በኩል የመዳቡ መስቀል ከብርና ከወርቅ አያንስም፤ የወርቅ እና የብር መስቀልም ከመዳብ አይበልጡም፡፡ ሊቃውንት በዕውቀት፣ ሹማምንት በሥልጣን ተዋረድ እንጅ በማኅበረሰባዊ ጠቅላላ ሥሪት በኩል ከምእመኑ የሚበልጡበት መሠረታዊ ጉዳይ የለም፡፡ በዚህ መልኩ የወርቅ፣ የብር እና የመዳብ ንዋየ ቅድሳት ውክልናዎች የጎንደርን ማኅበረሰባዊ መዋቅር የሚያሳዩ ናቸው፡፡

በጎንደር ጥምቀት ለገበያ የሚያቀርቡት ንዋየ ቅድሳትና መጊያጊያጫዎች አብዛኛዎቹ ሥሪታቸው ከመዳብ ነው። በቀጣይ ደግሞ ብር ሲኾን ከዚያም ወርቅ ይከተላል። መዳብ አብዛኛውን የሕዝብ ቁጥር የሚይዘውን ምእመን የሚወክል ነው። ቀጣዩ ደግሞ ሹማምንቱ ሲኾን እንደዚሁ በብር ይወከላሉ። በመጨረሻ በማኅበረሰቡ ሥሪትና በአላቸው እና በሚጠይቃቸው የዕውቀት ልሕቀት ምክንያት ሊቃውንቱ በቁጥር አናሳ በተግባር ውድ በመኾናቸው ምክንያት ከወርቅ ከተሠሩት ንዋዬ ቅድሳት ጋራ ይፈካከራሉ (መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ 12/05/13፣ ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 እና መ/ር ዳዊት ሥራው፣ 12/19/2011 ቃ.መ)።

በዚህ ውክልና መሠረት በጎንደር ጥምቀት በእነዚህ ማእድናት የተሠሩ መጊያጊያጫዎችና የቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት በብዛት ይሸጣሉ። እነዚህን በመሸጥ በዚህ ንግድ ሥራ የተሰማሩ ግለሰቦች ጥሩ የሆነ ገበያ አላቸው። በጥምቀት ሰሞን የቆሎ ተማሪዎች ሳይቀር የአንገት መስቀል እና የጆሮ ጉትቻዎችን በመሸጥ የዕለት ጉርሳቸውን እና የዓመት ልብሳቸውን እንዲሸፍኑ ያስችላቸዋል። ስለኾነም ልጃ ገረዶቹና እማውራዎቹ የሚያጌጡባቸው የእደ ጥበባት ውጤቶች እንደ አልቦ፣ ድሪ፣ መስቀል፣ ቀለበት ጉትቻ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

እያንዳንዳቸው የሚሰጧቸውና የሚያስሯቸው ግለሰቦች ትልቅ ገበያ የሚያገኙበት ነው። እነዚህ መጊያጊያጫዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ የራሳቸው ትእምርት አላቸው። ትእምርትነታቸው ደግሞ ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታው ጋራ የሚፈካከር ነው። ሴቶች በአንገታቸው ለጌጥ ከሚያስሯቸው ማጌጫዎች መካከል መስቀል አንዱ ነው። መስቀል ከሃይማኖታዊ ይዘቱ በመነሣት በስደት ተስፋ አለመቁረጥን፣ በመከራ መጽናትን እና ችግር መቋቋምን ያስተምራል። በዚህ መልኩ ምጣኔ ሀብቱን ከመደገፍ ባሻገር የጎንደርን ማኅበረሰብ ጽናት እና ጥንካሬ የሚያስቀጥል ነው (ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 ቃ.መ)።

*“ሌላው ጉትቻ ነው። ጉትቻ ጆሮ ላይ የሚደረግ የጌጥ ዐይነት ነው። ይህን በመሸጥ በአብዛኛው የቆሎ ተማሪዎችና “ሽቃጮች”[94] ገቢ ያገኙበታል” (ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 ቃ.መ)።*

[94]በአንስተኛ ገበያ እንደ ዐዲስ አበባ ጉልት የሚባለው ዐይነት በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ እናቶች የሚያደርጉት የገበያ ዐይነት ነው።

ጉትቻ እንደ መስቀልና አልቦ ኹሉ የራሱ ተምሳሌት አለው። የጉትቻ ተምሳሌት በዋናነት ዝምድናን፣ እኅትማማችን፣ ወንድማማችን እና ጓደኝነትን የሚያዘክር ነው። እኅትነት፣ ወንድማማችነት እና በጓደኝነት ደረጃ ደግሞ የዕድሜ ሻሞን ይወክላል። ወንድም ለወንድሙ ጌጥ እንደሆነ ኹሉ የአንዱ ጆሮ ጉትቻ ለሌላው ጆሮ ጌጥ ነው። አንዱ ጆሮ አጊጦ ሌላኛው ጆሮ ዓይተውም። ይኹን ቢባል እንኳን ግንጥል ጌጥ ሆኖ ከማሽማቀቅ እና ከማሳፈር ያለፈ ለትይንት እና ለአድናቆት የሚበቃ ውበት የለውም። በዚህ ምክንያት ጓደኞሞች፣ መንድማማቾች፣ እኅትማማቾች፣ ማኅበረሰቦች ከጆሮዎቹ ጌጥ ተመልክተው አንዳቸው ለሌላቸው አስፈላጊ መሆናቸውን ይማራሉ። ይህን በተመለከተ በጥምቀቱ ዕለት አንዲት እናንየ አልታሰብ የተባለች አቀንቃኝ ኹለት ምትኩና ካሳው የሚባሉ ጓደኞሞችን በተመለከተ

*ምትኩና ካሳው ምንና ምን ናቸው፣*
*የጆሮ ጉትቻ የአንገት ማተብ ናቸው።*
*(እናንየ አልታሰብ 11/05/12 ዓ.ም)*

የሚል ግጥም ስታቀነቅን አዳምጫታለሁ። የግጥሙን አንድምታ የተዘፈነለትን ወጣት ካሳው መኳንንትን ጠየቅኩት። እሱም *"እኔና ምትኩ የሥጋ ዝምድና ባይኖረንም በዕድሜ ሻሞ*[95] *ነን። ከልጅነት እስካሁን በጨዋታው፣ በሰርጉ፣ በጥምቀቱ፣ በዘፈኑ፣ በእንቁር ልጊያው ዐብረን ነን፤ አንለያይም። እንደዚህ ያሉ ጓደኞሞችን ከሌሉ ምማ ነው፤ ያገኘ ነው የሚያዋርደው" (ካሳው መኳንንት 11/05/ 2012 ቃ.መ)።*

በመሆኑም የጆሮ ጉትቻ ከጌጥነቱ ባለፍ በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚኖሩ ጓደኞሞች ተከባብረውና ተሳስበው እንዶኖሩ ያስችላል። በኹለቱ ጆሮዎች ተመሳሳይ የኾነ ጉትቻ መደረጉ እኔ ከሱ እበልጣለሁ ወይም አንሳለሁ የሚለውን የበላይነት ይኹን የዝቅተኝነት ዕሳቤን በማስወገድ ወደ እኩልነት እና መተሳሰብ የሚያመጣ ዕሳቤን ይቀርጻል። ይህም ግብረ ገብነትን፣ መተሳሰብን አንዱ ለሌላው መኖርን ያዘክራል (ሊቀ ሊቀውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/11/*ቃ.መ*. እና ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 *ቃ.መ*)።

የአንገት ማተብ ከቀይ፣ ከቢጫና አረንጓዴ ሦስት እኩል ኹነው የተሸረቡ አንድ ወጥ ክሮች ናቸው። እነዚህ ማተቦች በየቦታው የሚሸጡና መስቀሉ እየታሰረባቸው በአንገት ይደረጋሉ። ማተብ በጎንደር ትልቅ ስፍራ አለው። በጎንደር ማኅበረሰብ ማተብ የሐቀኝነት፣ የታማኝነት

[95] *ተቀራራቢ ዕድሜ ያላቸው ጓደኞሞች መጠሪያ ነው።*

እና የሰባዊነት መገለጫ ተደርጎ ይወሰዳል (ካሳው መኳንንት 11/05/ 2012 ቃ.መ እና እናንየ አልታሰብ 11/05/12 ቃ.መ)፡፡ ይህን በተመለከተ ልዕልና ኀይለ መስቀልን ማተብ ከሽያጭ በተጨማሪ ለጎንደር ማኅበረሰብ ምን ተምሳሌት አለው የሚል ጥያቄ አቅርቤላቸው ተከታዩን መልስ ሰጥተውኛል፡፡

> *በዚያን ወቅት ብዙ ግጥሞች ይወርዳሉ፤ ሃይማኖታዊ፣ የማኅበረሰቡን ማንነት የሚገልጹ፣ ቁንጅናን፣ ነጻነትን፣ እምነትን፣ ጽናትን የሚገልጹ ግጥሞች ይቀነቀናሉ፡፡ ገዳሙ፣ ገዳሙ የሚባሉ ግጥሞች በሙሉ ገጽታን ሰባዊ ግንባታን የሚገልጹ ግጥሞች ናቸው፡፡ አለው አለውና ያው በማተቡ ጠና፡፡ ይኽ ጽናትን፣ አለመዋሸትን፣ እውነተኝነትን፣ ሰብእናን ለአለማጉድፍ የሚደረግን የውስጥ ባህል የምትረዳበት መንገድ ነው* (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011)፡፡

ከላይ የተጠቀሰው መረጃ ማተብ በጎንደር ባህል ውስጥ ትልቅ ቦታ ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ማተብ የማኅበረሰባዊ ዝምድና እና የፍትሕ ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ እና በጥምቀት ዐውድ "አለው አለውና በማተቡ ጠና" የሚለው ዘፈን አዳምጫለሁ፡፡ ይህን ጉዳይ ለልዕልና ኀይለ መስቀል አቅርቤላቸው "በማተብ መጥናት ቃል ኪዳንን እውነትን አለመካድ ምሳሌ ነው" የሚል መልስ ሰጥተውኛል፡፡ የማተቡ ሦስት መኾን የሥላሴ ምልክት ነው፡፡ የአካባቢው ማኅበረሰብ በሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ያምናል፡፡

በሦስቱ ሥላሴ ከተባለ እንኳን ሰው ውሐ ይቆማል ይላሉ፡፡ ይህም የሃይማኖታቸውን ጽናት፣ የፍቅርና የመተሳሰባቸውን ብዛት ያመለክታል፡፡ የማተብ ቀለማት መለያየት የአብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው፡፡ ቢጫ የአብ፣ ነጩ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው፡፡ ቀዩ ደግሞ ወልድ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶና ተጠምቆ፣ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍሶ ሰውን ያዳነበትን ምሳሌ ነው (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡

የማተቡ ቀይ መሆን የመሥዋዕትነቱ ተምሳሌት ነው፡፡ ነጭ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው፡፡ ሦስቱ በአንድ መገመዳቸውና እኩል መኾናቸው ደግሞ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መካከል የአካል እንጂ የግዛት፣ የሥልጣን፣ የባሕርይ ልዩነት የሌላቸው አንድ አምላክ መኾናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ማተቡ የሥላሴ ምልክት ሲኾን ሥላሴ ደግሞ የእውነት እና የፍትሕ አምላክ ነው፡፡ እውነት እና ፍትሕ ካለ አድሎ፣ ሐሰት፣ ውሸት፣ ቅጥፍና፣ ክሕደት የተባሉት ነገሮች በማኅበረሰቡ እንዲወገዙ እና እንዲቀንሱ ያደርጋል፡፡

“አለው አለውና በማተቡ ጠና” የሚለው ቃል ግጥም ሃይማኖታዊ ትስስሩ በኦርቶዶክስ አማኞች ብቻ ሳይኾን በሙስሊሙ ማኅበረሰብም የሚታይ ሐቅ ነው። “እስላም ካበለ ሚዛን ካጋደለ” የሚለው ብሂል እውነት እና ፍትሕን የሚያዘክር ነው። በማተብና በሚዛን የሚነገሩት ብሂሎች ክርስቲያን እና እስላሙን በፍትሕ እና በእውነት ላይ አስተሳስረው የሚያስቀጥሉ የጎንደር ማኅበረሰባዊ ዕሴቶች ናቸው (ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 *ቃ.መ*፤ ወ/ሮ ሞሚና አሕመዴ 29/05/2012 *ቃ.መ* እና የሱፍ ወርቁ፣ 29/05/12 *ቃ.መ*)።

በጎንደር ጥምቀት ለንግድ ከሚውሉት መካከል ባህላዊ ቁሶች ተጠቃሾች ናቸው። የባህል ቁሶች በጎንደር ጥምቀት ሰሞን በብዛት ይሸጣሉ። ከሚጠቀሱት ቁሳቁሶች መካካል ጭራ፣ መቋሚያ እና ስፌት ይገኙበታል። እነዚህ ቁሶች ለጥምቀት ማድመቂያ፣ መዋቢያና ማክበሪያ ስለሚያገለግሉ የአገሬው ሰውም ኾነ ከውጭ የመጡት ቱሪስቶች በብዛት ይገዟቸዋል። ይህን በተመለከተ ለሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሀዲስ ጥያቄ አቅርቤላቸው እንደሚከተለው አስረድተውኛል።

> *ያን ጊዜ እደ ጥበባት ያላቸው የሚሠሩ ሰዎች ገበያቸው እንዴት ነው ሀበሻው፣ ፈረንጁ የሐበሻውን ልብስ እየገዛ ስለሚለብስ ዕጥፍ ይጨምራል። ባለ ሆቴሎች ዐልጋ ውድ ነው ያን ጊዜ አይገኝም። ብዙ ገቢ አለ። መጠጥ ምን እና በእውነቱ ሳስበው ለጎንደር ብቻ አይደለም። ለኢትዮጵያ በሙሉ የገቢ ምንጭ ነው። እንዲያውም እስካሁን ድረስ በዩኒስኮ ሳይመዘገብ መቆየቱ ለነጋዴውም፣ ለገበሬውም፣ ለአምራቹም፣ ለሸማ ሠሪውም፣ ለመስቀል ወርቅ፣ ጌጣጌት ለሚሰሩ፣ ሸማ ለሚሠሩት፣ለግብርና፣ ለቱሪዝም ለዚህ ለዚህ ኹሉ የገቢ ምንጭ፣ የመሠረተ ልማት ነው። በዓሉ ሃይማኖታዊ በዓል ተደርጎ ብቻ መወሰድ የለበትም። መስሕብነት ያለው ማን ነው መባል አለበት። ዓለማቀፋዊነት ያለው የቱሪስት መስሕብ ጥምቀት ኹለተኛ ገቢ የሚያስገኝ ማን ነው መባል አለበት። በጥምቀት በዓል ኹሉም ክብር ያገኛል። ቤቶቹን ኹሉ ጥምቀት ነጻ ያወጣቸዋል። ቀለም ይቀባሉ፤ ይጸዳሉ። እንዲያውም የጎንደር ጥምቀት ምን ልበልኽ ለኹሉም፣ ለኹሉም መሠረት ነው። ጭራውን ይገዛሉ፤ ይይዛሉ። ወንዶቹ መቋሚያውን በትሩን ይገዛሉ። ሴቶቹ አገልግሉን ይገዛሉ ያዝላሉ። ቅቤቅል ይይዛሉ* (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዘዲስ 15/11/2011 *ቃ.መ*)።

ቃለ መጠይቁ እንደሚያስረዳው እነዚህ ቁሳቁሶች በጥምቀት ሰሞን ጥሩ ገቢ ማስገኛዎች ናቸው። ወ/ሮ ምንትዋብ ደጌ በጎንደር ከተማ ባህላዊ ምግብና ጠጅ የሚያዘጋጁ ናቸው። ከእሳቸው ቤት በርካታ የባህላዊ ሞሰብና መመገቢያ ቁሳቁሶች በጥምቀት ዕለት ተደርድረው አገኘሁ። እነዚህ መሶቦች ለምንና መቼ እንደተገዙ ስለ ጥምቀት ሰሞን *ሥራ* ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የ*ሥራ* ድርሻቸው ጠጅ በመጣልና በመሸጥ እንደሚተዳደሩ ገልጸውልኛል።

በርካታ ሞሰቦችን የገዙት የጥምቀት በዓል ሲደርስ እንደሆነና ይህን የሚያደርጉትም በጥምቀት ሰሞን በሣሕን እንጀራ ከማቅረብ የውጭ ቱሪስቶች እና የውስጥ እንግዶች የጎንደርን ባህል እንዲያውቁ ለማድረግ ነው በሚል መነሻ እንደሆነ ነግረውኛል፡፡ እንግዶቹም በባህላዊ ምግብ ዝግጅቱ ደስ ብሏቸው እንደሚስተናገዱ ገልጸውልኛል፡፡ ከወ/ሮ ምንትዋብ እንደተረዳኹት ሞሶበ ወርቁን የሚሰፉት የጎንደር ወይዛዝርት ናቸው፡፡ እነዚህ ስፌት የሚሰሩ ባለ ሙያዎች በጎንደር ጥምቀት ሰሞን ከፍ ያለ ገቢ ያገኛሉ፡፡ የጥምቀት ዕለት በዚህ በወ/ሮ ምንትዋብ ቤት ገብቸ ነበር፡፡ በቤቱ ውስጥ ከባህላዊ ሞሰቡ እና ቆለምሽሽ በተጨማሪ ከባህላዊ ቆዳ የተዘጋጁ የግድግዳ ማስጌጫዎችንም ተመልክቻለሁ፡፡ በቆዳው ላይ የኢትዮጵያ ነገሥታት እነ ዐፄ ቴዎድሮስ፣ ዐፄ ዮሐንስ፣ ዐፄ ምኒልክ እና የእቴጌ ጣይቱ ምስሎች ተቀርጸውበታል፡፡ እነዚህ ምስሎች በግድግዳ ላይ መቀረጻቸው የጎንደርን፣ ብሎም የኢትዮጵያን ማነነት፣ እነማን ያስተዳድሩ እንደነበር ታሪክን በመንገር በኩል ትልቅ ፋይዳ አላቸው፡፡

ቤት ውስጥ ገብቶ ጠጅ የሚጠጣው፣ ምግብ የሚመገበው፣ ኮረፌ የሚጋተው ከመስተንግዶው በላይ ዐይኑን ወደ ግድግዳው እና የምግቡ መሶብ እና ቆለምሽሽ ላይ ሲያስተውልና አንዳንድ ጊዜም ሲጠይቅ ተመልክቻለሁ፡፡ እኔም በዚሁ ቤት ስታደም እንደዚሁ ጥያቄዎችን ፈጥሮብኝ ወ/ሮ ምንትዋብን አስፈቅጀ ስለ ባህላዊ ቁሶቹ ጠይቄአቸዋለሁ፡፡ ወ/ሮ ምንትዋብ ከሩቅ ቦታ የመጣኹ መኾኔን ተገንዝበው እስኪ ለእንግዳው ቡና አፍሉለት፣ "ጥቁር እንግዳ ነው"[96] ብለው፣ ቁርስ አቅርበው፣ ቡና አስፈልተው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *"ክረምት ባይመጣ ኹሉ ቤት፣ እንግዳ ባይመጣ ኹሉ ሴት" እንደተባለው የሴት መለኪያ እኮ በጎንደር ዶሮ ወጥና ስፌት ነው፡፡ ስፌት የሰፋች ልጃ ገረድ ትታጫለች፤ ትፈጫለች፤ ጥሩ ትዳር ትይዛለች፡፡ በጥምቀት ሰሞን እና በሰርግ ወቅት የሚያዘው ስፌት ዝም ብሎ ለሽክም አይደለም፡፡ የዚያች ሴት ሙያ ምስክር እንዲኾን ታስቦ ነው አኹን፣ አኹን በጥለት የተሰፋውን መሶበ ወርቅ ሴቶች ሲዳሩ በከተማ ይወስዳሉ፡፡ ለምን እንደሚወስዱት አያውቁም፡፡ አንድ ዙር የማታዞረው መሶብ ትሸከማለች፤ አንድ ክር የማትዘነግገው ጥልፍ ትለብሳለች፡፡ የጎንደር ሙያ ስፌት፣ ፈትል፣ ዶሮ ወጥ ነው፡፡ ጠጅ መጣል፣ ጠላ*

[96] *"ለአገሩ እንግዳ፣ ለሰው በዓዳ" የሆነ እንግዳ ነው፡፡ ይህ ሰው አገርና ቤትን ታዝቦ ጠንክር ሲልም ረግሞ እንዳይሄድ የሚደረግ የእንግድነት አቀባበል ስለ እንግድነት ሲነሳ ድሮ፣ ድሮ የጎንደር ባላባቶች ልጆቻቸውን ጎጆ ሲያወጡ፣ "የእዳ የእንግዳ" ብለው ከአውድማ እህል ያነሱ ነበር (በሪሁን አካላት) እስካሁንም ድረስ በዚህ ማኅበረሰብ እንግዳ ትልቅ ቦታ አለው* (መ/ር ዳዊት ሥራው 07/08/2013 ለሦስተኛ ጊዜ የተደረገላቸው ቃ..መ) ::

*መጥመቅም ይጨመራል። የጎንደር ጥምቀት የሚታወቅ በእኒኽ ነው። በተለይ የጥምቀት የዐማረ ምግብ በዐማረ መሶብ፣ በተለይ የዶሮ ወጥ በጤፍ እንጀራ፣ የዐማረ ጠላ በዐማረ ዋንጫ*[97] *ሲቀርብ ነው ጥምቀቱን ማክበራችንን የምናውቀው (ምንትዋብ ደጌ 11/05/2012ቃ.መ)* በማለት ቀስ ብለው በለኆሳስ[98] ድምፅ አስረድተውኛል።

ጎንደር በብዙ ቦታዎች ባህላዊ ምግብ ቤቶች ምጣኔ ሀብቱን የሚያሳድጉ ከመኾናቸው በተጨማሪ የጥንቱን የጎንደር ባህል የመዘከር ፋይዳ አላቸው።



*(በምንትዋብ ደጌ ቤት ውስጥ የሚገኙት መሶበ ወርቅ እና ባህላዊ ቅርጻ ቅርጾች 15/11/2011*[99]*)*

ወ/ሮ ምንትዋብ እንደሚያስረዱት አንድ መሶብ በዘወትር ጊዜ እስከ አራት መቶ ብር የሚሸጥ ሲኾን በጥምቀት ሰሞን ደግሞ እስከ ስድስት መቶና ሰባት መቶ ብር እንደሚሸጥ ገልጸውልኛል። የጎንደር ጥምቀት ለቅርጻቅርጽ ባለሙያዎች፣ ለስፌት ሰፊዎች፣ ለሥዕል

---

[97] ዋንጫው ከቀንድ የተሰራ ሲኾን በዚኹ ሞላላ ቅርጽ ባለው ዋንጫ ቀድተው ጠላ ሰጡኝ። እሳቸውም ቀጠል አደረጉና በዋንጫ የሰጡሁህ ስሞት እንድታለቅስልኝ ነው አሉኝ። በማኅበረሰቡ ዘንድ በዋንጫ የጠጣ ሰው አልቅሶ፣ አጥቦ እና አዝኖ እንደ ቤተ ዘመድ ሚችን የሚሸኝ ነው የሚል ዕሳቤ አለ (መ/ር ዳዊት ሥራው 07/08/2013 ለሦስተኛ ጊዜ የተደረገላቸው ቃ..መ) ።

[98] እንደ ጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ አንድም ብዙ ሰው በቤታቸው ነበር እና ነገር ከተዘራ እንደጥሬ ያገኝ ይለቅመዋል ከሚል እሳቤ፣ አንድም በእንግዳ ፊት ቀስ ተብሎ እንጅ እመር፣ እመር እና ቀደም. ቀደም ማለት አስነዋሪ መኾኑ ነው። ሌላው "ነገር በዐይን ይገባል" እንደተባለው የጎንደር ማኅበረሰብ ከጆሮ ይልቅ ለዐይን ትልቅ ቦታ ይሰጣል። ለዚህ ነው በለኆሳስ ያጫወቱህ (መ/ር ዳዊት ሥራው 07/08/2013 ለሦስተኛ ጊዜ የተደረገላቸው ቃ..መ) የሚል ምላሽ ሰጥተውኛል።

[99] በ2011 ክረምት ላይ በቤታቸው ተገኝቸ ነበር። ፎቶዎቹን አንስች ቢያደርሰን እንደ ስለት ለመጭው 11/05/12 ጥምቀት ተቀጣጥረን ተለያይተናል። በዚሁ ለጥር 11/2012 ሁላችንም አድርሶን በቤታቸው ለቃለ መጠይቁ ተገኝቻለሁ።

ሠዐሊዎች እና ለጭራ ቆናኞች ገቢ በማስገኘት ሚናው የጎላ ነው፡፡ በማራኪ ክፍለ ከተማ በቆብ አስጥልና በጨጭሆ ባህላዊ ጭፈራ ቤቶችና ሆቴሎች በጎንደር ባህላዊ ቁሳቁሶች፣ ባህላዊ ወንበሮች፣ የባህል ምግብ ዝግጅቶችን፣ የግድግዳ ላይ ምስሎች እና ሥዕሎች ተመልክቻለሁ፡፡ እነዚህ ኹሉ ተዳምረው ከምጣኔ ሀብት ጥቅማቸው በተጨማሪ የጎንደርን ባህል እና ማንነት የሚገልጹ ናቸው፡፡

በጥምቀት ሰሞን በየባህላዊ ጭፈራ ቤቶች እና ምግብ ቤቶች ታሪክና ባህልን ዘካሪ የሆኑ ቅርጻ ቅርጾች እና ሥዕሎች በብዛት ይታያሉ፡፡ የጎንደር ማስዋቢያ ሥዕሎች እና ሕንጻዎች የጥንቱ የጎንደር ቤት አሠራር እና የዐፄ ፋሲል ግንብ ቅርጽ ላይ የተመሠረቱ ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ ቅርጻ ቅርጾቹ ከምጣኔ ሀብት ጠቀሜታቸው ጎን ለጎን የባህል ዘካሪ፣ የዕሴት ነጋሪ እና የታሪክ መስካሪ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሌማቶቹ አንድም የጎንደርን ነገሥታት ከዘውዱ ጋራ፣ አንድም የጎንደርን ሊቃውንት ከቀጸላው ጋራ፣ አንድም የጎንደርን ቀሳውስት ከአክሊላቸው ጋራ፣ አንድም ጎንደርን አብያተ ክርስቲያን ከጉልላታቸው ጋራ፣ አንድም ጎንደርን አብያተ መንግሥታት ከግምባቸው ጋራ ሚተረጉሙ ናቸው፡፡ አንድም ሌማቱ እመቤታችን ሕብስቱ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስን ይተረጉማል፡፡ በመኾኑም የጎንደር ሞሰበ ወርቅ ሌማቶች ማኅበረሰቡን እና ሃይማኖቱን የሚወክሉ ናቸው፡፡

በአባ ሶኒ ሆቴል ላይ እንደተመለከትኩት ቀደምት የኢትዮጵያ ነገሥታት እና መንግሥታት የሆኑት የዐፄ ቴዎድሮስ፣ የዐፄ፣ ዮሐንስ፣ የዐፄ ምኒልክ፣ የእቴጌ እጣይቱ፣ የዐፄ ኀይለ ሥላሴ እና የኮሎኔል መንግሥቱ ኀይለ ማርያም ምስሎች በትልቅ ባነር ተሰቅለዋል፡፡ እነዚህ የነገሥታት ምስሎች በዘወትር የሚገዙ ሲኾን በብዛትና ደንበኛን ለመሳብ እንዲኹም ጎንደርን ለማስተዋወቅ ሲባል ቱሪስቶች በሚመጡበት የጥምቀትና የመስቀል ክብረ በዓላት ሰሞን ይበልጥ ይፈለጋሉ፡፡ በዚህ መልኩ ምስሎች ለሠዓሊዎች ገቢ ከማስገኘት በተጨማሪ ታሪክንም የመንገር እና የመዘከር ፋይዳ አላቸው (ስንታየሁ ሹሜ፣ 15/05/2011 ቃ.መ)፡፡

በብዙ ሆቴል ቤቶች እና የባህል ምግብ ቤቶች ጎንደርን ብሎም ኢትዮጵያን የሚያሳዩ ምስሎች እና ሥዕሎች በብዛት ይገኛሉ፡፡ በተለይ ጎንደርን የሚዘክሩ የፋሲል ግንብ እና የሰሜን ተራራ ፎቶዎች፣ የአርባ አራቱ አድባራት እና ቅዱሳን ሥዕሎች በጥምቀት ዕለት በብዛት እና በብዙ ቦታዎች ይስተዋላሉ፡፡ ስለዚህ የጎንደር ጥምቀት በዋናነት ገቢውን የሚደግፈው በባህላዊ ጥበባት ውጤት ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህ መልኩ በጎንደር ጥምቀት የሚገኘው በገንዘብ የሚሰላ ምጣኔ የሀብት ብቻ ሳይኾን ባህላዊ ቁሶችም በሚያስገኙት የገቢ

ምንጭ ምክንያት ከትውልድ ትውልድ እንዲቀጥሉ ያስችላል (ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን 12/05/2013 ቃ.መ. እና ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡

## 7.6. በጥምቀት ክብረ በዓል የንዋየ ቅድሳት ንግድ ምጣኔ ሃብታዊ ፋይዳ እና አንድምታቸው

ንዋየ ቅድሳት የሚባሉት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚሸጡትንና የሚገዙትን የአገልግሎት እቃዎች ይመለከታል፡፡ እነዚህ ለጥምቀት ሰሞን በአብዛኛው ስለት ያለበትና ለቤተ ክርስቲያን አበርክቶት የሚሰጡ ምእመናን ግዥ በመፈጸም ገበያውን ያደሩታል፡፡ በጎንደር ገበያ ጥምቀትን አስመልክተው የሚሸጡ የቤተ ክርስቲያኗ አገልግሎት መስጫዎች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል ጎንደር ትልቁ የገበያ ቦታ ተብሎ በሚጠራው አራዳ ገበያ ውስጥ መቋሚያ፣ ከበሮ፣ ጥላ፣ ጽና፣ መጋረጃ፣ መጎናጸፊያ፣ ጽናጽል፣ ድንኳን እና መሰል ንዋየ ቅድሳት ይሸጣሉ (ስንታየሁ ሹሜን፣15/05/2011 ቃ.መ፣ አስቻለው ደመላሽ 16/05/2012 ቃ.መ፣ መ/ር መሐሪ ጥሩር 15/05/12/ ቃ.መ)፡፡

በንዋየ ቅድሳት ንግድ የተሠማሩ ነጋዴዎች በጥምቀት ገበያ ሰሞን በደራ መልኩ የሚሸጡበት ወቅት ነው፡፡ የዚህ ምክንያቱ ደግሞ በርካታ የማኅበረሰብ ክፍሎች ከተለያዩ ቦታዎች ወደ ጎንደር ጥምቀት መምጣታቸው ነው፡፡ በጎንደር ማኅበረሰብ እምነት መሠረት አንድ ምእመን ከውጭ ሲመጣ ለታቦታቱ እጅ መንሻ ዐቅሙ በፈቀደ ልክ የማምጣትና የማበርከት የቆየ ትውፊት አለው፡፡ በዚህ መልኩ አራዳ ገበያ በመግባት የጥምቀት ሰሞን ጥላውን፣ ካባውን፣ መጎናጸፊያውን ይገዛሉ፡፡ ጥምቀት ኹለት ሳምንት ሲቀረው ጀምሮ የንዋየ ቅድሳት ሽያጭ በጎንደር ከተማ በተለይ በአራዳ ገበያ በጣም የናረ ነው፡፡ ነጋዴዎቹ ከጧት እስከ ማታ ትንፋሽ አጥተው፣ ቁርስና ምሳ ሳይቀምሱ ይውላሉ፡፡ በዚህ መልኩ እስከ ጥምቀቱ ዋዜማ ድረስ እጅግ በርካታ የኾነ ግብይት ስለሚኖር በዚህ ንግድ የተሠማሩ ግለሰቦች እና ነጋዴዎች ከፍተኛ ትርፍ ያገኛሉ (ስንታየሁ ሹሜን፣15/05/2011 ቃ.መ፤ አስቻለው ደመላሽ 16/05/2012 ቃ.መ እና መ/ር መሐሪ ጥሩር 15/05/12/ ቃ.መ)፡፡

## 7.7. በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ "ጥምቀትን በጎንደር" የሚሉ የባህላዊ ግብዣ[100] ቅርጻቅርጾች አንድምታ እና ምጣኔ ሀብት

የጎንደር ጥምቀት ከሃይማኖታዊ ግልጋሎቱ ከገበያ ሻጮችና ሸማቾች በተለየ መልኩ አሁን አሁን በጥምቀት ዙሪያ የሚዘጋጁ ግብዛዎች እና ልዩ ልዩ ቅርጻቅርጾች ብቅ ማለት ጀምረዋል፡፡ ከእነዚህ ዝግጅቶች መካከል በከተማው ውስጥ የኪነጥበብ ባለሙያዎች የአቋቋሙት "ጥምቀትን በጎንደር" የሚለው ግብዣ አንዱ ነው፡፡ ይህ ግብዣ ጥምቀትን በጎንደር መመልከት፣ ማየትና ማክበር ልዩ የሆነ ውበት፣ ትውፊት እና ሥርዐት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ነው (ልዕልና ጎይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡ ይህ ዝግጅት የጎንደርን ጥምቀት በሚያሳይ እና ባህሉን በጠበቀ መልኩ በቅንብር መቼት እየተዘጋጀ ለውጭ ቱሪስቶች መስኅብነት እየዋለ መጥቷል፡፡ ይህን በተመለከተ ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ ተከታን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ለውጡ የመጨመር ማለት የሕዝቡ ብዛት፣ የሊቃውንቱ ብዛት፣ ይኸ፣ ይኸ ለውጥ ኹኖ በየ ዓመቱ ዐዲስ በዓል፣ ዐዲስ በዓል ኹኖ ይታያል፡፡ የቱሪስቱ መብዛት መጨመር ዐዲስ ኹኖ ከነበረው ሳይቀንስ ከነበረው ላይ በሕዝብ ብዛትና በሊቃውንት ብዛት እየጨመረ የሚታይ የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲያውም ጎንደርን በጥምቀት እንይ ተብሎ ኢትዮጵያንም በጎንደር ተብሎ የወጣ የበዓል መርሐ ግብር ነበረ (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

የጎንደር ጥምቀት በዘመናዊ መልኩ ለሚዘጋጁ ድራማዎች፣ ሙዚቃዎች እና ሥነ ጽሑፍ ሥራዎች መነሻ በመኾን በኩል ያለው ድርሻ ከፍ ያለ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በሀገር በቀል ዕውቀቶች ላይ ተመሥርተው ለሚሠሩ ቅርጻቅርጽ ተግባራት አስተዋፅኦ አለው፡፡ በዚህ ሥራ ለተሠማሩ ግለሰቦች የሥራ ዕድል በማስገኘት እና ገቢ እንዲያገኙ በማስቻል ረገድ ያለው ድርሻ መልካም ነው፡፡ ይህም በሀገር በቀል ዕውቀት ላይ ተመሥርቶ የሚገኘውን ገቢ ያሳድጋል፡፡

[100] ፌትስተቫል የሚለውን ቃል ለመተካት ተጠቀምኩበት ነው፡፡




*(ጥምቀትን በጎንደር ባነር እና ጥምቀትን በጎንደር መስቀል 2011 እና 2.013 ከላይ ወደታች)*

እንደ መስቀል ያሉ ቅርጻቅርጾችን የጎንደርን ጥምቀት በሚዘክር መልኩ እያዘጋጁ እና እየሸጡ ኑሯቸውን የሚደጉሙ ግለሰቦች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካካል በጥምቀት ዋዜማ በባሕረ ጥምቀቱ ዚሪያ በአደባባይው በብዛት ተሸክሞ እየዞረ “ጥምቀትን በጎንደር” የሚል ልዩ መስቀል ግዙ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ የሚገኝ እያለ የሚሸጠውን የአብነት ተማሪ አየለ ቴዎድሮስን አግኝቸው ነበር፡፡ እሱም ራሱ እንደሚያዘጋጅ እና እንደሚሸጥ የነገረኝ ሲኾን ትርፋማ እንደሆነም አስረድቶኛል (አየለ ቴዎድሮስ 10/05/2013 *ቃ.መ.*)፡፡ በመሆነም የጥምቀት ክብረ በዓል ዐዳዲስ ሀገር በቀል ዕውቀቶች እና ፈጠራዎች እንዲመጡ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ጥምቀትን በጎንደር የሚሉ ፈጠራዎች አንድም ባህላዊ ዕሴትን በማሳደግ፣ አንድም የጎንደርን ጥምቀት በማስተዋወቅ፣ አንድም ምጣኔ ሀብቱን በመደጎም በኩል ትልቅ ድርሻ አላቸው፡፡

### 7.8. የጎንደር አዝማሪዎች ውዳሴ እና ገቢ በጥምቀት ክብረ በዓል

አዝማሪና ጎንደር የቀደመ ታሪክ አላቸው፡፡ የጥምቀት ክብረ በዓል የጎንደር አዝማሪዎች በከፍተኛ ኹኔታ ጥቅም የሚያገኙበት ወቅት ነው፡፡ አዝማሪዎች በጎንደር ሊቀ መኳስ፣ ዓለም

አጫዋች የሚሉ ስሞች አሏቸው። ይህንን ስም አዝማሪ ጋሻው ሙጨ እንደማይቀበለው ነግሮኛል። ለዚህ እንደ ዋና ምክንያት የሚያነሳው ዘመረ አመስገነ አዝማሪ አመስጋኝ የሚለው ነው ትክክለኛ የአዝማሪ መጠሪ መሆን ያለበት በማላት አለም አጫዋች እና ሊቀ መኳስ የሚሉትን መጠሪያዎች እንደማይቀበላቸው መረጃ ሰጥቶኛል (አዝማሪ ጋውሻው ሙጨየ 11/05/2013 ቃ.መ.)። የጎንደር አዝማሪ የጥምቀት ክብረ በዓል፣ የነገሥታቱ በዓለ ሲመት፣ የጦር ውሎ፣ የግብዣ በዓል እና መሰል ሃይማኖታዊ እና መንግሥታዊ በዓላት ወቅት ከሊቃውንቱና ከመኳንንቱ ጎን ለጎን ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጉ ነበር። ይህን ተከትሎ የመጣው ታሪክ አሁንም በጎንደር ጥምቀት በዓል ላይ ተሳትፏቸው የጎላ ነው (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ እና አዝማሪ ጋሻው ሙጨየ 11/05/2013 ቃ.መ.)።

አዝማሪ ጋሻው ሙጨየን በጥምቀት ክብረ በዓል ታቦታቱን እያከበረ እና እያገለገለ በፒያሳ አግኝቸዋለሁ። እኔም በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ያለውን የአዝማሪ ተሳትፎ እና የገቢ ኹኔታ ምን እንደሚመስል? እንዲያስረዳኝ ቃለ መጠይቅ አቅርቤለት ነበር። እሱም ተከታዩን መረጃ ሰጥቶኛል።

> *በጥምቀት በዓል ገቢያችን የተሻለ ነው። ገቢያችን የተሻለ ይኾናል፤ የተለያዩ እንግዶች ስለሚመጡ የማስታወስ ባሕርይ ስላለ የጥንቱንም የሀገራቸውንም እንዲህ ዝና እና ጨዋታ የሚቀሰቅሰው በጥምቀት ስለኾነ የተለያዩ እንግዶች ስለሚመጡ በጥምቀት በጣም የተሻለ ጥቅም እናገኛለን። በጣም የተሻለ ነው፤ የተሻለ ነው፤ ኑ ከኔ፣ ኑ ከኔ ነው። እኔ አኹን ከቀኑ የማታው ፈላጊዬ ይበዛል፤ ከማታው የቀኑ ፈላጊዬ ይበዛል። እወዛገባለሁኝ፤ ፈላጊዬ ስለሚበዛ፤ ምክንያቱም በጥምቀት ቀን ብዙ ተደሳች፣ ብዙ ባህሉን አክብሮ ስለሚመጣ ለመጫወት ለመዝናናት ከጓደኛው፣ ከባልንጀራው ጋር (አዝማሪ ጋሻው ሙጨየ፣ 12/ 05/ 2013 ቃ.መ)።*

ከላይ የተጠቀሰው መረጃ በጥምቀት ሰሞን አዝማሪዎች ተፈላጊ ከመኾናቸው የተነሣ ከየትኛው ልኺድ እና የትኛውን ላስቀድም በሚል እንደሚወዛገቡ አመላካች ነው። በወርኀ ጥምቀት አዝማሪዎች በዋዜማውና በዕለቱ የጥምቀትን በዓል ከፍ ባለ ኹኔታ ሲያከብሩ ይውላሉ። ከጥምቀቱ መልስ በታላላቅ ሆቴሎች፣ በጠጅ ቤቶችና በባህላዊ ምግብ ቤቶች በጥሩ ክፍያ ይሠራሉ። በዚህ ቀን ከወትሮው በተለየ ይከፈላቸዋል። የዚህ ምክንያት ከውጭ ሀገር የመጡ ቱሪስቶች የአዝማሪዎችን ሀገረሰባዊ ዘፈን ይበልጥ በመፈለጋቸው ነው። በጥምቀት ክብረ በዓል አዝማሪ ያለበት እና የሌለበት ቤት የምግብና የመጠጥ ሽያጩ ይበላለጣል። አዝማሪ አለ ከተባለ ከደንበኛው መብዛት በተጨማሪ የሽያጩ ኹኔታ በከፍተኛ ዋጋ ስለሚጨምር ለአዝማሪዎች የሚከፈለው ብርም በዚያው ልክ የተሻለ ነው (ልዕልና ኀይለ

መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ፤ ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/12 ቃ.መ እና አዝማሪ ጋውሻው ሙጨየ 11/05/2013 ቃ.መ.)፡፡

የጎንደር አዝማሪዎች በቤተ መንግሥትና ቤተ ክህነት የራሳቸው ቦታና ተቀባይነት ነበራቸው፡፡ በቤተ መንግሥት አካባቢ ነገሥታቱ ግብር ሲያበሉ፣ ወደ ጦር ሲኼዱና ከጦር ሜዳ ሲመለሱ ውሎአቸውን አስመልክቶ ሰም ለበስ ቃል ግጥሞችን እና ቅኔ ነክ ግጥሞችን ያወርዱ ነበር፡፡ በዚህ ኹኔታ የነገሥታቱን ታላቅነት፣ የሠራዊቱን ጠንካራነት ያውድሱ ነበር፡፡ ዐልፎ ዐልፎም ነገሥታቱ በሥልጣን ካባ ተሸፍነው፣ በአጉል ትቢት ተጋርደው ሕዝቡን ሲበድሉ "ድሐ ተበደለ ፍርድ ጎደለ" በማለት ምክር እና ትችት፣ ውዳሴ እና ግሣጼ ጣል ያደርጉ ነበር (ልዕልና ጎይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ፤ ዓለም ሰገድ በለጠ፣ 10/11/2011 ቃ.መ እና ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/12 ቃ.መ)፡፡

አዝማሪዎች በቤተ ክህነት በኩልም ከፍ ያለ ቦታ ነበራቸው፡፡ በዚህ ዘርፍ አምላክን በዝማሬና በምስጋና ፈጣሪያቸውን ያመሰግናሉ፡፡ የጎንደር ጥምቀት ላይ ከዋዜማው ጀምሮ ታቦት ሲወርድና ሲመለስ ፈጣሪያቸውን እያመሰገኑ ታቦታቱን ይከበክባሉ፡፡ ከጥምቀቱ በኋላ ደግሞ በሆቴሎች፣ በድግስ ቤቶችና በተለያዩ የግብዣ ቦታዎች ትልቅ ገቢ ያገኛሉ፡፡ አዝማሪዎች በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ሀገራዊ እና ወቅታዊ እንደዚሁም ባህላዊ ዘፈኖችን የሚዘፍኑ በመሆናቸው ታዳሚዎች እጅግ ይወዷቸዋል፡፡ አዝማሪ የሚዘፍንበት ወይም የአዝማሪ ምሽት ያለበት መጠጥ ቤት የመጠጡና የምግቡ ዋጋ ከመደበኛው ዋጋ በዕጥፍ ይጨምራል (ዓለም ሰገድ በለጠ፣ 10/11/2011 ቃ.መ፤ ሊቀ መኳስ ደርበው ድሌ 03/06/12 ቃ.መ እና አዝማሪ ጋሻው ሙጨየ 11/05/2013 ቃ.መ)፡፡

አዝማሪዎች በጥምቀት ሰሞን በኹለት መልኩ ተጠቃሚ ይኾናሉ፡፡ አንደኛው ከላይ እንደተጠቀሰው በሆቴሎች፣ ሬስቶራንት እና መጠጥ ቤቶች ከባለ ሀብቶቹ ጋራ ዋጋ በመደራደር የሚያገኙት ገቢ ነው፡፡ ኹለተኛው ደግሞ አዝማሪዎች በጎንደር ጥምቀት ድግስ ባለባቸው ቤቶች በራሳቸው እየተዘዋወሩ በመዝፈን የሚያገኙት ገቢ ነው፡፡ በዚህ ዕለት በየቤቱ እየተዘዋወሩ ሲዘፍኑ ከቤቱ ባለቤቶች የሚያገኙት ገቢ እንዳለ ኹኖ ከእንግዶችም ቢኾን ገንዘብ ያገኛሉ፡፡ አዝማሪዎች ባላቸው የኪነ ጥበብ ተሰጥዖ ምክንያት የቤቱን አባወራ እና እማወራ ከሥራቸው እና ከማንነታቸው ጋራ በሚጣጣም መልኩ ያወድሷቸዋል፡፡ የቤት እመቤቷን ከውይዝርና፣ ከውበቷ እና ከሙያ ጋራ በተያያዘ መልኩ የሚያወድሱበት አጋጣሚ

ብዙ ነው (ዓለም ሰገድ በለጠ፣ 10/11/2011 *ቃ.መ.* እና ሊቀ *መኳ*ስ ደርበው ድሌ 03/06/12 *ቃ.መ.*)፡፡

ይህ የአባወራውን፣ የእማውራዋንና የታዳሚዎችን ቀልብ መሳብ የሚችል ውዳሴ በመኾኑ ሰዎች በራሳቸው ፍላጎት ገንዘብ ይሰጣሉ፡፡ በአቶ ደመቀ አያሌው እና በወ/ዘሮ ቀኑ አስማማው ቤት ውስጥ ዓለም አጫዋች ቸኮለ ብዙየ እያቀነቀኑ ጥር 12/05/12 ዓም የመመልከት እድል ገጥሞኛል፡፡ ከአቀነቀኗቸው ዘፈኖች መካከል ተከታዩ ግጥም አንዱ ነው፡፡

*ወይዘሮ ቀኑብሽ ውጭ ተጠየቂ፣*
*የጠመቅሽው ጠላ ወይን ነው አረቂ፡፡*
*ወይን ነው ወይን ነው ወይን ነው ጠላው፣*
*እስከ ወይና ደጋ ተሰማ ወሬው፣*
*ተሰምቶም አልቀረ እኛም ዐየነው፡፡*
*(ቸኮለ ብዙየ 12/05/12 ዓ.ም ያቀነቀኑት)*

ከላይ የተጠቀሰው ቃል ግጥም የአካባቢውን ማኅበረሰብ ባህልና ዕሴትን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የጎንደር ማኅበረሰብ ሴቶችን አንቱና እመቤት ብሎ የመጥራት እና ከሙያ ጋራ በተያያዘ የማወደስ የዳበረ ልምድ አለው፡፡ የጎንደር ወይዘሮዎች ከሚታወቁባቸው ሞያዎች ውስጥ ፈትል፣ ስፌት፣ የዶሮ ወጥ፣ ዝልል የመሳሰሉት ሞያዎች ይጠቀሳሉ፡፡ ግጥሞቻቸውም በአብዛኛው በእነዚህ ሙያ ዙሪያዎች ሊያጠነጥን የሚችል ነው፡፡ በወ/ሮ ቀኑብሽ አስማማው ቤት ውስጥም የተጠመቀው ጠላ የውይዝርና ማዕረግ አሰጥቷቸዋል፡፡ ቃል ግጥሙ ቀኑብሽን ከአካባቢው ወይዘሮዎች ከፍ የሚያደርግና እስከ ወይና ደጋ ድረስ ዝናቸው የሚሰማ፣ የሚነገር እና የሚወደስ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ወይና ደጋ የተባለው ቦታ ከጎንደር ከተማ በስተ ደቡብ ምሥራቅ አቅጣጫ በጎንደር ዙሪያ ወረዳ ማስከኚት ከተማ አቅራቢያ የሚገኝ ቦታ ነው፡፡ የወይዘሮ ቀኑብሽ ስምና ዝና ከአካባቢው ማኅበረሰብ ዐልፎ ወንዝና ደብር ይሻገራል፤ በዚህ ቃል ግጥም ውስጥ ወዘሮ ቀኑብሽ የጠመቁት ጠላ ከወይን ጋራ የሚፎካከር እንደኾነ ይጠቁማል፡፡ አጥኚው በምልከታ እንዳረጋገጠው በጎንደር ጥምቀት አዝማሪዎች ገንዘብ የሚያገኙበት ዋናው ስልታቸው በሚያቀነቅኗቸው ግጥሞች ሰባዊ ይዘት የሚለካ ነው፡፡ ሰው በባሕርይው ሙገሳ፣ ውዳሴና ምስጋና ይፈልጋል፡፡ ሰው በውድድር ዓለም ውስጥ አንድም በተግባር አንድም በሐሳብ ልቆና ጥሎ ለመውጣት ያለው ውዴታ ከፍ ያለ ነው፡፡ የዚህ ቃል ግጥም ዋና ጭብጥም ወ/ሮ ቀኑብሽን ከአካባቢው ወይዛዝርት በማላቅና የውድድሩ አሸናፊ በማድረግ ልብን አሸፍቶ፣

ቀልብን ሰርቆ ሽልማት ለማግኘት የሚያስችል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ቤት ውስጥ ከጥምቀት በዓልና ከአባወራው ማንነት ጋራ የሚሠምር ቃል ግጥም እንደሚከተለው ወስጀዋለሁ፡፡

*ጥገቱና በሬው፣ የፍየሉ አቅማዳ፣*
*እግዜር በመስቀሉ ባርኮት በማለዳ፣*
*ዕሽቱ በንሮ፣ ጠጁ አለ በንዳ፣*
*አሳላፊ ቁሞ አያልቅም ቢቀዳ፡፡*
*ያደመቀ አያሌው በማተቡ ኗሪ፣*
*ከቤትኽ አይወጣም እንግዳና አዝማሪ፣*
*በጥምቀት በመስቀል ታቦቱን ዘካሪ፡፡*
*እምለምናቸው አርባራቱን ቁሜ፣*
*ለደመቀ አያሌው የማቱሳላ ዕድሜ፡፡*

ከላይ የተጠቀሰው ቃል ግጥም አዝማሪ ቸኮል በአቶ ደመቀ ቤት ያቀነቀነው ነው፡፡ እነ አቶ ደመቀ በጎንደር አምባ ገጥር ቀበሌ የሚኖሩ ሲኾን በግብርና ይተዳደራሉ፡፡ እኚህ ሰው የጎንደር ጥምቀት በየዓመቱ ስለት ስላለባቸው ከፍተኛ ድግስ ደግሰው ዘመድ አዝማድ በመጥራት ይዘክራሉ፡፡ እኔም በዚህ ቤት በእንግድነት ታድሜአለሁ፡፡ ወደ ቤት የኼድኩበት ዋናው ምክንያት የጥምቀት በዓል ከአካባበው ከሚኖሩ ማኅበረሰቦች የድግስ የአዝማሪና የማኅበረሰቡን ግንኙነት ለመመልከት ፈልጌ ነው፡፡ ዓላማየን ተናግሬ የአዝማሪዎችን ግጥም በማስታወሻዬ እንድይዝ አስፈቅጀ በክብረ በዓሉ ታደምኩ፡፡

የአቶ ደመቀ ቤት እንግዳው አዳራሹ ሞልቶ በታዛና በትርፍ ቤቱ ኹሉ ታድሟል፡ ሰውዬው በአካባቢው ማኅበረሰብ መለኪያ እና መጠሪያ ባዕለ ጸጋ ናቸው፡፡ እራት ከተበላ በኋላ ጭፈራና ዘፈን ተጀምሯል፡፡ የጠላ አሳላፊው ቁሞ ጥሩ ጠላ እየተከታተለ እየሞላ እየተዘፈነ ቆይቶ ሊቀ መኳስ ቸኮል ከባለቤታቸው ጋራ ተነሡ፡፡ ከንዳ ወደ በር ከበር ወደ ንዳ እየተዘዋወሩ ያቀነቅናሉ፡፡ ከአቀነቀኗቸው ቃል ግጥሞች መካከል ከላይ ለመረጃ የጠቀስኩትን ቃል ግጥም አንዱ ነው፡፡ ይህ ቃል ግጥም ታዳሚውን እና የቤቱን ባለቤቶች ትልቅ ርካታ እንደሰጣቸው ከእልልታውና ከጭብጨባው ተረድቻለሁ፡፡

ባለቤቶቹን እና የድግሱን ታዳሚዎች በሐሤት እንዲሞሉ ያደረገበት ምክንያት በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሱት ፍሬ ሃሳቦች ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል የሀብት መጠን፣ የቤተ ክርስቲያን አክባሪነት፣ የጥምቀት ዘካሪነት፣ እንግዳ ተቀባይነት፣ የዕድሜ ልመና የመሳሰሉት ዋና ዋና ሐሳቦች ናቸው፡፡ የጎንደር ማኅበረሰብ ዝክር ለሚዘክር እና ታቦታትን ለሚያስቀድስ ምእመን ትልቅ ቦታ አለው፡፡ በግጥሙ ውስጥ የዚህ ሰብእና ያላቸው መሆኑ መጠቀሱ እና መነገሩ

ምስክርነት መስጠት ስለኾነ ባለቤቶቹን ዐልፎ ቤተ ዘመዱንም በደስታ የሚሞላ ነው። ሌላው እንግዳና አዝማሪ ከቤታቸው የማይጠፋ መኾኑ መገለጹ ነው። እንግዳ በጎንደር ማኅበረሰብ ዘንድ ሃይማኖታዊ እና ታሪካዊ አንድምታ ያለው በመኾኑ ትልቅ ቦታ አለው። በማኅበሩ ዘንድ ሃይማኖታዊ ታሪኩ የሚመዘዘው ከአብርሃም ነው። ይህን በተመለከተ ቄስ ደስታው ዓለሙ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *አብርሃም የተባለው ደግ ሰው እንግዳ ከቤቱ ካለገባ እኽል አይቀምስም ነበር። በዚህ ደግ ሥራው የተመቀኘው ሰይጣን ራሱን በድንጋይ ፈንክቶ ወደ አብርሃም ቤት የሚኼዱትን እንግዶች ከመንገድ እየጠበቀ "እኔን ፈንክቶኛልና ወደ አብርሃም ቤት አትኺዱ እያለ ይከለክል ነበር። በዚህ ምክንያት ሦስቱ ሥላሶች ሐምሌ ሰባት ቀን ወደ አብርሃም ቤት በእንግድነት ኼዱ። በዚህ ተደስቶ አብርሃምም አዝሎ ወደ ቤቱ አስገባቸው። ወይፈን አርዶ አስተነገዳቸውና ወይፈኑ ተነስቶ ስብሐት ለአብ፣ ስብሐት ለወልድ፣ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ በሎ አከበረ። በእንግዳ ተቀባይነቱ አብርሃም ከበረ" (ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/06/12 ቃ.መ)።*

ከዚህ ሃይማኖታዊ ታሪክ መነሻነት ጎንደር ማኅበረሰቡ እንግዳ የሚቀበልን ሰው ያከብራል፣ ለሰብእናውም ከፍ ያለ ቦታ ይሰጠዋል። አዝማሪ በጥምቀት ክብረ በዓል እጁ ከሚፈታ፣ ስሙ ከሚጠራ፣ እንግዳ ከሚቀበል ሰው መርጦ ይገባል። በዚህም የነ ደመቀ ልዕልና ይከብራል። የጥምቀትን በዓል የሚዘክር ሰው በጎንደር ማኅበረሰብ ለአምላክ ቅርብ እና ለፈጣሪ ተገዥ ተደርጎ ይወሰዳል። በረከተ እግዚአብሔር አይለየውም ተብሎም ይታመናል። አርባ አራቱ ታቦታት በወጡበት እና ወንዝ ባደሩበት ቀን የሚዘክር ይከበራል፤ የሚደብቅ ይረገማል የሚል እምነት አለ። እንደነ አቶ ደመቀ ያሉ ለሀገር የተመቹ የተባረኩና የተቀደሱ ሰዎች ብዙ ዘመን እና ረጅም ዕድሜ ይሰጣቸው ዘንድ አቀንቃኙ አርባ አራቱን እየጠራ ይማፀናል። ይህ ተማፅኖ የሰዎችን ልብ በርብሮ የአዝማሪዎቹን ኪስ ይሞላል። በጎንደር ማኅበረሰብ ዘንድ አርባ አራቱን እየጠራ ዕድሜና ጤና መለመን ትልቅ ስፍራ ይሰጠዋል። የጎንደር ማኅበረሰብ አርባ አራቱን ከአፉ አያወጣም። በጥል ጊዜ ለማብረድ እና በእንግድነት ግልገላ ጊዜ በአርባ አራቱ ይዠሃለሁ ይላል። ጠብ እና አምባጓሮ ሲነሣ በአራባ አራቱ አቁም ካላ የተከፈተው አንደበት ይለጎማል፣ የተመዘዘው ሰይፍ ይመለሳል (ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 *ቃ.መ* እና መ/ር ሀረገወይን ተክሌ 11/05/2013 *ቃ.መ.*)። እንደዚኹም በወንዝ፣ በቀትርና በዐመድ በሰይጣን የተለከፈ ሰው ወይም ቡዳ ዛር እና መጋኛ ወግቶታል ተብሎ ሲታሰብ በአርባ አራቱ ይዠኻለሁ ከዚህ ሰው ውጣ ይባላል። አርባ አራቱ ለጎንደር ማኅበረሰብ ኹሉ ነገሩ ናቸው። የጥምቀቱ ጉዳይም ከአርባ አራቱ ጋራ የሚያያዝ ነው (ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 *ቃ.መ* እና መ/ር ሀረገወይን ተክሌ 11/05/2013 *ቃ.መ.*)።

የአርባ አራቱ ስም ተጠርቶ ዕድሜ መለመኑ እነ አቶ ደመቀ ይደርሳል ብለው እንዲያምኑ ያደርጋል፡፡ እነ አቶ ደመቀ እና እነ ወይዘሮ ቀኑብሽ ቀርቶ በቤቱ የተጠራው ቤተ ዘመድ በዚህ አንደተደሰተ የሚያስረዳው ዓለም አጫዋች ቸኮል ያገኘው ሽልማት ነው፡፡ በጥምቀት ክብረ በዓል ለአዝማሪ አለመሸለም እንደ ነውር ወይም የሚያሳፍር ኹኔታ ያለ ይመስላል፡፡ አዝማሪዎቹን ቤተ ዘመዱ ከዐሥር ብር እስከ ኀምሳና መቶ ብር ድረስ ሲሸልሟቸው ተመልክቻለሁ፡፡ ከቤተ ዘመድ ከሰበሰቡት ብር በተጨማሪ ከእነ አቶ ደመቀ ደግሞ አንድ ፍየል ተሸልመዋል፡፡ በዚህ መልኩ ሲታይ የጎንደር ጥምቀት ለአዝማሪዎች ያለው የምጣኔ ሀብት ደጋፊነት በውል የሚነሣ ነው፡፡ ከምጣኔ ሀብቱ በተጨማሪ የጥምቀት በዓል ዕሴትን በማስቀጠል፣ የአዝማሪዎችን እና የማኅበረሰቡን ግንኙነትን በማጠናከር በኩል ትልቅ ፋይዳ አለው (ቄስ ደስታው ዓለሙ 15/05/12 ቃ.መ፤ አዝማሪ ቸኮል 12/05/12ቃ.መ፤ መ/ር ሀረገወይን ተክሌ 11/05/2013 ቃ.መ እና አዝማሪ ጋሻው ሙጨየ 11/05/2013 ቃ.መ)፡፡

# ምዕራፍ ስምንት፡- የጥምቀት ክብረ በዓል ሰባዊ ንጽሕና እና አንድምታው

የጎንደር ጥምቀት በሰዊ ፋይዳ ላይ ያለው መገለጫ መንፈሳዊና ሥጋዊ ይዘት ያለው ነው፡፡ እነዚህን ኹለት ሰባዊ እና ጸናን ጉዳዮች ደግነትን የሚሰብኩ፣ ፍቅርን የሚያጸኑ፣ ሥነ ምግባርን የሚቀርጹ፣ ይቅር ባይነትን የሚያላምዱ ናቸው፡፡ እነሱም ከራስ ጋራ፣ ከአምላክ ጋራ፣ ከባላንጣ ጋራ፣ ከእጣ ፈንታ ጋራ፣ ከሰው ጋራ እና ከተፈጥሮ ጋራ መስማማትን ያሳድጋሉ፡፡

## 8.1. የጥምቀት ክብረ በዓል እና ግብረ ገብነት

ግብረ ገብነት በአንድ ማኅበረሰብ መዋቅር ውስጥ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ የሚቀጥል እና በባህል ላይ የተመሠረተ በጎ ተግባር ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ከግብረ ገብነት አኳያ ፋይዳው ጎልቶ የሚታይ ነው፡፡ በጎንደር ጥምቀት ወጣቶቹ አዛውንቶችን የመደገፍ፣ ቅድሚያ የመስጠት፣ መንገድ የመጥረግ ምንጣፍ የማንጠፍ፣ በአጠቃላይ የመታዘዝ፣ የማክበር፣ የመረዳዳት እና ጸጥታውን የማስከበር ሥራዎችን ይተገብራሉ፡፡ ወጣቶች በዚህ ቀን ደከመን እና ሰለቸን አይሉም፡፡ በፊታቸው ላብ እየተንቆረቆረ በቅንነት እና ታዛዥነት መንፈስ አምላክን እና ኅብረተሰቡን ያገለግላሉ (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ 12/05/2013 ቃ.መ)፡፡

የጎንደር ጥምቀት መቃረቡ ሲበሰር ጀምሮ የተጣላው የሚታረቅበት፣ ቀማኛው የሚመልስበት፣ በዳይ የሚክስበት ወቅት ነው፡፡ በጥምቀተ ባሕሩ ጀምሮ እስከ ጥምቀቱ ፍጻሜ ምእመናኑ ተስማምቶና ተከባብሮ በዓሉን ያከብራል፡፡ "ሳል ይዞ ስርቆት ቂም ይዞ ጸሎት" እንደሚባለው በዚህ ዕለት እያንዳንዱ ሰው የነበረውን መጥፎ አመል ከቤቱ ትቶ የሚወጣበት ነው፡፡ ጥምቀት ፍጹም የሆነ የግብረ ገብነት መነሻ ስላለው በዚህ የተባረከ ቦታ ሁሉም ሰው በሰላምና በጸባይ አክብሮ ይመለሳል፡፡ ይህን በተመለከተ አቶ ጌትነት አመራን የጎንደር ጥምቀት ለወጣቱ ምን የግብረገብነት ፋይዳ አለው የሚል ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ወጣቱ ‹‹ደጋጎች መጀን›› ይላሉ ሙስሊሞች ሲናገሩ፡፡ ያገሬ ገበሬ ሲያርስ ‹‹ኸረ ተው ተመለስ እሱ ነው ደምበሩ››፣ ጎበዝ የተለመው አይጠፋም ደንበሩ›› ይላሉ፡፡ ወጣቱ የሚገራው በጎንደር ጥምቀት ነው፡፡ ወጣቱ ጥምቀትን በጣም ያከብራሉ፡፡ ግብረ ገብነትም አላቸው፤ አይቻቸዋለሁ፡፡ በዚህ በተወሰነ ዓመት ወጣቶች ሰውን በጣም ያከብራሉ፡፡ በጥምቀት በዓላት ወጣቱ ስላከበረ አደለም እንጼ በዚያን ቀን ምንጣፉን እያነጠፈ፣ ታቦቱን*

*እየከበከበ የሚያስገባ። እንዴ ሽማግሎች ዳር ለዳር እያሉ ኮበሌውም እየፈከረ ታቦቱ ዙሮ እስኪገባ ወጣቱ ነው አሌንታችን (ጌትነት አመራ 13/05/2011 ቃ.መ)።*

የጎንደር ጥምቀት ትልቅ የግብረ ገብ ትምህርት ቤት መሆኑን መረጃው ያረጋግጣል። ወጣቶች ዝቅ ብለው ምንጣፍ በማንጠፍ፣ መንገድ በመጥረግ፣ ሽማግሌዎችን በመደገፍ፣ ሕጻናትን በማቀፍ፣ እንግዶችን በመቀበል፣ ጸጥታውን በመጠበቅ የተለያዩ በጎ ተግባራትን ሲፈጽሙ ይስተዋላል። በጎ ተግባራትን የሚደርጉት በተናጠል ሳይሆን በአብዛኛው በጽዋ ማኅበር የተደራጁ ናቸው።



*(በጽዋ ማኅበር የተደራጁ ወጣቶች በጎንደር ጥምቀት ከአጥኚው ጋራ 2013 ዓ. ም)*

በ2013 ዓ.ም በጥምቀቱ ዕለት የመንገዱን ግፊያ እና መጨናነቅ ወግ ለማስያዝ የሚታትሩ ወጣቶችን አግኝቻለሁ። ለዚህ ሥራ ያነሳሳችሁ ምንድን ነው? የሚል ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ነበር። እነሱም የጎንደርን ጥምቀት በየ ዓመቱ ለማስከበር በማኅበራቸው በሙሴው አማካኝነት ስለት እንዳለባቸው እና ስለታቸውን እየተወጡ እንደሚገኙ አስረድተውኛል። የጎንደር አካባቢ ወጣቶች የሚካኤል ጽዋ ማኅበር፣ የገብርዔል ጽዋ ማኅበር፣ የጊዮርጊስ ጽዋ ማኅበር፣ የእስጢፋኖስ ጽዋ ማኅበር፣ የዮሐንስ ጽዋ ማኅበር የሚባሉ መንፈሳዊ ማኅበራት አሏቸው። እነዚህ በማኅበር የተደራጁት ወጣቶች ከመካከላቸው

የሚያስተዳድራቸው ሙሴ አላቸው፡፡ በሙሴው አማካኝነት በጽዋው ያልተገኘ እየተቀጣ፣ የተጣላው እየታረቀ፣ የቀማው እየመለሰ ወደ በጎ መንገድ እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡ ወጣቶቹ በማኅበራቸው አማካኝነት በዓንድ ላይ ስለሚበሉ፣ ስለሚጠጡ፣ ስለሚለብሱ እና ስለሚወያዩ ብዙ ማኀበራዊ እና ሰባዊ ጉዳዮችን ያከናውናሉ፡፡ በጎንደር ጥምቀት ጊዜ እነዚህ ማኅበራት ብዙ መንፈሳዊ እና ሃይማኖታዊ የሆኑ በጎ ትግባራትን ያከናውናሉ (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ 12/05/2013 ቃ.መ)፡፡

አቶ ጌትነት አመራ የተባሉ መረጃ ሰጪዬ ስለ ጎንደር ወጣት እና ጥምቀት ግንኙነት ወጣቱ በጣም ሰው አክባሪና ጉልበቱን ለበጎ ነገር እንደሚያውለው አውቃለሁ የሚል መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ የጥምቀት መነሻ ሃይማኖታዊ እና ለሰው ልጆች ብቻ የሚውል በመሆኑ የጥምቀት ታሪክ ወጣቱን በግብረ ገብነት እንዲመራ አድርጎታል፡፡ በጎንደር ጥምቀት ላይ የሚደረገውን የመከባበር እና የወጣቱን ሥርዓት የተመለከተ ሰው መንፈሳዊ ቅናት እንደሚያድርበት አቶ ጌትነት አመራ አስረድተውኛል፡፡

አቶ ጌትነት የሙስሊሞችን “ደጋጎች መጀን” እና “ኧረ ተው ተመለስ እሱ ነው ደንበሩ ጀግና የተለመው አይጠፋም ደንበሩ” የሚለውን ዓረፍተ ነገር የተጠቀሙት ምንን ለመግለጽ እንደሆ ጠይቄያቸው ነበር፡፡ እሳቸውም *“ሰዎች በህግ መመራት እና “በህግ አምላክን” ማወቅ እንደሚገባቸው የሚገልጥ ነው”* የሚል መልስ ሰጥተውኛል፡፡ ሰፋ ባለ መልኩ አንድ ሰው የሚውልበት፣ የሚያድርበት፣ የሚበላው፣ የሚጠጣው፣ የሚናገረው፣ የሚመለከተው፣ የሚሰማው፣ የሚያሸተው፣ የሚቀምሰው፣ አጠቃላይ የሚፈጽማቸው ተግባራት ገደብና ድንበር ሊኖራቸው ይገባል በሚል ይገልጹታል፡፡

ከደንበር መውጣትና ፈር መልቀቅ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊና፣ ማኅበራዊ ቅጣትን የሚያስከትል እንደሆነ የአቶ ጌትነት መረጃ ያስገነዝባል፡፡ ከዚህ ላይ በደንበር ውስጥ የሚከናወነው ምንድነው የሚለው ጥያቄ መመለስ ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ በድንበር ውስጥ መሆን በሥነ ምግባር እና በግብረ ገብነት መመራትን ያሳያል፡፡ ከድንበር ማለፍ ደግሞ ማኅበረሰቡ የማይነኩ ጸያፍ ብሎ ፈረጃቸውን እኩይና ስህተት ተግባራት ይተረጉማል፡፡ ደንበር ማለፍ የማይሰበሰብ፣ የማይከወን እና የተዝረከረከ አካሄደን የሚተረጉም ነው፡፡ ደንብ ሲጣስ፣ ገደብ ሲታለፍ ማኅበረሰቡ በባህሉ እና በሥርዓቱ መሠረት የሚጥላቸው ቅጣቶች አሉት፡፡ እነዚህ ቅጣቶች የአካባቢውን ህግ እና ወግ የማስከበር፣ እሴት እና ባህል የማስጠበቅ ፋይዳ

አላቸው። እነዚህ ቅጣት መጣያ ባህላዊ እሴቶች ከትውልድ ትውልድ በማኅበረሰቡ ውስጥ እንደ ጥምቀት ባሉ ክብረ በዓላት እየተነገሩ እና እየተተረኩ የመጡ ናቸው። ይህን በተመለከተ ስለ ጎንደር ጥምቀት በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚነገረው ታሪክ ለግበረ ገብነት ትልቅ ፋይዳ ይኖረው ይሆን? የሚል ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው አባ እንባቆም ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *የጎንደር ጥምቀት ሁሉም ታቦቶች ወጥተው አገሩን፣ አድባሩን፣ አሽከሩን፣ ጨቅላውን፣ ወጣቱን፣ አዛውንቱን፣ የታመመውን፣ የታሰረውን እንስሳውን ሳይቀር ይባርካሉ። እነሱ ሲባርኩ ነውር ያደረገውን እንዳያደርግ ለአንድና ለኹለት ዓመት ይታገሱታል። የጥምቀት ያላጨበጨበ ታቦቱን ያላከበረ አይባረክም። ከቤት መዋልም ያስቀስፋል። የኩታራው (የሕጻናት) መባረኪያ ቀን ነው ጥምቀት። አሽከር የሚያድግ፣ ጥጃ የሚፈነጥዝ አርባአራቱ ወጥቶ ሲባርካቸው ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥን ንጹህ አድረጎ መቅረብ ነው። ዓለም ማየት ነው። የጎንደርን ጥምቀት ያላየች እረኛ ሞቷ ነው። ሁሉም በጥምቀት ታቦቱ ሲወጣ መባረክ አለበት። ትዳር ፈላጊውም፣ ትምህርት ፈላጊውም፣ ወረት[101] ፈላጊውም፣ እድሜና ጤና የሚገኘው በታቦቱ ፊት ልብን እንደ ብርሴ ለቅልቆ መቅረብ ነው። አብሉኝ አጠጡኝ አይልም ከተንኮል መራቅ ነው የሚፈለግ (አባ እንባቆም 10/05/ 2013 ቃ.መ)።*

አባ እንባቆምን በጥምቀት ዋዜማ የከተራ ከታቦታቱ መውረድ በኋላ ከምሽቱ 2፡10 ላይ በመቋሚያው ድንኳን ውስጥ ተገናኝተናል። እሳቸው በካህናቱ ማኅሌት መቆሚያ ውስጥ ሥርዓተ ቁመቱ እስኪጀመር ድረስ ቃለ መጠይቅ አካሂደናል። አባ እንባቆም መንበረ መንግሥት መድኀኔ ዓለም አካባቢ ሠለስቱ ቤተ ክርስቲያን በመሪጌትነት ለበርካታ ዓመታት ያገለገሉ ናቸው። ስለ ጎንደር ጥምቀትና ስለ ጥምቀቱ የሚነገረውን ታሪክ ዐዋቂ ናቸው። እኔም በጽሞና ከእግራቸው ሥር ሁኘ የሰጡኝን መረጃ በማስታወሻዬ አስፍሬአለሁ።

የአባ እንባቆም መረጃ እንደሚያስረዳው የጎንደር ጥምቀት እየተነገረ እና እየተተገበረ በሕፃናት ጆሮ እየፈሰሰ፣ በዐይን እየታየ፣ በአእምሮ እየተቀረጸ የሚማሩት እና መልሰው የሚያስተምሩበት የግብረ ገብ ትምህርት ቤት ነው። የጎንደር ማኅበረሰብ ጥምቀት ሲቃረብ እና ሲመጣ አርባ አራቱን ታቦታት እያነሣ እና እየዘከረ በቤተሰብ፣ በሰፈር፣ በደብር፣ በቀበሌ የነበሩ ጥላቻዎችን ያስወግድበታል። በዚህ መልኩ ግብረ ገብነትን እና ማኅበረሰባዊ ዕሴቶቹን ለልጆቹ ያስተምርበታል። ስለሆነም የጎንደር ጥምቀት ማኅበረሰቡ በመልካም ነገር የሚባረክበት ዕለት ተብሎ ስለሚታመን ኹሉም እንደውሃው ለመባረክ ይተጋል። ከዚህ ጋራ

---

[101] ወረት ማለት የነጋዴ ጥሪት፣ ጥሬ ገንዘብ፣ መነገጃና ትርፋማ መሆንን የሚመለከት ነው።

ተያይዞ የአባ እንባቆም መረጃ የሚያሳየው የጎንደር ጥምቀት ከሕፃናት እስከ ዐዋቂ፣ ከእጽዋት እስከ እንስሳት የሚባረኩበት ቀን መሆኑን ይገልጻል። በማንኛውም የሥራ መስክ ሆነ ሙያ የተሰማራ ግለሰብ ሥራው የሚሠምርለት በጥምቀት በዓል ሲባረክ እንደሆነ ማኅበረሰቡ ያምናል። ነጋዴው የሚያተርፈው፣ ገበሬው የሚያፍሰው፣ አዝማሪው የሚከስበው፣ ሰክሰክ ሰሪው የሚሸምነው በጥምቀት ሲባረክ ነው።

የጥምቀት ቡራኬ ይደርሰው ዘንድ ደግሞ ማኅበረሰቡ ውስጡን ንጹሕ ማድረግ እንዳለበት ያምናል። በዚህ እምነት በጥምቀት ሰሞንም ሆነ ከጥምቀት በፊት የአካባቢው ማኅበረሰብ ከቂም በቀል እና ከክፉ ተግባር ራሱን ንጹሕ አድርጎ ለመቅረብ ይዘጋጃል። ይህ ዝግጅት በኹለት መንገድ የሚታይ ነው። አንደኛው ከላይ እንደተጠቀሰው በተሰማራበት ሙያ ትርፋማ ለመሆን በመፈለግ ነው። ኹለተኛው ግብረ ገብ መኾን ከመቅሰፍት እና ከጥፋት ያድናል የሚለውን እምነት በልቡ በመትከል ነው። ብዙ ጊዜ የጥምቀት ክብረ በዓል የግብረ ገብነት ማስተማሪያና ማስቀጠያ መንገዶቹ ሦስት ናቸው። እነሱም አንድም ቡራኬ፣ አንድም መቅሰፍት፣ አንድም ስለት ናቸው።

ማኅበረሰቡ ስለ መቅሰፍት ካለው ፍራቻ እና ስጋት የተነሣ "መቅሰፍት" የሚለውን ስም ለመጥራት እንኳ ይቸገራል። መቅሰፍት በማኅበረሰቡ ዘንድ ያለ ዕድሜ፣ ያለ ጊዜ፣ ያለ ወቅት እና ያለ ፍርድ ስለ ክፉ ሥራ የሚታዘዝ መዓት እንደሆነ ያምናል። በዚህ መልኩ አምላኩን በበደለ፣ ታቦታቱን በተደፋፈረ፣ ሽማግሌን በአዋረደ እና ክፉ ትግባር በፈጸመ ግለሰብ ላይ መቅሰፍት ይወርዳል[102] ተብሎ ይታመናል። በዚህ መልኩ አርባ አራቱ ታቦታት በሚወጡበት የጎንደር ጥምቀት የሚታደም ማንኛውም የአካባቢ ነዋሪ ራሱን ንጹሕ አድርጎ መቅረብ ይጠበቅበታል። ይህ ዕሳቤ ከልጅነት ጀምሮ እየተነገረ እና እየተተረከ ስለሚመጣ ግለሰቦቹ ግብረ ገብነትን እንዲማሩ ያደርጋል። በመኾኑም የጎንደር ጥምቀት ስለ ጥምቀቱ የሚደረገው ትረካ ዋና የግብረ ገብነት ማስተማሪያ እና መባረኪያ መንገድ ነው። የጎንደር ማኅበረሰብ ይህን መባረክ በመሻት እና ሳይባረክ ከዋለ የሆነ ነገር ይገጥመኛል ወይም በረከት ይቀርብኛል ብሎ በማሰብ በከፍተኛ ግፊ እና ጭንቅንቅ ወደ ባሕረ ጥምቀቱ እና ወደ ታቦታቱ የሚደረግ ጉዞ አለ። ይህ በእርብራብ እና በእንጨት ላይ የሚደረግ ጉዞ በመኾኑ አንዳንድ ጊዜ አደጋ የሚያስከትልበት ሁኔታ ይገጥማል። ይሁን እንጅ ማኅበረሰቡ በዚህ ቀን

[102] ከላይ የሚታዘዝ የእግዚአብሔር ቁጣ እንደሆነ የሚገልጽ ነው።

በትግሥት እና በመቻቻል ግፊውን ተቋቁሞ እየተረገጠ እና እየወደቀ በርብራቡ ላይ ዐልፎ በረከቱን ይካፈላል፡፡



*(ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ለመባረክ እና ጸበል ለመረጨት የሚደረግ የርብራብ ላይ ጉዞ 2013 ዓ.ም)*

ይህ በሥነ ምግባር የተመሠረተ ጉዞ በሚደረግበት ወቅት የወደቀውን የሚያነሡ፣ ወደ ኋላ የተመለሰውን የሚደግፉ፣ ሌባን የሚቆጣጠሩ ከዚያው ጉዞው ከሚደረግበት ውስጥ በርካታ ወጣቶች ይገኛሉ፡፡ ይህን ምልከታዬን ይዤ የዚህ ዓይነቱን ሥነ ምግባር ወጣቱ እንዴት ተማረው? የሚል ቃለ መጠይቅ በ12/05/2013 ለኹለተኛ ጊዜ ለአባ እንባቆም ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም ይህ ዓይነቱ ልምድ እና ተግባር "እንደ ውሐ ፈሳሽ፣ እንደ እንግዳ ደራሽ" በአንድ ቀን ጀምበር የተገኘ አይደለም፡፡ ይልቁንም ከልጅነት ጀምሮ ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚነገረው ታሪክ በወጣቱ አእምሮ ውስጥ የተቀረጸ እንደሆነ መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

ይህ ስለ ጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል የሚደረገው የታሪክ ነገራ ከሃይማኖታዊ አስተምህሮው ውጭ በማኅበረሰቡ ውስጥ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ትውፊት ነው፡፡ ይህ የሚነገረው የጥምቀት ታሪክ እና የጥምቀቱ ሥርዓት ተዳምሮ ሰዎች በግብረ ገብነት እንዲመሩ የማድረግ ዐቅም አለው፡፡ የሚደረገው የታሪክ ነገራ ልብ የመመሰጥ፣ የማማለልና አንዳንድ ጊዜም በእነ እከሌ ላይ ደረሰ ስለሚባል ሰዎች በአጽንኦት ይቀበሉታል፡፡ ይህም ጥሩ ይሠሩ የነበሩ የእነ እከሌ ዘር በረከት አገኘ እና ተንኮለኞች የነበሩ እነ እከሌ ደግሞ ጣመኑ፣ መነመኑ፣ አነሱ፣

ፈለሱ የሚል ታሪክ ስላለው ግለሰቦች በጥሩ ሥነ ምግባርና ግብረ ገብነት ራሳቸውን ለማነጽ ጥረት ያደርጋሉ (አባ እንባቆም 12/05/ 2013 ቃ.መ.)፡፡

ሦስተኛው እና ሌላው የግብረ ገብነት መማሪያው ስለ ጎንደር ጥምቀት የሚደረገው ስለት ነው፡፡ የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ በየ ዓመቱ በጥምቀት በዓል ላይ ስለት የመሳል የቆየ ዕሴት አለው፡፡ የስለት ዓይነቱ የጉልበት፣ የገንዘብ እና የበጎ ተግባር ድርጊት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ወጣቱ የታቦቱን ምንጣፍ በማንጠፍ፣ ሰዎችን በማክበር ጥምቀቱ ስኬታማ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ስለ ስለት ምንነትና ሁኔታ መ/ር እንባቆምን ጠይቄያቸው "ምእመኑ ስለት የሚገባበት መንገድ ብዙ ነው፡፡ ስለት የሚገቡባቸው መንገዶች ይዘታቸው ሰላማዊ ነው" የሚል መልስ ሰጥተውኛል፡፡ በተጨማሪም ወጣት ምስጋን ሞላ የተባለውን ግለሰብ ምንጣፍ በማንጠፍ ታቦታቱን ሲሸኝ ውሎ ታቦት ከገባ በኋላ መስቀል አደባባይ አግኝቸዋለሁ፡፡ ፈቃደኝነቱን ጠይቄ ለዚህ ተግባር ያነሳሳህ ምንድን ነው የሚል ጥያቄ አቀረብኩለት፡፡ ምስጋን የራሱን እና የሌሎቹ ጓደኞቹ አገልግሎት መነሻው ስለት እንደሆነ ነግሮኛል፡፡ *"አሁን እኔ የ12ኛ ክፍል ተማሪ ነኝ ውጤቴ እንዲያምርና ለቁም ነገር እንድበቃ ነው የማገለግለው"* (ምስጋን ሞላ 11/05/ 2013 ቃ.መ) በማለት አስረድቶኛል፡፡ ቁም ነገር የሚለውን የምስጋንን ቃል ስወስደው በብዙ መልኩ የሚተረጎም ነው፡፡ ማንኛውም ሰው እንደ ስራ ባህሪውና ስራ ዘርፉ ባስመዘገበው ውጤታማነት ልክ ቁም ነገር ሰራ ተብሎ ይወሰዳል፡፡

ስለሆነም ቁም ነገር ነጋዴው በንግድ ሥራው፣ ገበሬ በግብርናው፣ ተማሪ በውጤቱ፣ መምህር በማስተማሩ፣ ካህን በክህነቱ፣ ሊቃውንት በዕውቀቱ ስኬታማ የሚሆኑበትን መንገድ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ በየ ዓመቱ ስለት በጎንደር ጥምቀት ትልቅ የግብረ ገብነት ማዕቀፍ በመሆን ያገለግላል፡፡ ወጣቶቹ በተሳሉት ስለት ሁሉ ይደርሳል ብለው ያምናሉ፡፡ በዚህ ምክንያት ክፉ ነገር ከመሥራት ተቆጥበው የጥምቀትን በረከት በመውሰድ የተሳሉትን ስለት ይጠባበቃሉ፡፡ በጥምቀት ዕለት የሚደረገው በጎ ሥራ ልጆችን ከስርቆት፣ ከሃሜት፣ ከስንፍና፣ ከተንኮልና ከክፋት እንዲርቁ ደርጋል (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 2013 ቃ.መ. እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ 2013 ቃ.መ.)፡፡

## 8.2. የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል እና ፍቅር[103]

“የጥምቀት በዓል የፍቅር በዓል ነው። የጥምቀት አመጣጥ ራሱ እግዚአብሔር አብ የሰውን ልጅ ከመውደዱና ከማፍቀሩ የተነሣ አንድያ ልጁን ወደዚህ ዓለም ላከ”። ከሚለው ሃይማኖታዊ ሀረግ ይመዘዛል። ይህ ሃይማነታዊ ታሪክ በጥምቀት አክባሪዎቹ ምእመናን ዘንድ ተደጋግሞ እየተተረከና እየተነገረ የመጣ ነው። ይህ ዕሳቤ በማኅበረሰቡ ዘምድ ዘልቆ የገባ በመኾኑ የጎንደርን ጥምቀት ሲያከብሩ ፍቅር የሚለውን ዕሳቤ በውስጣቸው ይሰንቃሉ። ጎንደር ባሕረ ጥምቀቱ ከሚገኝበት ማንኪት ከሚባለው ቦታ በዋዜማው ባደረግኩት ምልከታ ጓደኛሞች ሲገናኙ ይሳሳማሉ። ልጃ ገረዶች በጥምቀተ ባሕሩ ተገናኝተው በመነፋፈቅ ስሜት አብረው እጅ ለእጅ ተያይዘው ወዲያና ወዲህ ይላሉ። ልጃ ገረዶቹ ከአቻ ጓደኞቻቻው ጋራ ብዙ የፍቅር ተግባቦት መፍጠሪያዎች አሏቸው። ከእነዚህ መካካል ተመሳሳይ ሥሬት፣ ተመሳሳይ ጫማ እና ተመሳሳይ ቀሚስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በጥምቀት ዕለት ልጃ ገረዶቹ የሚፈጽሙት ተመሳሳይ አጊያጊያጥ ፍቅራቸውን እና አብሮነታቸውን ማሳያም፣ ማስቀጠያም ነው።

የጥምቀትን ክብረ በዓል ወጣቶቹ እና ልጃ ገረዶች ባልንጀሬ እና አብሮ አደጌ እየተባባሉ እስከመጨረሻው የሚዘልቅ ፍቅር ይመሠርቱበታል። በጥምቀት ዕለት ባደረግኩት ምልከታ ከቀበሌ 18 የመጡ መጣት ሴቶች አንዳቸው ለሌላቸው እየተደጋገፉ፣ ሲሮጡ ካንዳቸው ይልቅ ለሌላቸው መንገዱን እየለቀቁ ወደ ጥምቀቱ ክብረ በዓል እየተሯሯጡ ሲሄዱ አገኘኋቸው። አለባበሳቸው እና ሁኔታቸውን ተመልክቸ አጭር ቃለ መጠይቅ እና ፎቶ ግራፍ ለጥናቴ እንደማነሣቸው አስፈቅጀ ጥያቄየን ቀጠልኩኝ ይህ አለባበሳችሁ እና አጊያጊያጣችሁ የሚስገኝላችሁ ፋይዳ ምንድን ነው? ብየ ጠየኳቸው። ከመካከላቸው ደመቁ የምትባለዋ ልጃገረድ *“በመካከላችን ነፋስ እንዳይገባ በጥምቀት እንደዚህ ውለን ለዓመቱ አድረሰን ብለን፣ ዓይለየን የምንልበት ነው። በአዘቦትም ቢሆን የጥምቀት ባለንጀርነታችን አንለያይም፤ በጣም ነው የምንዋደደው” (ደመቁ ደመወዝ 11/05/13 ቃ.መ)* የሚል መረጃ ሰጥታኛለች።

[103] በሰዎች ዘንድ ስለሚኖረው መተሳሰብ፣ መረዳዳት፣ መዋደድ እና መስማማት የቆመ ነው። ከሩካቤ ወይም ከተቃራ ጾታ ጋራ የሚኖረውን ፍቅር አይመለከትም።



*(በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል በቀኝ በኩል ደመቁ እና ባልንጀሮቿ አለባበስ እና አጊያጊያጥ 2013 ዓ.ም)*

ሌላው በካህናቱና ሊቃውንቱ በጥምቀተ ባሕሩ ዋዜማ፣ በባሕረ ጥምቀቱና በጥምቀቱ ጉዞ ላይ አንዳቸው ለሌላቸው ክብር በመስጠት አዲስ እንግዳ ካህን ሲመጣ ከወገብ ሽብረክ ብለው እጅ ሲነሳሱና ምርፋቅ ቅደሚያ በመስጠት የተለየ ፍቅር ሲያሳዩ በ2011 ዓ.ም በነበረው የጥምቀት ክብረ በዓል ምልከታዬ አረጋግጫለሁ፡፡

ይህን ምልከታዬን ይዤ ለአባ ገብረ ሥላሴ 03/06/ 2011 ዓ.ም በሰሚው ቅዱስ ሚካኤል ወቅዱስ ጊዮርጊስ ደብር ቃለ መጠይቅ አደረግኩላቸው፡፡ የቃለ መጠይቁ ማጠንጠኛ በጎንደር ጥምቀት ዋዜማ የከተራ፣ በባሕረ ጥምቀቱ እና በጥምቀቱ ዕለት የተመለከትኩትን የካህናት፣ የሊቃውንት፣ የሕፃናት፣ የልጃ ገረዶችና የዘማርያኑን ሲገናኙ የሚያደርጉት ሰላምታ፣ ትሕትና፣ ፍቅር፣ አክብሮት እና ሂደት ምን አንድምታ አለው? የሚል ነበር፡፡ አባ ገብረ ሥላሴ ባቀረብኩት ቃለ መጠይቅ መነሻነት ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ጌታችን አምላካችን እየሱስ ክርስቶስ እንዳሳየው የጥምቀት በዓል ፍቅር ነው፡፡ ፍቅር ካለ ደግሞ ሁሉ ነገር ማንኛውም ሰው ይታደማል፡፡ ማንኛውም የእምነት ተከታይ በጥምቀት ቀን ጎንደር ይታደማል፡፡ መስለውም ሆነ በግልጽ ያለው መንፈሳዊ፣ ሃይማኖታዊ፣*

> *ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ አከባበር ስለሚያስደስታቸው በበዓሉ ይታደማሉ፡፡ ለምን ቢባል የታዩት ትሪቶች የፍቅር፣ የሰላምና የዕውቀት ናቸው፡፡ እነዚህ የተካተቱበት ስለሆነ ማንኛውም ሰባዊ ፍጡር ደግሞ እነዚህን የሚጠላ ስለሌለ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የእምነቱ ተካታይም ሆኑ ከእምነቱ ውጭ ያሉት ይታደማሉ፡፡ ግዴታ መልካም ነገር ስላየ ለመታደምና ለመሄድ የሚያሰገድደው ሌላ ሰው ሳይሆን ተፈጥሯዊ ባህሪው ነው፡፡ ዘና ብሎ ተዝናንቶ መጥቶ ተዝናንቶ ይሄዳል (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)፡፡*

መረጃው እንደሚያሳየው ጥምቀት መሠረቱ ክርስቶስ ነው፡፡ ክርስቶስ ደግሞ ፍቅር እንደሆነና ጥምቀት ደግሞ የፍቅር በዓል መኾኑንና የሚያጸና ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀትና በጥምቀቱ የሚታደሙት ምእመናን፣ ቱሪስቶች አጠቃላይ በበዓሉ የሚሳተፈው ማንኛውም ሰው በክብረ በዓሉ ፍቅር የተማረከ ነው፡፡ በጥምቀት ክዋኔ የሚመለከታቸው በሙሉ ፍቅር የሚጭሩ ናቸው፡፡ የጥምቀቱ ሥርዓት ፍቅርን ያጭራሉ ሲባል ከዋዜማው ጀምሮ እስከ ጥምቀቱ ፍጻሜ ድረስ ለሕፃናት፣ ለአረጋውያንና ለእንግዶች የሚደረገው ጥንቃቄ ሰዎች ለሰዎች የሚደርጉትን ፍቅር የሚያሳይ ነው፡፡ የጎንደር ማኅበረሰብ በጥምቀት የታደመውን ሰው በፍቅር የመመልከት የማክበር እና የማስተናገድ ትልቅ ልምድ አለው፡፡ ይህን በተመለከተ ይታያል ደመወዝ የተባሉ መረጃ ሰጭዬ የሚከተለውን ዝርዝር መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ከደብረ ወርቅ ምሥራቅ ጎጃም ነው የመጣሁት፡፡ እና የጎንደር በዓል በጣም ደስ ይላል የዛሬ ኹለት ዓመትም መጥቸ ነበር፡፡ የጎንደር ባህል በጣም ደስ ይላል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከበረው ጥምቀት ሁሉ ጎንደር ደስ ይላል፡፡ ሁሉን አይቻለሁ፡፡ በየ ዓመቱ ጎንደር እየመጣሁ አከብራለሁ፡፡ የእራያዎች አለባባስ እና አጨፋፈር ደስ ስለሚል እስኪ ይህን የራያ ልብስ እስኪ ለብሰን ጎንደር እንዋል ብለን ነው የመጣነ፡፡ እይው ጎንደር መጠናል፡፡ አሁን እኔ የሆነ ቦታ ላይ ጎድገዋዲት ሆቴል ገባን፡፡ አኔና እሱ (ጓደኛዬ) ጥልቅ ብለን ስንገባ ወንበር ሰው በዝቶ ሞልቷል፡፡ ኑ፣ኑ ብለው ብድግ ብደግ ብለው ከዚህ ቁጭ በሉ፣ ከዚህ ቁጭበሉ፣ ሲሉን በጣም ነው ደስታ የተሰማን፡፡ አልጋው በጣም ውድ ነው፡፡ ጠይቀነዋል በበዓል ምክንያት ነው ብለውናል፡፡ አልጋው በጣንም ውድ ነው፡፡ እንዴ ጎድጓዲት ሂድን የጎንደር ልጆች ብድግ ብድግ ብለው ነው ያስቀመጡን እንግዳ ተቀባዮች ናቸው፡፡ አለበሳቸው አንድ ዓይነት ነው፣ አካሄዳቸው አንድ ዓይነት ሥርዓታቸው፣ ጭፈራቸው አንድ ዓይነት ነው፡፡ በቃ ጎንደር ለየት ያለ ነው (ይታያል ደመወዝ 12/05/2013 ቃ.መ)፡፡*

ይህ የሚያሳየው የጎንደር ጥምቀት ዕለት የጎንደር ማኅበረሰብ ሰዎችን እንግዶችን የመቀበላቸው መጠን ምን ያህል እንደሆነ የሚያመላክት ነው፡፡



*(ዘውዱ ይርጋ እና ይታያል ደመወዝ ከአጥኚው ከግራ ወደ ቀኝ በቃለ መጠይቅ ላይ 2013 ዓ.ም)*

በዚህ ዕለት የሚታየው ለሰው ልጅ የሚሰጠው ፍቅር ሰላማዊ እና ትሕትና የተሞላበት ነው፡፡ ሰውን የመጥላት ዕሳቤ ተወግዶ በምትኩ በዚህ ቀን የአካባቢው ማኅበረሰብ ለሰው ልጅ አምላክ የሰጠውን ፍቅር በማስታወስ እና ልብ በማለት ራሱን የሚያስገዛበት ዕለት ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀት ሕግ የተሠራው ከአምላክ ነው የሚለውን መነሻ በመያዝ በማኅበረሰቡ ውስጥ ከትውልድ ትውልድ እየተላለፈ መጥቶ አሁንም ድረስ የፍቅር በዓል መሆኑ ቀጥሏል (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)፡፡

በጥምቀቱ ዕለት ከጥምቀተ ባሕሩ ታቦቱ ተነሥቶ ወደ ፒያሳ መስቀል አደባባይ በማምራት ላይ እያለ ዘፈኑ፣ ወረቡ፣ ሆታው፣ እልልታው፣ ዝማሬው በየዓይነቱ የሊቃውንቱ ለብቻ፣ የካህናቱ፣ የልጃገረዶቹ፣ የወጣቶቹ የሰንበት ዘማርያኑ የቱሪስቱ በዳር፣ በዳር እያገመገመ የሚመለከተው ሁሉ ትልቅ የሆነ መንፈሳዊና ሥጋዊ እርካታን የሚያስገኝ ነው፡፡ ይህን መንፈሳዊ ድባብ ለመመልከት መንገዱ አልበቃ ብሎ በአጥር ላይ፣ በድንጋይ ላይ እና በዛፍ ላይ የሚንጠላጠሉ ተመልካቾች ብዙ ናቸው፡፡ ግፊ ቢኖርም እንኳን የሚጣላ ወይም የሚተናኮል አይታይም፡፡ እንዲያውም ሲደጋገፉ አንተ ትብስ አንተ፣ አንቺ ትብሽ፣ አንቺ ሲባባሉ ተመልክቻለሁ፡፡ ይህን ሃሳብ ለሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ በጎንደር ጥምቀት

ከካህናቱ፣ ሊቃውንቱ ጀምሮ እስክ ደቂቅ ሕፃናት ድረስ ተስማምተው የሚያከብሩት ምን አመክንዮ ይኖረው ይሆን? ብየ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ ቀጣዩን ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

> *የጎንደር ጥምቀት ሴቶች እልል እያሉ ከጥምቀተ ባህር አንስቶ እስከ መስቀል አደባባይ ወይም እስከ አጼ ፋሲል ቤተ መንግሥት ድረስ ታቦታቱ ሲወርዱም ሲመለሱም ያለው የህዝብ ብዛትና ሆታው የእልልታው ድምቀት ህዝቡን አንድ አድርጎ ገፋኸኝ ገፋሸኝ አይባባልም፡፡ የፍቅር በዓል ነው፡፡ እንዳውም ፍቅር የሚገዛበት በዓል ነው፡፡ ተደጋግፎ አንዱ ቢገፋው እንኳን ስቆ ተሳስቆ ነው እንጅ በፍቅር የሚለያይ መጣላት የለም፡፡ ጠብን በጥምቀት በዓል ወደ ፍቅር እሚለወጥበት ተለውጦ የምናይበት በዓል ነው (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

የሊቀ ሊቃውንት መረጃ እንደሚያሳው የጎንደር ጥምቀት ፍቅር ለአንድ ቀን፣ ወይም ለአንድ አፍታ ታይቶ የሚጠፋ፣ ወይም ታልቦ የሚነጥፍ ሳይሆን የፍቅር ሀብት ከዓመት እስከ ዓመት የሚሸመትበት መሆኑን ገላጭ ነው፡፡ “በጎንደር ጥምቀት ጠብ ወደ ፍቅር የሚቀየርበት ነው” ሲባል በጥምቀት የታየው ፍቅር ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ መሠረት ስላለው የጥምቀት ዋዜማ፣ ዕለትና ማግስት የሚያልቅ ወይም እንደ ጥምቀት ልብስ ከጥምቀቱ በኋላ ተወልቆ የሚቀመጥ ሳይሆን ሰዎች የፍቅርን ምንነት ተምረው ገንዘባቸው የሚያደርጉበት ነው፡፡ በጥምቀቱ ላይ የተመለከተቱትን የጥምቀቱ ተዳሚዎች ከጥምቀት በኋላም ይደግሙታል፡፡ ሕፃናት በጥምቀት የተመለከቱትን ፍቅር ወደ ቤተሰቦቻቸው ሲመለሱ በጓደኞቻቸውና የዕድሜ አቻዎቻቸው ላይ የመግባባትና የመዋደድ ዕሳቤን ያዳብሩበታል፡፡

የጎንደርን ጥምቀት ከሁሉም በዓላት በተለየ የፍቅር በዓል የሚያደርገው ታቦታቱ ተሰልፈው ከሊቃውንቱና ካህናቱ ኅብረ ዜማ ጋራ በወርቅ ጥላ፣ በወርቅ ጽና፣ በወርቅ፣ ብርና እጸ መስቀል፣ አጊጠው መታየታቸው ነው፡፡ ሰው በሰው ፊት አንዳች ነውር ነገር ሊያደርግ ይከብደዋል፡፡ ይህ እሚከብደው ከሆነ ደግሞ አምላኩ እያየው በአምላኩ ፊት ነውር ነገር ሊያደርግ አይፈልግም፡፡ በዚህ ምክንያት አምላክ የሚወደውን ለማድረግ ይጥራል፡፡ አምላክ ከሚወደው ነገር ደግሞ ፍቅር አንዱ ነው፡፡ በጥምቀት ዕለት በታቦታት ፊት ነውር ነገር አይሰራም፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት የአካባቢው ማኅረሰብ ተከባብሮ ተፈቃቀሮ እና ተስማምቶ እንዲኖር የሚያስችል ሰባዊ ፋይዳ አለው (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)፡፡

### 8.3. የጥምቀት ክብረ በዓል እና ሀዘን

የጥምቀት ማግስት የቃና ዘገሊላ ወ/ሮ መልሸው ጌጡ በገቡልኝ ቃል መሠረት ከጧቱ ኹለት ሰዓት ላይ በአዘዞ ቅዱስ ሚካኤል የታቦት ማደሪያ አቅራቢያ ኹለት ሕፃናት ልጆቻቸውን ይዘው ጠብቀውኛል። ወ/ሮ መልሸው ጌጡ ባለቤታቸው ካረፉ ሦስተኛ ወራት መቆጠሩን ነግረውኛል። እስከ ጥምቀት ዕለት ድረስ በክፋ ሀዘን ጥቁር ለብሰው፣ ወገባቸውን ታጥቀው ከሰው ተራ ወጥተው ሀዘን ላይ እንደነበሩ ከፊታቸው በተጨማሪ በአንደበታቸውም አስረድተውኛል። የጥምቀት ዕለት ሀዘንተኛ ተከፍቶ እንዳይውል በማኅበረሰቡ ዘንድ ጥረት ይደረጋል። እሳቸውም ለአምላካቸው እና ለኹለቱ ሴት ልጆቻቸው ሲሉ እንደ አካባቢው ማኅበረሰብ ሕግ እና ሥርዓት መሠረት በጥምቀት ክብረ በዓል ተገኝተዋል። ከዚህ በኋላም ሀዘኑ ሀዘን ቢሆንም ከጥምቀት በኋላ ሀዘናቸውን ለመርሳት እንደሚሞክሩ አጫውተውኛል። *"ምን አባቱ በጥምቀት እነዚህን ኹለት ጨቅላዎች አላስከፋም ወደ እሱ ነው የሄደ" (ወ/ሮ መልሸው ጌጡ 2013 ቃ.መ)* በማለት በጥምቀት ሀዘናቸውን ለማስወገድ ያላቸውን ጥረት በቃለ መጠይቁ አስረድተውኛል። ሕጻን ናርዶስ ንጉሤ እና ማያ ንጉሤ የአባታቸውን ሞት ረስተው በጎንደር ጥምቀት ተገኝተዋል። *"ጥምቀትን እምናከብረው ከታቦቱ ጋራ አብረን ነው። እኛ በመጨፈር ጥምቀት ሲቃረብ ደስታ ነው የሚሰማን የአገራችን ባህል ስለሆነ ልብስም ጎንደርኛ ይገዛልኛል። ጫማም የሻሹ አስተሳሰሩ ጎንደርኛ ነው የድሮ (ሕጻን ናርዶስ ንጉሤ፣ 12/ 05/ 2013 ቃ.መ)* የሚል መረጃ ሰጥተውኛል። ይህ የሚሳየው የጎንደር ጥምቀት ሀዘንን በማስረሳት እና ወደ ቀደመ ሕይወት በመመለስ በኩል ለአካባቢው ማኅበረሰብ ከፍተኛ ሰባዊ ፋይዳ መኖሩን የሚሳይ ነው።



*(ናርዶስ ንጉሤ፣ ማያ ንጉሤ እና ወ/ሮ መልሸው ጌጡ ከግራ ወደ ቀኝ በቃለ መጠይቅ ላይ 2013 ዓ.ም)*

የዚህ አካባበቢ ማኅበረሰብ ዘመድ አዝማድ ሲሞትበት እስከ ዓመትና ከዚያ በላይ ጥቁር በመልበስ፣ ሴቶች ጸጉር በመላጨት፣ ፊት በመንጨት፣ ሰቆቃ የበዛበት ሀዘን ያደርጋሉ። ከዚህ መሪር ሀዘን አብዛኛውን የሚገላገሉት የጥምቀት ክብረ በዓልን አስመልክቶ ነው። የጥምቀት ሰሞን ሀዘንተኞች *"ደስ አይበለው፣ ተይው ተወው አሁን ፈጣሪን ማስቀየም ነው"። በጥምቀት አዝኖና ተክዞ አይዋልም። የሚል ምክር ከጎረቤትና አቅርብ ዘመድ ይሰነዘራል* (ልዕልና ሃይለ መስቀል 12/12/2011 *ቃ.መ*)። የነፍስ አባት፣ አበልዥ እና አገቡኝም ኹሉ በጎንደር የጥምቀት ሰሞን ሃዘንተኞች ሃዘናቸውን እንዲረሱ ይመክራሉ፤ ይገስጻሉ። ሀዘንተኞቹም ቢሆን በጥምቀት ዕለት አንገታቸውን ደፍተው ጥቁር ለብሰው መዋልን አይመርጡትም። በዚህ ምክንያት በጥምቀቱ እንዲታደሙና እንዲውሉ ይደረጋሉ። በጥምቀት ጥቁር መልበስን ማኅበረሰቡ የሚያወግዘው በመሆኑ ምክንያት ጥቁር ልብስ በመተው በምትኩ ነጭ ይለበሳል። በሀዘን የነጣውን ጸጉራቸው ቅቤ እንዲቀባ ይደረጋል። ይህ የሚሆነው በጥምቀት በዓል ምክንያት ነው። በጥምቀት የወለቀው የሀዘን ማቅ ተመልሶ አይለበስም፤ የተቀባው ጸጉር ተመልሶ አይነጣም። ይህ የሚሆንበት ዋናው ምክንያት ፈጣሪን በማስቀየም የሟችን ነፍስ ዓርያ ገነት እንዳትገባ ይከለክላል የሚል እምነት በማኅበረሰቡ ዘንድ መኖሩ ነው። የቅርብ ሥጋ ዘመድ ወይም ወዳጅ ነፍስ ገነት ትገባ ዘንድ በመፈለግ ሀዘንተኞች ጥምቀትን ያከብራሉ (መልሸው ጌጡ እና ቀለብ ሰጠኝ 2013 *ቃ.መ*)።

በመሆኑም ለሟች ነፍስ ሲባል አዘንተኞች ሀዘናቸውን ረስተው ጥምቀትን ያከብሩታል። "ሌላው ለሰው ደስ አይበለው" የሚለው ብሂል ነው። ይህ ብሂል ሀዘንተኞች ሀዘናቸውን እንዲረሱ ከሚያስችላቸው ምክንያት አንዱ ነው። መካሪዎች የጥምቀትን በዓል ምክንያት በማድረግ እስኪ የመጣው ዓመት በዓል ነው። ይህን ዓመት በዓል ለወዳጅ ለጠላት ደስ አይበለው፣ ምን አባቱ ተውት፣ ተይው፣ በዓሉን አክብሩ እና እሱ እኮ አያጣም፤ የሚል ማስጠንቀቂያ አዘል ምክር ስለሚመከሩ ከሀዘናቸው ወጥተው በዓሉን ያከብራሉ። ይህ "እሱ እኮ አያጣም" የሚለው ማስፈራሪያ ቃል የተጎዳውን ሀዘንተኛ ወደ ራሱ ተመልሶ፣ ሀዘኑን ረስቶ፣ የጥምቀትን በዓል እንዲያከብር የሚደርግ ሀይለ ቃል ነው። የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት ችላ ማለት ሌላ ተጨማሪ ችግር ያመጣል ተብሎ ይታመናል። በዚህ ምክንያት ተጨማሪ ችግር በቤተሰቡ እንዳይመጣ በመስጋትና በመፍራት በዓሉን ነጭ ለብሰው በማክበር ያለፈውን ሀዘን እንዲረሱ ይደረጋል። በክርስቶስ ጥምቀት የተቀደደው እዳ ደብዳቤ

ተመልሶ እንደማይመጣ ኹሉ የተረሳው ሀዘን፣ የተወለቀው ጥቁር ልብስም ተመልሶ አይለበስም (አበራሽ ነጋ እና አብነት ሰማ 2013 ቃ.መ)፡፡



*(አበራሽ ነጋ፣ አብነት ሰማ፣ ህይወት ገብሩ፣ ደመወዜ ዘለለው፣ የኛነሽ መለሰ፣ ቀለብ ሰጠኝ፣ አገሬ መስፍን ከግራ ወደ ቀኝ የቡድን ውይይት 2013 ዓም)*

የጎንደር ጥምቀት ከመከራ በተጨማሪ ገንዘብ የጠፋበት፣ በሬ የሞተበት፣ ቤት የተቃጠለበት ሰው ከችግሩ እና ከምሬቱ እንዲፈወስ ያደርጋል፡፡ በገንዘብ ችግር የደረሰበት ሰው የገንዘቡን እርዳታ ከዘመድም ሆነ ከማኅበረሰቡ በእርዳታ መልክ ሊያገኝ ይችላል፡፡ ችግሩ የተከሰተው በምቀኛ፣ በሽረና፣ በባላንጣ፣ በአስማተኛና በሟርተኛ ነው ብሎ ካሰበ በዚህ ቀን ለአርባ አራቱ ታቦታት ይሰጠዋል፡፡ በዚህ ምክንያት የሚያንሰላስለውን የውስጥ ብሶትና ችግር ለአምላክ በመስጠትና “አንተ አሳየኝ” ብሎ በመሳል የጎንደርን ጥምቀት ያከብራል (መልሽው ጌጡ እና ቀለብ ሰጠኝ 2013 ቃ.መ)

ብዙ ጊዜ የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ ከስጋትና ክፋት፣ ከባላንጣ እና መቅሰፍት የሚፈወሰው በኹለት መልኩ ይመስላል፡፡ አንደኛው በጥምቀቱ ባለው የእሰክስታ፣ የሆታ፣ በአጠቃላይ

በክዋኔው በመማረክ ለጊዜውም ቢሆን ሀዘኑን መርሳት መቻሉ ነው፡፡ ኹለተኛው ደግም በጥምቀት ዕለት አምላክ ጠላቶቹን ይቀጣልኛል ወይም መቅሰፍቱን ያርቅልኛል የሚል አምነት በውስጡ በማሳደሩ ነው፡፡ በእነዚህ ኹለት መሠረቶች የጎንደር ጥምቀት የአካባቢውን ማኅበረሰብ ከሀዘንና መከራ፣ ከመቅሰፍትና ስጋት በመፈወስ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ሰዎች መጻዒውን ጊዜ የተሻለ እንደሚኾን ተስፋ በማድረግ ሕይወታቸውን እንዲቀጥሉ ያስችላል፡፡ በተለያየ ምክንያት ብሶትና ችግር የደረሰባቸው ሰዎች በጎንደር ጥምቀት ሲታደሙ በሚያዩት መልካም ነገር እና በሚሰሙት ጣፋጭ ዜማ ከሀዘናቸው የመረጋጋትና የመጽናናት እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡ ይህን በተመለከተ ሊቀ ሊቀውንት እዝራ ሀዲስ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *በእውነቱ የጎንደር ጥምቀት ከዚህ ከዐፄ ፋሲል ይጀምርና ሊቃውንቱ "ሀዲጎ ተስዓ ወተስዓተ ነገደ" የሚለውን ዝማሬ በቅዱስ ያሬድ የተዘጋጀውን ባህሩ ከተባረከ በኋላ ሕዝቡ ከተመለሰ በኋላ ጥምቀተ ባሕሩ ቤተ መቅደስ ፊት ለፊት ታቦታቱ ተሰልፈው ጳጳሳቱ አንድ ላይ ሁነው ሊቃውንቱ ጥንግ ድርብ፣ ካባውን፣ ሸማውን፣ ሱፍ ካባውን፣ የብር መቋሚያ፣ የብር ጸናጽል ይዘው ሻሽ ጠምጥመው ሲያስረግጡ "ሀዲጎ ተስዓ" ሲሉ መላእክት ከሰማይ ወርደው በቤተ ልሔም ከኖሎት ጋራ "ስብሐት ለእግዚአብሄር በሰማያት ወሰላም በምድር" ብለው ያቀረቡትን ዝማሬ ይመስላል፡፡ እና ያን ጊዜ ልዩ፣ ልዩ መንፈሳዊ ስሜትን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኝ ያደርጋል፡፡ ሰው ይለወጣል ማለት ይቻላል፡፡ በአሉን ለማክበር የመጣው ሰው ተለውጦ ሀዘንተኛም ቢሆን ሀዘኑን ረስቶ የደስታ ሰው ይሆናል፡፡ ሙሉ በሙሉ ሰው መንፈሳዊ ይሆናል፡፡ ሥጋዊው ሁሉ ተለውጦ መንፈሳዊ ይሆናል (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

ከላይ የተወሰደው የሊቀ ሊቃውንት መረጃ የሚያስረዳው በጎንደር ጥምቀት የሚሳተፍ ሀዘንተኛ ሀዘኑን እንደሚረሳና አንደሚረጋጋ የሚያሳይ ነው፡፡ ከመረጃው ውስጥ "ሰው ይለወጣል" የሚለውን ቃል ብንወስድ የሰው መለወጥ ከነበረበት ድባብ መመሰጥን፣ ማምለጥንና ከህመም መፈወስን የሚተረጉም ነው፡፡ ይህም ከዐልጋ ቁራኛ፣ ከደወዬ ዳኛ መፈወስን፣ ከስደት መመለስንና ለማኅበረሰቡ መብቃትን ያሳያል፡፡ በዚህ በዓል ዕለት በቤተ ልሔም እረኞችና መላእክት በአንድነት "ምስጋና ለእግዚአብሔር በሰማያት ሰላም በምድር" ሰውን ወዶታልና" የሚለው ቃል በጎንደር እንደተፈጸመና ያን ዕለት እንደዚህ እንደሆነ ማኅበረሰቡ ያምናል፡፡ የእረኞችና የመላእክት በአንድ ላይ ዝማሬ ማቅረብ አንድነትንና ሰላምን የሚተረጉም ነው፡፡ የመላእክትና ሰዎች ኅብረት በቤተ ልሔም መታየትን የሚዘክር አሁንም በጎንደር ጥምቀት ማኅበረሰቡ በአንድነት ያከብረዋል፡፡ ሰውን ወዶታልና የሚለው ጥምቀትም የሰው ልጆች ብቻ ለሰዎች የተሠራች ሰዎችን የምታገለግል እንድትሆን አድርጓታል፡፡

በዚህም በጥምቀት ዕለት ሰዎች ሁሉ ከውስጥና ከውጭ ስቃያቸው የሚያመልጡበት የሚፈወሱበት ዕለት ነው፡፡

### 8.4. የጥምቀት ክበረ በዓል ቁሳዊ ባህል ሰባዊ ፋይዳ እና አንድምታቸው

በዚህ ሥር በጎንደር ጥምቀትና ጎንደር መገለጫ የሆኑት የጎንደር ቀሚስ፣መቀነት፣ ጥልፍ፣ አገልግል፣ ጃኖ፣ ሽማ እና መሰል የጎንደር መገለጫ የሆኑ ባህላዊ አልባሳት እና ቁሶች ለሰባዊ ፋይዳ ያላቸው አንድምታ የሚተነተንበት ነው፡፡ ቀሚስና መቀነት በጎንደር ጥምቀት ተደጋግፈው የሚያምሩ እና የሚለበሱ ናቸው፡፡ ይህን በመልበስ ሕፃናት ሴቶች፣ ልጃ ገረዶች እና ወይዘሮዎች በክብረ በዓሉ ደምቀውና አብበው ይታያሉ፡፡ ቀሚሱ የተጠለፈ ጥለቱ ወይም ጥበብ ከኋላ በኩል ከታች ከተረከዛቸውና ከቀሚሱ ህዳግ ላይ ይገኛል፡፡ ይህ ቀሚስ በሽንሽን መልክ በአረንጓዴ፣ በቢጫ፣ በቀይ፣ በጉራቻ፣ በድባዓይነት፣ በእሸቴ እና በወይነ ጠጅ ከሰባት ቀለማት ጥለት የተሠራ ነው፡፡

መቀነቱ ከኋላ በኩል ማግ ሲኾን በቀኝና በግራ በኩል ጥለቱና ትፍትፍ ወይም የጥበብ ጌጥ በረጅሙ አለው፡፡ የጎንደር ሴቶች ቀሚስ ለብሰው መቀነቱን የሚታጠቁት አንድ ወይም ኹለት ዙር ነው፡፡ የመቀነቱ የጥለት ክፍል ጌጥ በፊታቸው በኩል ወደታች ይወርዳል፡፡ የቀሚሱ ጥልፍ ደግሞ ከትክሻቸው ወደፊትና ወደ ኋላ ቀጥታ ከወረደ በኋላ ከታች የመስቀል ቅርጽ ያለው ነው፡፡ በግራና ቀኝ ትክሻቸው በኩል ያለው የቀሚስ ጥልፍ እኩልና ተመሳሳይ ነው፡፡ ምንም ዓይነት የቁመት፣ የብዛት፣ የቀለም፣ የቅርጽ ልዩነት የለውም፡፡

ወደ ታች የሚወርደው ሰፊ መስመር ጥልፍ ደግሞ ከኋላቸው በኩል ይነሣና የአንገትን ከብ በመያዝ ወደ ፊት በኩል በመሄድ በሰፊው ወደ ታች ይወርዳል፡፡ ከላይ አንድ ሁኖ ወርዶ ወደ ታች ሲደርስ ከዋናው ጥልፍ በመነሣት ወደ ጎንና ጎን ቅርንጫፍ እያወጣ ይሄዳል፡፡ የጥልፉ ውበት በጣም የሚደምቅ እና የሚስብ ነው፡፡



*(የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ እና መቀነት አለባበስ በጥምቀት ክብረ በዓል 2013)*

ይህ የጎንደር ጥልፍ ቀሚስና መቀነት የራሱ የሆነ ሰባዊ እና ማኅበረሰባዊ አንድምታ አለው፡፡ ጥልፍ ቀሚሱ ንጹሕ እና ዐዲስ መሆኑ በጥምቀት ክብረ በዓል ሰዎች ራሳቸውን ከሚያበሳጫቸውና ከሚያሳስባቸው ነገሮች ወጥተው በደስታ እና በንፁሕ ህሊና የማክበራቸው ተምሳሌት ነው (ህይወት ገብሩ፣ መልሽው ጌጡ እና የኛነሽ መለሰ 2013 ቃ.መ)፡፡

ዐዲስ ውሐ ያልነካውና ያላደፈ መሆኑ ደግሞ ሰዎች በጥምቀት ዐዲስ ሕይወት የመጀመራቸው ተምሳሌት ነው፡፡ ዐዲስ መሆን ከዚህ በፊት የነበረውን ውስብስብ የቤት እና የውጭ ጣጣ በጥምቀት በማደስ እንደገና እንደ ዐዲስ አዲስ ሕይወትን የመጀመር አንድምታ አለው፡፡ በዚህም ሰዎች ምንም ያክል የሚያስጨንቃቸው በርካት ምክንያቶች ቢኖሩም እንድገና ነገሮች ይሻገራሉ፡፡ በአሮጌው ዐዲስ፣ በመከራው ደስታ፣ በችጋር ጥጋብ፣ በኀጢያት ጽድቅ፣ በጨለማ ብርሃን፣ በክረምት፣ በጋ እንደሚታካ ሁሉ ዐዲስ ህይወት በጥምቀት የሚጀመር መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ ይህም ክርስቶስ ከተጠመቀ በኋላ ያለውን የሰው

ልጅ ነጻ መውጣት ይተረጉማል (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ 2013 ቃ.መ)፡፡

የጎንደር ቀሚስ በማኅበራዊ ደረጃቸው ላቅ ያሉ የማኅበረሰብ ክፍሎችን፣ ነገሥታቱን፣ ሊቃውንቱን እና ካህናቱን የሚወክል ነው፡፡ በዚህ ማኅበረሰብ ውስጥ ሥልጣነ ክህነትን እና ሹመትን ከቀሚስ ጋራ ያያይዙታል፡፡ የጎንደር ማኅበረሰብ ዕሴቱን ሃይማኖቱን አክባሪም ዘካሪም ነው፡፡ እነዚህ እሴቶቹና ሃይማኖቱ ከነውርና ነቀፋ፣ ከመበረዝና መከለስ እንዲጠበቁለት ይፈልጋል፡፡ የቀሚሱ ንጽሕና ከሥርዓተ ክህነት ጋራ ትይዩ ነው፡፡ ቀሚስ የማኅበረሰቡ ውክልና ነው ካልን የቀሚሱ ጥልፍ ደግሞ የማኅበረሰቡ ዕውቀት እና ትውፊት ጠቃሽ ነው፡፡ ጥልፍ ለቀሚሱ ልዩ ውበትና ጌጥ እንደቸረው ሁሉ ሃይማቱና ባህሉ ደግሞ የማኅበረሰቡን ማንነት ያስቀጥላል፡፡ የጥልፉ አንድ ኹኖ ወርዶ ከታች ዘርፋዘርፍ ማውጣቱና የመስቀል ቀርጽ መያዙ አንድም የማኅበረሰቡን አንድነት የሚያዘክር ነው፡፡ አንድም ማኅበረሰቡ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የሃይማኖት፣ የሥራ የመሳሰሉት እና የተለያዩ ማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና ተፈጥሯአዊ ልዩነቶቹን የሚያሳይ ነው፡፡

የቀሚሱ ጥልፍ በስተመጨረሻው የመስቀል፣ የክብ እና የፀሐይ ፍንጣቂ ቅርጽ የያዘ ነው፡፡ ለጎንደር ማኅበረሰብ መስቀሉ የሃይማኖቱ፣ ክቡ የሕይወቱ እና ፀሐይ ደግሞ የተስፋው ተምሳሌቶች ናቸው፡፡ ይህም የጎንደር ማኅበረሰብ ነጻነት ያለው ተፈጥሮን የሚቀበል፣ በሃይማኖት፣ በባህል እና በህግ የሚመራ መሆኑን ያሳያል፡፡ የጥልፉ ክብ ቅርጽ መያዙ ደግሞ የማኅበረሰቡን የሕይወት ክስተቶች ጠቋሚ ነው፡፡ ከክስተቶቹ መካከል ግጭት፣ ፍላጎት፣ እርጅና፣ ሞት እና የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የፀይ ፍንጣቂ በጥልፉ ክብ ቦታ ላይ መታየቱ ደግሞ ማኅበረሰቦቹ ያላቸውን ተስፋ፣ ልእልና እና ከፍታ የሚያዘክር ነው (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ፣ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡

ሌላው መቀነት ነው፡፡ የቀሚሱ ውበትና ጥልፍ አምሮ የሚታየው በመቀነቱ ነው፡፡ የጎንደር ቀሚስ ማኅበረሰቡን፣ ሹማምንቱን እና ሊቃውንቱን የሚወክል እንደሆነ ኹሉ መቀነት ደግሞ አንድም የጎንደርን ወይዛዝርት፣ አንድም ጎንደርን ይወክላል፡፡ መቀነት ጥልፍ ቀሚሱን እንዲያምር እና ሥርዓት እንዲኖረው ማድረጉ ትዳርን የሚተረጉም ነው፡፡ በጎንደር ማኅበረሰብ ዘንድ ሹማምንቱ እና ነገሥታቱ ንግሥናውን ይያዙት እንጅ ጨፈቃ እና ማገር፣ ጥርስና ከናፍር በመሆን ንግሥናው ጽኑ፣ ማንነቱ ቋሚ እንዲሆን የሴቶቹ ሚና ከፍተኛ

ነው። ዐፄ ቴዎድሮስ ከሽፍትነት ወደ ንጉሠ ነገሥትነት ማማ ያወጡት እቴጌ ተዋበች ናቸው። የጎንደር ንግሥቶች ዙፋን ከማጽናት፣ ሕዝብ ከመምራት ቀደም ብሎ "ታቦት በራሷ፣ ቃጭል በጥርሷ" በመያዝ ቤተ ክርስቲያንን በመትከል፣ ሃይማኖትን በማደላደል በቅድስና የሚጠሩ እንደነ ወለተ ጴጥሮስ እና ክርስቶስ ሰምራ ያለ ቅዱሳን አንስት የሚተረኩበት ቦታ ነው። በዚህ መልኩ የጎንደር ማኅበረሰብ በማኅበራዊ ሥርዓቱ፣ በሃይማኖቱ፣ በፖለቲካዉ እና በቅድስናዉ ውስጥ የሴቶች ቦታ ከፍ ያለ ነው። ከዚህ አንጻር መቀነት ቀሚሱን ወግ እና መልክ በማስያዝ እና የጎንደር እመቤቶች የንግሥናውን በማጽናት በኩል ተፈካካሪዎች ናቸው (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ፣ 15/11/2011 ቃ.መ)።

ሌላው የመቀነቱ ሰባት ቀለማት መሆን ደግሞ የሰውን ባህርያት የሚተረጉም ነው። እንደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት አስተምህሮ ሰዎች ከእሳት፣ ከነፋስ፣ ከውሐና ከአፈር ከአራት የሥጋ ባሕርት እና ከልባዊት፣ ነባቢትና ኀያዊት ሦስት የነፍስ ባህርያት በድምሩ ከሰባቱ ባህርያት የተፈጠረ መሆኑን የሚያዘክር ነው። እንደዚሁም ዕሥራኤል የኢያሪኮን ከተማ ሰባት ጊዜ እየዞሩ በጸለዩ ጊዜ የብረቱ አጥር ፈራርሶ ወድቋል (መጽሐፈ ኢያሱ፣6፣15) ዳግመኛ ነብዩ ኤልሳዕ "ላዕለ ውእቱ ሕፃን ወጸለየ እስከ ሳብዕ" በሕፃኑ ላይ ሰባት ጊዜያት ጸለየ (ነገሥተ ካልዕ፣ 4፣33)። ሌላው ልበ አምላክ ዳዊትም "ሰብዐ ለዕለት እሴብሐከ" በቀን ሰባት ጊዜ አመሰግንሐለሁ ያለውን የሚተረጉም ነው። እንደዚሁም የሰባቱ ሰማየ ሰማት እና የኖኅ ቃል ኪዳን ቀስተ ደመናም ምሳሌ ተደርገው ይወሰዳሉ (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ 2013 ቃ.መ)።

ጠቅለል ባለ መልኩ መቀነት እና ቀሚስ የጎንደር ተምሳሌቶች ናቸው። የጎንደር ወይዘሮ የጎንደርን ጥልፍ ቀሚስ ከመቀነቱ ጋራ በአንድ ላይ ስትለብስ ከግለሰቧ ባለፈ የጎንደር ትእምርት ሁና ትቀርባለች። የጎንደር ትእምርት የመሆኗ ምሳሌ በጥምቀቱ ዕለት በመርከብ ላይ በመሆን በአገልጋዮች እና በደንገጡሮች እየታጀበች አውደ ምሕረቱን ትዞራለች። ከአጃቢዎቹ በተጨማሪ ሰይፍና ጎራዴ በያዙ ወታደሮችም እየተጠበቀች በጥምቀቱ ክብረ በዓል ላይ ትውላለች (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ እና መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ 2013 ቃ.መ)።



*(ጎንደርን የወክለች ባለደንገጡር ወይዘሮ በጥምቀት ክብረ በዓል በመርከብ ላይ 2013 ዓ.ም)*

ሌላው የጎንደር ልጃ ገረድ የጎንደርን ጥልፍ ቀሚስ ለብሳ መንጥቅ የሚባለውን እስክስታ ስትመታና እንደ እንዝርት ስትበር ያላት ቅልጥፍና እና ቅርጽ ከንስር አሞራ ጋራ ይፈካከራል፡፡ በምልከታዬ ያረጋገጥኩትን የጎንደር አቀንቃኝ ልጃ ገረድ የንስር አሞራ ቅርጽ እና ፍጥነት ማኅበረሰባዊ አንድማታ እና ተምሳሌት አለው፡፡ አንድም ንስር አሞራ የጀግንነት፣ የአሸናፊነት ተምሳሌት ነው፤ አንድም ንስር አሞራ የየፍጥነት እና የባላንጣ ቀጭነት ተምሳሌት ነው፤ ይህ ደግሞ የጎንደር ማኅበረሰብ አገራቸውን ሊደፍር ከመጣው ምሐዲስት እና ጣሊያንና ጋራ ያደረጉትን ተጋድሎና ድል አድራጊነት ያሳያል፡፡ በመኾኑም ንስር አሞራ የሚመስለው መንጥቅ እስክስታ የጎንደር ጀግንነት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ ሌላው ንስር አሞራ "ገጸ ሰብ ወ ገጸ እንስሳ፣ ገጸ ንስር ወገጸ አንበሳ" ከሚባሉት ከዐራቱ `ጸወርተ መንበር ኪሩቤል መካካል አንዱ ነው፡፡ በመኾኑም ንስር አሞራ ቅርጽ ያለው መንጥቅ እስክስታ ከጀግግነት መገለጫ በተጨማሪ የጎንደር ማኅበረሰብ ሃይማኖት መገለጫም ነው (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)፡፡ ስለሆነም የጎንደር ቀሚስ፣ መቀነት

እና ጭፈራ የጎንደርን ማኅበረሰብ ጀግንነቱን፣ እምነቱን፣ ፍቅሩን ተስፋውን እና ሥነ ልቦናውን የሚያሳዩ ናቸው።

### 8.5. በጥምቀት ክብረ በዓል የሚቀነቀኑ ቃል ግጥሞች እና ሰባዊ አንድምታቸው

እባብ ሰለክላኬ መንታ ነው ምላሱ፣
ሲያምኑት የከዳ ሰው አይማርም ነፍሱ።
ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው (05/11/ 2013)።

በጥምቀት ክብረ በዓል እናቶች በቁርጥ በቁርጥ ሁነው ይዘፍናሉ። እኔም ወደ አንደኛው ቁርጥ ጠጋ ብየ መከታተልና መመልከት ቀጠልኩኝ። በዚህ ጊዜ ከላይ የተወሰደውን ቃል ግጥም ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው ታቦቱ ተነሥቶ ወደ አውቶ ፓርኩ አካባቢ ሲደርስ እያቀነቀኑት አዳመጥኩኝ። ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው ከላይ የተጠቀሰውን ቃል ግጥም እየዘፈኑ እስክስታ ይወርዳሉ። የዚህ ቃል ግጥም ዋና ጭብጥ "እምነት እና ክዳት" የሚሉት ኹለት ዕሳቤዎ ናቸው። የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ አምኖ መክዳትን በትዳር፣ በገበያ፣ በመሬት መጠመንና ማስጠመን፣ በብድር እና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ መወስለትን ያወግዛል። የውግዘቱ ማጠንጠኛ ከተከዳው ሰው ይልቅ የከዳው ሰው ተልቅ ቅጣት ይጠብቀዋል የሚል ነው።

በመሆኑም ሲያምኑት የከዳን ሰው ከእባብ ጋራ ይመስለዋል። እባብ መንታ ምላስ ያለው፣ መርዛም እና ገዳይ ፍጡር ነው። ሲያምኑት የከዳ ሰው ከዚህ አውሬ ጋራ መመሰሉ የምላሱ መንታ መሆን ነው። የምላስ መንታነት መወስለትን፣ መዋሸተን እና መክዳትን ይመለከታል። የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ "በአፉ ጨው አይሟሟም"ን እንጅ "በአንድ ራስ ኹለት ምላስ"ን አይቀበልም። በምስክርነት፣ በሽምግልና፣ በአደባባይ ሰዎች አንድ ጊዜ የተናገሩትን ቃል በሌላውም ጊዜ ሊደግሙት ይገባል እንጅ ዋሾን እና ተገለባባጭን ማኅበረሰቡ አጥብቆ ይጸየፈዋል። ለዚህም ከዳተኛን ከእባብ ጋራ ያመሳስለዋል። ሌላው እባብ እንደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ቀኖና መሠረት የተንኮል፣ የእኩይ እና የሰይጣን ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል። በመኾኑም ሲያምኑት የሚከዳን ሰው ከእባብ ጋራ በማመሳሰል ክህደትን ለመቀነስ የቆመ ቃል ግጥም ነው። የማኅበረሰቡ ፈርጀ ብዙ ስምምነቶች በመተማመን ላይ የተዋጁ በመሆናቸው በዚህ ላይ አጥብቆ በማስተማር ሥርዓቱ እንዲቀጥል የሚያስችል ነው። "አይማርም ነፍሱ" የሚለው ቃል የነፍስ ጉዳይ ሰዎችን የሚያሳስባቸውና የሚያስጨንቃቸው በመሆኑ ለጉዳዩ ትኩረት እንዲሰጠው ያደርጋል። የሥጋ ጉዳይ አብዛኛው

የሚታይ፣ የሚዳሰስ እና የሚቀመስ በመኾኑ ችግሮችን ለመጋፈጥ እንደ ሩቁ እና ረቂቁ የነፍስ ጉዳይ ሊከብድ አይችልም፡፡ በመኾኑም ይህ ቃል ግጥም በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ መቀንቀኑ ሰዎች እምነታቸውን፣ ታማኝነታቸውን እንዲቀጥሉ በማድረግ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ በአብዛኛው በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የሚቀነቀኑ ቃል ግጥሞች መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ ከዚሁ ጋራ በተያያዘ ሰዎችን ወደ በጎ ነገር ለማምጣት የሚስችል ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ ከላይይኛው ቃል ግጥም በተጨማሪ በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው ቀጣዩን ግጥም ሲያቀነቅኑ አዳምጫለሁ፡፡ ይህ ቃል ግጥም እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

*ደግሞስ ለአንድየ ምን ያኮራል፤*
*ደግሞ ለአንድየ ምን ኮራል*
*ኩታውም ቀሚሱም ነገ ጧት ይቀራል*
*ደግሞ ለሚካኤል ምን ያኮራል*
*ደግሞ ለሚካኤል ምን ያኮራል*
*ኩታውም ቀሚሱም ነገ ጧት ይቀራል*
*ደግሞ ለጊዮርጊስ ምን ያኮራል*
*ደግሞ ለጊዮርጊስ ምን ያኮራል*
*ኩታውም ቀሚሱም ነገ ጧት ይቀራል*
*ደግሞ ለጻድቁ ምን ያኮራል*
*ደግሞ ለተክልየ ምን ያኮራል*
*ኩታውም ቀሚሱም ነገ ጧት ይቀራል*
*ደግሞ ለጻድቁ ምን ኮራል*
*ደግሞ ለጻድቁ ምንያኮራል*
*ኩታውም ቀሚሱም ነገ ጧት ይቀራል*
ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው (11/05/ 2013)፡፡

የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኞቹ ሴቶች ናቸው፡፡ ግጥሙ በብዙ አቀንቃኞች ብዙ ጊዜና ተደጋግሞ ሲቀነቀን ሰምቸዋለሁ፡፡ ከእነዚህ እናቶች መካከል ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው ለቃለ መጠይቁ ፈቃደኛ ሁነዋል፡፡ ወ/ሮ እማዋይን ይህ ቃል ግጥም ምን አንድምታ እንዳለው ጠይቂያቸው ነበር፡፡ እሳቸውም ቀጣዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *እኛ ጨርቅ ለብሰን፣ እህል በልተን ስንሄድ ነው እንጅ ሲለቁን "ሜዳ ሙሉ ሲይዙን ጭብጥ ሙሉ" ጭብጥ አፈር ነን፡፡ "አየ ሰው ከንቱ" ለዚህ አድሜው መኩራት ክፉ መስራት መቼም አይበጅም፡፡ ዛሬ አፈሩ አቧራው ጥሐይው አይባልም፡፡ ለሚቀረው ገላ እመቤቴ ከመንበሯ ወታ ዝም ብሎ መመልከት አይሆንም፡፡ ለጎረቤት፣ ለሁሉም ኩራት መኩፈስ ሰው አንድ ነው፡፡ ለምን እኔ አለኝ ብሎ ድሃውን መናቅ፣ ሃብታሙም እኮ እኩል*

*ሦስት ክንድ መሬት ነው፡፡ ድሃ የናቀ ነፍሱ አይማርም (ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው፣ 11/05/ 2013 ቃ.መ)፡፡*

የወ/ሮ እማዋይ ቃል መጠይቅና ያቀነቀኑት ቃል ግጥሙ ተመሳሳይ ጭብጥ አላቸው፡፡ የመረጃዎቹ ማጠንጠኛ "ኩራት" የሚባለውን ዕሳቤ ማስወገድ ነው፡፡ ኩራት የሰዎች አንዱ ባሕርይ ነው፡፡ ይህ ባሕርይ ደግሞ እኔ ከእነ እከሌ እሻላለሁ ሳይሆን እበልጣለሁ፣ ከፍ እላለሁ ሳይኾን እለያለሁ፣ የሚል ስሜትን ስለሚፈጥር አብልጦ ራስ ወዳድነትን እና ግብዝነትን ያስከትላል፡፡ የበዛ ራስ ወዳድነት ደግሞ ለሌሎች ግድ የለሽነትን ስለሚያስከትል በማኅበረሰባዊ መዋቅሩ ውስጥ ያለውን የሰዎች ግንኙነት ያበላሻል፡፡ በመኾኑም ማኅበረሰቡ ኩራትን ያወግዛል፡፡ እከሌ ወይም እከሊት ኩራተኛ ናት ከተባለ ማኅበረሰቡ በጥርጣሬ ዓይን ማየቱና መመልከቱ አይቀርም፡፡ ኩራቱ የሚመነጭበት መንገድ እንደተባለው ብዙ ነው ይሁን እንጂ፣ ሀብት፣ በዕደሜ፣ በጾታ፣ በውበት፣ ዐልፎ ዐልፎም በዕውቀት እኔ የተሻልኩ ነኝ የሚል መነሻ ሊኖረው ይችላል (መ/ር መሃሪ ጥሩር፣ 15/05/13 ቃ.መ እና ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው፣ 11/05/ 2013 ቃ.መ)፡፡

ይህ ቃል ግጥም የሰዎችን እኩልነት በማሳየት ኩራት የሚባለውን ዕሳቤ ለመቀነስ ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ ይህን ለማረጋገጥ ኩራት በምድር እንጅ ከሞት በኋላ ሁሉም ሰው እኩል እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ቃል ግጥሙን ይዡ ስለ ኩራት እሳቤ ለመ/ር መሃሪ ጥሩር ቃለ መጠይቅ አድርጌላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ "*ኩራት ትልቅ በደል ነው፡፡ ዲያብሎስን ከክብሩ ያወረደ ኩራት ነው፡፡ ነገሥታቱም በሥላጣናቸው መኩራራት ሲጀምሩ ይዋረዳሉ፤ ሃብታሞችም በሃብታቸው መመካት ሲጀምሩ እርቃናቸውም ይቀራሉ፤ ፈጣሪ የማይወደው አንዱ ኩራትን ነው* (መ/ር መሃሪ ጥሩር፣15/05/13 ቃ.መ) የሚል መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

የቃል ግጥሙ ሌላው ማስኬጃ ደከመኝ እና ሰለቸኝ ሳይሉ በጥምቀት ዕለት ፈጣሪን ማገልገል እንደሚገባ የሚያዘክር ነው፡፡ ለአምላኩ የተገዛ ሰው ለሰዎችም ቢሆን ተገቢውን ክብርና ቦታ መስጠቱ የማይቀር ነው፡፡ በቃል ግጥሙ ውስጥ አማኑኤል ተጠቅሷል፣ ከመላእክት ሚካኤል የተጠቀሰ ሲኾን ከሰው ፍጡር ደግሞ እነ ተክልየ እና ጻድቁ ተጠቅሰዋል፡፡ ይህም የጎንደር ጥምቀት አብያተ ክርስቲያን በቦታው የሚወርዱትን እነ መንበር መንግሥት መድኀኔዓለም፣ አጣጣሚ ሚካኤል፣ ፊት አቦ አባጃሌ ተክለ ሃይማት፣ ወልደ ነጎድጓድ ዮሐንስ እና መሰል አጥቢያ ቤተ ክርስቲያንን ለመዘከር ነው፡፡ የቃል ግጥሙ ሌላው ደጋግሞ የሚነሳው ኩታና

ቀሚስ ነው። ኩታና ቀሚስ ልብስን ብቻ ወክለው የመጡ ዓይደለም። ከልብስነት ባለፈ ኩታ ትዳርን የሚወክል ሲኾን በውስጡም ወልዶ መሳምን አሽቶ መቃምን ይጨምራል። ኹለተኛው ቀሚስ ነው። ቀሚስ በዚህ አውድ ስልጣንን፣ ሹመትን፣ ማዕርግን፣ ክህነትን፣ አክሊልን እና መሰል ቅባ ሜሮንና ቅባ መንግሥትን የሚተረጉም ነው። በመሆኑም በጥምቀቱ ላይ የሚሳተፉትን ከልሂቅ እስከ ደቂቅ፣ ከአዛውንት እስከ ሕጻናት፣ ከሴቶች እስከ ወንዶች ያሉትን ምእመናን ሁሉ የሚያዘክር ነው (መ/ር መሃሪ ጥሩር፣ 15/05/13 ቃ.መ)።

ይህም በሃብታሙና ድሀዉ፣ በሊቃውንቱ እና ጨዋዉ፣ በነገሥታቱና ሕዝቡ መካከል ያለውን ሰባዊ ርቀት በማጥበብ፣ ክፍተት በመሙላት ሚዛን ያደላድላል። ክፍተቶቹን እና ርቀቶቹን ለማጥበብ ተጨባጭና የምናብ መንገዶችን ይጠቀማል። በተጨባጭ ትዳር፣ ሀብትና ሹመት ሀላፊ መኾናቸውን በሚለበስና በሚወልቅ ቀሚስና ኩታ መስሎ ሲያሳይ በምናብ በኩል ደግሞ ከሞት በኋላ ያለውን ተጠያቂነትና ቅጣት በመጠቆም ሚዛናዊነት ያረጋግጣል። በዚህ መልኩ ቃል ግጥሙ ሰዎችን በማቀራረብና በማሰናሰል ትልቅ ፋይዳ አለው። ሌላው በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ተደጋግሞ የሚቀነቀነው ቃል ግጥም

አረጀሽ እያለ ሰው ኹሉ ሲያመሽ፣
ጎንደር ሙሽራነሽ ይሰፋል ልበስሽ።

(ወ/ሮ የሽ፣ ወ/ሮ፣ ወ/ሮ ባዩሽ እና 11/05/2012፣ ወ/ሮ እማዋይ እና ወ/ሮ ደጊቱ 11/05/2013 ዓ.ም) ያቀነቀኑት ቃል ግጥም ነው። የዚህን ቃል ግጥም አቀንቃኝ እንደሌሎቹ ለመያዝ እና በአንድ አቀንቃኝ ለመውሰድ የተቸገርኩበት ሁኔታ ገጥሞኝ ነበር። ይህም በበርካታ አቀንቃኞች እና በየዘፈኖቹ አጋጣሚ ሁሉ ሲዘፈን ማዳመጤ ነው። ይሁን እንጂ ከብዙዎቹ በጥቂቱ ወ/ሮ የሽ እና ወ/ሮ ባዩሽ በ11/05/2012 እና ወ/ሮ እማዋይ እና ወ/ሮ ደጊቱ ደግሞ በ11/05/2013 ዓ.ም ሲያቀነቅኑት በማስታወሻየ ይዤዋለሁ። የዚህን ቃል ግጥም አንድምታ እንዲያስረዱኝ ለነ መቶ አለቃ አስፋው ፈረዳ እና መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ በ12/05/2013 ባደረግኩት የቡድን ውይይት ላይ ቃለ መጠይቅ አድርጌ ነበር።

በውይይቱም የዚህ ቃል ግጥም አንድምታ የጎንደርን ታሪካዊ፣ ሰባዊ እና ማኅበራዊ መዋቅር ጥንካሬን፣ ጥንታዊነት እና ቀጣይነት የሚተረጉም እንደሆነ አስረድተውኛል። ቃል ግጥሙ እርጅና እና ሙሽራ በሚሉ ኹለት በሚቃረኑ ቃላት የተዋቀረ ነው። ይሁን እንጂ የጎንደር ዕድሜ መግፋት እና ዘመናትን መሻገር ለእርጅና ብሎም ለመጥፋት አይዳርጋትም። የወይን ጠጅ ዕድሜው በጨመረ ቁጥር ዋጋው ከፍ እንዲል ሁሉ ጎንደርም ዕድሜዋ በጨመረ ቁጥር ባህሏ እና ቅርሷ ይበልጥ የሰውን ቀልብ የሚስቡ መኾናቸውን የሚያዘክር ግጥም ነው። ቃል

ግጥሙ ጎንደርን ከሙሽራ ጋራ ያመሳስላታል፡፡ ሙሽራ በሰርጓ እንደምትደምቅ ሁሉ ጎንደርም በጥምቀት ክብረ በዓል ትደምቃለች፤ ትዋባለች፡፡ ስለሆነም ሙሽራ እና ጎንደር ተመሳስሎ አላቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ጎንደር በጎንደር ሴቶች፣ ልጃ ገረዶች እና ሙሽሮች ተደጋግማ ትወከላለች፡፡ ይህ በጎንደር ወይዘሮዎች የመወከል ጉዳይ ከጎንደር ሴቶች ሰብና ጋራ የተያያዘ ነው፡፡ የጎንደር ሴቶች ውበታቸው፣ ይሉንታቸው እና ማኅበራዊ ግንኙነታቸው ጥብቅ እና ጠንካራ ነው፡፡ ማንነታቸው ከማጌጥ እስከ ብልህነት እና ሙያ የሚዘልቅ ነው፡፡

የጎንደር ሴቶች ሰባዊ ማንነታቸው የሚገነባው ከሕፃንነታቸው ጀምሮ ሲኾን በሙያ የተካኑ ናቸው፡፡ የጎንደር ሴቶች በስፌት፣ በፈትል፣ በዶሮ ወጥ፣ በዝልል፣ በጠጅ መጣል እና መሰል የሴትነት መለኪያ ሙያዎች አሏቸው፡፡ በማኅበራዊ ተሳትፎም ቢሆን በፖለቲካ አስተዳደር፣ በቤተ ክርስቲያን ማስገንባት እና ባለርስትነት ከወንዶች ጋራ የሚፎካከር ታሪክ አላቸው፡፡ ይህን ታሪካቸውን ከሚዘክሩ ሴቶች መካካከል እቴጌ ምንትዋብ፣ ቆራጣ ጴጥሮስ፣ እቴጌ ተዋበች እና መሰል የጎንደር ሴቶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ጎንደርና የጎንደር ወይዘሮዎች አንዳቸው በሌላቸው ላይ እየዋሉና እያደሩ ወይም እየተዳበሉ የሚገለጹ እንጅ ተነጣጥለው የሚቆሙ አይደሉም (መቶ አለቃ አስፋው ፈረዳ እና መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/2013 ቃ.መ)፡፡

በመኾኑም “አረጀሽ እያለ ሰው ሁሉ ሲያማሽ፣ ጎንደር ሙሽራ ነሽ ይሰፋል ልብስሽ፡፡” የሚለው ቃል ግጥም የዚህን አካባቢ ማኅበረሰብ “ከፍትፍቱ ፊቱ” የሚለውን ብሂል የሚተረጉም ነው፡፡ የሙሽራ ፊት ፈገግታ ነው ይህን ፈገግታ ሰዎች በእንግድነትም ሆነ በድግስ ጊዜ ሲመጡ ማየት ይፈልጋሉ፡፡ ጎንደሬዎች እንገዶች ወደ ቤታቸው ሲመጡ የመጀመሪያው መስተንግዶ የፊት ፈገግታ ነው፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ቅጭም ያለ ፊት ያየ የጎንደር እንግዳ ጨርቁ እሰኪቀደድ ቢገለግሉት በአካባቢው ባህል መሠረት ወደ ቤት አይገባም፡፡ ከቤት ገብቶ ከሚዘነበለው ጠጅና ከሚቆረጠው ጮማ ይልቅ ከውጭ ያለው ፈገግታ ይበልጥበታል፡፡ ይህም ከሙሽሪት ፊት ጋራ ይፈካከራል፡፡ እርጅና የሚለው ቃልም ቢሆን የጎንደር መገለጫ ነው፡፡ የጎንደር ማርጀት ከመጃጀት ሳይሆን ከጥንታዊነቷ፣ ከቅርሶቿ እና ከአብነት ትምህርት ቤቶቿ ጋራ የሚያያዝ ነው፡፡ ይህም የጎንደርን የዕውቀት፣ የጥበብ እና የመናገሻ ታሪካዊ እና ቀደምት ሀገር መሆኗን ለመግለጽ የቆመ ቃል ነው፡፡ በመኾኑም ሙሽራ እና እርጅና ለጎንደር መገለጫዎች ናቸው፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ እነዚህ በጎንደር ጥምቀት የሚቀነቀኑት ቃል ግጥሞች የጎንደር ማኅበረሰብ መገለጫና ተምሳሌቶች ናቸው፡፡

እነዚህ ቃል ግጥሞች የሰዎችን ተግባቦት እና መተሳሰብ የሚያሳድጉ ናቸው። ቀጣዩ ትንታኔ ያደረግኩበት ቃል ግጥም በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ሲዘመር የሰማሁት የእምዬ ማርያም የልመና ግጥም ሲኾን ሰባዊ ባሕርይን የሚገልጽ ነው።

*ተዋሸኝ እምየ ማርያም፣*
*ተዋሸኝ እምየ ማርያም፣*
*የአማኑኤል እናት የመድኀኔዓለም።*
(ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው 11/05/2013 ዓ.ም)።

ቃል ግጥሙ ሰው ደጋፊ እና ዋስ የሚያስፈልገው ፍጡር እንደሆነ ያስረዳል። የዚህ ቃል ግጥም አቀንቃኝ ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው ናቸው። ወ/ሮ እማዋይ ገደፋው ኹለት ጊዜ ላሊበላን ስመዋል። በዚህ ምክንያት የነፍስና የሥጋን እጣ ፈንታ ጠለቅ ብለው ተረድተዋል። ተዋሸኝ አምየ ማርያም የሚለው ቃል ግጥም ማርያምን በመማጸን እፎታን የመቸር ዐቅም አለው። የቃል ግጥሙ ዋና ጭብጥ ሰዎች በሚያደርጉት የነፍስ ጥሪ ከአምላካቸው ጋራ ተገናኝተናል ብለው ስለሚያምኑ አንድም የነፍስ እርካታን ያገኛሉ። አንድም መንፈሳዊነታቸውን በማሳደግ በማኅበረሰቡ ዘንድ ሰብናቸው ከፍ ይላል። በዚህ ምክንያት ሰዎች ጥሩ ነገር መሥራት እሚጠበቅባቸው ለነፍስ ዋጋ ሲባል ነው? ወይስ ለሥጋም ጠቃሚ ነው? የሚል ጥያቄ ለመቶ አለቃ አስፋው ፈረዳ በ12/05/2013 ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ነበር። እሳቸውም *"ጽድቅና ኩነኔ ቢኖርም ባይኖርም፣ ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም"* የሚል ማስረጃ ሰጥተውኛል። ይህ ቃል በዋናነት ሰዎችን ወደ በጎ ተግባር የሚወስድ እና የሚያስተምር ነው።

ስለ ነፍስ ጽድቅና ኩነኔ ለመረዳት ፈቃደኛ ያልሆኑትን ኢአማንያን እና ከሃይማኖቱ እና ባህሉ ፊቅ እና ራቅ ያሉ ሰዎችን ጭምር የሚያስተምር ነው። ማንኛውም ሰው የሆነ ሁሉ ደግነትን መሥራት ከክፋት የተሻለ እንደሆነ የሚያጸና ነው። የመቶ አለቃ እሰፋው ፈረደ መረጃ ሃይማቱን የሚጻረር አንድምታ የለውም። ምክንያቱም የግጥሙ ዓላማ በተጨባጭ ለማስረዳት እንጅ ጽድቅና ኩነኔ የለም ለማለት አይደለም። ለዚህም ክፋትና ደግነትን በማነጻጸር ደግ የሠራ ሰው አሸናፊና ስኬታማ እንደሆነ ያስረዳል። በዚህ አካሄድ "ሥራ ለሰሪው እሾክ ለአጣሪው" የሚለውን ብሂል በማከል መጥፎ መሥራት በነፍስ ብቻ ሳይሆን በሥጋም እዳ ከፋይ መሆኑን ያስረዳል። ከዚህ ጋራ በተያያዘ እማሆይ ካባ ይመር በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ተከታዩን ግጥም ሲያቀነቅኑ አዳምጫለሁ።

*ኸረ ተይ ሥጋየ ተመከሪ፣*

*ኧረ ተይ ሥጋየ ተመከሪ፣*
*አርብ እሮብን ጹመሽ ሰንበትን አክብሪ፣*
*ኧረ ተይ ሥጋየ ተመከሪ።*
*ኧረ ኔስ ሥጋየ አቃተችኝ፣*
*ኧረ እኔስ ሥጋየ አቃተችኝ፣*
*ያለ ካሪያ[104] ሥጋ እያስመተረችኝ።*
*(እማሆይ ካባ ይመር፣ 11/05/2013/ ዓ.ም)።*

ከላይ የተወሰደው የልመና ግጥም የጥምቀት ዕለት ታቦታቱ ጉዞ ላይ እያሉ በፒያሳ አረፍት አድርገዋል። በዚህ ጊዜ የወረቡ ዝማሬ እየተዘመረ እና እናቶች በቡድን በቡድን ሁነው እያቀነቀኑ ነው። በዕድሜ የገፉ፣ የቀረቡ፣ ምንኩስናን የተቀበሉ እና ለቤተ እግዚአብሔር ቅርብ የሆኑ እናቶች ቀሚሳቸውን ለብሰው ኩታቸውን አደግድገው ፈጣሪን በችሎታቸው እያመሰገኑ ነው። ከእነዚህ እናቶች መካከል እማሆይ ካባ ይመር የላይኛውን የልመና ግጥም እያቀነቀኑ ተመልክቻለሁ። ቃል ግጥሙ የሰዎችን ባሕርይ ምነንትና ሁኔታ የሚተረጉም ነው። ሰው ሥጋና ነፍስ በሚባሉ ኹለት ተቃራኒ አምዶች የተገነባ ሕንጻ እንደሆነም ግጥሙ ያስረዳል።

እነዚህ የሰው መገንቢያ የተባሉት ሥጋ እና ነፍስ በየራሳቸው ፍላጎት የቆሙ እንደሆኑ እና ሳበው ጎትተው እንደሚባባሉ ግጥሙ ያስረዳል። በዚህ መልኩ ሰው የሥጋ እና የነፍስ ፍላጎቶች የሚሻኮቱበት ፍጡር መሆኑን ከግጥሙ ጭብጥ መረዳት ይቻላል። ይህንም እማሆይ ካባ በጥምቀት አደባባይ የሚመሰክሩበት ሁኔታ ይታያል። ቃል ግጥሙ ምስክርነት የመስጠት ወይም ኑዛዜ የመግባት እና የመጸጸት ጭብጥ ያለው ነው። እማሆይ ኑዛዜውን የሚናዘዙበት በፈጣሪ ፊት፣ በካህናቱ ፊት እና በምእመኑ ፊት በመኾኑ ምክንያት የሠሩትን ኀጢያት ወይም ጥፋት ይቅር እንደሚላቸው ያምናሉ። ቃል ግጥሙ እንደሚያሳየው የሥጋ ባሕርይ የገመድ ጉተታውን እያሸነፈ ያለ ይመስላል። ይህም "ኧረ ተይ ሥጋየ ተመከሪ፣ ኧረ ተይ ሥጋየ ተመከሪ፣ አርብ ዕሮብን ጹመሽ ሰንበትን አክብሪ" የሚለው ግጥም አረጋጋጭ ነው። በመኾኑም ግጥሙ ሰዎች በዚህ ምድር ሲኖሩ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው አጥብቆ ይመክራል። ከእነዚህ ወሳኝ ምክር እና ተግባር መካከል ጾምና አክብሮት ዋናዎቹ ናቸው።

መጾም ከዚህ ላይ ከእህል ውሐ መታቀብን ብቻ የሚመለከት አይደለም። ጾም አንድም ቀድሞ ከመናገር እና ሰውን ከማስቀየም በኩል ያለውን የአንደበት ጾም ይመለከታል። አንድም የራስ ያልሆነውን ከመመልከት፣ ከመፈለግ እና ከመሻት መታቀብ ያለውን የዐይን

---

104 ቢላዋ ማለት ሲኾን በዚህ አካባቢ ካሪያ እያሉ ይጠሩታል።

ጾም ያዘክራል። አንድም ከእኩይ ሃሳብ እና ፍላጎት መታቀብ ያለውን የህሊና ጾም ይመለከታል። በመኾኑም ጾም የስሜት ህዋሳታቸውን ተጠቅመው ሰዎች የሚያደርጉትን እኩይ ተግባራት የሚከለክል ነው። ሌላው "አክብሪ" የሚለው ቃል ነው። ማክበር ክብር የሚገባውን ማክበር የሚለውን ዕሳቤ በሰዎች ዘንድ የሚያሰርጽ ነው። ሰዎች ለፈጣሪያቸው፣ ለራሳቸው፣ ለአካባቢያቸው፣ ለወላጆቻቸው፣ ለማኅበረሰቡና ለሚኖሩበት ምድር ጭምር ክብር መስጠት እንዳለባቸው ያስተምራል።

በመሆኑም ቃል ግጥሙ በዚህ መልኩ ሰዎችን በማስተማር ከጥምቀት ዕሳቤ ጋራ የማስተሳሰር ዐቅም አለው። ሌላው በዝማሬው የተነሳው "ኧረ እኔስ ሥጋየ አቃተችኝ፣ ያለ ካሪያ ሥጋ እያስመተረች" የሚለው ግጥም ነው። ግጥሙ ሀሜት ላይ የሚያጠነጥን ነው። የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ በዋናነት ሀሜትን እና በሐሰት መመስከርን አጥብቆ ይጠላል። እነዚህ ተግበራት በማኅበረሰቡ ዘንድ ትልቅ ትችትን የሚያስከትሉ ናቸው። ያለ ካራ ሥጋ እያስመተረችኝ የተባለቸው የሰውን ስም ያለ ግበሩና ኀጢያቱ ማንሣት መጣልን የሚመለከት ነው። ከላይ ተወሰደው የልመና ግጥም ሰዎች በሃይማኖት፣ በባህል፣ በማኅበረሰቡ ህግና ደንብ መመራት እና ተገዥ መሆን እንደሚገባቸው የሚያጸና ነው። ይህን ኑዛዜ ለምን እንዳቀነቀኑት እማሆይ ካባን ጠይቄያቸው ተከታዩን መልስ ሰጥተውኛል። *"አሁን እኔ ከዚህ በኋላ ለነፍሴ ማደር ነው እንጂ ለሥጋ አይገባኝም ግን ይች መናጢ ሥጋ እያቃተች። አበሳችን ለአንድየ ከነገሩት ይቅር ይላል። ሁሉም በዚች ቀን የሠሩትን ሥራ ለመቤቱ፣ ለተክልየ፣ ለፈጣኑ[105] መንገር ነው እሱ ማሪ[106] ነው ይምራል" (እማሆይ ካባ ይመር 2012 ቃ.መ)።*

ከላይ እማሆይ ካባ ከሰጡት መረጃ በመነሳት ሰዎችን የበደለ ሰው በጎንደር ጥምቀት ላይ ኑዛዜ ይገባል የሚል አንድምታ ያለው ነው። በዚህ መሠረት ያለፈውን ይቅር እንዲል ለመጭው እንዳይደገም በማድረግ የጎንደር ጥምቀት ለሰዎች ተግባቦት ትልቅ ፋይዳ አለው። የዚህ ዓይነቱ በጥምቀት ፊት የሚደረገው የልመና ግጥም ማቀንቀን ለአቀንቃኙ ለራሱ ቃል በመግባት ሠርቻቸዋለሁ ካለው ክፉ ሥራ እንዲታቀብ እንደ ስንቅ ይሆነዋል። አንድም

---

105 ፈጣኑ የሚሉት ቅዱስ ጊዮርጊስን ነው። ቅዱስ ጊዮርጊስ ለአመነው በፈረስ ፈጥኖ ደራሽ ነው። ቅዱስ ጊዮርጊስ ባለ ቡላው፣
በነፍስ በሥጋ ታዳጊ ነው፣
ለወዳጆቹ ፈጥኖ ሲደርስ፣
ለጠላጦቹ ሲያልከሰክስ፣
ፈጥኖ ይደርሳል ከአውሎ ነፋስ፣
ኮከበ ልዳ ኮከበ ፋርስ።
ተብሎ ተመሥክሮለታል። እማሆይ ካባ ይመር ከሆ ማርያም ቃል ግጥም የወሰዱት
106 መሐሪ ለማለት ነው

ተመልካቹ አድማጩና ተሳታፊው በባህሉ ውስጥ ስለሚኖረው ክፉና ደግ ሐሳቦች ተረድቶ ወደ ጥሩ ሰብእና እንዲመለስ ያደርጋል፡፡ በዚህ መልኩ ያለፈውን ጥፋት በማስተስረይ እፎይታን በመቸርና መጭውን ጊዜ ደግሞ በሰዎች መካካል መከባበርን በማስተማር ሰባዊ ፋይዳ አለው፡፡

ሰዎች በክብረ በዓሉ ምክንያት ሁኖልኛል ወይም ሰምሮልኛል የሚለውን ጉዳይ የበጎ ምስክርነት የሚሰጡ ቃል ግጥሞች በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ይቀነቀናሉ፡ ከእነዚህ መካከል ወ/ሮ ስንዱ ወርቂ ያቀነቀኑት ተከታዩ ቃል ግጥም ተጠቃሽ ነው፡፡

ኧረ እሰይ ስለቴ ሠመረ
ኧረ እሰይ ስለቴ ሠመረ
ለቅዱስ ሚካኤል ነግሬው ነበረ
ኧረ እሰይ ስለቴ ሠመረ
ኧረ እሰይ ስለቴ ሠመረ
ለቅዱስ ገብርኤል ነግሬው ነበረ
(ወ/ሮ ስንዱ ወርቄ 11/05/2013 ዓ.ም)፡፡

ወ/ሮ ስንዱ ወርቂ በ11/05/2013 ዓ.ም የጥምቀት ቀን ታቦታቱ በጉዞ ላይ እያሉ ዞብል ከሚባለው አካባቢ በቡድን ክብ ሠርተው እያቀነኑ ባለበት ወቅት ያዜሙት ነው፡፡ ስለ ቃል ግጥሙ ምንነት ጠይቄያቸው ነበር፡፡ ወ/ሮ ስንዱ ዐዲስ አበባ በሰው ቤት ሠራተኝነት ተቀጥራ የምትሠራ ልጅ አለቻቸው፡፡ ይህች ልጃቸው በአለፈው ዓመት ጥምቀት አሠሪዋ በመውለዳቸው ምክንያት አልመጣችም ነበር፡፡ አንዲት ልጃቸውን በጥምቀት ባለማየታቸው ባለፈው ዓመት የጥምቀት ከፍቷቸው እንደዋሉ ነግረውኛል፡፡ *ለዘንድሮ አደራህን ከርሞ ልጀን እንድታሳየኝ ብየ ለመድኀኔዓለም ነግሬው ነበር፡፡ አሁን ይኸው አመጣልኝ የማይሳነው አምላክ"* ብለውኛል (ወ/ሮ ስንዱ ወርቂ በ11/05/2013 *ቃ.መ.*)፡፡ የጎንደር ጥምቀት ተራርቆ የሚኖር ቤተሰብ የሚገናኝበት ነው፡፡ የወይዘሮ ስንዱ ስለት አዲስ አበባ ለምትኖር ልጅ ምን አሳሰባቸው የሚል እሳቤ ይነሳ ይሆናል፡፡ የጎንደር አካባቢ ማኅበረሰብ በጥምቀት ክብረ በዓል አዲስ አበባ ያለና አሜሪካም ያለ ቢሆን እኩል ነው፡፡ ለዚህ እንደማጠየቂያ የሚያነሡት ሰዎች ከሚኖሩት ይልቅ ሲሞቱ አጥበው እንዲቀብሯቸው እና አልቅሰው እንዲሸኟቸው የመፈለግ የቆየ ባህል አላቸው፡፡ ሞትን በራሳችን ተሸክመን ነው የምንዞር ለዐይነ ሥጋ ሳንገናኝ ከሞትን ነፍሳችንም አይማርም የሚል ባህላዊ ዕሳቤ አላቸው፡፡ ከአካባቢያቸው ርቆ የኼደውን ሰው በጥምቀት ሳይገኛኙ ከዋሉ ሞት ቢቀድመን እንደተለያየን መቅረታችን ነው

የሚል ስጋት እንዲያድርባቸው ያደርጋል፡፡ በዚህ ምክንያት ጥምቀት ለ“ዐይነ ሥጋ አብቃን” የሚል ስለት ይገባሉ፡፡ “እሰይ ስለቴ ሠመረ” የሚለው ቃል ስለት የገባው ሰው የደረሰለት መኾኑን ምስክርነት የሚሰጥበት በመኾኑ ትልቅ ሰባዊ ፋይዳ አለው፡፡ መጀመሪያ ሰዎች ስለት ሲገቡ ጀምረው ስለታቸው እንዲሠምር መልካም ነገሮችን ያደርጋሉ፡፡ በእነዚህ መልካም ነገሮች መካከል ሥለቴም ወድቆ አይቀርም የሚል ተስፋ ስለሚሰንቁ ከጭንቀትና ከሐሳብ እንዲወጡ ይሆናሉ፡፡ በዚህ መልኩ ሰዎች ተግባብተው እና ተዋደው እንዲኖሩ የማስቻል ዐቅም አለው፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ፡- የጥምቀት ክብረ በዓል ለቱሪስት፣ ለቅርስ እና ለአካባቢያዊ ጥበቃ ያለው ፋይዳ

## 9.1. የጥምቀት ክብረ በዓል የቱሪስት መስኅብ እና ፋይዳዎቹ

በጎንደር ጥምቀት የቱሪስት መስኅ ከፋይዳ አነጻር በብዙ ምልኩ ሊታይ የሚችል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ክፍል በጥምቀት ክብረ በዓል የቱሪስት ፍሰቱ ሂደት፣ ሀገር የማስተዋወቅ ፋይዳ እና የቱሪስት ፍሰት ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳው በሚሉት ላይ ትኩረት ተደርጎ ተጠንቷል፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የቱሪስት መስኅቡ ሂደት፣ የሀገር ማስተዋወቅ እና የቱሪስት ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ የሚለኩት በሀገረሰባዊ አልባሳት፣ በትውን ጥበባት፣ በሀገረሰባዊ ጭፈራዎች እና በቁሳዊ ባህል ላይ በመኾናቸው ነው፡፡ እነዚህ ደግሞ ከፎክሎር ዐይን የሚታዩ እና የጥናቱ ማጠንጠኛ በመኾናቸው ምክንያት ለጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ሁነዋል፡፡ ከዚህ ባለፈ የቱሪስት ፍሰቱ አሉታዊ ተጽኖ ላይ ጥናቱ አይዳሥሥም፡፡ ምክንያቱም በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የተገኘው መረጃ ወደ ጉዳዩ የሚመራኝ አለመኾኑ አንዱ ምክንያት ቢሆንም የቱሪስት "አሉታዊ ተጽኖ" ራሱን ችሎ ጥናት የሚሻ ርእሰ ጉዳይ ሁኖም ስላገኘሁት ነው፡፡

### 9.1.1. በጥምቀት ክብረ በዓል የቱሪስት ፍሰቱ ኺደት እና ሀገር የማስተዋወቅ ፋይዳው

የጎንደር ጥምቀት ካለው ድምቀት፣ ታሪካዊና ማኅበራዊ አንድምታ አኳያ በርካታ ቱሪስቶች ይታደሙበታል፡፡ የጎንደርን ጥምቀት ለመካፈል የሚመጡት ቱሪስቶች ከውጭ ሀገር ብቻ አይደለም፡፡ በሀገራችን የተለያዩ ክልሎች፣ ከተሞች፣ ገዳማትና አድባራት በርካታ ሕዝቦች ይመጣሉ፡፡ ይህን በተመለከተ አባ ገብረ ሥላሴ *"ህዝቡ ከውስጥ ብቻ ሳይሆን ከውጭ ይመጣል፡፡ ከአዲስ አበባ ያን ትተው ይመጣሉ የግንቦቹ አሰራር ያለው ፍቅር ሲጀመር ጎንደር ላይ ያለው የጥምቀት ድባብ ፍቅር ነው" (አባ ገብረ ሥላሴ 03/ 06/11 ቃ.መ)* የሚል መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ የጎንደር ጥምቀት ቱሪስት መብዛት የጥምቀቱ ውብነት፣ ማራኪነት እና የአብያተ ነገሥታቱ ግንብ ማማር እንደሆነ የአባ ገብረ ሥላሴ መረጃ ያሳያል፡፡ የጎንደር ጥምቀትን ከባህላዊ አልባሳቱ፣ ከባህላዊ ጭፈራው፣ ከባህላዊ ሆታው ጋራ የጥንታዊ አብያተ ክርስቲያናትንና ቤተ መንግሥታትን ማየት ትልቅ የሆነ እፎይታ እና ርካታን ስለሚያስገኝ የጎንደር ጥምቀት የቱሪስቶች መስኅብ እንዲሆን አስችሎታል፡፡ አቶ ጌትነት አመራ በሰሚው ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ጉባዔ ሊቀመንበር ሲኾሆኑ የጎንደርን ጥምቀት ከኩተት እስከ ሽበት

ጠንቅቀው ያውቁታል። እሳቸውም ስለ ጎንደር ጥምቀት እና ቱሪስት ፍሰት ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *የሕዝቡ መብዛትና የጥምቀቱ መድመቅ የጎንደር አካባቢ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ፈረንጆችም ከአገራቸው ከአፍሪካ[107] እየመጡ የኛን ባህል ፎቶ በማንሣት፣ እስክስታ በመወረድ ወደ ሀገራቸው ወስደው በማስተዋወቅ የማያደርጉት ጥረት የለም። ፈረንጆች፣ ፈረንጆች ሳይቀር አውራው እንደተነካበት ንብ ሆ ብለው መጥተው ነው እየተሳተፉ ጥምቀቱን የሚያከብሩት (ጌትነት አመራ 13/05/2011 ቃ.መ.)።*

መረጃ ሰጭየ የጎንደርን ጥምቀት ለበርካታ ጊዜያት ቤተኛ ሁነው በማክበራቸው ምክንያት በየ ዓመቱ የሚገኙትን የውጭ ዜጎች፣ የውጭ ጎብኚዎች ደጋግመው የመመልከት እድል ገጥሟቸዋል። ይህ ግንዛቤያቸው የቱሪስቱን ብዛት ቀፎው ከተነካ ንብ ጋራ እንዲያነጻጽሩት አስችሏቸዋል። ቀፎው የተነካ ንብ ገንፍሎ እንደሚወጣ ሁሉ ፈረንጆችም እንደዚሁ በርከት ብለው በጥምቀት በዓል የሚሳተፉ መኾናቸውን ያስረዳሉ። የቱሪስቶችን ብዛት ሁኔታና አመጣጥ ከጥምቀተ ባሕሩ ጀምሮ ጥምቀቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በብዛት በጥምቀተ ባሕሩ፣ እና በፋሲል ቤተ መንግሥት ጉብኚት ያደርጋሉ። ቱሪስቶች ወደ ጎንደር ጥምቀት የሚፈሱት በጥምቀቱ የሚታየውን ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክዋኔ በመመልከት መንፈሳዊና ሥጋዊ ርካታ ለማግኘት ከመሻት ነው። የጎንደር ንዋዬ ቅደሳት፣ የሊቃውንቱ ወረብ፣ የሰንበት መዘምራን ዝማሬ፣ የጥምቀቱ ባህላዊ አልባሳቱ፣ ሀገረሰባዊ ጭፈራ፣ የነገሥታቱ ቤተ መንግሥታት የአርባ አራቱ አብያተ ክርስቲያናት፣ በባሕረ ጥምቀቱ የሚገኙት አእዋፋት እና አጸድ የቱሪስቶቹ የዐይን ማረፊያዎች ናቸው (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ 15/11/2011 ቃ.መ እና ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን 12/05/13/ ቃ.መ.)።

ቱሪስቶቹ በካህናቱ እና ዘማርያኑ ወረብና ሽብሻቦ ወቅት አጠገባቸው በመሆን እጅግ በተመስጦና በትኩረት ይከታተላሉ። በጎንደር ጥምቀት ላይ የሚታደሙትን በርካታ ቱሪስቶች በተመለከተ ለሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ ባቀረብኩላቸው ቃለ መጠይቅ መሠረት ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *ቱሪስቶች በጣም ደስ ይላቸዋል። "ወናሁ መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅሮ" "ከሰማይ እንዲህ የሚል ቃል መጣ የምወደው ልጀ ይህ ነው"። ተብሎ ሲዘመር ከዚያ ላይ ለተገኘ ሰው ማንኪት ከሚባለው ቦታ ከጥምቀተ ባሕሩ ተገኝቶ ለሚያከብር ሰው ውነትም ከሰማይ ቃል እንደመጣና መንፈስ ቅዱስ በእርግብ አምሳል እንደወረደ ይታያል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)።*

---

[107] በደምሳሳው ፈረንጆች እንደሚባለው ሁሉ የዓለም አገራትን ለመወከል የተጠቀሙበት ቃል ነው።

ከመረጃው በተጨማሪ ባደረግኩት ምልከታ ቱሪስቶቹ ከቦታ አንጻር በጥምቀተ ባሕሩ እና ከጊዜ አኳያ ደግሞ ታቦታት ሲነሡ በይበልጥ በተመሥጦ የጥምቀቱን ክብረ በዓል ይከታተላሉ። በርግጥ የጎንደር ጥምቀት የቱሪስት መስኅብ ከሚያሰኘው አንዱ የጥምቀተ ባሕሩ ድባብ ነው። በጥምቀተ ባሕሩ ዙሪያ ከሚገኙ ትልልቅ ዛፎች እና የአዕዋፋቱ ዝማሬ ጋራ የሚዋሐደው የጥምቀት ክዋኔ የተለየ ስሜት ይሰጣቸዋል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ እና ጌትነት አመራ 13/05/2011 ቃ.መ)።

በባሕረ ጥምቀቱ ቦታ ከዋዜማው ጀምሮ የሚገኘው የሕዝብ ቁጥር በጣም በርካታ ነው። ይህ በቡድን፣ በቡድን ሁኖ በየ ፈርጁ የሚገኘው የሰው ድባብም፣ የተለያዩ ዘውጎች ክዋኔ ቱሪስቶቹን የሚስባቸው ይመስላል። ከጸበል ርጭት ጀምሮ የጥምቀተ ባሕሩን ክዋኔ ደስታቸውን በሚያሳይ ስሜት በካሜራና በመቅረጸ ድምጽ ሲቀርጹ ይስተዋላል። በተለይ በባሕረ ጥምቀቱ ወጣቶች ከዛፍ ላይ ወጥተው ቁልቁል ወደ ባሕረ ጥምቀቱ የሚያደርጉት መወርወር ቀልብን ስቦ የሚያስቀር ነው። የዚህ ዓይነቱን የጥምቀተ ባሕር ሥርዓት ቱሪስቶቹን የመሳብ ዐቅም ስላለው ቱሪስቶቹ ከአጠገብ አይጠፉም። ይህም የጎንደርን ማኅበረሰብ የመውጣት መውረድ፣ የማጣት፣ የማግኘት እና የመሾም መሻር የሕይወት ዑደት ያዘክራል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ እና ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን 12/05/13/ ቃ.መ.)።



*(በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ወጣቶች ወደ ባህረ ጥምቀቱ ሲወረወሩ የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ በአጥኝው የተነሳ 2013)*

ቱሪስቶቹ በሐሴት የሚከታተሉበትን ምክንያት ጨምሬ ስለ ጥምቀተ ባሕሩ እንዲያስረዱኝ ለሊቀ ሊቃውንተ ዕዝራ ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ቱሪስቶቹ ፈረንጆቹ በተለይ በእውነት አእምሮአቸውን መቆጣጠር እስከሚያንሳቸው ድረስ ይደሰታሉ፡፡ ልዩ ነው ዛሩ፣ ከዛሩ ብዛት አእዋፉ ደግሞ ከዛሩ ሁነው ወዲያ ወዲህ ሲሉ ርእግቦቹ በእውነት መንፈስ ቅዱስ በርእግብ አምሳል ሲወርድ በዮርዳኖስ ዮሐንስ እንዳየው የሊቃውንቱ "መጽአ ቃል እምውስተ ደመና ዘይብል" እያሉ ሲዘምሩ በትክክል በተወለደ በ፴ ዓመቱ ፈለገ ዮርዳኖስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠመቅ ዮሐንስ ለምስክርነት ያየውን የጥምቀት በዓል የሚገልጽ ነው፡፡ የጎንደር በዓል ለየት የሚያደርገው የቦታው ልዩነት ነው (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

በበዓሉ ውብነት እና ማራኪነት ምክንያት በተለይ ሴቶቹ ቱሪስቶች የጎንደርን የባህል ቀሚስ ለብሰው ያከብሩታል፡፡ የጎንደር የባህል ቀሚስና የጎንደር ጥምቀት አንዳቸው ለሌላቸው መገለጫዎች ናቸው፡፡ ቱሪስቶቹ የጥምቀትን በዓል ለመታደም ሲመጡ የጎንደርን ባህል አለባበስ፣ አመጋገብ፣ አጠጣጥ እና አጨፋፈር አክብረው እና ተቀብለው ነው፡፡ በጎንደር ጥምቀት ላይ ከሚታደሙት ቱሪስቶች መካከል የጎንደርን ቀሚስ ለብሰው የሚያከብሩ ሴቶች አይጠፉም፡፡ የሚለብሱት ቀሚስም በጎንደር ጥልፍ ያጌጠ ነው፡፡ ይህን ቀሚስ በመልበስ፣ መቀነቱን በመታጠቅ እና ቀሚሱን በመሸንሸን የጎንደሬዎችን ወይዛዝርት ለመምሰል ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በመኾኑም የጎንደር ጥምቀት ከቱሪስቶች የሚገኘው ገንዘብ ብቻ ሳይሆን የጎንደር ባህል ጎልቶ እንዲወጣ እና እንዲታወቅ የማድረግ ዐቅምም አለው፡፡ ቱሪስቶች የጎንደርን የባህል ልብስ እንደሚወዱት እና እንደሚለብሱት ሊቀ ሊቀውንት ዕዝራ ሐዲስ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ቱሪስቶቹ ፈረንጆቹ ማለት ነው ወንዶችም ሴቶችም የባህል ልብስ ይለብሳሉ በተለይ ሴቶቹ ፈረንጆች በእንግድነት ሁሉም ይቀበላቸዋልና እነሱ እንደገና ባለቤት ሁነው የኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይ ሁነው እናያቸዋለን፡፡ ባህሉን ማለቴ ነው፡፡ የአንድ አገር ባህል ሲወደድ አለባበሱም፣ አነጋገሩም፣ አካሄዱም፣ ከተወደደ አንዲት ሀገር አገሯ ላይ እንግዳ ተቀባይ ስትሆን እንደገና ደግሞ ሌሎቹ እሷን እንግድነት ይቀበሏታል፡፡ እና እሚመጡት ፈረንጆች ሴቶቹ ጥልፍ ቀሚሱን ለብሰው የጎንደርን መቀነቱን ታጥቀው ትፍትፍ መቀነት አለ ያን ይታጠቃሉ፡፡ የራስ ሻሻቸው ነጭ ቀይ ቢጫ አረንጓዴ ያለው ነው እሚለብሱት፡፡ ነጠላቸው ከቀሚሱ ጋራ አብሮ የተሠራ ነው፡፡ ያነን ለብሰው ሲታዩ የኢትዮጵያን ባህል ሙሉ በሙሉ እነሱ እንደባለቤት ሁነው በእንግድነት ሲያስተናግዱት ስናይ በጣም በጣም ይገርመናል እንዳው እሚገርመው ነገር ከአበሻዎቹ ይልቅ ፈረንጆቹ ይህን የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ ሲለብሱ በጣም ነው የሚያምርባቸው፡፡ እና ይህን ሁሉ የሚያሳይ የጥምቀት በዓል ስለሆነ እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ቱሪስቶች ይህን ልብስ ሲገዙ ሀገሪቱ ለልማት ገቢ እያስገኘች ነው*

*ማለት ነው። ወደው ነው ልብሱን የሚገዙት ተገደው አይደለም። ሁለንተናቸው። ጭራውን ይይዛሉ። ወንዶቹ መቋሚያውን በትሩን ይገዛሉ። ሴቶቹ አገልግሉን ይገዛሉ ያዝላሉ። ቅቤቅል ይይዛሉ (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዘዲስ 15/11/2011 ቃ.መ.)።*



*(በጎንደር ጥልፍ ቀሚስና መቀነት ያጌጡ ቱሪስት[108] የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ 2013)*

መረጃው እንደሚያሳየው የውጭ ሀገር ቱሪስቶች የጎንደርን ጥምቀት ሲታደሙ የጥምቀቱን ክዋኔ ተመልክቶ መሄድ ብቻ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ በሀገር ማስተዋወቅ፣ በባህል መሸማመት፣ በምጣኔ ሀብታዊ ፍሰት እና በመሰል ፈርጀ ብዙ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ ጎንደርን ብሎም ሀገርን የሚጠቅሙ ተግባራት ይፈጽማሉ። የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ለቱሪስት መስኅብ ነው ሲባል ከውጭ በሚመጡት ቱሪስቶች ብቻ የተገደበ አይደለም። ከሀገር ውስጥ ከዓመት ዓመት፣ ከጊዜ ጊዜ እየጨመረ እና እያደገ የመጣው የሰው ብዛት ቀላል አይደለም። ይህም ከተለያዩ ቦታዎች የጎንደርን ጥምቀት ለመታደም የሚፈልግው ሰው መብዛቱን አመላካች ነው። የጥምቀት ሰሞን መንገዣ እስኪቸግር ድረስ የሰው ፍሰት ከፍተኛ ነው። ከኹለት ሳምንት ጀምሮ አገር አቋራጭ አውቶብሶች ይሞላሉ። ከመደበኛው እና

[108] በጥምቀት ክብረ በዓል ፎቶግራፍ ለማንሳት ባህሉ አይከለክልም። ይሁን እንጅ ከጥናት ህግ እና ሥነ ምግባር አኳያ ከላይ የተወሰደውን ፎቶ ግራፍ ግለሰቧን ለጥናቱ እንደምጠቀመው አስፈቅጀ ነው።

ከተለመደው ውጭ ሌሎች ተጨማሪ ትራንስፖርት ሰጭዎች ቢመደቡም ተጓዡን ለመሸፈን የማይችሉበት ሁኔታ አለ፡፡ በመሆኑም የውጭ[109] እና የሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ከዓመት ዓመት፣ ከጊዜ ጊዜ በጎንደር ጥምቀት የሚጨምርበት አጋጣሚ እየታየ ነው፡፡ ይህን በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል የሀገር ውስጥ እና ውጭ ቱሪስቶች ተሳትፎ ምን እንደሚመስል ለሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ  ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *የጥምቀት በዓል በየ ዓመቱ ሲመጣ እየጨመረ ነው እንጅ እየቀነሰ አይሄድም፡፡ ቱሪስቶችን በተለይ የሚስብ ነው፡፡ የሀገሪቱን ሰውም ቱሪስት አድርጎታል ማለት ነው፡፡ ጥምቀትን በጎንደር እየተባለ ከተነገረበት ጊዜ ጀምሮ በዐዲስ አበባ ብዙ ሰዎች መጥተው ጎንደር ነው የሚያከብሩት ጥምቀትን፡፡ ባለፈው ዓመት ቀጥታ ከአሜሪካን እንኳን ፲፫ አውሮፕላን ቀጥታ ከአሜሪካን ተነሥቶ ጎንደር ዐፄ ቴዎድሮስ ማረፊያ ቀጥታ መጥቶ አርፏል፡፡ ብዙ በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ከአሜሪካን ከተለያየ ቦታ መጥተው አክብረውታል እያከበሩት ነውና ጎንደር ለኢትዮጵያውያንም ጭምር የትውልድ ሀገር ብትሆንም ባህልና ሥርዓቱ እየሳባቸው እየተሳቡበት የሚገኝ ሃይማኖታዊ በዓል ነው ማለት ነው (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

እነዚህ ከውጭ አገር የሚመጡት ፈረንጆች[110] በጥምቀት ክብረ በዓል ቋንቋ፣ ባህል እና ዕሴቱን ባያውቁትም ባይታውርነት አይታይባቸውም፡፡ ደጋግመው በመምጣት ይሁን በጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ተግባቦት ምክንያት ቱሪስቶቹ ግራ ሲጋቡ ዓይታይም፡፡ ከዚህ ይልቅ ልክ እንደ አካባቢው ማኅበረሰብ በበዛው እና በተዛነቀው የጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ውስጥ እየገቡ ይመለከታሉ፤ ይቀርጻሉ፡፡ አንዳንዴም ለመጨፈር፣ ለመዘመር እና እስክስታ ለመውረድ ሙከራ ያደርጋሉ፡፡ ይህን ምልከታየን ይዤ ለሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸውም እንደሚከተለው ምልከታየን የሚያጠናክር መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *የጥምቀት በዓል ሁሉም በመሳቅ እንዳውም የሚገርመው ነገር እነዚህ ፈረንጆቹ ቋንቋ እማያውቁት እንኳን፡፡ አብረው ከእስክስታው እየገቡ አብረው ይዘፍናሉ፡፡ ወንዶችም ከሆታው አብረው ይጨፍራሉ፡፡ በስሜት ቋንቋውን ሳያውቁት ከሚያውቁት ጋራ እንደሚያውቁት ሁነው አብረው ሲታዩ መንፈስ ቅዱስ ምስጢሩንና ቋንቋውን እንደገለጸላቸው በእውነት ያሳያል፡፡ እና የፍቅር በዓል መኾኑ የሚታወቀው ለዚህ ነው፡፡ እንኳን ቋንቋ የሚያውቁት ኢትዮጵያውያን በቋንቋ እሚስማሙ ይቅርና በቋንቋ የማይገናኙ*

---

[109] በሁኔታዎች እና አጋጣሚዎች (stuation) አማካኝነት አይቀንስም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ በ2013 ዓ.ም በኮሮና (ኮቢድ 19) ምክንያት የሀገሬው ቢጨምርም የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ቁጥር ዝቅተኛ ነበር፡፡ ይህ ግን ወቅት የሚወስደው እና ወቅት የሚመልሰው እንጅ ሚዛኑ እንደተደፋ ይቀራል ማለት አይደለም፡፡

[110] የአካባቢውን መጠሪያ ልጠቀም ብየ እንጅ በጥምቀቱ የሚታደሙት ቱሪስቶች ከፈረንሳይ ሀገር የመጡ ብቻ ዓይደሉም፡፡

*ቱሪስቶች ስቀው ተሳስቀው አብረው ካበሻው ጋራ እስክስታ ይገባሉ ፈረንጆቹ በማየት ብቻ አብረው መስለው ያከብሩታል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)፡፡*

ይህ የሚያሳየው የጎንደር ጥምቀት የቱሪስት መስኅብነቱ ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡ እነዚህ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች በክብረ በዓሉ የገዙትን ሸማ፣ ጥንግ ድርብ፣ ቀሚስ መቀነት ወደ ሀገራቸው ይዘው በመሄድ ጎንደር እንድትተዋወቅ ያደርጋሉ፡፡ እንደዚሁም ቱሪስቶቹ የዐፄ ፋሲል ግንብ ያለበት እና የዐፄ ቴዎድሮስ ምስል ያለበት ቅርጻቅርጽ በብዛት ይገዛሉ (ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን 12/05/13/ ቃ.መ.)፡፡

እንደዚሁም እንደነ ደብረ ብርሃን ሥላሴ ያሉ አብያተ ክርስቲያን እና እንደነ ፋሲል ያሉትን አብያተ ነገሥታት በፎቶ ካሜራ አንሥተው ወደ ሀገራቸው ይወስዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቱሪስቶቹ በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የሚከወኑትን የካህናት ማኅሌት፣ የሰንበት ተማሪዎች ዝማሬ፣ የወጣቶች ሆታ፣ ጭፈራ፣ የልጃገረዶቹ አለባበስ ጸጉር አሠራር፣ አጊያጊያጥ እና ባጠቃላይ በክብረ በዓሉ የሚተገበሩትን ክዋኔዎች ይቀርጻሉ፡፡ እነዚህን ሁሉ ወደ ሀገራቸው በመውሰድ ኢትዮጵያን ብሎም ጎንደርን በባህል፣ በሃይማኖት፣ በፍልስፍና፣ በማኅበራዊ መስተጋብር እና በዕውቀት ምን እንደምትመስል ለዓለም ያስተዋውቁበታል፡፡ በዚህ መተዋወቅ ምክንያት ከዓመት ዓመት በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የቱሪስት ፍሰቱ እየጨመረ እንዲሄድ ያደርጋል (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ 15/11/2011 ቃ.መ እና ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን 12/05/13/ ቃ.መ.)፡፡ በዚህ መልኩ በጎንደር ጥምቀት የቱሪስት ፍሰት በሀገር ማስተዋወቅ በኩል ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ የቱሪስት ፍሰቱ ከሀር ማስተዋወቅ በተጨማሪም በምጣኔ ሀብት እድገት በኩልም የራሱ ፋይዳ አለው፡፡

### 9.1.2. በጥምቀት ክብረ በዓል የቱሪስት ፍሰት እና የምጣኔ ሃብት ፋይዳ

የጎንደር ጥምቀት ከቱሪስት ገበያው አንጻር ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ በከተማዋ ውስጥ የሚዘዋወርበት ወቅት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ በጎንደር ጥምቀት የሚታደመው ቱሪስት በምጣኔ ሀብቱ በኩል ምን አስተዋጽኦ አለው? የሚል ቃለ መጠይቅ ለልዕልና ኀይለ መስቀል አቅርቤላቸው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ጎንደር በጥምቀት ልዩ ተጠቃሚ የምትኾንበት ወቅት ነው፡፡ ይህንን በዓል ለመታደም በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኝዎች ወደ ከተማዋ ይፈሳሉ፡፡ እነዚህ ጎብኝዎች ገንዘብ ይዘው ነው የሚመጡ፣ በዓሉ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ነው የሚከበረው፡፡ እንዳውም እስከወር ድረስ ይሄዳል፡፡ እያንዳንዱ በዓል በየ ራሱ ቤተ ክርስቲያን የሚያከብረው በመኾኑ እስከወር ድረስ ይቆያል፡፡ በተለይ ሦስቱን ቀናት*

*ከአገር ውስጥም ውጭም የመጡት ታዳሚዎች በዓሉን ለሦስት ቀናት ሲያሳልፉ አንደኛ ለዐልጋ፣ ለምግብ ለተለያዩ ነገሮች ወጭ ያወጣሉ፡፡ ይህ አንድ ጥቅም ነው፡፡ እንደ ኢኮኖሚ ሲታሰብ፡፡ ማኅበረሰቡ በዚህ አንደኛ ተጠቃሚ ነው (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡*

ከመረጃው እና ከአጥኚው ምልከታ በመነሣት የጎንደር ጥምቀት ከፍተኛ የሆነ የማኅበረሰብ ክፍል የሚሳተፍበት ነው፡፡ የማኅበረሰቡ ክፍል ከከተማዋና ከጎንደር አካባቢ በሀገር ውስጥና ከሀገር ውጭ የሚኖሩ የአካባበው ተወላጆች የሚታደሙበት ነው፡፡ ከአካባቢው ተወላጆች በተጨማሪ የጎንደርን የጥምቀት ሥርዓት ለመጎብኘት የሚመጡ የውጭ ሀገር ዜጎች በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህ የማኅበረሰብ ክፍሎች እስከ አንድ ወር ለሚዘልቅ ጊዜ ሊቆዩ ይችላሉ፡፡ አነሰ ሲባል ደግሞ ለሦስት ቀናት በጎንደር ከተማ በመቆየት በዓሉን ያከብራሉ፡፡ በዚህ ቆይታ ጊዜያቸው ከውጭም ሆነ ከሀገር ውስጥ የመጡ ዜጎች ገንዘባቸውን በተለያዩ ምክንያቶች በከተማ ውስጥ ያፈሳሉ፡፡ ይህ የገንዘብ ፍሰት ለከተማዋ ምጣኔ ሀብት መነቃቃት ትልቅ ድርሻ አለው (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ.፤ አክሊል አሰፋ 03/06/12 ቃ.መ. እና ወርቄ አባተ 03/11/12 ቃ.መ.)፡፡

በጥምቀት ሰሞን የገበያው መድራትና የከተማዋ የንግድ ሁኔታ መጧጧፍ ከፍ ያለ ነው፡፡ በአብዛኛው በጥምቀት ሰሞን ለሽመታ የሚቀርበው ሸማ እና የእጅ ሥራ የአካባቢው ማኅበረሰብ የዕውቀት ውጤት ነው፡፡ ይህ ማለት በጥምቀት ሰሞን ለገበያ የሚቀርቡት የባህል አልባሳት፣ ጥልፍ ቀሚስ፣ ትፍትፍ፣ ጉብጉብ፣ ጥሩር እና ጥበብ በሙሉ የአካባቢው የሽመና ባለሙያዎች፣ የጥልፍ ጠላፊዎች እና የጥበብ ሰሪዎች ውጤቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ባህላዊ አልባሳት በመሸጣቸው የግለሰቦችን ብሎም የጎንደርን ምጣኔ ሀብት ከፍ ከማድረግ ዐልፎ የአካባቢውን ማንነት የሚገልጹና የሚያስተዋውቁ በመኾናቸው ፋይዳቸው ላቅ ያለ ነው (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ፣ አክሊል አሰፋ 03/06/12 ቃ.መ እና ወርቄ አባተ 03/11/12 ቃ.መ)፡፡

ልዕልና ኀይለ መስቀል በጥምቀት የሚታደመውን የቱሪስት መጠን *“ወደ ሠላሳ ሺህ ጎብኝ የሚገኝበት ነው፡፡ ሠላሳ ሺህ ጎብኝ በሦስት ቀናት ውስጥ ለማግኘት ይቅርና በዓመትም ይከብዳል፡፡ ስለዚህ በዚህ መልኩ ይህ ጎብኝ መዋዕለ ንዋዩን በዚህ መልኩ አፍስሶ ከሄደ ማኅበረሰቡ ተጠቃሚ ነው ማለት ነው” (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ)* በማለት ብዛትና መጠኑን ይገልጹታል፡፡

የአቶ ልዕልና[111] መረጃ እንደሚያመለክተው ሠላሳ ሽህ ገደማ የውጭ ሀገር ጎብኚዎች የጥምቀትን በዓል ለመታደም ወደ ጎንደር ይገባሉ፡፡ እሳቸው እንደሚሉት እነዚህ የውጭ ሃገር ቱሪስቶች በጎንደር ከተማ ውስጥ ቢያንስ ለሦስት ተከታታይ ቀናት አንደሚቆዩ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ መልኩ ወደ ጎንደር ከተማ የገቡት ቱሪስቶች በቆይታ ጊዜያቸው ገንዘብ ወጭ ያደርጋሉ፡፡ ቱሪስቶቹን ወደ ጎንደር ጥምቀት ሲመጡ የሚስቧቸውና የሚያስደስቷው በርካታ የገንዘብ ማውጫ ባህላዊ ቁሶች ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የባህል አልባሳት የሆኑትን የጎንደርን ጥልፍ ቀሚስ የውጭ ሀገር ሴቶቹ በብዛት የመግዛት ሁኔታ ይታያል፡፡

እንደዚሁም የፋሲልን ግንብ፣ የራስ ዳሸንን ቅርጽ፣ ጭራ፣ መቋሚያ፣ አረንጓዴ፣ ብጫ፣ ቀይ የእጅ ሥራዎች በብዛት ይሸጣሉ፡፡ እነዚህ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች የሚገዙበት ዋጋ ተመን ከሀገርኛው ዋጋ ተመን ከፍ ያለ በመኾኑ በገንዘብ ሲሰላ ትርፋማ ያደርጋል፡፡ እንደዚሁም ቱሪስቶች በሆቴሎች፣ በሎጅዎች እና በትራንስፖርት ዘርፎች ከፍተኛ የሆነ ገቢ ያስገኛሉ፡፡ ይህን በተመለከተ መ/ር ዳዊት ሥራው ቀጣዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡ *"በኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ የጎንደር ጥምቀት እጅግ የላቀ ነው፡፡ ከአገር ውጭም ሆነ ውስጥ የሚመጡት በዓሉን ለማክበር የመጡት ባህላዊ አልባሳትን፣ ጌጣጌጦችን፣ መዋቢያዎችን ገዝተው ይሄዳሉ፡፡ ፈረንጆች ራሳቸው የባህል ልብሶችን ገዝተው ይሄዳሉ" (መ/ር ዳዊት ሥራው፣ 12/19/2011 ቃ.መ)፡፡*

እነዚህ የሚገዟቸው ባህላዊ ቁሳቁሶችና ቅርጻቅርጾች የጎንደርን ማኅበራዊ መስተጋብር፣ መልክዓ ምድር፣ ቅርስና ባህላዊ ዕሴት የሚገልጹ ናቸው፡፡ የውጭ ሀገር ዜጎችና በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የጎንደርን ጥምቀት በቪዲዮ እና በፎቶ ካሜራ በማንሣት ወደ የመጡበት ሀገር ይመለሳሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ጎንደር በዓለማቀፍ ደረጃ እንድትተዋወቅ እና የቱሪስት ፍሰቱ ቀጣይ እንዲሆን በማድረግ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡ የጎንደር ጥምቀት እነዚህ ሠላሳ ሽህ የሚደርሱ ጎብኚዎች ወደ ሀገር ቤት ሲገቡ የውጭ ምንዛሪ ይዘው ስለሚገቡ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ እጥረት በመፍታት በኩልም ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት ለገበያው መድራትና ለገበያው ድምቀት ያለው አበርክቶ ከፍ ያለ ነው፡፡ ጥምቀቱን ተከትሎ የአልባሳቱ፣ የመጠጥ ቤቱ፣ የምግብ ቤቱ ሁሉ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ይታይበታል፡፡ ጎንደር ገበያው ከጥምቀት በፊት ቀደም ብሎ ይጀምርና ከጥምቀት በኋላም ቢሆን ሌሎች ጥምቀቶች ስለሚኖሩ ገበያው እንደቀጠለ ለወራትና ከዚያ በላይ ይቆያል፡፡

---

[111] *አቶ ልዕልና ስለ ጎብኝዎች ቁጥርና ስለ ቆይታቸው ጊዜ በጎንደር ከተማ የባህልና ቱሪዝም ጽ/ ቤት አባል ከመሆናቸው ጋራ ተያይዞ የተሻለ መረጃ እና ግንዛቤ አላቸው ፡፡*

ይህን በተመለከተ የቱሪስት ፍሰቱ እና የምጣኔ ሀብት ፋይዳው በጎንደር ጥምቀት እንዴት ይታያል? የሚል ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *የጎንደር ጥምቀት ትልቅ የሀገር ልማት ነው፡፡ ምክንያቱም ከውጭ የሚመጡ ቱሪስቶች ወደ እኛ የሚያስገቡት ነገር አለ፡፡ ዜጎች ከዞን ወደ ዞን፣ ከክልል ወደ ክልል ከወረዳ ወደ ወረዳ በሚሄዱበት ሰዓት ላይ የኢኮኖሚ የራሱ ጥቅም አለው፡፡ ራሱን የቻለ ገንዘብ አለ፡፡ የሚበላ የሚጠጣ አለ፡፡ ባህልን መለዋወጥ አለ፡፡ በሙዚቃውም ዓለም ላይ እያለ ጎንደር እራሱ ብዙ ባህል አለው፡፡ ባህልን መወራረስ፣ መሸማመት፣ መገበያየት ሁሉም ስላለው ይህ ትልቅ አምባሳደር የሆነ ትስስር ያለው አምባሳደር ነው፡፡ ያን ጊዜ ራሱ ባለ ታክሲዎች፣ ባለ ባጃጆች ባለ ምግብ ቤቶች፣ ባለ ሆቴሎች፣ ባለ ድራፍት ቤቶች ምን ያህል ገቢ ያገኛሉ፡፡ ይህን ሰፋ ሰፋ በአለ እምሮ ካሰብነው ሰፊ ጥበቃም እንክብካቤ የሚደርግ መሆን አለበት፡፡ ከሃይማኖቱ እንዳውም በበለጠ ከ75% በላይ የጎንደር ጥምቀት ትልቅ ጥቅም እየሰጠ ያለው ለሀገር ነው (መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ 19/01/12 ቃ.መ)፡፡*

ከላይ የተሰጠውን መረጃ ስንመለከተው የጎንደር ጥምቀት ምጣኔ ሀብት በባህል፣ በገንዘብ፣ እርስ በርስ ትስስር፣ በማኅበራዊ ግንኙነት ጭምር መለካት እንዳለበት የሚያስረዳ ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀት የኢኮኖሚ ፋይዳ በባህል ልውውጥ እና በማኅበረሰብ ግንኙነት መካከል የሚገኝ በመሆኑ ምጣኔ ሀብቱን ከማኅበረሰባዊ ትስስሩ ጋራ አጣጥሞ የሚሄድ ነው፡፡ ቱሪስቱ ምጣኔ ሀብቱን ሲደግፍ በባህል እና ዕሴት፣ ትውፊት እና ዕውቀት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ምጣኔ ሀብቱ ከፎክሎሩ ጋራ ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡ ለዚህም በጎንደር ጥምቀት የሚደረጉት ግብይቶች፣ ቅርጻቅርጾች፣ አልባሳት እና የአዝማሪ ዘፈኖች ሁሉ በባህል ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ ከዓለም ዓቀፍ፣ ከአገር አቀፍ፣ ከክልል፣ ከዞን፣ ከወረዳ፣ ከቀበሌ፣ ከጎጥና ከቤተሰብ የሚመጡት የማኅበረሰብ ክፍሎች ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ባህላቸውንም ጭምር ይዘው ስለሚመጡ በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ባህልና ገንዘብ የሚገናኙበት ዐውድ ነው፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት ከሃማኖታዊ አንድምታው ትይዩ የቱሪስት መስኅቡ፣ የምጣኔ ሀበት እድገቱ፣ የማኅበራዊ ትስስሩ እና የሰባዊ ቅርርቡ ከፍ ያለ ነው፡፡ በጎንደር ጥምቀት የቱሪስቱ እንቅስቃሴ ከቁስ መሸማመት ባለፈ በዓይነትና በመጠን ልዩ የኾነውን የጎንደርን ባህል መሸማመት፣ መገበያየት እና መለዋወጥ ያስችላል፡፡ ይህም ሀገር በቀል ዕውቀት ላይ የተመሠረተው የቱሪዝም ምጣኔ ሀብት የሰፋ ነው፡፡ ከዚህ በመነሣት በጎንደር ጥምቀት የሚሳተፉት ቱሪስቶች ፈርጀ ብዙ የምጣኔ ሀብት ፋይዳዎችን እና ሀገራዊ ትውውቆችን ያስገኛሉ፡፡

### 9.2. የጎንደር ጥምቀት እና የቅርስ ጥበቃ

የጎንደር ጥምቀት ከቱሪስት መስኅብነቱ፣ በተጨማሪ የጎንደር ቅርሶች እንዲጠበቁ የማድረግ ፋይዳ አለው፡፡ የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ቅርሶቹን ጠንቅቶ የሚያውቃቸው እና የሚረዳቸው በጥምቀት ትዕይንት ነው፡፡ ማኅበረሰቡ በጥምቀት ክብረ በዓል ወቅት አካባቢውን ማየቱ፣ መረዳቱ እና መመልከቱ የባለቤትነት ስሜት እንዲሰማው እና ቅርሶቹን እንዲንከባከብ ያስችለዋል፡፡ የጥምቀት መከበሪያ እና የቱሪስት መስኅብ በመሆናቸው ቅርሶቹን ከፍ አድርጎ ይመለከታቸዋል፡፡ ይህን በተመለከተ ለንጋቱ ችሮቴ የጥምቀት ክብረ በዓል ከቅርስ ጥበቃ ጋራ ያለው ዝምድና ምን ይመስላል? የሚል ቃለ መጠይቅ አቅርቤለት ተከታዩን መረጃ ሰጥቶኛል፡፡

> *ከዚህ ላይ አሁን ፋሲል መዋኛውና አጠቃላይ ክበረ በዓሉ እንደ ቅርስ የሚወሰድ በመሆኑ ይህን ጠብቆ ማቆየቱ እንደ ቅርስ ጥበቃ ይወሰዳል፡፡ ሁሉም ኅብረተሰብ በባለቤትነት በመጠበቅ ሃላፊነት ይወስዳል ማለት ነው፡፡ የግድ የቅረስ ጥበቃ ሃላፊዎች ቢሮች አደሉም፡፡ ቅርስን መጠበቅ ያለባቸው፡፡ ማህበረሰቡ ሁሉም ተቆርቋሪ ነው፡፡ ትልቁ ጥምቀትን ለየት የሚያደርገው ይህ ስለሆነ (ንጋቱ ችሎቴ 17/06/11 ቃ.መ)፡፡*

መረጃው እንደሚሳየው የጎንደር ቅርሶች ከጎንደር ጥምቀት ጋራ ቀጥተኛ ዝምድና ስላላቸው እንደ ቅዱስ ስፍራ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ቅዱስ መሆናቸው ደግሞ ማኅበረሰቡ ከቅርስነት ባለፈ ቅድስና ስለሚሰጣቸው ከፍ ያለ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ እንዳውም የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ የመዋኛ ገንዳው የተሰራው እና ግንቦቹ የተገነቡት እስራኤልን በጎንደር ለማቆም ነው ብሎ ያምናል፡፡ የዚህ ዓይነቱ እምነት የጎንደር ቅርሶች በማኅበረሰቡ ዘንድ ከፍተኛ ጥበቃ እና እንክብካቤ እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡ ይህን ጉዳይ ለማረጋገጥ የባሕረ ጥምቀቱ ግንብ ነገሥታቱ የገነቡበት ማኅበራዊ እና መንፈሳዊ አንድምታ ምንድን ነው? የሚል ቃለ መጠይቅ ለልዕልና ሃይለ መስቀል አቅርቤላቸው ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛ፡፡

> *ከእስራኤል ሀገር ጋራ የምንመሳሰልበት አንደኛው ይህ ነው፡፡ ዮርዳኖስ ወንዝ ያለው እስራኤል ነው፡፡ ያነን ለመዘከር ጌታችን መድኀኒታችን እየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበትን ቦታና ዕለት በመዘከር እኛም ተመሳሳይ ወንዝ የሚመስል መዋኛ ማንም አገር መሰል መዋኛ ባልገነባበት ምንአልባትም ባላወቀበት ዘመን እኛ ገንብተናል፡፡ በዚህም ጥሩ ትስስር እንዲኖረን ያስችላል (ልዕልና ሃይለ መስቀል 12/12/2011)፡፡*

ይህ መረጃ የጎንደር ጥምቀት ከእስራኤል ጋራ ያለውን ግንኙነት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ይህ ግንኙነት ደግሞ ቅርሶቹ ከቅርስ ባለፈ ወደ ቅድስና ቦታ ከፍ የሚደርጋቸው ነው፡፡ ይህ

ከፍታቸው ደግሞ ማኅበረሰቡ ቅርሶቹን ተገዶ ሳይሆን ወዶ፣ ሰምቶ ሳይሆን ዐይቶ፣ ርቆ ሳይሆን ቀርቦ እንዲወዳቸው እና እንዲጠብቃቸው ሁኗል፡፡ የጎንደር አብያተ ነገሥታት የቅድስና ቦታ እንዲይዙ ያደረጋቸው በዋናነት የጥምቀት ክብረ በዓል ነው፡፡ በተለይ የጥምቀተ ባሕር ማክበሪያው ቅደስና ዘመናትን የዘለቀ በየ ዓመቱ በጥምቀት በዓል በሚደረገው ሥርዓት ነው፡፡ የጎንደርን ጥምቀት ከሌላው አካባቢ በተለየ ሁኔታ በደመቀ መልኩ እንዲከበር ከሚያደርጉት መካከል አብያተ ነገሥታቱ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ አብያተ ነገሥታቱ እና አብያተ ክርስቲያኑ ጥምቀትን ባደመቁት ልክ እነሱም በጥምቀት ይከብራሉ፡፡ የጥምቀት ዕለት ውበታቸው ይጨምራል፡፡ የማጥመቂያው ግንብ በጥምቀት ዕለት በሰንደቅ አላማ፣ በውሃ ሙሊት፣ በሊቃውንቱ፣ በካህናቱ፣ በወጣቱ፣ በቱሪስትና በሰንበት መዘምራን ያሸበርቃል፡፡ በዚህ ምክንያት የጎንደር ማኅበረሰብ እየደጋገመ ይጠብቀዋል፤ ያከብረዋል፡፡



*(በዕለተ ጥምቀት የጎንደር ባሕረ ጥምቀት ድባብ በአጥኚው የተነሳ ፎቶ ግራፍ 2013)*

ሌላው የአጼ ፋሲል ቤተ መንግሥት ነው፡፡ በነገሥታቱና ሃይማኖቱ ቅርርቦሽ ይሁን የታሪክ ግጥምጥሞሽ ምክንያት የአጼ ፋሲል ቤተ መንግሥት በጥምቀት ክብረ በዓል ከፍ ያለ ማኅበረሰባዊ እና እምነታዊ ታሪኮች ይነገሩለታል፡፡ ለጎንደር ጥምቀት ነገሥታቱ ለካህናቱ ድግስ ደግሰው ጠጅ ጥለው፣ ታቦታትን ያከብሩ ነበር የሚለው ትረካ የእነሱ አብያተ ነገሥታት ከምድራዊ አልፎ ሃይማኖታዊ ቅርጽ እየያዘ እንዲመጣ አስችሎታል፡፡ ከሃይማኖታዊ አውደ ዓመት መካካል ደግሞ እንደ ጥምቀት የከበረ በዓል በጎንደር ያለ አይመስልም፡፡ በዚህ ምክንያት በሰሙነ ጥምቀት ሥለ ነገሥታቱ ሃይማኖታዊ ቀናዒነት፣ አሥተዳደርና፣ የንግሥና ዘመን ይተረካል፡፡

የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች "በአንድ ድንጋይ ኹለት ወፍ" በሚመስል መልኩ የጥምቀትን ክብረ በዓል ይታደማሉ፡፡ ይህውም አንደኛው የጥምቀትን ክብረ በዓል መሳተፍ ሲኾን ኹለተኛው ደግሞ የነ አጼ ፋሲልን ግንብ ማየት መቻል ነው፡፡ ይህም በአንድ ድንጋይ ኹለት ወፍ የሚለውን ብሂል ያጸናል፡፡

ይህን በተመለከተ ወ/ሮ እማዋይ ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል ወ/ሮ እማዋይ የመጡት ከአዲስ አበባ ነው፡፡ ኹለት ሴት ልጆች አሏቸው፡፡ አንደኛዋ አዲስ አበባ ቦሌ አየር መንገድ ውስጥ ትሰራለች፡፡ ታናሽ ሴት ልጃቸው ደግሞ ጎንደር ዩኒቨርሲቲ የሜዲካል ሳይንስ ተማሪ ናት፡፡ ወ/ሮ እማዋይ የጎንደርን ጥምቀት ለማክበር ሲመጡ ለጎንደር 44ቱ በረከት ነው ብለው ደሮ ወጥ ሰርተው በትንሽ ፈሪጅ አሽገው በሻንጣ ውስጥ ማባያውን ከእንጀራ ጋራ ይዘዋል፡፡ ጃን ሜዳ ያለውን ጥምቀት ትተው ለምን ጎንደር ማክበር እንዳስፈለጋቸው ቃለ መጠይቅ አቅርቤላቸው ነበር፡፡ እሳቸው ቀጣዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *"አወ ጥምቀትማ አዲስ አበባም አለ፡፡ የጎንደር ጥምቀትን ብቻ ሳይሆን ባሕረ ጥምቀቱን የፋሲልን ግንብን፣ ቤተ መንግሥቱን ኹሉ ለማየት ነው የመጣሁት፡፡ የጎንደርን ጥምቀት በየ ዓመቱ እንድመጣ ልጀም ቤሆን በጣም ነው የምትወተውኝ ዓለም ማየት ነው እያለች፣ የጎንደርን ጥምቀት ማየት መታደል ነው ትለኛለች፡፡ ብዙው የአዲስ አበባ ሰው የሚመጣው ለጥምቀቱ ብቻ ሳይሆን ኹለቱንም ለማየት ነው (እማዋ ደሴ 10/05/ 2013 ቃ.መ)* የሚል መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

ይህ መረጃ የሚሳየው እና የአጥኚው ምልከታ የሚያስረዳው በጎንደር ጥምቀት ዕለት ዐይን ካልታከተ፣ ጆሮ ካልሰነፈ እና እግር ካላደከመ በቀር የሚታየው የሚሰማው እና የሚጎበኘው ጉዳይ እጅግ ብዙ ነው፡፡ ይህን የሚያረጋግጠው ታቦታቱ ከጥምቀተ ባሕሩ ከማንኪት ተነስተው ወደ እየ አብያተ ክርስቲያናቱ እየተጓዙ ፒያሳ ደርሰው ባሕረ ጥምቀቱ በሰው እንደተሞላ ይቆያል፡፡ የጎንደርን ጥምቀት ልዩ የሚያደርገው ሰው ከታቦታቱ ጋራ ብቻ

ተከትሎ የሚሔድ ሳይሆን ከማንኪት እስከ መስቀል አደባባይ ፒያሳ ድረስ ያለው ቦታ ጥምቀት የሚከበርበት ነው፡፡ ሁሉም ቦታ ጭፍራ ሁሉምቦታ ዝማሬ፣ እና ሁሉም ቦታ ሆታ ይታያል፡፡ ይህ ሁሉ ጥምቀቱን እየታደመ የፋሲልን ግንቦች የሚመለከተው ሰው በርካታ ነው፡፡ የሕንጻ አሰራሮቹ በአሁኑ ዘመን የሚታዩ ባለመሆናቸው የእንግዳን ቀልብ የመሳብ እና የመማረክ አቅም አላቸው፡፡ በተለምዶ ፋሲል ግንብ ይባላል እንጅ በጎንደር ጥምቀት ማክበሪያ ከባሕረ ጥምቀቱ ውጭ ያሉ አጥር ዙሪያ ገባው እና አካባቢው ሁሉ በማራኪ ግንቦች የተሞላ ነው፡፡



*(የባሕረ ጥምቀቱን ዙሪያ ገባ አጥር የሚያሳይ ፎቶ ግራፍ 2013)*

የጎንደር ማኅበረሰብ ሕፃናት፣ ልጃ ገረዶች፣ ወጣቶች እና እናቶች የጎንደርን ቅርሶች ያለ ከልካይ ሲመለከቷቸው የሚውሉት በጥምቀት ቀን ነው፡፡ ልጆች ከእናቶቻቸው አንቀልባ ሁነው የነገሥታቱን ግንቦች ሲዳስሱ፣ አጸዱን ሲደገፉ፣ ጸበሉን ሲረጩ፣ እምነቱን ሲታሹ የሚድጉት በጥምቀት ነው፡፡ ጥምቀት የአደባባይ በዓል በመሆኑ ጥምቀት አክባሪዎቹ ያለ ከልካይ ይመለከቷቸዋል ብቻ ሳይሆን በጥልቀት ይገነዘቧቸዋል፡፡ በዚህ መልኩ የባለቤትነት

ስሜት በማኅበረሰቡ ዘንድ እንዲኖር እና ወደ እንክብካቤው እንዲገቡ ያስችላል። ይህን በተመለከተ ልእልና ኀይለ መስቀል ተከታዩን መረጃ ሰጥተውኛል።

> *እንግዲህ ጥምቀት በጎንደር ሲከበር አከባበሩ የማኅበረሰቡን ባህልና ሥርዓት የተከተለ ነው። እነዚህ የማኅበሰቡን ባህል፣ ወግ ና ዕሴቶች እንዲተዋወቁና ተጠብቆ እንዲቆይ ያደርጋል ማለት ነው። ተዋወቀ ማለት ተጠበቀ ማለት ነው። ሌላው ማኅበረሰቡ የራሱን ባህል ማንነት ካወቀ እየተንከባከበው ይሄዳል ማለት ነው። ስለዚህ የጥምቀትን ባህል የሚያከብረው ማኅበረሰብ ከእሱ እንዲርቅበትና እንዲበረዝበት አይፈልግም። ሁል ጊዜ በድምቀት እንዲከበርልት ይፈልጋል። ይህ ደግሞ የኔ ባይነት ስሜት ይፈጠራል። ባህሉ በራሱ ይከበራል። ሲከበር ደግሞ የሚከበርበት ቦታ የፋሲል ግንቦች በመኾኑ እነዚህ ቅርሳዊ ግንቦች እንዲጠበቁና እንዲተላለፉ ያደርጋል። ያ መዋኛ ለዚህ ጉዳይ የተሠራ ነው። የነገሥታቱ ዘመን ለክርስትና እምነት የነበራቸው ቀናዒነት ለዚህ ቅርስ መኖር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህ በዓል ሲከበር የዮርዳኖስ ወንዝ አስመስሎ ማኅበረሰቡ እንዲገለገልበትና በዚያ መልኩ የተሠራ ስለሆነ። እንዲከበር ያደርጋል። ቅርሶች እነዲጠበቁ ያደርጋል (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011)።*

ይህ የሚሳየው የጎንደር ጥምቀት ቅርሶችን ማስጠብቅ ብቻ ሳይሆን የማስተዋወቁ ፋይዳም ከፍተኛ ነው። የጎንደር ጥምቀት ከውጭ ለሚመጡት እና ለታዳጊ ሕፃናት ቅርሶቹን በማስተዋወቅ በኩል ሁነኛ ፋይዳ አለው።

### 9.3. የባህላዊ አልባሳት፣ እደ ጥበባት ጥበቃ እና ፈጠራ

የጎንደር ጥምቀት አንዱ ፋይዳው ባህላዊ አልባሳት እና እደ ጥበባት እንዲጠበቁ እና እንዲቀጥሉ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን ዐዳዲስ አገር በቀል ፈጠራዎችም እንዲመጡ የማድረግ ዐቅም አለው። እናቶች፣ ልጃ ገረዶች እና ልጆች የጎንደርን ባህላዊ ጥልፍ ቀሚስ እየለበሱ ማክበር ከጥንት የቆየ ትውፊት ነው። በዚህ መልኩ ጥልፍ ቀሚሶቹ በጥምቀት ሰሞን ተፈላጊነታቸው ስለሚጨምር ሸማ ሠሪዎቹ በብዛት በመሥራት እና በማቅረብ እንዲቀጥሉ የማድረግ ዐቅም አለው። የጎንደር እናቶች ሴት ልጆቻቸውን በጎንደር ጥምቀት ዐዳዲስ ጥልፍ ቀሚስ አልብሰው እንደ ባህሉ አፈሳሶ፣ አሳ ስሬት፣ ቁንጮና ጋሜ አሠርተው እና አስጊጠው ወደ ጥምቀቱ አስከትለዋቸው ይሄዳሉ። በዚህ መልኩ ከልጅንት ጀምሮ የሚለበሰው የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ ቀጣይ እንዲሆን የጥምቀት ክብረ በዓል ትልቅ ሚና አለው።

ኹለተኛው በወንዶች በኩል የሚለበሰው የጎንደር መገለጫ ጃኖ ነው። ጃኖ ቀድሞ በነገሥታቱ ዘመን ጀምሮ የሚታወቅ የጎንደር ባህላዊ ልብስ ነው። አዛውንቱ ብቻ ሳይሆኑ ወጣት ወንዶች ጭምር በብዛት ጃኖ በመልበስ የጎንደርን ጥምቀት ሲያከብሩ ይስተዋላል። በዚህ መልኩ ጃኖ ዋናው የጎንደር መገለጫ ነው። ጃኖ የጎንደር መታወቂ እና መገለጫ መሆኑን አቶ ጌትነት አመራ እንደሚከተለው መረጃ ሰጥተውኛል።

*ጃኖው የጎንደር ባህል ለዓለም የሚያስተዋውቅ ነው። ሴቶቹ ደግሞ መቀነት የሚባል ነገር አለ። በአረንጓዴ ቀለም፣ በቢጫ ቀለም፣ በቀይ ቀለም እያደረጉ ለብሰው እያሸበሸቡ ሲታዩ እንኳን ለኛ ለተወላጆቹ ለዓለምም የሚስብ ነው። በጣም ደስ ይለኛል። ጃኖ ስትል ጃኖ ለጎንደር ምልክታችን ነው። ባንዲራችን ነው። እንዳው ጃኖ ለብሶ ሲሄድ አንተ ባትለብሰው እንዳው በውነት ሌላው ለብሶ ሲሄድ ሰውነትህ ፈተት አይልም? ምን ያህል ነው ደስ የሚልህ? አቅሙ ካለህ እስከ ሦስት ቀን ያን ለብሰህ ብትውል ምን አለበት" ጌትነት አመራ* (13/05/2011 *ቃ.መ*)።

ጃኖ ድሮ ድሮ በዕድሜ ከፍ ያሉ ወንዶች ይለብሱት ነበር። ዐሁን አሁን ግን የጥምቀት ዕለት ወጣቶቹ ሳይቀሩ ጃኖ ለብሰው የሚያከብሩበት ሁኔታ ብዙ ነው። በጎንደር ጥምቀት ባህላዊ ለብስ እየሆነ መጥቷል። በመኾኑም ጥምቀት የጃኖ ባህላዊ ልብስ እንዲቀጥል በማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ማለት ይቻላል። የጎንደር ጥምቀት ጥንት የነበሩት የባህል አልባሳት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ዐዳዲስ ባህላዊ አልባሳትም እንዲፈጠሩ ምክንያት እየሆነ ነው። በጎንደር ጥምቀት በማኅበር፣ በጉርብትና፣ በጓደኝነት፣ በዝምድና መለኪያዎች የየ ፎክ ቡድኑ የራሳቸው መገለጫ የሆኑ አልባሳትን እያሳተሙ እየለበሱ ይገኛሉ። አልበሳቱ ጎንደር ላይ ተሥርቶ የቡድኑን ማንነት ዕሳቤ እና ፍላጎት የሚገልጹ ናቸው። በወንዶቹ አላባሳት ላይ የመጡበትን አካባቢ የሚገልጹ፣ የሚከፍሉትን ጽዋ ማኅበር የሚዘክሩ፣ የሚስማሙበትን ፍልስፍና የሚያንጸባርቁ ዕሳቤዎች በልብሶቻቸው ላይ ያሳትማሉ። ከጥምቀተ ባሕሩ ጀምሬ ወደ ጥምቀቱ ማክበሪያ ፒያሳ በሚደረገው እንቅስቃሴ የሎዛ ማርያምን፣ የአጣጣሚ ሚካኤልን፣ የመንበረ መንግስት መድኀኔዓለምን እና የመጥምቁ ዮሐንስን የሚገልጹ አልበሳት የታተሙባቸውን የለበሱ ወጣቶች በቡድን በቡድን ሲንቀሳቀሱ ተመልክቻለሁ። ከፍልስፍና አኳያ ደግሞ ይቅርታን የሚያስተምሩ፣ ሰላምን የሚሰብኩ፣ ጎንደርን የሚያወሱ አልበሳት በጥምቀቱ ውስጥ በሚታደሙ ወጣቶች በሆታዎች፣ በአስተናጋጆች እና በጨፋሪዎቹ ዘንድ ተለብሰው ይውላሉ (አየለ ቴዎድሮስ 10/05/2013 *ቃ.መ*)።



*(በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የመጥምቁ ዮሐንስ አካባቢ ልጆች ዕድሜን መሠረት ያደረገ አለባበስ 2013)*

የጥምቀት ክብረ በዓል አልባሳትን መጠበቅ እና መፍጠር እንዳለ ሁኖ የአልባሰቱ ጽሑፍ የማኅበረሰቡን እሳቤ ፍልስፍና እና ምኞት የሚገልጹ ናቸው፡፡ በጎንደር ጥምቀት የአንድ ቡድን አባላት የሆኑ በአካባቢ፣ በዕድሜ፣ በሥራ፣ በፍላጎት ተመሳስሎ ያላቸው ወጣት ወንዶች አንድ ዓይነት አልበሳት ለብሰው ይታደማሉ፡፡ የቡድኑ አባላት ቁጥር በትንሹ ከአምስት እስከ ኹለት መቶ ሊዘልቅ ይችላል፡፡ እነዚህ ቡድኖች በጥምቀቱ ተሳትፎ ውስጥ በሥራቸው እና ግብራቸውም በብዛት ተመሳስሎ ይታያል (አየለ ቴዎድሮስ፣ 10/05/2013 ቃ.መ.)፡፡

የልጃ ገረዶቹ እልባሳት ደግሞ እንደ ወንዶቹ ስለ አንድ ጉዳይ የተጻፈባቸው እና የታተመባቸው አይደሉም፡፡ ከዚህ ይልቅ በአልባሳቱ ቀለማት ላይ ተመሥርተው ራሳቸውን የሚገልጹ እና የሚያስተዋውቁ ናቸው፡፡ የጥምቀት መቃረብ ተከትሎ ልጃ ገረዶቹ በአንድ ላይ ሁነው ወደ ባህል አልባሳት ቤቶች ይሄዳሉ፡፡ ከሄዱ በኋላ እነሱን የሚወክሉ፣ የሚስማሙ እና የሚያስጌጡ አልበሳትን መርጠው ያሰፋሉ፡፡ እነዚህን ዐዲስ አልባሳት ለብሰው ጥምቀቱን ያከብራሉ፡፡ በወንዶቹ እንደተስተዋለው ሁሉ በልጃ ገረዶቹም ቢሆን

ተመሳሳይ የሆነ ዐዲስ[112] ልብስ የለበሱት ልጃ ገረዶች የጥምቀት ተሳትፏቸው ተመሳሳይ ነው፡፡ አንደኛዋ ከጭፈራው ሌላኛዋ ከሆታው አይቀላውጡም፡፡ ከቡድኑ አባላት መካከል አንድ ብስል እንድ ጥሬ አይታይም፡፡ እነዚህ ልጃ ገረዶች ከዐዲሱ ልብስ ጋራ የራስ ሥሬታቸው፣ ጫማቸው እና እርባናቸውም ተመሳሳይ ነው፡፡ በዚህ መልኩ በጥምቀት ክብረ በዓል ዐዳዲስ አልባሳት መፈጠር እና መምጣት በከፍተኛ ሁኔታ ይታያል፡፡ ይህ የሚያሳየው የጎንደር ጥምቀት የቆውን ባህል አልባሳት መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ዐዳዲስ ሀገር በቀል ዕውቀቶችን መሠረት ያደረጉ አልባሳትም እንዲፈጠሩ እያደረገ መሆኑን አረጋጋጭ ነው፡፡ እነዚህ አዲስ የሚመጡት አልባሳት ለአሁኑ ባህል ናቸው ባንልም እየተለመዱ እና በማኅበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እያገኙ ሲመጡ ባህላዊ አልባሳት ወደ መሆን የመሄድ እድል ይኖራቸዋል፡፡ እነዚህን አዳዲስ አልባሳት የሚጠቀሙ ወጣቶቹ የዕድሜ መቀራረብ፣ የጾታ ተመሳስሎ፣ የፍላጎት መስማማት እና የቤተሰብ ዝምድና የሚታይባቸው ናቸው (አየለ ቴዎድሮስ 10/05/2013 ቃ.መ.)፡፡



*(በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ላይ ዝምድናን መሠረት ያደረገ አለባበስ እና አጊያጊያጥ 2013)*

[112] እነዚህን በጎንደር ጥምቀት በብዛት በአሁኑ ወቅት እየተፈጠሩ ያሉትን አልባሳት ባህላዊ ናቸው ለማለት እቸገራለሁ፡፡ በመኾኑም ዐዳዲስ እና የሚፈጠሩ አልባሳት እያልኩ እጠራቸዋለሁ፡፡

ሌላው የጎንደር ጥምቀት ባህላዊ ዕሴቶችና ዕውቀቶች ከነ አካቴው[113] እንዳይጠፉ እና እንዳረሱ የማድረግ መጠነኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ በጥምቀቱ ዕለት የጥምቀቱ ማክበሪያ የሆኑት እንደ ማሲንቆ፣ ዋሽንት፣ በገና ከበሮና መሰል መገልገያ መሳሪያዎች ብቻ ሳይሁን የበገናው ቅኝት፣ የከበሮ አመታት፣ የዋሽንት አነፋፍ፣ የማሲንቆ አመታት ዕውቀቶች እንዲቀጥሉ ያደርጋል፡፡ የምቀት ክብረ በዓል እየጠፋ እና እየተረሳ ያለውን የበገና ቅኝት እንደ መከወኛ ሰበብ በመኾን መጠኑ እንዲታውስ እና እንዲቀጥል የማድረግ አስተዋጸኦ አለው (አየለ ቴዎድሮስ፣ 2013 .መ)፡፡



*(በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል የበገና ቅኝትና ክዋኔ 2011)*

### 9.4. የጎንደር ጥምቀት ለአካባቢ ጥበቃ ያለው ፋይዳ

የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል አካባቢን የመጠበቅ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ የጎንደር ጥምቀት የውሐ ብክነትን እና የአየር ብክለትን የመቆጣጠር ፋይዳው የጎላ ነው፡፡ ወደ ጥምቀተ ባሕሩ ተጠልፎ ሲገባ የኖረው የቅሐ ወንዝ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት የአካባቢው ማኅበረሰብ በቅሐ ወንዝ ላይ ቆሻሻ አይጥልም፡፡ ይህ የሆነበት ዋናው ምክንያት ደግሞ በማኅበረሰቡ ዘንድ

113 መረጃው ቢያመላክትም በአጥኚው የባህል ምዘና መሠረት በጊዜ እና በቦታ ሊጠፋ የሚችልን ጉዳይ እንዲያብብ ያደርጋል ማለት ስለማይቻል ቢያንስ ከነ አካቴው እንዳይቀበር የማድረግ ሚና ይኖራል ከሚል ዕሳቤ የሚታይ ነው፡፡

የቅሐ ወንዝ በጥምቀት የተባረከ እና የተቀደሰ ተደርጎ መወሰዱ ነው፡፡ ለዚህም የጎንደሩ የቅሐ ወንዝ እና የዮርዳኖሱ የዮር ወንዝ ተፈካካሪዎች ናቸው፡፡ የዮር ወንዝ ዳኖስ ሲደርስ ክርስቶስ ተጠምቆበታል፡፡ የቅሐ ወንዝም ማንኪት ሲደርስ የጎንደር ሕዝብ ይጠመቅበታል፡፡ የቅሐ ወንዝ የጎንደርን ማኅበረሰብ በማጥመቅ ይባርካል፡፡ ማኅበረሰቡም መልሶ የቅሐ ወንዝን ይቀድሳል፡፡ ስለሆነም የቅሐ ወንዝ ለማኅበረሰቡ እና ማኅበረሰቡ ለቅሐ ወንዝ አንዳቸው ለሌላቸው መባረኪያ እና መቀደሻዎች ናቸው፡፡ በዚህ መልኩ ውሐዎች በየ ዓመቱ በጎንደር ጥምቀት ይጠበቃሉ፤ ይባረካሉ (አባ እንባቆም መሐሪ 10/05/2011 እና መ/ር ፍቃድ ቀለመወርቅ፣ 15/06/2012 ቃ.መ.)፡፡ እንደዚሁም የዕጽዋት እና የአእዋፋት ጥበቃ በጎንደር ጥምቀት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የህን በተመለከተ መ/ር ፍቃድ ቀለመወርቅ፣ ቀጣዩን መረጃ ሰጥተውኛል፡፡

> *ፄፀቱ ታቦታት ያለባት ከተማ በመኾኑ ለየት ያደርጋታል፡፡ ወጣቶች በአንድነት መንፈስ ጥንካሬ ታጥረው የሚያከብሩበት ነው፡፡ በአካባቢ ያሉ ቆሻሻዎችን በጽዳት መልክ የሚጸዱ ናቸው፡፡ የጎንደር ጥምቀተ ባሕር ከዓመት እስከ ዓመት ኹሌም ጽዱ ሁኖ ነው የሚገኘው፡፡ የአዕዋፋቱ የደኑ የአካባቢው ልምላሜ የወንዙ ሁኔታ የባሕረ ዮርዳኖስን የሚተካ ነው፡፡ ሥሪቱም ዮርዳኖስ ስለኾነ ዮርዳኖስ መሄድ አይጠየቅም፡፡ ዮርዳኖስን በጎንደር ማየት ነው፡፡ በጠበሉ የተጠመቀው፣ የጠጣው ባሕረ ዮርዳኖስ እንደተጠመቀ ይሆንለታል (መ/ር ፍቃድ ቀለመወርቅ፣ 15/06/2012 ቃ.መ.)፡፡*

ባሕረ ጥምቀቱ አካባቢ ያለው ታላላቅ ዛፎች እና አእዋፋት ዓመቱን ሙሉ መስኅብነታቸውን ጠብቀው ይኖራሉ፡፡ በዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ዘንድ ወፎች ልማዳዊ እና ሃይማኖታዊ አንድምታ አላቸው፡፡ ከልማድ አንጻር አንድም ወፎች የእጣ ፈንታ እና ገድ ይናገራሉ፤ አንድም እንደ እባብ እና ነብር ሰውን ጎጅ አራዊትን ሊተናኮሉ ሲሉ ቀድመው ይጠቁማሉ፤፣ አንድም ለገበሬ ዕድሜ ይለምናሉ የሚሉ እምነቶች አሉ፡፡ ከዚህ በመነሣት የአካባቢው አርሶ አደር ዘር ሲዘራ “ከአወፍ አይላፍ አብላኝ” የማለት ልምድ አለው (መ/ር ፍቃድ ቀለመወርቅ፣ 15/06/2012 ቃ.መ.)፡፡

ከሃይማኖታዊው ዕሳቤ ደግሞ አንድም በክርስቶስ ጥምቀት መንፈስ ቅዱስ በወፍ አምሳል መምጣቱ፣ አንድም ቅዱስ ያሬድ የቤተክርስቲያን ዕውቀት የኾኑትን ግእዝ፣ እዝል እና ዓራራይ ዜማዎችን በወፍ መረዳቱ፣ አንድም በኖህ ዘመን የርዕደተ ማዩን መጉደል ርእግብ በተባለች ወፍ መበሰሩ ከሃይማኖታዊ ዕሳቤው የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በመኾኑም ወፎች በጥምቀተ ባሕሩ ዙሪያ እና በመንበረ መንግሥት መድኀኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ጤፍ

እየተረጨላቸው ውሐ እየተቀዳላቸው ምግባቸውን ሲሰጡ ተመልክቻለኹ፡፡ በዚህ መልኩ በጎንደር ጥምቀተ ባሕር ዙሪያ አእዋፍ እና በግንቡ ላይ ተጠምጥመው ለበቀሉት ዛፎች በተደረገላቸው እንክብካቤ እና ጥበቃ ምክንያት የተመልካችን ልብ እና ቀልብ ማርከው የሚያያስቀሩ ናቸው (መ/ር ፍቃድ ቀለመወርቅ፣ 15/06/2012 ቃ.መ.)፡፡ ስለሆነም የጎንደር ጥምቀት የአካባቢውን ሥነ ምህዳር ከመጠበቅ አኳያ ክፍ ያለ ፋይዳ አለው፡፡



*(የባሕረ ጥምቀቱ ተፈጥሮ ሀብት ከውጭ ሲታይ 2013)*

## ምዕራፍ ዐሥር፡- ማጠቃለያ

ይህ ጥናት "የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ አንድምታ እና ፋይዳዎቹ በጎንደር" በሚል ርዕስ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡ የዚህ ጥናት ዓላማ የጎንደርን የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ አንድምታ እና ፋይዳዎች መተንተን እና ማጥናት ነው፡፡ ይኽን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ዐውድ ላይ የሚከወኑትን ቃል ግጥሞች፣ መንፈሳዊ ዝማሬዎችን፣ ንዋየ ቅድሳት፣ ቁሳዊ ባህል አንድምታ እና ፋይዳዎች በመተንተን ተጠንቷል፡፡ እንደዚኹም ከጥምቀት ክብረ በዓል ጋራ ተያይዞ ስለ ጎንደር ጥምቀት እና ነገሥታት የሚነገሩ ሚቶችን እና አፈ ታሪኮችን በመተንተን አንደምታቸውን አሳይቷል፡፡ ሌላው የጥናቱ ዓላማ የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ፣ ለማኅበራዊ፣ ለምጣኔ ሀብታዊ፣ ለሰባዊ፣ ለቱሪዝም እና ለአካባቢ ጥበቃ ያሉት አንድምታ እና ፋይዳዎች መመርመር እና ማጥናት ነው፡፡

ለጥናቱ መመልከቻ የክዋኔ ንደፈ ሐሳብ፣ የተግባራዊ ንድፈ ሐሳብ፣ የሚት ንድፈ ሐሳብ እና የሥነ ፍች ንድፈ ሐሳብ የተባሉት በጥምረት ተወስደዋል፡፡ እነዚህ ንድፈ ሐሳቦች የተመረጡበት ምክንያት የክብረ በዓሉን ክዋኔ ዐውድ እና ፋይዳዎች ለመመርመር እና ለማውጣት አስቻይ ኹነው በመገኘታቸው ነው፡፡

ጥናቱ ዐይነታዊ ሲኾን የጥናቱ መረጃዎች በቀዳማይ እና ካልዓይ የመረጃ ምንጮች የተሰበሰቡ ናቸው፡፡ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ከመስክ መረጃ ሰጭዎችን እና ተጠኚዎችን የሚመለከት ነው፡፡ እንደዚሁም ከቤተ መጻሕፍት እና ቤተ መዛግብት ካልዓይ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድም ለጥናቱ ሥነ ጽሑፋዊ ቅኝት፣ ንድፈ ሐሳባዊ ማሕቀፍ እና የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ግብዓት በሚኾን መልኩ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በተቻለ መልኩ በሥራ፣ በዕድሜ፣ በጾታ እና በሃይማኖት ስብጥር መረጃ ሰጪዎችን ለማሳተፍ እችል ዘንድ በዋናነት ታላሚ ንሞናን ለጥናቱ ተጠቅሜአለሁ፡፡ በታካይነት ደግሞ የተጠኚዎችን ተሳትፎ ለማካተት የብድግ ብድግ ንሞናን ተግባራዊ አድርጌአለሁ፡፡ እንደዚሁም ተተኳሪ የቡድን ውይይት ለማደራጃት ያስችለኝ ዘንድ የድርሻ ንሞናን በመጠኑ ተጠቅሜያለሁ፡፡ በመረጃ ስብሰባ ወቅት 66 መረጃ ሰጪዎችን በቃለ መጠይቅ እና 28 የመረጃ ተባባሪዎችን ደግሞ በተተኳሪ የቡድን ውይይት አሳትፌአለሁ፡፡ ከእነዚህ መካካል ወንድ 54 እና ሴት 40 በድምሩ 94 መረጃ

ሰጪዎች በጥናቱ ተካተዋል። በዚህ መልኩ ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት የተባሉት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ለጥናቱ ተግባራዊ ተደርገዋል። የክዋኔ፣ የአሐድ፣ የዐውድ፣ የዐይነታዊና የፍካሬ የመተንተኛ ስልቶችን ተከትሎ የጥናቱ ትንታኔ ተካሂዷል።

ጥናቱ በጥምቀቱ ዐውድ፣ በክዋኔ ሥርዓት፣ በማኅበራዊ ፋይዳ፣ ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ በሰባዊ ፋይዳ እና በቱሪስት መስሕብ እና አካባቢ ጥበቃ ላይ ተመሥርቶ የተተነተነ ነው። የጥምቀቱ ዐውድ ቅድመ ጥምቀት፣ የከተራ እና ዕለተ ጥምቀት በሚሉት ንዑሳን አርስት ተመሥርቶ የተተነተነ ነው። በዚህ ውስጥ የጎንደር ማኅበረሰብ የጥምቀት ግምግምታ ሲሰማ ከወር ቀደም ብሎ ዝግጅት ያደርጋል። ልጆች ቀርሚያ ለቅመው፣ ዶሮ አርብተው እና ጌሾ ለቅመው ልብስ ይገዛሉ፤ ያስገዛሉ። እረኞች ደግሞ ከጥምቀት ቀደም ብለው ሽልም ግና፣ እንቁር እና ጡሩምባ ያዘጋጃሉ። እንደዚሁም ወጣት ወንዶች የእስክስታ፣ የዘፈን እና የአይብላሆ መኔ ዝግጅት ያደርጋሉ። ጥምቀት ሲቃረብ ልጃ ገረዶች ደግሞ ጥልፍ ቀሚስ፣ መቀነት እና ሻሽ ወላጆቻቸውን ያስገዛሉ። ርባን፣ አልቦ ድሪ እና የጸጉር አሠራራቸው ምን እንደሚመስል ከጓደኞቻቸው ጋራ ይመካከራሉ። የጥምቀትን መቃረብ ተከትሎ የነጋዴዎች እንቅስቃሴ እና የጎንደር ከተማ ድባብ ደማቅ ይሆናል። የሽልምግናው ነጭ እና ጥቁር መኾን ነጩ የንጽሕና፣ ቅድስና፣ የልዕልና ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል። ጥቁሩ ደግሞ የቂም በቀል፣ የጥላቻ፣ የነውር እና የነቀፋ ምሳሌ ነው። ቅድመ ጥምቀት የመልካም ምኞት ማብሰሪያ ተደርጎ ይወሰዳል።

ከተራ ወይም የጥምቀት ዋዜማ ታቦታቱ ከየ አብያተ ክርስቲያኑ ወጥተው በካህናቱ፣ በሊቃውንቱ፣ በዘማርያኑ እና በምእመኑ ታጅበው ወደ ባሕረ ጥምቀቱ የሚወርዱበት ዕለት ነው። በዚህ ዕለት ጎንደርን፣ ኢትዮጵያን እና ማኅበረሰቡን የሚወክሉ ቅርጻቅርጾች፣ ባነሮች እና የቅዱሳን ሥዕላት አብረው ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ይወርዳሉ። ዕለተ ጥምቀት ደግሞ ሥርዓተ ቁመቱ እና ሥርዓተ ቅዳሴው ከተጠናቀቀ በኋላ ባሕሩ ይባረካል። የተባረከውን ባሕር ሕዝቡ እየተሻማ እና በሰው ላይ ሰው እየወጣ በካህናቱ ርጭት ይካኼዳል። በጸበል ርጭት ጊዜ እና ከርጭቱ በኋላ ጀምሮ ወጣቶች በባሕረ ጥምቀቱ እየዘለሉ በመግባት ዋና ያደርጋሉ። በዚህ ዋና ሥርዓት ውስጥ ከታላላቅ ዛፎች ላይ እየወጡ ወደ ባሕረ ጥምቀቱ የሚወረወሩ ወጣቶች ብዙ ናቸው። ይህ በዛፍ ላይ እየወጡ ወደ ታች መወርወር

የማኅበረሰቡን ሕይወት ጠቋሚ ነው፡፡ ሰዎች አንድ ጊዜ ሲወጡ ሌላ ጊዜ ደግሞ ሲወርዱ የሚራመዱትን ሕይወት ይተረጉማል፡፡ ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ለመግባት በርብራብ ላይ የሚደረገው ጉዞ እና ከዛፍ ላይ ወደ ታች የሚደረገው መወርወር በባሕረ ጥምቀቱ የሚከወኑ ፈታኝም፣ መሳጭም ተግባራት ናቸው፡፡ እነዚህን እና መሰል የባሕረ ጥምቀቱን ሥርዓት የአካባቢው ማኅበረሰብ፣ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ቱሪስቶች በጉጉት የሚመለከቱት እና የሚወዱት ክዋኔ ነው፡፡

በጎንደር ጥምቀት ታቦት ሲነሣ ታቦት ሲያረፍ እና ታቦት ሲገባ ለየት ያለ ድምቀት እና ሥርዓት ያለው ክዋኔ ይካሄዳል፡፡ የታቦታት መነሣት የመወለድ፣ የታቦታት ማረፍ በዚህ ዓለም የመኖር እና የታቦታት መግባት ደግሞ ከዚህ ዓለም በሞት የመለየት እና የመንግሥተ ሰማያት መውረስ ተምሳሌት ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

በጎንደር ጥምቀት ሥርዓተ ክዋኔ ውስጥ ሊቃውንቱ ከሥርዓተ ቁመት፣ ከወረብ፣ ከማሕሌት ጋራ የተያያዘ ተሳትፎ አላቸው፡፡ ካህናቱ ደግሞ ከሥልጣነ ክህነት ጋራ የተያያዘ የቅዳሴ፣ የውዳሴ፣ የጸበል ርጭት ተግባራት ያካኼዳሉ፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ ካህናቱ ባላቸው ልብሰ ተክህኖ እና ጸበል ርጭቱ ምክንያት ከፈጣሪ የማስታረቅ እና ከኀጢአት የማስተስረይ ተግባር ይሠራሉ ተብሎ ይታመናል፡፡ እንደዚኹም በጥምቀት የሰንበት ዘማርያን ወጣት ወንዶችን እና ሴቶች ክዋኔ ተጠቃሽ ነው፡፡ የዘማርያኑ የክዋኔ ድርሻ በወንድ እና በሴቶች መካከል እኩል የሆነ የአገልግሎት ተሳትፎ የሚታይበት ነው፡፡ በጥምቀት ክብረ በዓል ልጃ ገረዶች፣ እናቶች፣ ወጣቶች እና አባቶች የየራሳቸው የክዋኔ ተሳትፎ አላቸው፡፡ በተለይ ወንድ ወጣቶች የአይብላህ ወመኔ ሆታ ከፍተኛ የኾነ ትንቅንቅ እና ጉልበት የሚታይበት ዘርፍ ነው፡፡ በሆታው ላይ የሚቀነቀኑት ቃል ግጥሞችም ስለ እርጅና፣ ስለ ሞት፣ ስለ ጓደኛ እና ስለ ሀገር የሚዘክሩ ጭብጦች አሏቸው፡፡

የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል የተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮችን የማቀራረብ፣ ከጎንደር ውጭ የሚኖሩ ተወላጆችን የማገናኘት፣ ማንነትን የመገለጽ፣ ታሪክን የማሳወቅ እና ማኅበረሰቡን የማቀራረብ ማኅበራዊ ፋይዳ አለው፡፡ እንደዚሁም የጎንደር ጥምቀት ባህላዊ አልባሳት፣ ባህላዊ መጠጦች፣ ባህላዊ ምግብ እና ሀገር በቀል ዕውቀቶች ላይ የተመሠረት ምጣኔ ሀብታዊ ፋይዳ አለው፡፡ በጥምቀት ሰሞን የሥነ ጽሑፍ ተሰጥኦ ያላቸው ግለሰቦች፣ የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች እና አዝማሪዎች ከዘወትሩ የተሻለ ገቢ የሚያገኙበት ጊዜ ነው፡፡

የጥምቀት ክብረ በዓል ገቢ ከማስገኘቱ በተጨማሪ ሀገረሰብ ዕውቀቶች እና ፈጠራዎች እንዲቀጥሉ የማስቻል አስተዋፅኦ አለው፡፡

በጥምቀት ክብረ በዓል ሌላው ትንታኔ የተደረገበት ክፍል ሰባዊ ፋይዳ ነው፡፡ የጥምቀት ክብረ በዓል ፍቅርን፣ ደግነትን፣ ሰው መውደድን፣ ሥነ ምግባርን እና መሰል ከጥምቀት መምጣት ጋራ የሚገናኙ ናቸው፡፡ የክርስቶስን በጎ ተግባራት በማስታወስ እና በመዘከር ሰባዊ መተሳሰብ እና መታዘዝን በሰዎች አእምሮ ውስጥ ያሠርጻል፡፡ እንደዚኹም የጥምቀት ክብረ በዓል ባለው ልዩ ውበት እና ክዋኔ በመነሣት የሀገር ውስጥ እና የውጭ ሀገር ቱሪስቶችን የመሳብ ዐቅም አለው፡፡ ቱሪስቶቹ የጎንደርን አልባሳት በመልበስ የጥምቀትን ክዋኔ በቪድዮ፣ በፎቶ ካሜራ እና በኦዲኦ በመቅረጽ ጭምር ሀገርን ያስተዋውቁበታል፡፡ በጎንደር በሚቆዩበት ጊዜ ሀገረሰባዊ አልባሳትን፣ ቁሳዊ ባህልን፣ ንዋዬ ቅድሳትን እና መሰል ለምግብና ለዐልጋ የሚያወጧቸው ወጭዎች ምጣኔ ሀብቱን በመደገፍ በኩል ትልቅ ፋይዳ አላቸው፡፡

ሌላው የጎንደር ጥምቀት ፋይዳ አካባቢን መጠበቅ ማስቻሉ ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀት በቅድሚያ ማኅበረሰቡ ስለ ባህሉ፣ ስለ አካባቢው፣ ስለ ቅርሶቹ እና ስለ ታሪኩ እንዲረዳ ያደርጋል፡፡ ማኅበረሰቡ በዚኽ የጥምቀት መረዳት ውስጥ የራሱን ባህል እና ቅርስ እንዲጠብቅ ያስችለዋል፡፡ የጎንደር ጥምቀት ወደ ባሕረ ጥምቀቱ ተጠልፎ የሚገባውን ቀሐ ወንዝ እና ሌሎችንም ጨምሮ ከዮርዳኖስ ወንዝ ጋራ በማነጻጸር ቆሻሻ እንዳይጣልባቸው እና ቁርበት እንዳይነከርባቸው በማድረግ ንጽሕናቸውን ያስጠብቃል፡፡ የባሕረ ጥምቀቱ ዙሪያ ገባ በታላለቅ ዛፎች የተከበበ እና የተሸፈነ ነው፡፡ በማኅበረሰቡ ዘንድ በባሕረ ጥምቀቱ ዙሪያ የሚገኙ እፅዋቶች እና አእዋፋት የተባረኩ እና ተቀደሱ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ ጥምቀት በሰጣቸው ቅደስና ምክንያት በአካባቢው የሚገኙ ውሐዎች፣ እፅዋት እና አዕዋፋት ተጠብቀው እና ጸንተው ከትውልድ ትውልድ እንዲተላለፉ ያስችላል፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል አካባቢን በማስጠበቅ በኩል ትልቅ ሚና አለው፡፡

የጥናቱ ግኝት እንደሚያስረዳወም የጎንደር ጥምቀት ሥርዓተ ክዋኔ አንድምታ እና ፋይዳዎቹ ሲተነተኑ ለልጃ ገረዶች፣ ለወጣቶች፣ ከሀገር ለወጡ ማኅበረሰቦች፣ ለአዛውንቶች በአጠቃላይ ለተጠኚዎቹ ማኅበረሰበሰቦች ከፍ ያለ ማኅበራዊ ፋይዳ አለው፡፡ ማኅበራዊ ፋይዳዎቹ የተለያዩ የሃይማኖት ተከታዮችን የማቀራረብ፣ ማኅበራዊ ትስስርን የማጠናከር፣ ለልጃ ገረዶች ነጻነት እና ተሳትፎ የመስጠት፣ ማኅበራዊ ማንነትን የማስቀጠል፣ ትውፊትን እና ዕሴትን

የማስጠበቅ ማኅበረሰባዊ ፋይዳዎች ያሉት መኾኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ እንደዚኹም እነዚህ ማኅበረሰቦች በጎንደር ጥምቀት ድምቀት እና ታዳሚ ብዛት አማካኝነት በሚኖረው ከፍተኛ የኾነ የሀገር ውስጥ እና ውጭ ሀገር ቱሪስቶች ምክንያት ከፍተኛ የኾነ ገቢ በከተማዋ ውስጥ ይፈሳል፡፡ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ምጣኔ ሀብታዊ እንቅስቃሴው በዋናናት በሀገር በቀል ዕውቀቶች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቀጣይነት ያለው ከመኾኑ በተጨማሪ ዕሴትን፣ ባህልን ትውፊትን ለማስቀጠል እና ለማሳዳግ የሚያስችል ነው፡፡ የምጣኔ ሀብት ጠቀሜታው በዋናነት በሀገረሰባዊ አልባሳት፣ በሀገረ ሰባዊ ምግብ እና መጠጦች፣ በቁሳዊ ባህል፣ በንዋየ ቅድሳት እና በመሳሳሉት ንግድ የሚለካ እንደኾነ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በዚህ መልኩ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ለማኅበራዊ መዋቅር፣ ለምጣኔ ሀብታዊ ዕደገት፣ ለሰባዊ ዕሴት፣ ለቱሪዝም መስሕብ እና ለአካባቢ ጥበቃ ኹነኛ ፋይዳዎች ያሉት መኾኑ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡ እነዚህ በጥናቱ የተገኙት የጥምቀት ክብረ በዓል ፋይዳዎች ራሳቸውን ችለው የቆሙ ሳይኾን ርእስ በርሳቸው የመተጋገዝ፣ የመደጋገፍ እና አንዳቸው በሌላቸው ላይ የመከሰት ዝምድና ያላቸው ናቸው፡፡

## የይኹንታ ሐሳብ

አጥኚው ለቀጣይ ጥናት እና ምርምር ለሚያደርጉ አጥኚዎች መጠነኛ ጥቆማ ያደርጋል፡፡ እንደዚኹም በመረጃ አሰባሰብ ወቅት የተመለከታቸውን እና ጎጸጽ ብሎ የታዘባቸውን ጉዳዮች ይሻሻሉ ዘንድ ያለውን ሐሳብ እንደሚከተለው ይገልጻል፡፡

ይህ ጥናት በጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዐተ ክዋኔ አንድምታ እና ፋይዳ በጎንደር በሚል የተጠና ነው፡፡ አጥኚው ወደ ተግባር ሲገባ እጅግ ሰፊ እና ባለ ብዙ ዘርፍ ኹኖ አግኝቶታል፡፡ በመኾኑም ቀጣይ በሊቃውንተ፣ በአባቶች፣ በእናቶች፣ በወጣቶች፣ በልጃገረዶች፣ በአልባሳት፣ በቁሳዊ ባህል፣ በቃል ግጥሞች፣ በምልኪዎች፣ በአፈ ታሪኮች እና መሰል የጥምቀት ዘውጎች ላይ ተመሥርቶ ጥናቶች ቢካኼዱ መልካም ነው የሚል ጥቆማ አለኝ፡፡

እንደ ሃይማታዊ ክብረ በዓላት እና መሰል ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ላይ የሚደረጉ ጥናቶች ልብሳቸው ሃይማኖታዊ ይኹን እንጅ ውስጣቸው ሲፈለቀቅ ፎክሎራዊ፣ ባህላዊ እና ማኅበራዊ ፍሬዎች ናቸው፡፡ በመኾኑም ሃይማኖታዊ ጉዳይ ተደርጎ የሚታየው ዕሳቤ ቢስተካከል መልካም ነው እላለኹ፡፡

ሌላው እና ቀጣይ የምሰጠው አስተያየት በሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ላይ እና ከዚሁ ጋራ በተያያዘ ጥናት ለሚያደርጉ ተመራማሪዎች የሚወሰድ ምክር ነው፡፡ ሃይማኖታዊ ጥናት ሃይማኖት እና ባህል የተሰኙ ኹለት መንታ መንገዶች አሉት፡፡ በኹለት መንገዶች አማራጭ ምክንያት አጥኚው አንዱን መንገድ ተከትሎ ይነጉድ ዘንድ እድል አለው፡፡ ይኹን እንጂ አንዱን መንገድ መርጦ መጓዙ ጥናቱን ቀንጃ፣ ፍሬውን ጋጃ ያደርግበታል፡፡ በመኾኑም አንድ የሃይማኖታዊ ጉዳይ አጥኚ ሃይማኖቱን ከባህሉ፣ የሚያስተናግድ ዐዲስ ሦስተኛ መንገድ መፍጠር ግድ ይለዋል፡፡ ይህ ሦስተኛ የባህል እና የሃይማኖት መንገድ ደግሞ አጥኚውን አንድም በጉልበት አንድም በዕውቀት የሚፈትን ነው፡፡ በመኾኑም በሃይማኖታዊ ርእሰ ጉዳይ ላይ ሊሠራ የተነሣ አጥኚ ሦስተኛውን መንገድ ቀድሞ ማወቅ እና መዘጋጀት አለበት እላለሁ፡፡

ሌላው እንደ ፎክሎር ያሉ ጥናቶች ከፍተኛ የኾነ የመስክ ሥራ እንደሚጠይቁ የታወቃል፡፡ በመኾኑም አጥኚው ምንም ያክል ቢተጋ እንኳን አንዳንድ ጊዜ በአካባቢው ሹማምንት እና መሰል ያልተጠበቁ ዐውዶች ምክንያት የመስክ ሥራውን ለማከናውን ከዐቅሙ በላይ ሊኾንበት ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ትምህርት ክፍሉ ከተለመደው የትብብር ደብዳቤ መጻፍ ዐልፎ

ለሚመለከታቸው አካላት ስልክ እስከመደወል፣ መሰል ትብብር እና ክትትል ቢያደርግ መልካም ነው እላለሁ፡፡

ሌላው የጥናት አካባቢ መረጃ ነው፡፡ የጥምቀቱ ማክበሪያ በባሕረ ጥምቀቱ እና በዙሪያው ያለው ግንብ በጥምቀት ታዳሚዎች እየተናደ ይገኛል፡፡ በመኾኑም የጥምቀት ክብረ በዓል ሲከበር ለአብያተ ክርሥቲያኑ እና ለአብያተ መንግሥታቱ ጥንቃቄ ቢደረግ መልካም ነው እላለሁ፡፡

በክብረ በዓሉ ክዋኔ የጭፈራው ሥርዐት ላይ ዐልፎ ዐልፎ በሞንታርቦ በሚዘፈን የካሴት ዘፈን ወጣቶች፣ ልጃ ገረዶች፣ እናቶች እና እማወራዎች እስክስታ ሲውርዱ ይታያል፡፡ ይህ ደግሞ ዘፈኑን፣ ከእስክስታው የሚነጥል በመኾኑ ሀገር በቀል የኾነውን የጎንደር ጭፈራ ክዋኔ የሚያደበዝዝ በመኾኑ ወደ ተፈጥሮ መቼት ቢቀየር መልካም ነው እላለሁ፡፡

እንደዚኹም በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የሚወጡት ምስሎች እና ፎቶዎች አንዳንዶቹ በቂ ውይይት ይኹን መግባባት የተደረሰባቸው አይመስለኝም፡፡ ስለዚህ እነዚህ በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የሚያዙት የሚጻፉት ባነሮች፣ የሚያዙት ምስሎች እና ፎቶዎች የአካባቢውን ማንነት እና ዕሴት የሚወክሉ መኾናቸው ቢጤን መልካም ነው እላለሁ፡፡

ተከታይው ጥቆማየ ከጉዞ ጋራ የተያያዘ ነው፡፡ ከዐዲስ አበባ እና ከተለያዩ ቦታዎች ወደ ጎንደር ጥምቀት የታዳሚው ሕዝብ እና የጎብኚዎች ቁጥር ከዓመት ዓመት ከፍተኛ ነው፡፡ ይኹን እንጂ ይህን በወጉ እና በአግባቡ ሊያስተናግድ የሚችል የትራንስፖርት ምቹነት የለም፡፡ ከኹለት ሳምንት ጀምሮ የተመደቡት ተሽከርካሪዎች ትኬት ቆርጠው ስለሚጨርሱ ተጓዦቹ ለእንግልት ይዳረጋሉ፡፡ አንዳንዶቹ በተለይ ስለት ያለባቸው ታዳሚዎች ያለ ውድ በግድ የአውሮፕላን በረራ በማድረግ ላልተፈለገ ወጭ ይዳረጋሉ፡፡ እኔንም ቢኾን ይህ እድል በተደጋጋሚ ጎብኚቶኛል፡፡ በመኾኑም ለወደፊቱ በዚህ ዙሪያ የሚመለከተው አካላት መፍትኼ ቢያፈላልግ እላለኹ፡፡

ቀጣዩ አስተያየቴ ደግሞ በጥምቀተ ባሕሩ ያለው የመግቢያ በር ርብራብ አንድም ከእንጨት መሠራቱ፣ አንድም ከጥበቱ፣ አንድም ከውሽክሽክነቱ የተነሣ እየተደረመሰ ታዳሚዎችን እና ነባር ቅርሶችን የሚጎዳበት አጋጣሚ አለ፡፡ በመኾኑም በዚህ ጉዳይ ላይ የሚመለከተው አካል ዘላቂ መፍትኼ ይፈልግ ዘንድ አስተያየቴን እሰጣለሁ፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች (Reference)


ሀብተ ማርያም ወርቅነህ። <u>ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት።</u> ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ፣ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

መሶበወርቅ ቅጣው:: "የገና ክብረ በዓል አከባበር::" የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 1997::

<u>መዝሙረ ዳዊት</u>። ገብረ ስላሴ ብርሃኑ (አሳታሚ)፣ ዐዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1984።

<u>መጽሐፍ ቅዱስ</u>። London and Addis Ababa the British and Foreing Bible Society, printed in Great Brittain, 1986.

<u>መጽሐፈ ቅዳሴ ንባብና ትርጓሜ</u>። ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988።

"መስህብ መጽሔት።" በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት በየ ዓመቱ የሚታተም፣ ቅጽ-6 ቁጥር 9፣ ግራፊክስ ዲዛይንና ህትመት፣ ጨጨሆ ዲጅታል ህትመትና ማስታወቂያ ድርጅት፣ ጳጉሜ 2010።

<u>መድኀኒት በጥምቀት</u>። ዐዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1955።

በሰሜን አስተዳደር ዞንና የጎንደር ከተማ "የቱሪስት መስህብ ሃብቶች።" በሰሜን ጎንደር አስ/ ዞንና የጎንደር ከተማ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የተዘጋጀ፣ ፍኖተ ጥበብ ማተሚያ ቤት፣ ጥቅምት 2010።

በሰሜን አስ ዞንና የጎንደር ከተማ "የቱሪስት መስህብ ሃብቶች።" በሰሜን ጎንደር አስ/ ዞንና የጎንደር ከተማ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የተዘጋጀ፣ ፍኖተ ጥበብ ማተሚያ ቤት 2009።

ማኅበረ ቅዱሳን <u>የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2002</u>።

<u>ማኅደረ ቱሪዝም</u>። በኢትዮጵያ ቱሪዝም ሆቴል ኮሚሽን፣ ዐዲስ አበባ፣ 1972።

ሰሎሞን ደርቤ:: "የዝቋላ አቦ ክብረ በዓል አከባበር::" የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2000::

ተስፋየ ሞላ። "የክብረ በዓላት ስርዓተ ማኅሌት ተግባር" የኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ ዐዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ሥነ ጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ 2003።

ቴዎድሮስ ገብሬ። <u>በይነድስፕሊን የሥነ ጽሑፍ ንባብ</u>። ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ 2001።

አበባው ይርጋ። የጥምቀት በዓል፣ ምንነቱ፣ ማኅበረ ባህላዊ ዐውዶቹ እና ፋይዳዎቹ። Journal of Ethiopian studies vol. 39. No pp.151-174, December, 2006.

ኤርምያስ ወልደ እየሱስ። <u>ድርሳነ ቅዱስ ያሬድ በግዕዝና በአማርኛ</u>። ዐዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 2000።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ። <u>መጽሐፈ ሰዋሰው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሀዲስ</u>። ዐዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948።

ክንፈ ገብርኤል አልታዬ። <u>ጥምቀት</u>። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፣ ዐዲስ አበባ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

<u>ወንጌል ለልማት</u>። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን፣ የኤችአይቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ መምሪያ የወንጌል ለልማት ፕሮጀክት፣ ሦስተኛ እትም፣ 2007።

ደስታ ተክለ ወልድ። <u>ዐዲስ የአማርኛ መዝገበ ቃላት</u>። ዐዲስ አበባ፣ አርትስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

<u>ግብረ ሕማማት</u>። ዐዲስ አበባ፣ ተስፋ ገብረ ሥላሴ፣ ማተሚያ ቤት 1988።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን። <u>ስርዓተ ጥምቀት</u>። ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1947።

……...። <u>በዓለ ጥምቀት</u>። ዐዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1949።

--------። <u>መድኀኒት በጥምቀት</u> ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1959።

……..፡፡ የጥምቀት በዓል አከባበር በኢትዮጵያ፡፡ ቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ዐዲስ አበባ፣ 1963፡፡

……..፡፡ ጥምቀተ ክርስቶስ፡፡ ዐዲስ አበባ፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1959፡፡

ዮናስ አድማሱ፡፡ "አስረኛንኩዋ፣ ሀዲስ አለማዩሁና የማኅበራዊ ሂስ ሥልታቸው፡፡" የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና የሥነ-ጽሑፍ መጽሔት፣ ቁጥር 10፣ ገጽ 77-119፣ 1992፡፡

ዘማርያም ኤፍሬም እና በእደ ማርያም ዳንኤል "የጥምቀት በዓል አከባባር በኢትዮጵያ፡፡" በሐመር ዘኦርቶዶክስ ተዋሕዶ መጽሔት፡፡ 14ኛ ዓመት፣ ቁ.1፣ ገጽ 5-8 ዐዲስ አበባ፣ ሜጋ ማተሚያ ድርጅት፣ 1998፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ የሥነ ጽሑፍ መሰረታውያን፡፡ ዐዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት 1992፡፡

ዘወንጌል ገብረኪዳን እና ሌሎች፡፡ ቤተ ክርስቲያንክን እወቅ፡፡ 1996፡፡

ጥዑመ ልሳን ካሳ፡፡ ያሬድና ዜማው፡፡ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ 1962፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ የሥነ ቃል መምሪያ፡፡ ዐዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1991፡፡

African Folklore Encyclopedia. New York፡ London Published, 2004.

Aldashev, Gani and Platteau Jean Philippe. Religion, culture and development.,Volume 2, http://dx.doi.org/ 587-627, Oxford University press, 2014.

Atkinson, Paul and Hammersley, Martyn. (Eds). Ethnography Principles in practice (3rd edition) London and New York: published in the Taylor & Francis e-Library, 2007.

Aymro Wendimagegn and joachim Motuvu. The Ethiopian orthodox church Addis Ababa: Birhanina selam kedamawi Hayle silase printing press, 1970.

Barker, Christ. Dictionary of Cultural Studies. London, Thousand Oaks New Delhi: Sage Publications, 2004.

Barraw, C.J. envaromental management for sustaneble development. London, New York: Routldge, 2004.

Bart, Xox, George, W. An introduction to the science of comparative mythology and Folklore. (2nd Ed), London: 1983.

Bascom, William R. (ed). Four functions of Folklore Hand Book of American Folklore. Bloomington: Indiyana University Press, 1965.

Bauman, Richard. Verbal Arts as Performance. Long Grove Il; Wave Land Press, 1977.

-----. (Ed). Folklore cultural performance and Popular entertainment; New York: Oxford University Press, 1992.

-----."Toward New Perspectives on Verbal Art as Performance." Journal of The American Folklore, Vol. 115, No. 455, (pp. 62-91, Published by: University of Illinois Press on Stable URL: http://www.jstor.org/stable/542079, 2002.

Belkett, Chirist. Human grouth and development. London thousand oak, New Delhi: Sage publication, 2006.

Bell, Catherine. Ritual Perspectives and Dimensions. New York: Oxford University Press, 2009.

-------Ritual theory, ritual practice. New York: Oxford University Press, 2009.

-----. Ritual Perspectives and Dimensions. New York: Oxford University Press, 1997.

Bellu, Lorenzo G. "Development and Development Paradigms" A reasoned Review of Prevailing Visions Service, Policy and Programme Development Support Division 2011.

Ben-Amos, Dan. "Folklore in African Society."Vol, no 6, pp, 165-198, Indiana University Press, 1975.

-----. Folklore in context. New Delhi: Madras South Asian Publishiers, 1982.

-----. "Toward New Perspectives in Folklore" The Journal of American Folklore, Vol. 84, No. 331, (Jan.- Mar., 1971), pp. 3-15. published URL: http://www.jstor.org/ Thu Apr 12 06:33:25, 2007.

Bereans, E. M. The myths and legends of ancient Greece and Rome. New York: Clark & Maynard, publishers, 2009.

Berg L, Bruce. Qualitative research methods for the social sciences. California state university, 2001.

Bermmer, Jan. and Horsfall, Nicholas.Roman myth and mythography. University of London, No. 52 1982.

Blaxter, Loraine, Hughes, Christina and Malcolm, Tight.How to researchopen university press, 2006.

Bock, Hans Hermann, and Ihm, Peter. (Eds.) Classification, Data Analysis, and Knowledge Organization Models and Methods with Applications. Springer Verlag Berlin: Heidelberg, 1991.

Boyer, Pascal, and Lienard, Pierre.Why ritualized behavior? Precaution Systems and action parsing in developmental, pathological and cultural rituals. St. Louis: Washington University ,2002.

Byers, Jaco. "What is religion? An African understanding." vol. 66. No. pp 1-8 10 June, http://www.hts.org.za Published, 2010.

Callavaro, Dani. Critical and Culteral Theory.London; Theathlone Press, 2001.

Campbell, Josef. The mask of God: primitive mythology. London: Secker & Warburg, 1960.

-----. The hero with a thousand faces. Princeten university press, 1970.

Candace S. Alcorta. `Ritual, Emotion, and Sacred Symbols. ` The Evolution of Religion as Adaptive Complex Department of Anthropology U-2176 Connecticut University Storrs, CT 06269-2176, 2006.

Chalet Christian.The Ethiopian orthodox Tewahido tradition Poland orthodox Bialy stox, 2002.

Coffin Tristum P. the Relationships of Folklore Christianity Midwest Folklore, vol 2. No 1pp.43-46 published: Indiana university press, 1952.

Creswell, John W. Research design qualitative, quantitative, and mixed methods Approaches. (2nd edition), Thousand Oaks, London, New Delhi: Sage Publications, Inc. 2007.

David L, Morgan. Focus group as Qualitative research. port land, 1992.

Dawson, Catherin. A practical guide to research methods. United Kingdom: oxford OX5, 2007.

Daymon, Christine and Holloway Immy.Qualitative research methods in public relation and marketing communications. Taylor and Francis Library publishers, 2005.

Dorson M, Richard. (Ed), Folklore and Folk Life; An introduction, Chicago: University press, 1972.

-----."Mythology and Folklore." vol. 2.1973, http://wwwjstororg/ pp 107-126,wed May 1707:38:56 pp 107-126, 2006.

Dundes, Alan. "What is FolkloreThe Study of Folklore." New Jersey: Prentice- Hall, 1-3 1965.

-----. Intrpriting Folklore. Bilumington: Indiyana university, Press 1980.

-----. "Folklore Matters." The Folklore Scholarship of Alan Dundes and the New American Studies Perin Gürel, 2005.

Edelman Marc and Haugerud Angelique. (e.ds). The Anthropology of Development and Globalization. Blackwell: Publishing Ltd, 2005.

Ellen, R.F. (Ed) Ethnographic research A guide to general conduct. (8th printing) Oval Road, London: Academic press inc, 1995.

Entwhistele, William J. European Balladry; Oxford: Clarendon press, 1939.

Ethiopian Tourist organization. (n.d.). `Epiphany, Timkat`. in tourisim Miscellanies5. institute of Ethiopian studies, pp162-163, Addis Ababa: 1976.

Fekade, Azeze. Unheard voices Drought, Famine and God in Ethiopian Oral Poetry. Addis Ababa University Press, 1998.

-----. "The State of Oral Literature research in Ethiopia."Journal of Ethiopian studies, IES Vl. 34.1 2001.

Fetterman, David. Ethnography Applied Social Research Methods. Series Volume 17, London፡ SAGE Publications Inc, 1998.

Finnegan, Rut. Oral Literature in Africa. Nairobi: Oxford University Press, 1970.

-----. Oral Poetry its nature significance and social context. Cambridge: Cambridge University Press, 1977.

-----. Oral traditions and the Verval arts; A Guide to Research practices. London: Alan Barnard and Anthony Good Acadamic press, 1992.

Foley, J.M. The theory of Oral Composition History and Methodology. Bloomington University Press, 1988.

Geoffer, Walford, (ed). Methdological Issues and practices in Ethnography, volume 11.

Goldstein, Kenneth S. "Ridding Traditions in North Eastern Scotland." Journal of American Folklore 76:330,336. 1963.

-----. Guide for Field Workers in Folklore. Pennsyuania: Hatboro, Folklore Associates, Inc: 1964.

Gomm, Roger. Social Research Methodology A Critical Introduction. Great Britian: Cromwell Press, 2008.

Gray David. Doing Research in the Real world. New Delhi: SAGE Publication, 2004.

Gray, Ann.2003 research practice for cultural studies. New Delhi: Sage Publication, 2003.

Green, Thomas A. (Ed), Folklore an Encyclopedia of beliefs, customs, tales, music and art. California: Santa Barbara 1997.

Hammersley, Martyn, Atkinson, Paul. (3rd edition) Ethnography Principles in practice. New York: Taylor & Francis e-Library published, 2007.

Harrison, Lawrence E, Samuel P. Huntington. (Editors), Culture Matters, New York: 2000.

Holzbecher, Ekkehard. Environmental Modeling. (second edition) New York: Heidelberg, 2012.

Hooper, Antony. (Ed). culture and sustainable development in the pasfic. Australia: Asla pasfic press, 2000.

Huskinson, Lucy, (Ed). Dreaming the Myth Onwards, New directions in Jungian therapy and thought. New York: Taylor & Francis group peblish, 2008.

Inglehart, Ronald. Cultural Christian Wezel Modernization, cultural change, and democracy the human development sequence, Cambridge: Cambridge university press, 2005.

International Encyclopedia. Vol.5 (Ed) David. L sills p.497.

Islam Gazi and J. Zyphur Michael. "Rituals in Organizations: A Review and xpansion of Current Theory" DOI: 10.1177/1059601108329717, Washington: Sage Publications 2009, 34; 114.

J. Major, Andrew. "Ritual and symbolism" in the anti- infanticide campaign in early colonial Punjab, 95-108, Cambodia: Cambodia university, 1853.

Jackson, Bruce. Field Work. Urban and Chicago፡ Illinos Press, 1987.

Jarvien, C. "Limits to Functionalism and Alternative to it in Anthropology." in functionalism in the social sciences ed. Dan Martin dale; monography 5 in a series, American Acadamy of poletical and social science Phila delphia publish, 1965.

John, Tomany, et al. local and regional development. London New York: Routldge tayler francis group, 2008.

Kamwaria, Alex and Katola, Michael. "The Role of African Traditional Religion, Culture and World-View in the Context of Post War." International Journal of Humanities and Social Science, Vol. 2 No. 21; Pp 49-55, Kenya: Nairobi University, 2012.

Karbo, Tony. "Religion and social cohesion in Ethiopia." Addis Ababa, Ethiopia http://www. Academic journals. Org/IJDS, 2013.

Kay, Milton. Enviromentalism the view from anthropology. Published in the Taylor & Francis Library, 2005.

Kefyalew Merahi. `The most versa file Ethiopian scholars St. Yared and his outstanding work. ` Addis Ababa: commercial printing press, 2004.

Kerr, David. On Not "Becoming a Folklorist: Field Methodology and the Reproduction of Under development", Vol. 102, No. 1, pp. 48-61, Taylor & Francis, Ltd Published 1991. http://www.jstor.org/stable/ Accessed: 18/01/ 17:00, 2010.

Kothari, C.R. Research methodologe Methods & techniques. New Age International Ltd Published, 2004.

Kumar Sahu, Pradip. Research Methodology A Guide for Researchers in Agricultural Science, Social Science and Other Related Fields. New Delhi, Heidelberg, New York, London, India, Springer: 2013.

Kumar Yogesh. Fundamental of research metdology and statics, new age international publish, 2006.

Kyalo, Paul. "Initiation Rites and Rituals in African Cosmology." International Journal of Philosophy and Theology, School of Humanities and Social Sciences Mount, Kenya: Kenya University press, pp. 34-46, June 2013.

Lary R. Squeire. (ed). Encyclopedia of learning memory. New York: Macmillan publishing, 1992.

Last Jill. `Timket (feast Epiphany).` Ethiopian festivals sports games celebrations, occuations pilgrimages. Tourism commission, Addis Ababa: 1982.

Leach Maria. Funk and Wagnall's standard Dictionary of Folklore Mythology and Legend. 1986.

Lrrain, Jorge. Theories of development capitalism, colonialism, and dependency. Cambridge: polity press association, 1989.

Marana, Maider. Culture and development. Evolision and prospects, Bilbao, spain, 2010.

Martins, Nuno."Keywords capability approach human development." theory of justice, welfare and Measurement UNESCO, pp. 20-39. 2012.

Mathias, Mildred E. "Magic, Myth and Medicine." Vol. 48, No. 1 (Jan. - Mar., 1994), pp. 3-6, Published by: Springer on behalf of New York Botanical Garden Press, Stable URL: http: //www. jstor.org/stable/4255562. Accessed: 06/04/ 14:20, 2011.

Mccormick, and White; K.K. (eds). "Folklore an Encyclopedia of Beliefs Custms, Tales, Music and Art" 973-980, 2011.

Merkur, Dan. Psychoanalytic Approaches to Myth. Freud and the Freudians New York and London: Published by Routledge, 2005.

Milton, Kay. (Ed). Environmentalism. London and New York: 2005.

Momen, M. Understanding religion. A thematic approach. Oxford: Oxford, Publications, 1999.

Morford, Mark P.O and Lenardon, Robert J. Classical mythology. (7th ed), New York: Oxford University press, 2003.

Morgan, David L. Focus group as qualitative Research, Qualitative Research Methods Series Volume, 16, (2nd Edition), Thousand Oaks London New Delhi: Sage Publication,1996.

Mulugeta Negassa Chibsa "documentation and analysis of Ritual performance of Sera Gada among the Karrayu Oromo" Addis Ababa University, 2014.

Myrsiades, Kostas et al. "Using Information Management Systems to Study Modern Greek Folklore". Vol. 23, No. 4/5, http://www. jstor. org/stable/30204376. Accessed: 06/04/ 12:33. 2011.

Myrvold, Kristina `ritual performance and texst.` www. Ampere Publish, 2008.

Nchelle Williams "Methodology brief introduction to focus groups". 2004.

Ogunleye, Richard A. "Ritual Efficacy in Traditional African Environments Culture Adekunle," The Journal of Pan African Studies, vol.6, no. PP 209-219, 10, June Ajasin University, 2014.

Okpewho, Isidore. African Oral Literature Back Grounds Character and Continuity, Bloomington: Indian University Press, 1992.

Orign, Elliot. "Three functions of Foklore." The journal of American Folkore.67-80, 1976.

Peek, Philip M and Yankah Kwesi. (Ed). African Folklore an Encyclopedia. New York London: Rout ledge Published 2004.

Peet, Richard, Elaine Hartwick. Theories of development. New York, London: Guilford Press, 2009.

Peirano Mariza G.S. "The Anthropological analaysis of rituals". Brasil: Brasília, 2000.

Peter Bartis. Folk life and field work an introduction to field technique Washington: Congress library press, 2002.

Price S. R. F. Ritual and Power. The Roman imperial cult in Asia Minor, New York: Cambridge University Press, 1984.

Punch, Keith. Introduction to Social Research Quantitative and Qualitative Approaches. London, Thousand Oaks, New Delhi: SAGE publication, 2004.

Rappaport, Ray A. The abivious aspects of ritual in Ecology meanining and Religion. Atah state: Atah state university press, 1997.

-----. ritual and religion in the making of humanity. Cambridge University Press, 1999.

Rice, Michael and Hazel, John. Who's Who in Classical Mythology. London and New York: Taylor & Francis e-Library, publishe 2005.

Ricoeur, Paul. "Myth: Myth and History." *Encyclopedia of Religion*. Ed. Lindsay Jones.Vol 9. 2nd ed. Detroit: Macmillan Reference USA, PP. 6371-6380, 2005.

Ritchie, Jane and Lewis jane. (Eds). qualitative research practice. New Delhi: Sage publication Inc, 2010.

Rocha, Hector. "Dominant development paradigms a review and integration" Journal of market and morality, volume 16, pp 17-26, 2013.

Sabina Alkire et al. Introducing the Human Development and Capability Approach. 2016.

Sahu Pradip Kumar. Research Methodology: A Guide for Researchers in Agricultural Science, Social Science and Other Related Fields. New Delhi Heidelberg New York: Springer India, 2013.

Schilbrack Kevin. (Ed). Thinking Through Rituals Philosophical Perspectives. London New York: 2004.

Schramm, Genter and Warford Jeremy. (Eds). Environmental management and Economic Development. Baltimore and London: Johns Hopkins University Press, 1989.

Schoen Makers, Hans.The Power of Culture. Groningen university, 2012.

Schumpter, Joseph A. capitalism, socialism and democracy. London and New York: Stokholm university press, 2003.

Scribner Bob. "Religion, Society and Culture." No. 14 (, pp. 2-22, Publish stable URL: http://www. jstor.org/stable/4288428, Accessed, 30/11/2010 05:38, Oxford: Oxford University Press, 1982.

Segal, Robert A. Myth: A Very Short Introduction. New York: Oxford University Press, 2004.

Sen, Amartya. The concept of development. Volume L Edited by H. Chenery and T.N. Srinivasan, Harvard: Harvard university press, 1988.

-----."The human development paradigm operational zing ideas on capabilities". February 2003, 301 – 317, Routledge, 2003.

-----and Nussbaum, Martha. The Concept of Human Development a Comparative Study. Linkoping: Linkoping University press, 2008.

Sergew hable selasie. The church of Ethiopia a Pan aroma of history and spiritual life. Addis Ababa: The Ethiopian orthodox church united printers, 1970.

Shoemaker, George H. The Emergence of Folklore in Every Day Life. A Field Guide and Source Book, 1990.

Silverman, David. (ed). Qualitative research theory method and practice. London, thousand Oaks, New Delhi: Sage publication, 2004.

Sims, M.C and Martine Stephen. Living Folklore. an Introduction to the Study of People and their Tradition. Logan: Utah state University Press, 2005.

Smorda, Jacob Bulti. "Religion and Development in Ethiopia", Department of International Environment and Development Studies, Norwegian University of Life Science www.umb.no/noragric.no August 2012.

Tippins Deborah J. at et al, (Eds). Cultural studies Environmentalism. V.3 New York: New York university press, 2010.

Turner, Victor, Revelation and Divination in Ndembu Ritual. London: Cornell University Press, 1975

-----. The ritual process structure and anti-structure. New York, Seventh printing, U. S. A. printing press 1991.

UNICCO."Culture and development, a response to the challenges, of the future, sciences." Paris, 2009

Valisiner, Jaan. Culture and human development. London, thousand Oaks, New Delhi: Sage publication press, 2005

Van den Heever, G. Theoretical reflection on religion and identity in Africa Religion and Theology. 1−25, 2001.

Vanderstoep, Scott W, and Johnston, Deirdre. Research methods for every day life bleneding qualitative and quantitative approaches. Jossey Bas publication press, 2009.

Vaus, David de. Research design in social research. London, Thousand, New York: Sage publication inc, 2001.

Vernant, Jean Pierre. Myth and Society in Ancient Greece. (3rd printing), New York: Bogazici University press, 1996.

Walelign Emiru. "The Dynamic of religious rituals and secular ceremonies in public place of Addis Ababa (Spatial temporal and symbolic Aspects)" M.A thesis Department of Social anthropology, Addis Ababa University 2003.

Watson Jones Rachel. “The functions of ritual in social group in Behavioral and Brain Sciences,” Texas: Texas university, January, 2016.

Watts Jim. "Ritual theory and religious practice" in Bird library, 2013.

Wikipedia, the free encyclopedia "Education in Ethiopia". Jump to navigation jump to research, on 20 October on, at 18:21, 2018.

Willis, Katie. Theories and Practices of Development. London and New York: Routldge, Taylor & Francis group, 2005.

Yandell, Keith E. Philosophy of religion. London and New York: Taylor & Francis Library, 2002.

## የመረጃ ሰጭዎች ስም ዝርዝር

### 2011 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ተጠኚዎች ስም ዝርዝር በፊደል ተራ

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | አድራሻ | ጊዜ | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ | ወ | 62 | መድኀኔዓለም /ጎ[114] | 15/11/2011 | የአንድምታ መምህር |
| 2. | ልዕልና ኀይለ ስቀል | ወ | 34 | ማራኪ/ጎ | 12/12/2011 | ባህልና ቱሪዝም |
| 3. | መሠረት ሞላ | ሴ | 28 | ማራኪ/ጎ | 21/11/2011 | የቤት እመቤት |
| 4. | መ/ር ሰሎሞን ረዳ | ወ | 70 | አዘዞ/ጎ | 16/05/2011 | መሪጌትነት |
| 5. | መ/ር ዳዊት ሥራው | ወ | 38 | ዐዲስ ዘመን | 12/19/201 | መሪጌትነት |
| 6. | ሙሉ በዜ | ሴ | 23 | አይምባ/ጎ | 21/11/2011 | የቤት እመቤት |
| 7. | ስንታየሁ ሹሜ | ወ | 35 | ቀ/18/ጎ | 15/05/2011 | ታክሲ |
| 8. | ስንዱ ወርቁ | ሴ | 19 | አበራ/ጎ | 12/05/2011 | ተማና |
| 9. | በሪሁን አካላት | ወ | 78 | ሰሚው/ጎ | 12/12/2011 | አረጋዊ |
| 10. | ብርሀ እሸቱ | ወ | 35 | ላሊበላ | 11/05/11 | ቀለበት ነጋዴ |
| 11. | ቦሴ ወንድማገኝ | ሴ | 30 | ሰሚው/ጎ | 28/11/2011 | የቤት እመቤት |
| 12. | አለም ሰገድ በለጠ | ወ | 30 | ሰሚው/ጎ | 10/11/2011 | የኮሌጅ ተማሪ |
| 13. | አባ እንባቆም መሐሪ | ወ | 76 | ሠለስቱ/ጎ | 10/05/2011 | መሪጌትነት |
| 14. | አባ ገብረ ሥላሴ | ወ | 60 | ሰሚው/ጎ | 03/ 06/11 | ቤተ ክህነት |
| 15. | አወቀይ እንየው | ሴ | 27 | ማራኪ/ጎ | 21/11/2011 | የቤት እመቤት |
| 16. | አገሬ መሳፍንት | ሴ | 32 | ሰሚው/ጎ | 20/05/2011 | ነጋዴ |
| 17. | እማሆይ ጠጋ ደጀን | ሴ | 62 | አዘዞ/ጎ | 03/13/2011 | አቃቢ |
| 18. | እናና ተስፋው | ሴ | 26 | ጠዳ/ጎ | 21/11/2011 | ነጋዴ |
| 19. | ንጋቱ ችሮቱ | ወ | 32 | ቀ/18/ጎ | 17/06/11 | የመንግሥት ሠራተኛ |
| 20. | ዋለልኝ ደስታ | ወ | 34 | አዘዞ/ጎ | 20/5/2011 | ነጋዴ |
| 21. | ዘውዱ በየነ | ወ | 32 | ላሊበላ | 11/05/11 | ቀለበት ነጋዴ |
| 22. | የሽ ደሴ | ሴ | 24 | ቡልኮ/ጎ | 21/11/2011 | የኮሌጅ ተማሪ |
| 23. | የትዋለይ ሹሜ | ሴ | 24 | አራዳ/ጎ | 21/11/2011 | ኮልጅ ተማሪ |
| 24. | የዝና ተሻሜ | ሴ | 36 | አይራ/ጎ | 11/05/2011 | መምህርት |
| 25. | ደስታ አሻግሬ | ሴ | 29 | አበራ/ጎ | 21/11/2011 | መምህርት |
| 26. | ደስታው ፈንታው | ወ | 22 | አይምባ/ጎ | 11/05/2011 | አናጺ |
| 27. | ጀጃው ያለው | ወ | 39 | ሎዛ/ጎ | 28/11/2011 | ግብርና |
| 28. | ገነት ጌታሁን | ሴ | 32 | አይምባ/ጎ | 21/11/2011 | የቤት እመቤት |
| 29. | ጌትነት አመራ | ወ | 73 | ሰሚው/ጎ | 13/05/2011 | አርሶ አደር |

[114] ጎንደር ከተማ ውስጥ የሚገኙ መኾናቸውን የሚያመለክት ነው፡፡

## በ2012 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ተጠኚዎች ስም ዝርዝር በፌደል ተራ

| ተ.ቁ | ስም | ጾታ | ዕድሜ | አድራሻ | ጊዜ | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ | ወ | 62 | ሰሚው/ጎ | 19/01/12 | የደብር አስተዳዳሪ |
| 2. | ሙሔ ሰዒድ | ወ | 25 | አየር ማረፊያ/ጎ | 16/05/2012 | ነጋዴ |
| 3. | መርሻ ጌትነት | ወ | 51 | ፒያሳ/ጎ | 15/06/2012 | ግብርና |
| 4. | መ/ር ፍቃድ ቀለመወርቅ | ወ | 41 | አዘዞ/ጎ | 15/06/2012 | መሪጌትነት |
| 5. | ምንትዋብ ደጌ | ሴ | 47 | ሎዛ/ጎ | 11/05/2012 | ባለ ጠጅ ቤት |
| 6. | ሞሚና አህመዴ | ሴ | 40 | አራዳ/ጎ | 03/05/2012 | ነጋዴ |
| 7. | ሰጡ ዳርጌ | ወ | 67 | አራዳ/ጎ | 12/06/2012 | መምህር |
| 8. | ቄስ ደስታው አለሙ | ወ | 48 | በዓታ/ጎ | 15/05/2012 | ቅዳሴ |
| 9. | ተደመ ደጌ | ወ | 80 | ሳሙኤል/ጎ | 16/05/2012 | መዘምር |
| 10 | ትግሥት አባይነው | ሴ | 23 | ሳሙናበር/ጎ | 23/05/2012 | የቤት ሰራተኛ |
| 11 | ቸኮል ብዙየ | ወ | 38 | ቸቸላ/ጎ | 12/05/2012 | አዝማሪ |
| 12 | አማኑኤል ታደሰ | ወ | 26 | አዘዞ/ጎ | 16/05/12 | ባጃጅ ሹፌር |
| 13 | አስቻለው ደመላሽ | ወ | 33 | ኮሌጅ/ጎ | 16/05/2012 | ተራ አስከባሪ |
| 14 | አክሊል አሰፋ | ወ | 44 | ልደታ/ጎ | 03/06/2012 | የመንግሥት |
| 15 | አወቀ ዋጋው | ወ | 55 | ልደታ/ጎ | 03/06/2012 | ቤተ ክርስቲን ዘብ |
| 16 | አዳነች ደጀኔ | ሴ | 45 | ሎዛ/ጎ | 11/05/2012 | ባለ ሽሮ ቤት |
| 17 | እናንየ አልታሰብ | ሴ | 19 | አባጃሌ/ጎ | 11/05/12 | የቤት ሰራተኛ |
| 18 | እቴኑ መኮነን | ሴ | 40 | እልፍኝ/ጎ | 18/05/2012 | የቤት እመቤት |
| 19 | ካሳው መኳንንት | ወ | 39 | አዘዞ/ጎ | 11/05/ 2012 | ጫኝ አውራጅ |
| 20 | ወርቄ አባተ | ወ | 44 | ዞብል/ጎ | 03/05/12 | የመንግሥት |
| 21 | የሱፍ ወርቁ | ወ | 43 | አዲያ | 29/05/2012 | ሽማቃ ሰሪ |
| 22 | የልፍኝ ጣሰው | ሴ | 48 | አራዳ/ጎ | 27/04/2012 | የቤት እመቤት |
| 23 | ደርበው ድሌ | ወ | 50 | አራዳ/ጎ | 03/06/2012 | ዓለም አጫዋች |
| 24 | ደሴ እምሩ | ወ | 56 | ደምቢያ | 29/06/2012 | ሽማቃ ሰሪ |
| 25 | ደነቀው ማሩ | ወ | 20 | ዞብል/ጎ | 11/05/2012 | ተማሪ |
| 26 | ደጅጥኑ ስንቄ | ሴ | 30 | አራዳ/ጎ | 18/05/2012 | ነጋዴ |
| 27 | ደጉ አለቤ | ወ | 47 | አራዳ/ጎ | 20/04/2012 | ልብስ ሰፊ እና |
| 28 | ገዳሙ ዓለሙ | ወ | 40 | ጎንደሮች/ጎ | 03/06/2012 | አናጺ |
| 29 | ጠጋነው ደምሴ | ወ | 38 | እልፍኝ/ጎ | 25/05/2012 | ግምበኛ |
| 30 | ፀሐይነሽ ካሳ | ሴ | 60 | አዘዞ/ጎ | 12/05/2012 | ባለ ጠጅ ቤት |

## 2013 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ተጠኚዎች ስም ዝርዝር በፊደል ተራ

| ተ.ቁ | ስም | ጾ | ዕድ | አድራሻ | ጊዜ | ሥራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ሄለን አወቀ | ሴ | 12 | ፒያሳ/ጎ | 11/05/2013 | ተማሪ |
| 2. | ህይወት ገብሩ | ሴ | 43 | ደምቢያ | 12/05/2013 | የቤት እመቤት |
| 3. | መልሽው ጌጡ | ሴ | 40 | ሎዛ/ጎ | 12/05/2013 | የቤት እመቤት |
| 4. | መ/ር ሀረገወይን ተክሌ | ወ | 28 | ማስከኝት | 11/05/2013 | መሪጌታ |
| 5. | መ/ር መሐሪ ጥሩር | ወ | 47 | ጠዳ/ጎ | 15/05/2013 | መሪጌትነት |
| 6. | መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ | ወ | 64 | አዘዞ/ጎ | 12/05/2013 | መከላከያ (ጡረታ) |
| 7. | መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ | ወ | 60 | አዘዞ/ጎ | 12/05/2013 | መከላከያ (ጡረታ) |
| 8. | ምስጋን ሞላ | ወ | 19 | ማስከኝት | 11/05/2013 | ተማሪ |
| 9. | ሲሳይ ቢተው | ወ | 41 | ጫሂት | 12/05/2013 | አርሶ አደር |
| 10 | ስንታየሁ ሙጨ | ወ | 36 | አራዳ/ጎ | 12/05/2013 | ነጋዴ |
| 11 | ስንዱ ወርቁ | ሴ | 60 | አምባ/ጊ | 11/05/2013 | የቤት እመቤት |
| 12 | ቀለብ ሰጠኝ | ሴ | 33 | ልደታ/ጎ | 12/05/2013 | የቤት እመቤት |
| 13 | ትደነቅ ሙጨ | ሴ | 31 | ቡልኮ/ጎ | 12/05/2013 | የቤት እመቤት |
| 14 | ናርዶስ ንጉሤ | ሴ | 10 | ሎዛ/ጎ | 12/05/2013 | ተማሪ |
| 15 | ንጋቱ ዘውዱ | ወ | 72 | አዘዞ/ጎ | 12/05/2013 | አረጋዊ |
| 16 | አራጌ ጠጋው | ወ | 88 | አዘዞ/ጎ | 12/05/2013 | አረጋዊ |
| 17 | አስረስ ብርሃን | ሴ | 36 | አዘዞ/ጎ | 12/05/2013 | የቤት እመቤት |
| 18 | አስናቀው አበበ | ወ | 75 | አዘዞ/ጎ | 13/05/2013 | አረጋዊ |
| 19 | አበራሽ ነጋ | ሴ | 46 | አዘዞ/ጎ | 12/05/2013 | የቤት እመቤት |
| 20 | አብነት ሰማ | ሴ | 34 | ሳሙኤል/ጎ | 12/05/2013 | መምህርት |
| 21 | አበባ እንደሻው | ሴ | 60 | ሳሙኤል/ጎ | 13/05/2013 | የቤት እመቤት |
| 22 | አየለ ቴዎድሮስ | ወ | 26 | ኮሌጅ/ጎ | 10/05/2013 | የንዋየ ቅድሳት ነጋዴ |
| 23 | አገሬ መስፍን | ሴ | 40 | ሳሚናበር/ጎ | 12/05/2013 | የቤት እመቤት |
| 24 | እማሆይ ካሳነሽ አበራ | ሴ | 68 | አይምባ/ጎ | 13/05/2013 | እማሆይ |
| 25 | እማሆይ ካባ ይመር | ሴ | 70 | ወገራ | 11/05/2013 | እማሆይ |
| 26 | እማዋይ ደሴ | ሴ | 61 | ዐዲስ አበባ | 10/05/2013 | ጅንአድ ውስጥ |
| 27 | ደመቁ ደመወዝ | ሴ | 15 | ቀ/ዐሥራ ስምንት/ጎ | 11/05/2013 | ተማሪ |
| 28 | ደመወዜ ዘለለው | ሴ | 45 | አርባያ | 12/05/2013 | የቤት እመቤት |
| 29 | ዘውዱ ይርጋ | ወ | 31 | ሽበልበረንታ | 12/05/2013 | ነጋዴ |
| 30 | ደረጀ ስመኝ | ወ | 34 | አራዳ/ጎ | 12/05/2013 | ነጋዴ |
| 31 | ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን | ወ | 39 | ቡልኮ/ጎ | 12/05/2013 | ቅርጻ ቅርጽ ሠሪ |
| 32 | የኛነሽ መለሰ | ሴ | 35 | አዘዞ/ጎ | 12/05/2013 | የመንግሥት ሠራተኛ |
| 33 | ይታያል ደመወዝ | ወ | 32 | ደብረወርቅ | 12/05/2013 | ነጋዴ |
| 34 | ገዛኸኝ ተክሉ | ወ | 67 | አዘዞ/ጎ | 13/05/2013 | አረጋዊ |
| 35 | ጋሻው ሙጨየ | ወ | 40 | አራዳ/ጎ | 11/05/2013 | አዝማሪነት |

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ፦ የጥናቱ መነሻ ጥያቄዎች

### 1.1. የጥናቱ መነሻ ጥያቄዎች መንደርደሪያ

ስሜ ጋሻው አሻግሬ እባላለሁ። በአዲስ አበባ ዩኒበርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ፎክሎርን በሦስተኛ ድግሪ በመማር ላይ እገኛለሁ። ለዚህ ትምህርትም የመመረቂያ ጽሑፍ "የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ አንድምታ እና ፋይዳዎቹ በጎንደር" በሚል ርእስ ላይ ጥናት እያደረግኩ እገኛለሁ።

የጥናቱ ዓላማ የጥምቀት ክብረ በዓል ሥርዓተ ክዋኔ አንድምታ እና ፋይዳዎቹን መመርመርና ማሳየት ነው። በመሆኑም ጥናቱ ከግብ ይደርስ ዘንደ የጥምቀት ክብረ በዓል ላይ በመመሥረት በማቀርባቸው ጥያቄዎችና ጥያቄዎቹን ለመመለስ ፈቃደኛ ስለሆናችሁ መጀመሪያ በእግዚአብሔር ስም ምስጋና አቀርባለሁ። እንደዚሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ ቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ስም ምስጋናየን አቀርባለሁ።

በዚህ ቃለ መጠይቅ ላይ የምትሰጡኝ መረጃ እንደ ምሰሶ፣ ማገርና ጨፈቃ በመሆን ጥናቱ የሚገነባበት ዋና አካል ነው። የአንድ ጥናት እውነተኛነትና ውጤታማነት በመረጃው እውነተኛነት ላይ የሚገነባ ነው። በመሆኑም የምትሰጡኝ መረጃ ከተውሳክም ሆነ ከጎጸጽ የጸዳ እንደሚሆን ባለ ሙሉ ተስፋ ነኝ። በዚህ ቃለ መጠይቅ የምትሰጡኝ መረጃ ከጥናቱ ውጭ ለማንናቸውም ጉዳይ ተግባራዊ አይደረግም። ለፎቶግራፍና ለመቅረጸ ድምጽ ፈቃዳችሁን እየጠየቅኩኝ ይህም በጥናቱ ውስጥ አባሪ ሆኖ ይቀርባል።

በእናንተ ፈቃድ የምትሰጡኝን ስም፣ ዕድሜ፣ ስራና አድራሻ ለጥናቱ በአባሪ መልክ እጠቀመዋለሁ። ከዚህ ባለፈ በስውር፣ በድብቅና መረጃ ሰጭዎችንም ሆነ ተጠኚዎችን የሚያስከፋ ምንም ነገር በዚህ ጥናት ውስጥ አይሰራም። አሁንም ደግሜ ምስጋናየን እያቀረብኩ ጥያቄዎቹን እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

## 1.2. ለቃለ መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት የቀረቡ የጥናቱ መነሻ ጥያቄዎች[115]

1.2.1. የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ምን አንድምታ አለው? እንዴት ይከበራል? አክባሪዎቹስ እነማን ናቸው? ምን ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ የቅርስ ጥበቃ፣ ሰባዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል? በጥምቀት ወቅት ምን ዐይነት የቱሪስት እንቅስቃሴ አለ? ማኅበረሰቡ ጥምቀትን እንዴት ይረዳዋል? ያከብረዋል? ምን ምን ጠቀሜታዎችን ያገኝበታል?

1.2.2. የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል መገለጫው ምንድን ነው? ምን ሃይማኖታዊ፣ ታሪካዊና፣ ባህላዊ እሴቶች አሉት?

1.2.3. የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሰባዊ አንድምታ ምንድን ነው? በዓሉ በሥነ ምግባር፣ በሰባዊ፣ በማህበራዊ፣ በእርቀ ሰላም ያለው ፋይዳ ይኖር ይሆን? ካላ እንዴት ይገለጻል? በክብረ በዓሉ የሚሳተፉት እንማን ናቸው? በዚህ በዓል በመሳተፋቸው የሚያገኙት ሃይማኖታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባህላዊና ሰዋዊ ጠቀሜታዎች ይኖራሉ ወይ? ካሉ በምን መልኩ ይገለጻል?

1.2.4. የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ላይ የሚነገሩ ትረካዎች፣ ዝማሬዎች፣ የሚነገሩትን ሚታዊ ታሪኮች፣ቃል ግጥሞች ምን፣ ምን መገለጫዎች አሏቸው? የክብረ በዓሉ ጊዜ፣ ቦታ፣ ሥርዓት፣ ልማድ ምን አንድምታ አላቸው? ያላቸው የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ እና የሰባዊ ፋይዳዎች እና አስተዋጽኦ ምን ይመስላል?

1.2.5. የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ክዋኔ ላይ የሚገኙ ንዋዬ ቅድሳትና፣ ቁሳዊ ባህሎች ምን፣ ምን ናቸው? ምን ውክልናና ተምሳሌት አሏቸው?

1.2.6. በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የያሬዳዊ ዜማዎች ምን አንድምታ አላቸው? እንደዚሁም በሊቃውንት፣ በካህናት፣ በሰንበት ዘማሪዎች፣ በአዛውንት፣ በእናቶች፣ በአባቶች፣ በወጣቶች፣ በሴቶች፣ በልጃ ገረዶች፣ በሕጻናት፣በ"አሸከሮች" እንዴት ይተገበራል (ይከወናል) ተሳትፏቸውስ ምን ይመስላል? በተሳትፏቸው የሚያገኙት ሥጋዊና መንፈሳዊ በረከቶች ካሉ ቢያብራሩልኝ?

[115] ጥያቄዎቹ በቁጥር ይነሱ እንጅ በውስጣቸው በርካታ ዝርዝር ጥያቄዎችን የያዙ ናቸው፡፡ ጥያቄዎቹ ለቃለ መጠይቁ እና ለቡድን ውይይቱ ያሳተፉ እና የጥናቱን መሰረታዊ መረጃ ለማግኘት ያስቻሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች እንደመነሻ ይቀመጡ እንጅ አወዱን እና መረጃ ሰጭዎቹን ታሳቢ ያደረጉ ጥያቄዎች በመረጃ ስብሰባው ወቅት ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

## የመረጃ ሰጪዎች ቃለ መጠይቅ በፊደል ቅደም ተከተል

***ቃለ መጠይቅ አንድ (ሊቀ ሊቃውንት ዕዝራ ሐዲስ፣ 15/11/2011 ቃ.መ)፡-*** በህገ ኦሪት እግዚአብሔር የወደዳትና መሰከረላት ስለኾነ ኢትዮጵያ ይከበራል በጥንታዊዉና በህገ ወንጌሉ እንደተጻፈ ታቦታቱ እየወረዱ ድንኳን እየተተከለ ወንዙ እየተባረከ ሕዝበ ክርስቲያኑ በዓሉን እያከበረ ይገኛል፡፡ ሥርዐቱ ኹሉም ይከበራል፡፡ ታቦታት ይወርዳሉ ለምን ይወርዳሉ ቢባል በመጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነዌ ምዕራፍ ፫ እንደተጻፈው ኢያሱ እስራኤልን ይዞ ወደ ምድረ ርስት እየሩሳሌም ሲኼድ ሲደርሱ የዮርዳኖስ ወንዝ ተከፍሎላቸው በደረቅ ታቦታቱን ለተሸከሙ ካህናት ጽላቱን አስይዞ ነበር፡፡ ለማየ ዮርዳኖስ ትንቢት ተነግሯል፡፡ "ምንተ ኮንኪ ባሕር ዘጎየኪ ወአንተኒ ዮርዳኖስ ዘገባከ ድኅሬከ" ርዳኖስ ወደ ኋላ ተመለስክ ለምንድን ነው ለምን ሸሸህ፡፡ መጀመሪያ በኢያሱ ዘመን ታቦቱ ወደ ወንዝ ወርዶ ዮርዳኖስ ሲሻገር ወንዙ ታቦቱን አክብሮ እንደተከፈለላቸውና በደረቀቅ እንደተሸገሩ የሚያጠይቅ ነው፡፡ በኂላ ግን መድኀኔዓለም ክርስቶስ ከድንግል ማርያም በድንግልና ተጸንሶ በድንግልና ተወልዶ ያለ ዘርዓ ብሲእ ያለ ሩካቤ ያለ አባት ከድንግል ማርያም በኀቱም ድንግልና ተጸንሶ በኀቱም ድንግልና ተወልዶ በ፴ ዓመቱ በዮርዳኖስ እንደሚጠመቅና ታቦቱ የወረደባት ታቦቱ የተሻገረባት ለአማናዊ ለእውነተኛው መድኀኔዓለም ክርስቶስ እንዲኾ መጠመቂያ የመጠመቂያ ወንዝ እንደምትኾን ትንቢት አስቀድሞ እንደተናገረ መድኀኔዓለም ክርስቶስ በዮርዳኖስ ተጠምቋል፡፡

ዛሬ ቤተ ክርስቲያናችን ታቦታቱን ወደ ወንዝ ይዛ የምትወርደው መድኀኔዓለም ወንዝ ወርዶ እንደተጠመቀ ዛሬም ጥምቀት በዓል ሲከበር ጽላቱ ይወርዳል፡፡ ኹለት ነገሮች አሉ አንደኛ በዘመነ ኢያሱ የነበረው ኢያሱ ታቦቱን ጽላቱ ዮርዳኖስን ሲሻገር የተደረገ ታምር ስላለ ነው፡፡ ኹለተኛው ደግሞ ያለም ቤዛ ያለም መድኀኒት ኢየሱስ ክርስተስ ዮርዳኖስ ወንዝ ስለተጠመቀ ከወንዝ ወርደን ከወንዝ አድረን በዓሉን የምናከብረው በዚህ መጽሐፍ ቅዱስ በተጻፈው በኹለቱ ነገሮች ነው፡፡ በኦሪትና በህገ ዐዲስ በኦሪት በእነ ኢያሱ በህገ ዐዲስ በወንጌል ራሱ ባለቤቱ መድኀኔዓለም ክርስቶስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጥቶ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ ተጠምቆ አብ የምወደው ልጀ ይህ ነው ብሎ ሲመሰክር መንፈስ ቅዱስ በርዕግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ሲቀመጥ የሥላሴ አንድነት ሦስትነት የታየበት በዓል ነውና ኢትዮጵ ታቦቱንም ይዛ የምትወርደው ለዚህ ነው፡፡ ጥምቀቱን የምታከብረው ለዚህ ነው፡፡

እና ኢትዮጵያ ይከበራል ጎንደር በተለይ አከባበሩ እንደመላው ኢትዮጵያ ሲኾን የቦታው አቀማመጥና የባሕረ ጥምቀቱ በቋሚነት ከአንድ ቦታ ስለሚወርድ እንግዲህ ጎንደርን የቆረቆሩ ዐፄ ፋሲል ናቸው፡፡ ዐፄ ፋሲል ሰባት አብያተ ክርስቲያናትን ሠርተዋል፡፡ ሰምንተኛ ጥምቀተ ባሕሩን ታቦታቱ ወርደው የሚያድሩበትን በቅዱስ ፋሲለደስ ስም ሠርተው ፎቅና ምድር አድርገው ሠርተው ማሕሌቱ የሚቆምበት አድርገው ሠርተውታል፡፡ የሠሯቸው ቤተ ክርስቲያን

1. ፊት አቦ
2. ፊት ሚካኤል
3. አደባባይ ኢየሱስ
4. ግምጃቤት ማርያም
5. እልፍኝ ጊዮርጊስ
6. መንበረ መንግሥት መድኀኔዓለም
7. ደብረ ምሕረት አቡን ቤት ቅዱስ ገብርኤል ናቸው፡፡

ከዚህ በኋላ የመጨረሻው ማንኪት ከሚባለው ቦታ ላይ ለጥምቀተ ባሕር መከበሪያና ስምንተኛው ቤተ መቅደስ እሱ ነው፡፡

ፎቅና ምድር ነው ግቢው ሰፊ ነው፡፡ አጸዶች እስካሁን ድረስ አሉ፡፡ ሰፊ ብዙ ሕዝብ የሚስተናግድ ቱሪስቶችንም የሚያስተናግድ ቅጥር ነው ያለው፡፡ ቤተ መቅደሱ ቅኔ ማሕሌት አለው፤ መቅደስ አለው፤ ማሕሌቱ ከዚያው ይቆማል፡፡ ታቦታቱ ከዚያው ያድራሉ፡፡ ከታች ባሕር አለ ባሕሩ ውሐ ይሞላል፡፡ አሐዱ ተብሎ ከተባረከ በኋላ ሕዝቡ የበረከቱ ተሳታፊ ይኾናሉ፡፡ የሚችል ይዋኛል፡፡

ቱሪስቶች በጣም ደስ ይላቸዋል፡፡ ‹‹ወናሁ መጽአ ቃል እምደመና ዘይብል ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር›› ከሰማይ እንዲህ የሚል ቃል መጣ የምወደው ልጄ ይህ ነው››፡፡ ተብሎ ሲዘመር ከዚያ ላይ ለተገኘ ሰው ማንኪት ከሚባለው ቦታ ከጥምቀተ ባሕሩ ተገኝቶ ለሚያከብር ሰው ውነትም ከሰማይ ቃል እንደመጣና መንፈስ ቅዱስ በእርግብ አምሳል እንደወረደ ይታያል፡፡ ቱሪስቶቹ ፈረንጆቹ በተለይ በእውነት አእምሮአቸውን መቆጣጠር እስከሚያንሳቸው ድረስ ይደሰታሉ፡፡ ልዩ ነው ዛፉ፣ ከዛፉ ብዛት አእዋፉ ደግሞ ከዛፉ ኹነው ወዲያ ወዲህ ሲሉ ርእግቦቹ በእውነት መንፈስ ቅዱስ በርእግብ አምሳል ሲወርድ በዮርዳኖስ ዮሐንስ እንዳየው የሊቃውንቱ መጽአ ቃል እምውስተ ደመና ዘይብል እያሉ ሲዘምሩ

ብትክክል በተወለደ በ፴ ዓመቱ ፈለገ ዮርዳኖስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠመቅ ዮሐንስ ለምስክርነት ያየውን የጥምቀት በዓል የሚገልጽ ነው። የጎንደር በዓል ለየት የሚያደርገው የቦታው ልዩነት ነው። በእውነቱ የጎንደር ጥምቀት ከዚህ ከዐፄ ፋሲል ይጀምርና ሊቃውንቱ ሀዲጎ ተስዓ ወተስዓተ ነገደ የሚለውን ዝማሬ በቅዱስ ያሬድ የተዘጋጀውን ባሕሩ ከተባረከ በኋላ ሕዝቡ ከተመለሰ በኋላ ጥምቀተ ባሕሩ ቤተ መቅደስ ፊት ለፊት ታቦታቱ ተሰልፈው ጳጳሳቱ አንድ ላይ ኹነው ሊቃውንቱ ጥንግ ድርብ፣ ካባውን፣ ሸማውን፣ ሱፍ ካባውን፣ የብር መቋሚያ፣ የብር ጸናጽል ይዘው ሻሽ ጠምጥመው ሲያስረግጡ ሀዲጎ ተስዓ ሲሉ መላእክት ከሰማይ ወርደው በቤተ ልሔም ከኖሎት ጋራ "ሰብሐት ለእግዚአብሔር በሰማያት ወሰላም በምድር" ብለው ያቀረቡትን ዝማሬ ይመስላል። እና ያን ጊዜ ልዩ፣ ልዩ መንፈሳዊ ስሜትን ከእግዚአብሔር ጋር እንዲገናኝ ያደርጋል። ሰው ይለወጣል ማለት ይቻላል። በአሉን ለማክበር የመጣው ሰው ተለውጦ ሀዘንተኛም ቢሆን ሀዘኑን ረስቶ የደስታ ሰው ይኾናል።

ሙሉ በሙሉ ሰው መንፈሳዊ ይኾናል። ሥጋዊው ኹሉ ተለውጦ መንፈሳዊ ይኾናል። እና የጥምቀት በዓል በጎንደር የሚባለው ከቦታው ጋር ተያይዞ ከሊቃውንቱ ጋር ተያይዞ ቃለ እግዚአብሔሩም ያው ጎንደር የሊቃውንት አገር በመኾኗ ከዚያ ጋራ ተያይዞ ለየት ያደርገዋል። ይህ ሥርዓት እስካሁን ድረስ አልተቋረጠም። በዓሉም በየ ዓመቱ ዐዲስ እየኾነ ነው የሚታየው። ለውጡ የመጨመር ማለት የሕዝቡ" ብዛት፣ የሊቃውንቱ ብዛት፣ ይኽ፣ ይኽ ለውጥ ኾኖ በየ ዓመቱ ዐዲስ በዓል፣ ዐዲስ በዓል ኆኖ ይታያል። የቱሪስቱ መብዛት መጨመር ዐዲስ ኾኖ ከነበረው ሳይቀንስ ከነበረው ላይ በሕዝብ ብዛትና ሊቃውንት ብዛት እየጨመረ የሚታይ የሚያሳይ ነው። እንዲያውም ጎንደርን በጥምቀት እንይ" ተብሎ "ኢትዮጵያንም በጎንደር" ተብሎ የወጣ የበዓል መርሐ ግብር ነበረ። እንግዲህ የሊቃውንቱን አቀራረብና የሕዝቡን ብዛት አለባበሱን በተመለከተ የሊቃውንቱ አለባበስ እንዳለ ኾኖ የምእመኑ አለባበስ ወንዶቹ አዛውንቶቹ ነጭ ሱሪውን እጀ ጠባብ ሻሹ ነጭ እጀ ጠባቡ ነጭ፣ ጭራቸው ነጭ፣ ጋቢው ነጭ ኹለንተናቸው ነጭ ይለብሳሉ። እናቶቻችን እና እኅቶቻችንም እንዲሁ የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ አለ። ወደ ፲፫ መስቀል ያለው። የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ ፲፫ ቀሚስ አለው። በቀኝና በግራ እጅጌ ላይ በኋላ በፊት እና ሲቆጠር ፲፫ ነው ፲፫ቱ የሕማማተ መስቀሉ ምሳሌ ነው። ልብሱ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ በተሰቀለ ጊዜ መከራው ብዙ ሲኾን በተለይ ግን ፲፫ቱ ሕማማተ መስቀል ይነገራሉና በዚያ ልክ ነው የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ መስቀሉ ፲፫ የኾነበት አምሳል ነው። ጠላፊዎቹም ራሱ ይህን ምስጢር የተረዱ ናቸው ማለት ነው። ለባሾቹ ደግሞ ይህን

ሲያደርጉ ጌታችን በወንጌል ሲያስተምር በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፲ ላይ "ዘኢጸረ መስቀለ ሞትየ ኢይጸመደኒ" "መስቀሌን ተሸክሞ ያልተከተለኝ እኔን ሊያገለግል አይገባም" ብሎ አስተምሯልና ጥልፍ ቀሚስ ለብሰው የሚከተሉትም የወንጌልና የመጽሐፍ ቅዱስ ፈጻሚዎች ናቸው ማለት ነው፡፡ እና ሁሉም በምስጢር የተያዘ ነው፡፡ በዓሉ በዚህ መልኩ ይከበራል፡፡

እንግዳ ተቀባይነቱ ከዘመን ወደ ዘመን እየተሸጋገረ አባቶቻችን እንግዳ መቀበልን በተለይ በጥምቀት በዓል ጊዜ ከልማትና ከፍቅር ከአንድነት በትርጉም በተግባር እሚያሳዩበት በዓል ነው፡፡ ስለዚህ ቱሪስቶቹ ፈረንጆቹ ማለት ነው ወንዶችም ሴቶችም የባህል ልብስ ይለብሳሉ በተለይ ሴቶቹ ፈረንጆች በእንግድነት ኹሉም ይቀበላቸዋልና እነሱ እንደገና ባለቤት ኹነው የኢትዮጵያ እንግዳ ተቀባይ ኹነው እናያቸዋለን፡፡ ባህሉን ማለቴ ነው፡፡ የአንድ አገር ባህል ሲወደድ አለባበሱም፣ አነጋገሩም፣ አካኼዱም፣ ከተወደደ አንዲት ሀገር አገሯ ላይ እንግዳ ተቀባይ ስትኾን  እንደገና ደግሞ ሌሎቹ እሷን እንግድነት ይቀበሏታል፡፡ እና እሚመጡት ፈረንጆች ሴቶቹ ጥልፍ ቀሚሱን ለብሰው የጎንደርን መቀነቱን ታጥቀው ትፍትፍ መቀነት አለ ያን ይታጠቃሉ፡፡ የራስ ሻሻቸው ነጭ ቀይ ቢጫ አረንጓዴ ያለው ነው፡፡ እሚለብሱት ነጠላቸው ከቀሚሱ ጋራ አብሮ የተሠራ ነው፡፡ ያነን ለብሰው ሲታዩ የኢትዮጵያን ባህል ሙሉ በሙሉ እነሱ እንደባለቤት ኹነው በእንግድነት ሲያስተናግዱት ስናይ በጣም በጣም ይገርመናል፡፡ እንዳው እሚገርመው ነገር ከአበሻዎቹ ይልቅ ፈረንጆቹ ይህን የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ ሲለብሱ በጣም ነው የሚያምርባቸው፡፡ እና ይህን ሁሉ የሚያሳይ የጥምቀት በዓል ስለኾነ እንግዲህ እነዚህ ኹሉ ቱሪስቶች ይህን ልብስ ሲገዙ ሀገሪቱ ለልማት ገቢ እያስገኘች ነው ማለት ነው፡፡ ወደው ነው ልብሱን የሚገዙት ተገደው አይደለም፡፡ ኹለንተናቸው፡፡ ጭራውን ይገዛሉ ይይዛሉ፡፡ ወንዶቹ መቋሚያውን በትሩን ይገዛሉ፡፡

ሴቶቹ አገልግሉን ይገዛሉ ያዝላሉ፡፡ ቅቤቅል ይይዛሉ፡፡ የምን ተምሳሌት ነው?፡- አገልግል የጥንቱ ኢትዮጵያ ባህል ነው፡፡ አገልግል ሙሽራ ስትዳር ቅቤቅል፣ ሙዳይ አገልግል፣ ወስፌ፣ መርፌ፣ ይህን ሁሉ ይዛ ነው የምትሄድ ወደ ባሏ፡፡ የሙሽሪት መለያ ነው፡፡ እና የጥምቀት በዓል ሲከበር ይህን ወጣቶች ሴቶች ይዘው ነው የሚያከብሩት፡፡ ሙዳይ ይዘው አገልግል አዝለው ቅቤ ቅል ይዘው በጥምቀቱ ይታያሉ፡፡ እና ፈረንጆቹ ይህን ኹሉ ሙሉ በሙሉ ደስ ስለሚላቸው በተለይ ሴቶቹ አገልግሉን ያዝላሉ የቅቤ ቅሉን ይይዛሉ ከአለባበሱ ጋር አብሮ ስለሚኼድ ማለት ነው፡፡ እና ይህን እያንዳንዱ ይገዛሉ፡፡ ይህ ኹሉ ገቢ ነው የልማት ምንጭ ነው፡፡ የጥምቀት በዓል በየ ዓመቱ ሲመጣ እየጨመረ ነው እንጅ እየቀነሰ

አይኼድም፡፡ ቱሪስቶችን በተለይ የሚስብ ነው፡፡ የሀገሪቱን ሰውም ቱሪስት አድርጎታል ማለት ነው፡፡ ጥምቀትን በጎንደር እየተባለ ከተነገረበት ጊዜ ጀምሮ በዐዲስ አበባ ብዙ ሰዎች መጥተው ጎንደር ነው የሚያከብሩት ጥምቀትን፡፡ ባለፈው ዓመት ቀጥታ ከአሜሪካን እንኳን ፲፰ አውሮፕላን ቀጥታ ከአሜሪካን ተነስቶ ጎንደር አጼ ቴዎድሮስ አየር ማረፊያ ቀጥታ መጥቶ አርፏል፡፡ ብዙ በብዘ ሺሕ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ከአሜሪካን ከተለያየ ቦታ መጥተው አክብረውታል እያከበሩት ነውና ጎንደር ለኢትዮጵያውያንም ጭምር የትውልድ ሀገር ብትኾንም ባህልና ሥርዓቱ እየሳባቸው እየተሳቡበት የሚገኝ ሃይማኖታዊ በዓል ነው ማለት ነው፡፡

ከማኅበረሰባዊ ግንኙነት አንጻር ማኅበረሰቡ ደስ እያለው በጥምቀት በዓል ወጣቶቹ ወንዶቹ ጥንታውያን አለባበስ በመልበስ አብረው በአንድ ላይ ሆ በማለት ከሊቃውንቱ በኋላ ሥርዓት ባለው መልኩ የሰንበት ትምህርት ቤት ዘማርያን እየዘመሩ ከእነሱ በኋላ ኾነው ደግሞ ወጣቶቹ ሆ እያሉ ለጥምቀት በዓል የሚገባውን ሆታ ማለት ነው፡፡ ሴቶች እልል እያሉ ከጥምቀተ ባሕር አንስቶ እስከ መስቀል አደባባይ ወይም እስከ ዐፄ ፋሲል ቤተ መንግሥት ድረስ ታቦታቱ ሲወርዱም ሲመለሱም ያለው የህዝብ ብዛትና ሆታው የእልልታው ድምቀት ሕዝቡን አንድ አድርጎ ገፋኸኝ ገፋሸኝ አይባባልም፡፡ የፍቅር በዓል ነው፡፡ እንዳውም ፍቅር የሚገዛበት በዓል ነው፡፡ ተደጋግፎ አንዱ ቢገፋው እንኳን ስቆ ተሳስቆ ነው እንጂ በፍቅር የሚለያይ መጣላት የለም፡፡ ጠብን በጥምቀት በዓል ወደ ፍቅር እሚለወጥበት ተለውጦ የምናይበት በዓል ነው፡፡ የጥምቀት በዓል ኹሉም በመሳቅ እንዳውም የሚገርመው ነገር እነዚህ ፈረንጆቹ ቋንቋ እማያውቁት እንኳን፡፡ አብረው ከእስክስታው እየገቡ አብረው ይዘፍናሉ፡፡ ወንዶችም ከሆታው አብረው ይጨፍራሉ፡፡ በስሜት ቋንቋውን ሳያውቁት ከሚያውቁት ጋራ እንደሚያውቁት ሁነው አብረው ሲታዩ መንፈስ ቅዱስ ሚስጥሩንና ቋንቋውን እንደገለጸላቸው በእውነት ያሳያል፡፡ እና የፍቅር በዓል መሆኑ የሚታወቀው ለዚህ ነው፡፡ እንኳን ቋንቋ የሚያውቁት ኢትዮጵያውያን በቋንቋ እሚስማሙ ይቅርና በቋንቋ የማይገናኙ ቱሪስቶች ስቀው ተሳስቀው አብረው ካበሻው ጋራ እስክስታ ይገባሉ ፈረንጆቹ፡፡ እና በማየት ብቻ አብረው መስለው ያከብሩታል፡፡

የጎንደር ጥምቀት ታዳሚ አለባበሱ እንዴት ነው?፦ ቀይ፣ ብጫ፣ አረንጓዴ በአንድ ላይ ሲለበስ የኢትዮጵያ ባንዲራ ነው፡፡ አራት ዘፍጥረት ምዕራፍ ዘጠኝ ላይ እግዚአብሔር አምላክ ኖህን ዳግመኛ ዓለምን በንፍር ውሐ እንዳያጠፋው ‹‹እሰይም ቀስትየ በውስተ ደመና›› ብሎ በደመና ላይ ምልክት አሳያለሁ ቀይ፣ ብጫ አረንጓዴ ብሎ ለኖህ የሰጠው

ቃል ኪዳን ነውና የኢትዮጵያ ባንዲራ የኖህ ቀስተ ደመና ነው። በአንድ ላይ ሲለበስ ቀይ፣ ቢጫ አረንጓዴ ይባላል። በተናጠል ቀዩ ሲለበስ ጃኖ ይባላል። በየብቻ ሲለበስ ለየራሱ ሁሉም ሸማ ይባላል። አረንጓዴ፣ ጃኖ ለብቻ፣ ቀይ ጃኖ ለብቻ፣ ብጫው ጃኖ ለራሱ ይኾንና ስሙ ጃኖ ይባላል። በአንድ ላይ ሦስቱ ሲገናኙ የኢትዮጵያ ባንዲራ ይሆናል። ከጎንደር ጋራ የተለየ ትርጉም ይኖረው ይሆን?፦ ቀይ፣ብጫ፣ አረንጓዴ፣ ነጭ የ0ራቱ የሥጋ ባህርያት ምሳሌ ናቸው። አንዱ ነፋስ፣ እሳት፣ ውሃ፣ መሬት ነው። ቀዩ የሳት ምሳሌ ነው። የሰው ኀይሉ በእሳት ነው። እና የኀይል ምሳሌ ነው። እነ 0ዔ ቴዎድሮስ ኀያላን የኀይል መገለጫ ነው።

እነ 0ዔ ቴዎድሮስ ለብሰው የሚታዩት የሚጠመጥሙት ጃኖ ነው። ከአራቱ ባህርያት አንዱና ሃይለኛው እሳት ነው እሳት ደግሞ ሲያዩት ቀይ ነው። እና ቀዩ የእሳት ምሳሌ የጀግንነት፣ የኀይል ምሳሌ ስለኾነ እሱን ይለብሱታል። ብጫው የልምላሜ የመሬት ምሳሌ ነው። ነጩ የውሐ ምሳሌ ነው። እንደገና ወደ መንፈሳዊው ስንገባ ደግሞ ጌታችን መዳንኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ለነፍሳችን ድኅነት እንዲኾን ተሰጥቶናል። ሥጋውን ሰጥቶናል፣ ደሙን ሰጥቶናል። ቀዩ የደሙ ምሳሌ ነው። የክርስቶስ በቀራንዮ አደባባይ ያፈሰሰውን ደሙን ‹‹ዘበልአ ሥጋየ ወሰትየ ደምየ ቦ ሕይወት ዘለ0ለም›› ያለውን (ዮሐ፣ ምዕ፣፮፣፶፯)። ነጭ የጥምቀት ምሳሌ ነው ይህ ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ ለሥጋችንም ለነፍሳችንም ምልክት ነው። በዚህ መልኩ ነው በዓሉ ሲከበር ቀይ፣ ቢጫ አረንጓዴ የሚለበሰው። የጥምቀት ነጭ ልብስ ነው አብዛኛው የሚለብስ ነጭ ልብስ ብቻስ ለምን ተለበሰ ቢባል ቅድም እንዳልኩት ነጩ የውሐ የጥምቀት ምሳሌ ነው ብያለሁ።

ሀዲጎ ተስዓ ሲል ውነትም ጥምቀት ለሰው ልጅ ያዳላና ለሰው ልጆች ያለው መስተጋብር

አወ እሱ በወንጌል መድኀኔዓለም ክርስቶስ ሲያስተምር ከዕለታት አንድ ቀን ‹‹ምንተ ትብሉ›› ምን ትላላችሁ "ለእመቦ ብእሲ ዘቦቱ ሚት አባግዕ" መቶ በጎች አንድ ሰው ቢኖረው "ለእመ ተገድፈቶ አሐቲ እምኔሆን" ከመቶው አንድ በግ ቢጠፋበት "አኮኑ ይሀድግ ተስዓ ወተስዓተ" ዘጠና ዘጠኙን በጎች ትቶ "ይኅስስ፣ የሐውር ዘተሀጉለ" የጠፋውን በግ ሊፈልግ የሚኼድ የለምን? ብሎ አስተምሯልና ሀዲጎ ተስዓ ማለት ዘጠና ዘጠኙ ነገደ መላእክት ናቸው። መላእክት በነገድ መቶ ናቸው። ከመቶ ነገድ ዲያብሎስ ከክብሩ ስለወረደ ፺፱ ቀርተዋል። በመቶኛው ዲያብሎስ ቦታ ላይ አዳም ነው የተተካ እየሩሳሌም ሰማያዊት ለአዳም ተሰጥታለች። እና ወደዚህ ዓለም መድኀኔዓለም ክርስቶስ ሲመጣ በበግ የተመሰለ

የጠፋ በግ የተባለ አዳም ነው። የበግ ባለቤት የተባለ እራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የአዳምን መከራ እሱ ተቀብሎ ከሲኦል አውጥቶ ወደ ገነት መልሶታል።

እንዳውም የጥምቀት ዕለት ይህ ሀዲጎ ተስዓ ወተስዓተ ነገደ የሚለው ምስጢር አለው ጌታችን በዮርዳኖስ የተጠመቀበት ምስጢርም የአዳም የእዳ ደብዳቤ በዮርዳኖስና በሲኦል ነበር የተጣለ። "አዳም የወንድ ሰራተኛ ተገኘ ሎሌ፣ ሄዋን የሴት ተገኘ ብላችሁ ጽፋችሁ ስጡኝና መከራውን ላቅልላችሁ" አላቸው። ፈቀዱለት። "እሱ በኹለት እብነ በረድ አዳም የዲያብሎስ ተገኘ ሔዋን የዲያብሎስ ተገኘ ናት"። ብሎ ጽፎ አንዱን በዮርዳኖስ አንዱን በሲኦል ጥሎት ነበርና ጌታ ይህን ምስጢር ስለሚያውቅ የጠፋውን በግ አዳምን ሊፈልግ መጣ እሱ ራሱ በወንጌል እንዳስተማረ በዮርዳኖስ ነበርና የወደቀ በዮርዳኖስ ጌታ ሲጠመቅ ያን የአዳምና የሔዋንን የእዳ ደብዳቤ "እንደአምለክነቱ አቅልጦ፣ እንደሰውነቱ ረግጦ" "ወሰጠጠ መጽሐፈ እዳሆሙ ለአዳም ወለሔዋን" የአዳምና የሔዋንን እዳ ደብዳቤያቸውን አጠፋላቸው ብሎ ቅዱስ ፓውሎስ ተናግሮታል ሊቁ ቅዱስ ኤፍሬምም ተናግሮታልና ያነን ለመደምሰስ ስለመጣ "ሀዲጎ ተስዓ ወተስዓተ ነገደ ቆመ ማዕከለ ባሕር ገብአ ወወጽአ በሰላም" ዘጠና ዘጠኙን ነገደ መላእክት ትቶ ወደዚህ ዓለም መጣ። "ቆመ ማዕከለ ባሕር" በዮርዳኖስ መካከል ቆመ። ገብአ ወወጽአ በሰላም። ተጠምቆ በሰላም ወጣ" ይላል ቅዱስ ያሬድ።

ይህን ይዘን የጎንደር ጥምቀት ለሰው ልጅ ልማት ከሥነ ምግባር አኳያ ያለው ፋይዳ ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ እንግዲህ ልማት ማለት የገንዘብ ልማት ብቻ አይደለም የገንዘብ ልማትን የሚቀድመው ልማት አለ። የሚቀድመው የመጀመሪያው ልማት ዕውቀት ነው። ጥበብ ነው፣ ትምህርት ነው። ሌላው ቁሳዊ ልማት፣ ሀገራዊ ልማት፣ የግብርናው ልማት፣ የንግዱ ልማት፣ ሌላውም የማኅበረሰቡ ልማት ይፈጠራል ማለት ነው። እንደገና ደግሞ ጥበብም እውቀትም ትምህርት እንዲኖር የመጀመሪያው ልማት ፍቅር ነው። ይህ በዓል ሀገራዊዉም ከሀገር ውጭ የመጡትም ቱሪስቶችም በፍቅር ተስማምተው ሲያከብሩት ይህ የመጀመሪያውን የልማት መሠረት ወይም መሠረተ ልማት የሆነውን የፍቅር ልማት ያሳያል።

በጥምቀት በዓል ቀን የፍቅር ልማት ይለማል። የእውቀት ልማት አለ። ቱሪስቶቹ ፈረንጆቹ በያዙት መሳሪያቸው የጥምቀቱን በዓል የሊቃውንቱን ቃለ እግዚአብሔር የባህሩን እስከ ዋናው ድረስ እንደገና የሚቀርበውን መንፈሳዊ መዝሙር ጽላቱን ታቦተ ህጉን ቀሳውስቱ ተሸክመው ሲሄዱ የህዝቡን ሆታውን እልልታውን ሁሉ ባመጡት መሳሪያ በሙሉ

ቀርጸው፣ ቀርጸው ይዘው ይዘው ሂደው በአገራቸው ሰፊ ልማት ያለሙበታል። የጎንደር ጥምቀት ጥምቀት በዓል ልማቱ እንዳውም ከኢትዮጵያ ይልቅ ለአውሮፓውያን፣ ለምራባውያን፣ ለምሥራቃውያን ለሚመጡት ሰፊ፣ ሰፊ የገቢ ምንጭና ሰፊ የሆነ መሠረተ ልማት ነው። እንዳውም ከሀገር ውስጥ ካሉት ከሀገር ውጭ ላሉት ቀርጸው የሚወስዱትን ቅርጻቅርጽ ቤተ ክርስቲያን ኺደው የልማት ልማት ያስገኛሉ። እንዳውም ኢትዮጵያ ከሌሎቹ የምታገኘው እርዳታ በእጅ አዙር የራሷን ነው የምታገኘው። ምክንቱም ከዚህ ተቀርጾ የኼደው የበዓል አከባበር ፈረንጆቹ ለሌላ እያሳዩ ገቢ እያገኙ እንደገና ለኢትዮጵያ በእርዳታ ይሰጧታል። ግን የኸ ሊታሰብበት ይገባል ኢትዮጵያ ኹል ጊዜ በብድርና በእርዳታ መኖር የለባትም። ሳታጣ ያጣች ሀገር ናት ኢትዮጵያ። እና ልማታዊ ነው ማለት ነው።

ከአካበቢ ጥበቃ ጋራ ከመንገድ፣ ከውሐ ከአጸድ ጋራ ተያይዞ የጎንደር ጥምቀት ምን ፋይዳ አለው?፡- የጥምቀት ሰሞን መብራቱ ይበራል፣ በየ ምንገዱ ቱሪስቶች ስለሚመጡ እንዳው ሀገሪቱን ኹሉ የሚታደግ በዓል ነው። ለጎንደር ትልቅ ባለሥልጣን ነው የጥምቀት በዓል። መብራት ኀይልም አዞ የማያሠራውን የጥምቀት በዓል ሲመጣ ግን ኹሉን ያሠራል። እና ትልቅ በዓለ ሥልጣን ነው። የጥምቀት በዓል በጎንደር ይህ ብቻ አይደለም። የተበላሹ መንገዶችም ያን ጊዜ ነው የሚጠገኑ። ለቱሪስቶችም ለባለ ሥልጣኖችም ስለሚባል እነሱ እሚመጡ ጥምቀት በዓልን ብለው ስለኾነ ዋናው መሠረቱ ጥምቀት በዓል ነው። ጥምቀት በዓል ውሐውን ኹሉ፣ መንገዱ ኹሉ ይታጠባል። ከዚህ ከመንበረ ምንግሥት ጀምሮ እስከ ጥምቀተ ባሕሩ ድረስ ወጣቱ መንገዱን ያጸዱታል። ይጠረጋል እንደገና ይታጠባል። በእውነቱ ዓመቱን የክረምቱ ውሐ ያጥበዋል ከዚያ በተረፈ ግን አቧራ ነበርና ለትራኮማ ለምን፣ ለምን ይህ እየቦለለ አስቸጋሪ ነበር። የጥምቀት በዓል ዓይን ኹሉ የበራል። ያን ጊዜ የሚጨፍረው ኹሉ አቧራ የለም። መኪናው ኹሉ የመኪና ጎማ ራሱ በጥምቀት በዓል ነጻነት ያገኛል። በንጹሕ አስፓልት ላይ የሚኼድ ነው ለማለት ነው። ምኑን ዘርዝረነው እንዳው በእውነቱ እንዘርዝረው ከተባለ በአጭሩ ኹሉም ነገር በጥምቀት በዓል ትልቅ ልማት አለው።

ያን ጊዜ እደ ጥበባት ያላቸው ሽማ እሚሠሩ ሰዎች ገበያቸው እንዴት ነው ሀበሻው ፈረንጁ የአበሻውን ልብስ እየገዛ ስለሚለብስ እጥፍ ይጨምራል። ባለ ሆቴሎች አልጋ ውድ ነው ያን ጊዜ አይገኝም። ብዙ ገቢ አለ። መጠጥ ምን እና በእውነቱ ሳስበው ለጎንደር ብቻ አይደለም። ለኢትዮጵያ በሙሉ የገቢ ምንጭ ነው። እንዳውም እስካሁን ድረስ በዩኒስኮ ሳይመዘገብ መቆየቱ ለነጋዴውም፣ ለገበሬውም፣ ለአምራቹም፣ ለሽማ ሠሪውም፣ ለመስቀል ወርቅ፣

ጌጣጌት ለሚሠሩ፣ ሸማ ለሚሰሩት፣ለግብርና፣ ለቱሪዝም ለዚህ ለዚህ ኹሉ የገቢ ምንጭ፣ የመሠረተ ልማት ነው። በዓሉ ሃይማኖታዊ በዓል ተደርጎ ብቻ መወሰድ የለበትም። መስኅብነት ያለው ማን ነው? መባል አለበት። ዓለማቀፋዊነት ያለው የቱሪስት መስኅብ ጥምቀት ኹለተኛ ገቢ የሚያስገኝ ማን ነው? መባል አለበት። በጥምቀት በዓል ሁሉም ክብር ያገኛል። ቤቶቹን ሁሉ ጥምቀት ነጻ ያወጣቸዋል። ቀለም ይቀባሉ። ይጸዳሉ። እንዳው የጎንደር ጥምቀት ምን ልበልህ ለኹሉም፣ ለኹሉም መሠረት ነው።

የጎንደር ጥምቀትና 44ቱ ታቦታት ምን ግንኙነት አላቸው?፡- ጎንደር ውስጥ 44 አድባራት አሉ። የምትታወቀውም ጎንደር 44ቱ ተብላ ነው። ነገሥታቱ የጎንደር ነገሥታት አብያተ ክርስቲያናትን ይሠራሉ። ባላባቶቹም ይሠሯቸዋል። ጎንደር፣ 44ቱና ፋሲል ግንብ እጅና እግር ናቸው። እጅ ይዳስሳል እግር ይራመዳል። ወይም ጥርሰና ከናፍር ናቸው። 44ቱን ታቦታት አስፓልቱ ስለማይችል 8ቱ ናቸው። ከጻድቃንም፣ ከሰማእታትም፣ ለምሳሌ ተጠማቂው መድኀኔዓለም አጥማቂው መጥምቁ ዮሐንስ ስለዚህ መድኀኔአለም ከታች ደግሞ ቅሐ ኢየሱስ፣ አጥማቂው ዮሐንስ ይወርዳል። እንዲኹ ከመላእክት አጣጣሚ ሚካኤልና ፊት ሚካኤል ይወርዳሉ። ከሰማዕታት እልፍኝ ጊዮርጊስና ቅዱስ ፋሲለደስ ይወርዳሉ። ከጻድቃን አቡነ ተክለሃይማኖት አባጃሌ ተክለሃይማኖት ይወርዳል እና ልደታ ማርያም ትወርዳለች።

የቅሐ ወንዝ እና ጥምቀተ ባሕሩ ምን ግንኙነት አላቸው?፡- ተጠልፎ ጥምቀተ ባሕሩ እንዲሞላ ቅሐ ኢየሱስ ዐፄ ፋሲል ከመንገሳቸው በፊት ቀደም ይላል። ድንኳን ተተክሎ ቅሐ ኢየሱስ ወንዙ ዳር ነበር የሚወርድ እነ ዐፄ ፋሲል በምስጢር ነው የሠሩት ማንኪት ከሚባል ቦታ ጥምቀተ ባሕሩን ያሰሩት የቅሐ ኢየሱስ ይተከልበት ከነበረው ቦታ ነው። ቀድሞ ቅሐ ወንዙ ነበር የሚባረክ አትን ግን ያ ወንዝ ይሳብና ዐፄ ፋሲል ወደ አሠሩት የጥምቀተ ባሕር ይገባና ያ ይሞላል። ያ ይባረክና ቅሐ ወንዝና ጥምቀተ ባሕር ግንኙነት አለው። ድንኳን የነበረው አኹን ቤተ መቅደስ ነው። አኹን ያወንዝ ተስቦ ይመጣና በመሽረብ በመስኖ ተስቦ ይመጣና ይጠራቀማል። ደስ ይላል ንጹሕ ውሐ ነው። የቅሀ ወንዝ በከተማው መሐል ነው የሚመጣ ንጹሕ የሚኖነው ሰው ያከብረዋል ማለት ነው?፡- ጥምቀተ ባሕሩ ለቀሐ ወንዝ ቅርብ ነው። ቅርብ ስለኾነ ቅሐ ወንዝ ላይ እንኳን ቆሻሻ ሊጥል ሲጥል የተገኘም ሰው ካለ ይቀጣል። በጥምቀት ወንዙም ራሱ ክብር አግኝቷል። ጥምቀት ኹሉንም ነው የሚያስከብር ወንዞችም፣ እጸዋትም፣ አዕዋፋትም፣ በጥምቀት ይከበራሉ (ሊቀ ሊቃውንት እዝራ ሀዲስ 15/11/2011 ቃ.መ)።

**ቃለ መጠይቅ ኹለት (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011)፡-** የጎንደር ጥምቀትና ማኅበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል?፡- ጥምቀት ከማይዳሰሱ ቅርሶች መካከል በባህላዊ ሀብት ሰፊ ጥቅም አለው፡፡ የጋራ ማንነት ያጠናክራል፡፡ መቻቻልን የሚያሰፍን በዓል ነው፡፡ ይህ በዓል ዋናው ፋይዳው የማኅበረሰብን መተሳሰሰብ ይፈጥራል፡፡

የጎንደር ጥምቀት በቁጥር እጅግ ሰፊ የሆነ ማኅበረሰብ የሚሳተፍበት ነው፡፡ የዚህ አንድምታ ምንድን ነው?፡- በዓሉ ጎንደር ላይ በተለየ ኹኔታ ስለሚከበርና ልዩ ገጽታ ስላለው የተለየ የሚያደርጉት ብዙ ገጽታዎች የአለባበስ፣ በወቅቱ አመጋገቡ፣ ጭፈራው፣ ሥነ ሥርዓቱ ከሌላው አካባቢ ከፍ ያለ ስለሚያደርገውና ስለሚጎላ ይህን ክብረ በዓል ለመታደም ከውስጥም ከውጭም በርካታ ሕዝቦች ይታደማሉ፡፡

በጥምቀቱ ክብረ በዓል ላይ የአጨፋፈርና የአለባበስ ልዩነት ይታያል ይህ ምን አንድምታ አለው?፡- አዘፋፈኑን አጨፋፈሩን በሚመለከት ጎንደር የራሱ የኾነ ዜማ፣ ምት፣ ስልትና ዕውቀት አለው፡፡ የጎንደር አካባቢ የስልተ ምቱ አንድ ዓይነት ቢኾንም የአጨፋፈር ልዩነቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ የደንቢያ አለ፣ መሐል ጎንደር፣ ወገራ፣ ራሱን የቻለ ወደ ጥምቀት ሲመጡ የአካባቢያቸውን የጎንደርኛ አጨፋፈር ይዘው ይመጣሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ጎንደር በአጨፋፈር ስብጥር የኾነ ስልት አላት፡፡ የአጨፋፈር ስልቱ አንገር፣ አንገ በአንገ የሚሉት አለ፡፡ ዋንጫ ልቅለቃ የሚሉት አለ፡፡ ስለዚህ በጥምቀት ክብረ በዓል እነዚህ ኹሉ የጭፈራ ዓይነቶች ይታያሉ፡፡ አለባበሱን በሚመለከት ግን ጎንደር የራሱ ወጥ የኾነ የአለባበስ ስልት አለው፡፡ ሸማ ለባሽ ሕዝብ፣ ነጭ ለባሽ ሕዝብ ነው የሚባለው፡፡ ሴቶች ጥልፍ ከሙሉ ሸማ የተሠራ ኾኖ በጥልፍ የተሠራ ሙሉ እጅጌ ያለው እጅጌው አንባር አለው አንባሩና ልብሱ በዕድሜ ባገባና ባላገባ ተብሎ ይለያያል፡፡ ሕጻናት ከኾኑ ብዙ ጌጥ የበዛበት ጥልፎ ያደርጋሉ፡፡ በተለይ ትከሻቸው አካባቢ፡፡ ከደረት በኩልና ትከሻ አካባቢ በጣም የተዋቡ ናቸው፡፡ የልጃ ገረዶች ጥልፍ ቀሚስ፡፡ ያገቡትና ቤት የመሠረቱት እናቶች ጥልፍ ብዙም ጌጣጌጥ የለውም፡፡ አምረው ተውበው የሚታይበት ጊዜ አልፏል፡፡ በሰከነ ሕይወት ወልደው የሚያሳድጉበት ኹኔታን የሚገልጹበት የሚያሳዩበት ነው አለባበሳቸው፡፡ ሸማ ነው የጎንደር አልባሳት፡፡

ጎንደርና ሸማ ግንኙነታው ምንድን ነው?፡- ሽመና አንዱ የዕደ ጥበብ ውጤት ነው፡፡ የጎንደር ሸማ ከነገሥታቱ ይጀምራል በነገሥታቱ ዘመን ነገሥታቱ ሸማ ይለብሱ ነበር፡፡ ከላይ የሚደርቡት ኩታ፣ ባትተኹለት፣ ግብግብ ከሸማ እሚሠራ ነው፡፡ ነገሥታቱም ይህን ይለብሱ ነበር፡፡ በእጅ የተሳሉ በተለያዩ ቦታዎች የምናያቸውን ብታይ ሸማ ለብሰው ነው የምታያቸው፡፡ ረጅም ኩታዎች 50 ክንድ ለብሰው ነው የሚታዩ ይህ የማኅበረሰቡ የረጅም

ዘመን ያለውና ከማኅረሰቡ ጋራ ቁርኝት ያለው የረጅም ጊዜ የዕደ ጥበብ ውጤት ነው። ብዙ ታሪክ ያለው ነው። በጎንደር አገር በቀል ዕውቀት የሚወሰድ ነው ሸማ። እነዚህ ሸማዎችና መሰል መዋቢያዎች በጥምቀት ሰሞን በጣም ይደራል። ስለዚህ ጥምቀት በኢኮኖሚው ምን አስተዋጽኦ አለው?፦ ጎንደር በጥምቀት ልዩ ተጠቃሚ የምትሆንበት ወቅት ነው። ቅድም እንዳልኩት ይህንን በዓል ለመታደም በርካታ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ጎብኝዎች ወደ ከተማዋ ይፈሳሉ። እነዚህ ጎብኚዎች ገንዘብ ይዘው ነው የሚመጡ፣ በዓሉ ለሦስት ተከታታይ ቀናት ነው የሚከበረው። እንዳውም እስከወር ድረስ ይኼዳል። እያንዳንዱ በዓል በየ ራሱ ቤተ ክርስቲያን የሚያከብረው በመኾኑ እስከወር ድረስ ይቆያል። በተለይ ሦስቱን ቀናት ከአገር ውስጥም ውጭም የመጡት ታዳሚዎች በዓሉን ለሦስት ቀናት ሲያሳልፉ አንደኛ ለአልጋ፣ ለምግብ ለተለያዩ ነገሮች ወጭ ያወጣሉ። ይህ አንድ ጥቅም ነው። እንደ ኢኮኖሚ ሲታሰብ። ማኅበረሰቡ በዚህ አንደኛ ተጠቃሚ ነው። ኹለተኛ ከዕደ ጥበብ ምርትና ሽያጭ ቅድም ያልኳቸውን ባህላዊ አልባሳት በዚህ ወቅት ብብዛት ይሸጣሉ። ጌጣጌጦች ከመዳብ፣ ከብር፣ ከወርቅ የሚሰሩ ጌጣጌጦች እንደ ድሪ እንደ አልቦ ኹሉ በዚህ ወቅት ይሸጣሉ። ስለዚህ በዚህ ኹሉ አቅራቢዎቹ ተጠቃሚ ናቸው። ሌላው ሸቀጣ፣ ሸቀጥ ኹሉ በዚህ ወቅት ይሸጣሉ። ስለዚህ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ በጣም የሰፋ ነው። ሌላው ወደ ሠላሳ ሽህ ጎብኝ የሚገኝበት ነው። ሠላሳ ሽህ ጎብኝ በሦስት ቀናት ውስጥ ለማግኘት በዓመትም ይከብዳል። ስለዚህ በዚህ መልኩ ይህ ጎብኝ መዋዕለ ንዋዩን በዚህ መልኩ አፍሶ ከኼደ ማኅበረሰቡ ተጠቃሚ ነው ማለት ነው።

ከቅርስ ጥበቃ ጋራስ የጥምቀት ክብረ በዓል ምን ፋይዳ አለው?፦ እንግዲህ ጥምቀት በጎንደር ሲከበር አከባበሩ የማኅበረሰቡን ባህልና ሥርዓት የተከተለ ነው። እነዚህ የማኅበሰቡን ባህልና ወግ ና ዕሴቶች እንዲተዋወቁና ተጠብቆ እንዲቆይ ያደርጋል ማለት ነው። ተዋወቀ ማለት ተጠበቀ ማለት ነው። ሌላው ማኅበረሰቡ የራሱን ባህል ማንነት ካወቀ እየተንከባከበው ይኼዳል ማለት ነው። ስለዚህ የጥምቀትን ባህል የሚያከብረው ማኅበረሰብ ከእሱ እንዲርቅበትና እንዲበረዝበት አይፈልግም። ኹል ጊዜ በድምቀት እንዲከበርለት ይፈልጋል። ይህ ደግሞ የኔ ባይነት ስሜት ይፈጠራል። ባህሉ በራሱ ይከበራል። ሲከበር ደግሞ የሚከበርበት ቦታ የፋሲል ግንቦች በመኾኑ እነዚህ ቅርሳዊ ግንቦች እንዲጠበቁና እንዲተላለፉ ያደርጋል። ያ መዋኛ ለዚህ ጉዳይ የተሠራ ነው። የነገሥታቱ ዘመን ለክርስትና እምነት የነበራቸው ቀናዒነት ለዚህ ቅርስ መኖር ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጓል። ይህ በዓል ሲከበር የዮርዳኖስ ወንዝ አስመስሎ ማኅበረሰቡ

እንዲገለገልበትና በዚያ መልኩ የተሠራ ስለኾነ፡፡ "ታንጀብል ሄሬቴጅ" አብሮ እንዲከበር ያደርጋል፡፡ ስለዚህ የጎንደር ጥምቀት ለኹለቱም ለሚዳሰሱም ለማይደሰሱም ቅርሶች እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

የባሕረ ጥምቀቱ ግንብ ነገሥታቱ የገነቡበት አንድምታ ምንድን ነው?፡- ከእስራኤል ሀገር ጋራ የምንመሳሰልበት አንደኛው ይህ ነው፡፡ ዮርዳኖስ ወንዝ ያለው እስራኤል ነው፡፡ ያነን ለመዘከር ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀበትን ቦታና ዕለት በመዘከር እኛም ተመሳሳይ ወንዝ የሚመስል መዋኛ ማንም አገር መሰል መዋኛ ባልገነባበት ምንአልባትም ባላወቀበት ዘመን እኛ ገንብተናል፡፡ በዚህም ጥሩ ትስስር እንዲኖረን ያስችላል፡፡ የአዕዋፋት ዝማሬ፣ የጫካው መጠበቅ፣ የውሐዎች መንጻትና ጥምቀት ምን ግንኙነት አላቸው?፡- የጥምቀት መከበሪያ አካባቢ እንዲጠበቅለት ማኅበረሰቡ ይፈልጋል፡፡ ከዚህ አንጻር የማኅበረሰቡ ድጋፍና እንክብካቤ አለ፡፡ እኛ ነን የምንጠብቀው፡፡ የጎንደር ግንቦች በአብዛኛው ተጠብቀው ነው ያሉት፡፡ ይህ የኾነበት ምክንያት የማኅበረሰቡ የኔ ባይነትና ሃይማኖታዊ ግንኙነት ጭምር ስላላቸው ነው፡፡ ማኅበረሰቡ ራሳቸው ስለሚጠብቃቸው፡፡ የቅሐ ወንዝ ተጠልፎ የሚመጣበት አካባቢ እጅግ ንጹሕ ነው፡፡ በዚያ አካባቢ ያሉ እጽዋትም አዕዋፋትም ጥብቅ ናቸው፡፡ አዕዋፋቱም በዚያ ውስጥ ያሉ እጽዋት ይጠበቃሉ፡፡

የጥምቀት በዓል መነሻው ለሰው ልጆች ነው ከዚህ አንጻር በዓሉም ሰባዊ ነው ማለት ይቻላል?፡- በተባለው ልክ እውነት ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ እጅግ ፍጹም ሰዋዊ ነው፡፡ ሰዋዊ ሥርዓት አለው ሥርዓቱን ጠብቆ የሚከበር ነው፡፡ የጎንደር ሸማ የጎንደር ቀሚስ ለጥምቀት ካልሆነ ይበጣጠስ ይባላል፡፡ ገበሬውም በጥምቀት ወቅት የሚያርፍበት የሚዝናናበት፡፡ "ጠርን ጥምቀትን ካረሰ የቀላወጠ" የጎንደር ማኅበረሰብ በጥምቀት ወቅት ነጭ ለብሶ ደግሶ ብሉልኝ ጠጡልኝ ብሎ ነው፡፡ እውነትም አንዱ ለሌላው በመተሳሰብና ስብናን በመቅረጽ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ሥርዓቱ ራሱ ከጥንታዊ ትውፊቱ በተለየና በተዛባ መልኩ እንዳይከበር ስለሚከለክል የማኅበረሰቡን ስብእና በመቅረጽ፣ በማነጽ ደረጃ ጉልህ ነው የሚባለው በዚህ በኩል ነው፡፡

በጥምቀቱ የሚቀነቀኑ ቃል ግጥሞች አንድምታ ምንድን ነው?፡- ብዙ ግጥሞች በዚያን ወቅት ይወርዳሉ ሃይማኖታዊ፣ የማኅበረሰቡን ማንነት የሚገልጹ፣ ቁንጅናን፣ ነጻነትን፣ እምነትን፣ ጽናትን የሚገልጹ ግጥሞች ይቀነቀናሉ፡፡ ገዳሙ፣ ገዳሙ የሚባሉ ግጥሞች በሙሉ ገጽታን ሰባዊ ግንባታን የሚገልጹ ግጥሞች ናቸው፡፡ አለው አለውና ያው በማተቡ

ጠና፡፡ ይህ ጽናትን፣ አለመዋሸትን፣ እውነተኝነትን፣ ስብእናን ለአለማጉድፍ የሚደረግን ውስጥ ባህል የምትረዳበት መንገድ ነው፡፡ በዚህ ወቅት በጥምቀት ማንም ሰው ወጥቶ እንዲዘፍን፣ እንዲደሰት ይፈቀድለታል፡፡ ለዚያን ጊዜ ያልኾነ እስክስታ፣ ደስታ፣ አንገት፣ ለመቼ ሊኾን ነው? ለዚያን ጊዜ ያልሆነ መብል ለመቼ ሊኾን ነው? ለዚያን ጊዜ ያልኾነ ሽማ ለመቼ ሊኾን ነው? ስለዚህ በዚያን ጊዜ ሕጻናት እንዲቧርቁ ይፈቀዳል፡፡ አደለም ሰው በቤት ውስጥ ታስረው የሚጠበቁ እንስሳት፣ እንዲፈቱ ኹሉ ነው የሚደረገው፡፡ ወቅቱም መኸር ተሰብስቦ ጥጋብ የሚኾንበት ወቅት ስለኾነ ሰው እንዲዝናና ሥርዓቱን ጠብቆ፣ ባህሉን ጠብቆ ይደረጋል፡፡ በዚያን ቀን ከቤት የሚውል ጤና ያጣና ከዐቅም በላይ ካልኾነ አይቀርም፡፡ ምክንያቱም "ከቤት ይውላል ሞኛ ሞኙ፣ ከቤት ይውላል ሞኛ ሞኙ እንትና ልጁ ካንድ ላይ ሲገኙ"፡፡ ጥምቀት ለኹሉም ነጻነት የሚሰጥ በኢኮኖሚ፣ ለብሶ አጊጦ የሚውሉበት ለኹሉም ነጻነት የሚሰጥ፡፡ በዚያን ጊዜ ኹሉም ሠራተኛውም፣ አሠሪውም፣ ነጋዴውም፣ወጣቱም ሕጻኑም፣ ዐዋቂውም፣ በአንድ ላይ ወጥቶ እንዲያከብረው ስለሚጠበቅ ከቤት የሚውል የለም ይባላል፡፡

የጎንደር ጥምቀት ዐውድ የሚፈጥረው ድባብ ምን ይመስላል?፡- ጥምቀት ከመምጣቱ ኹለት ሳምንት ቀደም ብሎ የጎንደር ሰማይ ይጠራል ነው የሚባለው፡፡ እንኳን ሰው ሰማይው ውሐ ሰማያዊ ይኾናል እውነት ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ቤቶች ኹሉ ይቀባሉ፡፡ አካባቢው ይዋባል፡፡ ምእመናኑ በተለይ የእምነቱ ተከታዮች አካባቢውን በአገራችን ባንዲራ ያሸቀጠቁጣሉ፡፡ ግም፣ ግም ሲል ስሜቱ ኹለት ሳምንት ቀደም ብሎ ይጀምራል፡፡ ከዚያ በኋላ ዋናው በዓል ሲከበር ያድምቀት ገዝፎ ሕፃናቱ፣ ዐዋቂው፣ በየፊናው ዕድሜውና ችሎታው በሚፈቅድለት መንገድ በዚያ ባማረ የባህል ልብስ ሲያከብረው ጎንደር በተለየ መንገድ በተለያዩ ጌጣጌጦችና በብዙ ቀለማት ትዋባለች፡፡ ከሰማይው ከአድማሱ ጀምሮ ማለት ነው፡፡ እኔ አንድ ጸሐፊ የማስታውሰው (The glores celebration) ብሎ የጻፈውን አስታውሳለሁ፡፡ ይህን ስሜት ስለፈጠረበት ነው ኹኔታው፡፡ ስብጥሩ ይህ ነው የማትለው ድባብ ይፈጥራልና ዓመት ምን አለ ዕንደ ዕለት ፈጥኖ በደገምነው ኹሉ ያሰኛል፡፡ ስለዚህ የጎንደር ጥምቀት ይህን ያህል ጉልበት ያለው ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀት መነሻው ሃይማኖታዊ ነው፡፡ ከሃይማኖታዊ አንድምታው በተለየ በማኅበራዊ፣ ሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊ የቱሪስት መስኅብነትና መሰል ምን ፋይዳዎች ይኖሩታል? የሌላ ሃይማኖት ተከታዮችስ ከጥምቀት በዓል ምን ፋይዳ ያገኛሉ?፡- ሽማ በመሸጥ ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋራ መቀራረብን በመፍጠር ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ በጎንደር ያሉ የእስልምና እምነት ተከታዮች በጥምቀት ሰሞን በሥራ ይወጠራሉ ትልቅ

የኾነ የገበያ ትስስር አለ፡፡ በተለይ በሽመናው፣ በጥልፉ፣ በጌጣጌጡ፣ በሆቴል የተሰማራው፣ የተለያየ እምነት ተከታይም ቢኾን እጅጉን የሚጠቀምበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህም የጥምቀት በዓል እንዲነካባቸው አይፈልጉም፡፡ በዚህም ማኅበረሰቡ እንዲቻቻልና አብሮ እንዲኖር ያደረገው ዋናው ጥምቀት ነው፡፡ እንደክርስቲያኑ ኹሉ የጥምቀት በዓል ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው ባሻገር ማኅበራዊ ትስስርንም ስለሚፈጥር በዓሉን የጋራ ሀብት አድርጎ የመውሰድ የጋራ ስሜቱ አላቸው፡፡ ማኅበራዊ ትስስሩ የጎለበተ እንዲኾን ያደርጋል፡፡

የጎንደር ጥምቀት ታሪካዊ ዳራ ምን ይመስላል?፦ ታሪካዊ ዳራው ጥምቀት የጌታችን የመድኀኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ያደረገውን መጠመቅ ማስታወስና መዘከር ነው፡፡ አስተምህሮ አለው፡፡ በጎንደር ጥምቀት በዓል ከዚህ ጀምሮ ተከበረ የሚባልበት የለም፡፡ ግን ከዐፄ ፋሲል ቀደም ብሎ እና ጎንደር በዐፄ ፋሲል ተጀመረ ተብሎ ስለሚታሰብ ከ1628 ጀምሮ ነው ጎንደር የሚያነሣው፡፡ ግን ጎንደር ከዚያ በፊትም የከተማ ቅጥ የነበራት አካባቢ ናት፡፡ ጎንደር ታሪካዊ ዳራዋ የተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች የሲራራ ንግድ ይካኼድባት ስለነበር ጎንደር ከዚያ በፊትም ከተማ ናት፡፡ ያኔም ጥምቀት ይከበር ነበር፡፡ የፋሲል መዋኛ መገንባቱ የጥምቀትን በዓል በጎንደር ይበልጥ አጎላው፡፡ ዕሴት ሰጠው (ልዕልና ኀይለ መስቀል 12/12/2011 ቃ.መ)፡፡

**ቃለ መጠይቅ ሦስት መልሽው ጌጡ፡-** ጥምቀትን እንዴት እና በምን ኹኔታ ነው የምታከብሪው?፦ ጥምቀት አሪፍ ነው፡፡ በአንድ ላይ ኹነን በመሰባሰብ፣ በመጨፈር እናሳልፋለን፡፡ የጥምቀት ዝግጅት ከመቼ ይጀምራል?፦ ሳምንት ጀምሮ እንዘጋጃለን፡፡ ልጆች እንዴት ነው ጥምቀት ሲመጣ ዝግጅቱ?፦ ልብስ ይገዛላቸዋል ለሴቶች ሹርባ ይሰራሉ፡፡ ጫማ ይገዛላቸዋል፡፡ ከጓደኞቻቸው ጋር እየጨፈሩ ያከብራሉ፡፡ ይህ ነው ለየት የሚደርገው፡፡

የጎንደር ሥሬት የእናቶች የልጃገረዶች የአገቡ እና ያላገቡ ሴቶችን የሚለዩበት ኹኔታ አለው?፦ አወ አለው፡፡ እናቶች ሹርባ አለባሶ ይሠራሉ፡፡ ቀጭን ወደ ታች አሳ ሥሬት የሚባል አለ እሱን ይሠራሉ፡፡ እሱ የእናቶች ነው፡፡ የልጃ ገረዶች ደግሞ ወደ ታች እንደዚህ ጋሜ እና ቁንጮ የሚባል አለ፡፡ ገና ወጣት የመኾን ምሳሌ ነው (መልሽው ጌጡ፣ 12/ 05/ 2013 ቃ.መ)፡፡

**ቃለ መጠይቅ አራት (መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ 19/01/12)፡-** የጎንደር ጥምቀት ከማኅበራዊ ግንኙነት ጋር ማኅበረሰቡን ከማገናኘት ጋር ምን ፋይዳ ይኖረዋል?፦

በመጀመሪያ ስሜ ቆሞስ አባ ወልደ ሥላሴ እባላለሁ፡፡ የደብረ ሰላም ሰሚው ቅዱስ ሚካኤል ወ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን አስተዳዳሪ ነኝ፡፡ ጥምቀት በጎንደር ከማኅበረሰብ ትስስር ጋራ ከሃይማታዊ ግልጋሎቱ ውጭ ወደ ዚህኛው ወደ ሀገራዊ ልማት ስንወስደው ብዙ አንድምታ አለው፡፡ ጥምቀቱን ማየት ከመናገርም በላይ ይኸን ነበረ፡፡ ነገር ግን እንደቃላት ለመግለጽ በዚህች በትንሽ አእምሯችን እንገለጸው ብንል ጥምቀት ፍቅርን ያስተምራል፡፡ ማኅበረሰቡ አለባበሱን፣ አመጋገቡን፣ ባህሉን እንዲገልጥ ያደርጋል፡፡ የጎንደር ጥምቀት የኦሮሚያን፣ አፋርን፣ የወላይታን አቀፍ አድርጎ ያሳያል፡፡ ወንዶችም ሴቶችም ጾታ ሳይገድባቸው የተለያየ አለባበስን ለብሰው የዚያን ማኅበረሰብ ባህል ወግ እያስነበቡን የሚውሉበት፣ኹለተኛ ከእንቅስቃሴያዊ ራሱ ባህላቸውን በእንቅስቃሴያዊም የሚያስተምሩበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀት ከማኅበራዊ ኹኔታ ስናየው በመጀመሪያ ለታቦት ምንጣፍ እያነጠፉ ማስኬድን የጀመሩት የጎንደር ጫኝ አውራጅ ማኅበሮች ናቸው፡፡ ያኔ አንድ ሽሕ ብር ብዙ ብር በነበረበት ወቅት ላይ በትንሽ ብር በሜትሮች የሚለካ ምንጣፎችን ገዝተው አስፋልት መጥረግን፣ ወደ ተግባር አውርደው መጀመሪያ ላይ አስፈጸሙት ማለቴ ነው፡፡ ያ ማለት ደግሞ ከነፍሳዊና ከመንፈሳዊ በስተጀርባ ደግሞ ምን ያክል አንድምታ አለው፡፡ ጥምቀት በጎንደር ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያም ምን ያክል ማንነቱን፣ ምንነቱን እያንጸባረቀ ያለበት ኹኔታ ነው፡፡ ፈረንጆቹን ስናያቸው ነጮቹ ከውጭ መጥተው ጥምቀትን በጎንደር ብለው፡፡ ልዩነት የሚወስዱት በተለያየ ቦታ ላይ ከትንሽ ከጎጆ ቤተ ክርስቲያኗ ጀምሮ ጥምቀት አለ፡፡ ግን ያ ጥምቀትና የጎንደር ጥምቀት ልዩነት አለው፡፡ የጎንደር ጥምቀት የወረደ፣ የሚጨበጥ፣ የሚዳሰስ፣ የሚመገቡት እንዲህ የሚያዩትኝ ሰውም ተመልካቹ ራሱ ልዩ እንድምታ ይዞ እንዲያልፍ የሚያደርግበት ነው፡፡ በማኅበራዊ ትስስሩ ይህ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ በጎንደር ጥምቀት በተለየ መልኩ ደግሞ የሚታየው ሃይማኖቶች ማለት የሙስሊም ሃይማኖት ማኅበረሰቦች አስፓልት ጠርገው አጥበው ምን ብለው ያው ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ ያ ምንድን ነው የአካባቢው ማኅበረሰብ ፍቅር የሆነ ተፈጥሮ ባሕርይ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ እና ይህ የጎንደር ጥምቀት በተለያየ ኹኔታ ከመንፈሳዊነቱ በስተጀርባ የጎንደር ጥምቀት እንደታሪክም ስናየው ደግሞ ነገሥታቶቹ አክብረውት ዘውዳቸውን ዝቅ አድርገው ታቦት አጅበው፣ ሰራዊቱ ታቦቱን ተንከባክቦ ምንፈሳዊነት ማጥመቂያ፣ ቤተ መቅደስ፣ ባሕር ማጥመቂያ ሠርተው ባህሉን ጠብቀው የሚኼዱበት ኹኔታ ነበረ፡፡ አኹንም ያለው ያው ነው፡፡ ኹለተኛ ደግሞ የጎንደር ጥምቀት በተለያዩ አድባራት ነው የሚሸፈነው፡፡ ማለት ለምሳሌ የአደባባይ ኢየሱስ ዘንድሮ ጥምቀቱን አክብሮ

ከኾነ ቀጣይ ደግሞ አመራሩ፣ አሠራሩ ወይ አባጻሌ ተክለሃይማኖት ይውላል። ወይ በመንበረ መንግሥት እያለ አድባራቶቹ እንደ እቁብ እየተጣጣሉ በረከቱን የሚሳተፉበት እኔ እሠራ እኔ አደርግ እያሉ። በረከቱን የሚወስዱበት አለ። የጎንደር ጥምቀት ይኽ ብቻ አደለም። 44ቱም አድባራት ላይ ከዚያ ላይም ደግሞ ስናየው 44ቱ እንደ አንድ አድርገው ወይም ደግሞ እንደ ተወሰኑ አድርገው በአንድ ላይ አውርደው የሚያውሉበት ደግሞ ትልቅ ትርጉም አለው። ከሌሎቹ አገራት ወይም ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት የጎንደር ጥምቀት ለየት የሚያደርገው ይህ ነው።

ሌላው የጎንደር ጥምቀት አለባበሶቹ መልክታዊ ናቸው። የሚነዷቸውን መኪና ነኮች፣ መርከብ ነኮች፣ እንደዚህ የመላእክት ቅርጽ ያላቸው እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የኾኑ ሰው ማንም ወንጌል ሳያስተምረው የሚደረጉትን እንቅስቃሴ በማየት ብቻ እንዲገባው የሚያደርጉ። ለምሳሌ መስማት የተሳናቸው ዜጎች እራሱ ያንን በማየት የጎንደርን ጥምቀት እንድምታው ምን እንደኾነ የሚረዱበት ለኹሉም ማኅበረሰብ ማየት የተሳናቸው በጆሮ ሲሰሙት ከዝማሬው ጋራ መስማት የተሳናቸው ደግሞ በማየት ብቻ የሚተረጎም ትልቅ ታሪክ ያለው ነው። የጎንደር ጥምቀትና መንፈሳዊውም ዕይታ ለየት የሚያደርገው ይህ ነው። ሌላው የጎንደር ጥምቀት ከሌሎቹ ለየት የሚያደርገው እንደተባለው "ነገሥታቶቹ ክተት ሰራዊት፣ ምታ ነጋሪት" ብለው እንደ አዋጅ የሚደግፉት ነበር። ይህነን ሊቃውንቱን ግብዣ የሚጋብዙት ኹሉን ነገር የሚያደርጉት ነገሥታቶቹ ነበር። ከነገሥታቶቹ ከአባቶቹ የሃይማኖት ብቻ ሳይሆን የሀገር መሪዎች ራሱ እንደ ሀገር መሪ እንደ ፖለቲካ ሳያዩት እንደ ታሪክ እንደ ቅርስ አውርደው ለትውልዱ ሰጥተዋል። ዛሬ ምንም የታሪክ መሸዋወድ፣ የታክ ምዝበራ፣ የታሪክ ስረቆት፣ የአሻራ ስርቆት ቢኖርም እንኳ ይህ ታሪክ የማይሰረቅ ነው። ጎንደርነትን የጎንደር ታሪክን የጎንደር ባህሉን ሰርቆ መውሰድ አይቻልም። ምክንያቱም ባህሉ የሚዳሠሥ ስለሆነ። ባህሉ ወደ ትውልዱ ወርዶ ኹሉም ትውልድ ከእነዚህ፣ ከእነዚህ ከሕፃናቱ ጀምሮ እያንዳንዱ በቅብብሎሽ እያስተላለፈው ያለው ታሪክ ነውና የጎንደር ጥምቀት በዚህ የሚገለጽ አደለምና ይህን ይመስላል በኔ በኩል።

የጎንደር ጥምቀት ከሰዋዊ አስተምህሮውና ሥነ ምግባር ከማስተማር ወጣቱን ከመቅረጽ ጋራ ያለው አንድምታ ምን ይመስላል?፦ በእርግጥ መጀመሪያ ጌታችን መድኀኔታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ዝቅ አድርጎ በማዕከለ ዮርዳኖስ ራሱን በሰዎች ተራ አድርጎ ትሕትናን ያስተማረበት ነው የጥምቀት በዓል ራሱ ተምሳሌቱ እሱ ነው። እንዳለ ኾኖ

ደግሞ ይኸንንም ወደ ራሳቸው ወስደው ነገሥታቶቹ ቀደም የነበሩት ሊቃውነቶቹ ራሱ ከተራ ከሕፃናቱ ጀምሮ አብረው ዘምረው አሸብሸበው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ፍቅርን የሚያስተምር፣ ትሕትናን የሚያስተምር፣ እኔ የበላይ ነኝ ገዥና ተገዥ ሳይኖር ኹሉም ባለቤት ኹኖ የሚመራው፣ ባለቤት ኹኖ የሚከተለው በዓል ነው። የጎንደር ጥምቀት እንዳውም ከማኅበረሰቡ በበለጠ አገርን የሚመሩ ሰዎች እንደ አደራ ወይም እንደባለቤት ቢወስዱት ደግሞ የበለጠ ያምር ነበር። የጎንደር ጥምቀት ትልቅ ሀገር ልማት ነው። ምክንያቱም ከውጭ የሚመጡ ቱሪስቶች ወደ እኛ የሚያስገቡት ነገር አለ። ዜጎች ከዞን ወደ ዞን፣ ከክልል ወደ ክልል ከወረዳ ወደ ወረዳ በሚኼዱበት ሰዓት ላይ የኢኮኖሚ የራሱ ጥቅም አለው። ራሱን የቻለ ገንዘብ አለ። የሚበላ የሚጠጣ አለ። ባህልን መለዋወጥ አለ። በሙዚቃውም ዓለም ላይ እያለ ጎንደር እራሱ ብዙ ባህል አለው። ባህልን መወራረስ፣ መሸማመት፣ መገበያየት ኹሉም ስላለው ይህ ትልቅ አምባሳደር የኾነ ትስስር አለው አምባሳደር ነው። ያን ጊዜ ራሱ ባለ ታክሲዎች፣ ባለ ባጃጆች ባለ ምግብ ቤቶች፣ ባለ ሆቴሎች፣ ባለ ድራፍት ቤቶች ምን ያህል ገቢ ያገኛሉ። ይህን ሰፋ በአለ አእምሮ ካሰብነው ሰፊ ጥበቃም እንክብካቤ መደረግ አለበት። ከሃይማኖቱ እንዳውም በበለጠ ከ75% በላይ የጎንደር ጥምቀት ትልቅ ጥቅም እየሰጠ ያለው ለሀገር ነው።

የጎንደር ጥምቀት ከአካባቢ ጥበቃ ጋራ ምን አንድምታ አለው?፦ አካባቢ ጥበቃ በእርግጥ የመጀመሪያዋ ደን አልሚ፣ የመጀመሪያዋ ውበትን ጠባቂና ለትውልድ አስተላላፊ ቤተ ክርስቲያን ናት። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዛሬ ደን በተጨፈጨፉበት ቦታ ላይ ትንሽ ቅጠል አረንጓዴነት መልክ የሚታየው በቤተ ክርስቲያን ነው። በዚህ መካከል ላይ ደኖችን በመትከል፣ ታሪኮችን በመጠበቅ የጎንደር ጥምቀት በዓል ለኹሉም ሃይማኖቶች ተጠቃሚ ያደርጋል። ይህ ለኦርቶዶክስ ብቻ የሚጠቅም አደለም። የአገር ባህል ነው። የሀገር ልማት ነው። የሀገር ቅርስ ታሪክ ነው። ስለዚህ ሃይማኖቷን ብቻ ሳይኾን ማየት ያለብን ለሀገርም ያለውን ጥቅም ነው። ምእመኑ ራሱ በዓሉን ይጠብቀዋል። እንዳውም ወጣቱ እጅ ለእጅ ተያይዞ ተሳስሮ ያኔ ድሮ ከልብስ ልብስ አማርጠን በዓል ለማክበር የምንወጣው ሰዎች ዛሬ ያነ ተቀይሮ ወጣቱ ለአገልግሎት ነው የሚወጣው። ያ ማለት እንገዲህ ታሪኩን እየጠበቀው ነው ማለት ነው። ለኔ መዋብ፣ ለኔ ማጌጥ ይቅርብኝ ታቦቱ በሥነ ሥርዓት ወጥቶ በዓሉ ተከብሮ፣ ግብረ ገባዊ አንድምታ ተገንብቶ ልማት ይዞ እንዲያመጣልን ለክብረ በዓሉ ትልቅ ጥበቃ ማድረግ አለብን ብለው ታቦቱን ከመጠበቅ ጀምሮ በሰፈር መስከር

የለም፡፡ አኹን ዐልፎ ዐልፎ አንዳንድ ዐላዋቂዎች ካልኾኑ በቀር በሥነ ሥርዓት ውሐ እየጠጡ ነው የሚሄዱት ጨርሰውም ሲገቡ በዓሉን አክብረው ሲገቡ ወጣቶች ከቤታቸው ገብተው በጨዋነት ባህል ከቤታቸው የተገኘውን ቀምሰው ጠጥተው የተጠማ አጠጥተው፣ የተራበ አብልተው መጠጊያ አጥተው ከወረዳ ከሌላ ቦታ የመጣውን አስተናግደው አሳድረው ይህን ያህል የመተሳሰር፣ የመተሳሰብ፣ የመፈቃቀር፣ ይበልጥ ፍቅርን የሚያስተምር በዓል ነው ነው (መልአከ ሰላም አባ ወልደ ሥላሴ 19/01/12)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ዐምስት (ሙሔ ሰዒድ 16/05/2012 ቃ.መ)፡-*** ስሜ ሙሔ ሰዒድ እባላለሁ እምኖረው በጎንደር ክፍለ ከተማ ነው፡፡ እና ስለ መስቀል ጥምቀት ኹኔታ ብዙ ደስ የሚሉ ነገሮች አሉት፡፡ ያው እኔ በሃይማኖቴ ሙስሊም ነኝ፡፡ በጥምቀቱ የሚታየው ነገር አለባበሱ፣ በዝማሬ ነው የሚያከብሩት፡፡ በጥምቀት ዕለት ወጣቱ ለብቻ፣ ልጃገረዶች ለብቻ እና አለባበሳቸው የተለያየ ነው እና ይህን እንዴት ነው የምታየው በጥምቀቱ እምትታደምስ ለምንድን ነው?፡- እኔ የምኼድበት ዋናው ምክንያት በዓሉን በተለየ ኹኔታ ለማየትና ክብረ በዓሉ ስለሚስበኝ፣ በዓሉን የሚያከብሩት ከአለባበሳቸው ይጀምራል፡፡ አለባበሱ በጣም ደስ የሚል ነው፡፡ በማንኛውም ሰዓት የሚለበሰው ልብስ ሳይኾን በጥምቀቱ ከተራ ጊዜ የሚለብሱት አለባበስ ለየት ይላል ወንዶችም ሴቶችም፡፡ በየ ራሳቸው ግሩፕ የተለያየ ልብስ እነሱን የሚመስል ነው የሚለብሱ፡፡ ጥምቀት ስውልና ያነን ሳይ የበለጠ ውስጤ በጣም ደስ ይለኛል፡፡ በአካባቢው የሚኖሩ የሃይማኖቱ ተከታዮች ብቻ ሳይኾን የተለያዩ እምነት ተከታዮች በአንድነት ሲከብሩት ተመልክቻለሁ፡፡ ይህ ከማኅበራዊ ትስስር አንጻር ምን ፋይዳ አለው?፡- ማኅበራዊ ትስስሩ እንኳን ከዚህ ጎንደር ውስጥ ሙስሊምና ሌላም እምነት ተከተዮች ይቅርና ከውጭ ድረስ መጥተው የሚያዩትም ቱሪስቶች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ እንደገና የጎንደርን ጥምቀት ለማየት ሃይማኖት ይገድበዋል ብየ አላስብም፡፡ ምክንያቱም ይህ ባህላችን የኹላችንም በዓል ኹኔታ ስለሆነ በሃይማኖቱ እኔ የእስልምና ሃይማኖት ብከተልም ኢትዮጵያዊ በዓል እና ቅርስም ስለኾነ እኔ በተለየ ኹኔታ ነው የማየው የጎንደርን ጥምቀት እንደራሴም እንደኅብረተሰቡም ጥምቀትን ደስ ብሎን ነው የምናየው፡፡ ጎንደር ጥምቀት ላይ ያለው የወጣት የርስ በርስ ግንኙነት ምን ይመስላል?፡- ያለው ግንኙነት አኹን እኔ ለምሳሌ ክርስቲያን ጓደኞች አሉኝ፡፡ በዚህ በዓል ጊዜ ጠላ ይጠመቃል፣ ጥሪ አለ በዚያን ሰዓት የክርስቲያን ጓደኞቸ ላይ ኺጀ አከብራለሁ፡፡ የጥምቀት በዓል ከኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታው አኳያ ምን የተረዳኸው ነገር አለ?፡- በትክክል ጎንደር ከተማ እንደመኾኑ አኳያ ብዙ ለምሳሌ

የባህል ልብሶች፣ የተለያዩ ጥምቀት ላይ የሚካኼዱ ቁሳቁሶች በተለየ ኹኔታ የሚሸጡበት ሰዓት ነው። የጥምቀት በዓል ላይ እንደ ምሳሌ ልብሱም ምኑም የተለያየ እንደገና በራሱ በዓል ላይ ግሩፕ ኹነው የሚያሰፉት ልብስ ራሱ ያም የገበያ የሚያመጣው ጥቅም ነው። በዚያን ሰዓት ብቻ የሚለበሱ ልብሶች አሉ። ሌላ ጊዜ የማይለበሱ። እና እነዚያ፣ እነዚያ በመኖራቸው ጥቅም አለው። የበዓል ልብሰ በመሸጥ ሙስሊሙ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል?፡- በዚያን ሰዓት አወ በእርግጥ ሙስሊሙ ኅብረተሰብ ብቻ ሳይኾን ኹሉም ተጠቃሚ ነው። በዚያ ሙያ የተሳተፈ ለምሳሌ ነጠላዎች ቀሚሶች አወ ሙስሊም ሊሸጥ ይችላል። ከሸማቃ ጋር ስለሚያያዙ። የቱሪስት መስኅብነቱስ የጎንደር ጥምቀት ምን ይመስላል?፡- ከዚያ ላይ ባየኹት በበለጠ ኹኔታ ቱሪስቶች ይታያሉ። ጎንደር ውስጥ የማይኖሩ ከዐዲስ አበባም፣ ከተለያዩ ክልሎች አካባቢ ይመጣሉ። እየመጡ ጥምቀቱን ታድመው የሚውሉ አሉ። ምክንያቱም ጎንደር ላይ ጥምቀት ለየት ያለ ስለኾነ። የጎንደር ጥምቀት ለየት ያለ ነው የምንለው በምኑ ነው?፡- የሚመስለኝ ከዚህ 44 ታቦታት ይባላል 44 ታቦታት ሲባል የእያንዳንዱ ሌላ ቦታ ላይ አንድ ወይም ኹለት ብቻ ነው የሚያድረው ታቦት ማደሪያ ከዚህ ግን ቢያንስ እርግጠኛ ባልኾንም ከ፯፣ ከ፰፣ ከ፱ ያላነሱ ከአንድ ላይ ያድራሉ። በዚህ ጥምቀቱን ልዩ ያደርገዋል (ሙሔ ሰዒድ 16/05/2012 ቃ.መ)።

***ቃለ መጠይቅ ስድስት መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ፡-*** *መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ እባላለሁ። ጎንደር አዘዞ ቀበሌ 20 ነው የምኖረው። ስለ ጎንደር ስናነሣ ጎንደር ታሪካዊ አገር ናት። እና ከሌሎቹ አካባቢዎች ለየት የሚያደርጋት በታሪኳ፣ በባህሏ በአለባበሷ በተለያየ መልኩ ለኢትዮጵያ ምሳሌ የምትኾን አገር በመኾኗ ለየት ያለ አከባበር የምታደርገው ለዚህ ነው። ከጥምቀት በዓል ጋራ አያይዘው ቢያስረዱኝ? አንደኛ ከታሪክ በመነሣት ነው። ኹለተኛ ወጣቱም አዛውንቱም ሽማግሌውም ለየት ያለ አከባበር በተለይ በዛሬው ቀን የጥምቀት በዓል የደመቀ መኾኑ ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ታሪካዊ የኾነ ቀን ነው። በተለይ ጎንደር ጥምቀት ብሔር፣ ሃይማኖት ምናምን ሳይፈልግ ነው የሚያከብረው። ኹሉም ነገር ለየት የሚደርገው የሚስብ እና ለአብሮነት ነው የሚያከብሩት። ታዳሚዎቹ ከየት፣ ከየት ቦታ መጥተው ነው በዓሉን የሚያከብሩት?፡- ከተለያየ ቦታ ነው ሚመጡት በጎንደር ከንቲባ ባለሥልጣናትም ጥሪ ባደረጉት መሠረት ከወልቃይትም ጠገዴም ከኤርትራም የመጡ እንግዶቻችን ደስ ባለ ኹኔታ የሚያከብሩት በዓል ነው። ስለዚህ ጎንደር በጥምቀት የምታብብ እና የምታድግ ሀገር የኢትዮጵያ ምሳሌ የኾነች አገር ናት። ጥምቀትን በየ ዓመቱ በታሪካዊ ኹኔታ የምታከብር*

ሀገር መኾኑን ለወደፊትም ታሳያለች፡፡ የጎንደር ጥምቀት ለወጣቱ ምን ጠቀሜታ ይኖረዋል?፡- ለወጣቱ የሚጠቅመው ቀደም ሲል ከመጣው ታሪክ በመነሣት ለመቀበል እና ታሪኩንም ለወደፊት ለማሻገር ይጠቀምበታል፡፡ በጥምቀት ሰሞን ተጣልቶ የነበረ ወጣት ቢገናኝ ምን ይፈጠራል?፡- በዚህ በጥምቀት ሰሞን ማንም የሚጣላ የለም፡፡ ጎንደር የፍቅር ሀገር እንደኾነች ኹሉ በዚህ በጥምቀት ሰሞን የተጣላው ይታረቃል፡፡ ቂም የያዘው በጥምቀት ዕለት ምንም ቂም ጠብ የሚባል የለም፡፡ ኹሉም ግሩፕ ለይቶ የሚጨፍር ወጣት ነው፡፡ ወጣቱ ለወደፊት በምሳሌነት የሚያስነሣ ነው ጥምቀት፡፡ ወጣቶች በጥምቀት አይብላሆ መኔ እያሉ የሚገጥሟቸው ምንን የሚያስታውሱ ናቸው?፡- ግጥሞቹ ጀግንነትን፣ ባህልን፣ የተለያዩ ታሪካዊ ኹኔታዎችን የሚያሳዩ ናቸው የሚገልጹት፡፡ ምክንያቱም አንድም ከባህል አንድም ከታሪክ በመነሣት ደስ በሚል ኹኔታ የሚገልጽ ወጣት ነው በአኹኑ ሰዓት፡፡ ስለዚህ ለሀገር አንድነት ስለ ፍቅር ለማንኛውም ለእድገትም፣ ለልማትም የሚስብ ነው፡፡ የጥምቀት በዓል ዋናው ባህሉን መንተራስ ነው፡፡ “አይሎጋ ሽቦ” የሚለውም ጭምር፣ “አይብላሆመኔ” የሚለውም ጭምር ከአባቱ ከእናቱ ከባህሉ የመጣውን ባለ መርሣት ይህንም እያስታወሰ እየጨፈረ ነው በጥምቀት፡፡ አይብላሆመኔ አቀንቃኙ አውጪ ከላይ ተቀምጦ እንደልቡ እየተሽከረከረ ነው የሚያወጣ ለዚህ ምንድን ነው የተሰጠው ቦታ?፡- አውጪ እሽኮኮ ብለው የሚያሳዩት ምን መሰለህ አንደገና ሕፃናቶችን እሽኮኮ ብለው የሚያሳዩት ታሪክን ለወደፊቱ እንዲያጠኑ ባህሉንም እንዲከተሉ፣ ከመሬት ኹኖ ስለማይታያቸው ከፍ ብሎ ትክሻ ላይ ኹኖ ድምጹንም ኹሉንም ሆ እያለ የሚያሳይ ለወደፊቱም ያነን ታሪካዊ ቦታውን እንዲቀስሙ ነው (መቶ አለቃ ሞላ አድማሱ 12/05/2013 ቃ.መ)፡፡

**ቃለ መጠይቅ ሰባት (መ/ር ሰሎሞን ረዳ 16/05/2011 ቃ.መ)፡-** የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ያለው ሰባዊ፣ ማኅበራዊ ፋይዳ ምን ይመስላል?፡- ስሜ መሪጌታ ሰሎሞን ረዳ እባላለሁ፡፡ የአቋቋምና የዝማሬ መዋስዕት ከየንታ ዓንጉል ነው የተማርኩ፡፡ መምህር ነኝ፡፡ አኹን ግን በጎንደር ብዙ ዘመን ተቀምጫለሁ፡፡ በጎንደር ባህሉ እጹብ ድንቅ የሚያሰኘው አንደኛ የአየናቸው ዘጠኝ ታቦታት ከቤተ ክርስቲያናቸው ተነሥተው እስከ ፋሲል ድረስ ይኼዳሉ፡፡ በዋዜማው መንገዱ እየተጠረገ አኹን ጭማሬ አለ የዚያን ጊዜ ዘጠኝ ታቦት ነው የነበረ፡፡ ከዚያ ታቦቶቹ ሲመለሱ የ44 ሕዝብ በአንድ ላይ ኹኖ ሲመለሱ ኹለቱ አጣጣሚ ሚካኤልና ፊት ሚካኤል ያድራሉ፡፡ ያበሻ ሻሽ ያልጠመጠመ አያስረግጥም ክልክል ነው በጎንደር፡፡ አያስረግጥም የመቋሚያው አያያዝ ዐይነት አለው፡፡ የጸናጽል ዐይነት አለው፡፡ እያስተማርነ መቋሚያ አያያዝ ወደኋላ አያያዝ አለ፡፡ ዝም ብሎ አይያዝም፡፡ ጠቅላላው ነገር

አገሩ ግን ያስደረገው ነገሥታቱ ከጥንት ጀምሮ ከቦታው 4 ትርጓሜ፣ የአቋቋም ምስክር 4 ስላለ ያ ዘንዳ ያ ዘንዳ ኾኖ መቸም ድምቀቱ ዓይነት በዚህ አገር አለ አይባልም። ብዙ አገር በመላው ኢትዮጵያ ዙሬበታለሁ። ግን እንደጎንደር ያለ ባሂልና ተግባር የለም። አንድ ሊቅ ምን አሉ ቀደም በደብረታቦርና በደብረ ብርሃን የሚል ቅኔ አምጡ አሉት አሉ። ኋላ አንድ ባለ ቅኔ ስሙ ጠፍቶኛል። "ዮም ኮነ ዕለተ ብዙኀ ትፍስሕት፣ እስመ በደብረታቦር ቆመ ፈጣሪ ወ በደብረ ብርሃን ዳዊት" ተብሎ ይህ ኹሉ ታሪክ የኾነባት ሀገር ስለኾነ ግን ይህ ለወደፊት ብዙ ስለሚጠብቃት አኹንም ባህሉ ከዛ ደግሞ ዋናው ነገር ግን አቋቋሙ፣ ቅኔው፣ ትርጓሜ፣ ትመስገናለች። ኅብረተሰቡ በጎንደር ባህል ጎንደር ከተባለ በትግራይ፣ በዚህ በራያ አዘቦ ክቡር ነው። ጎንደር ተምሮ ከመጣ በላይ ነው እሚቀመጥ። ከድሮ ጀምሮ አባቶቻችን የተከበረች ሀገር ስለኾነች ጥምቀትን በጣም ነው የሚያከብረው። ነገሥታቱ፣ እነ ፋሲል ግንብ እነ ደብረ ብርሃን እነ ቁስቋም በሙሉ እንደተከበረ ነው እሚኖር ማለቴ ነው።

ወጣቱ ጥምቀትን እንዴት ያከብረዋ?፦ ወጣቱ ደግሞ በመስቀልና በጥምቀት ትንግርት፣ ትንግርት ነው ብታይ። ወጣቱ በጣም ነው ደስ የሚልህ ታቦቱ ሲወጣ ምንገዱን ያጠርጋል። ያዘጋጃል። አኹን ደግሞ ምንጣፍ ይጥላል። እየጣለ ደከመኝ፣ አመመኝ አይልም። ገና ታቦቱ ሲወጣ በደስታ ደስታ ታቦት መቼ ነው እሚወጣ እያለ ኩታራው ኹላ ይጠይቀናል። ነጭና ዐዲስ ልብስ እንደ ባህል ነው። ዐዲስ ልብስ ጥምቀት የደስታ ቀን ስለኾነ በጥምቀት ቀን ካባ ሸማ ይለበሳል። አንድ ጊዜ ካባ የለበሱ ያስረግጣሉ። አንድ ጊዜ ሸማ የለበሱ ያስረግጣሉ። በሕዝቡ ጥምቀት የደስታ ቀን ስለኾነ ነጭ ነገር ነው የሚለበስ። የነጩ ምሳሌ፣ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በደብረ ምጥማቅ "ወአልባሲኆሙ ኮነ ጸዐዳ ከመ በረድ" የደስታ ቀን ስለኾነ ነው። አኾን እኮ ሊቀ ጳጳሱ ኹላ ነጭ ነው የሚለብሱ።

የጎንደር ጥምቀት ምን ማህበረሰባዊ ፋይዳ አለው?፦ ምን ፋይዳ ጥምቀትማ ለማኅበረሰቡማ ፋይዳ አለው እንጂ። አንደኛ ለቤተ ክርስቲያኑ ጠቃሚ ነው። ኹለተኛ ማኅበረሰቡ ቃለ እግዚአብሔር ወዳጅ ስለኾነ ፋይዳ እየሰጠ ነው እንጂ። ፋይዳ ባይሰጥማ አይሰበሰብም ነበር። እንድናለን፣ እንፈወሳለን፣ ክረስቶስ የሠራውን ሠርተን አምላካችን እናገኘዋለን እያለ ነው እንጂ እያከበረው የሚያኼድ ያለ። ዘፈኑ "በወት ግባ በወት" እያሉ እናቶቻችን የሚዘፍኑ በሕይወት ግባ እያሉ ገጠሮች በሙሉ ኹሉ "የአገራችን ደብተራ እየው ቅኔውን" ሲመራ እያሉ እናቶቻችን በደምቢያ በወገራ የመጡት ኹሉ ዘፈናቸው ይኸ ነው። ከደምቢያ

ከወገራ ተነሥተው ይመጣሉ ጎንደር አይቀርም፡፡ በጥምቀት አይቀርም በፈረስ በስንት ነገር አለኮ!

***ቃለ መጠይቅ ስምንት ሲሳይ ቢተው፡-*** ምን እየጠጡ ነው? መጠጥ፣ ውሐ፣ ምግብ፣ እሸኮሸ፣ የጥምቀት ሆ፣ እያልነ ውለን ነው ስንሸኝ የምንጠጣ ሲጠማነ ይህን ነው የምንጠጣ አያሰክርም እሷ እንዳለቸው ዋጋውም አንድ ብር ነው፡፡ ጥሩ ነው ለዕለት ውሐ መጠጫ ጉልበት ሀብት ለጥምቀት አይሰሰትም መዘከር ነው (ሲሳይ ቢተው፣ 12/ 05/ 2013 ቃ.መ)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ዘጠኝ (በሪሁን አካላት 12/12/2011)፡-*** የጥምቀት ሹርባ ነው እሚሠራው ሹርባ ነው፡፡ እሚለበስም ነጠላ ነው፡፡ እርባን ነበር ድሮ ወጣቶች ሲዳሩ፡፡ ድሪ፣ ቀሚስ፣ መስቀል፣ ድኮት ስታየው ሳዱላው ልዩ ነው፡፡ ሳዱላ ዕድሜዋን እየለካህ ድርብ ሳዱላ አለ፡፡ ከፍ ስትል እየተደረበ ይኼድና እየጠበበ መጥቶ ሦስት እስክትወልድ ድረስ ይሠራል፡፡ ሳዱላው ሲደፈን እማውራ ኹናለች፡፡

የጎንደር ገበያ የሚደራው በጥምቀት ነው፡፡ ነጭ እጀ ጠባብ፣ ነጭ ሸሚዝ፣ ጎንደር ደስ የሚልህ በጥምቀት ዓመት በዓል አበባ መስሎ ነው የሚወጣ፡፡ የአገር ባህል ነው የሚለብሱ ቱሪስቶች ሲመጡ ባህሉን ነው የሚያዩ፡፡ አንዲት ሕንዳዊት ቱሪስት ከመድረኩ ላይ ኾና ከእናቷ ጋራ ጨቅላዋን የጎንደር ጥልፍ ቀሚስ ለብሳ አየቻት፡፡ ያች ልጅ የት ና የት ነው ያለችው መሰለህ፡፡ ያች ጨቅላ እንዲህ፣ እንዲህ ስትል ስታያት ስንቱን ሰው ሰንጥቃ መጥታ አቅፋ ሳመቻት፡፡ ቱሪስቶች ሲመጡ ቀሚስ ያለበሰውን አይወዱትም፡፡ ቱሪስቱ ሱሪ ለባሹን ትክ ብሎ አያየውም፡፡ ጥምቀት በየቦታው አለ የጎንደር ልዩ የሚያደርገው የቱሪስት መስኅቡ፣ የታሪካዊ ቦታነቱ ነው፡፡ ስመ ጥሩ ነው፤ የውጮችን በጣም ይስባቸዋል፡፡ ጎንደር ሲባል ስመ ገናን ናት፡፡ ጥምቀት በደብረታቦር፣ በእብናት፣ በክምከም ሞልቷል፡፡ የጎንደር ቅርስ ልዩ ነው፡፡

ወጣቱ አሞራ መስሎ ሲቀባበል ታቦት ማደሪያው አንስተህ ከቤተ ክርስቲያኑ እስክትደረስ ድረስ መሬት አትነካም፡፡ ድሮ የተወሰኑ ነበሩ አሁን ከመዘምራኑ ያልተነናነሰ ወጣት ነው ያለ፡፡ ዱርየውና መጥፎው እየተዋጠ መጥቷል፡፡ አዘዞ የተመሰረተ በወታደር ስለሆነ የተለያየ ብሔር ብሔረሰብ ይኖርበታል፡፡ ይሳተፍበታል፡፡ የጭፈራ ቤቶች እቀነሱ ነው፡፡ ጥምቀቱ ለወጣቱ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው የሰንበት ተማሪ በየ ደብሩ ትምህርት ቤት አሁን

ብዙውን ወጣት እያስተማረው መቷል፡፡ ባህሩ ሲቀደድ፣ ያለው ካህናት፣ ደስ ይላል በሪሁን አካላት 11፣11፣2011 ዓ.ም ቃለ መጠይቅ)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ዐሥር ትደነቅ ሙጩ፡-*** *የጎንደርን ጥምቀት በተመለከተ እርሰዎ እንዴት ነው የሚያዩት? ጥምቀት ጥምቀት ኹልጊዜ ነው ደስታ ዓለም፡፡ በልጃ ገረዶቹ እና በእናቶች መካካል የጥምቀት አከባባር እንዴት ይከበራል? ኹል ጊዜ ደስታ ነው ሌላ የለውም፡፡ ይኸው አለባበስማ ባህል እንለብሳለን ደሞ ነጭ ልብስ አለ የዓመት በዓል እሚለበስ ሌላ የለም፡፡ አኹን ለምሳሌ የዚህ መቀነት አላባሽ አለው፡፡ የሎዛ ከመጣችሁ የሎዛ*[116] *ለብሸ እመጣለሁ ሌላ የለም* (*ትደነቅ ሙጩ*፣ 12/ 05/ 2013 *ቃ.መ*)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ዐሥራ አንድ ሕጻን ናርዶስ ንጉሤ*** *ጥምቀትን እምናከብረው ከታቦቱ ጋራ አብረን ነው፡፡ እኛ በመጨፈር ጥምቀት ሲቃረብ ደስታ ነው የሚሰማን የሀገራችን ባህል ስለኾነ ልብስም ጎንደርኛ ይገዛልናል፡፡ ጫማም የሻሹ አስተሳሰሩ ጎንደርኛ ነው የድሮ* (*ሕጻን ናርዶስ ንጉሤ* 12/ 05/ 2013 *ቃ.መ*)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ዐሥራ ኹለት (ንጋቱ ችሎቴ 17/06/11)፡-*** *በጎንደር ጥምቀት ታድመህ ነበርና ልዩ የሚደርገው ምንድን ነው?፡- ጥምቀት በጎንደር ከሌሎች ልዩ የሚደርገው ኹሉም ታቦታት ወደ ፋሲል መዋኛ ገንዳው መኼዳቸው ነው፡፡ በድሮ በዐፄ ፋሲል የተመሠረተ በመኾኑ ጥምቀትን ልዩ ያደርገዋል፡፡ የጎንደርን ማለት ነው፡፡ ሌላው የተለያዩ ጭፈራዎች፣ ቱሪስቶችም በብዛት የሚታደሙበት በመኾኑ በጣም ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር የሚገኝበት ነው፡፡ በጎንደር፣ ከሌሎች ለየት የሚያደርገው ግን ቅድም እንደተናገርኩት የኹሉም 44ቱ ታቦታት ይባላል፡፡ የሚወጡት በዚያን ቀን ኺደው ወደ ታቦት ማደሪያው ቦታ ይኼዳሉ፡፡ ባሕረ ጥምቀቱም ከዚያው የፋሲል ገንዳው ስለሚሞላ ከዚያ ላይ ነው ገብቶ እሚዋኘውም እሚረጨውም ከዚያ ላይ ነው ማለት ነው፡፡*

*የጎንደር ጥምቀት ከማኅበራዊ ግንኙነት አንጻር ያለው ፋይዳ ምን ይመስላል?፡- የተለያዩ ቱሪስቶች ይመጣሉ ከዚያም ደግሞ ከሌሎች ወረዳዎች ይበልጥ ወደ ጎንደር ለመታደም ይመጣሉ፡፡ በዚህ አጋጣሚ የንግድ እንቅስቃሴውን እንዲፋጠን ያደርጋሉ፡፡ ከኢኮኖሚ*

---

[116] ሎዛ ማርያም ትባላለች በጎንደር ከተማ በስተ ምዕራብ አቅጣጫ አዘዞ አጠገብ ወደ አይምባ ከሚገኘው ከተራራው አናት ላይ የተመሠረተች ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ ክብረ በዓሏ ጥር 21 ቀን የአስተርዮ በድምቀት ይከበራል፡፡

ፋይዳው አንጻር፡፡ ከማኅበራዊ ግንኙነቶች የተለያዩ ቦታዎች ላይ መጥተው ተግባር ሲፈጥሩ የተለያዩ ባህሎችን የሚጋሩበት ኹኔታ አለ፡፡ የጎንደር ጥምቀት ለወጣቱ ምን አስተምህሮ ሰዋዊ ፋይዳ ይኖረዋል?፡- ምንድን ነው ከዚህ አንድ ሰው ጥምቀቱን ሲታደም እንደሰባዊ ጥሩ ጎኖችን ትመለከታለህ፡፡ ጥሩ ጎኖችን ወጣቱ አድንቆ የሚወስድ በመኾኑ ባህላዊ ኺደቶች ስለሚካኼዱበት ነው፡፡

የጎንደር ጥምቀት ከቅርስ ከመጠበቅ አኳያስ ምን ፋይዳ አለው?፡- ከዚህ ላይ አኹን ፋሲል መዋኛውና አጠቃላይ ክበረ በዓሉ እንደ ቅርስ የሚወሰድ በመኾኑ ይህን ጠብቆ ማቆየቱ እንደ ቅርስ ጥበቃ ይወሰዳል፡፡ ኹሉም ኅብረተሰብ በባለቤትነት በመጠበቅ ሃላፊነት ይወስዳል ማለት ነው፡፡ የግድ የቅረስ ጥበቃ ሃላፊዎች ቢሮች አደሉም፡፡ ቅርስን መጠበቅ ያለባቸው፡፡ ማኅበረሰቡ ኹሉም ተቆርቋሪ ነው፡፡ ትልቁ ጥምቀትን ለየት የሚያደርገው ይህ ስለኾነ፡፡ ኹሉም በደረጃቸው ካህናቱ፣ የሰንበት ተማሪዎች ለብቻቸው ይቆማሉ፡፡ መዘምራን ወንዶችም ሴቶች አንድ አካባቢ፣ ወንዶች ለብቻ እየኾኑ እንጂ ብዙ ጊዜ አንድ ላይ አይኾኑም፡፡ የተለየ ልብስ ለብሶ፣ ሌላው ግሩፕ የተለየ ልብስ ለብሶ ጭፈራ ይካኼዳል፡፡ ታቦቱ ሲኼድ ቀጤማ ተጎዝጉዞ ምንጣፍ ተነጥፎ ማኅበረሰቡ ጥምቀትን የሚያከብረው፡፡ ሌላው የሚሸጡ የተለያዩ የእደ ጥበብ ውጤቶች አሉ የሚሸጡ ብቻ ሳይኾኑ ለስጦታ የሚዘጋጁም አሉ፡፡ የውጭ ዜጋ የሚመጡ እየገዙ ይወስዳሉ፡፡ የጎንደር መገለጫ የኾኑትን የእደ ጥበብ ውጤቶች ከበዓሉ ጋር ሊኼዱ የሚችሉትን እንግዳ ለኾነው ሰው ስጦታ ይሰጣል (ንጋቱ ችሎቱ 17/06/11 ቃ.መ)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ዐሥራ ሦስት ንጋቱ ዘውዴ*፡-** የጎንደርን የጥምቀት ክብረ በዓል እንዴት ያስረዱኛል? በጎንደር ምርጥ ነው ዘንድሮ በተለይ ስናየው ድሮ አከባባሩ ጥሩ ነው፡፡ ደግሞ ደስ ይለናል፤ ዛሬ ያየነው ብዙም ወጣቱ ባህላዊ ነው የሚጨፍረው፡፡ ደስ ነው እሚል ዘንድሮ የወጣቱ በአንድ ላይ መጨፈር የጥምቀቱን አከባበር ያደምቀዋል፤ ባህላችን ስለኾነ፡፡ አንድ ዓይነት መልበስ የጎንደር ባህል ነው፡፡ የጎንደር ባህል ስለኾነ የባህል መልበስ ግድ ነው፡፡ ጥምቀቱ እሚደምቀው ነጭ በመልበስ ነው፡፡ ባህላችን ሃይማኖታችን ነው እሚከብረው ነጭ በመልበስ ባህላችን እንዲህ ስለኾነ (ንጋቱ ዘውዴ፣ 12/ 05/ 2013 ቃ.መ)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ዐሥራ አራት አስረስ ብርሃን*፡-** በጥምቀት ቀን ኹለት ሦስት ጀሪካን ይዘሽ ነው እየሸጥሽ ያገኘሁሽ ምንድን ነው የምትሸጪው?፡- ስሜ አስረስ ብርሃን ነው የምባል፡፡ ጄልጄስ ነው ምሸጠው ፈላጊ አለው የጥምቀት ውሐ የጠማቸው ሕጻናቶች ስለሚጠማቸው ግድ ነው

ይገዙናል፡፡ ሆ፣ ሲሉ ውለው ሲመለሱ፡፡ አንዱን ኩባያ አንድ ብር ነው የምሸጠው፡፡ ከጥምቀት ውጭስ ይሸጣል ይህ ጄልጄስ? ከጥምቀት ውጭ የሚገዛ የለም፤ አይሸጥም፡፡ ጥምቀትን በተመለከተ ነው (አስረስ ብርሃን፣ 12/ 05/ 2013 ቃ.መ)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ዐሥራ ዐምስት አራጌ ጠጋው፡-*** ጎንደር የታወቀ ነው ድሮም በጥምቀት 88 ነው ዕድሜዬ፡፡ ጥምቀትን የተጣላ ይታረቅበታል እንዴታ ትገሬ፣ አማራ፣ ኦሮሞ አይባልም ነበር ድሮ፡፡ የጥምቀት ቀርቶ አረ እንዳው በማንኛውም (አራጌ ጠጋው፣ 12/ 05/ 2013 ቃ.መ)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ዐሥራ ስድስት መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ፡-*** እኔ መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ እባላለሁ፡፡ ይኽ ጥምቀት መጥምቁ ዮሐንስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በዮርዳኖስ በተጠመቀበት ጊዜ ሰላምን፣ ፍቅርን በዓለም ላይ በሰው ልጆች ዘንድ ፍቅርና ትሕትናን ለማሳየት ለሰው ልጆች ድኅነትን በተለይም በሰው ልጆች ላይ የተጫነውን እዳ ደብዳቤ ለመቅደድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶ ራሱን ዝቅ አድርጎ የዓለም ሕዝብ በሙሉ በፍቅር በሰላም አብሮ የሚኖርበትን ተምሳሌት ያሳየበት ምልክት ነው ጥምቀት፡፡ ከዚህ ባሻገር በአኹኑ ሰዓት ወደ ራሱ ሰውነት እየተመለሰ ነው ሰው፡፡

ጥምቀት ሰዎች በሰላም ለመኖር ምን አስተዋጽኦ አለው?፡- ከተለያየ ብሔር ብሔረሰቦች ተውጣጥቶ መጥቶ የእስራኤል ትልቁ የሃይማኖት ክስተት የተከሰተበት ከዚህ ቦታ ነው፡፡ ትንሿ እስራኤል የምትገለጽበት ደግሞ ጎንደር ነው፡፡ ምክንያቱም ከተለያየ አካባቢ ጥምቀቱ ትውፊቱ ዋናው ቱባው ባህሉ ያለበት አገር ስለኾነ አካባቢ ስለኾነ ሰው አክባሪነቱ ባህሉ ሳይበወዝ ሳይከለስ በትክክል የሚሠራበት አገር ጎንደር ላይ ስለኾነ ለዚህ ከተለያየ አገር አውሮፓም ይኹን ከኢትዮጵያም ይኹን የተለያዩ ዲያስፖራዎች ውጭ ያሉት ኢትዮጵያኖችም በሙሉ መጥተው የሚያከብሩት፣ ሌሎችንም ይዘው መተው የሚያከብሩት እና ባህሉም በዩኒስኮ የተመዘገበው ከእነዚህ ትውፊቶች በመነሳት ነው፡፡

በጥምቀት የሚሸጠው ቅርጻቀርጽ እና አገልግል መያዝ አለ እነዚህ ምንን የሚያመለክቱ ናቸው?፡- መተዋወቅ ብቻ ሳይኾን መተጫጨትም አለ፡፡ ያልተገናኙት የሚገናኙበት ያልተዋወቁት የሚተዋወቁበት፣ ይህ ደግሞ ቀደም ሲል የነበረው አርበኝነት አገልግል ተሸክመው የሚኼዱት፣ ስንቅ ይዞ የሚኼዱት እነዚህ የአርበኝነት ምልክት፤ ዱላ ይዘው የሚኼዱት ወንድ ልጅ በጦር ሜዳ ኺዶ መክቶ አሸንፎ የመግባት ምልክትን የሚያሳይበት፣

ቆነጃጅቶች ደግሞ የተለያየ ጌጣጌጥ አድርጎ የሚሄደው የቁንጅና ምልክት የሚያሳዩት የተለያዩ ባህላዊ ገጽታዎች ይታዩበታል። የጎንደርን ታሪክ እና ማንነት የሚገልጹ ናቸው በጣም። የጎንደር ባህሉ ወጉ ልምዱ የሚታየው በጥምቀት ቀን ነው። በብትር አያያዙም በካሄዱም በእንግዳ አቀባበሉም እና በመስተንግዶው በሁሉም የጎንደር ባህል የሚታየው በጥምቀት ነው።

በአግልግሉ ውስጥ የሚያዙት መጊያጊያጫዎች መርፌ፣ ወስፌ፣ ምላጭ ማኅበረሰቡን ይወክላሉ ወይ?፦ አወ ይወክላል። የሰው ልጅ ከቤቱ ከወጣበት ጀምሮ አደጋዎች ሊያጋጥሙ ይችላሉ። ምላጭ የዚያን አደጋ አንዳንድ ነገሮች መቁረጫ፣ ወስፌዎች ደግሞ የተቀደዱ ልብስ ሊቀደድ ይችላል። ያንን ራሳቸው ጠግነው እንደነበረ አድርጎ የሚሄዱ አሁንም አለ። አንድ ወታደር ወታደርነቱ የሚገለጠው የመሳሰሉትን ነገሮች ሰውነቱ ያለአግባብ ሊቆረጥ ይችላል። አደጋ ሊያጋጥመው ይችላል። ያነን ጊዜያዊ እርዳታ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው። የጎንደርን ሽማግሌ ነገር ከመስፋት ጋርም ይመሳሰላሉ። የጎንደር ሽማግሌ አኹን እነዚያ ኹኔታዎች የተለያዩትን ለማጠጋጋት፣ የተበተኑትን ለማሰባሰብ፣ የተቀደዱትን ለመስፋት ሽማግሌዎቹን ተምሳሌት አድርጎ መውሰድ ይቻላል። ሴቶቹ ሌላ ሌላ ነገር ይይዛሉ። መስታውቱን ብልቃጡ ኹሉ ኩል መያዣ እነዚያን ኹሉ ይዘው ይኼዱበታል። እነዚህ የበዓሉ ምልክቶች ናቸው። ቀደም ሲል ከአባቶቻችን ተያይዘው በዓሉ ያወረሰን ትውፊቶች ናቸው። የጎንደር ጥምቀት እንግዲህ ትንሽቷ ኢትዮጵያ ሳይኾን ትልቂቷ ኢትዮጵያ በጎንደር ላይ የምትታይ ናት። በጎንደር አካባቢ ያለው ባህል ተከብሮ ተከባብሮ የምንኖርበት በዓሉ የሚከበርበት በሌላም ጎንደር ደጋፊ ነው። ከአክሱም ቀጥሎ ከላሊበላ ቀጥሎ ጎንደር የሥልጣኔ ማእከል ኹና ስታገልግል የቆየች ሀገር ስለኾነ የሥልጣኔ እምብርት ብለን መጥራት እንችላለን። ስለዚህ ከጎንደር ብዙ ነገር እንማራለን።

በጥምቀት ክብረ በዓል ላይ የመርከብ ቅርጽ ያለው እና ሴት ቆንጆ ትታያለች ሰይፍና ጎራዴ የያዙ ወጣቶች ይታያሉ። ምንን ይወክላሉ?፦ መርከቡ ሀገርን[117] ነው የሚወክለው። ሴቷ ደግሞ ኢትዮጵያን ነው የምትወክል። በመርከብ ላይ ተቀምጣ አንድነታችንን ክብራችንን ከአፍሪካ አገሮች ከፍ ብላ የምትታይ ኢትዮጵያን ለማሳየት ነው። እነዚያ ጋሻ ጦር ምናምን የሚባለው ደግሞ ከዚያ ከመርከቡ ላይ የሚታዩት የኢትዮጵያን ጀግንነት በምሥራቅ አፍሪካ

[117] አፍሪካ ለማለት የተጠቀሙት ቃል ነው።

ለጠላት ተንበርክካ የማታውቅ ኢትዮጵያን ለወደፊትም የማትንበረከክ ኢትዮጵያን ተከብራ እና ኀያል ኾና የምትኖር ኢትዮጵያ ከሀገር በላይ ኾና የምትታይ መኾኑን ለማሳየት የተቀመጡ ምስሎች ናቸው፡፡ እነዚህ ጎንደርን ነው በውነት ኢትዮጵያን የሚወክሉ

ሴቷ ጎንደርን ሰይፍና ጋሻ የያዙት የጎንደር ነገሥታትን አይወክሉም?፦ እናትነት ጎንደርን ትወክላለለች በአጠቃላይ እናቶች ኢትዮጵን ነው የሚወክሉት፡፡ ኢትዮጵያን አንቺ ብለን ነው የምንጠራት እናት በመኾኗ እና ወይዘሮ መርከብ ላይ የተቀመጠችው ኢትዮጵያን የምትወክል ናት፡፡ እና ጎንደር የኢትዮጵያ አንዷ አካል ናት ስለዚህ ጎንደር ማለት ኢትዮጵ ናት ኢትዮጵያ ማለት ጎንንር ናት፡፡ ስለዚህ ከፋፍለን አናያቸውም (መቶ አለቃ አስፋው ፈረደ12/05/2013 ቃ.መ)፡፡

**ቃለ መጠይቅ ዐሥራ ሰባት (አባ ገብረ ሥላሴ 03/06/11)፦** ጥምቀት በጎንደር ለየት ያለ ነው፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፡፡ እግዚአብሔር የፈቀደውን ከፍ ያደርጋል፡፡ የጎንደር ጥምቀትም እንደዚህ ነው፡፡ በመጀመሪያ ከተማው ሲመሠረት በነማንና እንዴት እንደተመሠረተ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ጎንደር ማርና ወተት የሚፈልቅባት ተብሎ በፈጣሪ የተነገረላት አገር ናት፡፡ ዋናው መሠረቱ ይህ ነው እግዚአብሔር አምላክ ለሙሴ ሕዝቤን ማርና ወተት ወደምታፈልቀው ወደ ከንአን ምድር ይዘህ ትገባለህ እንዳለው ኹሉ ጎንደርንም በቅዱሳኑ አማካኝነት ማርና ወተት የምታፈልቅ ነች ብሎ ገልጿል፡፡ ማርና ወተት የተባለው ቀጥታ የሥጋ ሳይኾን ምግበ ነፍሱንም የሚጨምር ነው፡፡ ነፍስን የሚያለመልመው ቃለ እግዚአብሔር ነው፡፡ ጎንደር መጀመሪያ “ወይነግሥ” የሚል ትንቢት ስለነበር ያ ትንቢት ነው ከዐፄ ሱስንዮስ ከዐፄ ፋሲል አባት ጀምሮ ከዚያም በፊት ይነገር ነበር፡፡ ትንቢቱ የተገለጠው ግን ለዐፄ ፋሲል ነው፡፡ በፈረሳቸው አማካኝነት ከዚህ ቦታ ላይ ከጎመንጌ ተነስታ ቤተ መንግሥቱ ላይ ጸበል ነበር ከዚያ ላይ ፈረሷን አገኟት፡፡ ከዚያ ቦታ ባህታዊ አግኝተው ወይነግሥ የተባለችው ይች ነች አልዋቸው፡፡ ሰባት ቀን ግብዣ አድርገው ባህታዊ አንድ ትልቅ ቦታ መጥተው ቤተ መንግሥቱ ከተሠራ በኋላም የመዝመም አቅጣጫ አሳይቶ ነበር፡፡ አባ ተስፋ ማርያም የሚባሉ አንድ ታላቅ ቦታ ባህታዊ መጥተው ቤተ መንግሥቱ እንዴት መጽናት እንዳለበት እነ ፊት ሚካኤል፣ ፊት አቦና ጊዮርጊስ መተከል እንደለባቸውና በዚህም ቤተ መንግሥቱ ጸና፡፡ ማርና ወተት የተባለው ትንቢት እንዲፈጸም የወንጌል ተርጓሚ ወጡ ከዚያ በኋላ ጎንደር የሊቃውንት የአቋቋም፣ ቅኔ የትርጓሜ ማእከል ኾነች፡፡ ከኹሉም በፊት የተሻለ በሃይማኖቱ የጸና ኾነ፡፡ ጎንደር በአብዛኛው ክርስቲያን ነው

ከነገሥታቱ ጥንካሬ የተነሣ ጥምቀቱም ከዚያ ጀምሮ የደመቀ ኾነ። የነግሥታቱ ቀናዒነትና ጥንካሬ ከዚያ ጀምሮ ጥምቀት በዓል በእግዚአብሔር ፈቃድ እየደመቀ መጣ። እንደ ምሳሌ ዐፄ ኢያሱን ብንወስድ ታቦት እስከመሸከም የደረሱ ንጉሥ ናቸው። ጻደቁ ዮሐንስም ሰሌን ሠርተው ለምግባቸው የሚጠቀሙ ጻድቅ ናቸው።
ከሚገበረው አይደለም የሚጠቀሙት። የሚገበረውን ለሕዝቡ ነበር የሚያውሉት። ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ማኅበረሰቡን አካባቢውን ቀርጸውታል። ከዚህ የተነሣ ኹሉም የዚህ ተሰጥኦ ስላለው የጥምቀት በዓል እየደመቀ፣ እየደመቀ፣መጥቷል። ሊቃውንቱም የአቋቋም፣ የቅዳሴ፣ የቅኔው በተለይ የአቋቋሙ ሃያ አራት ሰዓት ቢጮኹ ቢጮኹ አይደክሙም። በዚህ መልኩ ጥምቀቱን የጎላ ያደርገዋል።

ጉልህ የሚያደርገው አንደኛ አቀራረጹ ከዐፄ ፋሲል ጀምሮ ዐሥራ ሰባቱ ነገሥታት አብረው ቀርጸውታል። ተውልድ መሪውን ይመስላል። መምህሩ ከጎበዘ ተማሪውም እንደዚያው ነው። እነዚያ ነገሥታት ከቀረጹት ጥምቀተ ባሕሩን፣ አብያተ ክርስቲያናቱ እነቁስቋምን፣ ደብረ ብርሃንን ስናይ የጎንደር ጥምቀት ከጥንታዊ አንስቶ የጎንደር መገለጫ ኾኖ የመጣ ነው። ቤተ መንግሥቱ አብረው ከመንግሥታቸው በላይ ነበር የሚያዩት በዚህ በጣምራ የተመሠረተ ስለኾነ ኹሉም የኔባይነት እንዲሰማው አድርጎታል።

ሕዝቡ ከውስጥ ብቻ ሳይኾን ከውጭ ይመጣል። ከዐዲስ አበባ ያን ትተው ይመጣሉ። የግንቦቹ አሠራር ያለው ፍቅር ሲጀመር ጎንደር ላይ ያለው የጥምቀት ድባብ ፍቅር ነው። ጌታችን አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳሳየው የጥምቀት በዓል ፍቅር ነው። ፍቅር ካለ ደግሞ ኹሉ ነገር ማንኛውም ሰው ይታደማል። ማንኛውም የእምነት ተከታይ በጥምቀት ቀን ጎንደር ይታደማል። መስለውም ኾነ በግልጽ ያለው መንፈሳዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ማኅበራዊ፣ አከባበር ስለሚያስደስታቸው በበዓሉ ይታደማሉ። ለምን ቢባል የታዩት ትራቶች የፍቅር፣ የሰላምና የዕውቀት ናቸው። እነዚህ የተካተቱበት ስለኾነ ማንኛውም ሰባዊ ፍጡር ደግሞ እነዚህን የሚጠላ ስለሌለ ከውስጥም ኾነ ከውጭ የእምነቱ ተካታይም ኾኑ ከእምነቱ ውጭ ያሉት ይታደማሉ። ግዴታ መልካም ነገር ስላየ ለመታደምና ለመኼድ የሚያስገድደው ሌላ ሰው ሳይሆን ተፈጥሯዊ ባሕርይው ነው። ዘና ብሎ ተዝናንቶ መጥቶ ተዝናንቶ ይኼዳል። ካህናቱ ክዋኔ በበለጠ የሚያብራሩ ሊቃውንት ቢኖሩም ምስጋና ከመላእክት የመጣ ነው።

መቋሚያ የጌታችን የእጸ መስቀሉ ተምሳሌት ነው፡፡ ከአስጥራ እስከ ቀራንዮ ድረስ ደፋ ቀና እያለ የደረሰበትን እና ከሐና ወደ ቀያፋ ለሰው ልጆች ሲል የተንገላታበትንንና ተመላለሰበትን የሚመለከት እና ለማሰብ ነው፡፡

ለኛ ቆስለሐል፣ ደክመሐል የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ የሥጋና የመለኮትን መዋሐድ ይመለከታል፡፡ መቋሚያ መመርኮዣ ነው ምርኩዝ የሚያቆምና የሚያጸና ነው፡፡ ተጠመቀ፣ ወረደ፣ ሞተ ተነሣ የሚል አንድምታ አለው፡፡ ጥምቀት የሥላሴ ልጅነትን የምናገኝበት ነው፡፡ ሰይጣን ይርቃል ከእግዚአብሔር ጋራ መኖር ነው፡፡ እግዚአብሔርን የያዘ ኅብረተሰብ ደግሞ ሰላምን የሚሰብክ ኅብረተሰብ ስለኾነ የጎንደር ጥምቀት ይህ ነው፡፡ የጥምቀት በዓል አስተምህሮ ማንኛውም ሰው እንደሰው ሰውኛ አንድ ቢኾንም በቋንቋ፣ በሃይማኖት በአካባቢ የተለያዩ ሰዎች ተስማምተው እንዲኖሩ የሚያስችል ነው፡፡ ምክንያቱም ጥምቀት ለሰው ልጆች ብቻ የመጣም የተገኘም በመኾኑ የሰላምና የፍቅር ምንጭና አስተምህሮ ስለኾነ የሰው ልጆች ተከብረው እንዲኖሩ ያስችላል፡፡

**ቃለ መጠይቅ ዐሥራ ስምንት አብነት ሰማኝ፡-** ስሜ አብነት ሰማኝ ነው፡፡ የጎንደርን ቀሚስ ለብሰን ነው ይህ ጥልፍ ቀሚሱም መቀነቱም የጎንደር ነው አኹን የለበስሽው? አወ ጎንደር ነው፡፡ የጎንደር እንዴት ነው የሚለየው?፡- ጎንደሬ በልብሳችን እንለያለን፡፡ አለባበሳችን ይለያል፡፡ መቀነቱ ትፍትፋት አለው ጌጣጌጡ ምንድንን ነው የሚያመለክተው? አረንጓዴ ብጫ ቀይነቱ የኢትዮጵያ ምሳሌ ነው፡፡ እንደገናም የእመቤታችን የመቀነቷ ምሳሌ ነው፡፡ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በሦስትነት ስለሚመሰል አረንጓዴ ብጫ ቀዩ የሱ ምሳሌ ነው፡፡ እንዲኹም ለኖሕ የቃል ኪዳኑ ምሳሌ አርጎ የሰጠን ነው፡፡ ከሕፃን ጀምሮ ከጥንት ጀምሮ የተሰጠን ነው ከአባቶቻችን የሕፃናት ጥምቀትን ማክበር፡፡ ከሰማዬ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ለኛ ብሎ ሥጋችን ለብሶ ተወለደ (አብነት ሰማኝ፣ 12/ 05/ 2013 ቃ.መ)፡፡

**ቃለ መጠይቅ ዐሥራ ዘጠኝ ዘውዱ ይርጋ፡-** ዘውዱ ይርጋ የመጣነው ጎጃም ነው የራያ ልብስ ባህላችን ነው ብለን ነው የለበስነው፡፡ ጎንደር በዓሉ ስለሚያምር ጥምቀቱ ደስ የሚል ስለኾነ በእርግጥ ኹልም ቦታ ጥምቀት አለ የጎንደር ጥምቀት ይለያል፡፡ የጎንደርን ጥምቀት ለመታደም ያስፈለጋችሁ ምንድን ነው?፡- ለየት ያለ ነው፡፡ በጎንደር ጥምቀት የራያ ልብስ ለብሰን የመጣነው በጎንደር ጥምቀት ደስ ይላል፡፡ ጎንደር ጥምቀት ደስ ስለሚል ጎንደር ላይ

ተገኝተናል፡፡ የጎንደር ጥምቀት ለየት ያለ ስለሆነ ባህሉ ደስ የሚል በዓል ነው የጎንደር ጥምቀት፡፡ ብዙ ደስ የሚሉ ነገሮች አይተናል፡፡ የሕዝቡ እንግዳ አቀባበል፣ የጥምቀቱ ሥርዓት ኹሉ በጣም ደስ የሚል ነው፡፡ ጥምቀትን ለማክበር መጥተና፡፡ የሕዝቡ የእንግዳ አቀባበል የጥምቀቱ ሥርዓት ደስ የሚል የሚያምር ነው፡፡ ጠብ፣ ግጭት የለም (ዘውዱ ይርጋ 12/05/2013 ቃ.መ)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ሃያ ይታያል ደመወዝ ፡-*** ይታያል ደመወዝ እባላለሁ፡፡ ከደብረ ወርቅ ምሥራቅ ጎጃም ነው የመጣሁት፡፡ እና የጎንደር በዓል በጣም ደስ ይላል የዛሬ ኹለት ዓመትም መጥቸ ነበር፡፡ የጎንደር ባህል በጣም ደስ ይላል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚከበረው ጥምቀት ኹሉ ጎንደር ደስ ይላል፡፡ ኹሉን አይቻለሁ፡፡ በየ ዓመቱ ጎንደር እየመጣሁ አከብራለሁ፡፡ የእራያዎች አለባባስ እና አጨፋፈር ደስ ስለሚል እስኪ ይህን የራያ ልብስ እስኪ ለብሰን ጎንደር እንዋል ብለን ነው የመጣነ፡፡ እይው ጎንደር መጠናል፡፡ አኹን እኔ የኾነ ቦታ ላይ ጎድገዋዲት ሆቴል ገባን፡፡ አኔና እሱ (ጓደኛዬ) ጥልቅ ብለን ስንገባ ወንበር ሰው በዝቶ ሞልቷል፡፡ ኑ፣ኑ ብለው ብድግ ብደግ ብለው ከዚህ ቁጭ በሉ፣ ከዚህ ቁጭበሉ፣ ሲሉን በጣም ነው ደስታ የተሰማን፡፡ ዐልጋው በጣም ውድ ነው፡፡ ጠይቀነዋል በበዓል ምክንያት ነው ብለውናል፡፡ ዐልጋው በጣንም ውድ ነው፡፡ እንዴ ጎድጓዲት ኺደን የጎንደር ልጆች ብድግ ብድግ ብለው ነው ያስቀመጡን እንግዳ ተቀባዮች ናቸው፡፡ አለበሳቸው አንድ ዓይነት ነው፣ አካሄዳቸው አንድ ዓይነት ኹሉ ሥርዓታቸው፣ ጭፈራቸው አንድ ዓይነት ነው፡፡ በቃ ጎንደር ለየት ያለ ነው (ይታያል ደመወዝ 12/05/2013 ቃ.መ)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ሃያ*** **አንድ (*መ*/ር *ዳዊት ሥራው* 12/19/2011)፡-** የጎንደር ጥምቀት ለማኅበራዊ ልማት ያለው አስተዋጽኦ ለየት ያለ ባህል ነው፡፡ የጎንደር ጥምቀት ከሕፃናት እስከ አረጋውያን የሚያከብሩት ነው፡፡ በዓሉ ከሕፃናት እሰከ ዐዋቂ ነጭ ለብሰው ነው የሚያከብሩት፡፡ ነጭ የምን ተምሳሌት ነው? የመጠመቁ፣ የመንጻቱ የንጽሕና፣ የደስታ የትፍስእት ምሳሌ ነው፡፡ ከሻሽ ጀምሮ አጠቃላይ በነጭ ልብስ የሚያከብሩት ለዚያ ነው፡፡ መጀመሪያ ወደ በዓሉ ሲመጣ ከውስጥ ያለውን ከቂም ከበቀል፣ ክፋትና ክፉ ተግባር እንደ ድሪቶ ጨርቅ አውልቆ ጥሎ ነው፡፡ ወደ ታቦት ሲመጣ የበደለ ክሶ የቀማ መልሶ ውስጥን ንጹሕና ጽዱ አድርጎ ነው የሚቀረብ፡፡ በዚህም የአልባሳቱ ጸዓዳ መኾን ውስጣዊና ውጫዊ ንጽሕናን የሚመለከት ነው፡፡

የጥምቀት በዓል ነጻነትን የሚሰብክ ነው፡፡ ሃይማኖታዊ መነሻው ነጻነትን ማወጅ እስከኾነ ድረስ ሥጋዊና መንፈሳዊ ነጻነትን የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ቀን አሽከር፣ አለቃ፣ ምንዝር በአንድነት የሚያከብሩት ነው፡፡ በነጻነት አከአረጋዊያን እስከ ሕጻናት አይቀርም፡፡ የጥምቀት አከባበር በጎንደር ምን አንድምታ አለው? ከደብረታቦር ተነስኝ ከዚህ የመጣሑት የጥምቀት አከባባር በጎንደር ለየት ያለ በመኾኑ ነው፡፡ የእንግዳ አቀባበሉ ለየት ያለ ነው፡፡

በጥምቀት ዕለት በአብዛኛው የጠፋ እቃ ተመልሶ ለባለቤቱ ይሰጣል፡፡ ይህም የበዓሉን ፍጹም መንፈሳዊና የንጽሕና ትሳሌት መኾኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በጥምቀቱ በዓለ ክብር ብር ይጠፋቸዋል፣ ሞባይል ይጠፋቸዋል፡፡ የተገኙ እቃዎች በእስፒከር ተነግሮ የሚመለስበት ኹኔታ አለ፡፡ አንዳንድ ሰርጎ ገብ ካልኾኑ በጥምቀት በዓል በጎንደር ንብርት የሚመለስበት ነው ያለው ህግና ስርዓት፡፡ የጎንደር ሕዝብ በጥምቀት በምንም ዓይነት ስርቆትን በጣም ያወግዛል፡፡ በጥምቀቱ በዓል የሻሽ፣ የመቀነት፣ የጥልፍ ቀሚስ የተለያዩ ሥሬት፣ መዋቢያ ይጠቀማሉ እነዚህ የምን ተምሳሌቶች ናቸው?

እናቶቻችን የተለያዩ መዋቢያዎችን መልበሳቸው ማኀበራዊ ደረጃቸውን፣ ዕድሜያቸውን፣ ሰባዊ ማንነታቸውን ማሳወቂያ ነው፡፡ መቀነቱ ድሮ አባቶቻችን የጎንደር ነገሥታት የጀግንነት፣ የክብር የአይደፈሬነት ተምሳሌት ነው፡፡ መቀነት ተፈታ ማለት የጎንደር የነገሥታቱ የክብር የጀግንነት ተነካ ማለት ነው፡፡ ቀለማቱ የሰባቱ ቀለማት ተምሳሌት ነው፡፡ ይህ "ለኖሕ የተገባለት ቃል ኪዳን" ይመለከታል፡፡ "እያማስና በማየ አይኅ" የሰጠውን ምልክት የሚገልጽ ነው፡፡ በዚህ የጎንደር ጥምቀት በሰዎች ዘንድ ቅራኔን ማራቂያ መኾኑን ያጠይቃል፡፡ ወጣቶቹ በጥምቀት ቀን ወደ ታቦቱ እጅ ለእጅ ተያይዘው ያከብሩታል ይህ ምን አንድምታ አለው? ወጣቶቹ በጎንደር የሚገኙ በኮሚቴ ተዋቅረው ነው በዓሉን በአንድነት ለማክበር መኾኑን የጎንደር ትስስርን፣ የፍቅር አገር መኾኗን፣ ‹‹ኢንድግ ማኀበረነ›› አንድነትን በአንድነት መሠረት መኾኑን የሚያጠይቅ ነው፡፡ ባሕረ ጥምቀቱ በጫካ መሸፈን አዕዋፋቱ በብዛት አሉ እንዴት እንደዚህ ተጠብቆ ኖረ?

44ቱ ታቦታት ያለባት ከተማ በመኾኑ ለየት ያደርጋታል፡፡ ወጣቶች በአንድነት መንፈስ ጥንካሬ ታጥረው የሚያከብሩበት ነው፡፡ በአካባቢ ያሉ ቆሻሻዎችን በጽዳት መልክ የሚጸዱ ናቸው፡፡ የጎንደር ጥምቀተ ባሕር ከዓመት እስከ ዓመት ኹሌም ጽዱ ኾኖ ነው የሚገኘው፡፡ የአዕዋፋቱ የደኑ የአካባቢው ልምላሜ የወንዙ ኹኔታ የባሕረ ዮርዳኖስን የሚተካ ነው፡፡

ሥራቱም ዮርዳኖስ ስለኾነ ዮርዳኖስ መኼድ አይጠየቅም፡፡ ዮርዳኖስን በጎንደር ማየት ነው፡፡ በጠበሉ የተጠመቀው፣ የጠጣው ባሕረ ዮርዳኖስ እንደተጠመቀ ይኾንለታል የጎንደርን ባህል ለማክበር ከዘጠኙ ክልሎች በየዓመቱ ለቁጥር የሚያዳግት ሰው ይመጣል፡፡ ከውጭ የሚመጣው የቱሪስት ፍሰት እየጨመረ ነው የሚመጣ ከኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ አንጻር ጎንደር እጅግ የላቀ ነው፡፡ ከአገር ውጭም ኾነ ውስጥ የሚመጡት በዓሉን ለማክበር የመጡት ባህላዊ አልባሳትን፣ ጌጣጌጦችን፣ መዋቢያዎችን ገዝተው ይኼዳሉ፡፡ ፈረንጆች ራሳቸው አልባሳትን ገዝተው ይኼዳሉ፡፡

አገልግል የመያዝ ነገር ምን አንድምታ አለው? በዚያን ሰዓት በበዓሉ አምሮባቸው የሚታዩ ናቸው፡፡ ኮረዳዎች ያላገቡት የሚይዙት ሲኾን ለመታጨት ለመፈጨት የሚያበቃቸው ነው፡፡ ሌላው አገልግሉ ጌጣጌጥ ያለው መኾኑ የጎንደርን ውብነት የሚወክል ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃልም አለው፡፡ ‹‹አንቲ ውእቱ መሶበ ወርቅ›› እንዳለው ጥምቀትን የሚወክል ነው በጥምቀት መሶቡ የእመቤታችን ኅብስቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ተምሳሌት ነው፡፡ ጭፈራ፣ ዳውጃ የማንጠፍ ኹኔታ በወጣቶች ይታያል?

የጎንደር ጥምቀት ለወጣቱ ብቻ ሳይኾን ፋይዳው ለሌላም እምነት ተከታዮች በሙሉ ያገለግላል፡፤ የተጣላ የሚታረቅበት፣ ፍቅርን ሰላምን፣ የሚያበስር ነው በዚህ ለወጣቱ ትልቅ ፋይዳ አለው፡፡ ገበያው የሚደራበት ለወጣቱም የሥነ ምግባር ጠቀሜታ አለው፡፡ የጎንደር ጥምቀት ክብረ በዓል ከሌሎች አካባቢ የጥምቀት በዓል በጣም ልዩነት ዓለው፡፡ ታዳሚውን ሕዝቡ በቁጥር ለመግለጽ አይቻልም፡፡ እየሩሳሌም ማለት ይቻላል፡፡ በዓሉ ላይ ተቀምጠን ምግብ አያምረውም፡፡ ቁሩ ሀሩሩ ኹሉ ሳይገድበው ያከብሩታል፡፡ ጥምቀተ ባሕሩ ብቻ ከዋዜማ ሰዓት ጀምሮ ከዋዜማው ባሕረ ጥምቀቱ ለመግባት ሲል ምግብ ላይቀምስ ይችላል፡፡ ወጣቱ፣ መኳንንቱ፣ አዛውንቱ፣ መሳፍንቱ፣ ሕፃናቱ ኹሉ ምግብ ሳይበሉ ኼደው የሚታደሙበት ኹኔታ ኹሉ አለ (ዳዊት ሥራው፣12/19/2011)፡፡

**ቃለ መጠይቅ ሃያ ኹለት (ጌትነት አመራ፣ 13/05/2011 ቃ.መ)፡-** ስሜ ጌትነት አመራ እባላለሁ እድሜየ 60 ነው፡፡ የጎንደርን ጥምቀት እያከበሩ ነው ያገኘኹዎት ክብሩ ምን ይመስላል?፡- በዓሉን በጣም ነው የሚያከብረው ወጣቱ ምንጣፉን በማንጠፍ ሆ በማለት፣ በሆታ፣ በጭፈራ፣ በጣም የተለየ በጎንደር ክፍለ ሀገር በስሜት በፍቅር ነው የጎንደርን ጥምቀት የሚያከብረው፡፡ ቀጣይም እንደዚህ ያለ የእናት የአባቶቻችን አለባበስ ባህል

በመያዝ ይህንን ነገር በጣም እንደምናከብረው አዛዉንቱን፣ ወጣቱን፣ ቀሳውስቱን በአንድ ላይ በመያዝ በአንድነት የምናከብረው ነው። የሕዝቡ ብዛትና ከተለያየ ቦታ መጥቶ የጥምቀትን በዓል ሕዝቡ የሚያከብርበትና ሕዝቡ እንደዚህ የመብዛቱ ምክንያት ምንድን ነው?፦ የሕዝቡ መብዛትና የጥምቀቱ መድመቅ የጎንደር አካባቢ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ፈረንጆችም ከአገራቸው ከአፍሪካ እየመጡ የኛን ባህል ፎቶ በማንሣት፣ እስክስታ በመወወረድ ወደ ሀገራቸው ወስደው በማስተዋወቅ የማያደርጉት ጥረት የለም። ፈረንጆች ሳይቀር አውራው እንደተነካበት ንብ ሆ ብለው መጥተው ነው እየተሳተፉ ጥምቀቱን የሚያከብሩት። የጥምቀት ክብረ በዓል በጎንደር ምን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ አለው ይላሉ?፦ እንዴ በጣም አለው እንጂ የጥምቀት በዓል በጎንደር እኮ የማያስተምረው ነገር የለም። ለልማትም፣ ለጸጥታውም ለሰላሙ የሚጠቅም ነው።

የተለያዩ አልባሳት በክብረ በዓሉ ተመልክቻለሁ ምን አንድምታ አላቸው?፦ ጃኖው የጎንደር ባህል ለዓለም የሚያስተዋውቅ ነው። ሴቶቹ ደግሞ መቀነት የሚባል ነገር አለ በአረንጓዴ ቀለም፣ በቢጫ ቀለም፣ በቀይ ቀለም እያደረጉ ለብሰው እያሸበሸቡ ሲታዩ እንኳን ለኛ ለተወላጆቹ ለዓለምም የሚስብ ነው። በጣም ደስ ይለኛል። የጥምቀት ዕለት የተለያዩ ዘፈኖች ይዘፈናሉ "ለጥምቀት ያልኾነ ቀሚስ ይበጣጠስ" ይባላል እንዴት ነው?፦ ኧረ በስመ አብ የዛን ቀን ጥሩ አስታወስከኝ እንዳውም የገበሬ ልጅም ከቤት አይውልም አባትየው ነው ከብት ሲጠብቅ የሚውል ብትር፣ ብትሩን ይዞ ሆ ብሎ ነው ገጠሩ፣ ራሱ ገጠሩ ወደ ጥምቀቱ የሚኼደው። ከብቱን ራሱ አባቱ፣ አባቱ ነው ከብት የሚጠብቅ፣ እንዴት ብሎ ከቤት ይውላል፣ ሌላው ነጉዶ ነው የሚኼደው፣ በዚያች ቀን ኺዶ ወጣቱ ጥምቀትን ካላየ እሽ አይልም፤ ጦርነት ነው የሚያነሣ፤ ከአባት ከእናቱ ጋር እናት አባቱም እነሱ ደግሞ የኛን ይረከቡ እያሉ ያስኼዳሉ፤ ይፈቅዱላቸዋል። የጥምቀት ሰሞን በጎንደር ገበያውስ እንዴት ነው?፦ ውይ በገቢያው እማ የጥምቀት ሰሞን ትልቅ ገበያ አለ ማለት ይቻላል። ከጥምቀት በፊት አልባሳቱ ከጥምቀት ውሎ ሲመለስ በጠላ ቤቱ፣ በጠጅ ቤቱ፣ ኬክ ቤቱ የዚያን ቀን እማ ምኑን ብለኸው ቃውጢ ነው እንጂ። ከዓመቱ እንዲህ እያለን ያድረሰነ፣ ዓመት፣ ዓመት ይድገመነ፣ እየተባለ የዚያን ቀንማ "ለጥምቀት ያልኾነ ቀሚስ ይበጣጠስ" የጥምቀት ያልኾነ አንገት ይበጣጠስ፣ ለጊዮርጊስ ያልኾነ፣ ለሚካኤል ያለኾነ፣ ለተክለሃይማኖት ያልኾነ ይበጣጠስ እያለ ነው ወጣቱ የሚዘፍነው የኔ ወንድም።

ጥምቀት በዓል ላይ የሌላ ሃይማኖት ተከታዮች ሲሳተፉ አይቻለሁ ይህ ማኅበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል?፡- ይህ በውነቱ እኔ እንዳየሁት ሙስሊምም ቢኾን ተደስቶ ነው የሚውለው አሸብርቆ ወጣቱ የሙስሊም ሴቶች ወጣቶች አዛውንቶች በባህላቸው አብረው ተደስተው ነው የሚውሉ፡፡ በአካል ስላየሁት ነው፡፡ በጥምቀት ቀን ልጃገረዶች አገልግል መያዝ ከጥንት ከአባቶቻችን ጀምሮ የነበረ ነው፡፡ ከእናቶቻችን አገልግሉ ምግብ ይቀመጥበታል አገልግሉ የሰውልጅ ነው የሚመስለው፣ አሰፋፉ ምኑ ይማርካል እኮ ውቢቷ ጎንደር ተባለችውን የሚመለከት ነው፡፡ አንግተውት ነው የሚኼዱት ሴቶችም ወንዶችም፡፡ ወጣቱ ‹‹ደጋጎች መጀን›› ይላሉ ሙስሊሞች ሲናገሩ፡፡ ያገሬ ገበሬ ሲያርስ ‹‹ኧረ ተው ተመለስ እሱ ነው ደምበሩ››፣ ጎበዝ የተለመው አይጠፋም ደንበሩ›› ይላሉ፡፡ ወጣቱ የሚገራው በጎንደር ጥምቀት ነው፡፡ ወጣቱ ጥምቀትን በጣም ያከብራሉ፡፡ ግብረ ገብነትም አላቸው፤ አይቻቸዋለሁ፡፡ በዚህ በተወሰነ ዓመት ወጣቶች ሰውን በጣም ያከብራሉ፡፡ በጥምቀት በዓላት ወጣቱ ስላከበረ አደለም እንዴ በዚያን ቀን ምንጣፉን እያነጠፈ፣ ታቦቱን እየከበከበ የሚያስገባ፡፡ እንዴ ሽማግሌች ዳር ለዳር እያሉ ኮበሌውም እየፈከረ ታቦቱ ዙሮ እስኪገባ ወጣቱ ነው አሌንታችን፡፡ የታቦት ማደሪያውን የሚጠብቀው ኅኅብረተሰቡ ነው፡፡ የጎንደርን ጥምቀት ለማክበር ከገጠር፣ ፈረሱን በቅሎውን ይዞ ከአራቱም ማእዘን ይመጣል፡፡ ንብረቱን እያስጠበቀ ከዓመቱ ያድረሰን ለማልት ይመጣል፡፡ በተለይ ጎንደር ከአራቱም ማዕዘን ነው የሚዘንበው ኅብረተሰቡ የከተማው ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ገጠሬው ነው በአብዛኛው ገንፍሎ የሚመጣው፡፡ ጥምቀትን ሳይታደም ቢቀር የጎንደር ሰው እንዴት ያየዋል?፡- ኺዶ ጥምቀትን ሳይጫወት ሳይዘፍን ከዋለ ዓመት የሚደርስ አይመስለውም፤ ውነቱን ለመናገር፡፡ ኺጀ ከዚያ ፈክሬ፣ ዘፍኘ ስለት ካለብኝ ኺጀ አድርሽ ታልኾነ ዓመት የምደርስ አይመስለኝም ከራሴ ጀምሮ፡፡ ተስሌም ከኾነ ምንም ከኾነ ከጥምቀቱ ካልኼድኩ ዓመት የምደርስ አይመስለኝም፡፡ እና ስለዚህ ያን ማድረግ ግድ ነው፡፡

የጎንደር ከጥምቀት ያለው ታሪክ ምን ይመስላል?፡- የጎንደር ታሪክ እኮ አኹን እሚነገር አይደለም፤ የቆየ እኮ ነው፡፡ አያት ቅማንቶቻችን ናቸው ያቆዩን፡፡ እኛ ደግሞ እነሱ ያቆዩንን ይበልጥ ለማሻሻል ነው የኔ ወንድም፡፡ እነሱማ አስረከቡ እኮ ብዙ፣ ብዙ ነገር አድርገው ኼዱ እኮ እነሱማ፡፡ የነሱን ምልክት አድርገው አሳይተው መሠረት ጥለው ኺደዋል ያን መሠረት እንዳይፈርስ ነው እኛ ማድረግ ያለብን፡፡ ጎንደርና ጥምቀት ትስስራቸው በዚያች ዕለት ከአባት ከእናታችን የወረስነው ስለኾነ በዚያች ዕለት “ድር ቢያብር አንበሳ ያስር”

ተባብሎ ሆ ብሎ ነው የሚኼደው ወደ ጥምቀተ ባሕሩ፡፡ አውራው እንደተነካ ንብ ማንም ገላጋይ የለውም፤ ጥምቀት ኺድ የሚለው የለም፤ በራሱ ፍላጎት በወኔ ከዓመቱ አድረስኝ እያለ ነው ተነሥቶ የሚኼድ፡፡

ጃኖ ስትል ጃኖ ለጎንደር ምልክታችን ነው፡፡ ባንዲራችን ነው፡፡ እንዳው ጃኖ ለብሶ ሲኼድ አንተ ባትለብሰው እንዳው በውነት ሌላው ለብሶ ሲኼድ ሰውነትህ ፈተት አይልም? ምን ያህል ነው ደስ የሚልህ? ዐቅሙ ካለህ እስከ ሦስት ቀን ያን ለብሰህ ብትውል ምን አለበት፡፡ በጥምቀት የጎንደር ሞያ የሚለካበት ዶሮ ወጥ በለው፣ ጠጁ በለው፣ ጠላው በለው የተለያዩ ምግቦች ነው የሚቀርቡ፣ የጎንደር ባህላዊ ምግቦች ፈረንጆች ሲመጡ በጣም ይወዱታል፡፡ በቃ ፈረንጆች ሲመጡ በውነት እየሮጠ፣ እኽ፣ እኽ እያሉ ያን ለመቅመስ ይጓጓሉ ጌትነት አመራ (13/05/2011)

***ቃለ መጠይቅ ሃያ ሦስት አዝማሪ ጋሻው ሙጨየ***፡- የጥምቀት በዓል በጣም ደስ ይላል፡፡ በዓላችን በጣም የተዋበ እና የዐማረ ነው፡፡ እየው እንደምታየው ነው በጣም ቆንጆ ነው፡፡ በጥምቀት ቀን አዝማሪ ያለው ቦታ፣ ሥራ ምን ይመስላል?፡- አዝማሪ ይከበክባል፣ ታቦት ይከበክባል፣ በጎንም ደግሞ ሥራ ካለ ይሠራል፡፡ በሚፈልጉት እንዲኹ እሚደሰቱት ከሰው ጋራ ተስማምቶ እየዘፈነ፣ እያሞገሰ ሥራውን እየሠራ ታቦቱን እየከበከበ ይገኛል፡፡

ከኹል ጊዜው በተለየ ጥምቀትን ለእናንተ ልዩ የሚያደርገው ምኑ ነው?፡- በጥምቀት በዓል ገቢያችን የተሻለ ነው፡፡ ገቢያችን የተሻለ ይሆናል፣ የተለያዩ እንግዶች ስለሚመጡ የማስታወስ ባሕርይ ስላለ የጥንቱንም የሀገራቸውንም እንዲህ ዝና እና ጨዋታ የሚቀሰቅሰውን በጥምቀት ስለኾነ የተለያዩ እንግዶች ስለሚመጡ በጥምቀት በጣም የተሻለ ጥቅም እናገኛለን፡፡

ማኅበራዊ ግንኙነታችሁስ የጥምቀት ሰሞን እንዴት ይለካል?፡- በጣም የተሻለ ነው፤ የተሻለ ነው፤ ኑ ከኔ፣ ኑ ከኔ ነው፡፡ እኔ አኹን ከቀኑ የማታው ፈላጊዬ ይበዛል፤ ከማታው የቀኑ ፈላጊዬ ይበዛል፡፡ እወዛገባለሁኝ፤ ፈላጊዬ ስለሚበዛ ምክንያቱም በጥምቀት ቀን ብዙ ተደሳች፣ ብዙ ባህሉን አክብሮ ስለሚመጣ ለመጫወት ለመዝናናት ከኀደኛው፣ ከባልንጀራው ጋር (አዝማሪ ጋሻው ሙጨየ፣ 11/ 05/ 2013 ቃ.መ)፡፡

***ቃለ መጠይቅ ሃያ አራት ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን፡-*** ስሜ ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን እባላለሁ። እነዚህን ቅርጻቅርጾች ገዝተኻቸው ነው? ሠርተሀቸው? እንግዲህ እኔ እነዚህን ራሴ ነኝ የማዘጋጃቸው። የአካባቢው ባህሉ መገለጫ ስለሆነ ራሴ ነኝ እያዘጋጀሁ የምሸጣቸው። ቅዱሳን ስዕልም ቤተ መንግሥቱንም፣ የቴዎድሮስ ምስልንም ራሴ ነኝ የማዘጋጀው። ለኢኮኖሚውም ጥሩ እንቅስቃሴ አለው። የአካባቢውንም ባህል ያስተዋውቃል። በጥምቀት ሰሞን የተሻለ ሥራ አለው። ምክንያቱም ኹሉም ከየ አካባቢው ስለሚመጣ የአካባቢው ተወላጅም ሌሎችም ስለሚመጡ ይህንን እየገዙ ይኼዳሉ። ስለዚህ ኢኮኖሚውም ጥሩ እንቅስቃሴ አለው። የጥምቀት ሰሞን በብዛት የሚገዙት ከሩቅ የሚመጡ ሰዎች አሉ። ከዐዲስ አበባም ከውጭ የሚመጡ እንግዶች ይህንን እየገዙ ይኼዳሉ። የጥምቀት ሰሞን ዋጋቸው ከፍ ይላል። ባለ ኹለት መቶ ብር፣ ባለ መቶ፣ አምሳ ብር እና ባለ ሦስት መቶ ብር አለ። የፋሲል እና የቴዎድሮስ ኹለት መቶ ብር ነው የሚሸጥ፣ ቅዱሳን ስዕላት እንደ ሳይዛቸው መቶ፣ ኹለት መቶ እና ሦስት መቶ የሚሸጡ አሉ። እንጨቶችን ገዝቸ ነው። ይህንን ቆዳ ራሴ ነኝ የምተለትለው። እንጨቱን የምፈለፍለው ራሴ ነኝ። ራሴው እየፈለፈልኩ እና እያጋጠምኩ ነው የምሠራቸው። የጎንደር ጥምቀት እግዚአብሔር ይመስገን በጣም ያምራል። በሀሪፍ ነው እየተካኼደ ያለው። በጣም ደስ ነው የሚለው። ደስ የሚለው ሰላሙ አካባቢው ሰው ብዛቱ፣ ዘንድሮ በጣም የተሻለ ነገር አለ (ዲያቆን ፍስሐ መሥፍን፣ 12/ 05/ 2013 ቃ.መ)።